# የተሟላ ወንጌላዊ
# ደቀ መዝሙርነት

48 - ክፍል ትምህርቶች

**በ አንድሩ ዉማክ እና**
**በ ዶን ክሮው**

Andrew Wommack Ministries
Woodland Park, Colorado

አንድሩ ዉማክ የወንጌል አገልግሎት
ዉድላንድ ፓርክ፣ ኮሎራዶ

ካልተገለጸ በቀር ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት የኢትዮጵያ
መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ካሳተመው የ1954 ዓ.ም መደበኛ ትርጉም ነው።

© 2025 by Andrew Wommack Ministries, Inc
Andrew Wommack Ministries, Inc.
PO Box 3333
Colorado Springs 80934-3333
www.awmi.net

Andrew Wommack Ministries – Europe
PO Box 4392,
Walsall,
WS1 9AR,
England
www.awme.net

ISBN: 978-1-948876-34-6

Item Code: AM417

ያለ ክፍያ ለደቀ ደቀመዝሙርነት አገልግሎት ጥቅም ላይ ለማዋል እና በነጻ
ለማሰራጨት ከሆነ - ማባዛት እና እንደገና ማሳተም የተፈቀደ ነው።

# የተሟላ ወንጌላዊ ደቀ መዝሙርነት

## 48 - ክፍል ትምህርቶች

## ማውጫ

### ክፍል 1


| | | |
|---|---|---|
| 1. | የዘላለም ህይወት | 1- 7 |
| 2. | በጸጋ መዳን | 1- 11 |
| 3. | በጸጋ ስለመፅደቅ | 1- 17 |
| 4. | ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት | 1- 21 |
| 5. | የእግዚአብሔር ማንነት | 1- 26 |
| 6. | ንስሐ | 1- 31 |
| 7. | ውሳኔ | 1- 37 |
| 8. | የውሃ ጥምቀት | 1- 41 |
| 9. | በክርስቶስ የሆነ ማንነት - ክፍል 1 | 1- 45 |
| 10. | በክርስቶስ የሆነ ማንነት - ክፍል 2 | 1- 50 |
| 11. | ክርስቲያን ኃጢአት ሲሰራ ምን ይሆናል? | 1- 54 |
| 12. | የእግዚአብሔር ቃል ሐቀኛነት | 1- 58 |
| 13. | እግዚአብሔር በክፉ ተጠያቂ አይደለም | 1- 62 |
| 14. | በመንፈስ የተሞላ ህይወት ሃይል | 1- 66 |
| 15. | መንፈስ ቅዱስን መቀበል! | 1- 71 |
| 16. | በልሳን የመናገር ጥቅሞች | 1- 76 |


### ክፍል 2


| | | |
|---|---|---|
| 1. | ራስ - ወዳድነት የሐዘን ሁሉ ምንጭ | 2- 82 |
| 2. | በእግዚአብሔር ቃል እንዴት ማሰላሰል እንደሚቻል | 2- 86 |
| 3. | አእምሮን ማደስ | 2- 89 |
| 4. | የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አስፈላጊነት | 2- 93 |
| 5. | ነፃ መውጣት | 2-100 |
| 6. | የአማኝ ስልጣን | 2-105 |
| 7. | ፈውስ ያለው በስርየት ነው | 2-111 |
| 8. | የፈውስ እንቅፋቶች | 2-116 |
| 9. | ይቅርታ ስለማድረግ | 2-122 |
| 10. | ጋብቻ - ክፍል 1 | 2-129 |
| 11. | ጋብቻ - ክፍል 2 | 2-133 |
| 12. | እንደ እግዚአብሔር ያለ ፍቅር - ክፍል 1 | 2-140 |
| 13. | እንደ እግዚአብሔር ያለ ፍቅር - ክፍል 2 | 2-145 |
| 14. | ፋይናንስ - ክፍል 1 | 2-151 |
| 15. | ፋይናንስ - ክፍል 2 | 2-155 |
| 16. | ጸሎታችሁ ያልተመለሰ ሲመስል ምን ማድረግ እንዳለባችሁ | 2-159 |


### ክፍል 3


| | | |
|---|---|---|
| 1. | መለኮታዊው ፍሰት | 3-166 |
| 2. | ስጦታዎችን ለአገልግሎት ስለመጠቀም | 3-170 |
| 3. | ተዓምራት እግዚአብሔርን ያከብራሉ | 3-175 |
| 4. | የመልካም ግንኙነቶች ሃይል | 3-180 |
| 5. | ተቃውሞና ስደት | 3-184 |
| 6. | ንጉሡና መንግሥቱ | 3-189 |
| 7. | የመዳን ዕምነት ዓላማ | 3-196 |
| 8. | የእግዚአብሔር ሕግ ትክክለኛ አጠቃቀም | 3-200 |
| 9. | ከሕግ በታች ሳይሆን ከጸጋ በታች | 3-206 |
| 10. | የኃጢአት እውቀት ቀርቷል | 3-212 |
| 11. | ተወዳጅ ነኝ፣ ውብ ነኝ | 3-218 |
| 12. | የመዳን ፍሬ - ክፍል 1 | 3-224 |
| 13. | የመዳን ፍሬ - ክፍል 2 | 3-230 |
| 14. | ጥሪ ለደቀመዝሙርነት | 3-235 |
| 15. | ምስክርነታችሁን ስለመጠቀም | 3-241 |
| 16. | የሁሉን ሰው ስጦታዎች ለደቀመዝሙርነት መጠቀም | 3-248 |

- በዚህ ክፍል የሚገኙትን እያንዳንዱን ትምህርቶች በሚከተለው የበይነ መረብ አድራሻ ማውረድ ትችላላችሁ - https://www.awmi.net/about-us/demo/
- የፈለጋችሁትን ያህል ኮፒዎች ማካፈል (share) ማድረግ ትችላላችሁ፣
- እነዚህን ሰነዶች ለሽያጭ ማቅረብ የተከለከለ ነው፣

# የተሟላ ወንጌላዊ
# ደቀ መዝሙርነት

## ክፍል 1

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| 1. የዘላለም ህይወት | 1- 7 |
| 2. በጸጋ መዳን | 1-11 |
| 3. በጸጋ ስለመፅደቅ | 1-17 |
| 4. ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት | 1-21 |
| 5. የእግዚአብሔር ማንነት | 1-26 |
| 6. ንስሐ | 1-31 |
| 7. ውሳኔ | 1-37 |
| 8. የውሃ ጥምቀት | 1-41 |
| 9. በክርስቶስ የሆነ ማንነት - ክፍል 1 | 1-45 |
| 10. በክርስቶስ የሆነ ማንነት - ክፍል 2 | 1-50 |
| 11. ክርስቲያን ኃጢአት ሲሰራ ምን ይሆናል? | 1-54 |
| 12. የእግዚአብሔር ቃል ሐቀኛነት | 1-58 |
| 13. እግዚአብሔር በክፉ ተጠያቂ አይደለም | 1-62 |
| 14. በመንፈስ የተሞላ ህይወት ሃይል | 1-66 |
| 15. መንፈስ ቅዱስን መቀበል! | 1-71 |
| 16. በልሳን የመናገር ጥቅሞች | 1-76 |

## ትምህርት 1

# የዘላለም ህይወት

### በ አንድሩ ዉማክ

እጅግ ታዋቂ ከሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች መካከል ዮሐንስ 3፡16 አንዱ ነው። ከልጅነት ጀምሮ በብዙዎች ዘንድ የሚታወቅ ይሁን እንጂ፤ ብዙዎች በትክክል ያልተረዱትና በአግባቡም ያልተጠቀሙበት የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ነው ብዬ አምናለሁ። ዮሐንስ 3፡16 እንዲህ ይላል - *"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጅ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።"*

በተለምዶ ይህ ቃል፣ ኢየሱስ እንዳንጠፋ ለኃጢአታችን ሞተልን ለሚል ትምህርት ጥቅም ላይ ይውል ነበር። ይህ እውነት እንዳለ ሆኖ፣ ቃሉ በትክክል የሚናገረው ግን ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣበት እና ለኛ ሲል የሞተበት ትክክለኛ አላማ የዘላለም ህይወት እንድናገኝ ነው። በእኛና እግዚአብሔር ባዘጋጀልን የዘላለም ህይወት መካከል የእኛ ኃጢአት እንዲሁ ደንቃራ ሆኖ የቆመ ግድግዳ ነበረ።

ኢየሱስ ለኃጢአታችን መሞቱ እውነት ነው፤ በእርሱ ሰናምን አንጠፋም የሚለውም እውነት ነው፤ ነገር ግን ወንጌል ከዚህም ያለፈ ነገር አለው። የወንጌል ትክክለኛው መልዕክት እግዚአብሔር የዘላለም ህይወት ሊሰጣችሁ እንደሚፈልግ ይናገራል። ይህ እንዴት እንደሆነ ላብራራላችሁ።

ከስቅለቱ በፊት በነበረው ምሽት ኢየሱስ የሚከተለውን ጸሎት ጸለየ፡- *"እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ህይወት ናት"* (ዮሃንስ 17፡3)።

ይህ ቃል የዘላለም ህይወት ማለት እውነተኛ አምላክ የሆነውን አባት (አብ) እና እርሱ የላከውን ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ ነው ይላል። የዘላለም ህይወት ማለት ይህ ነው። ብዙ ሰዎች የዘላለም ህይወት ማለት ለዘላለም መኖር ነው ብለው ያስባሉ። አዎ ሁሉም ሰው ለዘላለም ይኖራል፣ ሰው ሲሞት መኖሩ ያበቃል ብሎ ማሰብ ትክክል አይደለም። ነፍሰና መንፈሱ ተመልሰው ወደ እግዚአብሔር ይሄዳሉ። ሰጋው ደግሞ በምድር ይበሰብሳል። ማንኛውም በምድር ላይ የኖረ ሰው በመንፈሰ መኖር ይቀጥላል እና ስለዚህ የዘላለም ህይወት ማለት ለዘላለም መኖር ማለት ብቻ እንዳልሆነ እውን ነው። በዚህ ቃል መሰረት ከእግዚአብሔር ጋር የዘላለም ህይወት መኖር ለሁሉም ሰው ወዲያውኑ የሚሰጥ እንዳልሆነ ግልጽ ይሆንልናል።

አንዳንድ ሰዎች "የዘላለም ህይወት በገነት ወይም በሲኦል ለዘላለም መኖር ነው" ይላሉ። ነገር ግን የዘላለም ህይወት ኢየሱስ በዮሃንስ 17፡3 እንደሚናገረው - እግዚአብሔርን እና ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ ነው። ይህም ከአዕምሮ እውቀት ያልፋል። ይህ "ማወቅ" የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናንተ ሊኖራችሁ የሚችለውን የጠበቀ፣ የግል ወዳጅነት ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል።

የመዳን ወንጌል ዋናው ዓላማ በሰማይ ለዘላለም መኖር ብቻ አይደለም። ምንም እንኳን ይህም እጅግ የሚያስፈልገን መሆኑ ባይካድም፤ ነገር ግን የመዳን ወንጌል ዋናው ዓላማ ከጌታ እግዚአብሔር ጋር ቅርበት እና - የግል ወዳጅነት እንዲኖረን ነው። እጅግ ብዙ ሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር እንዲላቸው ወደ እግዚአብሔር ከመጮህ ባለፈ ከእርሱ ጋር የግል ወዳጅነት የመመሰረት እቅድ የላቸውም።

የመዳንን ትክክለኛ ዓላማ ባለማሰረዳታችን ምክንያት፣ ወንጌል አገልግሎቱን እንዳይፈጽም እናደርጋለን። መዳንን ወይም ድህነትን ለወደፊት በሚመጣው ዓለም ብቻ የሚጠቅም ፍጹም መንፈሳዊ ነገር እንደሆነ አድርገን የምናቀርብ ከሆነ ሰዎችን እየረዳናቸው አይደለም። ዛሬ በምድር ላይ ኑሮ ሲኦል የሆነባቸው ብዙ ሰዎች ናቸው።

በድብርት የተጠቁ፤ በድህነት የሚኖሩ፣ በብስጭት፣ በመገለል፣ በበደል እና ባልተሳካ ትዳር ውስጥ የሚኖሩ እጅግ ብዙ ናቸው። ሰዎች እንዲሁ የዕለት ከዕለት ኑሮአቸውን ለማሸነፍ ይሞክራሉ። ጭንቅላቱን ከውሃ በላይ በማድረግ ላለመስመጥ እንደሚታገል ዓይነት ሰው ሆነዋል። የመዳናቸው ጥቅም ወደፊት በሚመጣው ዓለም ብቻ እንደሆነ በማሰባቸው ሁሉን ነገር እርግፍ አርገው ትተው በዛሬ ኑሮአቸው ላይ ብቻ ያተኩራሉ።

እውነቱ ግን ኢየሱስ የመጣው ከሲኦል የመርገም ቅጣት አድኖ የዘላለም መጨረሻችን ያምር ዘንድ በሰማይ፣ በበረከት ለዘላለም እንድንኖር ብቻ ሳይሆን ነገር ግን አሁን ካለው ክፉ አለም ያድነን ዘንድ (ገላትያ 1፡4) ነው። ኢየሱስ እያንዳንዳችሁ ዛሬ ከእግዚአብሔር አብ ጋር የጠበቀ ወዳጅነትና ግንኙነት ይሰጣችሁ ዘንድ ወደ እናንተ መጥቷል።

ኢየሱስ እንደገና ከእራሱ ጋር የቀረበ ወዳጅነትና የግል ግንኙነት እንዲኖራችሁ ነው የመጣው። ኢየሱስ ይወዳችኃል። ኢየሱስ የግል ወዳጃችሁ ይሆን ዘንድ ይፈልጋል። ኢየሱስ ከሌላ ከየትኛውም ምንጭ ልታገኙ ከምትችሉት እጅግ የሚበልጥ ውድና ምርጥ ህይወት ሊሰጣችሁም ይፈልጋል።

ኢየሱስ በዮሃንስ 10፡10 እንዲህ በማለት ይናገራል - *“ሌባው* [ሰይጣንን ማለቱ ነው] *ሊሰርቅ ሊያርድና ሊያጠፋም እንጅ ሰለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ”* (በቅንፍ ያለው በእኔ የተጨመረ ነው)። እግዚአብሔር የዘላለም ሕይወት ሊሰጣችሁ ይፈልጋል፣ እግዚአብሔር የተትረፈረፈ ህይወት ሊሰጣችሁ ይፈልጋል፣ እናንተም ይህን እንደምትፈልጉ አምናለሁ - በእርግጥ ያስፈጋችኃል። ኢየሱስ ወደ እራሱም ሊያቀርባችሁ ጭምር እንጂ ኃጢአታችሁን ይቅር ለማለት ብቻ አልሞተም። ጌታን የማታውቁ ከሆነ ለዚህ ዓላማ ልታውቁት ይገባል። ዳግመኛ የተወለዳችሁ ከሆነ ደግሞ የኃጢአት ይቅርታን ከማግኘት አልፋችሁ ከአብ ጋር ወደ ዘላለም ህይወት ግቡ።

## የዘላለም ህይወት እውነታዎች

1. የወንጌል አላማ የዘላለም ህይወት ነው፤ (ዮሐንስ 3፡16)።
2. የዘላለም ህይወት እግዚአብሔርን ማወቅ ነው፤ (ዮሐንስ 17፡3)።
3. እግዚአብሔርን ማወቅ ከእርሱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት መፍጠር ነው፡ (1ኛቆሮንቶስ 6፡16-17)።
4. የዘላለም ህይወት አሁን ይጀምራል፤ (1ኛ ዮሐንስ 5፡12)።
5. እግዚአብሔር የግል ወዳጅነት እንዲኖረን ይፈልጋል፤ (የዮሐንስ ራዕይ 3፡20)።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ዮሐንስ 3፡16 አንብቡና እግዚአብሔር ኢየሱስን ወደ ምድር የላከበት ዓላማ ምንድን ነው?

   **ዮሐንስ 3፡16** *በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።*

2. “ማወቅ” የሚለውን ቃል መጽሐፍ ቅዱስ የቀረበ የግል ወዳጅነት እንደሆነ ይነግረናል (ዘፍጥረት 4፡1)። የዮሐንስ ወንጌል 17፡3 አንብቡና በዚህ ቃል መሰረት የዘላለም ህይወት ምን ማለት ነው?

   **ዘፍጥረት 4፡1** *አዳምም ሚስቱን ሔዋንን አወቀ፤ ፀነሰችም፥ ቃየንንም ወለደች። እርስዋም። ወንድ ልጅ ከእግዚአብሔር አገኘሁ አለች።*

   **ዮሐንስ 17፡3** *እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።*

3. 1ኛ ዮሐንስ 5፡11-12 አንብቡና በዚህ ቃል መሰረት የዘላለም ህይወት የሚጀምረው መቼ ነው?

   **1ኛ ዮሐንስ 5፡11-12** *እግዚአብሔርም የዘላለምን ህይወት እንደሰጠን ይህም ህይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው። [12] ልጁ ያለው ህይወት አለው፣ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ህይወት የለውም።*

4. ዮሐንስ 10፡10 አንብቡና ኢየሱስ ምን አይነት ህይወት ሊሰጠን መጣ?

   **ዮሐንስ 10፡10** *ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ።*

5. እስኪ የተትረፈረፈ ህይወት ምን እንደሆነ በራሳችሁ አገላለጽ አብራሩ?

6. እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስን ለአለም ሁሉ ኃጢአት እንዲሞት እንደላከውና ይህን ለምናምን ለእኛ ደግሞ የዘላለም ህይወት እንደሰጠን ታምናላችሁ?

7. አሁን የዘላለም ህይወት ረጅም ጊዜ መኖር ብቻ ሳይሆን ጥራት ያለው፣ የበዛና፣ የተትረፈረፈ ህይወት እንደሆነ ግልጽ ሆኖላችኋል?

# ጠቋሚ መልሶች

1. የዮሐንስ ወንጌል 3፡16 ንእንብቡና እግዚአብሔር ኢየሱስን ወደ ምድር የላከበት ዓላማ ምንድን ነው?
**ዓለሙ እንዲድን፣ በኢየሱስ ለሚያምኑ ሁሉ የኃጢአትን ቅጣት በማስወገድ የዘላለም ህይወት ለመስጠት ነው።**

2. “ማወቅ” የሚለውን ቃል መጽሐፍ ቅዱስ የቀረበ የግል ወዳጅነት እንደሆነ ይነግረናል (ዘፍጥረት 4፡1)። የዮሐንስ ወንጌል 17፡3 አንብቡና በዚህ ቃል መሰረት የዘላለም ህይወት ምን ማለት ነው?
**የዘላለም ህይወት ማለት እግዚአብሔርንና ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ ነው (በአካል ሳይሆን በቅርበት)።**

3. 1ኛ ዮሐንስ 5፡11-12፣ አንብቡና የዘላለም ህይወት የሚጀምረው መቼ ነው?
**ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ስንቀበል (ለህይወታችን)።**

4. ዮሐንስ 10፡10 አንብቡና ኢየሱስ ምን አይነት ህይወት ሊሰጠን መጣ?
**የተትረፈረፈ ህይወት።**

5. እስኪ የተትረፈረፈ ህይወት ምን እንደሆነ በራሳችሁ አገላለጽ አብራሩ?
**ሌባው ሊያደርግ ይመጣል ሲል ኢየሱስ ከተናገረው ተቃራኒው የተትረፈረፈ ህይወት ነው።**

6. እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስን ለአለም ሁሉ ኃጢአት እንዲሞት እንደላከውና ይህን ለምናምን ለእኛ ደግሞ የዘላለም ህይወት እንደሰጠን ታምናላችሁ?
**አዎ።**

7. አሁን የዘላለም ህይወት ረጅም ጊዜ መኖር ብቻ ሳይሆን ጥራት ያለው፣ የበዛና፣ የተትረፈረፈ ህይወት እንደሆነ ግልጽ ሆኖላችኃል?
**አዎ።**

# ትምህርት 2

# በጸጋ መዳን

## በ ዶን ክሮው

ኢየሱስ የመንፈሳዊውን አለም እውነቶች ለመግለጥና ለማስረዳት ምሳሌዎችን እና ታሪኮችን ብዙ ጊዜ ይጠቀም ነበር። በሉቃስ 18:9-14 እንዲህ በማለት ይጀምራል - *"ፃድቃን እንደሆኑ በራሳቸው ለሚታመኑና ሌሎችን ሁሉ በጣም ለሚንቁ ይህን ምሳሌ ነገራቸው፤ እንዲህ ሲል"*። እየሱስ በዚህ ምሳሌ ትኩረት ያደረገባቸው ሰዎች አሉ። እነርሱም በራሳቸው ወይም በሚሠሩት ሥራ የሚታመኑ ሰዎች ናቸው። በሥራቸው ፃድቅ ነን ብለው ያምናሉና ራሳቸውን አፅድቀው ሌሎችን ግን ይንቃሉ፣ ዝቅ አድርገውም ይመለከታሉ። ይህን ምሳሌ ለእነዚህ በእራሳቸው ስራ ለሚመኩ ሰዎች ነገራቸው።እራሳቸውን ያጸደቁ ብለን ልንጠራቸው እንችላለን። ኢየሱስ ሌሎችን ሁሉ በጣም ለሚንቁ በማለት የተናገረውም፣ "ከአንተ የተሻልኩ ነኝ" ስለሚሉ ነው።

በቁጥር 10 *"ሁለት ሰዎች ሊጸልዩ ወደ መቅደስ ወጡ፣ አንዱ ፈሪሳዊ ሁለተኛውም ቀራጭ"* ይላል። በእኛ ዘመን ቢሆን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሊጸልዩ ሄዱ፣ አንደኛውም ፈሪሳዊ ነው እንላለን። ፈሪሳዊው እጅግ የኃይማኖት ሰው ነበር። የቃሉ ትክክለኛ ትርጉም "የተለየ" ማለት ነው። እጅግ ኃይማኖተኛ ከመሆናቸው የተነሳ "ታረክሰኛለህ፣ ወደ እኔ አትቅረብ። እንደ ሌሎች ሰዎች አይደለሁም፣ ከሌሎች ሁሉ የተሻልኩ ነኝ" ከሚሉ ዓይነት ሰዎች አንዱ ነበር። ኢየሱስ በንግግሩ የጠቀሰው ሌላው ሰው ቀራጭ ነበር። ቀራጮች ቀረጥ ሰብሳቢዎች ሲሆኑ እጅግ ክፉ መሆናቸው ይታወቃል፣ በኃጢአት የተሞሉ፣ አታላዮች እና አጭበርባሪዎች ነበሩ። በሚችሉት ዘዴ ሁሉ ከሚያስከፍሉት ግብር የእራሳቸውን ኪስ አጭቀው ጥቂቱን ብቻ ለሮማ መንግስት ይሰጣሉ፣ ስለዚህ ገዥዎቻቸውም በመልካም ፊት አይመለከቷቸውም ነበር።

ቁጥር 11 ላይ ታሪኩ ሲቀጥል፣ *"ፈሪሳዊውም ቆሞ በልቡ ይህን ሲፀልይ። እግዚአብሔር ሆይ እንደ ሌላ ሰው ሁሉ፤ ቀማኞችና አመፀኞች አመንዝሮችም፣ ሰላልሆንሁ ወይም እንደዚህ ቀራጭ ሰላልሆንሁ አመሰግንሃለሁ"*አለ። ይህን በትኩረት ተመልከቱ፣ ይህ ሰው ወደ ማን ነው የሚጸልየው? በእርግጥ "እግዚአብሔር" ሆይ በማለት መልካም በሆኑ ቃላት ይጸልይ እንጅ፣ የሚናገረው ለራሱ ነው፡- በእግዚአብሔርም ዘንድ ጸሎቱ ተቀባይነት ያላገኘ ሲሆን ይህም የሆነበትን ምክንያት በስተመጨረሻ እናያለን። አስተውሉ፣ "እግዚአብሔር ሆይ እንደ ሌላ ሰው ሰላልሆንኩ አመሰግንሃለሁ" ብሎ ጸለዬ። ይህ ፈሪሳዊ፣ ይህ የሃይማኖት ሰው "እንደ ሌላ ሰው አይደለሁም፣ ኃጢአተኛ አይደለሁም፣ ቀማኛ አይደለሁም፣ አመጸኛ አይደለሁም፣ አመንዝራ አይደለሁም፣ ደግሞም ወደ እዚህ ሊጸልይ እንደመጣው እንደዚህ ቀራጭ አይደለሁም" አለ። እያችሁ ሌሎችን ሁሉ እያቃለለ ዝቅ አድርጎ የተመለከተበት ምክንያት እራሱን ከእነርሱ የተሻለ አድርጎ ይቆጥር ስለነበር ነው።

ቁጥር 12 ላይ ፣ ፈሪሳዊው እንዲህ አለ፣ *"በየሳምንቱ ሁለት ጊዜ እጦማለሁ፣ ከማገኘውም ሁሉ አሥራት አወጣለሁ፣ አለ"*። ይህንን ሲናገር ለእግዚአብሄር፡- "የማደርገውን ተመለከትክ?" እያለ ነው። መጾም ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ? ምግብ አለመብላት ማለት ነው። ለቤተ ክርስቲያንም ገንዘብ ይሰጣል። ይህ ሰው "አትጨቅጭቀኝ! መልካም ህይወት እየመራሁ ነው! ምጽዋት እሰጣለሁ! ለቤተ ክርስቲያንም እለግሳለሁ" ከሚሉ ሰዎች መካከል አንዱ ነው።

ወደ ቀራጩ ስንመጣ በቁጥር 13 እንዲህ ይላል፣ *"ቀራጩ ግን በሩቅ ቆሞ ዓይኖቹን ወደ ሰማይ ሊያነሣ እንኳ አልወደደም፤ ነገር ግን። አምላክ ሆይ፤ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ እያለ ደረቱን ይደቃ ነበር"*። በአካላዊ እንቅስቀሴውም ሳይቀር የሚያደርገውን አስተውሉ "በሩቅ ቆሞ" ወደ ቤተ ክርስቲያን እንኳን ሊቀርብ አልደፈረም። በሚያደርጋቸው ነገሮችና በህይወት ዘይቤው ኃፍረት ተሰምቶት ከሩቅ ቆሞ አይኖቹን እንኳን ቀና አድርጎ ወደ ሰማይ ሊመለከት አልደፈረም፣ ነገር ግን ደረቱን ይደቃ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ደረትን ስለመድቃት

ሲናገር፣ በብሉይ ኪዳን ብዙ ጊዜ "ጌታ ሆይ ላደረኩት ሁሉ ይቅር በለኝ" ለማለት ልብሳቸውንም ይቀዱ እንደነበር ይናገራል፤ ይህም ባዘነ ልብ እና በተሰበረ መንፈስ ንሰሐ የመግባት ምልክት ሲሆን እግዚአብሔርም አይንቀውም። ይህ ቀራጭ፣ ኃጢአተኛ ሰው ስለነበር፣ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ እንዲህ ሲል ጸለዬ "ጌታ ሆይ እኔ ኃጢአተኛ ሰው ነኝ ማረኝ" አለ።

ቁጥር 14 እንዲህ ይላል፣ *"እላችኃለሁ፣ ከዚያ ይልቅ ይህ ፃድቅ ሆኖ ወደ ቤቱ ተመለሰ፤ ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳልና፣ ራሱን ግን የሚያዋርድ ከፍ ይላል"*። ቀራጩ ጸድቆ ወደ ቤቱ ተመለሰ፣ በእግዚአብሔር ፊት ትክክል ጻድቅ ተባለ፣ የእግዚአብሔርን ምህረት አገኘ። ለምን ይቅርታን አገኘ? ፈሪሳዊው ሳይሆን ቀራጩ በእግዚብሔር ፊት እንዴት ጻድቅ ሆኖ ወደ ቤቱ ተመለሰ? ምክንያቱም ፈሪሳዊው ራሡን ከሌሎች ጋር በማወዳደር የተሻለ አድርጎ በመቁጠሩ፣ "ከሌሎች የተሻልኩ ነኝ! ኃጢአተኛ አይደለሁም! እንደ ሌሎች ሰዎች አይደለሁም" በማለቱ ባዶውን ተመለሠ። ቀራጩ ግን በእግዚአብሔር ፊት ሊያቆመው የሚችል ምንም ነገር አልነበረውም፣ ሊያቀርብ የሚችለው መልካም ነገርም አልነበረውም። ኃጢአተኛ ሰው ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ጻድቃንን ሳይሆን ኃጢአተኞችን ሊያድን እንደ መጣ ይናገራል። ሁላችንም ኃጢአተኞች ነን፣ የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎናል። ይህ ቀራጭ ራሡን በትህትና በማቅረቡ ይቅርታንና ምህረትን አገኘ።

ርዕሣችን በጸጋ ስለመዳን ነው። ጸጋ ድንቅ ቃል ነው፣ እኔም ተቀባይነት ያገኘውን የቃሉን ትርጉም እንደ ሚከተለው አቀርብላችኃለሁ፤ ነገር ግን ጸጋ ከዚህ ትርጉም በላይም ነው። አዲስ ኪዳን በተጻፈበት የግሪክ ቋንቋ ጸጋ "ካሪስ" ማለት ነው። ተቀባይነት ያገኘው ትርጉም ይህ ነው፦ ያልለፋንበት፣ በነጻ የተሰጠ፣ ለማይገባቸው ሰዎች እንዲሁ የተሰጠ የእግዚአብሔር ውለታ ማለት ነው። ይህ ቀራጭ ከእግዚአብሔር ይገባኛል የሚለው ምንም ነገር የለም፣ ነገር ግን በትህትና ሰለቀረበ የእግዚአብሔርን ሞገስ አገኘ። ከዚህም ሌላ፣ ካሪዝማ የሚል የግሪክ ቃል አለ፣ ይህም ቃል **ካሪስ** ከሚለው ቃል የመጣ፣ መጨረሻው ላይ አንድ ፊደል "ማ" ተጨማሪ ተቀጥላ ያለው ነው። ትርጉሙም አንድ በአይነቱ ልዩ የሆነ መገለጥ ወይም አንድ የእግዚአብሔር ጸጋ ዓይነት ሲሆን ይህ ቀራጭ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሆኖ የሚቆምበትን ጽድቅ በነጻ አገኘ።

ሮሜ 5፡17 *"የፀጋን ብዛትና የፅድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ"*። እግዚአብሔር በፊቱ የምንቆምበትን ፅድቅ ሥጦታ አድርጎ አቅርቦልናል። በዚህ ክፍል እንዳየነው ቀራጩ ይህን በክርስቶስ ኢየሱስ የሚገኘውን የጽድቅ ሥጦታ ተቀብሏል፤ ይህን ብቃት አግኝቷል። መጽሐፍ ቅዱስ በዮሐንስ 1፡17 *"ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበርና ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ"* ይላል። ይህ ጸጋ የተሰጠው ለሚከተሉት ዓይነት ሰዎች ብቻ ነው እነርሱም - በእግዚአብሔር ፊት የሚቆሙበት ምንም ነገር እንደሌላቸው ለሚያውቁና እራሳቸውን ዝቅ አድርገው በትህትና ለሚቀርቡ፣ የእግዚአብሔርን ምህረት ለሚጠይቁ ሰዎች ነው። እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ምህረት እና ይቅርታ ያገኛሉ።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ሉቃስ 18፡9 አንብቡ። ምሳሌ ምንድን ነው?

   **ሉቃስ 18፡9** *ጻድቃን እንደ ሆኑ በራሳቸው ለሚታመኑና ሌሎቹን ሁሉ በጣም ለሚንቁ ይህን ምሳሌ ነገራቸው።*

2. ሉቃስ 18፡9 አንብቡ። የኢየሱስ ምሳሌ ማን ላይ ትኩረት ያደረገ ነው?

3. ሉቃስ 18፡9 (የጥቅሱን መጨረሻ) አንብቡ። ራሳቸውን ጻድቅ አድርገው የሚቆጥሩ ሰዎች ሌሎች ሰዎችን እንዴት ይመለከታሉ?

   1] ሌሎችን ይወዳሉ።

   2] ሌሎችን ይንቃሉ ወይም ዝቅ አድርገው ይመለከታሉ።

   3] ሌሎችን ሰዎች ያፈቅራሉ።

4. ሉቃስ 18፡10 አንብቡና በአሁኑ ዘመን ቢሆን ሁለቱ ሰዎች ሊጸልዩ ወዴት ይሄዳሉ?

   **ሉቃስ 18፡10** *እንዲህ ሲል። ሁለት ሰዎች ሊጸልዩ ወደ መቅደስ ወጡ፥ አንዱ ፈሪሳዊ ሁለተኛውም ቀራጭ።*

5. ሉቃስ 18፡10 እነዚህ ሰዎች እነማን ናቸው?

6. ሉቃስ 18፡11 የፈሪሳዊው ጸሎት ምን ነበር?

   **ሉቃስ 18፡11** *ፈሪሳዊም ቆሞ በልቡ ይህን ሲጸልይ። እግዚአብሔር ሆይ፥ እንደ ሌላ ሰው ሁሉ፥ ቀማኞችና ዓመፀኞች አመንዝሮችም፥ ወይም እንደዚህ ቀራጭ ስላልሆንሁ አመሰግንሃለሁ።*

7. ሉቃስ 18፡12 ፆም ምን ማለት ነው?

   **ሉቃስ 18፡12** *በየሳምንቱ ሁለት ጊዜ እጦማለሁ፥ ከማገኘውም ሁሉ አሥራት አወጣለሁ አለ።*

8. ሉቃስ 18፡12 አስራት መስጠት ምን ማለት ነው?

9. ሉቃስ 18፡13 ቀራጩ የት ነበር የቆመው? ለምን?

   **ሉቃስ 18፡13** *ቀራጩ ግን በሩቅ ቆሞ ዓይኖቹን ወደ ሰማይ ሊያነሣ እንኳ አልወደደም፥ ነገር ግን። አምላክ ሆይ፥ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ እያለ ደረቱን ይደቃ ነበር።*

10. ሉቃስ 18፡13 ቀራጩ አንገቱን ያስደፋውና ቀና ብሎ እንዳያይ ያደረገው ምን ነበር?

11. ሉቃስ 18፡13 የዚህ ቀራጭ ጸሎት ምን ነበር?

12. ሉቃስ 18፡14 ከሁለቱ ሰዎች የትኛው በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሆኖ ወደ ቤቱ ተመለሰ?

    **ሉቃስ 18፡14** *እላችኋለሁ፥ ከዚያ ይልቅ ይህ ጻድቅ ሆኖ ወደ ቤቱ ተመለሰ፤ ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳልና፥ ራሱን ግን የሚያዋርድ ከፍ ይላል።*

13. ሉቃስ 18፡14 ፈሪሳዊው ሳይሆን ቀራጩ ጻድቅ የተባለው ለምንድን ነው?

14. ሉቃስ 18፡14 ቀራጩን እግዚአብሔር ይቅር ብሎታል?

15. ሮሜ 10፡13 አንብቡና አሁን እናንተ ከልባችሁ በርከክ ብላችሁ "አባት ሆይ እኔ ኃጢአተኛውን ማረኝ፤ ይቅር በለኝ" ብላችሁ ብትጠይቁ እግዚአብሔር ልክ ለቀራጩ እንዳደረገው እናንተንም ይቅር ብሎ ጻድቅ ያደርጋችኋል?

    **ሮሜ 10፡13** *የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና።*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ሉቃስ 18፡9 አንብቡ። ምሳሌ ምንድን ነው?
**የመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌ መንፈሳዊ እውነትን የሚያሳይ ታሪክ ነው።**

2. ሉቃስ 18፡9 አንብቡ። የኢየሱስ ምሳሌ ማን ላይ ትኩረት ያደረገ ነው?
**በእራሳቸው ለሚታመኑና ራሳቸውን ጻድቅ በሚያደርጉ ላይ ያተኮረ ነው።**

3. ሉቃስ 18፡9 (የጥቅሱን መጨረሻ) አንብቡና፣ ራሳቸውን ጻድቅ አድርገው የሚቆጥሩ ሰዎች ሌሎች ሰዎችን እንዴት ይመለከታሉ?
**2] ሌሎችን ይንቃሉ ወይም ዝቅ አድርገው ይመለከታሉ።**

4. ሉቃስ 18፡10 በአሁኑ ዘመን ቢሆን ሁለቱ ሰዎች ሊጸልዩ ወዴት ይሄዳሉ?
**ቤተ-ክርስቲያን።**

5. ሉቃስ 18፡10 እነዚህ ሰዎች እነማን ናቸው?
**ፈሪሳዊና ቀራጭ።**

6. ሉቃስ 18፡11 የፈሪሳዊው ጸሎት ምን ነበር?
**እግዚአብሔር ሆይ እንደ ሌላ ሰው ሁሉ፤ ቀማኞችና አመፀኞች አመንዝሮችም፣ (ኃጢአተኛ) ስላልሆንሁ ወይም እንደዚህ ቀራጭ ስላልሆንሁ አመሰግንሃለሁ፤ አለ።**

7. ሉቃስ 18፡12 ፆም ምን ማለት ነው?
**ምግብ አለመመገብ።**

8. ሉቃስ 18፡12 አስራት መስጠት ምን ማለት ነው?
**አንድ ሰው ከሚያገኘው ከአስሩ አንድ እጅ ወይም አንድ አስረኛ ማለት ነው።**

9. ሉቃስ 18፡13 ቀራጩ የት ነበር የቆመው? ለምን?
**በሩቅ ቆሞ ነበር፣ በኃጢአተኛነቱ ምክንያት ወደ መቅደስ ወይም ቤተ ክርስቲያን ለመቅረብ ሐፍረት ስለተሰማው ነበር።**

10. ሉቃስ 18፡13 ቀራጩ አንገቱን ያስደፋውና ቀና ብሎ እንዳያይ ያደረገው ምን ነበር?
**ሐፍረት ስለተሰማው።**

11. ሉቃስ 18፡13 የዚህ ቀራጭ ጸሎት ምን ነበር?
**ይቅር በለኝ፣ ኃጢአተኛ ነኝ የሚል ነበር።**

12. ሉቃስ 18፡14 ከሁለቱ ሰዎች የትኛው በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሆኖ ወደ ቤቱ ተመለሰ?
**ቀራጩ።**

13. ሉቃስ 18፡14 ፈሪሳዊው ሳይሆን ቀራጩ ጻድቅ የተባለው ለምንድን ነው?

**በእግዚአብሔር ፊት በትህትና ስለቀረበ፣ ፈሪሳዊው ግን በትዕቢት ተወጥሮ ነበርና አዳኝ እንደሚሰፈልገው አላወቀም።**

14. ሉቃስ 18፡14 ቀራጩን እግዚአብሔር ይቅር ብሎታል?
**አዎ።**

15. ሮሜ 10፡13 አንብቡና አሁን እናንተ ከልባችሁ በርከክ ብላችሁ “አባት ሆይ እኔ ኃጢአተኛውን ማረኝ፤ ይቅር በለኝ” ብላችሁ ብትጠይቁ እግዚአብሔር ልክ ለቀራጩ እንዳደረገው እናንተንም ይቅር ብሎ ጻድቅ ያደርጋችኃል?
**አዎ፣ ይቅርታ አድርጎ ከኃጢአቴም ያነጻኛል።**

# ትምህርት -3

# በጸጋ ስለመፅደቅ

## በ ዶን ክሮው

በዚህ ርዕስ በጸጋ ስለሚገኝ ጽድቅ እንመለከታለን፡- ሮሜ 3፡21-23 *“አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ፅድቅ ያለ ሕግ ተገልጦአል፤ እርሱም፣ ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው፤ ልዩነት የለምና፣ ሁሉ ኃጢአትን ሰርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል።”*

ይህን ቃል አስተውሉ፣ *“የእግዚአብሔር ፅድቅ ያለ ሕግ ተገልጧል”* ይላል። በአንድ ወቅት ለአንድ ሰው “በገነት ለመሆን ምን ማድረግ አለብኝ ብለህ ታስባለህ?” ስል ጠይቄ ነበር። ሰውየውም አሰርቱን ትዕዛዛት መጠበቅ፣ ለትዳር አጋሩ ታማኝ መሆን፣ በመልካም ስነ-ምግባር መኖር፣ እና የመሳሰሉትን አለ። እኔም “በሰማይ ከእግዚአብሔር ጋር ለመሆን፣ በመንግስቱም ለመኖር የሚያስፈልግህ ምን እንደሆነ ልንገርህ? ከእግዚአብሔር ጽድቅ ጋር የተካከለ ጽድቅ ያስፈልግሃል” አልኩት። ሰውየውም “ይቅርታ አድርግልኝና ከእግዚአብሔር ጋር የተካከለ ጽድቅ ከኢየሱስ በቀር ማን ሊኖረው ይችላል? ማንም አይችልም” ሲል መለሰልኝ። እኔም “አሁን የምልህ ገብቶሃል። ያልከውም ትክክል ነው። ሁላችንም ብንሆን በራሳችን ህጉንም ሆነ ትዕዛዞችን በውስጣችንም በውጭም መጠበቅ የምንችልበት ብቃት የለንም። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር ለመሆንና በእርሱ ተቀባይነትን ለማግኘት እንደ እግዚአብሔር አይነት ጽድቅ ያስፈልገናል”።

ቁጥር 21-22 በቀጥታ የሚነግረን ይህንን ነው፣ *“አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ፅድቅ ያለ ሕግ ተገልጦአል፤ እርሱም፣ ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው”*። እግዚአብሔር ለእኔና ለእናንተ የሰጠን ጽድቅ “በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን” የሚገኝ ጽድቅ ነው፣ ይህም ለሚያምኑ ሁሉ ነው። ሁለት ዓይነት ፅድቅ አለ - የሰው ፅድቅ እና የእግዚአብሔር ፅድቅ። የሰው ፅድቅ አንድ ሰው በመልካም *ሥራ*፣ በመልካም ባህሪውና በሚሰራው *ሥራ* የሚያገኘው ሲሆን በእግዚአብሔር ፊት ግን ተቀባይነት ሊያስገኝላችሁ አይችልም። ከእግዚአብሔር ጋር የተካከለ ጽድቅ ያስፈልጋችኋል፣ ይህንንም ለእናንተ አቅርቦላችኋል - ያለ ሕግ የሆነ የእግዚአብሔር ጽድቅ።

በግሪኩ ሰነ ጽሑፍ ይህ ቃል እግዚአብሔር ያለ ሕግ *ሥራ* የእራሱን ጽድቅ ሠጥቶአል፣ የሚል እርግጠኛ ትርጉምን የያዘ አያሳይም። በህግ የሚገኘው ጽድቅ በ*ሥራ*፣ በተግባር፣ በአፈጻጸም ብቃት፣ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነትን ማግኘት ነው። ዛሬ ላይ ሁሉም የአለማችን ሐይማኖቶች በመልካም ስራ፣ በብቃትና በችሎታ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ማግኘት ይቻላል ብለው ያስባሉ። “ወንጌል” “የምስራች” ነው። የወንጌሉ የምስራችም እግዚአብሔር በልጁ *ሥራ* ለሚያምኑ ሁሉ የራሱን ፅድቅ የሠጠ መሆኑ ነው። እርሱም ለኃጢአታችን በመስቀል ላይ ሞቶ ከህጉ ጋር የተካከለ ጽድቅ እንዲቆጠርልን አደረገ። ይህም ጽድቅ ከህግ ያልሆነ እኛ ሳንለፋ፣ ሳንሰራ፣ ብቃትም ሳይኖረን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናችን ብቻ ያገኘነው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው።

ቁጥር 22 የሚናገረውን ካስተዋላችሁ ቃሉ የሚናገረው ለሁሉም በሁሉም በክርስቶስ ኢየሱስ ስለሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው። እግዚአብሔር ፅድቁን ለሁሉም ለምን ሠጠ? *“ልዩነት የለም። ሁሉም ኃጢአትን ሰርተዋል የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል”*። አንተም ኃጢአትን ሰርተሃል፣ እኔም ኃጢአትን ሰርቻለሁ ሁላችንም ከእግዚአብሔር የብቃት ሞዘናና ፍጹምነት ልክ ወድቀናል። በኃጢአታችን ምክንያት የሚያስፈልገን ትልቁ ነገር ተቀባይነትን ማግኘት ነው፣ ትክክለኛ ወዳጅነትና በእግዚአብሔር ፊት የሚያቆመን መለኪያ ያስፈልገናል … እግዚአብሔርም ይህንን በህግ *ሥራ* ሳይሆን በክርስቶስ ኢየሱስ ባለ እምነት ሰጥቶናል። የእግዚአብሔር ጽድቅ በ*ሥራ* ሞክራችሁ፣ በጥረት፣ በዋጋ የምታገኙት ሳይሆን ሙከራችሁና ጥረታችሁ በእምነት፣ በክርስቶስ ኢየሱስ

ባላችሁ መደገፍ እና መታመን የሚገኝ ነው።

አብርሃም (የአይሁድ አባት) መዳንን ያገኘው እንዴት ነበር? መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን አመነ ይላል፣ እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ሰላመነ ይህም ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት። ነገር ግን አብርሃም በእምነቱ ምክንያት በእግዚአብሔር ፊት የተቆጠረለት ጽድቅ ለእርሱ ብቻ አይደለም። በሮሜ 3፡21-22 ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው እምነት፣ እምነቱ ጽድቅ ሆኖ እንደሚቆጠርለት እንብበናል። ክርስቶስ በመስቀል ላይ በከፈለው ዋጋ፣ ደሙን ስለ ኃጢአታችን ባፈሰሰ ጊዜ ጽድቅ (በእግዚአብሔር ፊት የምንቆምበት) ማንነት በክርስቶስ ለሚያምን ሰው ሁሉ እንደሚቆጠርለት መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል።

ሮሜ 5፡17 *"በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ፤ ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ሥጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ"* ይላል። እግዚአብሔር በእራሱ ፊት የሚያቆማችሁን የጽድቅ ሰጦታ አቅርቦላችኋል። ሰጦታ ለሠጭው ዋጋ ያስከፍለዋል። ተቀባዩ ግን ምንም ዋጋ ሳይከፍል እንዲሁ በነጻ ይቀበላል። አንድ ሰው አንድን ነገር ክፈልና ውሰድ ወይም ይህን ሥራ ሥራና የራሥህ አድርግ ቢላችሁ ሥጦታ አይደለም የሥራችሁ ዋጋ ነው። እግዚአብሔር ግን ልጁ በከፈለው ዋጋ በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ከእርሱ ጋር የምንሆንበትን ጽድቅ በነፃ ሠጥቶናል።

# የደቀመዝሙር ጥያቄዎች

1. ቲቶ 3፡5 እንብቡና የሚያስፈልገን ጽድቅ እኛ መስራት የምንችለው ነው?

   **ቲቶ 3፡5** *እንደ ምህረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ ፡- እኛ ሰላደረግነው በፅድቅ ሰለ ነበረው ሥራ አይደለም።*

2. 2 ቆሮንቶስ 5፡21 ምን አይነት ጽድቅ ያስፈልገናል?

   **2 ቆሮንቶስ 5፡21** *እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሄር ፅድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢያት ያላወቀውን እርሱን ሰለ እኛ ኃጢያት አደረገው።*

3. ሮሜ 3፡22 ይህንን ጽድቅ መቀበል የምንችለው እንዴት ነው?

   **ሮሜ 3፡22** *እርሱም፡- ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ፡- በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሄር ፅድቅ ነው፤ ልዩነት የለምና።*

4. ፊሊጲስዩስ 3፡9 እንብቡና ከሕግ የሆነ ጽድቅ ምን ማለት ነው?

   **ፊሊጲስዩስ 3፡9** *በክርሰቶሰም በማመን ያለው ጽድቅ ማለት በእምነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለው ጽድቅ እንጂ ከሕግ ለእኔ ያለው ጽድቅ ሳይሆንልኝ፡- በእርሱ እገኝ ዘንድ ሁሉን እንደ ጉድፍ እቆጥራለሁ።*

5. ገላትያ 2፡21 እንብቡና የእግዚአብሔርን ጽድቅ የምንጥለው ምን ሰናደርግ ነው?

   **ገላትያ 2፡21** *የእግዚአብሔርን ጸጋ አልጥልም፤ ጽድቅሰ በሕግ በኩል ከሆነ እንኪያሰ ክርሰቶሰ በከንቱ ሞተ።*

6. ሮሜ 5፡17 የእግዚአብሔር ጽድቅ በምን ይገኛል?

   **ሮሜ 5፡17** *በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ፡- ይልቁንም የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ሰጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሳሉ።*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ቲቶ 3፡5 እንብቡና የሚያስፈልገንን ጽድቅ እኛ መስራት የምንችለው ነው?
   **አይደለም**።

2. 2 ቆሮንቶስ 5፡21 ምን አይነት ጽድቅ ያስፈልገናል?
   **የእግዚአብሔር ዓይነት ጽድቅ (በክርስቶስ የሚገኝ)**።

3. ሮሜ 3፡22 ይህንን ጽድቅ መቀበል የምንችለው እንዴት ነው?
   **በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን**።

4. ፊሊጲስዩስ 3፡9 እንብቡና ከሕግ የሆነ ጽድቅ ምን ማለት ነው?
   **በራሴ ስርቸ ላገኘው የምችለው፣ የእራሴ ጽድቅ**።

5. ገላትያ 2፡21 እንብቡና የእግዚአብሔርን ጽድቅ የምንጥለው ምን ስናደርግ ነው?
   **የእግዚአብሔርን ጽድቅ የምንጥለው በክርስቶስ ኢየሱስ እርሱም ለመዳናችን እንደሞተልን ከማመን ይልቅ በራሳችን መልካም ሥራ ለመዳን ስንሞክር ነው**።

6. ሮሜ 5፡17 የእግዚአብሔር ጽድቅ በምን ይገኛል?
   **በስጦታ**።

# ትምህርት 4

# ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት

## በ እንድሩ ዉማክ

ግንኙነትን በተመለከተ ማስተዋል ከሚገቡን እጅግ አስፈላጊ ነገሮች አንዱ ግንኙነቱን ስለምትመሰርቱት ግለሰብ መረዳት ሲሆን፣ ከእግዚአብሔርም ጋር ተመሳሳይ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ጤናማ ግንኙነት ይኖራችሁ ዘንድ የእግዚአብሔርን መሰረታዊ ማንነት እና ባህሪውን ማወቅ ያስፈልጋችኃል። ይህን አለማወቅ ብዙ ሰዎች ከእርሱ ጋር መልካም ግንኙነት እንዳይኖራቸው ከሚያደረጉ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ነው። በኤደን ገነት ውስጥ አዳምና ሔዋን በእባቡ ሲፈተኑ የተከሰተው ሁኔታ ይህ ነው፤ ፈቃዱን ወደ ጎን ትተው በራሳቸው ፈቃድ በመሄዳቸው የሰውን ዘር በሙሉ በኃጢአት እስራት ውስጥ የከተቱት የእርሱን ሥራና ፈቃድ ባለመረዳትና ባለመገንዘብ ነው። የእግዚአብሔርን ባህሪይ አለመረዳታቸው የፈተናቸው አንዱ ክፍል ነበር።

ዘፍጥረት 3፡1-5 ብዙዎች የሚያውቁት ታሪክ ነው፡ *"እባብም እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠረው ከምድር አውሬ ሁሉ ይልቅ ተንኮለኛ ነበረ። ሴቲቱንም በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? አላት። ሴቲቱም ለእባቡ አለችው በገነት ካለው ከዛፍ ፍሬ እንበላለን ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፉ ፍሬ፣ እግዚአብሔር አለእንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም። እባብም ለሴቲቱ አላት፣ ሞትን አትሞቱም። ከእርሰዋ በበላቸሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ"።*

እዚህ ላይ ሰይጣን በረቀቁ ቃላት እግዚአብሔር ለእነርሱ መልካም እንዳልሆነ የተናገረውን አረፍተ ነገር እናገኛለን ... ከአዳም እና ሔዋን የደበቀው ነገር እንዳለ፣ ይህም እነርሱ ሙሉ እውቀታቸውን እንዳይጠቀሙ ... እንደ እርሱ እንዲሆኑ እንደማይፈልግ ... መልካምና ክፉን ከሚያሳውቀው ዛፍ እንዳይበሉ ያዘዛቸው እነርሱን ለመከልከል ወይም ለመጉዳት እንደሆነ በማስመሰል ይናገራል። በዚህም ሰይጣን እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ማንነትና ፈቃድ በመቃረን ጨካኝ እንደሆነ፣ መልካምና ጥሩ ነገርን እንደደደበቃቸው አድርጎ ነገራቸው። ዛሬም በሰዎች ላይ እየተፈጸመ ያለው ያንኑ ተመሳሳይ ሁኔታ ነው። አሁንም ሰይጣን "እግዚአብሔርን የምትከተል ከሆነ እያንዳንዱን ቃልና ትዕዛዙን መጠበቅ ይኖርብሃልና ይህ ደግሞ ደስታ አይሰጥህም፣ ህይወትህ አሰልቺ ... ሙት ይሆናል" አይነት ሃሳቦችን ይነግራቸዋል። አሳዛኙ እውነት፣ ሰዎች በአደንዛዥ ዕፅ፣ በመጠጥ፣ በዝሙት፣ በአመጽ፣ በራስ ወዳድነት፣ በሥራ ሰኬት እና በሌሎች የሚሞክሯቸው ነገሮች ሁሉ ደስታን እንዳልሰጧቸው ይገነዘባሉ። ሆኖም በመጨረሻ ይህን በሚገነዘቡበት ጊዜ ግን በአሳዛኝ ሁኔታ ህይወታቸው፣ ቤተሰባቸው፣ ደግሞም ጤናቸው ሁሉም ነገር ተበላሽቶ ያገኙታል።

እውነታው ግን እግዚአብሔር ደግ አምላክ ነው፤ ለእኛ ያለው ፈቃድም መልካም ብቻ ነው። ሰይጣን ግን በኤደን ገነት ውስጥ  አዳምና ሔዋንን የፈተነበትን ያንኑ ተመሳሳይ ፈተና ዛሬም እግዚአብሔር ለእኛ መልካም እንዳልሆነ በማስመሰል ይናገራል። በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቂት እውቀት ያለው ሰው እግዚአብሔር ጨካኝ ነው ብሎ ሊገምት የሚችልባቸውን ሁኔታዎች በልዩ ልዩ ቦታዎች ሊያገኝ ይችላል። ኦሪት ዘኁልቁ ምዕራፍ 15 ቁጥር 32-36 በሠንበት እንጨት የለቀመ ሰው ሰንበትን አላከበረም ተብሎ በድንጋይ ተወግሮ እንዲሞት መደረጉን እናያለን። ይህ ለመሰማት የሚከብድ ይሁን እንጂ ከቅጣቱ ጀርባ የሚያስፈጽመው ግብ መኖሩን ቃሉን ዘወትር በማስተዋል ለማያነቡ ሰዎች ላይገለጥላቸው ይችላል። በጥንቃቄ ቃሉን ሥናጠና የምናገኘው - የብሉይ ኪዳን ህግ የተሰጠው ኃጢአት ጉልበትና ጥንካሬ እንዲያገኝና እጅግ ኃጢአተኛ እንዲሆን ነው ይላል ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 7፡13። አላማውም ሰዎች ኃጢአትን መተላለፍ ምን ያህል ገዳይ መሆኑን መገንዘብ ባለመቻላቸው ህጉ ይህንን እንዲያውቁና በእግዚአብሔርም ላይ ማመጻቸውን እና እርስ በእርስ መወዳደራቸውን እንዲተው በሥራቸው ከሌሎች የተሻልኩ ነኝ በማለት እንዳይመፃደቁ ነው።

ብዙዎች፡- አንድ ሰው ኃጢአት ሰርቶ ወዲያውኑ በሞት ካልተመታና ምንም ካልሆነ ኃጢአት ብዙም ጉዳት የለውም በሚል ደረጃቸውን ያወርዱና ክፉና ደጉን ለመለየት በሚያስቸግር ሁኔታ ውስጥ ይገባሉ። ለዚህ ነው እግዚአብሔር ህጉን በክፉና በበጎ መሃል መለኪያ ሆኖ እንዲያገለግል ያሰገባው። በዚህም የዲያብሎስን ፈተና አልፈው የተሳሳተ ምርጫ ውጤቱ ምን እንደሆነ ያውቃሉ። እርሱም ይህን በማድረግ የሰጠውን ህግ ያስፈጽማል ማለት ነው።

እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ህግን ሲሰጥ “ይህንን ካልፈፀማችሁ አትድረሱብኝ፣ አልወዳችሁም፣ እርቅ የለም፣ ልቀበላችሁ አልችልም” ብሎ አይደለም። ይህ የእርሱ ማንነት አይደለም፣ ባህሪው አይደለም። ይልቁን በክፉና በበጎ ላይ የጠራ ዕይታ እንዲኖረንና የሚረዳን፣ የሚያድነን አዳኝ እንደሚያስፈልገን እንድናውቅ ነው። የብዙዎች ችግር እግዚአብሔር እንዲወዳቸው ህጉን “በትክክል መፈጸም አለብን” ብለው ደፋ ቀና ማለታቸውና፤ ይህንን ካለደረጉ እግዚአብሔር እንደማይቀበላቸው ማሰባቸው ነው። በዚህም የእግዚአብሔር ፍቅር በሥራቸው ወይም በእነርሱ አፈጻጸም ልክ ነው ብለው ያሰባሉ። ይህ የእግዚአብሔር ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ አላማ አይደለም።

የእግዚአብሔር የልቡ ፈቃድ ሰውን ከራሱ ጋር ማስታረቅ እንጅ በሰው ላይ መፍረድ አይደለም። የሰውን ኃጢአት መቁጠርም አይደለም። የእግዚሰብሔርን ሃሳብ ልንረዳ ይገባል። ዛሬም ለእኛ ያለው ሃሳብ *“እግዚአብሔር ፍቅር ነው”* (1ኛ ዮሐ 4፡8) የሚል ነው። በእኛና በእርሱ መካከል ያለውን ኃጢአት በራሱ ማሰወገድ ይፈልጋል። ይህንንም በኢየሱስ ድንቅ ሥራ አማካኝነት ፈፅሞታል። በዚህም ከእኛ ከእያንዳንዳችን ጋር በልጁ በኩል አዲስ ግንኙነት መጀመር ይፈልጋል። ይህም በእናንተ ሥራ ሣይሆን ኢየሱስ ኃጢአታችሁን እንደተሸከመ ወይም እንዳሰወገደላችሁ በማመን ነው። በህይወት ካጋጠማችሁ ውድቀት ባሻገር ከእግዚአብሔር ጋር ዛሬ ግንኙነት መመሰረት ትችላላችሁ። እርሱ የሚጠይቃችሁ እምነታችሁን በኢየሱስ ክርሰቶስ እንድታደርጉ ብቻ ነው።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ዘፍጥረት 3፡1 ሰይጣን ሔዋንን ምን ብሎ ጠየቃት?

   **ዘፍጥረት 3፡1** *እባብም እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠረው ከምድር አውሬ ሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ ነበረ። ሴቲቱንም። በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? አላት።*

2. ዘፍጥረት 2፡17 እና 3፡3 እግዚአብሔር ለአዳም ከነገረው ቃል ውስጥ ሔዋን ምን የሚል ቃል ጨምራለች?

   **ዘፍጥረት 2፡17** *ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና።*

   **ዘፍጥረት 3፡3** *ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፉ ፍሬ፥ እግዚአብሔር አለ። እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም።*

3. ዘፍጥረት 3፡6 ሰይጣን አንድ ጊዜ በሔዋን ህሊና ውስጥ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ጥርጣሬን ከጫረባት በኃላ ምን አደረገች ይላል ቃሉ?

   **ዘፍጥረት 3፡6** *ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደ ሆነ፥ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ፥ ለጥበብም መልካም እንደ ሆነ አየች፤ ከፍሬውም ወሰደችና በላች፤ ለባልዋም ደግሞ ሰጠችው እርሱም ከእርስዋ ጋር በላ።*

4. ዘፍጥረት 3፡9-10 አዳምና ሔዋን ኃጢአት ካደረጉ በኃላ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ግንኙነቱን ቀጥሏል? እነርሱን መፈለጉንስ ቀጥሏል?

   **ዘፍጥረት 3፡9-10** *እግዚአብሔር አምላክም አዳምን ጠርቶ። ወዴት ነህ? አለው። [10] እርሱም አለ። በገነት ድምፅህን ሰማሁ፤ ዕራቁቴንም ስለ ሆንሁ ፈራሁ፥ ተሸሸግሁም።*

5. ዘፍጥረት 3፡22-24 እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ለምን ከገነት አባረራቸው?

   **ዘፍጥረት 3፡22-24** *እግዚአብሔር አምላክም አለ። እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፤ አሁንም እጁን እንዳይዘረጋ፥ ደግሞም ከሕይወት ዛፍ ወስዶ እንዳይበላ፥ ለዘላለምም ሕያው ሆኖ እንዳይኖር፤ [23] ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክ ከዔድን ገነት አስወጣው፥ የተገኘባትን መሬት ያርስ ዘንድ። [24] አዳምንም አስወጣው፥ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍን በዔድን ገነት ምሥራቅ አስቀመጠ።*

6. ይህ የእግዚአብሔር ቅጣት ሳይሆን ምህረት መሆኑን መገንዘብ ችላችኃል?

7. ሮሜ 5፡17 አንብቡና የእግዚአብሔርን የጽድቅ ስጦታና የተትረፈረፈ ጸጋ እንዴት ማግኘት እንችላለን?

   1] እንገዛዋለን።
   2] በላባችን እናገኘዋለን።
   3] እንቀበለዋለን።

**ሮሜ 5፡17** *በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ፥ ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ሰጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ።*

8. ሮሜ 6፡23 ኃጢአትን የሚያደርግ ምን ይገባዋል?

   **ሮሜ 6፡23** *የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው።*

9. ከዚህ ይልቅ ግን እግዚአብሔር በጸጋው ምን ሰጠን?

10. ሮሜ 10፡3 በእግዚአብሔር ፊት የራሳችንን ጽድቅ ለማቆም ብንሞክር ምን ከማድረግ እንወድቃለን?

    **ሮሜ 10፡3** *የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሳያውቁ የራሳቸውንም ጽድቅ ሊያቆሙ ሲፈልጉ፥ ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም።*

11. አንደኛ ዮሐንስ 1፡9 እና ሮሜ 4፡3፣ እግዚአብሔር በኃጢአታችን እና በአመጻችን ሁሉ ላይ ምን ሊያደርግ ተሰፋ ሰጠን?

    **አንደኛ ዮሐንስ 1፡9** *በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነፃን የታመነና ጻድቅ ነው።*

    **ሮሜ 4፡3** *መጽሐፍስ ምን አለ? አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት።*

12. ይህ ስለ እግዚአብሔር ባህሪ ምን ይነግራችኃል?

# ጠቋሚ መልሶች

1. ዘፍጥረት 3፡1 ሰይጣን ሔዋንን ምን ብሎ ጠየቃት?
**በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? አላት።**

2. ዘፍጥረት 2፡17 እና 3፡3 እግዚአብሔር ለአዳም ከነገረው ቃል ውስጥ ሔዋን ምን የሚል ቃል ጨምራለች?
**አትንኩት የሚል ቃል።**

3. ዘፍጥረት 3፡6 ሰይጣን አንድ ጊዜ በሔዋን ህሊና ውስጥ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ጥርጣሬን ከጫረባት በኋላ ምን አደረገች ይላል ቃሉ?
**ከፍሬውም ወሰደችና በላች።**

4. ዘፍጥረት 3፡9-10 አዳምና ሔዋን ኃጢአት ካደረጉ በኋላ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ግንኙነቱን ቀጥሏል? እነርሱን መፈለጉንስ ቀጥሏል?
**አዎ።**

5. ዘፍጥረት 3፡22-24 እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ለምን ከገነት አባረራቸው?
**ከሕይወት ዛፍ በልተው ለዘላለም በኃጢአት እንዳይኖሩ።**

6. ይህ የእግዚአብሔር ቅጣት ሳይሆን ምህረት መሆኑን መገንዘብ ችላችኃል?
**አዎ።**

7. ሮሜ 5፡17 እንብቡና የእግዚአብሔርን የጽድቅ ስጦታና የተትረፈረፈ ጸጋ እንዴት ማግኘት እንችላለን?
**3] እንቀበለዋለን።**

8. ሮሜ 6፡23 ኃጢአትን የሚያደርግ ምን ይገባዋል?
**ሞት።**

9. ከዚህ ይልቅ ግን እግዚአብሔር በጸጋው ምን ሰጠን?
**በኢየሱስ የዘላም ሕይወትን።**

10. ሮሜ 10፡3 በእግዚአብሔር ፊት የራሳችንን ጽድቅ ለማቆም ብንሞክር ምን ከማድረግ እንወድቃለን?
**መሐሪና ፍቅር መሆኑን።**

11. አንደኛ ዮሃንስ 1፡9 እና ሮሜ 4፡3፣ እግዚአብሔር በኃጢአታችን እና በአመጻችን ሁሉ ላይ ምን ሊያደርግ ተሰፋ ሰጠን?
**ሊያሰወግዳቸው፣ ላያስታውሳቸውና ይቅር ሊላቸው።**

12. ይህ ስለ እግዚአብሔር ባህሪ ምን ይነግራችኃል?
**ይቅር ባይ እና አፍቃሪ እንደሆነ።**

# ትምህርት 5

# የእግዚአብሔር ማንነት

## በ እንድሩ ዉማክ፣

ከእግዚአብሔር ጋር መልካም ግንኙነት ለመመስረት የእግዚአብሔርን ማንነት፣ ትክክለኛ ባህሪውንም ማወቅ ያስፈልጋል። በኃጢአታችን የሚቆጣ አምላክ ነው? ወይስ እንደኛ ሥራ ሳይሆን እንደራሱ ባህሪ፡- ህይወቱን፣ በረከቱን ሊሠጠን የሚፈልግ ደግና መሃሪ አባት ነው? በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ሁለት የተለያዩ ዕይታዎችን እናገኛለን። ይህ የሆነው ግን እግዚአብሔር ሐሳቡን ስለሚለውጥ ወይም በሌላ መልኩን ቀይሮ ስለሚሰራ አይደለም። በመፅሃፍ ቅዱስ አገላለፅ በአንድ ወቅት እግዚአብሔር "የሰውን ኃጢአት እንደሚቆጥር" የሚያመለክት ቃል እናገኛለን።

ይህ ሃሳብ ህጻናት ልጆችን ከማሳደግ ጋር ተመሣሣይ ነው። ልጆችን ገና በለጋነታቸው ከእነርሱ ጋር በንግግር ማግባባት እና ሥርዓት እንዲያደርጉ ወይም እራስ ወዳድ ሆነው የወንድም ወይም እህታቸውን አሻንጉሊት መውሰድ እንደሌለባቸው ልናስረዳቸው፣ እነርሱም ሊረዱን አይችሉም። ነገር ግን ሊያደርጉ የሚገባቸውን ትዕዛዝ እንሰጣቸውና ሲጥሱ ይቆነጠጣሉ ፤ ስርዓት እንዲይዙ ይደረጋል። ስለ እግዚአብሔርም ሆነ ስለ ዲያብሎስ የሚያውቁት ነገር ባይኖርም ወይም ራስ ወዳድ ሲሆኑ ለዲያብሎስ እድል ፈንታ መስጠት እንደሆነ ባይረዱም ትዕዛዞቹን ካልፈፀሙ እንደሚቀጡ ስለሚያውቁ የታዘዙትን ይፈፅማሉ። የትዕዛዙን መሰረታዊ ሃሳብ ባይረዱም ነገር ግን ደግመው ያንን ድርጊት ከፈጸሙ ቅጣት እንደሚያስከትልባቸው ይረዳሉ ወይም ይገባቸዋል።

እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ያደረገው የዚህን ተመሳሳይ ነው። ሰዎች ዳግመኛ ካልተወለዱ በቀር በአዲስ ኪዳን ያገኘነውን መንፈሳዊ መረዳት ሊኖራቸው አይችልም። ስለዚህ ሰዎችን ከኃጢአት እንዲርቁ ለማድረግ ከሕጉ ጋር ማስፈጸሚያ ቅጣቱንም ተግባራዊ ሊያደርግ የተገባ ነበር። ለዚህም ነው አንዳንድ ጊዜ ቅጣቱ እስከ ሞት ድረስ የሚደርስ የነበረው። ሰይጣን ብዙዎችን በኃጢያት አማካይነት እያጠፋ ስለነበር ሰዎች ከኃጢአት ይርቁ ዘንድ እግዚአብሔር ህግን ያስፈጸመ ሲሆን ይህም ህግን የሚተላለፍ ሁሉ ኃጢአት የሚያደርሰውን ጉዳት እንዲያውቅ ወይም እንዲረዳ ያደርገዋል። የህጉ ወይም የቅጣቱ ክብደት እግዚአብሔር በኃጢአታችን ምክንያት አይወደንም የሚል ምሰል የሚሰጥ ቢሆንም እውነቱ ግን በተቃራኒው ነው። ሮሜ 5፡13 *"ሕግ እሰከ መጣ ድረሰ ኃጢአት በዓለም ነበረና ነገር ግን ሕግ በሌለበት ጊዜ ኃጢአት አይቆጠርም።"* "ሕግ እስከ መጣ ድረሰ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው አሰሩና ሌሎች ብዙ ትዕዛዛት በሙሴ በኩል ለአይሁድ ከመሰጠታቸው በፊት ማለት ሲሆን "አይቆጠርም" ማለት ደግሞ በዕዳ አይያዝም ወይም በኃጢአት ዕዳ ተጠያቂ የሚሆን የለም ማለት ነው። እስከዚህም ጊዜ ቢሆን ኃጢአት በዓለም ነበረ፣ ነገር ግን አይቆጠርም ነበር። ሕጉ ወይም አሰሩ ትዕዛዛት ከመሠጠታቸው በፊት ኃጢአት በሰዎች ላይ አይቆጠርባቸውም ነበር ማለት ነው። ይህ አይቆጠርም የሚለው ቃል የሒሳብ ሰነድ ባለሙያዎች ቋንቋ ነው፡ ለምሳሌ አንድ እቃ ከሱቅ ብትወሰዱና በእናንተ ሰም እንዲቆጥረው ወይም መዝግቦ እንዲይዘው የነገራችሁት ባለ ሱቅ ዕዳውን በእናንተ ሰም መዝግቦ ባያስቀምጥ ተጠያቂ እንደማትሆኑት ማለት ነው።

በዚህ ቃል መሰረት ሕጉ ወይም አሰሩ ትዕዛዛት ከመሠጠታቸው በፊት ኃጢአት በሰዎች ላይ አይቆጠርም ነበር። ይህ እጅግ የሚገርም አባባል ነው። ዘፍጥረት 3 እና 4 ላይ እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን በኃጢአት ምክንያት ጠልቶ አባረራቸው፣ እርሱ ንጹህ ስለሆነ በኃጢአት ምክንያት ከተበላሸ ሰው ጋር ምንም ጉዳይ ስለሌለው አባረራቸው ብለው የሚያስቡም ብዙ ናቸው። ሰው ንፁህ ሥራ ሠርቶ ራሱን ካላነጻ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት መመሥረት አይችልም ብለውም ያሰባሉ። ይህ ከኢየሱስ መልዕክት ጋር ይቃረናል፡- ሮሜ 5፡8 ገና ኃጢአተኛ ሳለህ ክርሰቶስ ለአንተ ሞቶልሃልና እግዚአብሔር ላንተ ያለውን ፍቅር ያሰረዳል ይላል። ስለዚህ አዲስ ኪዳን፣ እግዚአብሔር ፍቅሩን ለአንተ የገለጠው ገና በኃጢአት ሳለህ ነው እንጂ ራስህን ከኃጢአት ሥራህ ካነጻህ በኃላ አይደለም ይላል። የወንጌል አንዱና ሕይወትን የሚቀይረው እውነት እግዚአብሔር እንዲሁ አሁን

ባለንበት እኛነታችን እንደወደደን ማወቅና መረዳት ነው። እንዲወድህ ብለህ ለመለወጥ የምትሰራው ሳይኖር እርሱን ወደ ህይወትህ በመጋበዝና በመቀበል በፍቅሩ ትለወጣለህ። እርሱን የሚቀበል ሰው ህይወቱ እንደቀድሞው አይቀጥልም፤ ይቀየራል። ነገር ግን በፍቅሩ ትለወጣለህ ፍቅሩ ይለውጥሃል እንጂ ፍቅሩን ለማግኘት አይደለም የምትለወጠው።

በዘፍጥረት 3 እና 4 ውስጥ እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ከወደቁ በኃላ እንኳን እንዲሁ እንዳልተዋቸውና ያናግራቸው እንደነበር እንመለከታለን። አቤልና ቃየንም መስዋዕታቸውን ሲያቀርቡ በሚሰሙት ድምጽ ያናግራቸው እንደነበር፣ ከምላሻቸውም በመነሳት ድምጹን እንደለመዱትና እንደማይፈሩት እናስተውላለን፤ ኃጢአታቸውንም አይቆጥርባቸውም ነበር። ቃየን ወንድሙን አቤልን በመግደል በዓለም ላይ የመጀመሪያው ነብሰ ገዳይ በሆነበት ቀን የእግዚአብሔር ድምጽ ከሰማይ ወደ እርሱ እንዲህ ሲል መጣ - “ወንድምህ አቤል የት ነው?” ቃየንም ያለ ምንም የጸጸት ስሜት እግዚአብሔርን ዋሸ። ይህም ሊሆን የሚችለው አንድ ሰው የእግዚአብሔር ድምጽ የለመደውና የሚያውቀው፣ የማይፈራውም ሲሆን ብቻ ነው። ይህን ሁሉ የምንለው በልማድ እንደሚባለው ሳይሆን፤ እግዚአብሔር ከሰው ልጅ ጋር የነበረውን ግንኙነት ያላቋረጠና ዘወትር ከእነርሱ ጋር ህብረት እንደነበረው ለማሳየት ነው። ኃጢአታቸውንም አይቆጥርባቸውም ነበር። ይህ ማለት ግን ጥፋተኛ አይደሉም ማለት ነው? ይቅር ብሏቸዋል ማለት ነው? አይደለም! በፍጹም። ለዚህ እኮ ነው ሕግን ያሰገባው።

ሕግ የገባው ሰውን ወደ ቀድሞው ትክክለኛ ማንነቱ ለመመለስ ነበር። በዚህም ሰው ሕጉን “አልችልም ይቅርታ ይደረግልኝ ከዚህ ጥፋት አድነኝ” ብሎ በትህትና በመቅረብ ይቅርታን በነፃ፣ በስጦታ እንዲያገኝ ነው የእግዚአብሔር ሥርዓት የሚያስተምረን። እግዚአብሄር ህጉን የሰጠበት አላማ ሰው በራሱ ምንም ማድረግ እንደማይችል እንዲያውቀና ወደ እግዚአብሄር በገዛ ሰራዬ ከሃጢያቴ መንፃት አልችልምና አንተ ታደገኝ ብሎ እንዲመጣ ለማድረግ ነው። የሚያሳዝነው ግን ብዙ ኃይማኖቶች ከዚህ በተቃራኒ “ሕጉን ፈፅሙ” ካልፈፀማችሁ እግዚአብሔር ይቅር አይላችሁም በሚል ሽክሙን መልሰው ሰው ላይ መጫናቸውና ሃሳቡን መቀየራቸው ነው። የብሉይ ኪዳን ሕግ አላማ ኃጢአት ምን ያህል ከባድ እንደሆነ እንድንገነዘብና መድኃኒት ወይም አዳኝ የሚያስፈልገን መሆኑን በማወቅ እግዚአብሔር ሆይ ይህ ያንተ ንፅህና ልኬታ ከሆነ እኔ አልችለውም፣ ይቅርታ አድርግልኝ፣ ምህረትህን ስጠኝ፣ እንድንለው ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ሙሉ ሃሳብ ለእኛ ሁልጊዜ ፍቅር ነው።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ሮሜ 5፡13 “አይቆጥርባቸውም” የሚለው ቃል ምን ማለት ነው?

   **ሮሜ 5፡13** *ሕግ እስከ መጣ ድረስ ኃጢአት በዓለም ነበረና ነገር ግን ሕግ በሌለበት ጊዜ ኃጢአት አይቈጠርም።*

2. ሮሜ 7፡7 የሕጉ ተግባር ምንድን ነው?

   **ሮሜ 7፡7** *እንግዲህ ምን እንላለን? ሕግ ኃጢአት ነውን? አይደለም፤ ነገር ግን በሕግ ባይሆን ኃጢአትን ባላወቅሁም ነበር፤ ሕጉ። አትመኝ ባላለ ምኞትን ባላወቅሁም ነበርና።*

3. ገላትያ 3፡24 በዚህ ቃል መሰረት የሕጉ አላማ ወይም ተግባር ምንድን ነው?

   **ገላትያ 3፡24** *እንደዚህ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኖአል።*

4. ዮሐንስ 8፡1-11 በዝሙት የተያዘችውን ሴት ጉዳይ ኢየሱስ እንዴት ፈታው?

   **ዮሐንስ 8፡1-11** *ኢየሱስ ግን ወደ ደብረ ዘይት ሄደ። [2] ማለዳም ደግሞ ወደ መቅደስ ደረሰ ሕዝቡም ሁሉ ወደ እርሱ መጡ። ተቀምጦም ያስተምራቸው ነበር።[3]ጻፎችና ፈሪሳውያንም በምንዝር የተያዘችን ሴት ወደ እርሱ አመጡ በመካከልም እርሱዋን አቁመው። [4] መምህር ሆይ፥ ይህች ሴት ስታመነዝር ተገኝታ ተያዘች። [5] ሙሴም እንደነዚህ ያሉት እንዲወገሩ በሕግ አዘዘን፤ አንተስ ስለ እርሰዋ ምን ትላለህ? አሉት። [6] የሚከሱበትንም እንዲያገኙ ሊፈትኑት ይህን አሉ። ኢየሱስ ግን ጐንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ፤ [7] መላልሰው በጠየቁት ጊዜ ግን ቀና ብሎ። ከእናንተ ኃጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት አላቸው። [8] ደግሞም ጐንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ። [9] እነርሱም ይህን ሲሰሙ ሕሊናቸው ወቀሳቸውና ከሽማግሌዎች ጀምረው እስከ ኋለኞች አንድ አንድ እያሉ ወጡ፤ ኢየሱስም ብቻውን ቀረ ሴቲቱም በመካከል ቆማ ነበረች። [10] ኢየሱስም ቀና ብሎ ከሴቲቱ በቀር ማንንም ባላየ ጊዜ። አንቺ ሴት፥ እነዚያ ከሳሾችሽ ወዴት አሉ? የፈረደብሽ የለምን? አላት። [11] እርሰዋም። ጌታ ሆይ፥ አንድ ሰንኳ አለች። ኢየሱስም። እኔም አልፈርድብሽም፤ ሂጂ ከአሁንም ጀምሮ ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ አላት።*

5. የኢየሱስ ቃልና ድርጊት የእግዚአብሔርን እውነተኛ ማንነት ያሳያል? ዮሐንስ 3፡34ን አንብቡ።

   **ዮሐንስ 3፡34** *እግዚአብሔር የላከው የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራልና፤ እግዚአብሔር መንፈሱን ሰፍሮ አይሰጥምና።*

6. 1ኛ ዮሐንስ 4፡8 በዚህ ቃል መሰረት የእግዚአብሔር እውነተኛ ማንነት እንዴት ይገለጻል?

   **1ኛ ዮሐንስ 4፡8** *ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም፥ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና።*

7. ሮሜ 5፡6 የእግዚአብሔር ፍቅር ወደ እኛ የመጣው እኛ ምን እያለን ነበር?

   **ሮሜ 5፡6** *ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና።*

8. ሮሜ 5፡8 እግዚአብሔር ምን ሳለን ወደደን?

   **ሮሜ 5፡8** *ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል።*

9. ሮሜ 5፡10 እግዚአብሔር ምን ሳለን ወደደን?

   **ሮሜ 5፡10** *ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን፥ ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን፤*

10. ኢየሱስ ለኃጢአታችሁ የከፈለውን መሰዋዕት በማመን፤ ኢየሱስ ክርስቶስ - ይቅር እንዲላችሁና የግል አዳኛችሁና የነፍሳችሁ ጌታ እንዲሆን ብትጠይቁት እግዚአብሔር እውነተኛ ምህረቱንና ጸጋውን ይገልጥላችኋል?

# የጠቋሚ መልሶች

1. ሮሜ 5:13 “አይቆጥርባቸውም” የሚለው ቃል ምን ማለት ነው?
   **በዕዳ አይመዘገብባቸውም።**

2. ሮሜ 7:7 የሕጉ ተግባር ምንድን ነው?
   **ኃጢአትን እንድናውቅ ማድረግ ነው።**

3. ገላትያ 3:24 በዚህ ቃል መሰረት የሕጉ አላማ ወይም ተግባር ምንድን ነው?
   **ሰው አዳኝ ወይም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚያስፈልገው ማሳየት ነው።**

4. ዮሐንስ 8:1-11 በዝሙት የተያዘችውን ሴት ጉዳይ ኢየሱስ እንዴት ፈታው?
   **በምህረት እና በጸጋ።**

5. የኢየሱስ ቃልና ድርጊት የእግዚአብሔርን እውነተኛ ማንነት ያሳያል? ዮሐንስ 3:34ን አንብቡ።
   **አዎ።**

6. 1ኛ ዮሐንስ 4:8 በዚህ ቃል መሰረት የእግዚአብሔር እውነተኛ ማንነት እንዴት ይገለጻል?
   **ፍቅር።**

7. ሮሜ 5:6 የእግዚአብሔር ፍቅር ወደ እኛ የመጣው እኛ ምን እያለን ነበር?
   **ደካሞች፣ ማለትም ረዳት የሌለን ክፉዎች እያለን ነበር።**

8. ሮሜ 5:8 እግዚአብሔር ምን ሳለን ወደደን?
   **ኃጢአተኞች።**

9. ሮሜ 5:10 እግዚአብሔር ምን ሳለን ወደደን?
   **ጠላቶች።**

10. ኢየሱስ ለኃጢአታችሁ የከፈለውን መስዋዕት በማመን፤ ኢየሱስ ክርስቶስ - ይቅር እንዲላችሁና የግል አዳኛችሁና የነፍሳችሁ ጌታ እንዲሆን ብትጠይቁት እግዚአብሔር እውነተኛ ምህረቱንና ጸጋውን ይገልጥላችኃል?
    **አዎ።**

# ትምህርት 6

# ንስሐ

## በ ዶን ክሮው

ብዙ ሰዎች ስለ ንስሐ ያላቸው አመለካከት የተሳሳተ ነው። ንስሐ የአቅጣጫ ለውጥ ማድረግ እንጂ ፍጹም መሆን አይደለም። የአባካኙን ልጅ ወይም የጠፋውን ልጅ ታሪክ በመቀጠል እንመለከታለን። ኢየሱስ አንድ ሰው ንስሐ ገባ ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ፍጹም፣ ሰዕላዊ በሆነ መልኩ የሚያሳይ አንድ ታሪክ ተናግሯል። በሉቃስ 15፡11-12 እንዲህ ይላል፣ *"እንዲህም አለ። አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት። ከእነርሱም ታናሹ አባቱን። አባቴ ሆይ፣ ከገንዘብህ የሚደርሰኝን ክፍል ሰጠኝ አለው። ገንዘቡንም አካፈላቸው"።*

ታናሹ ልጅ አባቱ ገና ሳይሞት የውርስ ድርሻውን መካፈል ፈልጓል፤ ይህ ከየትኛውም ሰው ልማድና ባህሪ የወጣ ተግባር ነው፤ አባቱ ግን ጥያቄውን ተቀብሎ ድርሻቸውን አካፈላቸው። (በአማርኛው ትርጉም "ገንዘቡን" የሚለው ብር ብቻ ሳይሆን ሙሉ ንብረቱን እንደሆነ ልብ እንላለን።) በቁጥር 13 *"ከጥቂት ቀንም በኃላ ታናሹ ልጅ ገንዘቡን ሁሉ ሰብስቦ ወደ ሩቅ አገር ሄደ፣ ከዚያም እያባከነ ገንዘቡን በተነ"* ይላል። ታናሹ ልጅ የተካፈለውን ሁሉ ይዞ ወደ ሩቅ አገር ሄደና ገንዘቡን በሙሉ አባከነ፤ እንዲያውም አንድ ትርጉም "ከሴተኛ አዳሪዎች ጋር በጭፈራ ገንዘቡን በትና ጨረሰ" ሲል ይናገራል።

በቁጥር 14-15 ደግሞ እንዲህ ይላል - *"ሁሉንም ከከሰረ በኃላ በዚያች አገር ጽኑ ራብ ሆነ፣* (ያች ምድር ችግር ላይ ወደቀች ሕዝቡም በረሐብ ተጠቃ) *እርሱም ይጨነቅ ጀመር። ሄዶም ከዚያች አገር ሰዎች ከአንዱ ጋር ተዳበለ እርሱም እሪያ ሊያሰማራ ወደ ሜዳ ሰደደው"* (በቅንፍ ያለው በእኔ የተጨመረ ነው)። በዚያች አገር ሥራ አገኘ፣ እረኛ ሆኖ ከአንድ ሰው ተቀጥሮ መስራት ጀመረ፣ እርሱም አሳማዎችን እንዲመግብ ወደ ሜዳ ሰደደው። ቁጥር 16 *"እሪያዎችም ከሚበሉት አሰር ሊጠግብ ይመኝ ነበር፣ የሚሰጠውም አልነበረም"* ይላል። ተራበ፣ እጅግ ከመራቡ የተነሳ ጠኔ ይዞት - "በቃ የአሳማዎችም ምግብ ቢሆን - ማንኛውንም ነገር እባካችሁ ስጡኝ" ቢልም ማንም፣ ምንም የሚሰጠው አልነበረም። በውርስ ያገኘውን ገንዘብ ሁሉ አባክኖ ጨርሶ ነበር። ቁጥር 17 ሲቀጥል *"ወደ ልቡም ተመልሶ እንዲህ አለ እንጀራ የሚተርፋቸው የአባቴ ሞያተኞች ስንት ናቸው? እኔ ግን ከዚህ በረሀብ እጠፋለሁ"*። አንድ ትርጉም "ወደ ህሊናው ተመልሶ" ይላል። በሌላ አነጋገር የአባቱ ሰራተኞች ከሚበቃቸው በላይ ምግብ ነበራቸው።

ታናሹ ልጅ ለመመለስ ወሰነ - ንስሐ ገባ። ንስሐ የሐሳብ ለውጥ ነው፣ የአዕምሮ ለውጥ፣ የልብ ለውጥ ሲሆን ሰውን ከቀድሞው በተለየ አዲስ ጎዳና እንዲራመድ የሚያደርግ ነው። በቁጥር 18 እና 19 እንዲህ አለ *"ተነሥቼም ወደ አባቴ እሄዳለሁና፣ አባቴ ሆይ በሰማይና በፊትህ በደልሁ፣ ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም፣ ከሞያተኞችህ እንደ አንዱ አድርገኝ እለዋለሁ።"* "አባት ሆይ ፍጹም ባሪያ አድርገኝ፣ በአንተ ላይ ኃጢአት ሰርቻለሁ፣ ንብረትህንም አባክኛለሁ፣ እግዚአብሔርንም በድያለሁ፣ በቃ ባሪያ አድርገኝ"። ከዛም ተነሥቶ ወደ አባቱ ሄደ። ንስሐ ከአቋም ለውጥ፣ ከሐሳብ ለውጥ እና ከልብ ለውጥ የበለጠና ያለፈ ነው፣ ሰው ያመነበትን ውሳኔ ተከትሎ በተግባር በአዲስ አቅጣጫ እንዲራመድ የሚያደርግ ነው። ሁላችንም ከአባታችን ከእግዚአብሔርና ከሰማይ ቤታችን ፊታችን አዙረን ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ በኢሳያስ 53፡6 *"እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቀበዝብዘን ጠፋን፣ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ ሲል ይናገራል። ነገር ግን እግዚአብሔር በምህረት ኃጢአታችንን በኢየሱስ ላይ አኖረ።"*

ታሪኩ ሲቀጥል ከቁጥር 20-24 እንዲህ ይላል - *"ተነሰቶም ወደ አባቱ መጣ"*። አንድ ምሽት ይህንን ታሪክ ከዚህ በፊት ሰምቶ ለማያውቅ አንድ ሰው እየነገርኩት ነበር፣ ታሪኩን የነገርኩት ሰው የጠፋው ልጅ ሲመለስ

“አንተ ልጅ ያደረስከውን በደል አየሁ፣ በህይወት ዘመኔ ያጠራቀምኩትን ሐብት ሁሉ አባክነሃል፣ ከባሪያዎቼ እንደ አንዱ ሁን” ብሎ አባቱ በቁጣ እንደሚናገረው እርግጠኛ ነበር። አብዛኞቹ የምድር አባቶች በእርግጥም እጅግ ተቆጥተው ሰውየው እንዳለው ያደርጉ ይሆናል። ነገር ግን የአባቱን አቋም እንመልከት - *“እርሱም ገና ሩቅ ሳለ አባቱ አየውና አዘነለት* [ለልጁ ከልብ የሚመነጭ ፍቅር]*፤ ሮጦም አንገቱን አቀፈውና ሳመው። ልጁም አባቴ ሆይ በሰማይና በፊትህ በደልሁ፣ ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም፣ አለው። አባቱ ግን ባሪያዎቹን አለ፣ ፈጥናችሁ ከሁሉ የተሻለ ልብስ አምጡና አልብሱት፣ ለእጁ ቀለበት ለእግሩም ጫማ ስጡ፣ የሰባውን ፍሪዳ አምጥታችሁ እረዱት፣ ደስም ይበለን፣ ይህ ልጄ ሞቶ ነበርና ደግሞም ሕያው ሆኖአል። ጠፍቶም ነበር ተገኝቶአልም። ደስም ይላቸው ጀመር”*። የደስታ ግብዣም አደረጉ።

ይህን ታሪክ በአንድ ወቅት ለአንድ ሰው ስነግረው እንዲህ አለ - “ኢየሱስ የተናገረውን ማየት ችያለሁ። ወደ ሰማዩ አባቴ በምህረት ተመልሼ - አባት ሆይ በፊትህ ኃጢአትን ሰርቻለሁ፣ ልጅህ ልባልም አይገባኝም ብዬ ብቀርብ፣ ይቀበለኛል”። የሰማዩ አባታችን ያዝንልሃልና ባሪያ አያደርግህም። በሙሉ የልጅነት ስልጣን ወደ እራሱ ይመልስሃል፣ እግዚአብሔር እየጠበቀህ ነው። ከእርሱ ርቀህ ነበር? ለምን ወደ እርሱ ወደ አባትህ እና ወደ ሰማይ ቤትህ ዛሬ አትመለስም?

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ንስሐን እንዴት ትገልጹታላችሁ?

   **ሉቃስ 13፡1-5** *በዚያን ጊዜም ሰዎች መጥተው ጲላጦስ ደማቸውን ከመሥዋዕታቸው ጋር ስላደባለቀው ስለ ገሊላ ሰዎች አወሩለት። [2] ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው። እነዚህ የገሊላ ሰዎች ይህ ስለ ደረሰባቸው ከገሊላ ሰዎች ሁሉ ይልቅ ኃጢአተኞች የሆኑ ይመስሉአችኋልን? [3] እላችኋለሁ፥ አይደለም፤ ነገር ግን ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንዲሁ ትጠፋላችሁ። [4] ወይስ በሰሌሆም ግንቡ የወደቀባቸውና የገደላቸው እነዚያ አሥራ ሰምንት ሰዎች በኢየሩሳሌምከሚኖሩት ሁሉ ይልቅ በደለኞች ይመስሉአችኋልን? አይደለም፥ እላችኋለሁ፤ [5] ነገር ግን ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንደዚሁ ትጠፋላችሁ።*

2. ሉቃስ 13፡1-5 እንብቡና ሰው እንዳይጠፋ ምን ማድረግ አለበት?

3. 2ኛ ጴጥሮስ 3፡9 አንብቡና ለሰው ሁሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምንድን ነው?

   **2ኛ ጴጥሮስ 3፡9** *ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፥ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል።*

4. ሉቃስ 16፡19-31 አንብቡና በቁጥር 28 ባለ ጠጋው አንድ ሰው ከሙታን ተመልሶ ለወንድሞቹ እንዲነግርለት ለምን ፈለገ?

   **ሉቃስ 16፡19-31** *ቀይ ልብሰና ቀጭን የተልባ እግር የለበሰ አንድ ባለ ጠጋ ሰው ነበረ፥ ዕለት ዕለትም እየተመቸው በደስታ ይኖር ነበር። [20] አልዓዛርም የሚባል አንድ ድሀ በቍስል ተወርሶ በደጁ ተኝቶ ነበር፥ [21] ከባለ ጠጋውም ማዕድ ከሚወድቀው ፍርፋሪ ሊጠግብ ይመኝ ነበር፤ ውሾች እንኳ መጥተው ቍስሉቹን ይልሱ ነበር። [22] ድሀውም ሞተ፥ መላእክትም ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት፤ ባለ ጠጋው ደግሞ ሞተና ተቀበረ። [23] በሲኦልም በሥቃይ ሳለ አሻቅቦ አብርሃምን በሩቅ አየ አልዓዛርንም በእቅፉ። [24] እርሱም እየጮኸ። አብርሃም አባት ሆይ፥ ማረኝ፥ በዚህ ነበልባል እሣቀያለሁና የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ መላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ሰደድልኝ አለ። [25] አብርሃም ግን። ልጄ ሆይ፥ አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አሰብ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ፤ አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል አንተም ትሣቀያለህ። [26] ከዚህም ሁሉ ጋር ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እንዳይችሉ፥ ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጎአል አለ። [27] እርሱም። እንኪያስ፥ አባት ሆይ፥ ወደ አባቴ ቤት እንድትሰደው እለምንሃለሁ፤ አምስት ወንድሞች አሉኝና፤ [28] እነርሱ ደግሞ ወደዚህ ሥቃይ ስፍራ እንዳይመጡ ይመሰክርላቸው አለ። [29] አብርሃም ግን። ሙሴና ነቢያት አሉአቸው፤ እነርሱን ይስሙ አለው። [30] እርሱም። አይደለም፥ አብርሃም አባት ሆይ፥ ነገር ግን ከሙታን አንዱ ቢሄድላቸው ንስሐ ይገባሉ አለ። [31] ሙሴንና ነቢያትንም የማይሰሙ ከሆነ፥ ከሙታንም እንኳ አንድ ቢነሣ አያምኑም አለው።*

5. ሉቃስ 16፡30 እንብቡና ወንድሞቹ ወደዚህ የሰቃይ ሰፍራ (ሲኦል) እንዳይገቡ ምን ማድረግ አለባቸው?

6. የሐዋርያት ሥራ 26፡18 በእርግጥ በልዩ ሁኔታ አይሁን እንጂ ይህ ቃል ስለ ንስሐ እንደሚያወራ እንገነዘባለን። ንስሐ የሚገቡ ሰዎች ምን ይሆንላቸዋል?

   **የሐዋርያት ሥራ 26፡18** *የኃጢአትንም ሰርየት በእኔም በማመን በተቀደሱት መካከል ርስትን ያገኙ ዘንድ፥*

*ከጨለማ ወደ ብርሃን ከሰይጣንም ሥልጣን ወደ እግዚአብሔር ዘወር እንዲሉ ዓይናቸውን ትከፍት ዘንድ፥ ከሕዝቡና ወደ እነርሱ ከምልክህ ከአሕዛብ አድንሃለሁ።*

7. የሐዋርያት ሥራ 26፡20 በዚህ ቃል አሕዛብ ሊያደርጉት የሚገባ ሶስት ነገሮች ምንድን ናቸው?

   **የሐዋርያት ሥራ 26፡20** *ነገር ግን አስቀድሜ በደማስቆ ላሉት በኢየሩሳሌምም በይሁዳም አገር ሁሉ ለአሕዛብም ንስሐ ይገቡ ዘንድና ለንስሐ የሚገባ ነገር እያደረጉ ወደ እግዚአብሔር ዘወር ይሉ ዘንድ ተናገርሁ።*

8. ማቴዎስ 7፡21-23 ኢየሱስ እነዚህ ሰዎች ከእግዚአብሔር ፈቃድ ይልቅ ምን ያደርጋሉ አለ?

   **ማቴዎስ 7፡21-22** *ሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም። [22] በዚያ ቀን ብዙዎች። ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፥ በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፥ በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል። [23] የዚያን ጊዜም። ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።*

9. ከዚህ በመነሳት በእውነተኛ ንስሐ ጥቅምና ከአንገት በላይ ወደ እግዚአብሔር በሚደረግ አገልግሎት መካከል ምን አስተዋላችሁ?

10. ኢሳያስ 55፡7 እንብቡና ክፉዎች ምን ማድረግ አለባቸው?

    **ኢሳያስ 55፡7** *ክፉ ሰው መንገዱን በደለኛም አሳቡን ይተው፤ ወደ እግዚአብሔርም ይመለስ እርሱም ይምረዋል፥ ይቅርታውም ብዙ ነውና ወደ አምላካችን ይመለስ።*

11. በደለኛስ ሊያደርጋቸው የሚገቡ ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው?

12. ከላይ የተዘረዘሩትን ለሚያደርግ ሰው እግዚአብሔር ምን ያደርግለታል?

13. ሉቃስ 15፡7 እንብቡና ንስሐ በሚገባ አንድ ኃጢአተኛ፤ ሰማይ ምን ዓይነት ምላሽ አለው?

    **ሉቃስ 15፡7** *እላችኋለሁ፥ እንዲሁ ንስሐ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል።*

14. የሐዋርያት ሥራ 3፡19 ንስሐ ገብታችሁ ብትመለሱ ኃጢአታችሁ ምን ይደረጋል?

    **የሐዋርያት ሥራ 3፡19** *እንግዲህ ከጌታ ፊት የመጽናናት ዘመን እንድትመጣላችሁ አስቀድሞም ለእናንተ የመረጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲልክላችሁ፥ ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ ግቡ ተመለሱም።*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ንስሐን እንዴት ትገልጹታላችሁ?
   - **አዲስ ውሳኔ።**
   - **የሃሳብ (የአዕምሮ) ለውጥ።**
   - **የልብ ለውጥ፣ ሰው ከቀድሞ ምንገዱ ወደ እግዚአብሔር መንገድ እንዲመለስ የሚያደርግ።**
   - **ፍጹምነት ሳይሆን፣ የአቅጣጫ ለውጥ።**
   - **የአንድን ሰው ህይወት የሚቀይር ውሳኔ።**
   - **ከአሮጌው ማንነት ተላቆ ለእግዚአብሔር እራስን መስጠት።**
   - **በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ወደ እግዚአብሔር መመለስ።**

2. ሉቃስ 13፡1-5 አንብቡና ሰው እንዳይጠፋ ምን ማድረግ አለበት?
   **ንስሐ መግባት።**

3. 2ጴጥሮስ 3፡9 አንብቡና ለሰው ሁሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምንድን ነው?
   **ሁሉም ወደ ንስሐ እንዲደርሱ።**

4. ሉቃስ 16፡19-31 አንብቡና በቁጥር 28 ባለ ጠጋው አንድ ሰው ከሙታን ተመልሶ ለወንድሞቹ እንዲነግርለት ለምን ፈለገ?
   **ወደ እዚህ የስቃይ ቦታ እንዳይመጡ።**

5. ሉቃስ 16፡30 አንብቡና ወንድሞቹ ወደዚህ የስቃይ ሰፍራ (ሲኦል) እንዳይገቡ ምን ማድረግ አለባቸው?
   **ንስሐ መግባት።**

6. የሐዋርያት ሥራ 26፡18 በእርግጥ በልዩ ሁኔታ አይሁን እንጂ ይህ ቃል ሥለ ንስሐ እንደሚያወራ እንገነዘባለን። ንስሐ የሚገቡ ሰዎች ምን ይሆንላቸዋል?
   - **አይናቸው ይከፈታል፣**
   - **ከጨለማ ወደ ብርሐን ይመለሳሉ፣**
   - **ከሰይጣን ኃይል ወደ እግዚአብሔር ኃይል ይመለሳሉ፣**
   - **የኃጢአትን ይቅርታ ያገኛሉ፣**
   - **ርስትን ይቀበላሉ።**

7. የሐዋርያት ሥራ 26፡20 በዚህ ቃል አሕዛብ ሊያደርጉት የሚገባ ሶስት ነገሮች ምንድን ናቸው?
   - **ንስሐ መግባት፣**
   - **ወደ እግዚአብሔር መመለስ፣**
   - **ለንስሐ የሚገባ ነገር ማድረግ ወይም በተግባር፣ በሥራ፣ መግለጽ፣**

8. ማቴዎስ 7፡21-22 ኢየሱስ እነዚህ ሰዎች ከእግዚአብሔር ፈቃድ ይልቅ ምን ያደርጋሉ አለ?
   **ዓመጻ ወይም ህግ አልበኝነት።**

9. ከዚህ በመነሳት በእውነተኛ ንስሐ ጠቀሜታና ከአንገት በላይ ወደ እግዚአብሔር በሚደረግ አገልግሎት

መካከል ምን አስተዋላችሁ?
**መዳን ከልብ እንጂ ከአንገት በላይ (የከንፈር) አግልግሎት አይደለም።**

10. ኢሳያስ 55፡7 ክፉዎች ምን ማድረግ አለባቸው?
**መንገዳቸውን መተው።**

11. በደለኛስ ሊያደርጋቸው የሚገቡ ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው?
**ሐሳባቸውን መተው፣ ወደ ጌታም መመለስ።**

12. ከላይ የተዘረዘሩትን ለሚያደርግ ሰው እግዚአብሔር ምን ያደርግለታል?
**ምህረትና የበዛ ይቅርታ።**

13. ሉቃስ 15፡7 ንሰሐ በሚገባ አንድ ኃጢአተኛ ሰማይ ምን ዓይነት ምላሽ አለው?
**በሰማይ ታላቅ ደስታ ይሆናል።**

14. የሐዋርያት ሥራ 3፡19 ንሰሐ ገብታችሁ ብትመለሱ ኃጢአታችሁ ምን ይደረጋል?
**ይደመሰሳል።**

# ትምህርት 7

# ውሳኔ

## በ ዶን ክሮው

***ሉቃስ 14፡25-26*** ***“ብዙም ሕዝብ ከእርሱ ጋር ይሄዱ ነበር፣ ዞወር ብሎም እንዲህ አላቸው፣ ማንም ወደ እኔ የሚመጣ ቢኖር አባቱንና እናቱን ሚስቱንም ልጆቹንም ወንድሞቹንም እኅቶቹንም የራሱን ሕይወት ሰንኳ ሳይቀር ባይጠላ፣ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።”***

*“ብዙም ሕዝብ ከእርሱ ጋር ይሄዱ ነበር፣ ዞወር ብሎም እንዲህ አላቸው”* (ሉቃስ 14፡25) ። በዚህ ወቅት በኢየሱስ አገልግሎት፣ እጅግ ብዙ ሕዝብ ኢየሱስን ይከተሉት ነበር። አማርኛው እምብዛም ጊዜውን በትክክል አጉልቶ አልገለጸውም፣ በግሪክ ቋንቋ ግን ሁኔታው በትክክል ተገልጾ እናገኘዋለን። ይኸውም፣ በዚህ ጊዜ እጅግ ብዙዎች በተደጋጋሚ እና በቀጣይነት ኢየሱስን ይከተሉት ነበር የሚል ነው። ምናልባት በሚሠራቸው ተዓምራት ይሁን ወይም በጥቂት እንጀራ ብዙዎችን ስለመገበ፣ ምክንያቱን በትክክል ባናውቅም፣ ብዙ ህዝብ ግን ይከተሉት ነበር። በዚህ ጊዜ ነው ሆን ብሎ፣ ምናልባት ብዙዎች እርሱን ከመከተል ሊያቆሙ የሚችሉበትን ቃል የተናገራቸው።

*“ማንም ወደ እኔ የሚመጣ ቢኖር* [ይህም ማለት ከእኔ ጋር የሚሄድ ከሆነ፣ አብሮኝ ሊሆን የሚወድ ቢኖር፣ የሚከተለኝ ከሆነ ማድረግ ያለበት ይህ ነው]፣ *አባቱንና እናቱን ሚስቱንም ልጆቹንም ወንድሞቹንም እኅቶቹንም የራሱን ሕይወት ሰንኳ ሳይቀር ባይጠላ፣ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም”* (ሉቃስ 14፡26) በቅንፍ ያለው ከእኔ የተጨመረ ነው። ይህንን ቃል እንዳነበብኩ - ጌታ ሆይ የምርህን አይደለም ብዬ አሰብኩ። ባይጠላ የሚለው ቃል ምን ማለት ነው? ምናልባት ባነሰ ፍቅር መውደድ የሚለውን ለመግለጽ ይሆናል ብዬ አሰብኩ። ጥናቴን ስጀምር ግን ይህ ቃል የሚናገረው ስለ “መጥላት” እንደሆነ ተረዳሁ።

ኢየሱስ አንድን ነጥብ አጉልቶ ለማሳየት እጅግ ጠንካራ ቃላቶችን ይጠቀማል። አባታችሁን፣ እናታችሁን፣ እኅታችሁን፣ ወንድማችሁን እና የእራሳችሁን ህይወት ሳይቀር ካልጠላችሁ የእርሱ ደቀ መዝሙር መሆን እንደማትችሉ ይናገራል። አንድ ጥያቄ እንጠይቅ፣ በዚህ አለም ላይ በጣም ጥብቅ ግንኙነት (ዝምድና) ያላችሁ ከማን ጋር ነው? ከእናትና ከአባታችሁ ወይም ከትዳር አጋራችሁ እና ከልጆቻችሁ ጋር ነው። ወላጆች በሕይወት ባይኖሩና ከትዳር ጓደኛችሁ ጋር ብትፋቱ ለእናንተ የሚቀርብ ዘመድ ማን ቀራችሁ? ወንድምና እህቶቻችሁ ናቸው። እንግዲህ እነርሱንም ካልጠላችሁ የኔ ደቀመዝሙር ልትሆኑ አትችሉም ሲል ምን ማለቱ ነው?

ኢየሱስ የተናገረው እኛ ሊኖረን ስለሚችለው የመጨረሻ ቅርብ ወዳጅነት ወይም ዝምድና ነው። እርሱ ዋነኛ የሆነበት ወዳጅነት ከእናንተ ጋር ይኖረው ዘንድ እንድትወስኑ ይፈልጋል፣ ይህን ውሳኔ እንድትወስኑ ይጠይቃችኋል። እርሱን በሕይወታችሁ ዋና (ቁጥር አንድ) እንድታደርጉት ይፈልጋል። ከእርሱ ጋር ያላችሁን ግንኙነት እጅግ ከሚቀርባችሁ ጥብቅ ዘመድ ጋር ያነጻጽረዋል። “ጥላቻ” ወይም መጥላት የሚለው ቃል ዘይቤያዊ ወይም ምሳሌያዊ ንግግር ነው። “ከእኔ ጋር ያላችሁ ወዳጅነት በአለም ላይ ከምትወዱት ወይም ከምታቀርቡት የኔ ነው ከምትሉት ምድራዊ ነገር ይልቅ እጅግ አስፈላጊ ነው” እያለን ነው። ደግሞም ከወላጆቻችሁ ከትዳር ጓደኛችሁ ከልጆቻችሁ ይልቅ የምትወዱት አንድ ሰው አለ። ያ ሰው ማን እንደሆነ ታውቃላችሁ? እግዚአብሔር አይደለም፣ ራሳችሁን ነው። እራሳችሁን ከማንም ከሚቀርባችሁ ሰው ይልቅ ትወዱታላችሁ።

ትዳር ለምን ይፈርሳል፣ ባልና ሚስት ለምን ይፋታሉ፣ ምክንያቱም ከትዳር አጋራችው ይልቅ እራሳቸውን አብልጠው ስለሚወዱ ነው። “እኔ እንደምፈልገው አልተደረገልኝም፣ ስለዚህ መገላገል እፈልጋለሁ” ይላሉ።

ኢየሱስ እኔ ልበልጠው የሚገባ አንድ ወዳጅ አላችሁ እርሱም ራሳችሁን የምትወዱበት ፣ እራስ ወዳድ የሆነው የእናንተ ሕይወት ነው ይላል። ይህ ነው እውነተኛ ደቀ መዝሙርነት። ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ዋጋ ስለማያስከፍል የደቀመዝሙርነት ህይወት አይደለም። እንድንከተለውና በሕይወታችን ቁጥር አንድ እንድናደርገው ይፈልጋል።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ሉቃስ 9፡57-62 ይህ ቃል ክርስቶስን የመከተል ልኩ እስከ ምን ያህል እንደሆነ ያስተምራል?

   **ሉቃስ 9፡57-62** *እነርሱም በመንገድ ሲሄዱ አንድ ሰው። ጌታ ሆይ፥ ወደ ምትሄድበት ሁሉ እከተልሃለሁ አለው። [58] ኢየሱስም። ለቀበሮዎች ጉድጓድ ለሰማይም ወፎች መሳፈሪያ አላቸው፥ ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም አለው። [59] ሌላውንም። ተከተለኝ አለው። እርሱ ግን። ጌታ ሆይ፥ አስቀድሜ ልሄድና አባቴን እቀብር ዘንድ ፍቀድልኝ አለ። [60] ኢየሱስም። ሙታናቸውን እንዲቀብሩ ሙታንን ተዋቸው፤ አንተስ ሄደህ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሰበክ አለው። [61] ደግሞ ሌላው። ጌታ ሆይ፥ እከተልሃለሁ፤ ነገር ግን አስቀድሜ ከቤቴ ሰዎች እንድሰናበት ፍቀድልኝ አለ። [62] ኢየሱስ ግን። ማንም ዕርፍ በእጁ ይዞ ወደ ኋላ የሚመለከት ለእግዚአብሔር መንግሥት የተገባ አይደለም አለው።*

2. ሉቃስ 8፡13-14፣ አንዳንድ ሰዎች ከክርስትና ህይወት ለምን ይወድቃሉ? ወይም ፊታቸውን ለምን ያዞራሉ?

   **ሉቃስ 8፡13-14** *በዓለት ላይም ያሉት ሲሰሙ ቃሉን በደስታ የሚቀበሉ ናቸው፤ እነርሱም ለጊዜው ብቻ ያምናሉ እንጂ በፈተና ጊዜ የሚክዱ ሥር የሌላቸው ናቸው። [14] በእሾህ መካከልም የወደቀ እነዚህ የሚሰሙት ናቸው፤ መንገዳቸውንም ሄደው በሕይወት ዘመን በአሳብና በባለ ጠግነት ምቾት ይታነቃሉ፥ ሙሉ ፍሬም አያፈሩም።*

3. ሕዝቅኤል 16፡8፣ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የነበረውን ግንኙነት በጋብቻ ይመስለዋል፤ በዚህ ግንኙነት አንዱ የማን ንብረት ነው?

   **ሕዝቅኤል 16፡8** *በአንቺ ዘንድ ባለፍሁና ባየሁሽ ጊዜ፥ እነሆ፥ ጊዜሽ የፍቅር ጊዜ ነበረ፤ እኔም መጐናጸፊያዬን በላይሽ ዘረጋሁ ኀፍረተ ሥጋሽንም ከደንሁ፤ ማልሁልሽም ከአንቺም ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፥ አንቺም ለእኔ ሆንሽ።*

4. 1ኛ ቆሮንቶስ 6፡19፣ እናንተ የማን ናችሁ?

   **1ኛ ቆሮንቶስ 6፡19-20** *ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።*

5. 1ኛ ቆሮንቶስ 6፡20፣ ሰውነታችሁና መንፈሳችሁ የማን እንደሆነ ይናገራል?

6. ያዕቆብ 4፡4፣ በእግዚአብሔር ላይ መንፈሳዊ አመንዝራነት ልትፈጽሙ ትችላላችሁ ማለት ነው?

   **ያዕቆብ 4፡4** *አመንዝሮች ሆይ፥ ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንዲሆን አታውቁምን? እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል።*

7. በእግዚአብሔር አይን መንፈሳዊ አመንዝራነት የሚያመጣ ምንድን ነው ማለት እንችላለን? ከሮሜ 1፡25 አንብቡ።

**ሮሜ 1፡25** *ይህም የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት ስለ ለወጡ በፈጣሪም ፈንታ የተፈጠረውን ስላመለኩና ስላገለገሉ ነው፤ እርሱም ለዘላለም የተባረከ ነው፤ አሜን።*

8. የሐንስ 2፡23-25፣ ስለ እምነት እና እርሱን ስለመከተል ምን እንማራለን?

   **የሐንስ 2፡23-25** *ስለዚህ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ይህን እንደ ተናገረ አሰቡና መጽሐፍንና ኢየሱስ የተናገረውን ቃል አመኑ። [23] በፋሲካ በዓልም በኢየሩሳሌም ሳለ፥ ያደረገውን ምልክት ባዩ ጊዜ ብዙ ሰዎች በስሙ አመኑ፤ [24-25] ነገር ግን ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ያውቅ ነበር፤ ስለ ሰውም ማንም ሊመሰክር አያስፈልገውም ነበርና አይተማመናቸውም ነበር፤ ራሱ በሰው ያለውን ያውቅ ነበርና።*

9. ሉቃስ 14፡28-30፣ ኢየሱስን መከተል የሚያስከፍለውን ዋጋ መዝናችኃል? ልትከተሉትስ ወስናችኃል?

   **ሉቃስ 14፡28-30** *ከእናንተ ግንብ ሊሠራ የሚወድ ለመደምደሚያ የሚበቃ ያለው እንደ ሆነ አስቀድሞ ተቀምጦ ከሳራውን የማይቈጥር ማን ነው? [29] ያለዚያ መሠረቱን ቢመሠርት፥ ሊደመድመውም ቢያቅተው፥ ያዩት ሁሉ። [30] ይህ ሰው ሊሠራ ጀምሮ ሊደመድመው አቃተው ብለው ሊዘብቱበት ይጀምራሉ።*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ሉቃስ 9፡57-62፣ ይህ ቃል ክርስቶስን የመከተል ልኩ እስከ ምን ያህል እንደሆነ ያስተምራል?
**ፍጹም ራስን እስከ መስጠት።**

2. ሉቃስ 8፡13-14፣ አንዳንድ ሰዎች ከክርስትና ህይወት ለምን ይወድቃሉ? ወይም ፊታቸውን ለምን ያዞራሉ?
**በእግዚአብሔር ቃል ሥር ሰደው ስላላደጉ፣ በሀሳብና በባለጠግነት ምቾት በዚህ ዓለም ደስታ ይወሰዳሉ።**

3. ሕዝቅኤል 16፡8፣ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የነበረውን ግንኙነት በጋብቻ ይመስለዋል፤ በዚህ ግንኙነት አንዱ የማን ንብረት ይሆናል?
**የእግዚአብሔር።**

4. 1ኛ ቆሮ 6፡19፣ እናንተ የማን ናችሁ?
**የእግዚአብሔር።**

5. 1ኛ ቆሮ 6፡20፣ ሰውነታችሁና መንፈሳችሁን የማን እንደሆነ ይናገራል?
**የእግዚአብሔር።**

6. ያዕቆብ 4፡4፣ በእግዚአብሔር ላይ መንፈሳዊ አመንዝራነት ልትፈጽሙ ትችላላችሁ ማለት ነው?
**አዎ።**

7. በእግዚአብሔር አይን መንፈሳዊ አመንዝራነት የሚያመጣ ምንድን ነው ማለት እንችላለን? ከሮሜ 1፡25 እንብቡ።
**ከእርሱ ወደ ጣኦት ዞር ያለ ልብ (ከእግዚአብሔር ይልቅ ውድ የሆኑባችሁ ነገሮች)።**

8. ዮሐንስ 2፡23-25፣ ስለ እምነት እና እርሱን ስለመከተል ምን እንማራለን?
**ኢየሱስ ልባችንን እንደሚፈልግ (ሙሉ መስጠት)።**

9. ሉቃስ 14፡28-30፣ ኢየሱስን መከተል የሚያስከፍለውን ዋጋ መዝናችኃል? ልትከተሉትስ ወስናችኃል?

# ትምህርት 8

# የውሃ ጥምቀት

## በ ዶን ክሮው

**ጥያቄ፡-** “አንድ ሰው ለመዳን በውሃ መጠመቅ አለበት ወይ የሚለውን ማወቅ እፈልጋለሁ። እግዚአብሔርን እወደዋለሁ የተጠመቀኩት ገና በሰባት አመቴ ነው። አሁን አስራ ስምንት ዓመት ሆኖኛል፣ እኔ በማመልክበት ቤተ ክርስቲያን አንድ ሰው በልጅነት እድሜ ስለተጠመቀ ድኗል ማለት እንደማይቻል ተነገረኝ። ደግሞም ወደ መንግስተ ሰማይ ለመግባት መጠመቅ እንደሚገባ ነገረውኛል፣ ቤተሰቦቼ ግን እንደዛ አይደለም አሉኝ። እኔ ወደ እግዚአብሔር መንግስት መግባት እፈልጋለሁ። በምችለው ሁሉ ለእግዚአብሔር ለመኖር እሞክራለሁ፣ ነገር ግን አሁን እድሜዬ ከደረስ እንደገና ደግሜ መጠመቅ ያስፈልገኛ እንደሆነ ማወቅ እፈልጋለሁ፣ እባካችሁ ምላሻችሁን በፍጥነት ስጡኝ፣ ጌታ ይባርካችሁ፣ አመሰግናለሁ”።

**መልስ፡-** መዳንና የኃጢአት ይቅርታ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን በነጻ የሚገኝ ነው። ሐዋ 10:43 - *“በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኃጢአቱን ሥርየት እንዲቀበል ነብያት ሁሉ ይመሰክሩለታል”* ይላል። መዳን የሚገኘው በእምነት ነው። ይኸውም በእርሱ (በኢየሱስ) ላይ እምነታችሁን በመጣል፣ ኢየሱስ ስለ እናንተ ደሙን ያፈሰሰላችሁ እና በአባቱ ቀኝ እንድትቆሙ ዋጋ የከፈለላችሁ መሆኑን በማመን ነው። በሐዋ ሥራ 10:44-48 ላመኑት መንፈስ ቅዱስ (የመዳናቸው ማረጋገጫ) የተሰጣቸው ሲሆን ይህም የሆነው ገና በውሃ ሳይጠመቁ ነበር።

ይህ እውነት እንዳለ ሆኖ በሌላ ጊዜ ደግሞ የኃጢአት ይቅርታ እና የንስሃ ጥምቀት በአንድ ጊዜ የሆኑበት አጋጣሚም አለ (የሐዋ ሥራ 2:38) ። ይህ የሆነው ጥምቀት የእምነት መግለጫ ስለሆነ ወይም ማመናቸውን በሥራ ለመግለጽ ንስሐ እየገቡና በኢየሱስ በማመን ወዲያውኑ ሥለተጠመቁ ነው፣ ማርቆስ 16:16 – *“ያመነ የተጠመቀም ይድናል፣ ያላመነ ግን ይፈረድበታል”* ይላል። በተጨማሪም ጥምቀት ወደ ጌታ የሚመጡትን ሰዎች ለበጎ ህሊና የመጥሪያ መንገድ መሆኑን (የሐዋ ሥራ 22:16 እና 1ኛ ጴጥሮስ 3:21) ይናገራል።

በ ሰባት ዓመት እድሜህም ቢሆን በሙሉ ልብህ ወደ ጌታ ተመልሰህ ከተጠመክ እግዚአብሔር የልጅነት እምነትህን ይቀበላል። ጥምቀት መስፈርቶች አሉት። አንደኛው መስፈርት ንስሐ ነው። ከኃጢአት ወደ ኢየሱስ እና ወደ ይቅርታው ተመልሰህ፣ የልብ ለውጥ፣ የሃሳብ ለውጥ አድርገሃል (ሐዋ 2:38፣ 20:21 እና 17:30)? ኢየሱስንስ እንደ ግል አዳኝህ ተቀብለህ የእምነት ልምምድ ውስጥ ገብተሃል (ማርቆስ 16:16፣ ዮሐንስ 3:16 እና ሮሜ 10:9-10)? ይህንን ካላደረግክ አሁኑኑ ወደ ኢየሱስ ተመለስ፣ ለኃጢአትህ ንስሐ ግባ፣ ይቅር ወደሚልህ ወደ ጸጋው ቅረብ እና እርሱን ለመከተል ውሳኔህን በውሃ በመጠመቅ ፈጽም። ይህንን ያደረገ ሰው ኢየሱስን ለመከተል ያደረገውን ውሳኔ በውሃ በመጠመቅ ያረጋግጣል ማለት ነው።

**ጥምቀት አንድ ሰው በኢየሱስ ማመኑን የሚገልጽበት ሥራ ነው**። ያለ እምነት ሥራ ዋጋ ቢስ ነው። ኢየሱስን የህይወታቸው ጌታ እና አዳኝ አድርገው የተቀበሉ ሰዎች በግልጽ እምነታቸውን ለመናገር እና ኢየሱስን በህዝብ ፊት ለመመስከር ፈቃደኞች ናቸው። የኢየሱስን ትዕዛዝ በግልጽ የሚቃወሙ ሰዎች በተወሰነ ደረጃ የሞተ እምነት ይታይባቸዋል። **ሰዎች እምነታቸውን ሊገልጹ ፈቃደኛ ካልሆኑ እምነታቸው የሞተ ነው** (ያዕቆብ 2:18-19)። እምነት ብቻውን ያድናል፣ ነገር ግን የሚያድን እምነት ምንጊዜም ብቻውን አይደለም። ሁሌም እራሱን ለመግለጽ ፈቃደኛ ነው። ጥምቀት እምነትን ለመግለጽ የሚሠራ ሥራ ነው። **የሚያድን ጥምቀት አይደለም፣ ኢየሱስ ነው። ውሃም ኃጢአትን አጥቦ አያነጻም፤ ኃጢአትን የሚያነጻ የኢየሱስ ደም ብቻ ነው**። ነገር ግን እምነት የኢየሱስን ደም በእናንተ ላይ ያፈሰዋል። ይህንን እምነትም አንድ የሚጠመቅ ሰው በመጠመቁ ይገልጸዋል (ሐዋ 22:16)። ዋናው ጥያቄ ንስሐ ገብታችኋል? በኢየሱስ ታምናላችሁ? የሚል ነው። ካመናችሁ ምን ያዘገያችኋል ተነሱና ተጠመቁ!

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ይህ ወጣት የጠየቀው ጥያቄ ምንድነው?

2. እንደ የሐዋርያት ሥራ 10፡43 መዳን የሚገኘው እንዴት ነው?

   **የሐዋርያት ሥራ 10፡43** *በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኃጢአቱን ስርየት እንዲቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል።*

3. ጥምቀት በመዳናችን ጊዜ እምነታችንን የምንገልጽበት የእምነታችን መገለጫ ነው። የሐዋርያት ሥራ 2፡38 ይህንን እንዴት ይገልጸዋል?

   **የሐዋርያት ሥራ 2፡38** *ጴጥሮስም። ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።*

4. ይህንን እውነት ማርቆስ 16፡16 እንዴት ይገልጸዋል?

   **ማርቆስ 16፡16** *ያመነ የተጠመቀም ይድናል፥ ያላመነ ግን ይፈረድበታል።*

5. ጥምቀት የጌታን ስም የመጥራት መንገድ ነው፤ ይህንን እውነት ሐዋርያት ሥራ 22፡16 እንዴት ይገልጸዋል?

   **የሐዋርያት ሥራ 22፡16** *አሁንስ ለምን ትዘገያለህ? ተነሣና ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ ከኃጢአትህም ታጠብ።*

6. ጥምቀት ወደ ጌታ በንጹህ ህሊና ልመናን ማቅረብ ነው፤ 1ኛ ጴጥሮስ 3፡21 ይህን እውነት ያረጋግጣል?

   **1ኛ ጴጥሮስ 3፡21** *ይህም ውኃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል፥ የሰውነትን እድፍ ማስወገድ አይደለም፥ ለእግዚአብሔር የበጎ ሕሊና ልመና ነው እንጂ፥ ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ነው፤*

7. እንደ የሐዋርያት ሥራ 2፡38 ለጥምቀት የሚያስፈልገው መስፈርት ምንድን ነው?

8. እንደ ማርቆስ 16፡16 የጥምቀት መስፈርት ምንድን ነው?

9. አንድ ህጻን ንስሐ መግባት ይችላል?

10. አንድ ህጻን ማመን ይችላል?

11. የሐዋርያት ሥራ 10፡43-48። በክርስቶስ ካመነ በኋላ፣ አንድ አማኝ ሊያደርገው የሚገባው ምንድን ነው?

    **የሐዋርያት ሥራ 10፡43-48** *በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኃጢአቱን ስርየት እንዲቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል። [44] ጴጥሮስ ይህን ነገር ገና ሲናገር ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደ።*

*[45] ከጴጥሮስም ጋር የመጡት ሁሉ ከተገረዙት ወገን የሆኑ ምዕመናን በአሕዛብ ላይ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ስለ ፈሰሰ ተገረሙ፤ [46] በልሳኖች ሲናገሩ እግዚአብሔርንም ሲያከብሩ ሰምተዋቸዋልና። [47] በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ መልሶ። እነዚህ እንደ እኛ ደግሞ መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉ እንዳይጠመቁ ውኃን ይከለክላቸው ዘንድ የሚችል ማን ነው? አለ። [48] በኢየሱስ ክርስቶስ ስምም ይጠመቁ ዘንድ አዘዛቸው። ከዚህ በኋላ ጥቂት ቀን እንዲቀመጥ ለመኑት።*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ይህ ወጣት የጠየቀው ጥያቄ ምንድነው?
   **ወደ ሰማይ ለመግባት መጠቀመቅ ያስፈልጋል።**

2. እንደ የሐዋርያት ሥራ 10፡43 መዳን የሚገኘው እንዴት ነው?
   **በነጻ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን**

3. ጥምቀት በመዳናችን ጊዜ እምነታችንን የምንገልጽበት የእምነታችን መገለጫ ነው። የሐዋርያት ሥራ 2፡38 ይህንን እንዴት ይገልጸዋል?
   **ጴጥሮስ "ንስሐ ግቡ እና ተጠመቁ" አለ።**

4. ይህንን እውነት ማርቆስ 16፡16 እንዴት ይገልጸዋል?
   **ኢየሱስ "ያመነ የተጠመቀም ይድናል" አለ፣ በዚህም በአንድ ላይ እንደሚፈጸምም ያሳያል።**

5. ጥምቀት የጌታን ስም የመጥራት መንገድ ነው፤ ይህንን እውነት የሐዋርያት ሥራ 22፡16 እንዴት ይገልጸዋል?
   **ይህ ቃል የጌታን ስም ለሚጠሩ ኃጢአታቸው እንደሚታጠብላቸው ይናገራል፣ በዚህም የጌታን ስም በአንደበት ስለመጥራት (ሉቃስ 18፡13) ወይም ደግሞ ይህ ቃል እንደሚያሳያው በመጠመቅም መሆኑን ይገልጻል።**

6. ጥምቀት ወደ ጌታ በንጹህ ህሊና ልመናን ማቅረብ ነው፤ 1ኛ ጴጥሮስ 3፡21 ይህን እውነት ያረጋግጣል?
   **አዎ።**

7. እንደ የሐዋርያት ሥራ 2፡38 ለጥምቀት የሚያስፈልገው መስፈርት ምንድን ነው?
   **ንስሐ።**

8. እንደ ማርቆስ 16፡16 የጥምቀት መስፈርት ምንድን ነው?
   **ሊያምን ይገባዋል።**

9. አንድ ህጻን ንስሐ መግባት ይችላል?
   **አይችልም።**

10. አንድ ህጻን ማመን ይችላል?
    **አይችልም።**

11. የሐዋርያት ሥራ 10፡43-48። ከክርስቶስ ካመነ በኋላ፣ አንድ አማኝ ሊያደርገው የሚገባው ምንድን ነው?
    **የውሃ ጥምቀት።**

## ትምህርት 9

# በክርስቶስ የሆነ ማንነት - ክፍል 1

### በ አንድሩ ዉማክ

ሁለተኛ ቆሮንቶስ 5፡17 እንዲህ ይላል፣ *“ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፣ ሁሉም አዲስ ሆኖአል”።* በአዲስ ኪዳን “በክርስቶስ” የሚለው ቃል ከ300 ጊዜ በላይ የተጠቀሰ ቃል ሲሆን ይህም ሁልጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ወሳኝ ህብረት ያመላክታል። ይህ አንዴ ከሆነ ጀምሮ አዲስ ፍጥረት ሆናችኃል። አንዳንድ ትርጉሞች “አዲስ ፍጡር” ይላሉ።

ይህም፣ በእኔ እምነት፣ በክርስቶስ ያላችሁን አዲስ ማንነት ለመረዳት እጅግ ጠቃሚና አስፈላጊ ወደ ሆነ ጉዳይ ያመራል። ጉዳዩ የተከናወነው በሚታየው ዓለም አይደለም፣ የሚናገረውም ስለ ስጋችሁ አይደለም። የሚታየው ስጋችሁ ፍጹም ተቀይሮ፣ መልካችሁ ወይም ቅርጻችሁ ተለውጧል እያለ አይደለም። ከመዳኑ በፊት ወፍራም የነበረ ሰው አመጋገቡን ካላስተካከለ፣ ከዳነ በኃላም ወፍራም ሆኖ ይቀጥላል። ደግሞም አዕምሮአችን፣ አስተሳሰባችን ወይም ስሜታችንም ብዙዎች “ማንነት” የሚሉት በዳንን ጊዜ ይቀየራል ማለት አይደለም። ለምሳሌ ድሮ በጣም ፈጣን ካልነበራችሁ አሁን ከዳናችሁ በኃላ በጣም ፈጣን፣ ብልህ ትሆናላችሁ ማለት አይደለም። የነበሯችሁ፣ የያዛችኃቸው አስተሳሰቦችና አመለካከቶች ገና እንዳሉ ናቸው።

ነገር ግን ሶስተኛ አካል አለ። በዚህ ጥቅስ መሠረት (2ኛ ቆሮ 5፡17) ስጋችን ካልሆነ፤ አዕምሮአችን ወይም አስተሳሰባችንም ካልሆነ፤ ሌላ ሶስተኛ አካላችን እንደሆነ እንረዳለን፣ እርሱም መንፈሳችን ነው። ይህን የሚገልጽልን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች በሚጸልይላቸው በ1ኛ ተሰሎንቄ 5፡23 የሚገኘው ቃል ነው፣ *“የሠላምም አምላክ ሁለንተናችሁን ይቀድስ መንፈሳችሁም ነፍሳችሁም ስጋችሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ”* (1ኛ ተሰሎንቄ 5፡23)። ይህ ቃል መንፈስ ነፍስና ስጋ እንዳለን ያሳያል። “ስጋ” የሚባለው በግልጽ የሚታየውና የምናውቀው ውጫዊ አካላችን ሲሆን ከዚህ የተለየ አካል እንዳለን ግን ሁላችን እናውቃለን፤ እርሱም ስሜታችንና የአዕምሮአችን ክፍል ነው፤ ይህንን ክፍል መጽሐፍ ቅዱስ “ነፍስ” በማለት ይጠራዋል። አንዳንድ ሰዎች በአካል ሳይነኳችሁ በንግግር ብቻ ስሜታችሁን የሚጎዳ ወይም የሚያስደስት ነገር ሲናገሩ ከመንካት በላይ ይሰማችኋል፣ ይህ የስሜት ክፍል ስጋችን አይደለም። ብዙዎቻችን እኔ ብለን የምንጠራው ማንነታችን ይህ የስጋ እና የነፍስ (ከላይ ያየናቸው ሁለቱን) ክፍሎቻችን ነው ብለን ብናስብም መጽሐፍ ቅዱስ ግን ሌላ ሶስተኛ ክፍል አለ፣ እርሱም መንፈሳችሁ ነው ይለናል።

ሰው በዳነ ጊዜ አዲስ የሆነውና የተለወጠው መንፈሱ ነው። በእርግጥ መንፈሳችን ህይወትን የሰጠን የሰውነታችን ክፍል ነው። የያዕቆብ መልዕክት 2፡26 “ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው” ይላል፤ የእንግሊዝኛው የንጉስ ጀምስ ትርጉም “ከመንፈስ የተለየ ሥጋ ...” ይላል። ይህ ቃል የሚያመለክተው ለዚህ፣ ለሚታየው አካላችን የህይወት እስትንፋስ የሰጠው መንፈስ መሆኑን ነው። ህይወታችን የመጣው ከዚህ ነው። በዘፍጥረት 2 አዳምና ሔዋን ሲፈጠሩ የአዳም ሰውነት ከተዘጋጀ በኃላ እግዚአብሔር የህይወት እስትንፋስ እፍ አለበትና ህያው ሆነ። በዕብራውያን የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ይህ “እስንትፋስ” የሚለው ቃል መንፈስ በሚል ተተርጉሞ እናገኘዋለን። እግዚአብሔር የአዳምን የስጋ እና የነፍስ ክፍሎች ካዘጋጀ በኃላ የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት፤ እርሱም ህያው ነፍስ ያለው ሆነ። ህይወትን ለሰውነታችን የሰጠው አካል መንፈሳችን ነው።

ሰው፣ ከመዳኑ በፊት ወይም ክርስቶስን አዳኝ አድርጎ ለመቀበል ከመወሰኑ በፊት፣ ወይም ኢየሱስ ወደ ህይወቱ ከመምጣቱ በፊት፣ መንፈሱ የሞተ ነው። ኤፌሶን 2፡1 *“በበዳላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ”* ይላል:: ነገር ግን ዳግመኛ ከመወለዳችን በፊትም ቢሆን እንደ አሁኑ በህይወት እንደምንንቀሳቀስ

ግልጽ ነውና ስለዚህ ሙታን ነበራችሁ የሚለው ቃል ስለመንፈሳችን የሚያወራ መሆኑን ልብ እንላለን። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ከሆነ ሞት ማለት መኖር ማቆም ማለት አይደለም። ነገር ግን መለየት ማለት ነው። አንድ ሰው በአካል ሲሞት መኖር ያቆማል ማለት አይደለም ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው ወደ እግዚአብሔር ወይም ወደ ሲኦል ወዲያውኑ ይሄዳል። መንፈሱና ነፍሱ ከሰጋው ተለይተው መኖራቸውን ሲቀጥሉ አሁን ያለው ሰጋው ግን በምድር ይበሰብሳል።

በዘፍጥረት 2፡17 *"ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፣ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና"* የሚለው ቃል በስጋ ሳይሆን በመንፈስ መሆኑን፤ በመንፈስ ከእግዚአብሔር መለየታቸውን ያመለክታል። ያ ህይወትን እና መነቃቃትን የሰጠን፣ የእግዚአብሔር እስትንፋስ የሆነው መንፈሳችን ከልዕለ ተፈጥሮ በላይ ከሆነው የእግዚአብሔር ሕይወት ተለየ ... ቅዱስ ከሆነው የእርሱ ፍጹም ህይወት ... መጽሐፍ ቅዱስ "ዞይ" ከሚለው "ከፍጹምነት ወይም የመትረፍረፍ ህይወት" ተለየ። ከዚህ በኃላ ሰው መበስበስ ጀመረ። አሁንም ይንቀሳቀሳል ይሰራል ነገር ግን የሚሰራው ከእግዚአብሔር ተለይቶ በእራሱ ነበር። በህይወት ለሚያጋጥሙን ችግሮች ሁሉ ምንጩ ይህ ነው ... የሰሜት ውጥረትና ጭንቀቶቻችን ሁሉ ምንጭ ይህ ነው።

ሰው ወደ ክርስቶስ ሲመጣ፣ አዲስ መንፈስ ይሰጠውና "ዳግመኛ" ይወለዳል፣ ይህም ኢየሱስ በዮሐንስ 3፡5 የተጠቀመበት ቃል ነው። ሰው ሲወለድ፣ በአካል፣ መንፈስ ነፍስና ስጋ ኖሮት ይወለዳል፤ ዳግመኛ ሲወለድ ደግሞ የክርስቶስን መንፈስ ይቀበላል። ገላትያ 4፡6 *"ልጆችም ስለ ሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት ብሎ የሚጮኽ የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ"* ይላል። እግዚአብሔር የራሱን መንፈስ እንዲሁ በውስጣችን ያስቀምጣልና አሁን አዲስ ህይወት፣ አዲስ ማንነት፣ ሙሉ በሙሉ በመንፈሳችን ውስጥ አዲስ ሰው ሆነናል ማለት ነው።

ቀሪው የክርስትና ህይወት በመንፈሳችን ውስጥ የሆነውን የተከናወነውን "ማንነት" ነፍሳችን፣ አዕምሮአችን የሚማርበትና የሚለወጥበት ሂደት ነው። ዋናው እውነት ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታ አድርገን በተቀበልን ጊዜ 1/3ኛው አካላችን የዳነ ወይም የተለወጠ መሆኑ ነው። መንፈሳችሁ ሙሉ በሙሉ ተቀይሮአል ከአሁን በኃላ "የዘላለም ህይወት"ን የምትኖሩት በዚሁ በመንፈሳችሁ ነው። መንፈሳችሁ ውስጥ አሁን ፍቅር ደስታና ሰላም እንዲሁም የእግዚአብሔር መገኘት አለ። በመንፈሳችን ጉድለት ወይም ይህ ይቀራል የምንለው ችግር ብሎ ነገር የለም። ነገር ግን ይህ መረዳት ሊኖረን ይገባል ለዚህ ነው የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናትና መማር በክርስትና ሕይወታችን ውስጥ የሚያስፈልገን። ሙሉ በሙሉ አዲስ ሰው ሆናችኃል ነገር ግን ይህ እውቀት ከሌላችሁ መለወጥ አትችሉም። በክርስትና ህይወት ውስጥ በአሸናፊነት ለመውጣት የሚቻለው መንፈስና ህይወት የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል መረዳት ሥንችል ነው። ቃሉ ውስጥ ራሳችሁን ፈልጉና እዩ፣ ማን እንደሆናችሁ እግዚአብሔርም ያደረገላችሁን እዩ፣ በእምነት ተቀበሉ እና እመኑ።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17፣ ማንም በክርስቶስ ቢሆን ምን ይሆናል?

   **2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17** *ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል።*

2. 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17፣ አሮጌዎቹ ነገሮች ምን ሆነዋል?

3. 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17፣ አዲስ የሆኑት ነገሮችስ ምንድን ናቸው?

4. ኤፌሶን 2፡1፣ ዳግመኛ ከመወለዳችሁ ወይም ህይወት ከማግኘታችሁ በፊት ምን ነበራችሁ?

   **ኤፌሶን 2፡1-5** *በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ፤ [2] በእነርሱም፣ በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ፥ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ፥ በፊት ተመላለሳችሁባቸው። [3] በእነዚህም ልጆች መካከል እኛ ሁላችን ደግሞ የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን፣ በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን እንደ ሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን። [4] ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለ ጠጋ ስለ ሆነ፣ [5] ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፥ በጸጋ ድናችኋልና።*

5. ኤፌሶን 2፡2፣ እንደማያምን ሰው እንዴት ትኖሩ ነበር?

6. ኤፌሶን 2፡3-5፣ እግዚአብሔር ባለ ጠጋ (ሃብታም) የሆነው በምንድን ነው?

7. ኤፌሶን 2፡4-5 እግዚአብሔር ለምን ምህረት ሰጠ?

8. ኤፌሶን 2፡5፣ ሙታን በነበርን ጊዜ እግዚአብሔር ምን አደረገልን?

9. ኤፌሶን 2፡5፣ እግዚአብሔር እንዴት ነው ያዳነን?

10. 1ኛ ቆሮንቶስ 6፡9-10፣ ከተዘረዘሩት ውስጥ የሚገናኝ ነገር ይኖራችኋል?

    **1ኛ ቆሮንቶስ 6፡9-10** *ወይስ ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ፤ ሴሰኞች ቢሆን ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ [10] ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።*

11. 1ኛ ቆሮንቶስ 6፡11፣ ይህ ነበራችሁ የሚለው ቃል ያለፈ፣ የአሁን፣ ወይስ ወደ ፊት የሚሆንን ያመለክታል?

    **1ኛ ቆሮንቶስ 6፡11** *ከእናንተም አንዳንዶቹ እንደ እነዚህ ነበራችሁ፤ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፥ ተቀድሳችኋል፥ ጸድቃችኋል።*

12. 1ኛ ሮንቶስ 6፡11፣ ዳግመኛ ስትወለዱ የሚሆኑላችሁ ሶስት ነገሮች ምንድን ናቸው?

13. 1ኛ ቆሮንቶስ 6፡11፣ ይህ ያለፈ፣ የአሁን፣ ወይስ ወደ ፊት የሚሆን ነው?

14. 1ኛ ቆሮንቶስ 6፡17፣ ከጌታ ጋር የሚተባበር ግን ...? ነው።

**1ኛ ቆሮንቶስ 6፡17** *ከጌታ ጋር የሚተባበር ግን አንድ መንፈስ ነው።*

# ጠቋሚ መልሶች

1. 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17፣ ማንም በክርስቶስ ቢሆን ምን ይሆናል?
   **አዲስ ፍጥረት።**

2. 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17፣ አሮጌዎቹ ነገሮች ምን ሆነዋል?
   **አልፈዋል።**

3. 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17፣ አዲስ የሆኑት ነገሮችስ ምንድን ናቸው?
   **ሁሉም ነገር።**

4. ኤፌሶን 2፡1፣ ዳግመኛ ከመወለዳችሁ ወይም ህይወት ከማግኘታችሁ በፊት ምን ነበራችሁ?
   **በበደሌ እና በኃጢአቴ ሙት ነበርኩ።**

5. ኤፌሶን 2፡2፣ እንደማያምን ሰው እንዴት ትኖሩ ነበር?
   **በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ፣ የዲያብሎስን (በአየር ላይ ስልጣን እንዳለው አለቃ) ፈቃድ፣ ባለመታዘዝ መንፈስ እኖር ነበር።**

6. ኤፌሶን 2፡3-5፣ እግዚአብሔር ባለ ጠጋ (ሃብታም) የሆነው በምንድን ነው?
   **በምህረት።**

7. ኤፌሶን 2፡4-5 እግዚአብሔር ለምን ምህረት ሰጠ?
   **ለእኛ ካለው ትልቅ ፍቅር የተነሳ።**

8. ኤፌሶን 2፡5፣ ሙታን በነበርን ጊዜ እግዚአብሔር ምን አደረገልን?
   **ከክርስቶስ ጋር ሕይወትን ሰጠን።**

9. ኤፌሶን 2፡5፣ እግዚአብሔር እንዴት ነው ያዳነን?
   **በጸጋው።**

10. 1ኛ ቆሮንቶስ 6፡9-10፣ ከተዘረዘሩት ውስጥ የሚገናኝ ነገር ይኖራችኃል?
    **አዎ።**

11. 1ኛ ቆሮንቶስ 6፡11፣ ይህ ነበራችሁ የሚለው ቃል ያለፈ፣ የአሁን፣ ወይስ ወደ ፊት የሚሆንን ያመለክታል?
    **ያለፈ።**

12. 1ኛ ሮንቶስ 6፡11፣ ዳግመኛ ስትወለዱ የሚሆኑላችሁ ሶስት ነገሮች ምንድን ናቸው?
    **ታጥባችኃል፣ ተቀድሳችኃል፣ ጸድቃችኃል።**

13. 1ኛ ቆሮንቶስ 6፡11፣ ይህ ያለፈ፣ የአሁን፣ ወይስ ወደ ፊት የሚሆን ነው?
    **የአሁኑ።**

14. 1ኛ ቆሮንቶስ 6፡17፣ ከጌታ ጋር የሚተባበር ግን ...? ነው።
    **አንድ መንፈስ ነው።**

# ትምህርት 10

# በክርስቶስ የሆነ ማንነት - ክፍል 2

## በአንድሩ ዉማክ

ባለፈው ትምህርታችን፣ ዳግመኛ መወለድ ምን ማለት እንደሆነ፣ በመንፈሳችንም ልባችን መቀየሩን አውርተን ነበር። 2ኛ ቆሮ 5፡17 *“ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው አሮጌው ነገር አልፎአል እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል”* የሚለውንም ቃል ተጠቅመን ይህንን እውነት ለመረዳት ሞክረን ነበር። ዳግመኛ ስንወለድ በመንፈሳችን ሙሉ በሙሉ ለውጥ ተከናውኗል፣ ይህን መረዳት የምንችልበት መንገድ ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል መሆኑን አይተናል። ይህን በውጫዊ ነገሮች መገንዘብ አንችልም፣ በነፍሳችን ክፍል በስሜታችንም ልንረዳው የምንችለው አይደለም። ነገር ግን በመንፈሳችን በኩል ሙሉ በሙሉ ለውጥ ተፈጽሟል።

ሰዎች ኢየሱስን ወደ ህይወታቸው ሲጋብዙ ወይም ኢየሱስን አዳኝ አድርገው ሲቀበሉ የሚሆኑላቸውን አዳዲስ ነገሮች የሚያሳዩንን ጥቂት ጥቅሶችን ልጠቀም። ኤፌሶን 4፡24 *“እውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱት”* ይላል። ሰው ዳግመኛ ሲወለድ፣ መንፈሱ ጻድቅ፣ በእውነትም ቅዱስ ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ ሁለት አይነት ጽድቅ እንዳለ ይናገራል።

በራሳችሁ ስርታችሁ የምታገኙት ጽድቅ አለ፣ ይህንንም ከሰዎች ጋር ባላችሁ ግንኙነት ልትጠቀሙበት የሚገባ ነው። በአግባቡ ካልኖራችሁና ስራችሁን በአግባቡ ካላከናወናችሁ አለቃችሁ ሊያባርራቸሁ የትዳር አጋራችሁም ፍች ሊፈጽሙባችሁ ይችላሉ፤ ስለዚህ የግድ የራሳችን ጽድቅ ያስፈልገናል ማለት ነው። እግዚአብሔር ግን በውጫዊው ጽድቃችሁ ወይም በሌላ አነጋገር በእናንተ የጽድቅ ስራ ፈጽሞ አይቀበላችሁም። እግዚአብሔር የእራሱን ጽድቅ እንዲሁ ሠጥቶአችኋል።

በ2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21 እኛ በእርሱ የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ እግዚአብሔር አብ ልጁን ስለእኛ ኃጢአት አደረገው ይላል። ስለዚህ ከእኛ የጽድቅ ሥራ ያለፈና እጅግ የላቀ እግዚአብሔር ለእኛ የሰራው የእግዚአብሔር ጽድቅ አለ። ይህ የእግዚአብሔር ጽድቅ በክርስቶስ በማመን እንዲሁ የሚገኝ ጽድቅ ነው። ይህንን ጽድቅ እንዲሁ ስንቀበል ጻድቅ፣ እውነተኛና ቅዱስ ሆነን ተፈጥረናል። ወደ ጽድቅ እያደግን ወይም በኛ በኩል እያሻሻልን የምንሔደው ነገር የለም ወዲያውኑ ጻድቅ ሆነናል። በቀላል አገላለጽ በእግዚአብሔር ቀኝ ቆመናል።

እግዚአብሔር በሌላ በምንም ሳይሆን በክርስቶስ ምክንያት በእኛ ደስተኛ ነው። ለውጥ የተከናወነው በመንፈሶቻችን ነው። በጽድቅና እውነተኛ ቅድስና አዲስ ፍጥረት ሆነን ተፈጥረናልና ፍጹም አዲስ ፍጥረት ነን። ኤፌሶን 2፡10 *“እኛ ፍጥረቱ ነንና፣ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን”* ይላል። አሁን በመንፈሳችን ሙሉና ፍጹም ሆነናል፤ ኃጢአት ወይም ችግር የሚባል ነገር የለም። አዲስ ፍጥረት ሆነናል። ይህንን ኤፌሶን 1፡13 *“እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ በተሰፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ”* ሲል ያረጋግጥልናል።

አንዳንድ ሰዎች “አዎ መጀመሪያ ባመንኩ ጊዜ ይቅር እንደተባልኩና እንደነጻሁ አውቃለሁ። ከዛ በኃላ ግን ሰንት ኃጢአት ሰርቻለሁ፣ እግዚአብሔርንም አስቀይሜዋለሁ” የምትሉ ትኖራላችሁ። ሆኖም ከወደቃችሁም ውድቀታችሁ በሰራችሁ፣ በአእምሮአችሁና በስሜታችሁ ክፍል እንጅ መንፈሳችሁ ኃጢአት አይሰራም፤ ልክ ሴቶች ፍራፍሬዎችን በጠርሙስ ውስጥ አድርገው በተኅዋሲያን ሳይበላሽ ረጅም ጊዜ እንዲቆይ ኮምጣጤ ወይም ሌላ መከላከያ ፈሳሽ ጨምረው እንደደሚያሸጉት አይነት - መንፈሳችን ታሽጓል። ዳግመኛ ስትወለዱ አዲስ መንፈስ ተቀብላችኃል፣ እግዚአብሔር አትሟችኃልና ኃጢአት መንፈሳችሁን መድረስ አይችልም። አዲስ ማንነት

አግኝታችኃል። ስለዚህ ከእግዚአብሔር ጋር ያላችሁ ማንኛውም ግንኙነት አምልኮና ወዳጅነት ሊሆን የሚገባው በመንፈስ ማንነታችሁ እንጅ በስጋችሁ አይደለም።

በክርስትና ህይወት ውስጥ የምናገኘው ትልቁ ለውጥ ሰዎች ማንነታቸው መለወጡ ወይም መቀየሩ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖራችሁ ግንኙነት በስሜታችሁ ወይም በሚታየውና በሚዳሰሰው ሳይሆን እርሱ በሰራላችሁ ስራ በመንፈስ ባገኛችሁት አዲስ ማንነት ሊሆን ይገባል። ይህም የተፈጸመ ሥራ ነው፣ ይህ የእግዚአብሔር ሥራ አይዋዥቅም (ወደ ፊት እና ወደ ኃላ አይለዋወጥም)። በጽድቅ እና እውነተኛ ቅድስና ተፈጥራችኃል። ይህም የመንፈሳችሁ ክፍል ነው። ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖራችሁ ግንኙነት እግዚአብሔርን በመንፈስ እና በእውነት ማምለክ ይኖርባችኃል። በክርስቶስ በሆነው ማንነታችሁ ጸንታችሁ ቁሙ።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. 1ኛ ቆሮንቶስ 6፡17 አንብቡ፣ ሙሉ ለውጥ የተከናወነው መንፈሳችን ላይ እንደሆነ የምንረዳው በእግዚአብሔር ቃል ነው። ይህ ጥቅስ ምን ሆናችሁ ይላል?

    **1ኛ ቆሮንቶስ 6፡17** *ከጌታ ጋር የሚተባበር ግን አንድ መንፈስ ነው።*

2. ኤፌሶን 3፡17 አንብቡና ክርስቶስ አሁን የት ይኖራል?

    **ኤፌሶን 3፡17** *በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነክሩ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ ባለ ጠግነት መጠን ይሰጣችሁ፤ የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ።*

3. ኤፌሶን 3፡17 ይህ እንዴት ሆነ?

4. 1ኛ ዮሐንስ 5፡12 ለመዳን ማን ሊኖረን ይገባል?

    **1ኛ ዮሐንስ 5፡12** *እግዚአብሔርን ማንም ከቶ አላየውም፣ እርስ በርሳችን ብንዋደድ እግዚአብሔር በእኛ ይኖራል፣ ፍቅሩም በእኛ ፍጹም ሆኖአል።*

5. ቆላስያስ 1፡26-27 ከዘላለምና ከትውልዶች ተደብቆ የነበረው፣ አሁን ግን የታወቀው ምስጢር ምንድን ነው?

    **ቆላስያስ 1፡26-27** *ይህም ቃል ከዘላለምና ከትውልዶች ጀምሮ ተሰውሮ የነበረ ምሥጢር ነው፥ አሁን ግን ለቅዱሳኑ ተገልጦአል። [27] ለእነርሱም እግዚአብሔር በአሕዛብ ዘንድ ያለው የዚህ ምሥጢር ክብር ባለ ጠግነት ምን እንደ ሆነ ሊያስታውቅ ወደደ።*

6. ኤፌሶን 4፡23-24 በጽድቅና እውነተኛ ቅድሰና የተፈጠረው ምንድን ነው?

    **ኤፌሶን 4፡23-24** *በአእምሮአችሁም መንፈስ ታደሱ [24] ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድሰና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ።*

7. 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21 የማንን ጽድቅ ይዘናል?

    **2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21** *እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው።*

8. ኤፌሶን 1፡4 አማኝ በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ነው የሚቆመው?

    **ኤፌሶን 1፡4** *ዓለም ሳይፈጠር፥ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን።*

9. ኤፌሶን 1፡6 እንዴት ነው ተቀባይነት ያገኘነው?

    **ኤፌሶን 1፡6** *በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ይህን አደረገ።*

# ጠቋሚ መልሶች

1. 1ኛ ቆሮ 6፡17 አንብቡ፣ ሙሉ ለውጥ የተከናወነው መንፈሳችን ላይ እንደሆነ የምንረዳው በእግዚአብሔር ቃል ነው። ይህ ጥቅስ ምን ሆናችሁ ይላል?
   **መንፈሶቻችን ከጌታ ጋር አንድ ሆነዋል።**

2. ኤፌሶን 3፡17 አንብቡና ክርስቶስ አሁን የት ይኖራል?
   **በልባችን።**

3. ኤፌሶን 3፡17 ይህ እንዴት ሆነ?
   **በእምነት።**

4. 1ኛ ዮሐንስ 5፡12 ለመዳን ማን ሊኖረን ይገባል?
   **ወልድ (ኢየሱስ ክርስቶስ)።**

5. ቆላስያስ 1፡26-27 ከዘላለምና ከትውልዶች ተደብቆ የነበረው፣ አሁን ግን የታወቀው ምስጢር ምንድን ነው?
   **የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በእኛ ዘንድ መሆኑ ነው።**

6. ኤፌሶን 4፡23-24 በጽድቅና እውነተኛ ቅድስና የተፈጠረው ምንድን ነው?
   **የእኛ አዲሱ ሰው (ዳግመኛ የተወለደው መንፈሳችን)።**

7. 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21 የማንን ጽድቅ ይዘናል?
   **በክርስቶስ የእግዚአብሔርን ጽድቅ።**

8. (ኤፌ 1፡4) አማኝ በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ነው የሚቆመው?
   **ቅዱስ፣ ነውር የሌለው።**

9. (ኤፌ 1፡6) እንዴት ነው ተቀባይነት ያገኘነው?
   **በውዱ (በኢየሱስ ክርስቶስ)።**

## ትምህርት 11

# ክርስቲያን ኃጢአት ሲሰራ ምን ይሆናል?

## በዶን ክሮው

ዛሬ ደግሞ "ክርስቲያን ኃጢአት ሲሰራ ምን ይሆናል?" የሚለውን ርዕሰ እናያለን። መጽሐፍ ቅዱስ በ1ኛ የሐንስ 1:8-9 እንዲህ ይላል - *"ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን እውነትም በእኛ ውስጥ የለም። በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነፃን የታመነና ጻድቅ ነው።"* እንደ ክርስቲያን እንቅፋት ሊገጥመን፣ ኃጢአትም ልንሰራ እንችላለን። ቀድሞ ከማመናችን በፊት ከነበርንበት ሁኔታ የሚለየን ነገር ቢኖር አሁን አዲስ ተፈጥሮ ያለን መሆኑ ነው፤ ኃጢአትን ማድረግ ያሳቅቀናል፣ ሐዘን ይሆንብናል። ኃጢአት መሥራት አንፈልግም፣ የጽድቅ ህይወት መኖር እንፈልጋለን። ነገር ግን ኃጢአት ብንሰራ ምን እንሆናለን? እንደገና መዳን ያስፈልገናል? መጽሐፍ ቅዱስስ ይህን ያስተምራል? በዚህ ዓይነት ምንም ዋሰትና የለንም ማለት ነው፤ እንዲያውም በዓለም ካሉት ይልቅ ኪሳራ በሆነብን ነበር። ምክንያቱም በዓለም ያሉት በህይወታቸው ስለ ኃጢአት የሚወቅሰ ህሊና የላቸውምና። እንደ አማኝ ኃጢአት የእኛ ዋና ትኩረት ሊሆን አይገባም። በዕብራውያን 10፡2 አገላለጽ በኢየሱስ መስዋዕትነት አማካኝነት አማኞች ምንም ዓይነት የኃጢአት እውቀት የላቸውም። በሌላ አነጋገር የህይወት ትኩረታችን ኃጢአት ሊሆን አይገባም፤ ትኩረታችን እግዚአብሔር ሊሆን ይገባል።

ሮሜ 4፡2 – *"አብርሃም በሥራ ጸድቆ (ጻድቅ ተብሎ) ቢሆን የሚመካበት አለውና፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ዘንድ አይደለም"* ይላል (ቅንፍ ከራሴ ነው)። መዳን በሰራችን፣ በምግባራችን ወይም በጥረታችን ቢሆንስ ኖሮ በራሳችን በተመካንና በሥራችን በተመጻደቅን ለዘላለም ስንኖርም በኩራት - "ጌታ ሆይ አንተ በመስቀል ላይ ስራ እንደሰራህ አውቃለሁ፣ እኔ የሰራሁት ስራ ደግሞ የሚደንቅ ነው" እንል ነበር። ነገር ግን አይደለም። እግዚአብሔር መዳንን በልጁ በኢየሱስ በማመን አድርጎታልና ልንኮራበት የሚያስችለን ሥራ ምንም የለንም። ኩራትም ሆነ ትምክህት በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው (ሮሜ 3፡27)። "የዘላለም ህይወት ስጦታ" ስጦታ ነውና በኛ ልፋት የሚገኝ አይደለም (ሮሜ 6፡23)።

ሮሜ 4፡2 አብርሃም በሥራ ጸድቆ ቢሆን ኖሮ የሚመካበት አለው ይላል ነገር ግን እንደዛ አይደለም። ስለዚህ እንደ እግዚአብሔር ቃል፣ ሰው የሚድነው በምንድን ነው? በየቀኑ በሚያስመዘግበው መልካም ውጤት? በሥራው? በምግባሩ? አብርሃም ጽድቅ ሆኖ የተቆጠረለት በምንድን ነው? በመልካምነቱ ነው? ወይስ እንዲሁ እምነቱን በእግዚአብሔር ላይ በመጣልና በእግዚአብሔር በማመን ነው? መጽሐፍ ቅዱስ በሮሜ 4፡3 – *"አብርሃምም አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት"* ይላል።

ታዲያ እኔን አሁን ያጸናኝና ያቆመኝ፣ ብሳሳትም፣ ኃጢአት ብሰራም፣ እንዳልጠፋ የሚጠብቀኝ ምንድን ነው? ይህ የሆነው ኢየሱስ በመስቀል ላይ ኃጢአቴን እንደወሰደልኝና እንዳስወገደልኝ (እንጅ በራሴ ሥራ እንዳልሆነ) በማመንና በእርሱም ያለኝ እምነት በእግዚአብሔር ፊት ጽድቅ ሆኖ እንደተቆጠረልኝ በማመን ነው።

ሮሜ 4፡6 – *"እንደዚህ ዳዊት ደግሞ እግዚአብሔር ያለሥራ ጽድቅን ስለሚቆጥረለት ስለሰው ብጽዕና ይናገራል"* ይላል። ዳዊት በብሉይ ኪዳን ዘመን ሆኖ እግዚአብሔር በአዲስ ኪዳን፣ ያለ ሰው ሥራ ጽድቅን የሚቆጥርበት ዘመን ይመጣል ሲል ተናገረ። በቁጥር 7 እንዲህ አለ - *"ዓመጻቸው የተሰረየላቸው፣ ኃጢአታቸውም የተከደነላቸው ብጹዓን ናቸው"* ማሰሪያው ደግሞ ቀጣዩ ቃል ነው፤ *"ጌታ ኃጢአቱን የማይቆጥርበት ሰው ብፁዕ ነው* (ሮሜ 4፡8)። አንዳንዴ የሚቆጠርበት፣ አንዳንዴም ምናልባት የማይቆጠርበት አይልም። "ጌታ ኃጢአቱን የማይቆጥርበት ሰው ብፁዕ ነው" ይላል። አንዳንድ ጊዜ ወይም አልፎ አልፎ የማይቆጥርበት አይደለም። ነገር ግን እንዲሁ "የማይቆጥርበት" ይላልና መቼም በምንም ሁኔታ እንደማይቆጥርበት እንገነዘባለን። የአዲስ ኪዳን የምስራች ይህ ነው። ዕብራውያን 10፡16 – *"በልባቸው ህጌን አኖራለሁ በልቡናቸውም እጽፈዋለሁ"* ይላል።

የዚህ ጽሁፍ ሥምምነት ቀሪው ክፍልም በቁጥር 17 እንደዚህ ይላል፡- *"ኃጢአታቸውንና ዓመፃቸውንም ደግሜ አላስብም"።*

ኃጢአት ሰርታችሁ ለንስሐ እንኳን ጊዜ ባላገኛችሁበት ሁኔታ ውስጥ ብትሆኑ እንኳን በጽድቅ በእግዚአብሔር ቀኝ እንድትቆሙ የሚያደርጋችሁ በምን ሁኔታ ይመስላችኃል? አዎ! በኢየሱስ ክርስቶስ ባላችሁ እምነት ነው። ሰሙ ኢየሱስ ነው እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋል (ማቴዎስ 1፡21)።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ሮሜ 4፡5 እንብቡና እግዚአብሔር ... ? አይነት ሰዎችን ያጸድቃል።

   **ሮሜ 4፡5** *“ነገር ግን ለማይሠራ፥ ኃጢአተኛውንም በሚያደድቅ ለሚያምን ሰው እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቆጠርለታል”።*

2. ምንድን ነው የተቆጠረለትብሔር ድሮ አብርሃም ያልነበረውን አንድ ነገር በማመኑ ቆጥሮለታል። ምንድን ነው የተቆጠረለት?

   **ሮሜ 4:2-3** *እብርሃም በሥራ ጸድቆ ቢሆን የሚመካበት አለውና፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ዘንድ አይደለም። [3] መጽሐፍሰ ምን አለ? አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት”።*

3. ሮሜ 4፡6 እንደ አብርሃም ብናምን እግዚአብሔር ምን ይቆጥርልናል?

   **ሮሜ 4:6** *እንደዚህ ዳዊት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ሥራ ጽድቅን ስለሚቆጥርለት ስለ ሰው ብፅዕና ይናገራል እንዲህ ሲል።*

4. ሮሜ 4፡6 እግዚአብሔር ለአንድ ሰው ጽድቅን የሚቆጥርለት፡
   1] እንደ ሥራው።
   2] ከሥራው ውጭ።
   3] እንደ መልካምነታቸው።

5. ዕብራውያን 10፡14 ላመኑ እግዚአብሔር ጽድቅን ለምን ያህል ጊዜ ይቆጥርላቸዋል?

   **ዕብራውያን 10፡14** *አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጎአቸዋልና።*

6. ሮሜ 5፡17 ጽድቅ የምንቀበለው፣

   1] በልፋታችን።
   2] በስጦታ።
   3] ስርተን።

   **ሮሜ 5፡17** *በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ፥ ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ።*

7. ስጦታ የሚለው ቃል ምን ያመለክታል?

8. ኢየሱስን የግል አዳኝ በማድረጋችሁ፣ እስከመጨረሻው የት እንደሚያደርሳችሁ ታምናላችሁ፣

   1] ቤተ ክርስቲያን።
   2] ሰማይ።
   3] ሩሲያ።

# ጠቋሚ መልሶች

1. ሮሜ 4፡5 እንብቡና እግዚአብሔር ...? አይነት ሰዎችን ያጸድቃል?
   **ኃጢአተኞችን።**

2. ሮሜ 4፡2-3 እግዚአብሔር ድሮ አብርሃም ያልነበረውን አንድ ነገር በማመኑ ቆጥሮለታል። ምንድነው የቆጠረለት?
   **ጽድቅ ወይም በእግዚአብሔር ቀኝ የሚቆምበትን።**

3. ሮሜ 4፡6 እንደ አብርሃም ብናምን እግዚአብሔር ምን ይቆጥርልናል?
   **ጽድቅ ወይም በእግዚአብሔር ቀኝ የምንቆምበትን።**

4. ሮሜ 4፡6 አግዚአብሔር ለአንድ ሰው ጽድቅን የሚቆጥርለት፡-
   **2] ከሥራው ውጭ።**

5. ዕብራውያን 10፡14 ላመኑ እግዚአብሔር ጽድቅን ለምን ያህል ጊዜ ይቆጥርላቸዋል?
   **ለዘላለም።**

6. ሮሜ 5፡17 ጽድቅ የምንቀበለው፣
   **2] በስጦታ።**

7. ስጦታ የሚለው ቃል ምን ያመለክታል?
   **በነጻ የተሰጠን ነገር፣ ለተቀባዩ ምንም ወጭ የማያሰወጣን።**

8. ኢየሱስን የግል አዳኝ በማድረጋችሁ፣ እስከመጨረሻው የት እንደሚያደርሳችሁ ታምናላችሁ፣
   **2] ሰማይ።**

# ትምህርት 12

# የእግዚአብሔር ቃል ሐቀኛነት

## በአንድሩ ዉማክ

የማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 4 የእግዚአብሔርን ቃል ሐቀኛነት እና ሙሉነት፣ ሃይሉን፣ ውስጡ ያለውን እምነት የሚያሳይ ድንቅ ምዕራፍ ነው። በዚህች አንድ ቀን ውስጥ ከአስር ያላነሱ ምሳሌዎችን ያስተማረ ሲሆን ሁሉንም ለማየት ማርቆስ (4)ን ከማቴዎስ 13 እና ሉቃስ 8 ጋር ማነፃፀር ያስፈልጋል። ከምሳሌዎቹ መካከል አንዱ "የዘሪው ምሳሌ" ሲሆን ማርቆስ 4፡26 እንዲህ ይላል፡- *"እርሱም አለ። በምድር ዘርን እንደሚዘራ ሰው የእግዚአብሔር መንግሰት እንደዚህ ናት"።* ቀደም ሲል በቁጥር 14 ዘሩ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ የነገረንን እናስታውሳለን። እግዚአብሔር ስለ እርሻ ሊያስተምረን ወይም ስለ ግብርና እየነገረን ሳይሆን ይልቁንም መንፈሳዊውን እውነት በዚህ አለም በምናውቀው ነገር፤ ሰዎች ሁሉ በሚያውቁትና ዘወትር በሚኖሩበት ሙያ፣ በሚገባን ግልጽና ቀላል ምሳሌ ያስረዳናል። ቁጥር 27 እንዲህ ይላል - *"ሌሊትና ቀን ይነሳልም እርሱም እንዴት እንደሚሆን ሳያውቅ ዘሩ ይበቅላል፣ ያድግማል"* አሁን ይህ እንደሚያስፈልገን እምናለሁ። ገበሬው ወይም ዘሪው በትክክል መረዳት አይችልም ይላል። ይህ እንዴት እንደሚሆን የሚያውቀው ነገር የለም።

አንዳንድ ሰዎች "የምትለው ነገር አይገባኝም፣ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ብቻ እንዴት የእግዚአብሔር ቃል ሊለውጠኝና የራሱን ህይወት ሊሰጠኝ ይችላል?" ብለው ይጠይቃሉ። እኔም እንዴት የሚለውን አላውቅም። ነገር ግን እንደሚሰራ አውቃለሁ። እንዲት የበቆሎ ዘር መሬት ውስጥ ተቀብራ፣ እንዴት በቅላ፣ መጀመሪያ ቡቃያ ከዛም የበቆሎ ራስ፣ በመጨረሻም ሙሉ ሰብል እንደምትሆን ማንም አያውቅም፤ ነገር ግን ሆኖ አይተናል፣ ዘርተን ምርት እያፈሰን ነው፣ አሁንም። እንደዚሁ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል በማንበብ ልባችንን እንዲሞላ ስናደርግ ማንነታችንን፣ ልማዳችንን፣ አስተሳሰባችንን ይቀይራል።

ቁጥር 28 *"ምድሪቱም አውቃ በመጀመሪያ ቡቃያ፣ ኃላም ዛላ፣ ኃላም በዛላው ፍጹም ሰብል ታፈራለች"*። ምድር ዘር ተቀብላ፣ አብቅላ ህይወት እንድትሰጥ ሆና ነው የተሰራችው። እንዲሁ በተመሳሳይ ልባችንም የተሰራው ለእግዚአብሔር ቃል ነው። የእግዚአብሔር ቃል በልባችን እንዲቀመጥ ሆኖ ተሰርቷል። መጽሐፍ ቅዱሳችን ሸጉጠን በመያዝ፣ የቡና ጠረጴዛችን ላይ በማስቀመጥ ወይም ተሸክመን በመዞር የሚመጣ ለውጥ የለም። ለህይወት የሚያስፈልጋችሁን ሃይል አይሰጣችሁም። ነገር ግን ቃሉን ወሰደን ዘር ልናደርገውና ልባችን ውስጥ ልንተክለው ይገባል። ይህን ስናደርግ ልባችን ፍሬ ሊያፈራ የተዘጋጀ፣ የተሰራ፣ የተፈጠረ ነውና በእራሱ ፍሬ ያፈራል። ወዲያውኑ ነገሮች በህይወታችን ሙሉ በሙሉ እንዲቀየሩ ያደርጋል። ቃሉ በመቀጠል - *"በመጀመሪያ ቡቃያ፣ ኃላም ዛላ ኃላም በዛላው ፍጹም ሰብል"* ይላል። ይህ የሚያሳየን ዘሩ ለማፍራት ብሎም ለመብሰል የሚያልፍባቸውን ደረጃዎች ነው። ብዙ ጊዜ ሰዎች ወደ እኔ ይመጡና እግዚአብሔር አንድ መልካም ነገር እንደሚያደርግላቸው እንደሚያምኑ ይገልጹሉኛል፣ መልካሙን ነገር እኔም የምስማማበት ዓይነት ቢሆንም ነገር ግን ምንም ሥራ ሰርተው የማያውቁ ከሆነ፣ አንድም ሰው እንኳን ወደ ጌታ ያላመጡ ሰዎች ከሆኑ በቀጣዮቹ ሳምንታት የቴሌቪዥን ወይም የሬዲዮ የወንጌል አገልግሎት ሊኖራቸው እንደማይችል አረጋግጥላችኃለሁ።

ነገሮችን ደረጃ በደረጃ መሰራት ይኖርባችኃል። ከእግዚአብሔር የምንቀበልባቸው ደረጃዎች እንዳሉ ምሳሌው ያስረዳል። በቅድሚያ መጀመር አለብን፤ ከዛም ተስፋ ማድረግ፤ በመቀጠልም እምነት፣ ከዚህም በኃላ ውጤት እናያለን። ሁሌም ወደ ድል አድራጊነት ለመድረስ የምንጓዝባቸው መንገዶችና የምናሳልፋቸው ደረጃዎች አሉ። ማንም ከዜሮ ተነስቶ አንድ ሽህ ኪሎሜትር ላይ አይደርስም። የእግዚአብሔርን ቃል በሙሉ በአንዴ ለማወቅ ቅናት ቢኖረንም እንኳ እንደዚህ ግን አይሰራም። የእግዚአብሔር ቃል እንደ ዘር የሚሰራ መሆኑን ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ያስተምረናል። ቃሉ በልባችን ተዘርቶ መብቀልና ደረጃ በደረጃ ማደግ ይኖርበታል፤ መጀመሪያ ቡቃያ፣ ኃላም ዛላ፣ ኃላም በዘላው ሠብል። በመቀጠል ቃሉ እንዲህ ይላል -

*“ፍሬ ግን ሲበሰል መከር ደርሶአልና ወዲያውኑ ማጭድ ይልካል”*፡፡ ደረጃዎቹ ይኑሩ እንጅ በመጨረሻ ፍሬያማና ምርታማ የምንሆንበት ጊዜ እንዳለ እንረዳለን፡፡

አሁን የምሳሌውን ማጠቃለያ በቁጥር 35 እንመልከት፡፡ *“በዚያም ቀን በመሸ ጊዜ ወደ ማዶ እንሻገር አላቸው”*፡፡ እስተውሉ ቀኑን ሙሉ ኢየሱስ ስለ ቃሉ ሃይል እንደ ዘር መሆኑን የእግዚአብሔር የሆነው ህይወት ወደ ህይወታችን እንዴት እንደሚመጣ ከአስር በማያንሱ ምሳሌዎች ካስተማራቸው በኃላ ቀላል ሙከራ ሰጣቸው “ወደ ማዶ እንሻገር አላቸው”፡፡ “ጀልባ ውስጥ እንግባና ሐይቁ መካከል ድረስ ሄደን እንስምጣለን” አላላቸውም ነገር ግን “ወደ ማዶ እንሻገር” አላቸው፡፡ ይህንን ብሎም ጀልባ ውስጥ ገብቶ ተኛ፡፡ ታሪኩ ሲቀጥል ከባድ ማዕበል እንደተነሳ እና ጀልባዋንም ውሃ እንደሞላት ይናገራል፡፡ ይህች ጀልባ ከታች ኢየሱስ ርጥበት ሳይነካው የሚተኛበት የውስጥ ክፍልፋዩችና እላይ የመቆጣጠሪያ ደርዝ ያላት ዘመናዊ የመንገደኛ ጀልባ እንዳልሆነች ልብ በሉ፡፡ ክፍት ጀልባ ናትና ጀልባዋ በተናጠች ቁጥር ኢየሱስም በውሃ እየራሰ ነበር፡፡ ይህን ማወቅ የሚያስፈልገን ኢየሱስ እየሆነ ያለውን ነገር ያውቅ እንደነበር እያወቀም ቢሆን መተኛት ይፈልግ እንደነበር ለማስረዳት ነው፡፡ ደቀ መዛሙርቱ ግን ተበሳጭተው ወደ እርሱ መጡና እንዲህ አሉ “ጌታ ሆይ ስንጠፋ አይገድህምን?” በሌላ አነጋገር - አንድ ነገር አድርግ፣ እቃ ያዝና ውሃውን ወደ ውጭ ቅዳ፣ ወይም ቅዘፍ፣ ብቻ አንድ ነገር አድርግ እንደማለት ነበር፡፡

ብዙ ጊዜ፣ በዚህ ዘመንም ቢሆን ሰዎች በተመሳሳይ - “እግዚአብሔር ሆይ ለምን አንድ ነገር አላደረግክም?” ይላሉ፡፡ እግዚአብሔር አንድ ነገር አድርጓል እርሱም የሚያስፈልገንን ሁሉ በልጁ በጌታ በኢየሱስ ቤዛነት በኩል መስጠቱ ነው፤ ቃሉን ልኮ የሚያስፈልገንን ዘር ሁሉ እንዲያው ሰጥቶናል፡፡ ዘሩን ወስደን በልባችን መዝራት የእኛ ድርሻ ነው፡፡ እርሱ ቃሉን ሰጥቶናል፣ ቃሉ ዘር ሆኖ በልባችን ውስጥ እንዲበቅል ደጋግመን በጥሞና በማንበብና በማሰላሰል ህይወት ሆኖ እንዲገለጥ መስራት የእኛ ኃላፊነት ነው፡፡ ደቀ መዛሙርቱ ግን ኢየሱስን ቀስቅሰው “አንድ ነገር አድርግ” አሉት፣ እርሱም ተነሳና ነፋሱንና ወጀቡን ገስጸው ታላቅ ጸጥታም ሆነ፡፡ እነርሱንም “ለምን እነደዚህ ፈራችሁ፣ እንዴትስ እምነት የላችሁም?” አላቸው እንጅ “ኀበዝ ይቅርታ አንድ ነገር ማድረግ ነበረብኝ” አላላቸውም ሙከራውን ወድቀዋልና፡፡ የእርሱ ድርሻ ቃሉን ማስተማርና በቃሉ መሰረት የተሰጣቸውን ተሰፋ መግለጥ ነው፡፡ የእነርሱ ድርሻ ደግሞ ቃሉን ወሰደው የተሰጣቸውን ተሰፋ ማመን ነው፡፡ እግዚአብሔር ኢየሱስን ወደ ምድር ሲልከው የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ አሟልቶ ነው፡፡ በምድር ላይ በየትኛውም መሰክ የተከናወነ ህይወት ይኖራችሁ ዘንድ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ዘር አድርጎ በቃሉ በኩል ልኳል፡፡ ማድረግ ያለባችሁ ደጋግሞ በእርጋታ በማንበብ በማሰላሰልና በማሰተዋል፣ በመረዳት የቃሉን ዘር በልባችሁ ውስጥ ስር ሰዶ እንዲያድግ ማድረግ ነው፡፡ ይህን ስታደርጉ፣ በህይወታችሁ ማዕበልና ወጀቡን ጸጥ እንዲል የምታደርጉበትን ሃይል ታገኛላችሁ፡፡

በእኔ እምነት እግዚአብሔር የሚፈልገው ደቀ መዛሙርቱ በዛች ቀን ያስተማራቸውን ትምህርት አስታውሰው “በቃ ወዳ ማዶ እንሻገር” እንዲሉ ነበር፡፡ እንዲህ ማለት ይችሉ ነበር - “እርሱ ዛሬ እንዳስተማረን ይህ የተሰፋ ቃል ነው፡፡ እርሱም አለማትን የፈጠረ ነውና ወደ ማዶ እንሻገር ነው እንጅ መሃል ላይ ደርሳችሁ በወጀብ ትጠፋላችሁ አላለንም” ብለው ይህን ቃል በመውሰድ በእምነት ቃል ማዕበልና ወጀቡን በእምነት መገሰጽ ነበረባቸው፡፡ ኢየሱስ በቀጥታ የተናገረው ይህንን ነው - “አንተ እምነት የጎደለህ ለምን ትጠራጠራለህ?” ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ - የእግዚአብሔርን ቃል አምነን በእምነት መፈጸም አለብን፡፡

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ማቴዎስ 13:19 - ቃሉን በማስተዋል በልባችን ካልተከልን፣ ቃሉ ምን ይሆናል?

   **ማቴዎስ 13:19** *የመንግሥትን ቃል ሰምቶ በማያስተውል ሁሉ፥ ክፉው ይመጣል፥ በልቡ የተዘራውንም ይነጥቃል፤ በመንገድ ዳር የተዘራው ይህ ነው።*

2. ኢያሱ 1:8 - ቃሉን መቼ ወይም በምን ጊዜ ልናስበውና ልናሰላስለው ይገባል?

   **ኢያሱ 1:8** *የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፥ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው፤ የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል ይከናወንልሃልም።*

3. ዮሃንስ 6:63 - በዚህ ቃል መሠረት የእግዚአብሔር ቃል ...? ነው::

   **ዮሐንስ 6:63** *ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው፤ ሥጋ ምንም አይጠቅምም፤ እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው።*

4. ማቴዎስ 4:4 - የሰው ልጅ በእንጀራ ብቻ ሳይሆን በ ...? ሊኖር ይገባል::

   **ማቴዎስ 4:4** *እርሱም መልሶ። ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል አለው።*

5. ኤፌሶን 6:17 - የእግዚአብሔር ቃል ከምን አይነት የጦር መሳሪያ ጋር ይመሳሰላል?

   **ኤፌሶን 6:17** *የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።*

6. ሰይፍ ጠላት ላይ ጉዳት ማድረስ ይችላል?

7. ሮሜ 8:6 - ለእግዚአብሔር ቃል በህይወታችን ትክክለኛውን ቦታ ስንሰጠው ...? ይሆንልናል::

   **ሮሜ 8:6** *ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና፥ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው።*

8. 2 ቆሮንቶስ 3:18 - ትኩረት የሰጠነውና የፈቀድነው ነገር በህይወታችን ይሆናል። ትኩረታችን ምን ላይ ልናደርግ ይገባል?

   **2 ቆሮንቶስ 3:18** *እኛም ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመሰል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን።*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ማቴዎስ 13፡19 ቃሉን በማስተዋል በልባችን ካልተከልን፣ ቃሉ ምን ይሆናል?
   **ክፉው ይመጣል የተዘራውንም ይነጥቃል በህይወታችንም ውጤት እንዳያመጣ ያደርጋል።**

2. ኢያሱ 1፡8 ቃሉን መቸ፣ ወይም በምን ጊዜ ልናሰበውና ልናሰላሰለው ይገባል?
   **በቀን እና በሌሊት።**

3. ዮሃንስ 6፡63 በዚህ ቃል መሠረት የእግዚአብሔር ቃል ...? ነው።
   **መንፈስ እና ሕይወት።**

4. ማቴዎስ 4፡4 የሰው ልጅ በእንጀራ ብቻ ሳይሆን በ ...? ሊኖር ይገባል።
   **ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ቃል ሁሉ።**

5. ኤፌሶን 6፡17 የእግዚአብሔር ቃል ከምን አይነት የጦር መሳሪያ ጋር ይመሳሰላል?
   **ከ ሰይፍ።**

6. ሰይፍ ጠላት ላይ ጉዳት ማድረስ ይችላል?
   **አዎ።**

7. ሮሜ 8፡6 ለእግዚአብሔር ቃል በህይወታችን ትክክለኛውን ቦታ ስንሰጠው ...? ይሆንልናል።
   **ሕይወት እና ሰላም።**

8. 2 ቆሮ 3፡18 ትኩረት የሰጠነውና የፈቀድነው ነገር በህይወታችን ይሆናል። ትኩረታችን ምን ላይ ልናደርግ ይገባል?
   **ጌታን እና ክብሩን።**

## ትምህርት 13

# እግዚአብሔር በክፉ ተጠያቂ አይደለም

### በአንድሩ ዉማክ

ዛሬ ደግሞ እግዚአብሔር በህይወቴ ካደረጋቸው እጅግ ጠቃሚ ነገሮች ውስጥ አንዱን አካፍላችኃለሁ። ሰዎች ማንኛውንም በህይወት የሚያጋጥማቸውን ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ይቆጣጠራል፣ ከእግዚአብሔር ነው ብለው የሚያምኑ ይመስላል። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ እግዚአብሔር ከሁሉም በላይ ስለሆነ፣ ሁሉን ማድረግ የሚችልና ኃያል በመሆኑ በህይወታቸው የሚያጋጥማቸውን ነገር ሁሉ ይቆጣጠራል ከሚል ሃሳብ የተነሳ ነው፡ ፡ አማኝ ያልሆኑ ሰዎች እንኳን ይህንን ያምናሉ። በብዙ ክርስቲያኖች ህይወት ውስጥ ስር በመስደዱ እንደ አንድ ትምህርት ተቆጥሮ ብዙዎች ያስተጋቡታል፣ ይኖሩበታል። የእግዚአብሔር ቃል የሚያስተምረን ግን በተቃራኒው ነው ብዬ አምናለሁ፣ ለእናንተም ይህን መማር እጅግ ይጠቅማችኃል። ያዕቆብ 1፡13-17 *“ማንም ሲፈተን በእግዚአብሔር እፈተናለሁ አይበል፣ እግዚአብሔር በክፋ አይፈተንምና፤ እርሱ ራሱስ ማንንም አይፈትንም፡ ፡ ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል። ከዚህ በኃላ ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች ፣ ኃጢአትም ካደገች በኃላ ሞትን ትወልዳለች። የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ አትሳቱ። በጎ ስጦታ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው። መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ”* ይላል።

እነዚህ ቃላት እግዚአብሔር የመልካም ነገሮች ደራሲ መሆኑን በግልጽ ያስረዳሉ። ኢየሱስ በዮሐንስ 10፡10 *“ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጅ ስለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ህይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ”* ይላል። ስለዚህ መልካም ከሆነ ከእግዚአብሔር ክፉ ከሆነ ደግሞ ከዲያብሎስ ነው። ይህ እንግዲህ ቀላል መረዳት ነው። ሆኖም ይህን መረዳት እጅግ ጠቃሚ መሆኑን የምናውቀው አሁንም የያዕቆብን መልዕክት መገንዘብ ስንችል ነው፣ እንደዚህ ይላል፦ ያዕቆብ 4፡7 *“እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል”*። በዚህ ቃል መሰረት ራሳችን ለእግዚአብሔር ማቅረብ ወይም ፈቃዳችንን ለእግዚአብሔር ማስገዛት እና ዲያብሎስን ግን መቃወም እንዳለብን እንረዳለን። መቃወም ማለት በጽኑ መዋጋት ማለት ነው።

እንግዲህ ሰዎች በህይወት የሚያጋጥማቸው ሁሉ ለምሳሌ፦ ህመም፣ ኪሳራ፣ ከሥራ መሰናበት፣ የልጆች አስቸጋሪነት፣ የትዳር ፍች ከእግዚአብሔር ነው ብለው ካመኑ፣ ምንም ምላሽ መስጠት የማይችሉ ይሆናሉ። እግዚአብሔር የነገሮች ሁሉ ደራሲ ነው ብለው ይህንንም በእርግጠኝነት እንደ ቅጣት እና እነርሱን ለማስተማርና ለማረም ያደረገው ነው ብለው ካመኑ፣ ችግሮችን ለማስወገድ ሲሞክሩ እርሱን መቃወም ይሆንባቸዋል ማለት ነው። ነገር ግን ያዕቆብ 4፡7 ዲያብሎስን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል፤ ለእግዚአብሔርም ተገዙ ይላል። ይህም ከፊሎቹ ነገሮች ከእግዚአብሔር ከፊሎቹ ደግሞ ከዲያብሎስ መሆናቸውን ያሳየናል። በዚህች አለም የክፋ ሃይል አለ፤ ሁሉም በህይወታችን የሚያጋጥሙን ነገሮች ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደሉም። ይህን ካልተረዳችሁ እራሳችሁን ለዲያብሎስ ልታዝገዙና በእርግጥም ሃይል ሰጥታችሁት ልትገኙ ትችላላችሁ።

እዚህ ላይ ብዙ ጊዜ ያለአግባብ ጥቅም ላይ ሲውል የሚስተዋለውን አንድ ስንኝ ከሮሜ መጽሐፍ ላቀርብላችሁ እፈልጋለሁ። አማኝ ያልሆኑ ሰዎች የቀብር ስነስርዓት ሄጄ አውቃለሁ፣ ስለ እግዚአብሔር ምንም የሚያውቁት ነገር የለም፣ ቤተ ክርስቲያንም ሄደው አያውቁም፣ ከእግዚአብሔር ቃል የሚያውቁት ምንም ጥቅስ ባይኖርም ይህን በሮሜ መጽሐፍ ያለውን ጥቅስ ግን ያውቁታል። ሮሜ 8፡28 እንዲህ ይላል፦ *“እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን”*። ይህ ቃል በህይወት የሚያጋጥማችሁ ነገር ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፤ ይህንንም በሆነ መንገድ እርሱ ለበጎ ያደርገዋል የሚል ትርጉም እንዲይዝ ሲደረግ ይስተዋላል። እንድቀን፣ ወንድ እናሴት ሁለት ወጣቶች አልኮልና አደንዛዥ ዕጽ ቀላቅለው

ከወሰዱ በኃላ ወደ መኪናቸው በመግባት በሚያንሸራትት መንገድ ላይ በፍጥነት ሲያሽከረክሩ ከሰልክ እንጨት ጋር ተጋጭተው በመሞታቸው በልጆቹ የቀብር ስነ ስርዓት ላይ ተገኝቼ ነበር። ሰባኪው ይህንን ጥቅስ በመጥቀስ “ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን” እናም እግዚአብሔር ይህን ያደረገበት አላማ አለው፣ አለ። እነዚያን ታዳጊዎች እግዚአብሔር አልገደላቸውም፣ ሰይጣን ነው የገደላቸው ልትሉ የምትችሉበት ሁኔታም የለም። የታዳጊዎቹ የእራሳቸው ሥራ ነው ለሞት ያበቃቸው። ወላጆቻቸውና ሌሎችም ካስተማሯቸው የሥነ ምግባር መርህ ውጭ በአመጽ እንዲሄዱ ለማድረግ የዲያብሎስ ሽንገላና ማባበል እንደሚኖር እርግጠኛ ነኝ፣ ምርጫው ግን ሙሉ በሙሉ የልጆቹ ነው። አልኮል እና አደንዛዥ ዕጹን የወሰዱት እራሳቸው ናቸው፣ የሰልክ እንጨቱንም የገጩት እነርሱ ናቸው። ይህ ነባራዊ እውነት ነው፣ ምንጩ እግዚአብሔር አይደለም።

ለመሆኑ *“ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን”* ማለት ምን ማለት ነው? ሲጀመር ይህ ቃል ሁሉም ነገር ከእግዚአብሔር እንደሚመጣ እናውቃለን ሁሉም ደግሞ በጎ ይሆናል አይልም። ሁሉም ነገሮች አንድ ላይ ለበጎ ይደረጋሉ ይልና፡- *“እግዚአብሔርን ለሚወዱ ሁሉ”* የሚል ቅድመ ሁኔታ ያስቀምጣል። ይህ ጥቅስ እግዚአብሔርን ለማይወድ ሰው አይሰራም። ባይናገሩትም እንኳን ይህ ሲበዛ ግልጽ ነውና በእነዚህ ታዳጊዎች እንደነበረው አጋጣሚ ዓይነት በአደንዛዥ ዕጽ እና በአልኮል አማካኝነት ከእግዚአብሔር እና ከመመሪያዎቹ ሙሉ በሙሉ በተቃራኒ መንገድ ለሚያደርጉ ሰዎች ቃሉን ሲጠቀሙበት ማየት ያስገርማል። ነገር ሁሉ ለበጎ የሚደረገው እግዚአብሔርን ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነው ይላል።

በ1ኛ ዮሐ 3፡8 *“ስለዚህ የዲያብሎስን ስራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ”* ይላል። እግዚአብሔር የሰይጣንን ስራ ሊያፈርስ እራሱን ገለጠ። አላማው ይህ ነው እና እንግዲህ በዚህ ጥሪ ውስጥ ላሉና ለሚወዱት ሁሉ ነገር ሁሉ ለበጎ ነው፤ እነርሱም ዲያብሎስን ይቃወማሉ ስራውንም ያፈርሳሉ። የፈለገ ነገር ቢያደርግባቸውም እግዚአብሔር ያንን ወደ በጎ ይቀይርላቸዋል ወይም ለበጎ እንደሚያደርግላቸው ያውቃሉና መልካም እንደሚሆንላቸው መናገር የሚችሉ እነርሱ ናቸው።

በህይወታችን እግዚአብሔር ሁሉንም ነገሮች እንደማይቆጣጠርና ሊሰርቅ፣ ሊያርድና ሊያጠፋ የሚመጣ ጠላት እንዳለ ልናውቅና ኢየሱስም ህይወት ሊሰጠንና ሊያበዛልን እንደመጣ ውስጣችን ሊሰርጽና ልንረዳ ይገባል፡ ፡ ህይወትን መምረጥና በፈቃዳችንም በህይወት ለሚያጋጥሙን ነገሮች ሁሉ እግዚአብሔር ተጠያቂ እንዳልሆነ እውነቱን መለየትና መገንዘብ ይኖርብናል።

እግዚአብሔር ስጋ ለባሽ ሰው ቢሆን ኖሮ ከእርሱ ናቸው ተብሎ የሚከሰሰባቸውን ነገሮች ማለትም ሰዎችን ካንሰር ማስያዝ፣ ቅርጻቸውን ማበላሸት፣ ድብርት፣ ሐዘን፣ ስቃይን ሁሉ በሰዎች ላይ ያደረገው እርሱ ቢሆን ኖሮ በዓለም ላይ እርሱን ለማስቆም፣ ለመያዝ እና ለማሰር የማይንቀሳቀስ መንግስት እንደማይኖር አረጋግጥላችኃለሁ። ነገር ግን በህይወታችን ከምናውቀው ወይም ከምናስበው ሰው ይልቅ እጅግ አብልጦ ምህረቱ የበዛውን ደግ አምላክ ሰዎችን እንዳሻው በችግርና በስቃይ እንደሚመታ እናስባለን። አንዳንድ ችግሮች በአጋንንት ምክንያት የሚመጡ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ተፈጥሯዊ ናቸው፤ ሁሉም ችግሮች ግን በእግዚአብሔር የታዘዙ አይደሉም። የኢንሹራንስ ድርጅቶች በሰነዳቸው (በፖሊሲያቸው) ላይ “የእግዚአብሔር ስራ፣ ማለትም መሬት መንቀጥቀጥና ቸነፈር” በሚል ይጽፋሉ። ትክክል አይደለም፣ እግዚአብሔር የእነዚህ ነገሮች ሁሉ ደራሲ አይደለም።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ያዕቆብ 1፡13 እግዚአብሔር ሰዎች በክፉ እንዲፈተኑ ያደርጋል?

   **ያዕቆብ 1፡13** *ማንም ሲፈተን፣ በእግዚአብሔር እፈተናለሁ አይበል፤ እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንምና፤ እርሱ ራሱስ ማንንም አይፈትንም።*

2. ያዕቆብ 1፡17 መልካም ስጦታዎች ሁሉ ከየት ይመጣሉ?

   **ያዕቆብ 1፡17** *በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፥ መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ።*

3. ዮሐንስ 10፡10 ሌባው ማነው?

   **ዮሐንስ 10፡10** *ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ሰለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ።*

4. ዮሐንስ 10፡10 ሥራዎቹ ምን፣ ምን ናቸው?

5. ዮሐንስ 10፡10 ኢየሱስ የመጣበት ምክንያት ምንድን ነው?

6. ያዕቆብ 4፡7 ራሳችሁን ለእግዚአብሔር ማስገዛት እና ዲያብሎስን መቃወም ምን ውጤት አለው?

   **ያዕቆብ 4፡7** *እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል፤*

7. ሮሜ 8፡28 ይህ ቃል ሁሉ ነገር ከእግዚአብሔር ነው ይላል?

   **ሮሜ 8፡28** *እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።*

8. የሐዋርያት ሥራ 10፡38 ህመም ከእግዚአብሔር ነው?

   **የሐዋርያት ሥራ 10፡38** *እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀባው፥ እርሱም መልካም እያደረገ ለዲያብሎስም የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ፥*

9. 1ኛ ዮሐንስ 3፡8-9 የእግዚአብሔር ልጅ የተገለጠበት ምክንያት ምንድን ነው?

   **1ኛ ዮሐንስ 3፡8-9** *ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው፣ ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኃጢአትን ያደርጋልና። [9] ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ። ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም፣ ዘሩ በእርሱ ይኖራልና፣ ከእግዚአብሔርም ተወልዶአልና ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም።*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ያዕቆብ 1፡13 እግዚአብሔር ሰዎች በክፉ እንዲፈተኑ ያደርጋል?
   **አያደርግም።**

2. ያዕቆብ 1፡17 መልካም ስጦታዎች ሁሉ ከየት ይመጣሉ?
   **ከብርሃናት አባት።**

3. ዮሐንስ 10፡10 ሌባው ማነው?
   **ዲያብሎስ።**

4. ዮሐንስ 10፡10 ሥራዎቹ ምን፣ ምን ናቸው?
   **መስረቅ፣ ማረድ እና ማጥፋት።**

5. ዮሐንስ 10፡10 ኢየሱስ የመጣበት ምክንያት ምንድን ነው?
   **የተትረፈረፈ ህይወት ሊሰጠን።**

6. ያዕቆብ 4፡7 ራሳችሁን ለእግዚአብሔር በማስገዛት ዲያብሎስን ስትቃወሙ ምን ውጤት ታገኛላችሁ?
   **ከእኛ ይሸሻል።**

7. ሮሜ 8፡28 ይህ ቃል ሁሉ ነገር ከእግዚአብሔር ነው ይላል?
   **አይልም።**

8. የሐዋርያት ሥራ 10፡38 ህመም ከእግዚአብሔር ነው?
   **አይደለም።**

9. 1ኛ ዮሐ 3፡8-9 የእግዚአብሔር ልጅ የተገለጠበት ምክንያት ምንድን ነው?
   **የዲያብሎስን ስራ እንዲያፈርስ።**

## ትምህርት 14

# በመንፈስ የተሞላ ህይወት ሃይል

## በዶን ክሮው

ማርቆስ 16፡15-16 ታላቁ ተልዕኮ በመባል ይታወቃል። ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን፡- *"እንዲህም አላቸው። ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ። ያመነ የተጠመቀም ይድናል፣ ያላመነ ግን ይፈረድበታል"*። በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 ቁጥር 5-12 ፊሊጶስ ለሰማርያ ሰዎች ክርስቶስን በሰበከላቸው ጊዜ ይህ ተልዕኮ እንዴት ተግባራዊ እንደሆነ እንመለከታለን፡- *"ፊሊጶስም ወደ ሰማርያ ከተማ ወርዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው … [8] ነገር ግን ስለ እግዚአብሔር መንግስትና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም እየሰበከላቸው ባመኑት ጊዜ ወንዶችም ሴቶችም ተጠመቁ"*።

አሁን ጥያቄው፡- እነዚህ የሰማርያ ሰዎች በማርቆስ 16፡15-16 መሰረት ክርስቲያን ሆነዋል? አዎ ሆነዋል። ፊሊጶስ ክርስቶስ ኢየሱስን በመሰከረላቸው ጊዜ አምነው በመጠመቅ ወንዶችም ሴቶችም ድነዋል። በታላቁ ተልዕኮ አማካኝነት እነዚህ ሰዎች ድነዋል ነገር ግን የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ተጠምቀዋል ወይ?

መጽሐፍ ቅዱስ ዮሐንስ በውሃ እንዳጠመቀ እና በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ ኢየሱስ ብቻ እንደሆነ ይነግረናል። እንደ ቃሉ ከሆነ እነዚህ ሰዎች አምነዋል፣ ድነዋል እና በውሃ ተጠምቀዋል ነገር ግን የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ገና አልተቀበሉም። የሐዋርያት ሥራ 8፡14-17 ቀጥሎ እንዲህ ይላል፡- *"በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያት የሰማርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንደተቀበሉ ሰምተው ጴጥሮስንና የሐንስን ሰደዱላቸው። እነርሱም በወረዱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ ጸለዩላቸው፤ በጌታ በኢየሱስ ሰም ብቻ ተጠምቀው ነበር እንጅ ከእነርሱ በአንዱ ላይ ሰንኳ ገና አልወረደም ነበርና። በዚያን ጊዜ እጃቸውን ጫኑባቸው መንፈስ ቅዱስንም ተቀበሉ"*።

ከቃሉ እንደምንረዳው አንድ ሰው ስላመነ፣ በውሃ ስለተጠመቀ እና ስለዳነ መንፈስ ቅዱስን ተቀብሏል ማለት አይደለም። በዮሐንስ 20፡22 መንፈስ ቅዱስ ወደ ሐዋርያት ህይወት መጥቷል እንደገናም አነቃቅቶአቸዋል። ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁት እና የእግዚአብሔርን ሃይል የተቀበሉት በበዓለ ሃምሳ (በጴንጤቆስጤ) ቀን ነበር። መንፈስ ቅዱስ ወደ አንድ ሰው በሚመጣበት ጊዜ ከመንፈስ ቅዱስ የተነሳ ህያው ሆኖ በመዳን እና በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በመጠመቅ መካከል ልዩነት አለ። ሰው በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቆ የእግዚአብሔርን ሃይል የሚቀበልበት ሁኔታ አለ፤ ነገር ግን ሰዎች ስለዳኑ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ተቀብለዋል ማለት አይደለም።

የሐዋርያት ሥራ 19፡1-2 ይህን ይናገራል፡- *"እጵሎስም በቆሮንቶስ ሳለ ጳውሎስ በላይኛው አገር አልፎ ወደ ኤፌሶን መጣ፤ አንዳንድ ደቀ መዛሙርትንም አገኘ። "ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?" አላቸው። እነርሱም "አልተቀበልንም መንፈስ ቅዱስ እንዳለ ሰንኳ አልሰማንም አሉት"*። ጳውሎስ "ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁ ወይ?" በማለት ሲጠይቃቸው እነርሱ የሰጡት መልስ "ስለ መንፈስ ቅዱስ የምናውቀው ነገር የለም" የሚል ነው። ጳውሎስም በመቀጠል "በመንፈስ ቅዱስ ካልተጠመቃችሁ በምን ተጠመቃችሁ?" አላቸው፤ እነርሱም "በዮሐንስ ጥምቀት" አሉት። ጳውሎስ ስለ ኢየሱስ እርሱም ክርስቶስ እንደሆነ በትክክል እንዳስረዳቸው እነዚህ አማኞችም በውሃ ጥምቀት ስለ ኢየሱስ ማወቅ የሚገባቸውን ያህል እንዳወቁ አምናለሁ። በቁጥር 6-7 እንዲህ ይላል - *"ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው በልሳኖችም ተናገሩ፣ ትንቢትም ተናገሩ። ሰዎቹም ሁሉ አሰራ ሁለት ያህሉ ነበር"*።

ምንም እንኳን እነዚህ ሰዎች በክርስቶስ መምጣት ያመኑ ደቀመዛሙርት ቢሆኑም በመንፈስ ቅዱስ አልተጠመቁም ነበር። አንድ ዳግመኛ የተወለደ ሰው በውሃ ተጠምቆ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ላይጠመቅ ይችላል። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከመዳን ወይም ከመመለስ በኃላ ራሱን የቻለ የተለየ ክንውን ነው።

እኔ ሰውን በውሃ ላጠምቅ ብችልም በመንፈስ ቅዱስ ላጠምቅ ግን አልችልም። ያን ማድረግ የሚችለው ኢየሱስ ብቻ ነው። ስለዚህ ምን ትጠብቃላችሁ? እስካሁን ድረስ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ እንዲያጠምቃችሁ ካልጠየቃችሁት ለምን አሁን አትጠይቁትም? ሉቃስ 11፡13 እንዲህ ይላል፦ *"እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፤ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?"* ለምን ዛሬውኑ አትጠይቁትም?

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ማርቆስ 16፡16፣ ደግሞም የሐዋርያት ሥራ 8፡5 እና 12 አንብቡ። በሐዋርያት ሥራ 8፡12 የተጠቀሱት ሰዎች ክርስቲያን ሆነዋል?

   **ማርቆስ 16፡16** *ያመነ የተጠመቀም ይድናል፥ ያላመነ ግን ይፈረድበታል።*

   **የሐዋርያት ሥራ 8፡5** *ፊልጶስም ወደ ሰማርያ ከተማ ወርዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው።*

   **የሐዋርያት ሥራ 8፡12** *ነገር ግን ስለ እግዚአብሔር መንግሥትና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም እየሰበከላቸው ፊልጶስን ባመኑት ጊዜ፥ ወንዶችም ሴቶችም ተጠመቁ።*

2. የሐዋርያት ሥራ 8፡14-16 እነዚህ ሰዎች የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ተቀብለዋል?

   **የሐዋርያት ሥራ 8፡14-16** *በኢየሩሌም የነበሩት ሐዋርያት የሰማርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንደተቀበሉ ሰምተው ጴጥሮስንና ዮሐንስን ሰደዱላቸው። [15] እነርሱም በወረዱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ ጸለዩላቸው[16] በጌታ በኢየሱስ ስም ብቻ ተጠምቀው ነበር እንጂ ከእነርሱ በአንዱ ላይ ስንኳ ገና አልወረደም ነበርና።*

3. የሐዋርያት ሥራ 19፡1-5 እነዚህ ሰዎች አማኞች ናቸው?

   **የሐዋርያት ሥራ 19፡1-5** *አጵሎስም በቆሮንቶስ ሳለ ጳውሎስ በላይኛው አገር አልፎ ወደ ኤፌሶን መጣ [2] አንዳንድ ደቀ መዛሙርትንም አገኘ። ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን? አላቸው። እነርሱም፦ አልተቀበልንም፣ መንፈስ ቅዱስ እንዳለ ስንኳ አልሰማንም አሉት። [3] እንኪያ በምን ተጠመቃችሁ? አላቸው። እነርሱም፦ በዮሐንስ ጥምቀት አሉት።[4] ጳውሎስም፦ ዮሐንስስ ከእርሱ በኋላ በሚመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ ያምኑ ዘንድ ለሕዝብ እየተናገረ በንስሐ ጥምቀት አጠመቀ አላቸው።[5] ይህንም በሰሙ ጊዜ በጌታ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ፤*

4. የሐዋርያት ሥራ 19፡6-7 የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ተቀብለዋል?

   **የሐዋርያት ሥራ 19፡6-7** *ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው በልሳኖችም ተናገሩ፥ ትንቢትም ተናገሩ።[7] ሰዎቹም ሁሉ አሥራ ሁለት ያህሉ ነበር።*

5. ሉቃስ 11፡13 አንንብቡና፤ መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል ሉቃስ 11፡13 ምን ማድረግ አለብን ይላል?

   **ሉቃስ 11፡13** *እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፥ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?*

6. 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡2 ሰዎች በልሳን ሲናገሩ ምን እያደረጉ ነው?

   **1ኛ ቆሮንቶስ 14፡2** *በልሳን የሚናገርስ ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርም፤ የሚያስተውለው የለምና፥ በመንፈስ ግን ምሥጢርን ይናገራል፤*

7. 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡14 ሰው በልሳን ሲናገር ምን እያደረገ ነው?

   **1ኛ ቆሮንቶስ 14፡14** *በልሳን ብጸልይ መንፈሴ ይጸልያል አእምሮዬ ግን ያለ ፍሬ ነው።*

8. 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡16-17 ሰዎች በልሳን ሲናገሩ፣ ምን እያደረጉ ነው?

   **1ኛ ቆሮንቶስ 14፡16-17** *እንዲያማ ካልሆነ፥ አንተ በመንፈስ ብትባርክ ባልተማሩት ስፍራ የተቀመጠው የምትለውን ካላወቀ እንዴት አድርጎ ለምስጋናህ አሜን ይላል? [17] አንተማ መልካም ታመሰግናለህ፥ ሌላው ግን አይታነጽበትም።*

9. የሐዋርያት ሥራ 2፡4 አንድ ሰው በልሳን ሲናገር ንግግሩን የሚያደርገው መንፈስ ቅዱስ ነው ወይስ ሰውየው እራሱ?

   **የሐዋርያት ሥራ 2፡4** *በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።*

10. የሐዋርያት ሥራ 2፡4 ለሰዎቹ የሚናገሩትን የሰጣቸው ማነው?

# ጠቋሚ መልሶች

1. ማርቆስ 16፡16፣ ደግሞም የሐዋርያት ሥራ 8፡5 እና 12 አንብቡ። በሐዋርያት ሥራ 8፡12 የተጠቀሱት ሰዎች ክርስቲያን ሆነዋል?
   **አዎ።**

2. የሐዋርያት ሥራ 8፡14-16 እነዚህ ሰዎች የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ተቀብለዋል?
   **አልተቀበሉም።**

3. የሐዋርያት ሥራ 19፡1-5 እነዚህ ሰዎች አማኞች ናቸው?
   **አዎ።**

4. የሐዋርያት ሥራ 19፡6-7 የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ተቀብለዋል?
   **አልተቀበሉም።**

5. ሉቃስ 11፡13 አንንብቡና፤ መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል ሉቃስ 11፡13 ምን ማድረግ አለብን ይላል?
   **መጠየቅ።**

6. 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡2 ሰዎች በልሳን ሲናገሩ ምን እያደረጉ ነው?
   **ለእግዚአብሔር እያወሩ እና ምስጢርን እየተናገሩ ነው።**

7. 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡14 ሰው በልሳን ሲናገር ምን እያደረገ ነው?
   **መንፈሳቸው ወደ እግዚአብሔር እየጸለየ ነው።**

8. 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡16-17 ሰዎች በልሳን ሲናገሩ፣ ምን እያደረጉ ነው?
   **በመንፈሳቸው እግዚአብሔርን እየባረኩ እና እያመሰገኑ (እያከበሩ) ነው።**

9. የሐዋርያት ሥራ 2፡4 አንድ ሰው በልሳን ሲናገር ንግግሩን የሚያደርገው መንፈስ ቅዱስ ነው ወይስ ሰውየው እራሱ?
   **ሰውየው ነው።**

10. የሐዋርያ ሥራ 2፡4 ለሰዎቹ የሚናገሩትን የሰጣቸው ማነው?
    **መንፈስ ቅዱስ።**

# ትምህርት 15

# መንፈስ ቅዱስን መቀበል!

## በዶን ክሮው

ዛሬ ደግሞ መንፈስ ቅዱስን ስለ መቀበል እናወራለን። የሐዋርያት ሥራ 10፡1 እንዲህ ይላል *"በቂሳርያም ኢጣሊቄ (ኢጣሊያ) ለሚሉት ጭፍራ የመቶ አለቃ የሆነ ቆርኔሊዎስ የሚሉት አንድ ሰው ነበረ"*፡ ይህ ወታደራዊ ማዕረግ ሲሆን እርሱም የጭፍራው ወይም የምድቡ መሪ ነበር። ቁጥር 2 በመቀጠል *"እርሱም ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር እግዚአብሔርን የሚያመልክና የሚፈራ ለሕዝብም እጅግ ምጽዋት የሚያደርግ ወደ እግዚአብሔርም ሁልጊዜ የሚጸልይ ነበረ"*። ይህ ሰው ጻድቅ ነበር፣ ትክክለኛ ነገሮችን ያደርጋል፣ እግዚአብሔርን ይፈራል፣ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎችም ገንዘቡን በብዛት ይሰጣል፣ መጽሐፍም እንደሚለው ወደ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ይጸልያል። ነገር ግን ምንም እንኳን ትክክለኛ ነገሮችን ቢያደርግም፣ ምንም እንኳን እግዚአብሔርንም ቢፈራ፣ መልካም የሆነ የጸሎት ህይወት ይኑረው እንጂ ይህ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ጋር የግል ግንኙነት አልነበረውም፣ ይህም የሚያስገርም ነው።

በቁጥር 3-6 እንዲህ ይላል፡- *"ከቀኑም ዘጠኝ ሰዓት ያህል ቆርነሊዎስ ሆይ የሚለው የእግዚአብሔር መልአክ ወደ እርሱ ሲገባ በራዕይ በግልጥ አየው። እርሱም ትኩር ብሎ ሲመለከተው ደንግጦ። ጌታ ሆይ፥ ምንድር ነው? አለ። መልአኩም አለው። ጸሎትህና ምጽዋትህ በእግዚአብሔር ፊት ለመታሰቢያ እንዲሆን አረገ። አሁንም ወደ ኢዮጴ ሰዎችን ልከህ ጴጥሮስ የሚባለውን ሰምዖንን አስመጣ። እርሱ ቤቱ በባሕር አጠገብ ባለው በቍርበት ፋቂው በሰምዖን ዘንድ እንግድነት ተቀምጦአል፤ ልታደርገው የሚገባህን እርሱ ይነግርሃል"*።

ይህ ሰው ምንም እንኳን እግዚአብሔርን የሚፈራ፣ ትክክለኛ ነገሮችን የሚያደርግ ጻድቅ ሰው ቢሆንም፣ በእግዚአብሔር ፊት መልካም የጸሎት ሕይወት ቢኖረውም፣ መልአክ እንደተላከለትና መልአኩም መጥቶ ጴጥሮስን እንዲያስመጣና የሚያደርገውንም ሁሉ እርሱ እንደሚነግረው ሲነግረው እንመለከታለን። በሐዋርያት ሥራ 10፡43 ጴጥሮስ በመጣ ጊዜ እግዚአብሔር ለቆርኔሊዎስ እንዲነግረው የላከውን የመልዕክቱን ትክክለኛ ፍሬ ነገር እንመለከታለን፡- *"በእርሱ የሚያምን ሁሉ በሰሙ (በጌታ በኢየሱስ ሰም) የኃጢአቱን ሥርዬት እንዲቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል"* (በቅንፍ ያለው በእኔ የተጨመረ ነው)። አይገርምም? ይህ ሰው በእነዚህ ሁሉ መልካም ምግባሮቹ ከእግዚአብሔር ጋር በክርስቶስ ኢየሱስ የሆነ ትክክለኛው ህብረት አልነበረውም። እግዚአብሔርም "የምታደርጋቸው ነገሮች ሁሉ መልካም ናቸው፣ ድንቅ ነገሮች አድርገሃል፣ በፊቴም ለማስታወሻ ሆነዋል፣ ነገር ግን የማደርገውን እነግርሃለሁ። ጴጥሮስ የሚባል ሰው እንድታስመጣ የሚነግርህን መልአኬን ወደ አንተ ልኬአለሁ፣ እርሱም ማድረግ የሚገባህን ሁሉ ይነግርሃል"። በሐዋርያት ሥራ 10፡43 ጴጥሮስም ወደ ቆርነሊዎስ በመጣ ጊዜ *"በእርሱ (በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ) የሚያምን ሁሉ የኃጢአቱን ሥርዬት ያገኛል"* ብሎ ተናገረ (በቅንፍ ያለው በእኔ የተጨመረ ነው)።

አሁን የተከሰተውን ነገር እንመልከት፡- *"ጴጥሮስም ይህን ነገር ገና ሲናገር ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደ"* (ሐዋ 10፡44)። ቆርኔሊዎስ - መዳን በክርስቶስ መሆኑን ሰምቶ ፤ ከኃጢአቱም ስርየትን (ነጻነት) የሚያገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን መሆኑን አምኖ ተቀበለ። ወዲያውኑ መንፈስ ቅዱስ በእርሱና በቤተሰዎቹ ላይ ወረደ። በቁጥር 45 *"ከጴጥሮስም ጋር የመጡት ሁሉ ከተገረዙት ወገን የሆኑ ምዕመናን በአህዛብ ላይ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ስለፈሰሰ ተገረሙ"* ይላል። እንዴት አወቁ? – *"በልሳኖች ሲናገሩ እግዚአብሔርንም ሲያከብሩ ሰምተዋቸዋልና"* (ቁጥር 46)።

በአዲስ ኪዳን መንፈስ ቅዱስ በአንድ ሰው ላይ በወረደ ጊዜ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በሰውየው ላይ መገለጥ ይጀምራሉ በልሳን (አዲስ ቋንቋ) መናገር፣ ትንቢት መናገር፣ በመንፈስ ለመሞላታቸው የሚጠቀሱ

ጥቂቶቹ ምልክቶች ናቸው።

አንድ ምሽት ዳላስ ቴክሳስ ውስጥ መስክ ላይ፣ በጉልበቴ በርከክ ብዬ እንዲህ አልኩ - "ጌታ ሆይ በልሳን ስለመጸለይም ሆነ ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በተመለከተ ሰዎች ስለሚናገሩት ነገር እኔ የማውቀው ነገር የለም፣ ነገር ግን በዚህ አንተን የማከብርበት መንገድ ካለ፣ አንተን ከፍ የማደርግበት መንገድ ካለ፣ እኔ ከማውቀው የእንግሊዝኛ ቋንቋ በላይ የሆነ መንገድ ካለ ያንን እኔ እፈልገዋለሁ፣ያስፈልገኛል።" በመቀጠል እግዚአብሔርን ማመስገን ጀመርኩ፣ ይህን በማድረግ ላይ እያለሁ መንፈስ ቅዱስ የማላውቀውን ወይም ያልተማርኩትን ቋንቋ ሰጠኝ። መጽሐፍ ቅዱስ በሐዋርያ *ሥራ* 2፡4 – *"በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር"* ይላል። የሚናገረው ማን ነው? ሰዎቹ። የሚናገሩትን ማን ሰጣቸው? መንፈስ ቅዱስ።

ሉቃስ 11፡13 እንዲህ ይላል - *"እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፥ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው!"* አሁን ማድረግ ያለባችሁ መጠየቅ ብቻ ነው፣ ከጠየቃችሁ በኃላ እንደተቀበላችሁ እመኑ፣ እራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ፣ ጌታን ማመስገን ጀምሩ እርሱን የምታከብሩበትን፣ የምታመሰግኑበትንም ከዚህ በፊት ባልተማራችሁት ቋንቋ የምትናገሩትን ቃላት ይሰጣችኃል።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. መዳንን በተመለከተ ከተጻፉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ውስጥ የምታውቋቸውን አብራሩ።

   **ዮሐንስ 3:3** *ኢየሱስም መለሰ። እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው።*

   **የሐዋርያት ሥራ 3:19-20** *እንግዲህ ከጌታ ፊት የመጽናናት ዘመን እንድትመጣላችሁ፣ አስቀድሞም ለእናንተ የመረጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲልክላችሁ ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ ግቡ ተመለሱም።*

   **ማርቆስ 16:16** *ያመነ የተጠመቀም ይድናል፥ ያላመነ ግን ይፈረድበታል።*

   **ቆላስያስ 2:13** *እናንተም በበደላችሁና ሥጋችሁን ባለመገረዝ ሙታን በሆናችሁ ጊዜ፥ ከእርሱ ጋር ሕይወትን ሰጣችሁ። በደላችሁን ሁሉ ይቅር አላችሁ።*

   **ሮሜ 8:9** *እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥ በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም። የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም።*

   **ማቴዎስ 25:46** *እነዚያም ወደ ዘላለም ቅጣት፥ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ።*

2. የሐዋርያት ሥራ 11:15 ይህ ቃል የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን እንዴት ይገልጸዋል?

   **የሐዋርያት ሥራ 11:15** *ለመናገርም በጀመርሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ለእኛ ደግሞ በመጀመሪያ እንደ ወረደ ለእነርሱ ወረደላቸው።*

3. የኢየሱስ ደቀመዛሙርት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ (ዮሐንስ 20:20) ከጥቂት ቀን በኃላ በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀዋል (ሐዋ 2:4)። እነዚህን ቃሎች (ዮሐንስ 20:20 እና ሐዋ ሥራ 2:4)ን አስተውሉና አነጻጽሩ።

   **ዮሐንስ 20:22** - *ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና። መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ።*

   **የሐዋርያ ሥራ 2:4** *በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።*

4. የሐዋርያ ሥራ 1:18 በመንፈስ ቅዱስ የመጠመቅ አላማው ምንድን ነው?

   **የሐዋርያ ሥራ 1:18** *ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።*

5. የሐዋርያት ሥራ 2:38-39 እና 1ኛ ቆሮንጦስ 1:7 የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፣ አሁን ለእኛ አለ?

   **የሐዋርያት ሥራ 2:38-39** *ጴጥሮስም፦ ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ*

*ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።[39] የተሰፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና አላቸው።*

**1ኛ ቆሮንቶስ 1፡7** *እንደዚህ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ ስትጠባበቁ አንድ የጸጋ ስጦታ እንኳ አይጎድልባችሁም፤*

6. ሉቃስ 11፡13 የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን ካልተቀበላችሁ ምን ማድረግ አለባችሁ?

**ሉቃስ 11፡13** *እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፥ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?*

7. ሐዋ 2፡4 እግዚአብሔር በሚሰጣችሁ አዲስ ቋንቋ ጠይቃችሁ፣ ለመቀበልና ለመናገር እግዚአብሔርንም ለማክበር ፈቃደኛ ናችሁ?

**የሐዋርያ ሥራ 2፡4** *በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።*

# ጠቋሚ መልሶች

1. መዳንን በተመለከተ ከተጻፉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ውስጥ የምታውቋቸውን አብራሩ።
**ዳግመኛ መወለድ (ዮሐንስ 3:3)፣ መለወጥ (ሐዋ 3:19)፣ ማመንና መጠመቅ (ማርቆስ 16:16)፣ ይቅርታን ማግኘት (ቆላስያስ 2:13)፣ የክርስቶስን መንፈስ መቀበል (ሮሜ 8:9)፣ እና የዘላለም ህይወት (ማቴዎስ 25:46)።**

2. የሐዋርያት ሥራ 11:15 ይህ ቃል የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን እንዴት ይገልጸዋል?
**መንፈስ ቅዱስ በአንድ ሰው ላይ ወረደ በሚል ይገልጸዋል።**

3. የኢየሱስ ደቀመዛሙርት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ (ዮሐንስ 20:20) ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀዋል (ሐዋ 2:4)። እነዚህን ቃሎች (ዮሐንስ 20:20 እና ሐዋ ሥራ 2:4) አስተውሉና አነጻጽሩ።
**በዮሐንስ 20:22 ደቀመዛሙርት መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፤ በሐዋርያ ሥራ 2:1-4 እነዛው ደቀመዛሙርት መንፈስ ቅዱስን ተሞሉ (ይህም የውስጥ እና የውጭ መጥለቅ ማለት ነው)። የሐዋርያት ሥራ 1:8 ተመልከቱ።**

4. የሐዋርያት ሥራ 1:8 በመንፈስ ቅዱስ የመጠመቅ አላማው ምንድን ነው?
**ለአገልግሎት ለማዘጋጀት (ወይም ለምስክርነት)።**

5. የሐዋርያት ሥራ 2:38-39 እና 1ኛ ቆሮንቶስ 1:7 ለእኛ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፣ አሁን አለ?
**አዎ። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በክርስቶስ ዳግም መምጣት ነው፣ እስከዛው ግን ይቀጥላል።**

6. ሉቃስ 11:13 የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን ካልተቀበላችሁ ምን ማድረግ አለባችሁ?
**መጠየቅ።**

7. የሐዋርያት ሥራ 2:4 እግዚአብሔር በሚሰጣችሁ አዲስ ቋንቋ ጠይቃችሁ፣ ለመቀበልና ለመናገር እግዚአብሔርንም ለማክበር ፈቃደኛ ናችሁ?
**አዎ፣ እናገራለሁ፣ ነገር ግን የምናገረውን ቃል (ቋንቋ) መንፈስ ቅዱስ ይሰጠኛል።**

## ትምህርት 16

# በልሳን የመናገር ጥቅሞች

### በአንድሩ ዉማክ

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በመጀመሪያ በመጣ ጊዜ ከሆኑት ነገሮች መካከል አንደኛው - በቦታው የነበሩ ሰዎች ሁሉ በልሳኖች መናገራቸው ነው። የሐዋርያት ሥራ 2:4 *"በበዓለ ሃምሳ ቀን በሁሉም መንፈስ ሞላባቸው፣ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር"* ይላል። በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በተከታታይና በቀጣይነት ሰዎች መንፈስ ቅዱስን በተቀበሉ ጊዜ የእግዚአብሔር መገኘት አብሮ ይታይ ነበር።

በእርግጥ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት በልሳን መጸለይ ብቻ ሳይሆን ከዚህም በላይ እጅግ ብዙ ነገሮች አሉት፣ ሆኖም ግን በልሳን መናገር አንደኛው እና አስፈላጊ መገለጫ ነው።1ኛ ቆሮንቶስ 14:13-14 – *"ስለዚህ በልሳን የሚናገር እንዲተረጉም ይጸልይ። በልሳን ብጸልይ መንፈሴ ይጸልያል አዕምሮዬ ግን ያለፍሬ ነው"*፡ ፡ በልሳን ሰትጸልዩ መንፈሳችሁ ይጸልያል። እንዴ በልሳን መናገር እንደ ጀመራችሁ ስለምትናገሩት ነገር ያላችሁ መረዳት ሙሉ እና ፍሬያማ ይሆን ዘንድ ትርጉም ለማግኘትም ጸልዩ።

የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ተቀብዬ በልሳን መጸለይ እንደጀመርኩ ህይወቴን በአስገራሚ ሁኔታ የቀየረው መሆኑን የእራሴን ምስክርነት ልሰጣችሁ እችላለሁ። ዳግመኛ በተወለድኩ ጊዜ ክርስቶስ ወደ እኔ እንደመጣ፣ በእኔ ውስጥ እንደሚኖር እና ሁሉንም ነገር በውስጤ እንዳሰቀመጠ አምናለሁ፤ መንፈስ ቅዱስ በእኔ ላይ በመጣ ጊዜ ግን ለእኔም ሆነ ለሌሎች ሰዎች መገለጥ ጀመረ። የተወሰኑ አንዳንድ ነገሮች ተከናውነው ነበር። ሆኖም በልሳን በምጸልይበት የመጀመሪያው ዓመት ላይ አዕምሮዬ - በማይረባ ነገር ጊዜህን አታቃጥል እያለ ይነግረኝ ነበር። በልሳን ለመጸለይ እምነት አስፈልጎኝ ነበር፤ ለዚህ ነው የይሁዳ መልዕክት 1:20 ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ በመንፈስ ቅዱስም እየጸለያችሁ የሚለው። ከተለመደው አስተሳሰብ እና አመክንዮ አውጥቶ ከልዕለ ተፈጥሮ በላይ ወደ ሆነ የእምነት ክልል ይወስዳችኃል።

ሌላው ያጋጠመኝ ነገር ደግሞ በልሳን በምጸልይበት ጊዜ ለብዙ ዘመን የረሳኃቸውን ሰዎች ማስታወስ መቻሌ ነው። ለእነርሱም እጸልይላቸው ጀመር። ይህ ከሆነ አንድ ወይም ሁለት ቀን በኃላ፣ ሰዎቹ ይደውሉልኛል በህይወታቸው አስገራሚ ተዓምር እንደተደረገላቸውም እረዳለሁ። ይህም በተደጋጋሚ ይሆን ነበር እና እነዚህን ነገሮች በማስተዋልና በማገጣጠም በመጨረሻ፣ በልሳን በምጸልይበት ጊዜ ከአዕምሮዬ ችሎታ በላይ በሆነ ጥበብ እየጸለይኩ መሆኑን ተገነዘብኩ። ሁሉን የሚያውቀውና የክርስቶስ ልብ ያለው መንፈሴ እኔ በተፈጥሮ ባለኝ መረዳት ላደርገው በማልችልበት መንገድ ለሰዎች እየጸለየላቸው ነበር።

አንድ ቀን በልሳን እየጸለይኩ ነበር፣ በልሳን ለመጸለይ እምነት ያስፈልገኝ እንደነበር ተናግሪአለሁ፣ እናም ከአንዳንድ ሃሳቦች ጋር መታገል ጀመርኩ፤ በዚህ ዝብርቅርቅ ነገር ከምትለፈልፍ ይልቅ በእንግሊዝኛ ቋንቋ እየተናገርክ መልካም ነገሮችን ማድረግ ትችል ነበር፣ ዓይነት ሃሳቦች በአዕምሮዬ ይመላለሱ ነበር። እነዚህን ሃሳቦች ታግዬ ለማስወገድ መጸለይ ቀጠልኩ። ይህ በዚህ እንዳለ ላለፉት አራት ዓመታት ያላየሁት አንድ ሰው በሬን አንኳኳ። ምንም ሳይናገር፣ ሰላምም ሳይለኝ ገብቶ ተቀመጠ፣ ብዙ ችግር ደርሶበት ነበርና እያለቀሰ የልቡን ሁሉ መዘርገፍ ጀመረ። እኔም ተቀመጥኩና - በእንግሊዝኛ መጸለይ ነበረብኝ፣ ብዬ አሰብኩ። በመቀጠልም - ላለፉት አራት ዓመታት ያላገኘሁትን ሰው እንዴት፣ ምን ብዬ ልጸልይለት እችላለሁ? ብዬ ደግሞ አሰብኩ። በመጨረሻ ግን እኔም እንደጸለይኩ፣ እግዚአብሔርም ያዘጋጀኝ እንደነበር ግንዛቤው ወደ እኔ መጣ፣ እንዲሁ ተረዳሁ። በራሴ መረዳት ብጸልይ ኖሮ ላደርግለት በማልችለው መንገድ ለዚህ ሰው እየማለድኩለት ነበር። ወዲያውኑ መገለጥ አገኘሁና - "ችግርህ ምን እንደሆነ ልነግርህ እችላለሁ" አልኩት። የእራሱን ታሪክ በሙሉ፣ መልሱንም ጨምሬ ነገርኩት።

ይህ የሆነው ገና ወግ አጥባቂ ቤተ ክርሰቲያን ውሰጥ እያለሁ እንደ ነበር እንድትረዱልኝ እፈልጋለሁ። ሰውዬው ምን እንደነካኝ አላወቀም፣ እኔም እርግጠኛ አልነበርኩም እና ለሁለታችንም አስፈሪ ነበር። ነገር ግን ከልዕለ ተፈጥሮ በላይ የሆነው የእግዚአብሔር ሃይል ተገልጦ እየሰራ ነበር። ይህም ማለት በልሳን ሰትጸልዩ የሚጸልየው መንፈሳችሁ ነው። መንፈሳችሁ ዳግመኛ ተወልዷል፣ የክርሰቶሰም ልብ አለው እና የሚያደርገውን ያውቃል። ቅዱሱን ቅባት ከእግዚአብሔር ተቀብሏልና ሁሉንም ነገር ታውቃላችሁ፣ በመንፈሳችሁ ጉድለት ወይም እጥረት የሚባል ነገር የለም። በመንፈሳችሁ ሃይል እና መገለጥ መራመድ ብትችሉ ነባራዊ ህይወታችሁን ይቀይረዋል። ይህን ለማድረግ፣ ብቸኛው መንገድ ባይሆንም፣ አንደኛው መንገድ በልሳን መናገር ነው። ይህን በምታደርጉበት ጊዜ ማሰታወስ እና ማመን የሚገባችሁ - እራሳችሁን በተቀደሰ እምነታችሁ እያነጻችሁ ነው፣ መንፈሳችሁ የተደበቀውን የእግዚአብሔር ጥበብ እየጸለየ ነው ደግሞም የእግዚአብሔር ፍጹም መገለጥ እየመጣ ነው። ሰለዚህ፣ እንደ 1ኛ ቆሮንቶሰ 14፡13 መተርጎም እንድትችሉ ጸልዩ። ይህ ማለት ግን በልሳን መጸለያችሁን አቋርጡና ለመተርጎም በአማርኛ ጸልዩ ማለት አይደለም፣ ነገር ግን ግንዛቤአችሁ ፍሬያማ ይሆናል ማለት ነው።

በቤተክርሰቲያን አገልግሎት በልሳን መልዕክት የምትናገሩ ከሆነ ደግሞ ቆም ብላችሁ ሰዎች በሚያውቁት ቋንቋ (በአማርኛ) የመልዕክቱን ትርጉም ማሰተላለፍ ይኖርባችኃል። በግል በልሳን በምትጸልዩበት ጊዜ ግን እኔ የማደርገው በልሳን ሰጸልይ እግዚአብሔር መገለጥ እንደሚሰጠኝ አምኜ እጸልያለሁ። አንዳንድ ጊዜ አመለካከቴ እንዲሁ ይቀየራል። ምንም ዓይነት የተለየ ቃል ሳይኖረኝ ነገር ግን ባልተጠበቀ ሁኔታ ነገሮችን በግልጽ የማይበትና አመለካከቴ የሚቀየርበት ጊዜ አለ። ሙሉ መገለጥ ለማግኘት ምናልባት ሳምንት ሊወሰድብኝም ይችላል፣ በልሳን እየጸለይኩ የማሳልፈው ጊዜ እና ለመተርጎም ያለኝ እምነት የዚህ አካል ነው።

በልሳን መጸለይ መንፈሰ ቅዱሰን ለመቀበላችሁ ማረጋገጫ ከመሆን ባለፈ በብዙ ምክንያቶች እጅግ በጣም አሰፈላጊ ነው፤ የዘወትር ተግባራችሁ አካል ሊሆን ይገባል። አዕምሮአችሁን ከጥርጣሬ እና ፍርሃቱ ጋር አልፋችሁ ከልባችሁ ወደ እግዚአብሔር የቀጥታ ግንኙነት ለማድረግ -የምትጠቀሙበት መንገድ ነው። በተቀደሰ እምነታችሁ ያንጻችሁአል፣ የተደበቀውን የእግዚአብሔር እውቀት ትገልጣላችሁ፣ ሁላችሁም በዚህ ውሰጥ መፍሰሰ እንድትችሉ፣ እምነታችሁ እንዲገለጥ እና በልሳን የመጸለይ ጠቀሜታዎችን በሙሉ እንድትቀበሉ እጸልያለሁ።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. የይሁዳ መልዕክት 1፡20 በመንፈስ ቅዱስ በመጸለይ የምናገኘው ትልቅ ጥቅም ምንድን ነው?

   **ይሁዳ 1፡20** *እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ፥ ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ ሃይማኖታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ በመንፈስ ቅዱስም እየጸለያችሁ።*

2. የሐዋርያት ሥራ 2፡4 በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ምን ያህሉ ሰዎች ናቸው?

   **የሐዋርያት ሥራ 2፡4** *በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።*

3. የሐዋርያት ሥራ 2፡4 በመንፈስ ቅዱስ በመሞላታቸው ምን አደረጉ?

4. 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡14 በልሳን ስትጸልዩ የትኛው አካላችሁ ይጸልያል?

   **1ኛ ቆሮንቶስ 14፡14** *በልሳን ብጸልይ መንፈሴ ይጸልያል አእምሮዬ ግን ያለ ፍሬ ነው።*

5. 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡2 በልሳን የሚጸልዩ የሚናገሩት ለማን ነው?

   **1ኛ ቆሮንቶስ 14፡2** *በልሳን የሚናገርሰ ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርም፤ የሚያስተውለው የለምና፥ በመንፈስ ግን ምሥጢርን ይናገራል።*

6. 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡2 አንድ ሰው በልሳን ሲጸልይ የሚናገረውን ሌሎች ሰዎች ይረዱታል?

7. 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡2 በልሳን ስትጸልዩ መንፈሳችሁ ምን እየተናገረ ነው?

8. 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡4 በልሳን ስትጸልዩ ምን ታደርጋላችሁ?

   **1ኛ ቆሮንቶስ 14፡4** *በልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል፤ ትንቢትን የሚናገር ግን ማኅበሩን ያንጻል።*

9. 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡16 በልሳን ስትጸልዩ ምን ታደርጋላችሁ?

   **1ኛ ቆሮንቶስ 14፡16** *አሁን ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ወደ እናንተ መጥቼ በልሳኖች ብናገር፥ በመግለጥ ወይም በእውቀት ወይም በትንቢት ወይም በትምህርት ካልነገርኋችሁ ምን እጠቅማችኋለሁ?*

# ጠቋሚ መልሶች

1. የይሁዳ መልዕክት 1፡20 በመንፈስ ቅዱስ በመጸለይ የምናገኘው ትልቅ ጥቅም ምንድን ነው?
   **በመንፈስ ቅዱስ ስጸልይ እራሴን እንጻለሁ።**

2. የሐዋርያ ሥራ 2፡4 በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ምን ያህሉ ሰዎች ናቸው?
   **ሁሉም።**

3. የሐዋርያት ሥራ 2፡4 በመንፈስ ቅዱስ በመሞላታቸው ምን አደረጉ?
   **በልሳኖች ተናገሩ።**

4. 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡14 በልሳን ስትጸልዩ የትኛው አካላችሁ ይጸልያል?
   **መንፈሴ ይጸልያል።**

5. 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡2 በልሳን የሚናገር ሰው የሚናገረው ለማን ነው?
   **ለእግዚአብሔር።**

6. 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡2 አንድ ሰው በልሳን ሲጸልይ የሚናገረውን ሌሎች ሰዎች ይረዱታል?
   **አይረዱትም።**

7. 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡2 በልሳን ስትጸልዩ መንፈሳችሁ ምን እየተናገረ ነው?
   **ምስጢር፣ በእግዚአብሔር እና በእኔ መሃል ያለውን ቅርበት።**

8. 1ኛ ቆሮቶስ 14፡4 በልሳን ስትጸልዩ ምን እያደረጋችሁ ነው?
   **እራሴን እያነጻሁ (እያነጽኩ)።**

9. 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡16 በልሳን ስትጸልዩ ምን ታደርጋላችሁ?
   **እየባረኩ እና እግዚአብሔርን እያመሰገንኩ።**

# የተሟላ ወንጌላዊ
# ደቀ መዝሙርነት

ክፍል 2

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| 1.ራስ - ወዳድነት የሐዘን ሁሉ ምንጭ | 2- 82 |
| 2.በእግዚአብሔር ቃል እንዴት ማሰላሰል እንደሚቻል | 2- 86 |
| 3.አእምሮን ማደስ | 2- 89 |
| 4.የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አስፈላጊነት | 2- 93 |
| 5.ነፃ መውጣት | 2-100 |
| 6.የአማኝ ስልጣን | 2-105 |
| 7.ፈውስ ያለው በስርየት ነው | 2-111 |
| 8.የፈውስ እንቅፋቶች | 2-116 |
| 9.ይቅርታ ስለማድረግ | 2-122 |
| 10.ጋብቻ - ክፍል 1 | 2-129 |
| 11.ጋብቻ - ክፍል 2 | 2-133 |
| 12.እንደ እግዚአብሔር ያለ ፍቅር - ክፍል 1 | 2-140 |
| 13.እንደ እግዚአብሔር ያለ ፍቅር - ክፍል 2 | 2-145 |
| 14.ፋይናንስ - ክፍል 1 | 2-151 |
| 15.ፋይናንስ - ክፍል 2 | 2-155 |
| 16.ጸሎታችሁ ያልተመለሰ ሲመስል ምን ማድረግ እንዳለባችሁ | 2-159 |

# ትምህርት 1

# ራስ - ወዳድነት የሐዘን ሁሉ ምንጭ

## በአንድሩ ዉማክ

አብዛኛው የህይወት ገጠመኞቻችን ምንጫቸው ራስ-ወዳድነት ነው። በመጽሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ 13 ራሳችሁ እንብባችሁ ካልሆነ በቀር ሌላ ማንም ሰው ቢነግራችሁ የማታምኑትን ቃል ታገኛላችሁ። ቁጥር 10 እንዲህ ይላል *“በትዕቢት ጠብ ብቻ ይሆናል። ጥበብ ግን ምክርን በሚቀበሉ ዘንድ ናት”።* ይህ ቃል ብዙ ሰዎችን አንድ ጥያቄ እንዲያነሱ ያደርጋል “ቆይ፣ ቁጣ እና ጠብ የሚመጣው በትዕቢት ብቻ አይደለም። ምሳሌ 17፡14 የጠብ መጀመሪያ እንደ ውኃ አፈሳሰስ ነው ይላል፣ ስለዚህ ከትዕቢት ሌላ የጠብ መነሻ የሆኑ ብዙ ምክንያቶች አሉ። ሰው በሆነ ምክንያት ሊያስቀይመኝ ይችላል” ይላሉ። ሌሎች ደግሞ “ባህሪዬ እንዲህ … ነው፣ ስፈጠር እንዲህ ዓይነት ሰው ነኝ” ሊሉ ይችላሉ። ነገር ግን አይደለም፣ የእግዚአብሔር ቃል በትዕቢት ብቻ ጠብ ይሆናል ይላል። ትዕቢት ከጠብ ዋና ዋና ምክንያቶች አንዱ ሳይሆን ብቸኛው ምክንያት ነው። አንዳንድ ሰዎች ይህን ለመቀበል ሊቸገሩና “በእርግጥ ብዙ ዓይነት ችግሮች አሉብኝ፣ ትዕቢት ግን የለብኝም። እንዲያውም እኔ እራሴን ዝቅ ስለማደርግ በምንም ምክንያት በትዕቢተኛነት የሚከሰኝ ሰው አይኖርም” ይላሉ።

እንግዲህ ትዕቢት ምን ማለት እንደሆነ ዳግመኛ ማጤን ሊኖርብን ነው። ትዕቢት እራስን ከሌሎች የተሻልኩ ነኝ ብሎ ማሰብ ሳይሆን ነገር ግን በቀላል ቋንቋ እራስን የሁሉ ነገር ማዕከል አድርጎ ማዬት ነው። ራስ ወዳድነት የትዕቢት ሁሉ ሥር መሰረት ነው። በኦሪት ዘኁልቅ 12፡2 የሙሴ ወንድምና እህት የሆኑት አሮንና ማርያም፣ ሙሴ ከነገዱ ውጭ ኢትዮጵያዊት ሴት በማግባቱ ምክንያት ሊቃወሙት እና ሊገስጹት ተነሱ፣ እንዲህም አሉ *“በውኑ እግዚአብሔር በሙሴ ብቻ ተናግሯልን? በእኛስ ደግሞ የተናገረ አይደለምን?”።* የእግዚአብሔር ቃል ግን በቁጥር 3 ሙሴም በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ ትሑት ሰው እንደ ነበረ ይናገራል። እነርሱ በተናገሩት ቃል ቂም ከመያዝ ይልቅ ለሁለቱም ይጸልይላቸውና ይማልድላቸው ነበር።

ሙሴ በምድር ላይ ካሉ ሰዎች ይልቅ እጅግ ትሁት ሰው ነበረ የሚለውን ቃል ቆም ብላችሁ አሰቡት። በዛ ዘመን ምን ያህል ሰዎች በምድር ላይ እንደነበሩ ባናውቅም ነገር ግን በእርግጠኝነት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ነበሩ፣ እናም ሙሴ ከሁሉም ሰዎች ይልቅ ትሁት ነበረ። ይህንን አረፍተ ነገር ይበልጥ አስገራሚ የሚያደርገው የዚህ ቃል ጸሃፊ ራሱ ሙሴ መሆኑ ነው። ብዙ ሰዎች በእውነት ትሁት ከሆንክ ትህትናህ ለአንተ ለራስህ አይታወቅህም ይላሉ። ይህ እንዲያውም በተቃራኒው የዕብሪተኝነት መለያ ነው። ትዕቢት እራሳችሁን ከሌሎች ሁሉ እንደምትበልጡ ወይም ከሌሎች ሰዎች ያልተሻላችሁ አድርጋችሁ ማሰብ ሳይሆን፣ ራስ-ወዳድነት ነው። ይህ ማለት  አንድ በትር ብንወስድ እና አንደኛው ጫፍ ራስን ዝቅ ማድረግ ሌላኛው ጫፍ ደግሞ ትዕቢተኛነት ነው ብለን እንደማሰብ ነው። የአንድ ነገር ሁለት የተለያዩ ባህሪያት ወይም መገለጫዎች እንደማለት ነው፤ ነገር ግን ሁለቱም አንድ በትር ላይ ናቸው። ይህ ነው ራስ ወዳድነት። ቁም ነገሩ እራሳችሁን ከሌሎች የተሻላችሁ ወይም እራሳችሁን ከሌሎች ያነሳችሁ አድርጎ ማሰባችሁ ላይ አይደለም፣ እራስን ማዕከል ማድረግ ፍጹም ራስ ወዳድነት ነው። ማንኛውም ነገር በዚህ ማጣሪያ ውስጥ መታየት አለበት። አይን-አፋር ፣ አንገቱን የደፋ የምንለው ሰው ስለ እራሱ ብቻ የሚያስብ ስለሆነ በጣም ኩሩ እና ራስ ወዳድ ሰው ነው።

የመልዕክቴ ዋናው ነጥብ ራስ ወዳድነት በእርግጥ የትዕቢት መሰረት ነው የሚል ነው፤ ይህን ቃል እንደገና ከምሳሌ 13፡10 *“በትዕቢት ጠብ ብቻ ይሆናል”* ከሚለው ጋር አንድ ላይ ከተመለከትነው በቁጣ የሚያንገበግበን የእኛ ራስ - ወዳድነት እንጂ ሌሎች በእኛ ላይ ያደረሱብን በደል አይደለም። ሰዎች ለሚያደርጉት ነገር ምላሽ እንድንሰጥ የሚያደርገን ራስ ወዳድነት ነው ማለት ነው። ሰዎች እንዳያስቀይሟችሁ ወይም በተሳሳተ መንገድ እንዳያሰቡአችሁ ማድረግ አትችሉም። እምነት ሌሎችን ሰዎች ለመቆጣጠር ሳይሆን እራሳችሁን ለመግዛት እና በውስጣችሁ ያለውን ነገር መቆጣጠር እንድትችሉ ያግዛችኋል። እንዲህ ከሆነ ሰዎች ምንም ቢያደርጉባችሁ ግድ አይሰጣችሁም።

ኢየሱስ በመስቀል ላይ ወደ ሚሰቅሉት ሰዎች መለስ ብሎ በማዬት *"አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው"* አለ። እርሱ እራሱን ተቆጣጠረ እንጂ የሚሰቅሉትን ሰዎች አልተቆጣጠረም። ብስጩና ቁጡ የሚያደርገን ራስ ወዳድነት ነው። ኢየሱስ የመጣው ለራሱ ጉዳይ አይደለም፣ ነገር ግን ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና፣ ሊያድነን ወደ አለም መጣ። በመስቀል ላይ ሆኖ በዛች የጣር ሰዓትም ቢሆን እንኳን እናቱን አሰበ፣ ለሚወደው ደቀመዝሙር እንዲንከባከባት አደራ ሰጠው። ኢየሱስ በፍርድ መጓደል ምክንያት በከባድ መከራ እና ስቃይ ውስጥ ሆኖ ለሚገጥመው ነገር ሁሉ ምህረት እንዲያደርግና በፍቅር እንዲሰራ ያደረገው "ራስ ወዳድ" አለመሆኑ ነው።

ቁጡ የሚያደርጋችሁ የእራሳችሁ ራስ ወዳድነት ነው። የእግዚአብሔር ቃል ለእራሳችሁ መሞታችሁን ማሰብ እንደሚገባ ይናገራል። ፊት ለፊቴ አንድ የሞተ ሰው ቢኖር፣ እኔም ተነስቼ ብገላምጠው፣ ብሰድበው፣ ብመታውም እንኳን ሙት ከሆነ አይመልስልኝም። በዙሪያችሁ ላሉት ነገሮች ምላሽ የምትሰጡበት መንገድ በዙሪያችሁ ካሉት ነገሮች የተነሳ ሳይሆን በእናንተ ውስጥ፣ ውስጣችሁ ባለው ምክንያት የተነሳ ነው። ዙሪያችሁ ያለውን ችግር ሁሉ ማስተካከል እና በመንገዳችሁ የሚያጋጥማችሁን ሁሉ ማስወገድ የምትችሉበት የእምነት ጥንካሬ መቼም ቢሆን ሊኖራችሁ አይችልም፣ ነገር ግን ከእራሳችሁ ጋር መምከርና መወሰን ትችላላችሁ። ኢየሱስን የሕይወታችሁ ጌታ አድርጋችሁ በመቀበል፣ እርሱን በመውደድ፣ ከእራሳችሁ ይልቅ መንግስቱንና ሌሎችን ሰዎች መውደድ የምትችሉበት ደረጃ ላይ መድረስ ትችላላችሁ። ይህን ባደረጋችሁ እና እራሳችሁን በተቆጣጠራችሁ ጊዜ ከህይወታችሁ ውስጥ ጠብ እና ጭቅጭቅ ምንጫቸው ይደርቃል።

እግዚአብሔር በህይወታችሁ ያደረጋቸውን እነዚህን ነገሮች ሁሉ መተግበር ከምትችሉባቸው ታላላቅ ቁልፎች ውስጥ አንደኛው፦ እግዚአብሔር መንግስቱን የሰጣችሁ ሰግብግብ እንድትሆኑ አለመሆኑን ማወቅና መገንዘብ ነው። እርሱ ይህን ሁሉ ያደረገው የግል ፍላጎቶቻችሁን በሙሉ ለሟሟላት አይደለም። ይልቁንም ህይወታችሁን በመተው እራሳችሁን መካድ በተማራችሁ ጊዜ በእርግጥ ስለ ህይወት ምንነት መረዳት ትጀምራላችሁ። ሌሎች ሰዎችን እና እግዚአብሔርን ከራሳችሁ ይልቅ አስበልጣችሁ መውደድ በጀመራችሁ ጊዜ ቁጣ እና ጠብ፣ ጥል እና ጥላቻን የመሳሰሉ በውስጣችሁ ያሉ መልካም ያልሆኑ ነገሮች መክሰምና መጥፋት ይጀምራሉ።

እነዚህን የነገርኳችሁን ጥቂት ነገሮች ተጠቅሞ እግዚአብሔር ልባችሁን በመክፈት፣ ሐዘንን የሚያመጣባችሁ የእራሳችሁ እራስ ወዳድነት መሆኑን እንዲያሳያችሁ ጸሎቴ ነው። ሌሎችን ሰበብ ከማድረግ ይልቅ እራሳችሁ ኃላፊነቱን ውሰዱ፣ ተጋፈጡ፣ በእግዚአብሔር ፊት እራሳችሁን በትህትና በማቅረብ ወደ እናንተ እንዲመጣ እና በህይወታችሁ ከፍ እንዲል ጠይቁት። በአሸናፊነት መጓዝ የምትችሉበት የድል ጎዳና ይህ ነው፡

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ማርቆስ 9፡33-34 እንብቡና ደቀመዛሙርቱ በቅፍርናሆም መንገድ ላይ የሚከራከሩት በምን ጉዳይ ነበር?

   **ማርቆስ 9፡33** *ወደ ቅፍርናሆምም መጣ። በቤትም ሆኖ። በመንገድ እርስ በርሳችሁ ምን ተነጋገራችሁ? ብሎ ጠየቃቸው። [34] እነርሱ ግን በመንገድ። ከሁሉ የሚበልጥ ማን ይሆን? ተባብለው ነበርና ዝም አሉ።*

2. ይህ በሁላችን ውስጥ ያለውን ራስ ወዳድነት ያሳያል?

3. ማርቆስ 9፡35 በዚህ ቃል መሰረት፣ መጀመሪያ መሆን የሚፈልገ ቢኖር ምን መሆን አለበት?

   **ማርቆስ 9፡35** *ተቀምጦም አሥራ ሁለቱን ጠርቶ። ሰው ፊተኛ ሊሆን ቢወድ ከሁሉ በኋላ የሁሉም አገልጋይ ይሁን አላቸው።*

4. በሉቃስ 22፡24-27 ያለውን የኢየሱስን ትምህርት በጥልቀት አብራሩ?

   **ሉቃስ 22፡24** *ደግሞም ማናቸውም ታላቅ ሆኖ እንዲቈጠር በመካከላቸው ክርክር ሆነ። [25] እንዲህም አላቸው። የአሕዛብ ነገሥታት ይገዙአቸዋል፥ በላያቸውም የሚሠለጥኑት ቸርነት አድራጊዎች ይባላሉ። [26] እናንተ ግን እንዲህ አትሁኑ፤ ነገር ግን ከእናንተ ታላቅ የሆነ በመካከላችሁ እንደ ታናሽ፥ የሚገዛም እንደሚያገለግል ይሁን። [27] በማዕድ የተቀመጠ ወይስ የሚያገለግል ማናቸው ታላቅ ነው? የተቀመጠው አይደለምን? እኔ ግን በመካከላችሁ እንደሚያገለግል ነኝ።*

5. ምሳሌ 13፡10 ጠብን የሚያመጣ ብቸኛው ምክንያት ምንድን ነው?

   **ምሳሌ 13፡10** *በትዕቢት ጠብ ብቻ ይሆናል፤ ጥበብ ግን ምክርን በሚቀበሉ ዘንድ ናት።*

6. ገላትያ 2፡20 ሕይወታችንን እንዴት መኖር አለብን?

   **ገላትያ 2፡20** *ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው።*

7. ማቴዎስ 7፡12 የራስ ወዳድነት ማስወገጃ ፍቱን መፍትሔ ምንድን ነው?

   **ማቴዎስ 7፡12** *እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ ሕግም ነቢያትም ይህ ነውና።*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ማርቆስ 9፡33-34 አንብቡና ደቀመዛሙርቱ በቅፍርናሆም መንገድ ላይ የሚከራከሩት በምን ጉይ ነበር?
**ከሁሉ የሚበልጥ ማን ነው? በሚል ይከራከሩ ነበር።**

2. ይህ በሁላችን ውስጥ ያለውን ራስ ወዳድነት ያሳያል?
**አዎ።**

3. ማርቆስ 9፡35 በዚህ ቃል መሰረት፣ መጀመሪያ መሆን የሚፈልግ ቢኖር ምን መሆን አለበት?
**የሁሉም አገልጋይ ይሁን።**

4. በሉቃስ 22፡24-27 ያለውን የኢየሱስን ትምህርት በጥልቀት አብራሩ?
**እነርሱም በሚመጣው መንግሰት ከመካከላቸው ማን ታላቅ ሆኖ እንደሚቈጠር ይከራከሩ ነበር። ኢየሱስም መልሶ "በዚህ ዓለም ነገስታትና ሃያላን ሰዎች ሕዝባቸውን ይገዛሉ፣ ሆኖም ግን "የሕዝብ ወዳጅ" ተብለው ይጠራሉ። በእናንተ መካከል ግን ከፍ ያለ ሰው ዝቅ ያለውን ደረጃ ይያዝ፣ መሪም እንደ አገልጋይ ይሁን። በተለምዶ መሪው ከፍ ያለ ቦታ ላይ ይቀመጥና አገልጋዮች ያገለግሉታል። እዚህ ግን እንደዛ አይደለም! እኔ እያገለገልኳችሁ ነው።"**

5. ምሳሌ 13፡10 ጠብን የሚያመጣ ብቸኛው ምክንያት ምንድን ነው?
**ትዕቢት።**

6. ገላትያ 2፡20 ሕይወታችን እንዴት መኖር አለብን?
**በክርስቶስ እምነት (በክርስቶስ ባለ እምነት)፣ የእራሳችንን ጥንካሬ ወይም ድክመት ማዕከል ያላደረገ።**

7. ማቴዎስ 7፡12 የራስ ወዳድነት ማሰወገጃ ፍቱን መፍትሔ ምንድን ነው?
**እግዚአብሔርን ማዕከል ማድረግ፣ ሌሎችንም ማዕከል ማድረግ። ለእኛ እንዲደረግልን የምንፈልገውን ለሌሎች ሰዎችም ማድረግ።**

## ትምህርት 2

# በእግዚአብሔር ቃል እንዴት ማሰላሰል እንደሚቻል

## በዶን ክሮው

ማሰላሰል የሚለው ቃል "በጥልቀት ማሰብና መመርመር፣ ማቀድና ማሰላት፣ ማውጣትና ማውረድ" ማለት ነው። ይህ ቃል በግሪክ "አንድን ነገር በአዕምሮ ውስጥ ማንሸራሸር" የሚለውን የሚያመላክት ሲሆን በተጨማሪም በምናብ ማየት የሚል ትርጉምን ይዟል።

መጽሐፍ ቅዱስን የምናሰላስልበት ሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች "እስተሳሰባችን በትክክለኛ እውቀት ላይ የተመሰረተ ለማድረግ ማለትም አዕምሮን ማደስ ብለን ለምንጠራው እና በቃሉ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ለማድረግ" ይህም በጸሎት፣ በምስጋና፣ እርእያነቱን ለመከተልና ስለ እርሱ ለማሰብ ነው።

አርዕስት መርጦ በማጥናት ዘዴ ማሰላሰል ይቻላል፡- ይህም አንድ የተመረጠን ርዕሰ በጥልቀት መመርመር ነው። ለምሳሌ "ጥምቀት" የሚለውን ቃል እንውሰድ። ይህንን ቃል ከግሪክ፣ ከዕብራውያን ወይም ከአንድ ጥሩ ዲክሽነሪ በመፈለግ ማብራራት እንችላለን። ቃሉ የመጣበትን ምንጭ ወይም ስረ-መሰረቱን ፈልጉ። የቃሉን አውድ በጥንቃቄ መርምሩ፣ አገባብና አጠቃቀሙን ለማየትና ለማወቅ በምታደርጉት ጥናት ሌሎች ቃሎችን ማወቅ ትጀምራላችሁ ከእነዚህም መካከል፡- ስርዬት (ሐዋ 2፡28)፣ ንስሐ (ሐዋ 2፡38)፣ እምነት (ማር 16፡16)፣ ህሊና (1ኛ ጴጥ 3፡21)፣ የጌታን ስም መጥራት (ሐዋ 22፡16) ወዘተ ይገኙበታል።

በውስጣችሁ የሚነሱ ጥያቄዎች እና ቃሉ የሚያነሳቸውን ጥያቄዎች ለምሳሌ፡- ከጥምቀት በፊት ሊሟሉ የሚገባቸው መመዘኛዎች አሉ? የጥምቀት ጥቅም ምንድን ነው? መቼ ነው መጠመቅ ያለብን? በምን አይነት ጊዜ ውስጥ? የሚሉትን መመርመር ያስፈልጋችኋል።

ቃልን በመግለጥ ጥናት ማሰላሰል ይቻላል፡- ይህም ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ አንደኛውን መጽሐፍ፣ ቃል በቃል በማንበብ የማጥናት ዘዴ ነው። የዚህም ቁልፍ ለረጅም ጊዜ አንድን መጽሐፍ በጥልቀት በመመርመርና በማሰብ ይዘቱን (ምዕራፎቹንና ቃሎቹንም) ከራሳችሁ ጋር የምታዋህዱበት ዘዴ ነው።

በቃላት ጥናት ውስጥ ማሰላሰል ይቻላል፡- አንዳንድ ቃሎች ምን ማለት ናቸው? ማመን ምን ማለት ነው? ጌታ የሚለው ቃል ምን ማለት ነው? ኢየሱስ የሚለው ቃል ምን ማለት ነው? ክርስቶስ የሚለውስ ምን ማለት ነው? መጽደቅ ምን ማለት ነው፣ ወዘተ።

ከመጽሐፍ ቅዱስ አንቀጾች በማጥናት ማሰላሰል ትችላላችሁ፡- አንቀጽ በአንድ መጽሐፍ ውስጥ ንዑስ ሃሳብ የያዘ የጽሑፍ ክፍል ሲሆን በውስጡም ብዙ አረፍተ ነገሮችን ይይዛል። አንድ ደራሲ የጽሑፉን ርዕሰ ጉዳይ በሚቀይርበት ጊዜ በአብዛኛው በአዲስ አንቀጽ ይጀምራል።

ቃሉን በምናሰላስልበት ጊዜ፣ እንደ ጥያቄ ምልክት ዓይነት ሥርዓተ ምልክቶችን ማስተዋል ተገቢ ነው። ይህ ጥያቄ ለምን ተጠየቀ? ከዐውዱ ወይም ይዘቱ ጋር እንዴት አብሮ ይሄዳል፣ ወዘተ?

በመጽሐፍ ቅዱስ ማሰላሰል ሲባል ቃላትን መመልከት አይደለም። ይልቁንም ከቃሉ ጀርባ ወይም ቃሉ ውስጥ ያለው እግዚአብሔር መሆኑን ምንጊዜም መዘንጋት የለብንም።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ማሰላሰል የሚለው ቃል ምን ማለት ነው?

2. መጽሐፍ ቅዱስን የምናሰላስልበት ሁለት ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

3. በአርዕስት የማጥናት ዘዴ ምንድን ነው?

4. ቃልን በመግለጥ የማጥናት ዘዴ ምን ማለት ነው?

5. ሉቃስ 6፡46 ጌታ የሚለው ቃል ምን ማለት ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?

   **ሉቃስ 6፡46** *ስለ ምን፦ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ ትሉኛላችሁ፥ የምለውንም አታደርጉም?*

6. ማቴዎስ 1፡21 "ኢየሱስ" የሚለው ቃል ምን ማለት ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?

   **ማቴዎስ 1፡21** *ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ።*

7. ሉቃስ 23፡1-2 "ክርስቶስ" የሚለውስ፣ ምን ማለት ይመስላችኋል?

   **ሉቃስ 23፡1** *ሁሉም በሞላው ተነሥተው ወደ ጲላጦስ ወሰዱትና፦ [2] ይህ ሕዝባችንን ሲያጣምም ለቄሣርም ግብር እንዳይሰጥ ሲከለክል ደግሞም። እኔ ክርስቶስ ንጉሥ ነኝ ሲል አገኘነው ብለው ይከሱት ጀመር።*

8. አንቀፅ ምንድን ነው?

9. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቃላትን ፍለጋ ሳይሆን ____ ፍለጋ ነው?

# ጠቋሚ መልሶች

1. ማሰላሰል የሚለው ቃል ምን ማለት ነው?
   **በጥልቀት መመርመር፣ ማሰብ፣ ወይም አንድን ነገር በአዕምሮ ውስጥ ማንሸራሸር።**

2. መጽሐፍ ቅዱስን የምናሰላስልበት ሁለት ምክንያቶች ምንድን ናቸው?
   **ትክክለኛ እውቀት እንዲኖረን (አዕምሮን ለማደስ)፣ ከቃሉ ጀርባ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት (ስለ እርሱ በመመርመር፣ እርአያነቱን ለመከተልና ስለ እርሱ ለማሰብ ነው)።**

3. በእርዕሰት የማጥናት ዘዴ ምንድን ነው?
   **ከመጽሐፍ ቅዱስ እርዕሰት በመምረጥ ማጥናትና ማሰብ።**

4. ቃልን በመግለጥ የማጥናት ዘዴ ምን ማለት ነው?
   **ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድን መጽሐፍ ቃል በቃል የማጥናት ዘዴ ነው።**

5. ሉቃስ 6፡46 ጌታ የሚለው ቃል ምን ማለት ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?
   **የምንታዘዝለት ሰው (እንደ አለቃ)።**

6. ማቴዎስ 1፡21 “ኢየሱስ” የሚለው ቃል ምን ማለት ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?
   **ሌሎችን ከኃጢአት የሚያድን፣ አዳኝ።**

7. ሉቃስ 23፡1-2 “ክርስቶስ” የሚለውስ፣ ምን ማለት ይመስላችኋል?
   **ንጉስ ሊሆን የተቀባ።**

8. አንቀፅ ምንድን ነው?
   **በጽሑፍ ውስጥ የሚገኝ አንድ የሃሳብ ክፍል።**

9. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቃላትን ፍለጋ ሳይሆን ____ ፍለጋ ነው?
   **ከቃሉ ጀርባ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት።**

## ትምህርት 3

# አእምሮን ማደስ

### በዶን ክሮው

ዛሬ ደግሞ አእምሮን ስለማደስ የምናወራ ሲሆን ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በማንበብ እንጀምራለን። ፊሊጵስዩስ 4፡8 እንዲህ ይላል፣ *“በቀረውሰ ወንድሞች ሆይ፣ እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ፣ ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ፣ ጽድቅ ያለበትን ነገር ሁሉ፣ ንጹህ የሆነውን ነገር ሁሉ፣ ፍቅር ያለበትን ነገር ሁሉ፣ መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ፣ በጎነት ቢሆን ምስጋናም ቢሆን፣ እነዚህን አስቡ”።* ሐዋርያው ጳውሎስ ልናስባቸው የሚገቡን ነገሮች ያሉ መሆኑን ዘርዝሮ ይነግረናል። በሌላ አነጋገር ሃሳባችንን ወይም ልናስበው የሚገባንን መምረጥ እንችላለን ማለት ነው። እንደ ሮሜ መጽሐፍ ምዕራፍ 7 ቁጥር 22 እና 23፣ ሁላችንም፣ አንዳንድ ጊዜ ከእግዚአብሐሔር ቃል ተቃራኒ የሆኑ ሃሳቦችን እንደምናስብ እናውቃለን። ይህም የሆነው በውስጣችን የሚዋጋን የኃጢአት ህግ አእምሯችንን ስለሚያጠቃ ወይም በአእምሮአችን ላይ ተጽዕኖ ስለሚፈጥር ነው። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በፊሊጵስዩስ መልዕክት ይህንን ሃሳብ ዝም ብለን በማስተናገድ እላያችን ላይ ጎጆ እንዲቀልስ መፍቀድ እንደሌለብንና ይልቁንም ማሰብ የሚገባንን ወይም የምናስበውን ነገር መምረጥ እንደምንችል ያስተምረናል። መጽሐፈ ምሳሌ 23፡7 ደግሞ ሰው በልቡ የሚያስበውን ያንኑ እንደሆነ ይናገራል። ስለዚህ በእርግጥ የምናስበው ነገር ዋጋ አለው ማለት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በሮሜ 12፡1 እና 2፣ የሚከተለውን ይነግረናል፡- *“እንግዲህ ወንድሞች ሆይ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሰዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጅ ይህን ዓለም አትምሰሉ”።* የእግዚአብሔር ቃል፣ አእምሮአችን በማደስ መለወጥ እንደምንችል ይናገራል። የሰው ልጅ አፖሎ በተባለችው የጠፈር መንኮራኩር ወደ ጨረቃ ባደረገው የመጀመሪያ ጉዞ፣ ጠፈርተኞቹ በየአስር ደቂቃው የአቅጣጫ ማስተካከያ ያደርጉ እንደ ነበር ታውቃላችሁ? ወደ ጨረቃ የተጓዙበት መንገድ እንደ መጋዝ ጥርስ ዓይነት ጠመዝማዛ ወይም “ዚግዛግ” ነበር። የታቀደላቸው የማረፊያ ክልል 500 ማይል ወይም 800 ኪሎ ሜትር የነበረ ሲሆን ከዚህ ክልል በጥቂት ሜትሮች ርቀው ቢያርፉም ሙሉ ጉዞው ግን የተሳካ ነበር። እንደዚሁ እኛም ሰውነታችንን ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ሕያውና ደስ የሚያሰኝ መሰዋዕት አድርገን ለማቅረብ አንድ አቅጣጫ ወስነን ያንኑ መከተል ይኖርብናል። የሕያው መሰዋዕት ችግር አንዳንድ ጊዜ ከመሰዊያው ላይ መንሸራተቱ ወይም ዞር ማለቱ ነው። ስለዚህ የአቅጣጫ ማስተካከያ ማድረግ ተገቢ ነው። ለዚህም - “አባት ሆይ ታስፈልገኛለህ፤ እፈልግሃለሁ መንገድህን አሳየኝ!” የሚል ልብ ሊኖረን ይገባል።

ሙሉ ውሳኔ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ውጤታማና አሸናፊ የክርስትና ህይወት፣ በሂደት በአዕምሮ መታደስ መለወጥን ይጠይቃል። የዓለም የሆነውን ከንቱ ነገር ካልፈለግን በቀር እንደ ዓለም ማሰብ የለብንም። ፊሊጵስዩስ 4፥8ን ስናነብ የምናስተውለው፣ የምናስበውን መምረጥ መቻላችንን ነው። ፍቅር የሆነውን ሁሉ፣ ቀጥተኛ፣ የምስራች የሆነውን፣ በነዚህ ነገሮች ላይ ማሰብ ይኖርባችኋል። በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔርን ቃል በበራቸው መቃን እና በልብሶቻቸውም ላይ ጽፈው ያስቀምጡት ነበር። ምንጊዜም ከፊታቸው አይጠፋም። እግዚአብሔር ቃሉን በቀንም በማታም እንዲያስቡና እንዲጫወቱት፣ ቃሉ የሚለውንም ነገር እንዲያስተውሉና እንዲጠብቁት አዟቸው ነበር። ይህንንም ለልጅ ልጆቻቸው ያስተላልፉ ነበር። እለት እለት የምናስባቸው ነገሮች ላይ ማተኮር እጅግ ጠቃሚ ነው። የተሳካና የድል ህይወት ይኖረን ዘንድ የእግዚአብሔርን ቃል ዘወትር፣ ሁሌም በፊታችን መጠበቅ እጅግ አስፈላጊ ነው። እንግዲህ የምስራች የሆነውን፣ ፍጹምና ፍቅር የሆነውን፣ ማሰብ ካልቻልን ከእግዚአብሔር ከሆነው ነገር፣ ከመንፈሳዊውም ነገር ሁሉ በተቃራኒው እየተጓዝን ነው ማለት ነው። ሮሜ 8፡6 *“ሥጋን ማሰብ ሞት ነው፤ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ህይወትና ሰላም ነው”* ይላል። ስለ እግዚአብሔር መንፈስ ማሰብ ሰላምና ህይወት ነው። ነገር ግን በዓለም ስላሉት ነገሮች ማሰብ በጀመርን ጊዜ፣ ስለ እመንዝራነት፣ ገንዘብ፣ ሞኞች፣ የመሳሰሉትን ማሰብ ስንጀምር በህይወታችን

ምን እንደሚፈጠር ታውቃላችሁ? ሰው በልቡ እንዳሰበ እንዲሁ ነው። እነኝህን ነገሮች ማድረግ ወይም መፈጸም እንጀምራለንና በህይወታችን ላይ ጥፋትን ያመጡብናል። ለአንድ አማኝ እውነተኛው መንፈሳዊ ውጊያ ከሰይጣን ጋር የሚደረግ ወይም እርሱን መገሰጽና ማባረር አይደለም። አንዳንድ ጊዜ በእርግጥ ይህም አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ አለ። ነገር ግን መንፈሳዊው ውጊያ በዋነኛነት የምናሰበው ሃሳባችንና የምንኖርበት ወይም የቆምንበት ሃሳብ መሰረት ላይ ያለ ውጊያ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ፣ በእግዚአብሔር የሚታመን እና የሚደገፍን ሰው እግዚአብሔር ፍጹም በሰላም እንደሚጠብቀው በኢሳይያስ 26፡3 ይናገራል። ሮሜ 12 እንደሚናገረው ደግሞ በቀን ውስጥ መንገዳችንን በተደጋጋሚ እንድናስተካክል የሚያደርጉን ብዙ አጋጣሚዎች እንዳሉ እናውቃለን። ታዲያ "አባት ሆይ እነዚህ የተሳሳቱ ሃሳቦች ናቸው። መለሰ ብዬ አእምሮዬን ማደስ እና ፍቅር የሆኑትን ነገሮች፣ ፍጹም እና መልካም ወሬ ያለባቸውን ነገሮች ማሰብ ይገባኛል" ማለት ያስፈልጋል።

እንግዲህ ከአቅማችሁ በላይ ሆኖ የተቆጣጠራችሁ ነገር ካለ፣ በእሰራት ውስጥ ከሆናችሁ፣ ማሰብ የማይገባችሁን እያሰባችሁ ከሆነ፤ ፈጥናችሁ ወደ እራሳችሁ ተመለሱ፣ እራሳችሁን በመግዛት ቆም ብላችሁ አስተውሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ወደ እግዚአብሔር ከቀረብን እርሱ ወደ እኛ እንደሚቀርብ ይናገራል። ጠላታችን ከተቃወምነው ከእኛ ይሸሻል። በእኔ ሕይወት ውስጥ ነገሮች ከእጄ ያመለጡበት እና የመንፈስ ጭንቀት ውስጥ የገባሁባቸው ጊዜያት ነበሩ። በእነዚያ ጊዜያት ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ማንሳትና ቁጭ ብሎ ቃል በማንበብ "ጌታ ሆይ አንተ ስለ እኔ የተናገርከው መልካም ነው፣ አንተ "ነህ ያልከኝን" ነኝ። ጥንካሬዬ አንተ ነህ" ብሎ መናገር እጅግ ከባድ ነበር፤ አሸናፊነታችሁ እንደዚህ ቀላል መሆኑን አስባችሁታል? መናገር ያለባችሁ "ጠላት በእኔ ላይ እንዲያደርግ ዝም ያልኩትን ሁሉ አሁን እቃወማለሁ፣ አረፍ ብዬ መጽሐፍ ቅዱሴን እከፍታለሁ፣ በገጾቹ ውስጥ ያሉትን ፊደሎች ለማንበብ አይደለም፣ ነገር ግን ከቃሉ ጀርባ ያለው አምላኬ ጋር እገናኛለሁ። አእምሮዬም ከእርሱ ጋር እንዲሆን አደርጋለሁ። ጌታ ሆይ አንተ ስለ እኔ የተናገርከው ይህንን ነው፣ ይቅር እንደተባልኩ ነግረኸኛል። እንደነጻሁ ነግረኸኛል። ከፍቅርህ ሊለየኝ የሚችል ምንም ነገር እንደሌለ ነግረኸኛል"። አረፍ ብላችሁ በተቀመጣችሁበት እግዚአብሔር ያደረገላችሁን መልካሞቹን ነገሮች ማሰብ በጀመራችሁ ጊዜ፣ በጥቂት ጊዜ ውስጥ እነዚያን ሌሎቹን ነገሮች መርሳት ትጀምራላችሁ።

ይህን ሰዕላዊ በሆነ መልኩ ላቅርበው። አንድ ቀን፣ አንድ ሰው እንዲህ በማለት ጥያቄ እነሳልን፣ "አሁን አንድ ነገር እንድታደርጉልኝ እጠይቃችኋለሁ፣ ለሚቀጥሉት አስር ደቂቃዎች ስለ ሐምራዊ ዝሆኖች እንዳታስቡ እጠይቃችኋለሁ" አለ። ምን እንደተፈጠረ ታውቃላችሁ? ሁላችንም በቀጣዮቹ አስር ደቂቃዎች ስለ ሐምራዊ ዝሆኖች ማሰብ ጀመርን። እርሱም እንዲህ ሲል ሌላ ቀጣይ ጥያቄ አቀረበልን "የአሜሪካ የነጻነት ሐውልት ቀለም ምን ዓይነት ነው?" ከእኛም አንደኛው አረንጓዴ አለ። "የነጻነት ሐውልት የትኛውን እጇን ነው ከፍ አድርጋ ያነሳችው?" ሲል ጠየቀ። ሁለተኛው መላሽ ቀኝ እጇን ነው አለ። በመቀጠል ጠያቂአችን "በቀኝ እጇ የያዘችውስ ምንድን ነው?" ችቦ ነው ሲል መለሰ ሌላው። ጠያቂአችን መለሰ አለና "ስለ ሐምራዊ ዝሆኖች የነበሯችሁ ሃሳቦች የት ገቡ?" ሲል ጠየቀ፣ የሉም ሄደዋል። አስተዋላችሁ "እንደዚህ ዓይነት ሃሳብ አታስብ" ስለተባላችሁ ማሰብ አታቆሙም፣ ምክንያቱም ማሰባችሁን ማቆም እንደማትችሉ ታውቃላችሁ። በእርግጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የሚነግረንም ይህንኑ ነው። እነዛን ሌሎች ሃሳቦች በእግዚአብሔር ሃሳብ ቀይሩ ይለናል። ሌሎቹ ሃሳቦች ወደ አዕምሮአችን ተመልሰው በመምጣት ሲያስቸግሩን ወዲያውኑ አዲሱን ማንነታችን በማስታወስ ወደ ጌታ ዘወር ማለትና መለሰ ብለን እርሱን ማዬት፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች ውስጥ ካሉት ቃላት ሳይሆን ከቃሉ ጀርባ ያለውን እግዚአብሔርን ማግኘት ያሰፈልጋል። በዚህ መልኩ አእምሮአችንን በእርሱ እና በመንፈሳዊ ነገሮች ላይ ባደረግን ጊዜ፣ የእግዚአብሔር ሰላምና ህይወት የሚሰጠውን ለውጥ ማዬት እንደምንጀምር መጽሐፍ ቅዱስ በሮሜ 8፥6 ይናገራል። ወዳጆች፣ እነዚህን በማሰብ ዛሬ በክርስቶስ ኢየሱስ በተገዛላችሁ ነጻነትና እርነት በአዲስ ጎዳና በአሸናፊነት ተጓዙ።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ሮሜ 12፥1 እንብቡና፣ ሰውነታችንን ምን እናድርገው ይላል?

   **ሮሜ 12፡1** *እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው።*

2. ሮሜ 12፡2 ይህ ቃል ከ ____ የተለየን እንድንሆን ይነግረናል።

   **ሮሜ 12፡2** *የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።*

3. የሐዋርያት ሥራ 17፡11 አስተሳሰባችንን እንደ ምን እናድርግ ይላል?

   **ሐዋርያት 17፡11** *እነዚህም በተሰሎንቄ ከሚኖሩት ይልቅ ልበ ሰፊዎች ነበሩና። ነገሩ እንደዚሁ ይሆንን? ብለው ዕለት ዕለት መጻሕፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ።*

4. ሮሜ 8፡5-6 ስለ መንፈስ ማሰብ ____ ነው።

   **ሮሜ 8፡5-6** *እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ የሥጋን ነገር ያስባሉና፥ እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር ያስባሉ። [6] ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና፥ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው።*

5. ሮሜ 12፡1-2 በዚህ ቃል መሰረት ልናደርጋቸው የሚገባን ሁለት ነገሮች ምን እና ምን ናቸው?

6. ኢሳይያስ 26፡3 ፍጹም ሰላም እንዴት ማግኘት እንችላለን?

   **ኢሳይያስ 26፡3** *በአንተ ታምናለችና በአንተ ለምትደገፍ ነፍስ ፈጽመህ በሰላም ትጠብቃታለህ።*

7. ኢሳያስ 26፡3 አዕምሯችን በጌታ ለመጠበቅ የምንጠቀምባቸውን መንገዶች ዘርዝሩ።

# ጠቋሚ መልሶች

1. ሮሜ 12፡1 አንብቡና፣ ሰውነታችንን ምን እናድርገው ይላል?
**ለእግዚአብሔር ማቅረብ ወይም መስጠት።**

2. ሮሜ 12፡2 ይህ ቃል ከ ____ የተለየን እንድንሆን ይነግረናል።
**ከዓለም ወይም ከማያምኑ ሰዎች።**

3. የሐዋርያት ሥራ 17፡11 አስተሳሰባችንን እንደ ምን እናድርግ ይላል?
**እንደ እግዚአብሔር ቃል**

4. ሮሜ 8፡5-6 ስለ መንፈስ ማሰብ ____ ነው።
**ሕይወት እና ሰላም።**

5. ሮሜ 12፡1-2 በዚህ ቃል መሰረት ልናደርጋቸው የሚገባን ሁለት ነገሮች ምንና ምን ናቸው?
**እራሳችን እንደ ሕያው መሰዋዕት ለእግዚአብሔር ማቅረብ እና አእምሮአችንን ማደስ።**

6. ኢሳይያስ 26፡3 ፍጹም ሰላም እንዴት ማግኘት እንችላለን?
**አእምሮአችንን በእግዚአብሔር ላይ በማድረግ።**

7. ኢሳያስ 26፡3 አዕምሯችን በጌታ ለመጠበቅ የምንጠቀምባቸውን መንገዶች ዘርዝር።
**ጸሎት፣ አምልኮ፣ ቃሉ ላይ ማሰላሰል፣ ምስጋና በማቅረብ፣ ወዘተ … ።**

# ትምህርት 4

# የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አስፈላጊነት

## በዶን ክሮው

ዛሬ ደግሞ ስለ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አስፈላጊነት እናወራለን። የእግዚአብሔር ቃል በዕብራውያን መልዕክት የሚናገረውን በማንበብ እጀምራለሁ። ዕብራውያን 10:25 እንዲህ ይላል *“በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደሆነው፣ መሰብሰባችንን አንተው እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ፣ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ።”* የክርስቶስን ቤተክርስቲያን አስፈላጊነት በምንመለከትበት ጊዜ ማንሳት የምፈልገው አንድ ጥያቄ አለ፣ እርሱም “ቤተ ክርስቲያን ምንድን ነው?” የሚል ነው።

መርሃ ግብሩን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ለሰዎች ስልጠና ከሰጠን በኋላ የመስክ ትግበራ አደረግን። ከዚህች ቤተ ክርስቲያን ጋር በነበረን የስድስት ሳምንት ቆይታ ከቤተክርስቲያኗ ጉባኤ ውጭ ሃያ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖችን መመሰረት ችለን ነበር። በእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች ውስጥ ካሉ ሰዎች ጋር ለወራት አብረን ሰርተናል። ነገር ግን አንድ ቀን የቤተክርስቲያኗ ፓስተር በጠየቀኝ ነገር ግር ተሰኘሁ። ጥያቄው እንዲህ የሚል ነበር፡- “እንደምታውቀው፣ ጌታም የዳኑትን ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያን ይጨምር ነበር ይላል የእግዚአብሔር ቃል። ታዲያ እነዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ እንዲታቀፉ ያደረጋችኋቸው ሰዎች ወደ እኛ ቤተክርስቲያን ሲመጡ የማናያቸው ለምንድን ነው?” አለኝ።

በማንኛውም ቦታ ሰዎች ተመስክሮላቸው ከዳኑ በኋላ ደቀ መዝሙር እንዲሆኑ እናገለግላቸዋለን። እናም የፓስተሩ ጥያቄ - “እነዚህ ሰዎች እሑድ በዚህ ህንጻ ተገኝተው አንድ ላይ ከእኛ ጋር የማያመልኩት ለምንድን ነው?” የሚል ነው። ስለ ቤተክርስቲያን የነበረኝ የግል ግንዛቤ እምብዛም ነበርና ፓስተሩ ያነሳው ጥያቄ ለእኔም አስቸጋሪ ስለሆነበኝ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላወቅኩም። ይህ የወንጌል ደቀ መዝሙርነት መርሃ ግብር በእርግጥ ውጤት እያመጣ ይሆን? ወደ ሰዎች ሕይወትስ በእርግጥ እየደረሰን ይሆን? ብየ አሰብኩ። ወደ ብዙ ሰዎች እየደረሰን እንደነበር አውቃለሁ፣ ነገር ግን ለእኔ ግልጽ ያልሆነልኝ ሰዎቹ እሑድ ጠዋት ወደ አገልግሎት የማይመጡት ለምንድን ነው? የሚለው ነው።

ስለሆነም “ቤተክርስቲያን” በሚለው ቃል ላይ ጥናት ለማካሄድ ወሰንኩ። እያነበባችሁ ያላችሁት የዚህ ትምህርት ይዘት የሚሸፍነው ይህንን ጥናት በማደርግበት ጊዜ የተገነዘብኩትን ነው። በሮሜ 16:3፣ በ1ኛ ቆሮ 16:19፣ በቆላስያስ 4:15፣ ፊሊሞን 1:2፣ የሐዋርያት ሥራ 5:42 እና 20:20 ውስጥ፣ መጽሐፍ ቅዱስ የቀድሞዋ የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን በግለሰቦች ቤት ውስጥ የነበረች ህብረት መሆኗን ይናገራል። በእርግጥ ሁሉም አይነት አብያተ ክርስቲያናት እንዳሉ አውቃለሁ። በቤት ውስጥ ያለች፣ ጥቂት ወይም ብዙ የምዕመናን ጉባኤ ያላት ወይም በጣም ብዙ ህዝብ ያላቸው ትልልቅ አብያተ ክርስቲያናት ይኖራሉ። ሆኖም የእኔን ትኩረት የሳበውና በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የምናስተውለው ጉዳይ የአዲስ ኪዳኗ ቤተ ክርስቲያን ጥቂት አማኞችን የያዘች፣ በየግለሰቦች ቤት ውስጥ የነበረች መሆኗን ነው።

በሎውረንስ ኦ ሪቻርድስ የተጻፈው የመጽሐፍ ቅዱስ ገላጭ መዝገበ ቃላት (ገጽ 164)፣ (Expository dictionary of Bible Words by Lawrence O. Richards, Page 164) እንዲህ ይላል፡- “ማንኛውም ሰው ‘ቤተክርስቲያን’ በሚለው ቃል ትርጉም ግር ቢሰኝ አያስገርምም። ምክንያቱም ቃሉን በብዙ አግባብ እንጠቀምበታለን። አንድ ሕንጻን ለማመላከት ሊሆን ይችላል (ለምሳሌ በአራተኛው ጎዳና ላይ ያለ ቤተክርስቲያን)፣ የተደራጁ የእምነት ተቋምን ለማመላከት (ለምሳሌ የባፕቲስት ቤተክርስቲያን፣ የተሐድሶ ቤተክርስቲያን) እና የእሑድ ጉባኤን ለማመላከት (ለምሳሌ ዛሬ ወደ ቤተክርስቲያን አልሄድክም? እንላለን)። እነዚህ ሁሉ አጠቃቀሞች መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደሉም” ይላል። እኔም እንዲህ

ብዬ ማሰብ ጀመርኩ፣ ምን ማለት ነው? ታዲያ ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል ትክክለኛ ትርጉም ምንድን ነው? በማለት ሌሎች ተጨማሪ ጥቅሶችን ማዬት ቀጠልኩ፦ “እንግዲህ ብዙ ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን አንድ ሐይማኖታዊ ስርዓት የሚፈጸምበት ህንጻ እንጂ ለአምልኮ የተሰባበሰቡ ሰዎች ህብረት አድርገው እያሰቡምና ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል የተሳሳተ ትርጉም እንዲይዝ የተደረገ ይመስላል”። ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ “ኤክሌዥያ” የሚል ሲሆን የዚህ ቀጥተኛ ትርጉም፦ እግዚአብሔርን ብለው ወይም እርሱን ፈልገው ለአምልኮ፣ ለምስጋና፣ ወይም ለጸሎት የተሰበሰቡ ሰዎች ህብረት ማለት ነው። በዚህ ላይ ሌሎች ጽሑፎችንም ልጨምር፦ “ኤክሌዥያ በአዲስ ኪዳን የትኛውንም ያህል ቁጥር ያላቸውን አማኞች ሊያጠቃልል ይችላል። በመኖሪያ ቤት ውስጥ የሚሰበሰቡ ትንሽ ህብረቶችን (ሮሜ 16፡5)። በአንድ ትልቅ ከተማ ውስጥ የሚኖሩ ሁሉንም አማኞችን የሚያጠቃልል (የሐዋርያት ሥራ 11፡22) ወይም በአንድ ትልቅ አካባቢ እንደ እስያ ወይም ገላትያ ያሉ መልክዓ ምድራዊ ክልሎችን የሚያጠቃልል ሊሆን ይቸላል”። በመቀጠልም እንዲህ ይላል፦ “ዓይነተኛው የቤተክርስቲያን ህብረት በመኖሪያ ቤቶች ውስጥ ነበር። በሚገናኙበት ጊዜም ለእያንዳንዳቸው መዝሙሮች፣ የሚመሩበት ቃል፣ መገለጦች፣ ልሳኖች፣ ወይም ትርጉም ነበራቸው (1ኛ ቆሮ 14፡26)። ሆኖም አይነተኛ የቤተክርስቲያን ሰብሰብ በመኖሪያ ቤቶች ውስጥ ነበር። እያንዳንዱ ሰው ያካፍላል ሌሎች ደግሞ የተነገረውን በጥንቃቄ ይመዝናሉ ይህ ክፍፍል ለቤተክርስቲያን ህልውና እንደ እምነት ማህበር ሆኖ ለመቀጠል አስፈላጊ ነበር። እያንዳንዱ ሰው በተሰጠው መንፈሳዊ ስጦታ ወይም ስጦታዎች ማካፈልና ሌሎችንም ማገልገል ይጠበቅበት ነበር።

ዕብራውያን 10፡25 *“በአንዳንዶች ልማድ እንደሆነው መሰብሰባችን አንተው”* ይላል። ቤተክርስቲያን ኢየሱስን ብለው በአንድነት የመጡ ሰዎች ሰብሰብ ስትሆን ይህም ጌታን ለማምለክ፣ ከጌታ አቅጣጫ ለመቀበልና፣ በተቀበሉት አቅጣጫም ለመቀጠል ነው። የቀድሞዋ የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ዋና ተግባር ማነጽ ነው። ሁሌም በአንድነት የሚሰባሰቡት እርስ በርሳቸው በእምነት ለመታነጽ ነበር።

የቀድሞዋ ቤተክርስቲያን ወንጌላዊት ነበረች። ሰዎች ተበታትነው በሚኖሩበት ቦታ ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ያላቸውን እምነት ያካፍሉ ነበርና ጌታም ሰዎች ንስሐ ገብተው በተመለሱና ባመኑ ጊዜ ወደ አንድ ህንጻ ወይም ተቋም ሳይሆን ወደ ቤተክርስቲያን፣ ወደ እግዚአብሔር ሕዝቦች ይጨምር ነበር። እነርሱም እርስ በእርስ በእምነት ለመጠንከርና መንፈሳዊ ስጦታዎችንም ለመለማመድ አንዱ አንዱን ለማገልገልና ለመገልገል ምግብንም አብረው በመካፈል ህብረት ያደርጉ ወይም ይሰባሰቡ ነበር። አንድ ላይ በሚሆኑበት ጊዜ እርስ በእርስ ለመተናነጽ መንፈሳዊ ስጦታዎቻቸውን ይጠቀማሉ። በመቀጠል ይወጡና ቃሉን መሰበክ ይጀምራሉ በዚህ አይነት ሂደቱ እንደገና ይጀምርና በተመሳሳይ መልኩ ይቀጥላል ማለት ነው። በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ያምናሉ፤ በእራሳቸው በአንድነት ይሰባሰባሉ። የት እንደሚሰባሰቡ አሳሳቢ አልነበረም። በአንድ ግለሰብ ቤት ወይም ህንጻ ሊሆን ይችላል። ቁጥራቸውም ብዙ ወይም ጥቂት ሊሆን ይችላል። በጌታ በኢየሱስ አምነው መንፈሰዊ ስጦታዎቻቸውን ለመለማመድ፣ እርስ በርስ ለመጽናናት እና እርስ በእርስ ለመረዳዳት፣ ግቡ ለመተናነጽ እና እርስ በእርስ ለመደጋገፍ እስከሆነ ድረስ፣ የትም ቢሰባሰቡ አሳሳቢ አልነበርም።

ከዚህም በመነሳት፣ በወንጌል ደቀመዝሙርነት መርሃ ግብር ሥራችን፣ ከላይ ስሟን በጠቀስኩላችሁ ከተማ ውስጥ በአጥቢያ ቤተክርስቲያኗ ካሉት ሃያ የመጽሐፍ ቅደስ ጥናት ቡድኖች ጋር የነበረን ግንኙነት፣ ከሃያ አብያተ ክርስቲያናት ጋር የተደረገ ግንኙነት መሆኑን መገንዘብ ችያለሁ። ዛሬ ላይ ቤተክርስቲያንን በምናውቅበት መንገድ አይደለም፣ ነገር ግን እንደ "ቤተክርስቲያን" በሳምንት ሃያ ጊዜ እየተገናኘን ነበር፣ ምክንያቱም የምንሰባሰበው በጌታ በኢየሱስ ሰም እርስ በርስ ለመጽናናት፣ ጌታን ኢየሱስን ለመፈለግ፣ በእግዚአብሔር ቃል ለመመራት እና መንፈሳዊ ስጦታዎቻችንንም ለመጠቀም በመሆኑ ነው።

ወደ የትኛውም ቤተክርስቲያን ሂዱ፣ የየትኛው ግዙፍ እና ታዋቂ ወይም ትንሽ ቤተክርስቲያን ወይም

የቤት ውስጥ ማኅበር ተካፋይ ሁኑ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚነግረን ቀኑ እየቀረበ በመጣ ቁጥር፣ ኃጢአትም በበዛ ጊዜ የእግዚአብሔር ፀጋ በይበልጥ ይበዛል። ፀጋ በእነዚህ የእግዚአብሔር ሰዎች ህብረት ውስጥ እጅግ ይበዛል። በቤተክርስቲያን፣ እያንዳንዱ አማኝ የክርስቶስ ኢየሱስ አገልግሎት ድርሻ ያለው እንደ መሆኑ እንዳችሁ ሌላውን ለማገልገል፣ ለመምከር፣ ለማበረታታት እና መንፈሳዊ ስጦታዎቻችሁን ለመጠቀም ትችላላችሁ።

ሁላችንም በአማኞች ኅብረት ውስጥ በመሳተፍ በዚህ መልኩ ተጠቃሚ መሆን እንችላለን። ምንም እንኳን በቁጥር ሁለት ወይም ሶስት ሆነው በጌታ በኢየሱስ ስም የተሰባበሱ ቢሆንም ዘወትር በተወሰነ ጊዜ በመገናኘት መሰብሰብ አስፈላጊ ነው። መንፈሳዊ ስጦታዎቻችን ለመጠቀም በጋራ መገናኘታችን መልካም ነው፤ እርስ በእርስ ለመመካከር፣ ለመበረታታት፣ ጌታ ኢየሱስን ለመፈለግ እና በጋራ ለመጸለይ መሰብሰባችን መልካም ነው። ስለ ቤተክርስቲያን ብዙ ነገር መናገር እንችላለን። ስለ ሽማግሌዎች፣ ስለ መሪዎች፣ መጋቢዎች እና ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ብዙ ማውራት እንችል ነበር፣ ነገር ግን የዚህ ትምህርት ትኩረት ይህ አይደለም። የዚህ ትምህርት ዓላማ የቤተክርስቲያንን ዓላማ ማወቅና እኛም በተናጠል ብቻችንን በደሴት ውስጥ እንዳለ ሰው መሆን እንደማይገባን ማወቅ ነው። በዚህ መልኩ መቀጠል አንችልም። መዳናችን በተቀበልን ጊዜ እግዚአብሔር የክርስቶስ አካል ውስጥ ጨምሮናል - በመላው ዓለም ያለችው የክርስቶስ አካል ነን። አንዳችን ለአንዳችን እናስፈልጋለን። እንደ እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ሁላችንም በአንድነት እየተገናኘን እርስ በእርስ ለመጽናናት፣ እግዚአብሔር በሰጠን መንፈሳዊ ስጦታዎቻችን አንዳችን ሌላውን ለማገልገል መሰባሰብ ያስፈልገናል። ከእግዚአብሔር ህዝቦች ጋር በመገናኘት ኅብረት ታደርጉ ዘንድ ዛሬ፣ በፍቅር አበረታታችኋለሁ።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ዕብራውያን 10፡25 አንብቡና፣ መተው የሌለብን ነገር ምንድን ነው?

   **ዕብራውያን 10:25** *በአንዳንዶች ልማድ እንደሆነው መሰብሰባችን አንተው።*

2. የሐዋርያት ሥራ 5፡42 በቤተመቅደስና በቤታቸው ኢየሱስን ____ እና ____ ነበር።

   **ዕብራውያን 5:42** *ዕለት ዕለትም በመቅደስና በቤታቸው ስለ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ማስተማርንና መሰበክን አይተዉም ነበር።*

3. የሐዋርያት ሥራ 2፡42 የቀድሞዋ ቤተክርስቲያን ማድረግ ያላቆመቻቸው አራት ነገሮች ምን ምን ነበሩ?

   **ዕብራውያን 2:42** *በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር።*

4. የሐዋርያት ሥራ 2፡44-45 የቀድሞዋ ቤተክርስቲያን ለተቸገሩ ምን ታደርግ ነበር?

   **የሐዋርያ ሥራ 2:44** *ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ፤ [45] ያላቸውንም ሁሉ አንድነት አደረጉ። መሬታቸውንና ጥሪታቸውንም እየሸጡ፥ ማንኛውም እንደሚፈልግ ለሁሉ ያካፍሉት ነበር።*

5. 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡28 እግዚአብሔር በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ያኖራቸውን ስምንት የተለያዩ ስጦታዎችን ዘርዝሩ።

   **1ኛ ቆሮንቶስ 12:28** *እግዚአብሔርም በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹን አስቀድሞ ሐዋርያትን፥ ሁለተኛም ነቢያትን፥ ሦስተኛም አስተማሪዎችን፥ ቀጥሎም ተአምራት ማድረግን፥ ቀጥሎም የመፈወስን ስጦታ፥ እርዳታንም፥ አገዛዝንም፥ የልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖችንም አድርጎአል።*

6. 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡26 የእግዚአብሔር ሕዝቦች እንደ ቤተክርስቲያን ሲሰባሰቡ ስጦታዎቻቸውን ለመግለጥ ነጻነት ነበራቸው። ሲሰባሰቡ ከሚያከናውኗቸው ነገሮች ውስጥ አምስቱን ዘርዝሩ።

   **1ኛ ቆሮንቶስ 14:26** *እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ምንድር ነው? በምትሰበሰቡበት ጊዜ ለእያንዳንዱ መዝሙር አለው፥ ትምህርት አለው፥ መግለጥ አለው፥ በልሳን መናገር አለው፥ መተርጐም አለው፤ ሁሉ ለማነጽ ይሁን።*

7. የሐዋርያት ሥራ 6፡1 የቀድሞዋ የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ምግባቸውን ከ ____ ጋር ይካፈሉ ነበር።

   **የሐዋርያት ሥራ 6:1** *በዚህም ወራት ደቀ መዛሙርት እየበዙ ሲሄዱ ከግሪክ አገር መጥተው የነበሩት አይሁድ በይሁዳ ኖረው በነበሩት አይሁድ አንጐራጐሩባቸው፥ በየቀኑ በተሠራው አገልግሎት መበለቶቻቸውን ቸላ ይሉባቸው ነበርና።*

8. ያዕቆብ 1፡27 እግዚአብሔር የሚወደውና የሚፈልገው ዓይነት አምልኮ____ ነው።

   **ያዕቆብ 1:27** *ንጹሕ የሆነ ነውርም የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ይህ ነው፤ ወላጆች የሌላቸውን ልጆች ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ፥ በዓለምም ከሚገኝ እድፍ ሰውነቱን መጠበቅ ነው።*

9. 1ኛ ጢሞ 5፡9-11 በቀድሞዋ የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን የሚገለገሉ መበለቶች ምን መስፈርት ነበራቸው?

**1ኛ ጢሞቴዎስ 5፡9-11** *ባልቴት በመዝገብ ብትጻፍ ዕድሜዋ ከስድሳ ዓመት እንዳያንስ፥ የአንድም ባል ሚስት የነበረች እንድትሆን ያስፈልጋል፤ [10] ልጆችን በማሳደግ እንግዶችንም በመቀበል፥ የቅዱሳንንም እግሮች በማጠብ፥ የተጨነቁትንም በመርዳት በጎንም ሥራ ሁሉ በመከተል፥ ይህን መልካም ሥራ በማድረግ የተመሰከረላት ልትሆን ይገባል። [11] ባል የሞተባቸውን ቆነጃጅት ግን አትቀበል፤ በክርስቶስ ላይ ተነሥተው ሲቀማጠሉ ሊያገቡ ይወዳሉና፤*

10. 1ኛ ቆሮንቶስ 9፡14 መበለቶችን፣ ወላጅ አልባ ልጆችንና ድሆችን ከመርዳት በተጨማሪ ቤተክርስቲያን ____ ትረዳ ነበር።

**1ኛ ቆሮንቶስ 9፡14** *እንዲሁ ደግሞ ወንጌልን የሚሰብኩ ከወንጌል ቀለብ እንዲቀበሉ ጌታ ደንግጎአል።*

11. ማቴዎስ 25፡35-40 ሰዎች ለእግዚአብሔር ለመስጠት ሲያስቡ ሙዳየ ምጽዋትን (መባ መሰብሰቢያን) ብቻ የመስጫ መንገድ አድርገው ለምን ያስባሉ?

**ማቴዎስ 25፡35-40** *ተርቤ አብልታችሁኛልና፥ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፥ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፥ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፥ [36] ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፥ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና። [37] ጻድቃንም መልሰው ይሉታል። ጌታ ሆይ፥ ተርበህ አይተን መቼ አበላንህስ? ወይስ ተጠምተህ አይተን መቼ አጠጣንህ? [38] እንግዳ ሆነህስ አይተን መቼ ተቀበልንህ? ወይስ ታርዘህ አይተን መቼ አለበስንህ? [39] ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ አይተን መቼ ወደ አንተ መጣን? [40] ንጉሡም መልሶ። እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት ይላቸዋል።*

12. የሐዋርያ ሥራ 4፡32-35 እና መጽሐፈ ምሳሌ 3፡9-10፣ የቀድሞዋ ቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችና መጋቢዎች በገንዘብ አስተዳደር ዙሪያ ምን ያደርጉ ነበር?

**የሐዋርያት ሥራ 4፡32-35** *ያመኑትም ሕዝብ አንድ ልብ አንዲትም ነፍስ ነበሩአቸው፥ ገንዘባቸውም ሁሉ በአንድነት ነበረ እንጂ ካለው አንድ ነገር ስንኳ የራሱ እንደ ሆነ ማንም አልተናገረም። [33] ሐዋርያትም የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በታላቅ ኃይል ይመሰክሩ ነበር፤ በሁሉም ላይ ታላቅ ጸጋ ነበረባቸው። [34] በመካከላቸው አንድ ስንኳ ችግረኛ አልነበረምና፤ መሬት ወይም ቤት ያላቸው ሁሉ እየሸጡ የተሸጠውን ዋጋ ያመጡ ነበርና፥ [35] በሐዋርያትም እግር አጠገብ ያኖሩ ነበር፤ ማናቸውም እንደሚፈልግ መጠን ለእያንዳንዱ ያካፍሉት ነበር።*

**ምሳሌ 3፡9-10** – *ለጠቢብ ሰው ትምህርትን ሰጠው፣ ጥበብንም ያበዛል፣ ጽድቅንም አስተምረው፣ እውቀትንም ያበዛል። [10] የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፣ ቅዱሱንም ማወቅ ማስተዋል ነው።*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ዕብራውያን 10፡25 አንብቡና፣ መተው የሌለብን ነገር ምንድን ነው?
**እንደ አማኞች አንድ ላይ በህብረት መሰብሰባችንን።**

2. የሐዋርያት ሥራ 5፡42 በቤተመቅደስና በቤታቸው ኢየሱስን ____ እና ____ ነበር።
**ያስተምሩ እና ይሰብኩ።**

3. የሐዋርያት ሥራ 2፡42 የቀድሞዋ ቤተክርስቲያን ማድረግ ያላቆመቻቸው አራት ነገሮች ምን ነበሩ?
**በሐዋርያት ትምህርት መቀጠላቸው፣ ኅብረት፣ እንጀራን በመቁረስ (ያላቸውን አንድ ላይ በመመገብ) እና ጸሎት።**

4. የሐዋርያት ሥራ 2፡44-45 እውነት ወይም ሐሰት፣ የቀድሞዋ ቤተክርስቲያን ለመኪና ማቆሚያ መሰሪያ ገንዘብ መሰጠት ቀጥላ ነበር።
**ሐሰት።**

5. 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡28 እግዚአብሔር በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ያኖራቸውን ሰምንት የተለያዩ ስጦታዎችን ዘርዝሩ።
**ሐዋርያት፥ ነቢያት፥ አስተማሪዎች፥ ተአምራት የሚያደርጉ፥ የመፈወስን ስጦታ ያላቸውን፥ እርዳታ የሚያደርጉ፣ የአስተዳደር ችሎታ ያላቸውን፥ ልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖች የሚናገሩትን።**

6. 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡26 የእግዚአብሔር ሕዝቦች እንደ ቤተክርስቲያን ሲሰባሰቡ ስጦታዎቻቸውን ለመግለጥ ነጻነት ነበራቸው። ሲሰባሰቡ ከሚያከናውኗቸው ነገሮች ውስጥ አምስቱን ዘርዝሩ።
**አንዱ መዝሙር አለው፥ ሌላው ትምህርት አለው፥ ሌላው እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር መግለጥ አለው፥ አንዱ በልሳን መናገር አለው፥ ሌላው ደግሞ የተነገረውን ልሳን መተርጐም አለው።**

7. የሐዋርያት ሥራ 6፡1 የቀድሞዋ የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ምግባቸውን ከ _____ ጋር ይካፈሉ ነበር።
**ከመበለቶቻቸው ጋር።**

8. ያዕቆብ 1፡27 እግዚአብሔር የሚወደውና የሚፈልገው ዓይነት አምልኮ _____ ነው።
**ወላጆቻቸው የሞቱባቸውን ልጆችና ባሎቻቸው የቱባቸውን በችግራቸው መርዳት።**

9. 1ኛ ጢሞ 5፡9-11 በቀድሞዋ የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን የሚገለገሉ መበለቶች ምን መስፈርት ነበራቸው?
**ባልቴት በመዝገብ ብትጻፍ ዕድሜዋ ከሰድሳ ዓመት ያላነሰ እና የአንድ ባል ሚስት የነበረች እንድትሆን ያስፈልጋል፤ በመልካም ሥራዋ በሁሉም ዘንድ የተመሰገነች መሆን ይገባታል። ልጆቿን በመልካም ታሳድጋለች? ለእንግዶች መልካም ነች? ሌሎች ክርስቲያኖችን በትህትና ታገለግላለች? የተቸገሩትንስ ትረዳለች? ሁሌ መልካም ለማድረግ የተዘጋጀች ነች? ባል የሞቱባቸው ወጣት ሴቶች በዚህ መዝገብ ሊካተቱ አይገባም።**

10. 1ኛ ቆሮ 9፡14 መበለቶችን፣ ወላጅ አልባ ልጆችንና ድሆችን ከመርዳት በተጨማሪ ቤተክርስቲያን _____ ትረዳ ነበር።
**የቃሉን አገልጋዮች።**

11. ማቴዎስ 25፡35-40 ሰዎች ለእግዚአብሔር ለመስጠት ሲያስቡ ሙዳየ ምጽዋትን (መባ መሰብሰቢያን) ብቻ የመስጫ መንገድ አድርገው ለምን ያስባሉ?
    **ምክንያቱም በዚህ መንገድ ስለተማሩ ነው።**

12. የሐዋርያ ሥራ 4፡32-35 እና መጽሐፈ ምሳሌ 3፡9-10፣ የቀድሞዋ ቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችና መጋቢዎች በፋይናንስ ላይ ምን ያደርጉ ነበር?
    **እንደሚፈልግ መጠን ለእያንዳንዱ ያካፍሉት ነበር.፣ በመስጠት ጌታን ያከብሩ ነበር።**

# ትምህርት 5

# ነፃ መውጣት

## በዶን ክሮው

ዛሬ ደግሞ አጋንንትን በተመለከተ እናወራለን። ኢየሱስ በምድር ላይ የነበረውን አገልግሎት አጋንንትን በማውጣት፣ የታመሙትን በመፈወስ፣ የሞቱትን በማስነሳትና ሌሎች ተዓምራትን በማድረግ ያሳልፍ ነበር። የአገልግሎቱን አንድ አራተኛ የሚሆነው ጊዜ የሚወስደው ከሰዎች ላይ ክፉ መንፈስን ማባረር ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ በሐዋርያት ሥራ 10:38 እንዲህ ይላል፦ *“እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በሃይልም ቀባው፤ እርሱም መልካም እያደረገ ለዲያብሎስም የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ፤ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነበርና።”* ደግሞም በ1ኛ ዮሐ 3:9 *“ስለዚህ የዲያብሎስን ሰራ እንዲያፈርሰ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ”* ይላል። ቀደም ሲል ስለ አጋንንት የነበረኝ አመለካከት የተለዬ ነበር - አጋንንት፣ ክፉ መናፍስት፣ እርኩስ መንፈስ፣ ዲያብሎስ፣ ብቻ የምታውቁትን ሰም ሰጧቸው የሚገኙት ከእውነተኛው ህያው አምላክ ይልቅ በጣዖት እና በልዩ ልዩ ሌሎች ነገሮች በሚያመልኩ እንደ አፍሪካ፣ ህንድና ሌሎች ኋላ ቀር አገሮች ወይም ህዝቦች ላይ ብቻ ይመስለኛ ነበር። ተሳስቻለሁ።

ከጥቂት ዓመት በፊት ዳላሰ ቴክሳሰ ውሰጥ ባለች አንዲት ቤተክርሰቲያን የተከሰተ እውነተኛ ታሪክ ላቅርብላችሁ። ሁሉም ሰው በመዝሙርና በአምልኮ ውሰጥ በነበረበት ጊዜ አንዲት ልጅ እግር ሴት ወለሉ ላይ ወድቃ መንፈራገጥ ትጀምራለች። ከአማኞች መሃል ዶክተር ራይሰ የሚባል አንድ ሐኪም ነበርና የአንዳንድ አማኞች ቤት ቅርብ ስለነበር በአቅራቢያው ካሉ ቤቶች ወደ አንዱ እንድንወሰዳት፣ እርሱም በኋላ እንደሚያያት በተናገረው መሰረት ወደ አንደኛው ቤት ተወሰደች። እቤት ባሰገባናት ጊዜ ይህች ልጅ እንደ አውሬ ሆና ነበር። በድንገት አይኗ ፈጠጠና፣ ሃምሳ ኪሎ እንኳን ከማይሞላው ቀጫጫ ሰውነቷ፣ አንድ የፈረጠመ ሰው ዓይነት ጎርናና ድምጽ መሰማት ጀመረ። ወዲያውም በእኔ ላይ የቃላት ውርጅብኙን በማውረድ- “ወደ ሲኦል ትወርዳለህ” ሲል ተናገረ። እኔም “አይ! አልወርድም” አልኩ። ከዚህ በፊት እንዲህ አይነት ነገር አይቼ ስለማላውቅ መፍራቴ ግን አልቀረም። “አዎ፣ ትወርዳለህ፣ ወደ ሲኦል ትወርዳለህ” አለ በድጋሚ። እኔም “አልወርድም፣ በፍጹም ወደ ሲኦል አልወርድም” አልኩት። በእኔ ላይ ሃይል ወይም ስልጣን ያለው መሰሎ ይታይ ነበርና በዚህች ልጅ ውሰጥ ባለው ነገር ላይ ምን ዓይነት መፍትሔ እንዳለ ወይም ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላወቅኩም።

ከውድ ጓደኞቼ ውሰጥ አንዱ እጅግ ፈርቶ እግሬ አውጭኝ አለ። እኔም ፊት ለፊት ተፋጥጬ ምን ባደርግ ይሻለኛል? እያልኩ ማሰብ ጀመርኩ። ልዕለ ተፈጥሯዊ ሃይል ልጅቷ ውሰጥ ነበርና ከዚህ በፊት ተምራ በማታውቀው እንደ ጀርመንኛ ዓይነት ቋንቋ ከማውራቷም በላይ ሁሉም ዓይነት የዲያብሎሰ አጋንንታዊ ምልክቶች ይገለጡባት ጀመር። ይህች ልጅ ጋኔን አለባት፤ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ለጊዜው ባላውቅም ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ሃይል እንዳለው አምን ነበር። ሁኔታው ልጅ ሆነን በተረት እንሰማ የነበረውን አሰፈሪ የጭራቅ አፈ ታሪክ በዓይን እንደመመልከት ዓይነት ነበር። በተረት እንደምናውቀው አንድ ጭራቅ ወደ አንድ ሰው ሲመጣበት ሰውዬውም በጉያው ደብቆ የያዘውን መሰቀል ሲያወጣበት ጭራቁ “እርርር …” እያለ ተመልሶ ከሰውዬው ርቆ እንደሚሄድ ዓይነት፣ እኔም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የነበረኝ ግንዛቤ በተመሳሳይ መልኩ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ሃይል እንዳለው ባውቅም ነገር ግን ይህን ሃይል እንዴት መጠቀም እንዳለብኝ አላወኩም ነበር። ነገር ግን ከዚህ በፊት እንደዚህ ዓይነት ነገር አጋጥሞኝ ስለማያውቅ የእግዚአብሔር ጸጋ አረዳኝ። መጽሐፍ ቅዱሴን ከአዲስ ኪዳን በኩል በመክፈት ገለጥኩና የፊሊጵሰዩሰ መልዕክትን ሰላገኘሁ ከምዕራፍ 2 ቁጥር 8-11 ያለውን ማንበብ ጀመርኩ፦ *“በምሰሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፣ ለሞትም ይኸውም የመሰቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ። በዚህም ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፤ ከሰምም ሁሉ በላይ ያለውን ሰም ሰጠው፤ ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱሰ ሰም ይንበረከኩ ዘንድ፤ መላሰም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱሰ ክርሰቶሰ ጌታ እንደሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው”*

ወዲያው - "ይህን አትናገር፤ እነዚህን ቃላት መቋቋም አልችልም፣ ይህን አትናገር" አለ። ምን ዓይነት ምላሽ ነው! ብዬ በመገረም አሰብኩ። ስለዚህ ቀጠልኩና እንዲህ አልኩ፦ "እንግዲህ፣ በኢየሱስ ስም ማንኛውም ጉልበት ይንበረከካል - በሰማይ ያሉ ነገሮች፣ በምድርም ያሉ ነገሮች፣ እናም ከምድርም በታች ያሉ ሁሉ" አልኩ። "እንደዚህ አትናገር፣ እነዚህን ቃሎች መቋቋም አልችልም! ይህን አትናገር" ብላ በሃይል ጮኸች። እኔም፣ ይሄ ዲያብሎስ በዚህች ልጅ ውስጥ ሆኖ ማበዱ ነው፣ ያደረኩት ነገር ቢኖር የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ ብቻ ነው፣ ብዬ አሰብኩ። ስለዚህ ደግሜ አነበብኩ፦ *"በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፣ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ። በዚህም ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፤ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤ ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፤ ነው።"*እሁንም በድጋሚ ተመሳሳይ ምላሽ ነበረው፤ "ይህን ቃል አትናገር፣ መቋቋም አልችልም"፣ አለ ጋኔኑ። እርሷንም በጆሮዋ ቆንጥጦ እንደያዛት ዓይነት ሆና እንዲህ አለች "ይህን ቃል አትናገር፣ እነዚህን ቃላት መቋቋም አልችልም" አለች። ጋኔኑ ልጅቱን እግሬ ስር ወረወራት፣ እርሷም ለኢየሱስ ስም መሰገድ ጀመረች። እኔም "ለኢየሱስ ስም በሰማይም፣ በምድርም ከምድርም በታች ያለ ጉልበት ሁሉ ይንበረከካል" አልኩ።

ከጥቂት ገዜ በፊት አጋንንቱ በእኔ ላይ ሃይልና ስልጣን ነበረው። የሚገርፈኝ፣ የሚደበድበኝና አውጥቶ የሚወረውረኝ መሰሎኝ ነበር - የማውቀው ነገር ቢኖር መጽሐፍቅዱስ ሃይል እንዳለው ብቻ ነበር እንጂ ሌላ የማውቀው ነገር አልነበረምና መጽሐፍ ቅዱሴን አውጥቼ ማንበብ ጀመርኩ። የእግዚአብሔር ቃል በኤፌሶን መልዕክቱ እንዲህ ይለናል፦"የመዳንን ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሄር ቃል ነው"። እስተዋላችሁ ጠላትን ቆራርጦ የሚጥል መሳሪያ አለን ይህም የመንፈስ ሰይፍ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ነው። ኢየሱስ ሲፈተን የሆነውን ታስታውሳላችሁ? ዲያብሎስ ቀረበና ‹‹ወድቀህ ብትሰግድልኝ የዓለምን መንግስታት ሁሉ እሰጥሃለሁ›› አለው። ኢየሱስም "ሂድ አንተ ሰይጣን ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ብቻ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፏል" (ማቴዎስ 4፥10) ብሎ መለሰለት። ዲያብሎስም እንደገና ፈተነው፣ ደግሞም እንደገና ፈተነው፣ ኢየሱስም "እንዲህ ተጽፏል ሰይጣን፣ ... እንዲህ ተብሎ ተጽፏል" በማለት የእግዚአብሔርን ቃል ይጠቅስለት ነበር። የመንፈስን ሰይፍ ይጠቀም ነበር፣ መጽሐፍ ቅዱስም ዲያብሎስ ለጊዜው ከእርሱ ተለይቶ ሄደ ይለናል።

ጠላትን የምናሸንፍበት ብቸኛው መሳሪያ የመንፈስ ሰይፍ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ነው። ከዚህ ሁሉ ምን መማር እንደቻልኩ ታውቃላችሁ? አዎ፣ አንድ ነገር ተምሬአለሁ። ሁሌም ቃሉን ማጥናት በፈለግኩ ጊዜ እንደተራብና ምግብ እንደሚያስፈልገው ሰው ወይም በዛም ቀን ያልሰራሁትና መሰራት ግን የነበረብኝ ነገር እንዳለ እሰባለሁ። በደቀመዝሙርነት ትምህርት ያሉ ሰዎች ለምን መምጣት እንዳልቻሉ የሚያቀርቧቸው ብዙ ዓይነት ምክንያቶች ቢኖሩም በመጨረሻ ግን ለምንድን ነው የሚለውን መገንዘብ ችያለሁ። እግዚአብሔር እንድናውቅ የሚፈልጋቸው፣ ዲያብሎስ ግን እንድናውቅ የማይፈልጋቸው ነገሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ። ሁሌም የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት ስትፈልጉ ወይም የደቀመዝሙርነት ትምህርት መከታተል ስትፈልጉ ጠላት በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እንድታውቁት የማይፈልገው ነገር አለ - ከቃሉ ጀርባ ያለውን እግዚአብሔርን እንድታውቁ አይፈልግም።

የጨለማው መንግስት አለ፤ ደግሞም የእግዚአብሔር ውድ ልጅ መንግስት አለ። ቆላስያስ 1፡13 ይህንን ይነግረናል፦ "እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፣ ቤዛነቱንም እርሱንም የኃጢአትን ሥርዬት ወደገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግስት አፈለሰን"። የትኛው መንግስት ውስጥ ነው ያላችሁት? አንድ መንግስት የራሱ ገዥ እና መሪ አለው። ኢየሱስ ክርስቶስ ንጉስ ነው። ህይወታችሁን ለእርሱ ሰጥታችኋል? ዛሬስ እርሱን እየተከተላችሁት ነው፣ ወይስ በህይወታችሁ ቅድሚያውን የወሰዱ ሌሎች ነገሮች አሉ? ኢየሱስ በሉቃስ 6፡46 ይህን ይናገራል፦ "ስለ ምን። ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ፣ ትሉኛላችሁ፤ የምለውንም አታደርጉም?"። በህይወታችሁ ቅድሚያ እንድትሰጡት ይፈልጋል፣ ኢየሱስ የህይወታችን ዋና ወይም የመጀመሪያ ሊሆን ይፈልጋል። ደግሞም ኢየሱስ ዋና እንዳይሆን እርሱ በህይወታችን እንዳይነግስ እርሱንም እንዳናውቅ ለማድረግ የሚጥር ወይም የሚሰራ የጨለማው መንግስት አለ። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ጠላት በህይወታችን ቢችል ዋናውን የገዥነት ቦታ መቆናጠጥ ሥለሚፈልግ ነው።

ጠላት እንዳለ በመገንዘብ ዛሬውኑ ወደ ኢየሱስ ከልባችሁ ተመለሱ። ጠላታችሁ ሰሙ ሰይጣን ነው፤ ያለውም ሃይል አጋንንታዊ ሃይል ብቻ ነው። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በእርሱ ላይ ስልጣን የተሰጠን መሆኑን ይናገራል።

ኢየሱስ በማቴዎስ 10፡8 “ድውዮችን ፈውሱ፣ ሙታንን አስነሡ፣ ለምጻሞችን አንጹ፣ አጋንንትን አውጡ፣ በከንቱ ተቀበላችሁ በከንቱ ስጡ” ይላል። የእግዚአብሔርን መንግስት ወንጌል ሰበኩ፣ በምትሄዱበትም ሁሉ በጠላት ላይ ስልጣን አላችሁ። እግዚአብሔር ለህይወታችሁ ካለው መልካም ነገር እንድትወጡ ለማድረግ ጠላት የሚነግራችሁን ማንኛውም ነገር ከእንግዲህ ወዲያ አትስሙ። ኢየሰስን የህይወታችሁ ጌታ እና ቁጥር አንድ አድርጉት። መቼም ቢሆን አትጸጸቱበትም።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ኤፌሶን 6፡12 አንብቡና ይህ ቃል ከአጋንንት ዓለም ጋር ያለንን መንፈሳዊ ተቃርኖ እንዴት ይገልጸዋል?

   **ኤፌሶን 6፡12** *መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።*

2. ማርቆስ 16፡17 ስለአማኝ ስልጣን ይህ ቃል ምን ያስተምረናል?

   **ማርቆስ 16፡17** *ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፤ እባቦችን ይይዛሉ፥*

3. ያዕቆብ 4፡7 ከአጋንንት ነጻ መውጣት የሚፈልግ ሰው ምን ማድረግ አለበት?

   **ያዕቆብ 4፡7** *እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል።*

4. ያዕቆብ 1፡14 ሰይጣን ክፉ ነገርን መልካም አስመስሎ እንድናይ የሚያታልለን በምንድን ነው?

   **ያዕቆብ 1፡14** *ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል።*

5. ሮሜ 6፡13 አንድ ሰው ህይወቱን በክርስቶስ ነገሮች ከሞላ፣ አጋንንት ምቾት ያጡና በራሳቸው ጥለውት ይሸሻሉ። ይህ ቃል ምን እንድናደርግ ይነግረናል?

   **ሮሜ 6፡13** *ብልቶቻችሁንም የዓመፃ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ፥ ነገር ግን ከሙታን ተለይታችሁ በሕይወት እንደምትኖሩ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ፥ ብልቶቻችሁንም የጽድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ።*

6. ሮሜ 13፡14 አጋንንት የሚመገቡት የስጋ ሥራን ስለሆነ በእግዚአብሔር የፍቅር መንገድ በመራመድና በንጽህና እንዲራቡ አድርጓቸው። ለስጋ ____ አናድርግ።

   **ሮሜ 13፡14** *ነገር ግን ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት፤ ምኞቱንም እንዲፈጽም ለሥጋ አታስቡ።*

7. ሉቃስ 10፡17-19 ኢየሱስ አጋንንት ለማውጣት ወደ እርሱ እንድንጸልይ አልነገረንም። ነገር ግን ስልጣን ሰጥቶናል። ይህ ቃል በ ____ ላይ ሃይልና ስልጣን እንዳለን ይናገራል።

   **ሉቃስ 10፡17-19** *እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፥ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፥ የሚጐዳችሁም ምንም የለም። [18] እንዲህም አላቸው ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ። [19] እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፥ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፥ የሚጐዳችሁም ምንም የለም።*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ኤፌሶን 6፡12 አንብቡና ይህ ቃል ከአጋንንት ዓለም ጋር ያለንን መንፈሳዊ ተቃርኖ እንዴት ይገልጸዋል?
**እንደ ትግል ይገልጸዋል።**

2. ማርቆስ 16፡17 ስለአማኝ ስልጣን ይህ ቃል ምን ያስተምረናል?
**በኢየሱስ ስም አጋንንትን እናወጣ ዘንድ ስልጣን ተሰጥቶናል።**

3. ያዕቆብ 4፡7 ከአጋንንት ነጻ መውጣት የሚፈልግ ሰው ምን ማድረግ አለበት?
**እራሳቸውን ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ እና ዲያብሎስን መቃወ።ም**

4. ያዕቆብ 1፡14 ሰይጣን ክፉ ነገር መልካም መሰሎ እንዲታዬን የሚያታልለን በምንድን ነው?
**በገዛ ምኞቶቻችን ይሰራል (ክፉን መልካም በማስመሰል)።**

5. ሮሜ 6፡13 አንድ ሰው ህይወቱን በክርስቶስ ነገሮች ከሞላ፣ አጋንንት ሞቾት ያጡና በራሳቸው ጥለውት ይሸሻሉ። ይህ ቃል ምን እንድናደርግ ይነግረናል?
**እራሳችን ለኃጢአት ሳይሆን ለእግዚአብሔር እንድናቀርብ። የአካል ክፍሎቻችን የመልካም ሥራ መሳሪያ አድርገን ማቅረብ።**

6. ሮሜ 13፡14 አጋንንት የሚመገቡት የስጋ ሥራን ስለሆነ በእግዚአብሔር የፍቅር መንገድ በመራመድና በንጽህና በርሃብ እንዲጠቁ አድርጓቸው። ለስጋ አስፈላጊውን ____ እናድርግለት።
**አቅርቦት።**

7. ሉቃስ 10፡17-19 ኢየሱስ አጋንንት ለማውጣት ወደ እርሱ እንድንጸልይ አልነገረንም። ነገር ግን ስልጣን ሰጥቶናል። ይህ ቃል በ ____ ላይ ሃይልና ስልጣን እንዳለን ይናገራል።
**በጠላት ሃይል ሁሉ።**

## ትምህርት 6

# የአማኝ ስልጣን

### በአንድሩ ዉማክ

አማኝ በመሆናችን እግዚአብሔር ስልጣን ሰጥቶናል። ስልጣን እንደተሰጠን ለመረዳት ፤ የእኛን ብቻ ሳይሆን፣ ሰይጣን ያለው ስልጣን ምን እንደሆነ ጭምር እንመለከታለን ምክንያቱም የሌለው ስልጣን ሁሉ እንዳለው ሆኖ ያለ ልክ ተለጥጧልና ። ከዚህም የተነሳ ክርስቲያኖች የምንዋጋው ከእኛ ይልቅ ትልቅ ሃይል ካለው ፍጡር ጋር እንደሆነና ከአቅማችን በላይ ስለሆነ ከእርሱ ጋር መወዳደር እንደማይቻል እንድናምን ተደርገናል። የእግዚአብሔር ቃል ግን ይህን በፍጹም አያስተምርም። በኤፌሶን 6፡12 እንዲህ ይላል፡-*“መጋደላችን ከሰጋና ከደም ጋር አይደለምና፤ ከአለቆችና ከሰልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሰራዊት ጋር ነው እንጅ”*። ስለዚህ ሰይጣን አለ፤ የክፋት ሁሉ ምክንያት ነው፤ የእኛን ሥራ የሚጠይቁ የሥልጣን ተዋረዶች አለቆችና ሃይላት አሉት። ከዚህ ቃል ቀደም ብሎ ያለው ቁጥር የዲያብሎስን ሽንገላ መቃወም እንዳለብን ይናገራል። ሠይጣን በእኛ ላይ ያለው ብቸኛ ሃይል ሽንገላ ወይም ማታለል ነው። እኛን ሊያሸንፍ የሚችልበት ሌላ ምንም ሃይል የለውም።

በዘፍጥረት 3 የመጀመሪያው ፈተና ወደ አዳምና ሔዋን በመጣ ጊዜ፣ ሰይጣን ከእነርሱ የሚበልጥ ከፍ ያለ ሃይል ይዞ አልመጣም። ለምሳሌ እንደ ዝሆን ወይም አውራሪስ ዓይነት ሌላ ግዙፍ እንሰሳ በመጠቀም ራሳቸውን ረግጦ “ለእኔ ባሪያ ሆናችሁ አገልግሉኝ ካልሆነ ግን …” ብሎ ለማስገደድ ከመሞከር ይልቅ እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ ተንኮለኛ በነበረው እባብ ውስጥ ገባ። “ተንኮለኛ” የሚለው ቃል “አታላይ፣ መሰሪ፣ ክፉ፣ ሸረኛ፣ መሄጃው የማይታወቅ” ማለት ነው። በእባብ በኩል የመጣበት ዋናው ምክንያት አዳምና ሔዋን አንዳች እንዲያደርጉ በምንም አይነት ሁኔታ ሊያስገድዳቸው የሚችልበት ሃይልም ሆነ ስልጣን ስለሌለው ነው። ማድረግ የሚችለው ማታለል ብቻ ነበር። በዚህም የእግዚአብሔርን ማንነትና ባህሪ በመቃረን እግዚአብሔርን መተቸት ጀመረ፣ እንዲህም አላቸው - “በእውነት እግዚአብሔር አይወዳችሁም ከእናንተ የደበቃቸው ነገሮች አሉ” አላቸው። ማታለልን ተጠቅሞ አዳምና ሔዋንን ወደ ፈተና በማስገባት በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት እንዲሰሩ አደረጋቸው። ሙሉ ስልጣን የነበራቸው ግን እነርሱ ነበሩ፤ ሰይጣን በዚህ በኩል ወደ እነርሱ የቀረበበት ምክንያት እግዚአብሔርን ለመቃወም የሚችልበት ምንም ሃይል ስላልነበረው ነበር።

በዚህ ዙሪያ ብዙ ለመናገር ጊዜ የሚወስነን እንደ መሆኑ ወደ ተነሳንበትና ዋናው ትኩረታችን ወደ ሆነው የአማኞች ስልጣን ስንመለስ ሰይጣን በእናንተ ላይ ያለው ሃይል እና ስልጣን ዜሮ መሆኑን ማስታወስ ይኖርባችኋል። ሰይጣን በአማኝ ላይ ምንም ሃይልና ስልጣን የለውም። የተሸነፈ ጠላት ነው። በሃሰትና በማታለል ወደ እናንተ ከመቅረብ ውጭ መቅረብ የሚችልበት ሌላ ሃይል የለውም። ስለዚህ ሕይወታችሁ ችግር ላይ በሚወድቅበትና ጉዳት ባገኛችሁ ጊዜ “ሰይጣን ፍላጻዎቹን ወረወረብኝ” ካላችሁ፣ መሳሪያ ያቀበላችሁት እናንተው እራሳችሁ መሆናችሁን ማወቅ ይኖርባችኋል። ለውሸትና ለማታለሉ ምላሽ የምትሰጡት እራሳችሁ ናችሁ። እራሳችሁን ካላቀረባችሁለት በቀር ሰይጣን ወደ እናንተ የሚቀርብበትም ሆነ በእናንተ ላይ ሃይል የሚያገኝበትን መንገድ በፍጹም አያገኝም። የእግዚአብሔር ቃል በ2ኛ ቆሮንቶስ 10፡3-5 እንዲህ ይላል፡- *“በሰው ልማድ ምንም እንኳ የምንመላለስ ብንሆን፤ እንደ ሰው ልማድ አንዋጋም፤ የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና፣ ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው፤ የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን”*። እነዚህ ቃላት ስለ ጦር ዕቃዎቻችሁ ይናገራሉ፣ የጦር ዕቃዎች ተብለው የሚጠሩት ሁሉ አእምሮአችሁን የሚመለከቱ ሲሆኑ ከሃሳባችሁ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ናቸው። ሰይጣን በማታለል ካልሆነ በቀር ምንም ሊያደርጋችሁ የሚችልበት ሃይል የለውም።

እዚህ ላይ አንዳንድ ነገሮችን ጠቅለል አድርጌ ማቅረብ ይኖርብኛል። በመጀመሪያ ስልጣን ሁሉ በእርግጥ

የእግዚአብሔር ነበር። ምክንያቱም በእራሱ ሃይል ያለው ማንም ስለ ሌለ እና በእራሱ ሃይል ያለው እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ፣ ሁሉም ሃይል እና ስልጣን ከእግዚአብሔር የሚገኝ ነው። ሌላው ነገርም ሁሉ ከእርሱ የሚሰጥ ነው። ሰማይና ምድርን ሲፈጥር ሁሉም ሃይል እና ስልጣን የእራሱ ነበር። በመቀጠል በዘፍጥረት 1:26 እግዚአብሔር አዳም እና ሔዋንን ከፈጠራቸው በኋላ እንዲህ አለ፦ *"... ምድርን ሁሉ፣ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ"።* ይህን ቃል ከመዝሙር 115:16 ጋር አንድ ላይ ከተመለከታችሁት፦ *"የሰማያት ሰማይ ለእግዚአብሔር ነው፤ ምድርን ግን ለሰው ልጆች ሰጣት"* ይላል። እግዚአብሔር የሁሉም ፈጣሪ ስለሆነ በሁሉም ላይ የባለቤትነት ስልጣን አለው። ሆኖም በምድር ላይ ስልጣንን ወይም ገዥነትን ለሰው ልጆች ሰጠ። ሰይጣን በምድር ላይ የመግዛት መብትም ሆነ ሃይል በፍጹም አልነበረውም። ነገር ግን ሰውን አታሎና አሳስቶ በኃጢአት ምክንያት እንዲወድቅ በማድረግ ስልጣኑን ወሰደ። እግዚአብሔር ያንን ሃይል ለሰው ልጅ ሰጠ፤ ነገር ግን ሰው ሲወድቅ እግዚአብሔር የሰጠውን ሃይል እና ስልጣን ለዲያብሎስ አስረከበ። የሰውን ልጅ እንዲጨቁንና ባሪያ እንዲያደርግ፣ ምድርንም እንዲገዛ እግዚአብሔር ለሰይጣን ስልጣን አልሰጠውም።

የእግዚአብሔር ቃል፣ ሰይጣንን የዚህ ዓለም ገዥ ይለዋል፣ ነገር ግን እግዚአብሔር የዚህ ዓለም ገዥ ስላደረገው አይደለም። እግዚአብሔር ከሰው ይልቅ ለሰይጣን ከፍ ያለ ቦታ ሰጥቶት አያውቅም። ይልቁ በምድር ላይ ገዥነትና ስልጣን ሁሉ ለሰው ልጅ የተሰጠ ነው። ሰይጣን በሰው ልጆች ላይ የምናየውን ጭቆና ችግርና ስቃይ የሚያደርሰው ሰዎች ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ስልጣን ስለሚያስረክቡት ብቻ ነው። ይህ ደግሞ ለእግዚአብሔር ትልቅ እንቅፋት ይፈጥርበታል። ምክንያቱም እግዚአብሔር መንፈስ ነው፣ በምድር ላይ ስልጣን የተሰጣቸው የሰው ልጆች ግን ስጋ ለባሽ ወይም የስጋ አካል ያላቸው ናቸው። ባለንባት ምድር ላይ ተጽዕኖ የመፍጠር፣ የመግዛት፣ ሃይልና ስልጣን ያላቸው ስጋ ለባሽ የሆኑት የሰው ልጆች ብቻ ናቸው። ሰይጣን እኛ የተሰጠንን ስልጣን ለእርሱ እንድንሰጠው ለማድረግ ወደ እኛ ይመጣል። ለዚህም ነው በሰው አካል ውስጥ መግባትና መኖር የሚፈልገው። ከእግዚአብሔር ቃል እደምንረዳው አጋንንት የሰውን አካል የሚይዙበት ወይም በሰው ላይ የሚያድሩበት ምክንያት፣ ሰይጣን የሚሰራበት ወይም የሚያድርበት የሰው አካል ወይም ስጋ ካላገኘ በቀር ምንም ዓይነት ነገር ማድረግ ስለማይችል ነው።

እንግዲህ እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ ስልጣኑን ደግሞ የስጋ አካል ላላቸው የሰው ልጆች የሰጠ በመሆኑ፣ በዚህ በኩል እጁ ይታሰራል እንደ ማለት ነው። ይህም የሆነው በእርግጥ እግዚአብሔር ሃይልና ስልጣን ስለሌለው ሳይሆን በሐቀኛነቱ ምክንያት ነው። እግዚአብሔር ለራሱ ቃል ታማኝ ስለሆነ፣ ስልጣንን ለሰው ልጆች ከሰጠ በኃላ መልሶ ለመንጠቅ፣ "እኔ ያሰብኩት እንዲህ አይደለም፣ ይበቃል፣ በቃ አቁሙ፣ ጨርሰናል" አይልም። እግዚአብሔር በራሱ ቃል እራሱን አሰሯል። ከታሪክ እንደምንረዳው ለዘመናት እግዚአብሔር ፈቃዱንና ሃሳቡን የሚፈጽምበት ወይም ከእርሱ ጋር የሚሄድ ሰው ሲፈልግ እናያለን። ችግሩ ግን ሰዎች ራሳቸውን ለሰይጣን አሳልፈው የሰጡና በብልሽት ውስጥ የሚኖሩ ነበሩ። ስለዚህ እግዚአብሔር ምን ያደርጋል?

እግዚአብሔር በመጨረሻ ያደረገው ራሱ ወደ ምድር መምጣትና ሰው መሆን ነበር። ይህ እጅግ ድንቅ የሆነ ታላቅ ክስተት ነው። አሁን ዲያብሎስ ትልቅ ችግር ውስጥ ይገባል። ምክንያቱም እንደ ፈለገ እንዲጠቀምበት ሰው እግዚአብሔር የሰጠውን ሃይልና ስልጣን በራሱ ፈቅዶ ለሰይጣን የሰጠበት ሁኔታ ስለ ነበር፣ እግዚአብሔር ጣልቃ ገብቶ ችግሩን መፍታት እንዳይችል ያደረገው ያንን ስልጣንና ሃይል የሰጠው እራሱ ሰው ስለ ነበር ነው። ሰይጣን ያደረገው ሁሉ ስሕተት ነው። ነገር ግን የራሱን ስልጣንና ሃይል የሰጠው ሰው ነበር። አሁን ግን እግዚአብሔር መጣ። በመንፈስ ሳይሆን ስጋ ለብሶ ነውና የተገለጠው ይህም ሰይጣንን አጣብቂኝ ውስጥ ያስገባ ነበር። ምክንያቱም እግዚአብሔር በሰማይ ብቻ ሳይሆን በምድርም ሰው ሆኖ ስልጣንን የራሱ አድርጓል። ዮሐንስ 5:26-27 እንዲህ ይላል፦ *"አብ በራሱ ህይወት እንዳለው እንዲሁ ደግሞ ለወልድ በራሱ ህይወት እንዲኖረው ሰጥቶታልና። የሰው ልጅም ስለሆነ ይፈርድ ዘንድ ስልጣን ሰጠው"*። በስጋ የተገለጠበትን ሁኔታ ሲገልጽ ይህንን ተናገረ።

ኢየሱስ መጣ፣ እናም እግዚአብሔር ለሰው የሰጠውን ስልጣን ተጠቅሞ መስራት ጀመረ። ዲያብሎስም ፈተነው ነገር ግን አልተንበረከከም። ሰይጣንም ከኢየሱስ ጋር ባደረገው ውጊያ ሁሉ ተሸነፈ። በመቀጠል ኢየሱስ ኃጢአታችንን ሁሉ ወሰደ፤ ለኃጢአታችንም ሞተ፣ ወደ ሲኦልም ወረደ፣ ደግሞም እንደገና ተነሳና በማቴዎስ 28:18 እንዲህ አለ፦ *"ስልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ"*። እግዚአብሔር ለሰው ዘር የሰጠውንና ሰው በአግባቡ ያልተጠቀመበትን ስልጣን አስመለሰ። በስጋ የተገለጠ አምላክ እንደመሆኑም ኢየሱስ በሰማይም በምድርም ስልጣን ሁሉ የእርሱ ነው። ቀጥሎ ባለው ቃል እንዲህ አለ፦ "ሂዱና እነዚህን ነገሮች አድርጉ"። ወይም በሌላ አነጋገር "አሁን በሰማይና በምድር ሁሉ ስልጣን የኔ ነው፤ እኔ ደግሞ ስልጣኔን ለእናንተ አካፍያችኋለሁ" አለ። ነገር ግን፣ አሁን እግዚአብሔር አማኝ በመሆናችን መልሶ በሰጠን ስልጣን ውስጥ እጅግ የተለዬ ነገር እናገኛለን። አሁን የተሰጠን ስልጣን ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተካፈልነው የጋራ የሆነ ስልጣን ነው። ለአዳምና ሔዋን እንደተሰጣቸው ሙሉ በሙሉ በእኛ እጅ ላይ ያለ ስልጣን አይደለም። እነርሱ ስልጣናቸውን ለዲያብሎስ ሊያስረክቡና እንደገና ወደ ባርነትና ወደ ጭቆና፣ ወደ ተሰፋ መቁረጥ ሊገቡ ይችላሉና፣ ነገር ግን ለእኛ የተሰጠን ስልጣን ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በጋራ የተካፈልነው፣ ልክ የጋራ ወይም ጣምራ ፊርማ እንደሚያስፈልገው የባንክ ሒሳብ (Joint account) ዓይነት ነው። ስልጣናችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የተካፈልነው ነው። ኢየሱስ ደግሞ ስልጣኑን ለቤተክርስቲያን አካፍሏታል።

ምንም እንኳን እኛ ብንወድቅ፣ እግዚአብሔር ይህን ስልጣን እንዲወስድ ለሰይጣን አይፈርምለትም። ሰይጣን ሙሉ በሙሉ ሃይል አልባ ሆኗል። በእናንተ ህይወት ውስጥ፣ ካልተታለላችሁና በፈቃዳችሁ ካልሰጣችሁት በቀር፣ ምንም ነገር ለማድረግ ችሎታ የለውም። ምናልባት በህይወታችሁ ላይ ስልጣን ከሰጣችሁት ግን ራሳችሁ ትሰቃዩበታላችሁ እንጅ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሰጠው ስልጣን በፍጹም ወደ ዲያብሎስ እጅ ተመልሶ እንደገና መግባት አይችልም። ምክንያቱም በእኛና በጌታ ኢየሱስ መካከል የጋራ ስልጣን ነው፣ እርሱ ደግሞ ለዘላለም፣ ምንግዜም ታማኝ ሆኖ ይኖራል። አሁን ስልጣን ያላችሁ እናንተ መሆናችሁን ልታውቁ ይገባል። ሰይጣን የሚዋጋችሁ በሃሳባችሁ ወይም በምታስቡት ነገር ላይ ነው። ለዚህ ደግሞ የጦር እቃዎቻችሁ ሃሳባችሁን ለመማረክ ያገለግሉአችኋል። አካላችሁ ላይ ዲያብሎስ ምንም ዓይነት ስቃይ ሊያደርስ አይገባምና የእግዚአብሔር ቃል ስለ ፈውስ - የሚናገረውን አስታውሱ፣ ዮሐንስ 8:32 እንዲህ ይላል፦ *"እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው"*። ሃይልም ስልጣንም ያላችሁ እናንተ ናችሁ። እግዚአብሔር ለእናንተ ሰጥቷችኋል። ነገር ግን ይህንን እንዳትጠቀሙ የሚከለክላችሁ ሃሳባችሁን አለመማረካችሁ ወይም ሃሳባችሁን አለመግዛታችሁ ነው። እነዚህን በእግዚአብሔር ቃል ያሉትን መንፈሳዊ የጦር እቃዎች ተጠቅማችሁ አዕምሯችሁን ባለማደሳችሁና ባለመለወጣችሁ፤ ያላችሁንና የተሰጣችሁንም አልተጠቀማችሁም። ሃይልና ስልጣን የእናንተ መሆኑን ታውቁና ትፈልጉ ዘንድ የሚበረታታ ጉዳይ ነው።

ይህን እንድታውቁ፣ እንድታስቡና እንድታሰላስሉ እለምናችኋለሁ። እግዚአብሔርም ሰይጣን በእናንተ ፊት ምን ያህል እንደሚንቀጠቀጥ የምታዩበትን መገለጥ ይስጣችኋል። የእግዚአብሔር ሃይልና ስልጣን የተሰጠው ለእናንተ ነው። እርሱ እንጂ እናንተ ለሰይጣን መደንገጥና መንቀጥቀጥ ከቶ እያስፈለጋችሁም ዲያብሎስን ከተቃወማችሁት ከእናንተ ይሸሻል (ያዕቆብ 4:7)።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ዘፍጥረት 3:1 እንብቡና ሠይጣን መኖሩን እናውቃለን፣ እኛ ላይ ያለው ሃይል ግን ማታለል ብቻ ነው። እባብ (ዲያብሎስ) ሔዋን ምን እንድትጠይቅ ለማድረግ ሞከረ?

   **ዘፍጥረት 3:1** *እባብም እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠረው ከምድር አውሬ ሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ ነበረ። ሴቲቱንም። በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? አላት።*

2. ዘፍጥረት 3:1 ሰይጣን ለምን ማታለልን የመረጠ ይመስላችኋል?

3. ዘፍጥረት 1:26 እና 28 ለሰው ስልጣንን የሰጠው ማነው?

   **ዘፍጥረት 1:26** *እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌኣችን እንፍጠር፤ የባህር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፣ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፣ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ።*

   **ዘፍጥረት 1:28** *"እግዚአብሔርም ባረካቸው፣ እንዲህም አላቸው፦ ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት*

4. መዝሙር 8:4-8 እግዚአብሔር ሰውን እንዴት ፈጠረው?

   **መዝሙር 8:4-8** *ታስበው ዘንድ ሰው ምንድር ነው? ትጐበኘውም ዘንድ የሰው ልጅ ምንድር ነው? [5] ከመላእክት እጅግ ጥቂት አሳነስኸው፤ በክብርና በምስጋና ዘውድ ከለልኸው። [6] በእጆችህም ሥራ ሁሉ ላይ ሾምኸው፤ ሁሉን ከእግሮቹ በታች አስገዛህለት፥ [7] በጎችንም ላሞችንም ሁሉ ደግሞም የምድረ በዳውን እንስሶች፥ [8] የሰማይንም ወፎች የባሕርንም ዓሦች፥ በባሕር መንገድ የሚሄደውንም ሁሉ። 2ኛ ቆሮንቶስ 4:4 ይህ ቃል ምን እንደተከሰተ ያመለክታል?*

   **2ኛ ቆሮንቶስ 4:4** *"ለእነርሱም የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው፥ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ።"*

5. ማቴዎስ 4:8-9 እነዚህ ቃላት ይህንን ያጠናክራሉ?

   **ማቴዎስ 4:8-9** *ደግሞ ዲያቢሎስ እጅግ ረጅም ወደ ሆነ ተራራ ወሰደው፥ የዓለምንም መንግሥታት ሁሉ ክብራቸውንም አሳይቶ። [9] ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ አለው።*

6. ማቴዎስ 28:18 ከኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ በኋላ በሰማይና በምድር ስልጣን የማነው?

   **ማቴዎስ 28:18** *ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው። ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ።*

7. ማቴዎስ 28:18-19 በዚህ ቃል መሰረት ኢየሱስ ሰልጣኑን ለማን አካፈለ?

   **ማቴዎስ 28:18-19** *ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው። ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። [19] እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤*

8. ኤፌሶን 1፡19 ከሁሉ የሚበልጥ የሃይሉ ታላቅነትን ለማን ነው?

   **ኤፌሶን 1፡19** *ይህም የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለ ጠግነት ምን እንዲሆን ለምናምን ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ ነው፤*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ዘፍጥረት 3፡1 እንብቡና ሠይጣን መኖሩን እናውቃለን፣ እኛ ላይ ያለው ሃይል ግን ማታለል ብቻ ነው፡፡ እባብ (ዲያብሎስ) ሔዋን ምን እንድትጠይቅ ለማድረግ ሞከረ?
   **የእግዚአብሔርን ቃል (እግዚአብሔር አዟል?)፡፡**

2. ዘፍጥረት 3፡1 ሰይጣን ለምን ማታለልን የመረጠ ይመስላችኋል?
   **በሃይል እንዳይቀበሉት ማድረግ ስለማይችል፡፡ ስልጣናቸውን እንዲጥሉ ለማድረግ እነርሱን ማታለል ነበረበት፡፡**

3. ዘፍጥረት 1፡26 እና 28 ለሰው ስልጣንን የሰጠው ማነው?
   **እግዚአብሔር፡፡**

4. መዝሙር 8፡4-8 እግዚአብሔር ሰውን እንዴት ፈጠረው?
   **በእጆቹ (በእግዚአብሔር) ሥራ ሁሉ ላይ በመሾም፡፡**

5. 2ኛ ቆሮንቶስ 4፡4 ይህ ቃል ምን እንደተከሰተ ያመለክታል?
   **ሰይጣን የሰውን ስልጣን ወሰዶ የዚህ ዓለም (የዚህ ስርዓት ወይም የዚህ ዘመን) ዓምላክ እንደተባለ ያመለክታል፡፡**

6. ማቴዎስ 4፡8-9 እነዚህ ቃላት ይህንን ያጠናክራሉ?
   **አዎ፡፡**

7. ማቴዎስ 28፡18 ከኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ በኋላ በሰማይና በምድር ስልጣን የማነው?
   **የኢየሱስ፡፡**

8. ማቴዎስ 28፡18-19 በዚህ ቃል መሰረት ኢየሱስ ስልጣኑን ለማን አካፈለ?
   **ለአማኙ፡፡**

9. ኤፌሶን 1፡19 ከሁሉ የሚበልጥ የሃይሉ ታላቅነትን ለማን ነው?
   **ለእኛ ለምናምነው፡፡**

## ትምህርት 7

# ፈውስ ያለው በስርየት ነው

### በአንድሩ ዉማክ

ፈውስ በኢየሱስ ተገዝቶልናል። በማርቆስ ምዕራፍ 2 እና በሉቃስ ምዕራፍ 5 ኢየሱስ በቤት ውስጥ ሆኖ እያስተማረ በነበረበት ጊዜ፣ ከህዝቡ ብዛት የተነሳ ቤቱ በሰው ተጨናንቆ ስለ ነበር አንድ ሽባ የነበረን ሰው ጓደኞቹ የቤቱን ጣሪያ ነድለው በአልጋ ወደታች አዲወርድ አደረጉት፣ ኢየሱስም በድንቅ ተዓምር ፈወሰው። ማቴዎስ 8፡14-16 ህዝቡን ሁሉ ከፈወስ በኋላ በመቀጠል የሆነውን ሲናገር፦ *"ኢየሱስም ወደ ጴጥሮስ ቤት ገብቶ አማቱን በንዳድ ታማ ተኝታ አያት፣ እጅዋንም ዳሰሰ፣ ንዳዱም ለቀቃት፣ ተነሰታም አገለገለቻቸው። በመሸም ጊዜ አጋንንት ያደረባቸውን ብዙዎችን ወደ እርሱ አመጡ"* ይላል። የዚህን ምክንያት በቁጥር 17 እንዲህ ሲል ይናገራል፦ *"በነብዩ በኢሳይያስ እርሱ ድካማችንን ተቀበለ ደዌያችንንም ተሸከመ የተባለው ይፈጸም ዘንድ መናፍስትን በቃሉ አወጣ፣ የታመሙትንም ሁሉ ፈወሰ"* ይላል። እንግዲህ በእነዚህ ጊዜያት ኢየሱስ ብዙ ሰዎችን እየፈወሰ ነበርና የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኋላ ተመልሶ በነብዩ በኢሳይያስ መጽሐፍ ምዕራፍ 53 ቁጥር 3 እስከ 5 የተጻፈውን ቃል ይጠቅሳል። *"የተናቀ ከሰውም የተጠላ* [ይህ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረ ትንቢት ነው]፣ *የህማም ሰው፣ ደዌንም የሚያውቅ ነው፤ ሰውም ፊቱን እንደሚሰውርበት የተናቀ ነው። እኛም አላከበርነውም። በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንም ተሸክሞአል፣ እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደተቀሰፈ እንደተቸገረም ቆጠርነው። እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቆሰለ፣ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሳጽ በእርሱ ላይ ነበረ በእርሱም ቁሰል እኛ ተፈወስን"* ይላል፣ (በቅንፍ ያለው በእኔ የተጨመረ ነው)።

ከላይ ያነበብነው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሃይለ ቃል እጅግ ከተሞሉ ክፍሎች ውስጥ አንዱን ነው። አንዳንድ ሰዎች እነዚህ ቃላት - "ስለ መንፈሳዊ ነገር የሚናገሩ ናቸው" ሊሏችሁ ይችላሉ። እኔ ያደግኩባት ቤተክርስቲያንም ብትሆን በሥጋ ፈውስ አታምንም ነበር። እነዚህ ሰዎች እንዲህ ዓይነት ቃላትን ወሰደው መንፈሳዊ በማድረግ ይጠቀሙባቸዋል - በውስጥ ስሜታችን ተጎድተን ነበር፣ ህይወታችንን ለጌታ ከሰጠን በኋላ ግን እርሱ ያድነናል ይላሉ። ነገር ግን በኢሳይያስ የተነገሩትን ቃሎች ከላይ ካየነው የማቴዎስ ወንጌል ቃል ጋር አንድ ላይ ከተመለከትናቸው፤ በቃሎቹ ላይ የሚነሳውን ብዥታ ፍጻሜ እንዲያገኝ ያደርጋል። እውነት ነው፣ በእርግጥ ኢየሱስ የሰሜት መጎዳታችሁንም ሆነ ሌላውን ችግሮቻችሁንም ሁሉ ይፈውሳል፣ ነገር ግን እነዚህ ቃላት ስለ ሰውነታችን ወይም ስለ ሥጋ ፈውስ የሚናገሩ ናቸው። ይህን የሚያረጋግጥልንም ከላይ በማቴዎስ 8፡17 ፈውሶቹ የተከናወኑት በኢሳይያስ የተነገረው የትንቢት ቃል ፍጻሜ ማግኘቱን ለማመላከት ነው ሲል የሚናገረው ቃል ሲሆን *"በእርሱም ቁሰል እኛ ተፈወሰን"* የሚለውንም አንብበናል። ይህም የሚነግረን እርሱ ራሱ ደዌአችንን እንደተቀበለ ሕመማችንንም እንደተሸከመ የተናገረው ቃል መፈጸሙን ነው። በሥጋ ስለ መታመም፣ ስለ መጎዳትና ስለ መቁሰል ይናገራል። ኢየሱስ በእርሱ ቁሰል እኛ ተፈወስን ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸም ዘንድ አካላቸው ወይም ሥጋቸው ላይ ከሚያጋጥማቸው ችግር ሁሉ ሰዎችን ይፈውስ ነበር።

በመቀጠል መጽሐፍ ቅዱስ በ1ኛ ጴጥሮስ 2፡24 እንዲህ ይላል፦ *"ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፣ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤ በመገረፉ ቁሰል ተፈወሳችሁ።"* ይህም ያለፈን የተከናወነን የሚያሳይ ቃል ነው። ኢየሱስ መጥቷል፣ በመምጣቱም ከሰራልን ስራዎች መካከል አንዱ የሥጋችን ፈውስ ነው። የኃጢአት ይቅርታ ሊያደርግልን እንደ መጣ የምናውቀውን እውነት ለማኮሰስ ፈልጌ አይደለም። ይህም እጅግ ያስፈልገናል፣ የኃጢአት ይቅርታ ወደ ሌሎቹ ነገሮች ሁሉ እንደ መተላለፊያ፣ የመግቢያ በር ነው። ነገር ግን ኢየሱስ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ብቻ ሳይሆን አካላችን ወይም ሥጋችን ሊፈውስም ጭምር መጥቷል። በግሪክ "መዳን" ለሚለው ቃል የአዲስ ኪዳን ትርጉም ሶዞ (sozo) ሲሆን ይህ ቃል ለብዙ የተለያዩ ነገሮች መዋል የሚችል ሁሉን አቀፍ ቃል ነው። በደምብ ካስተዋላችሁት ይህ ቃል "ፈውስ" የሚል ትርጉም ጭምር እንደያዘ ትገነዘባላችሁ። ያዕቆብ 5፡14-15 *"ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ሽማግሌዎች*

*ወደ እርሱ ይጥራ፤ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት። የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል ጌታም ያስነሳዋል፣ ኃጢአትንም ሰርቶ እንደሆነ ይሰረይለታል"* ይላል። ድውዩን ‹‹ያድናል›› የሚለው ቃል የግሪኩ SOZO ነው። የሚናገረውም የታመሙ የሥጋ ፈውስ ስለሚያገኙበት ሁኔታ ነው። ይህ በአዲስ ኪዳን ከመቶ በላይ በሚሆኑ ቦታዎች የኃጢአት ይቅርታ የሚል ትርጉምን የያዘ ቃል፣ ፈውስ በሚል ጭምር ተተርጉሟል።

በማቴዎስ 10 ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ሲልካቸው የሰጣቸው ትዕዛዝ፡- ድውዮችን እንዲፈውሱ፣ ለምጻሞችን እንዲያነጹ፣ ሙታንን እንዲያስነሱ፣ አጋንንትን እንዲያወጡ እና ወንጌል እንዲሰብኩ ነው። ወንጌልን እንዲሰብኩ ባዘዘበት ቃል እኩል የታመሙትን እንዲፈውሱ፣ ለምፃሞችን እንዲያነፁ እና አጋንንትን እንዲያወጡ ልኮአቸዋል። ኢየሱስ ለኃጢአት ይቅርታ የመጣውን ያህል በህይወታችሁ ሊያከናውናቸው ከመጣባቸው ጉዳዮች አንዱ ፈውስ ነው።

የኃጢአትን ጎጅነት ታውቁ ዘንድ ከኃጢአት ለመማር ኃጢአት እንድንሰራ ጌታ አይፈልግም ብላችሁ እንደምታስቡ ሁሉ፣ በህመም እንድትኖሩ ወይም በሽተኛ እንድትሆኑም አይፈልግም። እግዚአብሔር በእናንተ ላይ ያለው በሽታ ወይም ህመም ደራሲ አይደለም። አንዳንድ ሰዎች ሲታመሙ ‹‹ይህ ህመም ወደ ጌታ እንድመጣ አድርጎኛል እግዚአብሔር ወደ እርሱ እንድመለስ የሰጠኝ በረከት ነው›› ይላሉ። እርግጥ ነው በችግር ጊዜ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ይመለሳሉ። ነገር ግን እግዚአብሔር ሰዎችን ለመመለስ ወይም ለማስተማር በሽታን አይልክም። ኃጢአትን እንደማይልክ ሁሉ እግዚአብሔር እናንተን ለማስተማር በሽታን አይልክም።

በኃጢአት ውስጥ ሆናችሁ ልትማሩ የምትችሉት ምን ደህና ነገር አለ? በዝሙት ወይም በግብረሰዶም ውስጥ ገብታቸሁ በበሽታ ብትያዙ እንዲህ ዓይነት ህይወት መልካም እንዳልሆነ ትምህርት ታገኙበታላችሁ? በእርግጥ ትምህርት ልታገኙበት ትችላላችሁ፣ ነገር ግን ይህን መልካም ያልሆነ ሕይወት እንድትኖሩ ያደረጋችሁ እግዚአብሔር አይደለም። እግዚአብሔር በሕይወታችሁ ውስጥ ኃጢአትን አያመጣም፣ ይሁን እንጂ ከኃጢአታችሁ ልትማሩ ግን ትችላላችሁ። እራሳችሁን ከግድግዳ ጋር በሃይል አጋጭታችሁ ይህን ማድረግ እንዳልነበረባችሁ ልትማሩ ትችላላችሁ፣ ነገር ግን ሰውነታችሁን ሳትጎዱ እራሳችሁን ሳታጋጩም ቢሆን መማር ትችሉ ነበር። ሁሉንም ነገር በጉልበት መማር የለባችሁም። እግዚአብሔር ትሁት እንድትሆኑና አንዳንድ ነገሮችን ለማስተማር በሽታን በሕይወታችሁ አያመጣም። ኃጢአታችሁን በገዛ ሰውነቱ ተሸክሞአል፣ በመገረፋም ቁስል ተፈውሳችኋል።

የእግዚአብሔር ልዕለ ተፈጥሮ (Supernatural) ፈውስ ለሁላችንም የተሰጠ እና ኢየሱስ በሞቱ ካስገኘልን ስርየት ውስጥ አንዱ ክፍል ነው። ፈውስ ባታገኙም ግን እግዚአብሔር ቅር ይሰኛል ማለት አይደለም። እግዚአብሔርን ለመውደድ የግድ ፈውስ ማግኘት አለባችሁ ማለት አይደለም። ፈውስ እንዳለ ሳታምኑም ቢሆን እግዚአብሔርን በሙሉ ልባችሁ ልትወዱትና በዘመናችሁም ፍጻሜም ወደ ሰማይ ቤታችሁ በሰላም ልትሄዱ ትችላላችሁ። እውነት ለመናገር በፈውስ መኖርን ባታውቁ እንኳን ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር ፈጥናችሁ ከዚህች ምድር ትሄዳላችሁ እንጅ ፈውስ ግን ለእናንተ ተዘጋጅቶላችኋል። ኢየሱስም ይህን ሊሰጠን መጥቷልና። እግዚአብሔር ደህና መሆናችሁን ይወዳል፤ ያስደስተውማል።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ማቴዎስ 8፡16-17 ኢየሱስ የፈወሳቸው ምን ያህል ሰዎችን ነው?

   **ማቴዎስ 8፡16-17** *በመሸም ጊዜ አጋንንት ያደረባቸውን ብዙዎችን ወደ እርሱ አመጡ፤ በነቢዩ በኢሳይያስ። እርሱ ድካማችንን ተቀበለ ደዌያችንንም ተሸከመ የተባለው ይፈጸም ዘንድ፥ መናፍስትን በቃሉ አወጣ፥ የታመሙትንም ሁሉ ፈወሰ።*

2. ኢሳያስ 53፡3-5 እነዚህ ቃላት ስለ ምን አይነት መዳን ይናገራሉ?

   **ኢሳይያስ 53፡3** *የተናቀ ከሰውም የተጠላ፥ የሕማም ሰው ደዌንም የሚያውቅ ነው፤ ሰውም ፊቱን እንደሚሰውርበት የተናቀ ነው፥ እኛም አላከበርነውም። [4] ፤ በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸክሞአል፤ እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቈጠርነው። [5] ፤ እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን።*

3. ማቴዎስ 8፡17 ደዌዎቻችንና ድካማችን ምን ሆነዋል?

4. 1ኛ ጴጥሮስ 2፡24 በዚህ ቃል መሰረት ኢየሱስ የሰራልን ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው?

   **1ኛ ጴጥሮስ 2፡24** *"ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፥ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ"*

5. ያዕቆብ 5፡14-15 ቁጥር 15 ላይ "ያድናል" የሚለው ቃል በግሪኩ SOZO የሚለው ሲሆን ትርጉሙም ነፃ መውጣት፣ መጠበቅ (ጥበቃ ማግኘት)፣ መፈወስ፣ መንከባከብና ሙሉ ማድረግ የሚል ነው። በዚህ ቃልና በግሪኩ ትርጉም መሰረት በመዳናችሁ ላይ የተጨመረላችሁ ምንድን ነው?

   **ያዕቆብ 5፡14** *ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ሽማግሌዎች ወደ እር ሱ ይጥራ፤ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት። [15] የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል ጌታም ያስነሣዋል፤ ኃጢአትንም ሠርቶ እንደ ሆነ ይሰረይለታል።*

6. ማቴዎስ 10፡7 ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ሲልካቸው ምን እንዲናገሩ አዘዛቸው?

   **ማቴዎስ 10፡7** *"ሄዳችሁም። መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች ብላችሁ ስበኩ"።*

7. ማቴዎስ 10፡8 ኢየሱስ ምን እንዲያደርጉ አዘዛቸው?

   **ማቴዎስ 10፡8** *ድውዮችን ፈውሱ፤ ሙታንን አስነሡ፤ ለምጻሞችን አንጹ፤ አጋንንትን አውጡ፤ በከንቱ ተቀበላችሁ፥ በከንቱ ስጡ።*

8. ማርቆስ 16፡15 ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ምን እንዲያደርጉ አዘዛቸው?

   **ማርቆስ 16፡15** *እንዲህም አላቸው። ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ።*

9. ማርቆስ 16፡16 ወንጌሉን የተቀበሉ ምን ማድረግ አለባቸው?

   **ማርቆስ 16፡16** *ያመነ የተጠመቀም ይድናል፥ ያላመነ ግን ይፈረድበታል።*

10. ማርቆስ 16፡17 ያመኑትን ምን ምልክቶች ይከተሉአቸዋል?

    **ማርቆስ 16፡17** *ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፤ እባቦችን ይይዛሉ፥*

11. ማርቆስ 16፡18 ያመኑትን ምን ሌሎች ምልክቶች ይከተሉአቸዋል?

    **ማርቆ 16፡18** *የሚገድልም ነገር ቢጠጡ አይጎዳቸውም፤ እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ።*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ማቴዎስ 8፡16-17 ኢየሱስ የፈወሳቸው ምን ያህል ሰዎችን ነው?
**ወደ እርሱ የመጡትን ሁሉ።**

2. ኢሳያስ 53፡3-5 እነዚህ ቃላት ስለ ምን አይነት መዳን ይናገራሉ?
**ሁሉንም ዓይነት ፈውስ (የአካልን ጨምሮ)።**

3. ማቴዎስ 8፡17 ደዌዎቻችንና ድካማችን ምን ሆነዋል?
**ኢየሱስ ተሸክሟቸዋል።**

4. 1ኛ ጴጥሮስ 2፡24 በዚህ ቃል መሰረት ኢየሱስ የሰራልን ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው?
**በሥጋው ኃጢአታችንን ተሸከመ ለፈውሳችንም ተገረፈ።**

5. ያዕቆብ 5፡14-15 ቁጥር 15 ላይ ‹‹ያድናል›› የሚለው ቃል በግሪኩ SOZO የሚለው ሲሆን ትርጉሙም ነፃ መውጣት፣ መጠበቅ (ጥበቃ ማግኘት)፣ መፈወስ፣ መንከባከብና ሙሉ ማድረግ የሚል ነው። በዚህ ቃልና በግሪኩ ትርጉም መሰረት በመዳናችሁ ላይ የተጨመረላችሁ ምንድን ነው?
**ፈውስ።**

6. ማቴዎስ 10፡7 ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ሲልካቸው ምን እንዲናገሩ አዘዛቸው?
**መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች።**

7. ማቴዎስ 10፡8 ኢየሱስ ምን እንዲያደርጉ አዘዛቸው?
**ድውዮችን ፈውሱ፤ ሙታንን አስነሡ እና አጋንንትን አውጡ።**

8. ማርቆስ 16፡15 ኢየሰሱስ ደቀ መዛሙርቱ ምን እንዲያደርጉ አዘዛቸው?
**ወደ ዓለም ሁሉ እንዲሄዱ እና ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ እንዲሰብኩ።**

9. ማርቆስ 16፡16 ወንጌሉን የተቀበሉ ምን ማድረግ አለባቸው?
**ማመንና መጠመቅ።**

10. ማርቆስ 16፡17 ያመኑትን ምን ምልክቶች ይከተሉአቸዋል?
**አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ።**

11. ማርቆስ 16፡18 ያመኑትን ምን ሌሎች ምልክቶች ይከተሉአቸዋል?
**እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ።**

## ትምህርት 8

# የፈውስ እንቅፋቶች

### በአንድሩ ዉማክ

በትምህርት ሰባት፣ ፈውስ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነና የስርየት አንዱ ክፍል መሆኑን ጭምር ተመልክተናል። በዚህ ዙሪያ ብዙ መነጋገር እንችላለን፣ ምክንያቱም ይህን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያነበባችሁና ያመናችሁ ብትሆኑም እንኳን - “እግዚአብሔር ሊፈውስን ፈቃዱ ከሆነ፣ ሰው ሁሉ የማይፈወሰው ለምንድን ነው?” የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሳታችሁ አይቀርም። ምክንያቶቹ ብዙ ናቸው፣ እኔም ከማውቀው ውስጥ እንዲሁ ላይ ላዩን በጨረፍታ ካልሆነ በቀር አሁን ልገልጻቸው የማልችላቸው ብዙ መረጃዎች ያሉ ሲሆን፣ ፈውስ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ ሰዎች ለምን አይፈወሱም ለሚለው የተወሰነውን ክፍል እዚህ ላይ ለማቅረብ እወዳለሁ። የመጀመሪያው ምክንያት “አለማወቅ” (Ignorance) ነው። በማታውቁት ወይም ባልተረዳችሁት ነገር መጠቀም አትችሉም፣ በእኔ ህይወት ያጋጠመኝ ይህ ነበር።

የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲሁ እንደሚፈጸም እና እኔም ምንም ሃይል፣ ስልጣንም ሆነ ይሁንታ እንደሌለኝ እንዳምን ሆኜ ነበር ያደኩት። ስለዚህ ባለማወቄ ውስጥ አንዳንድ ነገሮች ይከሰቱ ጀመር። አስራ ሁለት ዓመት ሲሞላኝ አባቴ ሞተ፣ በሃያ አንድ ዓመት እድሜዬም ሁለት ወይም ሦሥት ሰዎች እኔ ባለሁበት ሲሞቱ ተመልክቻለሁ። ሁሉም እንዲፈወሱ የጸለይኩላቸው ቢሆንም አንዳቸውም ያልተፈወሱ ሲሆን፣ ሰዎቹ ያልተፈወሱት እግዚአብሔር ሊፈውሳቸው ፈቃዱ ስላልሆነ ሳይሆን በእኔ በኩል ባለው አለማወቅ ምክንያት ነበር። አለማወቅ የነገሮች ምክንያት እንጂ ሽፋን መሰጫ አይደለም። ልክ እንደ ሰበት ሕግ ነው፡ አንድ ሰው - “ከአንድ ሕንጻ አስረኛ ፎቅ ወደ መሬት መዝለል ሊገድለኝ ይችል እንደሆነ አላውቅም” ብሎ ሊናገር ይችላል። ነገር ግን ሕግ ሙሉ በሙሉ እንዴት እደሚሰራ ለማወቅ እራሳችሁ ላይ ሙከራ በማድረግ ለማረጋገጥ መሞከር አይኖርባችሁም። ሰዎች ስለ አንዳንድ የእግዚአብሔር ሕጎች ምንም እውቀት የላቸውም። የእግዚአብሔር የፈውስ ስርዓት እንዴት እንደሚሰራ ባለማወቃቸው ምክንያት ብዙዎችን አለማወቅ እያጠፋቸው ይገኛል።

ፈውስ እንዳንቀበል ሌላው እንቅፋት የሚፈጥርብን ኃጢአት ነው። ምናልባት እንዲህ ብላችሁ ስትናገሩ ሰዎችን ሊያስቆጣ ይችላል። ከንግግራችሁ በመነሳት የሁሉም በሽታዎች ምክንያት የእራሳችን ኃጢአት ነው የሚል ትርጉም ሊሰጡት ይችላሉ፣ ነገር ግን አይደለም። በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ዘጠኝ ኢየሱስ ከመቅደስ እየወጣ በነበረበት ጊዜ ያጋጠመውን ብንመለከት፣ ደቀ መዛሙርቱ ከመወለዱ ጀምሮ ማዬት የተሳነውን አንድ ሰው አሳዩት። ወደ እርሱ ቀርበውም በቁጥር 2 ፡- *“መምህር ሆይ ይህ ሰው ዕውር ሆኖ እንዲወለድ ኃጢአት የሠራ ማን ነው? እርሱ ወይስ ወላጆቹ ብለው ጠየቁት?”* በሌላ አነጋገር በሽታውን በቀጥታ ከኃጢአት ጋር በማያያዝ የእርሱ ነው ወይስ የወላጆቹ ኃጢአት፣ የትኛው ነው ይህ ህመም በእርሱ ላይ እንዲመጣ ያደረገው የሚለውን ለመለየት እየሞከሩ ነበር። የኢየሱስ ምላሽ ግን እርሱ ወይም ወላጆቹ ኃጢአት አልሰሩም የሚል ነበር። ይህ ማለት ግን እርሱ ወይም ወላጆቹ ኃጢአት ሰርተው አያውቁም ማለት ሳይሆን ነገር ግን ሰውየው ማዬት የተሳነው በቀጥታ በእነርሱ ኃጢአት ምክንያት አለመሆኑን ለማመልከት ነው። ሁሉም በሽታዎች ከኃጢአት ጋር ግንኙነት አላቸው ብሎ መናገር ትክክል አይደለም፣ ነገር ግን ኃጢአት ከምክንያቶቹ ውስጥ አንዱ አይደለም ማለትም ትክክል አይደለም።

የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 5፣ ኢየሱስ ቤተሳይዳ ተብሎ ወደ ሚጠራው የመጠመቂያ ስፍራ በመጣ ጊዜ ለአንድ ሰው ተዓምራዊ ፈውስ እንዳደረገ ይነግረናል። በስፍራው እጅግ ብዙ ሰዎች የነበሩ ቢሆንም ፈውስ ያገኘው አንድ ሰው ብቻ ነበር። በኋላ ግን አይሁድ ሰውዬውን በጠየቁት ጊዜ ማን እንደፈወሰው እንኳን እንደማያውቅ በዚሁ ምዕራፍ እንመለከታለን፤ ቁጥር 12 እንዲህ ይላል፡- *“እነርሱም አልጋህን ተሸክመህ ሂድ፣ ያለህ ሰው ማን ነው?”* በመቀጠል ቁጥር 13-14፡- *“ዳሩ ግን በዚያ ስፍራ ሕዝብ ስለነበሩ ኢየሱስ ፈቀቅ ብሎ ነበርና የተፈወሰው ሰው ማን እንደሆነ አላወቀም። ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በመቅደስ አገኘውና እነሆ ድነሃል፤ ከዚህ የሚብስ እንዳይደርስብህ ወደ ፊት ኃጢአት አትሥራ አለው”*። እዚህ ላይ ኃጢአት ከሸባነቱ በላይ የከፋ ሌላ ችግር ሊያስከትልበት

እንደሚችል ኢየሱስ ለዚህ ሰው በቀጥታ ሲነግረው እናያለን። በዚህም የህመም ምክንያት ከኃጢአት ጋር ሲተሳሰር እንመለከታለን። በተጨማሪም በዮሐንስ 9 በማንም ኃጢአት ምክንያት ይህ ሰው አይነ ስውር ሆኖ እንዳልተወለደ ይናገራል።

አንዳንድ ነገሮች እንዲሁ በተፈጥሮ ሊከሰቱ ይችላሉ። ይሁን እንጂ ህመም፣ በሽታ ወይም ችግሮች በቀጥታ የኃጢአት ውጤት የሚሆኑበትም ጊዜ አለ። ታዲያ እነዚህን ነገሮች በእኛ ላይ እንዲመጡ ያደረገው እግዚአብሔር ነው ማለት አይደለም። ለምሳሌ ከተፈጥሮ ተቃራኒ በሆነ መንገድ በግብረ ሰዶም ህይወት ውስጥ የሚኖርን አንድን ሰው ውሰዱ። ሰውነታችን በዚህ መንገድ እንዲኖር አልተፈጠረም። በግብረ ስጋ የሚተላለፉ በሽታዎች ከዚህ ዓይነት የሕይወት ዘይቤ የሚመጡ ናቸው። ተፈጥሮ ይህን በእራሷ ትቃወማለች ወይም አትቀበለውም እንጂ የእነዚህ በሽታዎች ደራሲ እግዚአብሔር አይደለም፤ ተፈጥሮ ግን በዚህ ዓይነት መንገድ እንድትሰራ አልተዘጋጀችምና ኢ-ተፈጥሯዊ የሆነውን ሥርዓት ትቃወማለች። ለሰውነታችሁ የማይስማማ ምግብ ብትመገቡ ሰውነታችሁ ይቆጣል፣ ያን ያደረገው ግን እግዚአብሔር አይደለም የሰውነታችሁ ተፈጥሮ ሰለማይቀበለው ነው። እዚህ ላይ የተፈጥሮ ሕጎች፣ የተፈጥሮ ምክንያቶች አሉ። ሰለዚህ ሰዎች ፈውስ መቀበል እንዳይችሉ ኃጢአት ምክንያት ሊሆን ይችላል የሚለው እውነት ነው።

እግዚአብሔር ፈውስ እንደሚሰጣችሁ አምናችሁ ነገር ግን በሕይወታችሁ የሚታወቅ እና አሁንም አብሯችሁ ያለ ኃጢአት ቢኖር፣ በኃጢአት ምክንያት ለሌባው በር ከፍታችሁለታልና ፈውስ ይሆንላችሁ ዘንድ ኃጢአታችሁን ልታቆሙ ወይም ልታሰወግዱት ይገባል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ያዘጋጀላችሁን ፈውስ እንዳታገኙ እንቅፋት ስለሚሆንባችሁ ነው። ሮሜ 6፡16 እንዲህ ይላል፡- *“ለመታዘዝ ራሳችሁን ለምታቀርቡለት፣ ለእርሱ ለምትታዘዙለት ባሪያዎች እንደሆናችሁ አታውቁምን? ወይም ለሞት የኃጢአት ባሪያዎች ወይም ለጽድቅ የመታዘዝ ባሪያዎች ናችሁ”*። ይህ ማለት ግን ሰይጣን ጌታችሁ ይሆንና መዳናችሁ ቀርቶ ሲኦል ትወርዳላችሁ ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ክርስቲያን ሆናችሁ አልሆናችሁ በኃጢአት ውስጥ የምትኖሩ ከሆነ ለሰይጣን ወደ ህይወታችሁ ሰተት ብሎ የሚገባበትን በር ትከፍቱለታላችሁ ማለት ነው። ዮሐንስ 10፡10 ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ፣ ሊያጠፋም እንጅ ሰለ ሌላ እንደ ማይመጣ፤ ኢየሱስ ግን ህይወት ሊሰጣችሁ እንደ መጣ ይናገራል። ኢየሱስ ሕይወት እንዲሆንላችሁ የራሱን ሕይወት ጤናውንም ሰጥቷችኋል፤ ነገር ግን በሌላ በኩል ሰይጣን ደግሞ እንድትታመሙ ለማድረግ ይሞክራል። ሰለዚህ በኃጢአት ምክንያት ለሰይጣን ከታዘዛችሁ፣ በእናንተ ላይ ጉዳት የሚያደርስበትን ሃይል እና እድል እየሰጣችሁት ነው። ለሚያሰፈልጋችሁ አይነት ፈውስ ወደ እግዚአብሔር ልትጸልዩና ልትጠይቁ ትችላላችሁ። በሌላ በኩል በድርጊታችሁ ህመም የሚያሰገባበትን በር ለሌባው ከፍታችሁ ይሆናል። ሰለዚህ በኃጢአት ውስጥ የምትኖሩ ከሆነ አሁኑኑ ልታቆሙ ይገባል።

በተጨማሪም የራሱን ውስጥ ብቻ የሚመለከት ዓይነት ሰው ከሆናችሁ - “እኔ ሁሌም መሆን ከሚገባኝ በታች ነኝ” በሚል፣ ምንም እንኳን እግዚአብሔር እንደሚፈውስ ብታምኑም እናንተ ግን የማይገባችሁ ስለሆናችሁ እንደምትፈወሱ ላታምኑ ትችላላችሁ። ይህም ፍጹም ትክክል አይደለም። ምክንያቱም ፈውስን ከእግዚአብሔር ለማግኘት ማናችንም ብንሆን በራሳችን የበቃን ወይም የተገባን አይደለንም። ለእርሱ የሚሰራለት ፍጹም የሆነ ሰው መቸም ቢሆን እግዚአብሔር ኖሮት አያውቅም፣ ሰለዚህ እግዚአብሔር በሕይወታችሁ የሚንቀሳቀስበትን መንገድ ከአፈጻጸማችሁ እና ከቅድስናችሁ ልክ ጋር ማያያዝ ተገቢ አይደለም። ይልቁንም ኢየሱስ ለእናንተ የሰራላችሁ ስራ እና በእርሱ ማመናችሁ ብቻ መሰረት ሊሆናችሁ ይገባል። ከዚህም በተጨማሪ የእናንተን ተግባር ችላ ብላችሁ ያለተቃውሞ ለዲያብሎስ እራሳችሁን ማስገዛትም አይገባም። ንስሐ በመግባት እና ለሰይጣን ወደ ሕይወታችሁ የመግቢያ በር የሚከፍትለትን ማንኛውንም ዓይነት ተግባር ከህይወታችሁ በማሰወገድ፣ ፈውስ በቀላሉና በተሻለ ሁኔታ በሕይወታችሁ ሲገለጥ ማየት ትችላላችሁ።

ፈውስን በተመለከተ ሌላው፣ ግን ደግሞ ብዙ ሰዎች ብዙም ትኩረት የማይሰጡት የሌሎች ሰዎች አለማመንና

ተቃውሞ በእናንተ ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖ ነው። ለዚህ በጣም ጥሩ ማሳያ አለን። በማርቆስ ወንጌል ምእራፍ 6 ኢየሱስ ወደ ገዛ መንደሩ በመጣ ጊዜ ወገኖቹ ገና ልጅ እያለ ስለሚያውቁት ያንን በማስታወስ አላከበሩትም ነበር። አባቱንና እናቱን፣ ወንድሞቹንና እህቶቹን ያውቋቸዋልና ስለዚህ ሌሎች ሰዎች እንደሚያከብሩት የገዛ ወገኖቹ አላከበሩትም። እንዲያውም ይቃወሙትና ይተቹት ነበር። ማርቆስ 6፡4-6፡- *"ኢየሱስም። ነብይ ከገዛ አገሩና ከገዛ ዘመዶቹ ከገዛ ቤቱም በቀር፣ ሳይከበር አይቀርም አላቸው። በዚያም በጥቂቶች ድውዮች ላይ እጁን ጭኖ ከመፈወስ በቀር፣ ተአምር ሊያደርግ ምንም አልቻለም። ስለ አለማመናቸውም ተደነቀ። በመንደሮችም እያስተማረ ይዞር ነበር"* ይላል። ይህ ቃል ኢየሱስ ብዙ ታላላቅ ተአምሮችን አላደረገም እያለ አይደለም፣ ነገር ግን ከጥቂቶች በቀር ምንም ተአምር ሊያደርግ አለመቻሉን ይነግረናል። እንግዲህ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ፣ ሰው ሆኖ ወደ ምድር የመጣ፣ የእምነት ችግር የሌለበት፤ በእርግጥ በሕይወቱ ምንም ዓይነት የኃጢአት መግቢያ በር የሌለበት። በአለማመናቸው ምክንያት ለሰዎች ምንም ነገር ማድረግ እንዳይችል እንደተወሰነ ወይም እንደተገደበ እንመለከታለን። ይህንን ቃል ከማቴዎስ 13፡58 ጋር ካየነው *"በአለማመናቸው ምክንያት በዚያ ብዙ ተዓምር አላደረገም"* ይላልና እንግዲህ በእራሱ ምንም እጥረት ወይም ጉድለት የሌለበት ኢየሱስ፣ ለሰይጣንም መግቢያ ይከፍት ዘንድ ምንም ኃጢአት የሌለበት ኢየሱስ፣ ዙሪያውን በነበሩ ሰዎች ምክንያት በሰራው እንደተወሰነ እናስተውላለን።

አንድ ነገር ማስተዋል ይኖርብናል፡- የእግዚአብሔር ፈቃድ ምንጊዜም ሁሉም እንዲድኑ፣ ፈውስንም እንዲያገኙ ነው። ይህን ካመናችሁ ምናልባት ወደ አንድ ሆስፒታል ሄዳችሁ የታመሙትን በሙሉ ለመፈወስና ከበሽታ ነፃ ለማድረግ እንደሚቻልና የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ እምነት ሊያድርባችሁ ይችላል። በእርግጥ የታመሙ ሁሉ ይፈወሱ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን እንጅ ከእነርሱ ፈቃድ ውጭ ምንም ማድረግ አይችልም። እግዚአብሔር የራሳቸውን ያለመፈወስ ፈቃድ፣ ወይም የሕመም መብታቸውን ያከብራል፣ ማንም ፈውስ እንዲያገኙ ሊያስገድዳቸው አይችልም - እናም በሌላ ሰው እምነት አማካኝነት ሊፈወሱ አይችሉም። ምናልባት ሰዎቹ በትግል ውስጥ ያሉ ከሆኑ ግን የሌላው ሰው እምነት ሊጠቅማቸው የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል። ነገር ግን እነርሱን ተክቶ የሚያደርግላቸው ነገር አይኖርም። አንድ የቆመ መኪና ማርሽ ዜሮ ላይ በሚሆንበት ጊዜ በመግፋት እንዲንቀሳቀስ ማድረግ ትችላላችሁ። ነገር ግን ማርሹ በገባ ጊዜ መግፋትና ማንቀሳቀስ አትችሉም። በተመሳሳይ አንድ ሰው በእምነት ፈውስ አገኛለሁ ብሎ ባላመነበት ሁኔታ ወይም በእምነት ከሚገኝ ፈውስ በተቃራኒ ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ በምንም መልኩ ፈውስ ልታደርጉለት አትችሉም። በዚህም ምክንያት ሆስፒታልን ባዶ ማድረግ አትችሉም ወይም በቤተክርስቲያን አገልግሎት ሁሉም ሰው ፈውስ ሲያገኝ ላትመለከቱ ትችላላችሁ። ያለ ሰዎቹ ፈቃድ ወይም ትብብር ፈውስ ሊኖር አይችልም። በዚህ ጉዳይ ብዙ ማለት እንችላለን። ኢየሱስ ሰዎችን በሚፈውስበት ጊዜ፣ ሙታንንም ሲያስነሳ ወደ ሰዎቹ ቀርቦ "አታልቅሱ" ይላቸው ነበር፣ ልጇ የሞተባትንም ሴት አታልቅሽ ካላት በኋላ ልጇን ከሞት አስነስቶላታል። የአንድ ሰው እምነት አንዳንድ ቦታ ጥቅም ላይ ይውላል። በእኛ በኩል እምነት አስፈላጊ ነው። በፈውስ ዙሪያ ሌሎች እጅግ ብዙ ነገሮች በተጓዳኝ እንዳሉም ይታወቃል። በዚህ ትምህርት ውስጥ ያቀረብኳቸው ጥቂቶችን ሲሆን፣ እንደሚጠቅሟችሁ ተስፋ እያደረግኩ ከዚህ ሁሉ ማወቅና መረዳት የሚገባችሁ ግን እግዚአብሔር ታማኝ መሆኑን ነው። ትፈወሱ ዘንድ የእርሱ ፈቃድ ነው፣ ነገር ግን ከእርሱ ጋር እንዴት መተባበር እንዳለባችሁ መማር ከእናንተ ይጠበቃል። በእናንተ አልፎ ይሰራል እንጂ በእናንተ ቦታ ሆኖ አይሰራም። ከውስጣችሁ ሊመጣ የሚገባ ጉዳይ ነው።

እነዚህ ነገሮች የእግዚአብሔር ሃይል በእናንተ ውስጥ እንዲፈስ ለማድረግ፣ እራሳችሁን ለማዘጋጀት እንዲረዷችሁና በእግዚአብሔር ልዕለ ተፈጥሮ ጤንነት መራመድ ትችሉ ዘንድ እንዲረዷችሁ እጸልያለሁ።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ማቴዎስ 8፡17፣ እኛ ፈውስ እናገኝ ዘንድ ኢየሱስ ምን አደረገልን?

   **ማቴዎስ 8፡17** *በመሸም ጊዜ አጋንንት ያደረባቸውን ብዙዎችን ወደ እርሱ አመጡ፤ በነቢዩ በኢሳይያስ። እርሱ ድካማችንን ተቀበለ ደዌያችንንም ተሸከመ የተባለው ይፈጸም ዘንድ፥ መናፍስትን በቃሉ አወጣ፥ የታመሙትንም ሁሉ ፈወሰ።*

2. ሆሴዕ 4፡6 አንዳንድ ሰዎች ፈውስ ያላገኙት በምን ምክንያት ነው?

   ሀ. ባለማወቅ (እውቀት በማጣት)።
   ለ. ወደ ቤተ ክርስቲያን ባለመሄዳቸው።
   ሐ. ብቁ ስላልሆኑ ነው።

   **ሆሴዕ 4፡6** *ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል፤ አንተም እውቀትን ጠልተሃልና እኔ ካህን እንዳትሆነኝ እጠላሃለሁ፤ የአምላክህንም ሕግ ረስተሃልና እኔ ደግሞ ልጆችህን እረሳለሁ።*

3. ዮሐንስ 9፡1-3 ደቀ መዛሙርቱ ይህ ሰው እውር የሆነበት ምክንያት ምን ሊሆን ይችላል ብለው አሰቡ? ሃሳባቸው ትክክል ነው?

   **ዮሐንስ 9፡1-3** *ሲያልፍም ከመወለዱ ጀምሮ ዕውር የሆነውን ሰው አየ።[2] ደቀ መዛሙርቱም። መምህር ሆይ፥ ይህ ሰው ዕውር ሆኖ እንዲወለድ ኃጢአት የሠራ ማን ነው? እርሱ ወይስ ወላጆቹ? ብለው ጠየቁት። [3] ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰ። የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ እንዲገለጥ ነው እንጂ እርሱ ወይም ወላጆቹ ኃጢአት አልሠሩም።*

4. ዮሐንስ 5፡14 ሁልጊዜም ባይሆን፣ ኃጢአት ለበሽታ በር ይከፍታል። ከበሽታ ውጭ ኃጢአት በሰው ላይ ምን ያስከትላል?

   **ዮሐንስ 5፡14** *ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በመቅደስ አገኘውና። እነሆ፥ ድነሃል፤ ከዚህ የሚብስ እንዳይደርስብህ ወደ ፊት ኃጢአት አትሥራ አለው።*

5. ሮሜ 5፡12-14 የህመም ምክንያት ሁልጊዜ ኃጢአት ካልሆነ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል?

   **ሮሜ 5፡12-14** *ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ፤[13] ሕግ እስከ መጣ ድረስ ኃጢአት በዓለም ነበረና ነገር ግን ሕግ በሌለበት ጊዜ ኃጢአት አይቈጠርም፤[14] ነገር ግን በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኃጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ፥ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ፤ አዳም ይመጣ ዘንድ ላለው ለእርሱ አምሳሉ ነውና።*

6. ሐዋ 10፡38, እንደ ሐዋርያት ሥራ 10፡38 - ህመም በምን ሊመጣ ይችላል?

   **ሐዋርያት ሥራ 10፡38** *እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀባው፥ እርሱም መልካም እያደረገ ለዲያብሎስም የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረና።*

7. ማቴዎስ 13፡58 ፈውስን ሊከለክል የሚችል ምንድን ነው?

   **ማቴዎስ 13፡58** *በአለማመናቸውም ምክንያት በዚያ ብዙ ተአምራት አላደረገም።*

8. ያዕቆብ 5፡15 የታመመውን ምን ያድነዋል?

   **ያዕቆብ 5፡15** *የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል ጌታም ያስነሣዋል፤ ኃጢአትንም ሠርቶ እንደ ሆነ ይሰረይለታል።*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ማቴዎስ 8፡17፣ እኛ ፈውስ እናገኝ ዘንድ ኢየሱስ ምን አደረገልን?
   **እርሱ ድካማችንን ተቀበለ ደዌያችንንም ተሸከመ።**

2. ሆሴዕ 4፡6 አንዳንድ ሰዎች ፈውስ ያላገኙት በምን ምክንያት ነው?
   **ሀ. ባለማወቅ (እውቀት በማጣት)።**

3. ዮሐንስ 9፡1-3 ደቀ መዛሙርቱ ይህ ሰው እውር የሆነበት ምክንያት ምን ሊሆን ይችላል ብለው አሰቡ?
   **ኃጢአት።**
   ሃሳባቸው ትክክል ነው?
   **አይደለም።**

4. ዮሐንስ 5፡14 ሁልጊዜም ባይሆን፣ ኃጢአት ለበሽታ በር ይከፍታል። ከበሽታ ውጭ ኃጢአት በሰው ላይ ምን ያስከትላል?
   **ከበሽታ የከፉ ብዙ ነገሮችን፣ ሞትንም (ሮሜ 6፡23)።**

5. ሮሜ 5፡12-14 የህመም ምክንያት ሁልጊዜ ኃጢአት ካልሆነ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል?
   **ውድቀት (ዘፍጥረት 3)። አዳም በመተላለፉ ምክንያት ኃጢአትን እና ህመምን ወደ ሰው ዘር እንዲገባ አደረጓል።**

6. ሐዋ 10፡38፣ እንደ ሐዋርያት ሥራ 10፡38 - ህመም በምን ሊመጣ ይችላል?
   **ለዲያብሎስ በመገዛት።**

7. ማቴዎስ 13፡58 ፈውስን ሊከለክል የሚችል ምንድን ነው?
   **አለማመን።**

8. ያዕቆብ 5፡15 የታመመውን ምን ያድነዋል?
   **የእምነት ጸሎት።**

## ትምህርት 9

# ይቅርታ ስለማድረግ

## በዶን ክሮው

ማቴዎስ 18፡21-22 *“በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ ወደ እርሱ [ወደ ኢየሱስ] ቀርቦ፡ ጌታ ሆይ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት? እስከ ሰባት ጊዜን? አለው። ኢየሱስ እንዲህ አለው፡ እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ አልልህም።”* ጴጥሮስ በደል ላደረሰበት ሰው ስንት ጊዜ ይቅር ማለት እንደሚችል ደግነትን ለማሳየት በማሰብ የጠየቀው ጥያቄ ይመስላል - “በቀን ውስጥ እስከ ሰባት ጊዜ፣ ምን ይመስልሃል?” ሲል ይጠይቃል። ኢየሱስ ግን “ጴጥሮስ፣ ሰባት ጊዜ አይደለም፣ ሰባ ጊዜ ሰባት” አለው። ይህም 490 ጊዜ መሆኑ ነው። ነገር ግን ከ 490 ጊዜ በኋላ ይቅርታ አታድርጉ ማለት አይደለም። ኢየሱስ ስፍር ቁጥር የሌለው በደል በቀን ውስጥ በአንድ ሰው ላይ ሊደርስ የሚችልበትን ሁኔታ ለማሳየት ነው ይህንን የተናገረው። ይቅርታ መጨረሻ የሌለው ቀጣይ ነገር መሆኑን ያስገነዝበናል። ይቅርታ የእውነተኛ ክርስቲያን አይነተኛ መለያ ሊሆን ይገባል። ኢየሱስ በሉቃስ 23፡24፡- *“አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ”*። ሰማዕቱ እስጢፋኖስም በሐዋርያት ሥራ 7፡60፡- *“ጌታ ሆይ ይህንን ኃጢአት አትቁጠርባቸው ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ”*። ታዲያ ሁሉም ሰው ይቅርታ ያገኛል ማለት አይደለም፤ ነገር ግን በአንድ ክርስቲያን ልብ ውስጥ ምንጊዜም ይቅርታን ሰጭ የሆነ ልብ ሊኖር ይገባል።

በመቀጠል በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 18 ቁጥር 23፣ ኢየሱስ ይቅርታን በተመለከተ በምሳሌ ይናገራል። *“ስለዚህ መንግሥተ ሰማያት ባሮቹን ሊቈጣጠር የወደደን ንጉሥ ትመስላለች። መቈጣጠርም በጀመረ ጊዜ፥ እልፍ መክሊት ዕዳ ያለበትን አንድ ሰው ወደ እርሱ አመጡ።* [ዕዳው አሁን በእኛ ዘመን 10 ሚሊዮን ብር ያህል ይሆናል]:: *የሚከፍለውም ቢያጣ፥ እርሱና ሚስቱ ልጆቹም ያለውም ሁሉ እንዲሸጥና ዕዳው እንዲከፈል ጌታው አዘዘ። ስለዚህ ባሪያው ወድቆ ሰገደለትና። ጌታ ሆይ፥ ታገሠኝ፥ ሁሉንም እከፍልሃለሁ አለው። የዚያም ባሪያ ጌታ አዘነለትና ለቀቀው፥ ዕዳውንም ተወለት”* (በቅንፍ ያለው ከእኔ የተጨመረ ነው)። ሁኔታው ይህን ይመስል ነበር፡- አንድ ሰው ከጌታው 10 ሚሊዮን ብር የሚያህል ገንዘብ የተበደረ ሲሆን ዕዳውን ሊከፍል የሚችልበት ምንም ነገር የለውም። ሰውዬው የተበደረውን ገንዘብ ለጌታው መመለስ እንደማይችል ያውቃል፣ ጌታውም ይህንን ተገንዝቧል። በዛ ዘመን ዕዳ ቢኖርባችሁና መክፈል ባትችሉ ንብረትም ባይኖራችሁ፣ ኪሳራ ደርሶብኛል ብላችሁ (bankruptcy) ማስመዝገብ አትችሉም፤ ንብረት ባይኖራችሁ እራሳችሁን ይሸጧችኋል፣ ሚስቶቻችሁን፣ ልጆቻችሁንም፣ ያላችሁንም ይሸጡና ባሪያ ያደርጓችኋል። ሁሉም ነገር ተከፍሎ እስኪያልቅ በእስር ቤት ትቆያላችሁ ካልሆነም እድሜ ልክ ከእስር ቤት አትወጡም። ይህ ሰው የሚያውቀውን አንድ ነገር አደረገ፣ ይኸውም በጉልበቱ ወድቆ ምህረት እንዲደረግለት ተማጸነ - “እባክህ ጌታ ሆይ፣ እንድትታገሰኝ እለምንሃለሁ፣ ሁሉንም እከፍልሃለሁ፣ እባክህን ጊዜ ስጠኝ” ብሎ ጮኸ። በመቀጠል የሆነውን ነገር በቁጥር 27 ተመልከቱ። ጌታውም ለዚህ ሰው አዘነለት ይላል፣ የነበረበትንም ዕዳ ተወለት።

እኛም ልንከፍለው የማንችለው ዕዳ አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ይላል (ሮሜ 6፡23) - ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም መለያየት - የአለም ሁሉ ወርቅና ብር ቢሰበሰብ ቤዛ ሊሆነን አይችልም። እግዚአብሔር ግን በርህራኄው እና በጸጋው ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ምድር ልኮ እኛ ልንከፍለው የማንችለውን ዕዳ እርሱ ራሱ ከፈለልን። እግዚአብሔር በርህራሄና በምህረት ተመለከተንና “ዕዳችሁን ይቅር ብያለሁ” አለን።

ይህ ብዙ ሚሊዬን ብር ዕዳ የተተወለት ሰው እንደ እርሱ አገልጋይ ለሆነ ለሌላ ሰው ጥቂት ሽህ ብር የሚያህል ገንዘብ አበድሮ ነበር። የተበደረውንም ሰው መንገድ ላይ ሲያገኘው “እኔ አስር ሚሊዬን ብር ዕዳ ተትቶልኛልና የአንተ ጥቂት ሽህ ብር ብድር ለኔ ምንም አይደለም፣ እንደ እኔ ነጻ እንድትሆን እፈልጋለሁ፣ ዕዳህን ትቼልሃለሁ” ቢለው ኖሮ መልካም ይሆን ነበር። ነገር ግን አይደለም። ይልቁንም በተበዳሪው ላይ ምን እንዳደረገ በቁጥር 28-31 እንመለከታለን፡- *“ነገር ግን ያ ባሪያ ወጥቶ ከባልንጀሮቹ ከባሮቹ መቶ ዲናር ዕዳ ያለበትን አንዱን*

*አገኘና። ዕዳህን ክፈለኝ ብሎ ያዘና አነቀው። ስለዚህ ባልንጀራው ባሪያ ወድቆ። ታገሠኝ፥ ሁሉንም እከፍልሃለሁ ብሎ ለመነው። እርሱም አልወደደም፥ ግን ሄዶ ዕዳውን እስኪከፍል ድረስ በወኅኒ አኖረው። ባልንጀሮቹ የሆኑ ባሮችም ያደረገውን አይተው እጅግ አዘኑ፥ መጥተውም የሆነውን ሁሉ ለጌታቸው ገለጡ።”* አስባችሁታል? እስር ሚሊዬን ብር ዕዳ የተተወለት ሰው፣ ለጥቂት ብር ብሎ ባልንጀራውን እስር ቤት እንዲወረወር አደረገ።

ቁጥር 32-34 እንዲህ ይላል፡- “ከዚያ ወዲያ ጌታው ጠርቶ። አንተ ክፉ ባሪያ፥ ስለ ለመንኸኝ ያን ዕዳ ሁሉ ተውሁልህ፤ እኔ እንደ ማርሁህ ባልንጀራህ የሆነውን ያን ባሪያ ልትምረው ለአንተስ አይገባህምን? አለው። ጌታውም ተቈጣና ዕዳውን ሁሉ እስኪከፍለው ድረስ ለሚሣቅዩት አሳልፎ ሰጠው። ከእናንተ እያንዳንዱ ወንድሙን ከልቡ ይቅር ካላለ፥ እንዲሁ ደግሞ የሰማዩ አባቴ ያደርግባችኋል”። ይህ ሰው ለወዳጁ ምህረት ባለማድረጉ ምክንያት የእርሱም ይቅርታ ተሰርዞ በተራው ወደ እስር ቤት ተወረወረ። በቁጥር 35 ኢየሱስ *“ከእናንተ እያንዳንዱ ወንድሙን ከልቡ ይቅር ካላለ እንዲሁ ደግሞ የሰማዩ አባቴ ያደርግባችኃል”* ይላል። ለዘላለም ከእግዚአብሔር ሊለየንና ለሞት ሊዳርገን የነበረው ኃጢአት ሁሉ ይቅር ተብሎልን እኛ ሌሎችን ይቅር አለማለት ሞኝነት አይደል? እግዚአብሔርን “ማረኝ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ይቅር በለኝ” ብለን እንለምናለን፤ ነገር ግን በትንሽ ነገር እንደኛ ያለ ወገናችንን ይቅር ማለት አንፈልግም። እግዚአብሔር እናንተ ደካሞች የሚለን ለዚህ ነው።

የዚህ ትምህርት አቅራቢ በአንድ ወቅት መጋቢ ሆኜ በማገለግልበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንዲት ወጣት ነበረች። እርሷም ማንኛውንም ወደፊት የሚሆነውን ነገር ቀድማ ታያለች። አንድ ቀን ወደ እኔ መጣችና- “ወደፊት የሚሆነውን ነገር የሚነግረኝና የሚመጣውን የሚያሳየኝ መንፈስ ቅዱስ ይሆንን? ሰዎች ሊሞቱ ሲሉ ቀድሜ አያለሁ፣ የመኪና አደጋ ከመድረሱ በፊትም አያለሁ፣ ሌሎችንም ነገሮች…” ስትል ጥያቄ አቀረበችልኝ። እኔም “መልሴ ላያስደስትሽ ይችላል ነገር ግን ያን የሚያደርገው መንፈስ ቅዱስ ነው ብየ አላምንም። ይልቁንም ወደፊት ሊሆን ያለውን ነገር የሚናገር የጥንቆላ (የሟርተኝነት) ርኩስ መንፈስ ነው። ይህ እነ ጳውሎስን በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 16 እየተከተለ ያስቸግራቸው የነበረ ያው መንፈስ ነው፤ ጳውሎስም በመጨረሻ በገሠጸውና ከእርሷም እንዲወጣ ባዘዘው ጊዜ የሴትዮዋ የጥንቆላ ሃይልም አብሮ ሄደ” በማለት ነገርኳት። ንግግሬን በመቀጠልም እኔ እግዚአብሔር ስላልሆንኩ እርሷ ማድረግ የሚገባትን እንዲህ ስል አሳወቅኳት “ወደ ኢየሱስ ቀርበሽ ይህን እንድትጠይቂው እመክርሻለሁ፣ ጌታ ሆይ ገና ሳልድን ጀምሮ ቀድሞ ነገሮችን የሚገልጥልኝና የሚነግረኝ ምንድን ነው? የአንተ ቅዱስ መንፈስ ነው ወይስ ሌላ? ብለሽ ጠይቂው” አልኳት። በሌላ ቀን መጣችና “ጌታን አናገሬዋለሁ፣ እንደሚመስለኝ ሁሉም ነገር እኔ እንዳሰብኩት ትክክል ነው” አለችኝ። እኔም “ጌታ የተናገረሽ ማንኛውም ነገር ትክክል ነው - እኔ መልካሙ እረኛ አይደለሁም” አልኳት።

ይህ የሆነው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 1986 ዓ.ም. ነበር፣ በዚህ ዓመት ዓለምን በሙሉ ያሳዘነ አንድ አስደንጋጭ አደጋ አሜሪካ ውስጥ ተከስቶ ነበር፣ ምን እንደሆነ ታስታውሳላችሁ? “ቻሌንጀር” የተባለችው የአሜሪካ የጠፈር መንኮራኩር ሰምንት ጠፈርተኞች ይዛ ለመምጠቅ ተዘጋጅታ ነበር። ከጠፈርተኞችም አንዷ በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ መምህር የነበረች ሴት ነች። ከላይ ያነሳናት ወጣት ከበረራው አንድ ቀን በፊት፣ ጠፈርተኛዋ - “በነገው እለት በቻሌንጀር ወደ ላይ እወጣለሁ” ብላ ስትናገር ሰማች። መንፈስም ነገራትና “ይህች ሴት ትሞታለች፣ ትሞታለች” ብላ ተናገረች። በነጋታው አለም ሁሉ እያየ ቻሌንጀር እንደመጠቀች አየር ላይ ፈነዳችና ጠፈርተኞቹ በሙሉ አለቁ። በዚህ ጊዜ ይህች ወጣት ወደ እኔ መጣችና “ወንድም ዶን ነገሮችን አስቀድሞ የሚነግረኝና መረጃዎችን የሚሰጠኝ መንፈስ ቅዱስ አልመሰለኝምና ትፀልይልኛለህ?” አለችኝ። የዛ ቀን አገልግሎት አብቅቶ ሁሉም ሰው ወደየቤቱ ከሄደ በኋላ፣ እጇን ያዝኩና “አንተ የጥንቆላ ርኩስ መንፈስ፣ ከእርሷ ላይ ውጣ!” ብየ አዘዝኩት። ምንም የተፈጠረ ነገር አልነበረም። የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ከአንድ ልጅ ላይ አንድ ርኩስ መንፈስ ለማስወጣት ሞክረው ያልቻሉበት ጊዜ ነበር። ኢየሱስም “ወደ እኔ አምጡት” አላቸው። እኔም “ጌታ ሆይ እዚህች ልጅ ላይ ያለው ርኩስ መንፈስ እንደሆነ አስባለሁ፤ ወደ አንተ አመጣታለሁ አንተ ማድረግ የሚገባንን አሳውቀን” አልኩ። ባለቤቴም አብራን እየጸለየች ነበርና እግዚአብሔር የመገለጥ ቃል ሰጣት እና

“ይህ ነገር ከልጅቱ እናት ጋር የተያያዘ ነው” አለች። እኔም ወጣቷን “እናትሽን ይቅር ትያታለሽ?” ስል ጠየቅኳት። ልክ ይህን እንደተናገርኩ ሃይለኛ ጩኸት ከልጅቱ ወጣና “አይሆንም! እርሷ ትታኝ ነበር!” እያለ መጮህ ጀመረ። “አንተ ርኩስ መንፈስ አስሪሃለሁ” አልኩና ዳግመኛ ልጅቱን “እናትሽን ይቅር ትያለሽ?” ስል ጠየቅኳት። እርሷም “አዎ” አለችና በእግዚአብሔር ጸጋ እና እርዳታ እናቷን ይቅር አለች፤ ካሰረችበትም ፈታች። ይቅር ለማለት በመወሰኗ ሁሉንም ነገር ለመተው ከመቻሏም በላይ እርሷም ወዲያውኑ እርነት ወጣች ነፃነቷንም አገኘች።

ኢየሱስ በማቴዎስ 18 በምሳሌ እንደሚነግረን የሰማዩ አባታችን ዕዳችንን ሁሉ ይቅር ካለን በኃላ እኛም ከልባችን ሌሎችን ይቅር ካላልን ‹‹በሚያሰቃዩን እጅ›› ተላልፈን እንሰጣለን። እነዚህ አሰቃዮቻችን (tormenters) የሚባሉት እነማን ናቸው? ሁሉም ዓይነት ችግሮች፣ የአጋንንት ወጥመድ፣ ጭቆና፣ ህመም፣ በሽታ፣ ድባቴ እና ሌሎችም ሊሆኑ ይችላሉ። የእነዚህ ሁሉ ሥር ደግሞ ይቅርታ አለማድረግ ነው። ይቅርታን ካገኘን በኃላ ሌሎችን ይቅር አለማለት ለሰይጣን እግር ማስገቢያ በር በህይወታችን ይከፍታል። መጽሐፍ ቅዱስ ይቅር ለማለት ውሳኔ ማድረግ እንዳለብን ይናገራል። ኢየሱስ በማቴዎስ 6:9-11 የጌታ ጸሎት፣ እኛ ይቅር እንደተባልን ሁሉ ሌሎችን ይቅር እንድንላቸው ያዛል።

ማርቆስ 11:25-26 ደግሞ በምንጸልይበት ጊዜ በሌሎች ላይ የያዝነው ማንኛውም ነገር ቢኖር ይቅር ማለት እንዳለብን ይናገራል። ይህ ምን ማለት ነው? ይቅር ሳንል ለምን ያህል ጊዜ በልባችን መያዝ አለብን? በጌታ ፊት ለጸሎት እስክንቆም ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ። በሌሎች ላይ ጥቂትም ቢሆን ይቅር ያላልናቸው ነገር ቢኖር “አምላኬ ሆይ ዛሬ ፈትቻቸዋለሁ፤ ይቅር ብያቸዋለሁ። አንተ ትልቁን ዕዳዬን ይቅር ስላልከኝ እኔም እነርሱን ይቅር ማለት ምርጫዬ ነው” ብለን መፍታት ይገባናል።

እንፀልይ፦

“ጌታ ሆይ፣ ዛሬ ይህንን ትምህርት ከሚያነብቡ እና ይቅርታ ያላደረጉለት ሰው በልባቸው ውስጥ ካለባቸው ሰዎች ጋር እጸልያለሁ፣ አሁን የያዙትን ያንን ሰው ይቅር ለማለት ውሳኔ እንዲያደርጉና ፈትተው እንዲለቁ፣ በህይወት ያሉም ቢሆኑ በሞት የተለዩ ሰዎችን ይቅር እንዲሉ፣ እንዲፈቱ፣ እንዲለቁ እጸልያለሁ። የተጎዳው ነፍሳቸው እንዲጠገንና ቁስላቸውም ዛሬ በአንተ ሃይልና በጸጋህ እንዲፈወስ እጸልያለሁ። አመሰግንሃለሁ፣ በጌታ በኢየሱስ ስም አሜን።”

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ማቴዎስ 18፡21 ጴጥሮስ ምን ያህል ጊዜ ይቅር ለማለት ጥያቄ አቀረበ?

   **ማቴዎስ 18፡21** *በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ ወደ እርሱ ቀርቦ። ጌታ ሆይ፥ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት? እስከ ሰባት ጊዜን? አለው።*

2. ማቴዎስ 18፡22 ኢየሱስ ምን ያህል ጊዜ ይቅር ማለት እንዳለብን ተናገረ?

   **ማቴዎስ 18፡21** *ኢየሱስ እንዲህ አለው። እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ አልልህም።*

3. ማቴዎስ 18፡23-24 ይህ ሰራተኛ ከጌታው ምን ያህል ገንዘብ ነበረበት?

   **ማቴዎስ 18፡23-24** *ስለዚህ መንግሥተ ሰማያት ባሮቹን ሊቈጣጠር የወደደን ንጉሥ ትመስላለች። [24] መቈጣጠርም በጀመረ ጊዜ፥ እልፍ መክሊት ዕዳ ያለበትን አንድ ሰው ወደ እርሱ አመጡ።*

4. ማቴዎስ 18፡25 ይህ ሰው ኪሳራ ደርሶብኛል ብሎ በነጻ መሔድ ስለማይችል ምን ይደርስበት ነበር?

   **ማቴዎስ 18፡25** *የሚከፍለውም ቢያጣ፥ እርሱና ሚስቱ ልጆቹም ያለውም ሁሉ እንዲሸጥና ዕዳው እንዲከፈል ጌታው አዘዘ።*

5. ማቴዎስ 18፡26 ለጌታውስ ምን ዓይነት ጥያቄ አቀረበ? ዕዳውንስ መክፈል ይችል ነበር?

   **ማቴዎስ 18፡26** *ስለዚህ ባሪያው ወድቆ ሰገደለትና። ጌታ ሆይ፥ ታገሠኝ፥ ሁሉንም እከፍልሃለሁ አለው።*

6. ማቴዎስ 18፡27 ጌታው አገልጋዩን በምን አይነት መልክ ተመለከተ? እግዚአብሔርስ እኛንና ዕዳችንን (ኃጢአት) በምን መልክ ተመለከተ?

   **ማቴዎስ 18፡27** *የዚያም ባሪያ ጌታ አዘነለትና ለቀቀው፥ ዕዳውንም ተወለት።*

7. ማቴዎስ 18፡28 ያ ዕዳው የተሰረዘለት ሰው ለጓደኛው ምን ያህል ገንዘብ አበድሮ ነበር?

   **ማቴዎስ 18፡28** *ነገር ግን ያ ባሪያ ወጥቶ ከባልንጀሮቹ ከባሮቹ መቶ ዲናር ዕዳ ያለበትን አንዱን አገኘና። ዕዳህን ክፈለኝ ብሎ ያዘና አነቀው።*

8. ማቴዎስ 18፡28 ይህ ሰው ወደ በጓደኛው ላይ ምን ዓይነት አቋም ነበረው?

   **ማቴዎስ 18፡28** *ነገር ግን ያ ባሪያ ወጥቶ ከባልንጀሮቹ ከባሮቹ መቶ ዲናር ዕዳ ያለበትን አንዱን አገኘና። ዕዳህን ክፈለኝ ብሎ ያዘና አነቀው።*

9. ማቴዎስ 18፡ 29-30 ይህ ሰው በጓደኛው ላይ ምን ዓይነት እርምጃ ወሰደ?

**ማቴዎስ 18፡29-30** *ስለዚህ ባልንጀራው ባሪያ ወድቆ። ታገሠኝ፥ ሁሉንም እከፍልሃለሁ ብሎ ለመነው። [30] እርሱም አልወደደም፥ ግን ሄዶ ዕዳውን እስኪከፍል ድረስ በወኅኒ አኖረው።*

10. ማቴዎስ 18፡31-33 ጌታው ይህን ይቅርታ ያላደረገውን አገልጋይ ምን ብሎ ጠራው?

**ማቴዎስ 18፡31-33** *ባልንጀሮቹ የሆኑ ባሮችም ያደረገውን አይተው እጅግ አዘኑ፥ መጥተውም የሆነውን ሁሉ ለጌታቸው ገለጡ። [32] ከዚያ ወዲያ ጌታው ጠርቶ። አንተ ክፉ ባሪያ፥ ስለ ለመንኸኝ ያን ዕዳ ሁሉ ተውሁልህ፤ [33] እኔ እንደ ማርሁህ ባልንጀራህ የሆነውን ያን ባሪያ ልትምረው ለአንተስ አይገባህምን? አለው።*

11. ማቴዎስ 18፡33፣ ጌታው ሰራተኛውን ምን ማድረግ ነበረብህ አለው?

12. ማቴዎስ 18፡34፣ ጌታው ይህንን ነገር በሰማ ጊዜ ስሜቱ ምን ሆነ?

**ማቴዎስ 18፡34** *ጌታውም ተቈጣና ዕዳውን ሁሉ እስኪከፍለው ድረስ ለሚሣቀዩት አሳልፎ ሰጠው።*

13. ማቴዎስ 18፡34 ይህ ይቅር ተብሎ የነበረ ሰው ይቅር ባለማለቱ (ላለማለት በመወሰኑ) ቀድሞ ለእራሱ የተሰጠውን ይቅርታ አጥቷል?

14. ማቴዎስ 18፡35 የዚህ ምሳሌ አላማ ምንድን ነው?

**ማቴዎስ 18፡35** *ከእናንተ እያንዳንዱ ወንድሙን ከልቡ ይቅር ካላለ፥ እንዲሁ ደግሞ የሰማዩ አባቴ ያደርግባችኋል።*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ማቴዎስ 18፡21 ጴጥሮስ ምን ያህል ጊዜ ይቅር ለማለት ጥያቄ አቀረበ?
**እስከ ሰባት ጊዜ።**

2. ማቴዎስ 18፡22 ኢየሱስ ምን ያህል ጊዜ ይቅር ማለት እንዳለብን ተናገረ?
**አራት መቶ ዘጠና ጊዜ (ወይም ምንጊዜም፣ እስከመጨረሻው ድረስ)።**

3. ማቴዎስ 18፡23-24 ይህ ሰራተኛ ከጌታው ምን ያህል ገንዘብ ነበረበት?
**እልፍ መክሊት ወይም እስር ሚሊዮን ብር።**

4. ማቴዎስ 18፡25 ይህ ሰው ኪሳራ ደርሶብኛል ብሎ በነጻ መሔድ ስለማይችል ምን ይደርሰበት ነበር?
**እርሱና ሚስቱ ልጆቹም ያለውም ሁሉ እንዲሸጥና ዕዳው እንዲከፈል ይደረጋል።**

5. ማቴዎስ 18፡26 ለጌታውስ ምን ዓይነት ጥያቄ አቀረበ?
**ጌታው እንዲታገሰው እና ሁሉንም እንደሚከፍለው።**
ዕዳውንስ መክፈል ይችል ነበር?
**የሚችል አይመስልም።**

6. ማቴዎስ 18፡27 ጌታው አገልጋዩን በምን አይነት መልክ ተመለከተ?
**በአዘኔታ እና በምህረት።**
እግዚአብሔርስ እኛንና ዕዳችንን (ኃጢአት) በምን መልክ ተመለከተ?
**በአዘኔታ እና በምህረት።**

7. ማቴዎስ 18፡28 ያ ዕዳው የተሰረዘለት ሰው ለጓደኛው ምን ያህል ገንዘብ አበድሮ ነበር?
**አንድ መቶ ብር (የአንድ ቀን የሰራተኛ ደሞዝ)።**

8. ማቴዎስ 18፡28 ይህ ሰው በጓደኛው ላይ ምን ዓይነት አቋም ነበረው?
**ያለ መታገስ፣ ቁጣ እና ይቅር ያለማለት።**

9. ማቴዎስ 18፡ 29-30 ይህ ሰው በጓደኛው ላይ ምን ዓይነት እርምጃ ወሰደ?
**ዕዳውን እስኪከፍል ድረስ በወኅኒ አኖረው።**

10. ማቴዎስ 18፡31-33 ጌታው ይህን ይቅርታ ያላደረገውን አገልጋይ ምን ብሎ ጠራው?
**"አንተ ክፉ ባሪያ"።**

11. ማቴዎስ 18፡33፣ ጌታው ሰራተኛውን ምን ማድረግ ነበረብህ አለው?
**ጌታው እንዳደረገለት እርሱም ለባልንጀራው ሊያዝንለት፣ ይቅር ሊለው እና በነጻ ሊያሰናብተው እንደሚገባ ነገረው።**

12. ማቴዎስ 18፡34፣ ጌታው ይህንን ነገር በሰማ ጊዜ ስሜቱ ምን ሆነ?
**ተቈጣ።**

13. ማቴዎስ 18፡34 ይህ ይቅር ተብሎ የነበረ ሰው ይቅር ባለማለቱ (ላለማለት በመወሰኑ) ቀድሞ ለእራሱ የተሰጠውን ይቅርታ አጥቷል?
**አዎ።**

14. ማቴዎስ 18፡35 የዚህ ምሳሌ አላማ ምንድን ነው?
**“ከእናንተ እያንዳንዱ ምህረት ለሚጠይቃችሁ ሰው ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ከልባችሁ ይቅር ካላላችሁ፥ እንዲሁ ደግሞ የሰማዩ አባቴ ያደርግባችኋል” (የማቴዎስ 18፡35 መልዕክት)።**

# ትምህርት 10

# ጋብቻ - ክፍል 1

## በዶን ክሮው

ዛሬ ደግሞ ስለ ጋብቻ እናወራለን። በቅድሚያ ግን በዚህ ዙሪያ በአንድ ወቅት አሜሪካ ውስጥ በተደረገ የጥናት ዳሰሳ የተገኘውን ውጤት ላቅርብላችሁ፡- 75% የሚደርሱ በትዳር ውስጥ ያሉ ጥንዶች አንድ አይነት የጋብቻ የምክር አገልግሎት ያስፈልጋቸዋል። 50% በሚሆኑጋብቻዎች ውስጥ በመጀመሪያዎቹ አምስት ዓመታት ከጥንዶቹ አንዳቸው ለትዳራቸው ታማኝ ላይሆኑ ይችላሉ። በክርስቲያኖች መካከልም ቢሆን 30% የሚሆኑ አገልጋዮች በቤተክርስቲያናቸው ውስጥ ካሉ ሰዎች ከአንዳቸው ጋር ያልተፈለገ ዓይነት ግንኙነት ውስጥ ገብተው ሊገኙ ይችላሉ። እንግዲህ እነዚህ ጥናቶች ትክክል የሚሆኑ ከሆነ የመጽሐፍ ቅዱስን መርሆዎች ምን ያህል እንደማናውቃቸውና እንዳልገቡንም የሚያሳይ ይመስለኛል። በዚህ ርዕስ ስለ ጋብቻ ምንነትና እግዚአብሔር ስለ ጋብቻ በተናገራቸው አንዳንድ ነገሮች - በጋብቻ ውስጥ ያላችሁን ግንኙነት እንዴት ማጠናከር እንደምትችሉ እንመለከታለን።

ጋብቻ የእግዚአብሔር ሃሳብ ነው። የሰራውም እርሱ ራሱ ነው። ዘፍጥረት 2፡18 – *"እግዚአብሔር አምላክም አለ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት"*። ደግሞም ዘፍጥረት 1፡31 *"እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ። ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ ስድስተኛ ቀን።"* ይህ የእግዚአብሔር ፍጹም ስራ እንደነበር ማስታወስ ያስፈልጋል። እግዚአብሔር ከሰው ጋር እጅግ መልካም ግንኙነት ነበረው፣ በየእለቱ ነፋሻማ ምሽት ላይ እየመጣም አዳምን ያገኘው ነበር። ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም የሆነ ወዳጅት ቢኖረኝ ሌላ ምንም አልፈልግም ብለን አንዳንድ ጊዜ እናስባለን፤ ይህ ትክክል አይደለም። እግዚአብሔር የሰራውን ስራ በተመለከተ በዘፍጥረት 1፡31 ሲናገር *"እነሆም እጅግ መልካም ነበረ"* ብሏል። ለመጀመሪያ ጊዜ እግዚአብሔር "መልካም አይደለም" ያለው ነገር የሚገኘው በዘፍጥረት 2፡18 ነው፣ *"ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም"*። ስለዚህ ጋብቻ፣ ሰው በህይወቱ ብቸኝነት እንዳያጠቃውና ብቻውን እንዳይሆን ፍላጎቱን ለሟሟላት ሲል እግዚአብሔር የሰራው የእግዚአብሔር ሃሳብ ነው። መመሪያውን መከተል ከቻልን እና በውስጡም እግዚአብሔር የሚፈልገውን እንዲይዝ ካደረግን፣ ጋብቻ ደስታን የሚሰጥ እንጅ ችግርን የሚያመጣ አይደለም።

ዘፍጥረት 2፡24 ለመጀመሪያ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጋብቻ የሚያወራበት ክፍል ነው። *"ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል በሚስቱም ይጣበቃል፣ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ"* ይላል። ጋብቻ ሌሎች ግንኙነቶቻችን በመተው ህይወታችንን እንደገና ከሌላ ሰው ጋር የምናቆራኝበት ሲሆን እግዚአብሔርም እንዲህ እንዲሆን አድርጎ ሰርቶታል። የሦሥትዮሽ ግንኙነት ወይም አንድነት ነው። ወደዚህ የጋብቻ ግንኙነት እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን አንድ ላይ ሲጠራቸው ለየብቻ በአዳምና በእግዚአብሔር ወይም በሔዋንና በእግዚአብሔር መካከል የነጠላ ወዳጅነት እንዲኖር ሳይሆን እንደ ጥንድ በዓላማም አንድ እንዲሆኑ እና ከእርሱ ጋርም የአንድነት ወዳጅነት እንዲኖራቸው ነው።

በ1ኛ ጴጥሮስ 3፡7 *"እንዲሁም እናንተ ባሎች ሆይ፣ ደካማ ፍጥረት ሥለሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ"* (የእንግሊዝኛው KJV ትርጉም - giving honour unto the wife, as unto the weaker vessel - ወይም እንደ ተሰባሪ ዕቃ ሚስቶቻችሁን በጥንቃቄ አክብራችሁ) ይላል፣ (በቅንፍ ያለው እኔ የጨመርኩት ነው)። ዘፍጥረት 5፡1-2 ድንቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው *"የአዳም የትውልዱ መጽሐፍ ይህ ነው። እግዚአብሔር አዳምን በፈጠረ ቀን በእግዚአብሔር ምሳሌ አደረገው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፣ ባረካቸውም። ሰማቸውንም በፈጠረበት ቀን አዳም ብሎ ጠራቸው"* ይላል። አስተውሉ - አዳም ሚስቱን "ሔዋን" ብሎ ሰም አወጣላት፤ እግዚአብሔር ግን አዳምና ሔዋንን አንድ ላይ "አዳም" ብሎ ጠራቸው። ስለዚህ ጋብቻን በተመለከተ እግዚአብሔር እና እኔ ወይም እግዚአብሔር እና ይህች ሴት የሚባል ነገር አይኖርም፤ ይልቁንም እኔና ባለቤቴ

እግዚአብሔርን በማገልገል ዓላማ በአንድነት እና በህብረት በህይወት ፀጋ የተጠራን ወራሾች ነን።

ከላይ በዘፍጥረት 2፡24 እንዳነበብነው ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ስጋ ይሆናሉ ይላል። ይጣበቃል የሚለው ቃል መጣበቅን፣ መያያዝን፣ በአንድ ዓላማ ወይም ተግባር መሆንን ያመለክታል። እንግዲህ በትዳር ግንኙነታቸሁ ውስጥ ዛሬ ችግር ላይ ከሆናችሁ፣ የሚከተሉትን ጥቂት ጥያቄዎች እንድጠይቃችሁ ፍቀዱልኝ፡- የምትሰሯቸው ሥራዎች፣ ከአጋራችሁ ጋር ያላችሁ እንቅስቃሴ፣ ለትዳር አጋራችሁ የምትናገሯቸው ነገሮች፣ ከትዳር አጋራችሁ ጋር እንድትስማሙ የሚያደርጉ ናቸው? ወይስ መለያየትን የሚፈጥሩ? ጋብቻን በተመለከተ የቃሉ ትዕዛዝ መጣበቅ መያያዝን ነው። ስለዚህ የምታደርጓቸው ነገሮች ግንኙነታችሁን እያጠናከሩ፣ እያነጹ ነው ወይስ እያፈረሱ? እነዚህን ጥያቄዎች ማጤን ያስፈልጋችኋል።

ሰዎች ፍቅር ስሜታዊነት እንደሆነ ያስባሉ፡- “አፈቅርህ/ሽ ነበር። አሁን ግን በቅቶኛል ከዚህ በኃላ ላፈቅርህ/ሽ አልችልም” ይላሉ። መልካም ትዳር ከሌለበት ቤተሰብ እንደመጣችሁ እናስብ። የቤተክርስቲያን አገልጋይ ወይም የጋብቻ ሰነድ አፈራራሚ ፊት ለመጋባት ቀርባችኋል፣ ህይወታችሁንም ለአጋራችሁ ለመሰጠት ወሰናችኋል እንበል፣ ሞት እስኪለያችሁ ድረስ ለመዝለቅ ወሰናችኋል። ነገር ግን ስኬታማ ካልሆነ ቤተሰብ በመምጣታችሁ ምክንያት ምንም ዓይነት ፍቅር አታውቁም፣ በቤተሰባችሁ መካከል የፍቅር መገለጫዎችን አላያችሁም፣ ወላጆቻችሁም የሞቀ ፍቅር ሲለዋወጡ አይታችሁ አታውቁም። የትዳር አጋራችሁ ደግሞ የሞቀ ፍቅር ከሞላበት ቤተሰብ የመጡ ይሆናሉ፣ እናንተ ግን እንዴት እንደሆነ እንኳን አታውቁም። የህይወት አጋራችሁን ማፍቀር ብትፈልጉም እንኳን እናንተ እራሳችሁ ከዚህ በፊት የፍቅር መገለጫዎችን ያላያችሁና በዚህ በኩል ስኬታማ ባለመሆናችሁ ምክንያት ላይሳካላችሁና ውጤታማ ሳትሆኑ ልትቀሩ ትችላላችሁ። ምናልባት በጥቂት ዓመታት ውስጥ የሚኖራችሁ ምርጫ ወደ ምክር አገልግሎት መሰጫ ሄዳችሁ፡- “ከዚህ በላይ መቀጠል አልቻልንም። ከአሁን በኋላ ማናቸውንም ላፈቅር አልችልም” ትላላችሁ። እንግዲያውስ ዛሬ ለእናንተ የምስራች አለኝ። በትዳራችሁ ውስጥ ችግር ካጋጠማችሁ ይህንን ማስተካከል የሚችል መፍትሔ አለ።

አንድ አዲስ ፍሪጅ ገዝታችሁ ችግር ቢያጋጥማችሁ በመጀመሪያ የምታደርጉት የአጠቃቀም መመሪያውን (manual) መመልከት ነው። መመሪያው የችግሩን ምንነትና መፍትሔውን ይነግራችኋል ወይም ወደ ጥገና ባለሙያ ትወሰዱታላችሁ። ጋብቻችሁንም በተመለከተ የሚሰራና የሚጠግን መመሪያ አለ። እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ይባላል። መጽሐፍ ቅዱስ በቲቶ መልዕክት 2፡4 ፍቅር የምናሰተምረው፣ ደግሞም የምንማረውም ነገር እንደሆነ ይናገራል። ምናልባት ስኬታማ ካልሆነ ቤተሰብ የመጣችሁ ከሆነ እና የትዳር አጋራችሁን ማፍቀር ቢያቅታችሁ - ትዳራችሁ ይቃወሳል - ይሁን እንጂ የምስራች አለ። 1ኛ ዮሐንስ 5፡3 *“ትዕዛዛቱን ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነው ትዕዛዛቱም ከባድ አይደሉም”* ይላል። ፍቅርን ባሳየን፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ትዕዛዛት በኩል ሌሎችን እንዴት መውደድ እንዳለብን፣ ቸርነትና ርህራሄን ለሌሎች ማድረግን ብሎም በጋብቻ ግንኙነት ውስጥ ለሌሎች ጥቅም መስራት እንዳለብን እናውቅ ዘንድ እግዚአብሔር ሁኔታዎችን ሁሉ ሊያመቻችና ለእናንተ ሊቀይር ይችላል።

ይህ ስለጋብቻ የመግቢያ ትምህርት ነው። ዛሬ ጥናታችሁን በምትቀጥሉበት ጊዜ እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርካችሁ። በዚህ ርዕስ ዙሪያ በምታደርጉት ጥናት እግዚአብሔር ብዙ ጥበብ እና እውቀት እንደሚሰጣችሁ እምናለሁ።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ኤፌሶን 5፡31-32። ኤፌሶን 5፡31 ከዘፍጥረት 2፡24 የመጣ ጥቅስ ነው። ኤፌሶን 5፡32ን በመመልከት በዚህ ቃል እግዚአብሔር እየነገረን ያለው ምንድን ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?

   **ኤፌሶን 5፡31-32** *ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። [32] ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው፥ እኔ ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን እላለሁ።*

2. ያዕቆብ 4፡4-5 እነዚህ ቃላት ምን ያስተምራሉ?

   **ያዕቆብ 4፡4-5** *አመንዝሮች ሆይ፥ ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንዲሆን አታውቁምን? እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል። [5] ወይስ መጽሐፍ። በእኛ ዘንድ ያሳደረው መንፈስ በቅንዓት ይመኛል ያለው በከንቱ እንደ ተናገረ ይመስላችኋልን?*

3. 1ኛ ጴጥሮስ 3፡7 ወደ ትዳር አጋራችሁ በአንድነት እና በፍቅር መጓዝ ያለባችሁ ለምንድን ነው?

   **1ኛ ጴጥሮስ 3፡7** *እንዲሁም፥ እናንተ ባሎች ሆይ፥ ደካማ ፍጥረት ስለ ሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ፤ ጸሎታችሁ እንዳይከለከል አብረው ደግሞ የሕይወትን ጸጋ እንደሚወርሱ አድርጋችሁ አክብሩአቸው።*

4. ዮሐንስ 15፡5 ክርስቶስ የሕይወታችሁ ጌታ ባልሆነበት የትዳር ጋብቻችሁ ስኬታማ ሊሆን ይችላል?

   **ዮሐንስ 15፡5** *እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፥ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል።*

5. ቲቶ 2፡4 ፍቅር ስሜት ብቻ አይደለም፤ ይልቁንም በቃሉ መሰረት ____ ነው፤

   **ቲቶ 2፡4** *ቆነጃጅትም የእግዚአብሔር ቃል እንዳይሰደብ፥ ባሎቻቸውን የሚወዱ፥ ልጆቻቸውን የሚወዱ፥ ራሳቸውን የሚገዙ፥ ንጹሖች፥ በቤት የሚሠሩ፥ በጎዎች፥ ለባሎቻቸው የሚታዘዙ እንዲሆኑ ይምከሩአቸው።*

6. 1ኛ ዮሐንስ 5፡3 በእግዚአብሔር ትዕዛዝ የምንራመድ ከሆነ በ ____ እንራመዳለን።

   **1ኛ ዮሐንስ 5፡3** *ትዕዛዛቱን ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነውና፣ ትእዛዛቱም ከባዶች አይደሉም።*

7. ማቴዎስ 7፡12 በትዳራችን ውስጥ ችግር ካጋጠመን፣ ለዚህ ምክንያቱ አንድ ሰው በ ____ እየተራመደ ባለመሆኑ ነው፤

   **ማቴዎስ 7፡12** *እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ ሕግም ነቢያትም ይህ ነውና።*

8. 1ኛ ቆሮንቶስ 13፡4 ፍቅር የሆነው የቱ ነው -

   ሀ. ስሜታዊነት።
   ለ. የጋለ ስሜት።
   ሐ. ቸርነት።

   **1ኛ ቆሮንቶስ 13፡4** *ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም፤*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ኤፌሶን 5፡31-32። ኤፌሶን 5፡31 ከዘፍጥረት 2፡24 የመጣ ጥቅስ ነው። ኤፌሶን 5፡32ን በመመልከት በዚህ ቃል እግዚአብሔር እየነገረን ያለው ምንድን ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?
   **በክርስቶ እና በእርሱ ቤተክርስቲያን መካከል ያለውን ግንኙነት (ጋብቻን የሚመስል)።**

2. ያዕቆብ 4፡4-5 እነዚህ ቃላት ምን ያስተምራሉ?
   **እግዚአብሔር በእኛ ቀናተኛ ነው ለእርሱ እውነተኛ እንድንሆን ይፈልጋል።**

3. 1ኛ ጴጥሮስ 3፡7 ወደ ትዳር አጋራችሁ በአንድነት እና በፍቅር መጓዝ ያለባችሁ ለምንድን ነው?
   **ጸሎቴ እንዳይከለከል።**

4. ዮሐንስ 15፡5 ክርስቶስ የሕይወታችሁ ጌታ ባልሆነበት የትዳር ጋብቻችሁ ስኬታማ ሊሆን ይችላል?
   **አይችልም።**

5. ቲቶ 2፡4 ፍቅር ስሜት ብቻ አይደለም፤ ይልቁንም በቃሉ መሰረት ____ ነው፤
   **የምንማረው።**

6. 1ኛ ዮሐንስ 5፡3 በእግዚአብሔር ትዕዛዝ የምንራመድ ከሆነ በ ____ እንራመዳለን።
   **ፍቅር።**

7. ማቴዎስ 7፡12 በትዳራችን ውስጥ ችግር ካጋጠመን፣ ለዚህ ምክንያቱ አንድ ሰው በ ____ እየተራመደ ባለመሆኑ ነው፤
   **ፍቅር።**

8. 1ኛ ቆሮንቶስ 13፡4 ፍቅር የሆነው የቱ ነው -
   **ሐ. ቸርነት።**

# ትምህርት 11

# ጋብቻ - ክፍል 2

## በዶን ክሮው

ዛሬም እንደገና ስለ ጋብቻ ማውራታችን እንቀጥላለን፣ ለመሆኑ “ጋብቻ ምንድን ነው?” ይህን ጥያቄ አስባችሁት ታውቃላችሁ? እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ከሆነ ጋብቻን የመፍጠር ሃሳብ የእግዚአብሔር ነው። ጋብቻ መጣመር ነው። አንድነት እና መዋሃድ ነው። ዘፍጥረት 2፡24 *“ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል በሚስቱም ይጣበቃል (*አንድ ይሆናሉ፣ እርሱም ከሚስቱ ጋር ይጣበቃል) *ሁለቱም አንድ ሰጋ ይሆናሉ”* ይላል (በቅንፍ ያለው በእኔ የተጨመረ ነው)። ነገር ግን ትዳር ከመጣመርና አንድ ከመሆን በላይ መሆኑን አስባችሁ ታውቃላችሁ? ለምሳሌ 1ኛ ቆሮንቶስ 6፡16 ክርስቲያን ከሆንኩ በኋላ፣ ወደ ጋለሞታ ሄጄ ከእርሷ ጋር ብገናኝ ከእርሷ ጋር አንድ ሰጋ እንደምሆን ይናገራል። ዘፍጥረት 2፡24 ስለ ጋብቻ የሚናገረውን ደግመን እንመልከት። ከጋለሞታ ጋር ግንኙነት ማድረጌ አንድ ሰጋ ቢያደርገኝም ከጋለሞታዋ ጋር በጋብቻ እንድተሳሰር እና ወዲያውኑ ሚስቴን እንድፈታ አያደርገኝም። ስለዚህ ጋብቻ ምንድን ነው? ጋብቻ አንድ መሆንና መጣመር ከሆነ፣ ደግሞም አንድ ሰጋ መሆንም ከሆነ፤ ከጋለሞታ ጋር ግንኙነት በማድረግ እና በጋብቻ መካከል ልዩነቱ ምንድን ነው? በእርግጥ ከጋለሞታ ጋር ግንኙነት ያደረገ ሰው ከእርሷ ጋር አንድ ሰጋ ይሆናል።

እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ ጋብቻ - አንድነት፣ መጣመር፣ መዋሃድ ነው ይላል፣ ነገር ግን ከዚህም በላይ ነው። ጋብቻ በቃል ኪዳን መጣመር ነው። ይህ ኪዳን የሚለው ቃል በዕብራይስጥ “berith” ሲሆን ይህም አንድ ሆኖ የመጣበቅን ሃሳብ የያዘ ነው። ይህም አንድ ሰው በሞት እስኪለይ ድረስ ለመጽናት የሚያደርገው የመጨረሻ ውሳኔ ነው። እንግዲህ ወደ ጋለሞታ ሄጄ ክፉና አስነዋሪ የዝሙት ኃጢአት ብፈጽም፣ በእኔ በኩል ቃል ኪዳን ገብቼላታለሁ ማለት አይደለም። የጋብቻ መሰረታዊው ፍሬ ነገር በቅድሚያ ሌሎችን ሁሉ መተው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አባትና እናታችሁን ትተዋላችሁ ከሚስታችሁም ጋር ትጣበቃላችሁ ይላል። ሕዝቅኤል ደግሞ *“የኔ ሆነሃል”* ይላልና ይህ ሌሎችንም መተው ነው። ለአንድ ሰው ስትሉ ሌሎችን መተው-ራስን ለአንድ ሰው መስጠት፣ መወሰን ማለት ነው። ስለዚህ ከጋብቻ በኋላ በነውር ከትዳራችሁ ውጭ ከሌላ ሰው ጋር ግንኙነት ብታደርጉ በቃል ኪዳን የታሰረውን በአንድነትና በመጣመር የተመሰረተውን መሰረታዊ የጋብቻ መመሪያ ትጥሳላችሁ። ሕዝቅኤል 16፡8 የጋብቻ ቃል ኪዳን ሲል ይጠራዋል። በኤፌሶን 5 ደግሞ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት ባል ሚስቱን ሊወድ እንደሚገባ ያስተምረናል፤ ስለዚህ ቃል ኪዳኑ የፍቅር ኪዳን ነው። የፍቅር ኪዳን የሆነበት ዋናው ምክንያት ፍቅር የትዳር ማሰሪያ ዋና መርህ ስለሆነ ነው። ከሁሉም ነገር በላይ የትዳር መሰረቱ ፍቅር ሊሆን ይገባል።

ጋብቻ አንድ የመሆን ኪዳን ነው። በ1ኛ ጴጥሮስ 3፡7 ሚስቴን እንደ ተሰባሪ ዕቃ አክብሬ የማልንከባከባትና በጋራ የጸጋ ሕይወትን እንደምንካፈል በማወቅ ካልያዝኳት ጸሎታችን እንደሚከለከል ይናገራል። አስቡት - እግዚአብሔር ለትዳር ግንኙነት ባዘጋጀው መንገድ በፍቅርና በአንድነት ካልተጓዝን መንፈሳዊ ህይወታችን የሚጎዳ ተግባር እንፈጽማለን። ምሳሌ 2፡16-17 ቃሏን ስለምታለዝብና የልጅነት ወዳጇን ስለምትተው፣ የጋብቻ ግንኙነት የአምላኳ ቃል ኪዳን መሆኑን ስለ ምትረሳ፣ ስለ ጋለሞታ ሴት ይነግረናል። ይህ ጥብቅ ትኩረት ሊደረግበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ጋብቻ ከአንድ ሰው ጋር የምንገባው ኪዳን ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር ፊት የምንገባው ኪዳን ጭምር ነው። ሰዎችን ለማገልገል የምወደውን ያህል፣ ለእግዚአብሔር ቅድሚያ መስጠት ያስፈልገኛል፣ ይህም በትዳሬ ላይ ትኩረት ማድረግ ነው። ጋብቻ በእርግጥ ሕይወቴን በሌላ ሰው ላይ ትኩረት የማደርግበት ሲሆን፣ ከላይ እንዳልኩት፣ የሚመራበት መርህ ደግሞ ፍቅር ነው።

ማቴዎስ 7፡12 ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ ሕግም ነቢያትም ይህ ነውና ይላል። በትዳር ውስጥ ገዥ ሊሆን የሚገባው መመሪያ በእርግጥ ይህ ነው። ለራስ ብቻ ማሰብ ወይም ራስ ወዳድ መሆንም አይደለም፣ የትዳር አጋራችሁ ስለሚያደርግላችሁ ወይም ስለሚሰጣችሁ ነገር

ብቻም አይደለም። 1ኛ ቆሮንቶስ 13፡4 ፍቅር ቸርነትን ያደርጋል ይላል። ይህም ስለ ለሌሎች መልካም ማሰብ ነው፣ ለጋስ እና ቸር መሆን፣ ሁሌም ለሌሎች በጎ እንዲሆንላቸው መፈለግ ነው። ትዳር እንዲህ እንዲሆን ተደርጎ የተሰራበት ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ወዳጅነት ማለት ምን እንደሆነ የሚያሳይ ምሳሌ ወይም ሞዴል ስለሆነ ነው። የዚህ ወዳጅነት ሰዕል እንዲኖረን ተደርጎ ነው የተሰራው። መልካም ጋብቻ እንዴት ሊኖረን እንደሚችል አሳይቶናል፣ ጥሩ ጋብቻ ምን መሆን እንዳለበት ያሳየን ሲሆን ይህም ከእርሱ ጋር የሚኖረን የዘላለም ወዳጅነት ምን እንደሚመስል የሚያሳይ ምሳሌ ነው። ትዳር በሞት እስክንለይ ድረስ የሚቆይ፣ ጊዜያዊ ነገር ነው። በትንሳኤ ማግባትና መጋባት እንደሌለ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። እግዚአብሔር - መልካም ጋብቻ ማለት አንዱ ለሌላው ራሱን የሚሰጥበት የፍቅር መርህ፣ መሆኑን እንድንረዳ ይፈልጋል። እርሱም “በትክክል እንድትገነዘቡ የምፈልገው ጊዚያዊ ወዳጅነት ሳይሆን፣ ለጥቂት ዓመት ቆይቶ የሚጠፋውን ወዳጅነት ሳይሆን፣ ለዘላለም ፀንቶ የሚኖረውን፣ ፍቅሬንም ዘወትር ሁልጊዜ ለዘላለም ለእናንተ የምገልጥበትን፣ የጋብቻ ዓይነት ወዳጅነት ከእኔ ጋር እንዲኖራችሁ የጠራኋችሁ መሆኑን ነው” እያለን ነው።

አንዳንድ የጋብቻ መመሪያዎችን እስኪ አብረን እንመልከት፡- ጋብቻ ውህደት ነው እንጂ ሽርክና አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ በዘፍጥረት 4 እውቀት መሆኑን፣ በ1ኛ ጴጥሮስ 3፡7 ደግሞ የህይወትን ዋጋ አንድ ላይ መውረስ መሆኑን ይናገራል። ጋብቻ ኪዳን ነው፣ ትስስር ነው፣ ቃል መገባባትንም ያጠቃልላል። ኃጢአት ወደ መጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን ሳይሆን ወደ መጀመሪያው ትዳር ነውና የገባው የትዳር/ጋብቻን መመሪያ ማወቅ እና የፍቅርን መርህ ወደ ህይወታችን ማካተት አስፈላጊ ነው ማለት ነው። በተጨማሪም “ፍቅር ምንድን ነው?” የሚለውን ጥያቄ አብረን እንመልከት፡- የፍቅር መሰረታዊ ትርጉም ራስ ወዳድ አለመሆን ነው። ኢሳይያስ 53፡6 ሁላችንም እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፣ ከእኛ እያንዳንዱም ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ ይላል። በትዳር ግን ለሌላ ሰው ትኩረት እንሰጣለን፣ ለደህንነቱ/ቷ፣ ለጥቅሙ/ሟ እንሰራለን።

መጽሐፍ ቅዱስ በኤፌሶን መልዕክቱ ሚስትን መውደድ የእራሳችሁን አካል መውደድ ነው በማለት ይነግረናል። እኛ ባሎች እግዚአብሔር የሰጠንን ሚስቶቻችንን ማክበርና መንከባከብ፣ መጠበቅ ይገባናል፣ ይህም ሚስትን ማድነቅ፣ ማሞጋገስ ማለት ነው። የእራሳችሁን አካል መውደድ ማለት እራሳችሁን እየደባበሳችሁና “እወድሃለሁ” እያላችሁ ትከሻችሁን በእጃችሁ መታ መታ ማድረግ ማለት አይደለም። እራስን መውደድ ማለት፣ ራስን መጠበቅ፣ መመገብ እና ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ማለት ነው። ሚስቶቻችን እንዲሁ እንዳገኛናቸው ልንቆጥር አይገባም፣ በሰዎች ፊት ድክመታቸውን እያነሳን ልንተቻቸው፣ ልንቀልድባቸውና የሚያሳዝናቸውን ነገር ልናደርግ አይገባም። እራሳችንን እንደምንወድ አድርገን ልንወድ ይገባል።

እራሳችሁን ወደ እግዚአብሔር ለጸሎት አንሱ፣ በቅድሚያም ስለወደዳችሁ አመስግኑት። በመቀጠል ስለ ሰጣችሁ ስለ አጋራችሁ አመስግኑ። ይህም የችግሩ አንድ አካል ሊሆን ስለሚችል ነው። ምናልባት ከዚህ ቀደም አጋራችሁን ዝቅ አድርጋችሁ የምታዩ እና አድንቃችኋቸውም የማታውቁ ከሆነ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ራስ ወዳድነት ደግሞም ኃጢአት ነው ይላል። በኤፌሶን 5 ኢየሱስ ቤተክርስቲያንን በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንደቀደሳት፣ በቃሉ በቤተክርስቲያን ላይ እንደተናገረ ይናገራል። እናንተም በትዳር አጋራችሁ ላይ ቃል ስትናገሩ አጋራችሁ ወደ ተናገራችሁት ቃል ልክ ከፍ ይላሉ። አጋራችሁን - “ጥሩ አይደለሽም፣ አታምሪም፣ በጣም ወፍረሻል ...” ብላችሁ የምትናገሩ ከሆነ ትዳራችሁ ላይ ጫና እያሳደራችሁ እና ከአንድነት ይልቅ ልዩነትንና መለያየትን እየፈጠራችሁ ነው። ነገር ግን በትህትና ቃላት “ማሬ አደንቅሻለሁ፣ የምትሰሪው መልካም ነው፣ እወድሻለሁ ...” ብትሏቸውና በስራም ብትደግፏቸው ወደ ተናገራችሁት ቃል ልክ ከፍ ይላሉ።

በአሁኑ ጊዜ አብዛኛው በትዳር ግንኙነት ውስጥ ያለው ችግር የምንናገራቸው የቃሎቻችን ችግር መሆኑን አስተውላችኋል? የምትናገሩት ቃል አጋራችሁን ዝቅ የሚያደርግ ነው ወይስ ከፍ የሚያደርግ? ዛሬ አጋራችሁን መልካም ቃል እንድትናገሩ እመክራችኋለሁ። ፍቅር ስሜት አይደለም፤ ፍቅር በየትኛውም ዓይነት ስሜት ውስጥ

ብትሆኑም እንኳን ለሌላው ሰው መልካም ማሰብና መስራት ነው። ውበት እንዲጨምር ደጋግመን መልካም ቀለም እንደምንቀባው ቤት ዛሬ ለአጋራችሁ መልካም ነገር በማድረግ ጀምሩ፤ ፍቅር የሚገነባው እንዲህ ነው - ትንሽ መልካም ነገር ማድረግን በመጀመር። በአድናቆትና በአክብሮት ጀምሩ፣ ቦታ ስጥታችሁ የፍቅር ቃላትን ተናገሩአቸው፣ ልዩነቱን ማየት ትጀምራላችሁ። እነኛህን መርሆች ተግባራዊ በምታደርጉበት ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር ይባርካችሁ!!

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ምሳሌ 18፡22 አንብቡና ትዳር ምንድን ነው?

   ሀ. መልካም ነገር፣
   ለ. አሰፈሪ፣
   ሐ. እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ፣

   **ምሳሌ 18፡22** *“ሚሰት ያገኘ በረከትን አገኘ፥ ከእግዚአብሔርም ሞገሰን ይቀበላል።”*

2. ዕብራውያን 13፡4 አንብቡና በትዳር ውስጥ ያለ ጾታዊ ግንኙነት (መኝታ) –

   ሀ. ኃጢአት ነው፣
   ለ.አስጸያፊ እና ክፉ ነው፣
   ሐ.ንፁህ ነው፣

   **ዕብራውያን 13፡4** *“መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን፤ ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል”።*

3. መክብብ 9፡9 አንብቡና እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ - መልካም ትዳር፣ በዚህ ዓለም ህይወት፣ ከእግዚአብሔር የተሰጣችሁ ሽልማት ነው።

   **መክብብ 9፡9** *“በሕይወትህ፥ አንተም ከፀሐይ በታች በምትደክምበት ድካም ይህ እድል ፈንታህ ነውና ከንቱ በሆነ በሕይወትህ ዘመን ሁሉ፥ ከፀሐይ በታች በሰጠህ፥ በከንቱ ዘመንህ ሁሉ፥ ከምትወድዳት ሚሰትህ ጋር ደስ ይበልህ።”*

4. 1ኛ ዮሐንሰ 3፡18 አንብቡና ፍቅራችንን እንዴት እናሳይ?

   **1ኛ ዮሐንሰ 3፡18** *“ልጆቼ ሆይ፣ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ።”*

5. ኤፌሶን 5፡28 እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ - የራሴን ሰውነት ችላ እንደማልል ሁሉ ሚስቴንም ችላ ማለት የለብኝም።

   **ኤፌሶን 5፡28** *“እንዲሁም ባሎች ደግሞ እንደ ገዛ ሥጋቸው አድርገው የገዛ ሚሰቶቻቸውን ሊወዱአቸው ይገባል። የገዛ ሚሰቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል፤”*

6. 1ኛ ዮሐንሰ 3፡16 እውነት ወይም ሐሰት በሉ - “እውድሻለሁ” የሚለው ቃል በሥራ ሲደገፍ ውበት ይኖረዋል። ኢየሱሰ ሕይወቱን ለእኛ በመሰጠት ቃሉን እንደጠበቀ ሁሉ እኛም ለአጋራችን በምንችለው መጠን እራሳችን በልዩ ልዩ መልኩ መሰጠት ይገባናል፤

   **1ኛ ዮሐንሰ 3፡16** *“እርሱ ሰለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና በዚህ ፍቅርን አውቀናል፣ እኛም ሰለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል።”*

7. ኤፌሶን 5፡25-26 አንብቡና እውነት ወይም ሐሰት በማት መልሱ - ባለቤቴ እኔ በምናገረው ቃል ከፍታ ልክ ለመኖር ትችላለች፣ በምናገረው ቃል ወደ ምናገረው ልክ ማምጣት እችላለሁ።

**ኤፌሶን 5፡25-26** *“ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤”*

8. ሮሜ 8፡38-39 እና 1ኛ ዮሐንስ 4፡ 19 አንብቡና እውነት ወይም ሐሰት ብላችሁ መልሱ፦ በሚነገረን ቃል እና በድርጊት አማካኝነት መወደዳችን እናውቃለን። እግዚአብሔር እኛን ስለመውደዱ በቀጥታ የፍቅር ቃል የተናገረው ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል ተጽፎ ይገኛል።

**ሮሜ 8፡38-39** *“ሞት ቢሆን፥ ሕይወትም ቢሆን፥ መላእክትም ቢሆኑ፥ግዛትም ቢሆን፥ ያለውም ቢሆን፥ የሚመጣውም ቢሆን፥ ኃይላትም ቢሆኑ፥ [39] ከፍታም ቢሆን፥ ዝቅታም ቢሆን፥ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ።”*

**1ኛ ዮሐንስ 4፡19** *“እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን።”*

9. 1ኛ ዮሐንስ 5፡3 እና 2ኛ ዮሐንስ 6 አንብቡና እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ - ፍቅር ምን መሆኑን ከኢየሱስ ትዕዛዞች፣ የፍቅርን መርሆችንም ከእግዚአብሔር ቃል መማር እንችላለን።

**1ኛ ዮሐንስ 5፡3** *“ትእዛዛቱን ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነውና፣ ትእዛዛቱም ከባዶች አይደሉም። „*

**2ኛ ዮሐንስ 1፡6** *“እንደ ትእዛዛቱም እንሄድ ዘንድ ይህ ፍቅር ነው፤ ከመጀመሪያ እንደሰማችሁ፣ በእርስዋ ትሄዱ ዘንድ ትእዛዙ ይህች ናት።”*

10. ዮሐንስ 14፡15 እውነት ወይም ሐሰት በሉ - ፍቅር የስሜታችሁ ሳይሆን የፈቃዳችሁ ጉዳይ ነው። ሁሉም የእግዚአብሔር ቃል ለፈቃዳችን እንጂ ለስሜታችን አልተሰጠም። እግዚአብሔርም ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ነው እንጂ ምን እንደሚሰማችሁ አልተናገረም።

**ዮሐንስ 14፡15** *“ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ።”*

11. ገላትያ 5፡22-23 አንብቡና ፍቅር ተፈጥሯዊ አይደለም፤ ከመንፈስ የምንማረውና የምንካፈለው ነው። ፍቅር የምን ፍሬ ነው?

ሀ. የሰው ሐሳብ፣

ለ. የሰው ተፈጥሮ፣

ሐ. የእግዚአብሔር መንፈስ፣

**ገላትያ 5፡22-23** *“የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራሰን መግዛት ነው።”*

12. አፌሶን 5፡31-32 አንብቡና መልካም ጋብቻ የምን ታናሽ ምሳሌ ነው?

**አፌሶን 5፡31-32** *“ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። [32] ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው፥ እኔ ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን እላለሁ።*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ምሳሌ 18፡22 አንብቡና ትዳር ምንድን ነው?
**ሀ. መልካም ነገር እና ሐ. እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ።**

2. ዕብራውያን 13፡4 አንብቡና በትዳር ውስጥ ያለ ጾታዊ ግንኙነት (መኝታ) –
**ሐ.ንፁህ ነው።**

3. መክብብ 9፡9 አንብቡና እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ፤- መልካም ትዳር፣ በዚህ ዓለም ህይወት፣ ከእግዚአብሔር የተሰጣችሁ ሽልማት ነው።
**እውነት።**

4. 1ኛ ዮሐንስ 3፡18 አንብቡና ፍቅራችንን እንዴት እናሳይ?
**በሥራና በእውነት መዋደድ።**

5. ኤፌሶን 5፡28 እውነት ወይም ሐሰት፤ የራሴን ሰውነት ችላ እንደማልል ሁሉ ሚስቴንም ችላ ማለት የለብኝም።
**እውነት።**

6. 1ኛ ዮሐንስ 3፡16፤ እውነት ወይም ሐሰት በሉ - “እወድሻለሁ” የሚለው ቃል በሥራ ሲደገፍ ውበት ይኖረዋል። ኢየሱስ ሕይወቱን ለእኛ በመስጠት ቃሉን እንደጠበቀ ሁሉ እኛም ለአጋራችን በምንችለው መጠን እራሳችን በልዩ ልዩ መልኩ መስጠት ይገባናል፤
**እውነት።**
ፍቅር እንደሚያሰፈልጋችሁ የሚያመላክቱ አንዳንድ ተግባራትን አካፍሉ

7. ኤፌሶን 5፡25-26 አንብቡና እውነት ወይም ሐሰት በሉ - ባለቤቴ እኔ በምናገረው ቃል ከፍታ ልክ ለመኖር ትችላለች፣ በምናገረው ቃል ወደ ምናገረው ልክ ማምጣት እችላለሁ።
**እውነት፣ የኤፌሶን 5፡26 የግሪክ ትርጉም “ሬማ” ሲሆን ይህም “የሚነገር ቃል” ማለት ነ።ው**

8. ሮሜ 8፡38-39 እና 1ኛ ዮሐንስ 4፡ 19 አንብቡና እውነት ወይም ሐሰት ብላችሁ መልሱ - በሚነገረን ቃል እና በድርጊት አማካኝነት መወደዳችን እናውቃለን። እግዚአብሔር እኛን ስለመውደዱ በቀጥታ የፍቅር ቃል የተናገረው ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል ተጽፎ ይገኛል።
**እውነት፣ የእግዚአብሔር ቃል እኛን ስለመውደዱ በሚናገሩ ቃላት የተሞላ ነው።**

9. 1ኛ ዮሐንስ 5፡3 እና 2ኛ ዮሐንስ 1:6፤ እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ - ፍቅር ምን መሆኑን ከኢየሱስ ትዕዛዞች፣ የፍቅርን መርሆችንም ከእግዚአብሔር ቃል መማር እንችላለን።
**እውነት።**

10. ዮሐንስ 14፡15 እውነት ወይም ሐሰት በሉ - ፍቅር የሰሜታችሁ ሳይሆን የፈቃዳችሁ ጉዳይ ነው። ሁሉም የእግዚአብሔር ቃል ለፈቃዳችን እንጂ ለሰሜታችን አልተሰጠም። እግዚአብሔርም ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ነው እንጂ ምን እንደሚሰማችሁ አልተናገረም።
**እውነት።**

11. ገላትያ 5፡22-23 አንብቡና ፍቅር ተፈጥሯዊ አይደለም፤ ከመንፈስ የምንማረውና የምንካፈለው ነው። ፍቅር የምን ፍሬ ነው?
**ሐ. የእግዚአብሔር መንፈስ።**

12. ኤፌሶን 5፡31-32 አንብቡና መልካም ጋብቻ የምን ታናሽ ምሳሌ ነው?
**ክርስቶስ እና የእርሱ ቤተክርስቲያን።**

## ትምህርት 12

# እንደ እግዚአብሔር ያለ ፍቅር - ክፍል 1

## በዶን ክሮው

1ኛ ቆሮንቶስ 13፡13 *"እንዲህም ከሆነ እምነት፣ ተስፋ፣ ፍቅር እነዚህ ሶስቱ ፀንተው ይኖራሉ፣ ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው"*። እንደገናም 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡1 *"ፍቅርን ተከታተሉ፣ መንፈሳዊ ስጦታንም ይልቁንም ትንቢት መናገርን በብርቱ ፈልጉ"* ይላል። መጽሐፍ ቅዱስ ፍቅርን ተከታተሉ፣ ፈልጉ፣ ዋና አላማችሁም ይሁን ሲል ይመክራል። አንዳንድ ትርጉሞች ታላቁ ፍለጋችሁ እርሱ ይሁን ይላሉ። አሁን ካለንበት ሕይወት ወደ ዘላለም ሕይወት ስንሔድ ይዘነው የምንሄደው ብቸኛው ነገር ፍቅር ነው። መኪኖቻችን፣ ቤታችን ወይም ገንዘባችን መውሰድ አንችልም፣ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ በኩል ለህይወታችን ያካፈለንን ፍቅር ይዘን እንሔዳለን። ብቸኛው ዘላለማዊ ዋጋ እና ቁም ነገር ያለው ፍቅር ብቻ ነው።

ለመሆኑ ፍቅር ምን ማለት ነው? "ሚስቴን እወዳታለሁ፣ አይስክሬም እወዳለሁ፣ በፍራፍሬ የተሰራ ኬክ እወዳለሁ" ብዬ እናገራለሁ። ስለ ፍቅር ስናገር ሚስቴን አፈቅራታለሁ እንደምል ድመቴንም አፈቅራታለሁ ብዬ ብናገር ሚስቴን የሚያስደስት ቃል አይሆንም፣ የምለው ግልጽ ሆነላችሁ? ፍቅር የሚለውን ቃል ስንጠቀም አንዳንዶች ለጾታዊ ግንኙነት፣ ሌሎች ደግሞ ለአንድ ነገር ያላቸውን ጥልቅ ስሜት ለመግለጽ ይጠቀሙበታል። ሰዎች ለፍቅር ብዙ የተለያዩ ትርጉም ይሰጡታል - የግሪክ ቋንቋ ግን ለፍቅር መግለጫ አራት ዋና ዋና ቃሎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ኢሮስ (eros) ሲሆን፣ በእርግጥ ቃሉን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አታገኙትም፣ ሆኖም በጾታዊ ግንኙነት መሳብን ወይም ጾታዊ ፍቅርን ያመላክታል። እግዚአብሔር - ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ስጋ ይሆናሉ ሲል ያንን የፍቅር ዓይነት ወስኗል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መኃልዩ መኃልዩ ዘሰለሞን የተባለው መጽሐፍ እግዚአብሔር በጋብቻ ግንኙነት ውስጥ በባልና ሚስት መካከል ይኖር ዘንድ የፈቀደውን የፍቅር ዓይነት ያመለክታል። ከኢሮስ ውጭ ሌሎችን የፍቅር ዓይነቶች የሰው ልጆች በነጻነት ሊጠቀሙባቸው የተፈቀዱ ናቸው ሲል፣ እግዚአብሔር የገለጻቸው ሲሆን፣ ኢሮስ ግን በትዳር ውስጥ ላለ ግንኙነት ብቻ ተፈቀደ የፍቅር ዓይነት ነው።

ሌላው የፍቅር ዓይነት ስቶርጅ (storge) ሲሆን ይህም በቤተሰብ ወይም በቤተዘመድ ተፈጥሯዊ ትስስር እና ግንኙነት ውስጥ ያለ የፍቅር ዓይነት ነው። ደግሞም ሌላው ፊሊዎ (phileo) ሲሆን ይህም ፊሊኣ (philea) ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ነው። ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን ከ72 ጊዜ በላይ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ቃሉ እንደሚያመለክተው በቅጽበት ወይም በድንገት የሚመጣና የሚሄድ የሞቀ ወይም የጋለ የመውደድ ስሜት ነው፡፡ ብዙ ሰዎች ስለ ፍቅር ሲናገሩ ፍቅር ብለው የሚገልጹት ይህንን ዓይነት ፍቅር ነውና "ፍቅር ያዘኝ እና ፍቅሬ ቀዘቀዘ" ብለው ሲናገሩ እንሰማለን። ትዳራችሁ በእንዲህ ዓይነት ፍቅር ላይ የተመሰረተ ከሆነ፣ አንዴ ከፍ ሌላ ጊዜ ደግሞ ዝቅ የሚል ይሆናል፣ እንደ ሁኔታው በፍቅር ልትወድቁ ወይም ከፍቅር ልትወጡ ትችላላችሁ ማለት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደ እግዚአብሔር ዓይነት በሆነ ፍቅር እርስ በእርሳችን ልንዋደድ የሚገባ መሆኑን የሚናገር ሲሆን፣ ይህም አጋፔ (agape) ፍቅር በመባል ይታወቃል። አጋፔ ፍቅር ምንድን ነው? ይህንን በተመለከተ ብዙ ዓይነት እይታዎች ያሉ ሲሆን በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 13 የፍቅርን ሙሉ ትርጓሜዎች እናገኛለን። 1ኛ ዮሐንስ 5፡3 ደግሞ *"ትዕዛዛቱን ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነውና ..."* ይላል። የኢየሱስ ትዕዛዞች የፍቅር መገለጫ መሆናቸውን መመልከት እንችላለን፣ ሁሉንም ጠቀለል ባለ መልኩ የሚያቀርብልን ግን ማቴዎስ 7፡12 ነው፡ *"እንግዲህ ሰዎች እንዲያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ ሕግም ነቢያትም ይህ ነውና"*። የቤተክርስቲያናችን ሰዎች ስለማይወዱኝ፣ ሌሎች ሰዎችም ስለሚጠሉኝ፣ በዚህ ወይም በዚያ ምክንያት ብለን ምክንያት የምናቀርብበት ጉዳይ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ሌሎች እንዲያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ መጀመሪያ እናንተ አድርጉላቸው ይለናል። ፍቅር ይህ ነው። ሆኖም ግን ከራሳችን ይልቅ ለሌሎች

ሰዎች መቆርቆርና የሌሎችን ብልጽግና መፈለግ፣ ከራሳችን ይልቅ ለሌሎች በጎ ነገርን ማድረግ፣ ከተፈጥሮ የሥጋ ባህሪአችን ተቃራኒ ነውና ለዚህም እግዚአብሔር ያስፈልገናል። ይህ ያለ እግዚአብሔር ሊሳካ ይችላል እያልኩ እንደሆነ እድርጋችሁ ማሰብ የለባችሁም። መጽሐፍ ቅዱስ ፍቅር የመንፈስ ፍሬ መሆኑን ይነግረናል፣ እግዚአብሔር ፍቅር ነው። እግዚአብሔር የፍቅር ምንጭ ሲሆን በትዕዛዛቱም ሌሎችን ማፍቀር እንዴት እንደሚቻል የሚያሳየን እርሱ ነው። ምንም በሰጋ ብንሆን ዕንኳን እንዴት ትክክለኛ ምርጫና ውሳኔ ማድረግ እንደምንችል ጥንካሬን የሚሰጠን እርሱ ነው።

ከዕለታት አንድ ቀን፣ ሁሌም ከሥራ በኋላ እንደማደርገው መጸለይ እፈልግ ነበርና በአንድ መናፈሻ (ፓርክ) ውስጥ ሳለሁ “እግዚአብሔር ሆይ ዛሬ አንድን ሰው ማገልገል እፈልጋለሁ” ብዬ ተናገርኩ። ብዙም ሞቃታማ ያልሆነ ቀን ነበርና አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት፣ ሁለት ልጆች በዥዋዥዌ መጫወቻ ላይ ተቀምጠው አየሁ። አጠገባቸው ሄጄ በመቀመጥ ትንሿን ልጅ “ዛሬ ደስ የሚል ቀን ነው፣ አይደል?” ስል ጠየኳት። እርሷም በተሰባበረ እንግሊዝኛ “እኔ እንግሊዝኛ መናገር አልችልም” አለች። እኔም “ከየት ነው የመጣችሁት?” ስል በድጋሚ ጠየኳት። እርሷም ከሮሜኒያ እንደመጡ ነገረችኝ። ከዚህ ቀደም ከሮሜኒያ የመጡ ሰዎች በዚህ አካባቢ እንደሚኖሩ አውቅ ነበር፣ እነርሱም ምናልባት ከትንሿ ልጃቸው ጋር በማውራቴ ተደንቀው በመገረም ሲመለከቱኝ አየኋቸውና ወደ እነርሱ በመሄድ “ልረዳችሁ እፈልጋለሁ” አልኳቸው። እነርሱም “ልትረዳን ትፈልጋለህ? ለምን ልትረዳን ፈለግህ? ማን እንደሆንን እንኳን አታውቅም!” አሉኝ። እኔም “እግዚአብሔር ሊረዳችሁ ስለሚፈልግ ነው” አልኳቸው። በ1ኛ ዮሐንስ 3፡18 ያለውን የፍቅር መመሪያ እያሰላሰልኩ ነበር፣ እንዲህ ይላል *“ልጆቼ ሆይ፣ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ”* ይላል። ከአንደበታችን በሚወጡ ቃሎች ብቻ ማፍቀር የሌብንም፣ ነገር ግን በሥራ ወይም በተግባር ጭምር ነው እንጂ። ምንም እንኳን ገንዘብ ይዤ የመዞር ልማድ ባይኖረኝም፣ በዛች ቀን ግን ኪሴ ውስጥ መጠነኛ ገንዘብ ይዣለሁ። ገንዘቡን አወጣሁና “ይህ ለእናንተ ነው” ብዬ ሰጠኋቸው። ያን ቀን እየጾምኩ ነበርና የተወሰነ ምግብ በቦርሳዬ ይዤ ነበር፣ ያንንም አውጥቼ “ጥቂት ምግብ ደግሞ ለቤተሰባችሁ ይሄው” አልኳቸው። ልባቸው ተነካና “አንተ ማን ነህ?” አሉኝ። እኔም “እግዚአብሔር በገዛ ጥበቡ ዛሬ እንድንገናኝ አድርጓል፣ ደግሜ አያችኋለሁ” አልኳቸው።

ወደ ቤት እንደሄድኩ ከሮሜኒያ ሰዎች ጋር የነበረኝን ቆይታ በተመለከተ ለባለቤቴ አጫወትኳት። ፍሪጅ ውስጥ የነበረኝንም ምግብ አበሰልኩ። በቀጣዩ ቀን የሚያስፈልገንን ያህል ምግብ እና መመገቢያ ዕቃዎች ገዝተን በመጫን ከባለቤቴ ጋር ወደ መናፈሻው ሄድን። ሮሜኒያውያኑ ከልጆቻቸው ጋር እዛው ነበሩ። እኔም “ስጦታ ይዘንላችሁ መጥተናል፣ ነገር ግን ጥቂት ክብደት ስላለው ቤታችሁን ካሳያችሁኝ እዛው ድረስ ላደርስላችሁ እችላለሁ” አልኩ። ወደ ባለ አንድ መኝታ ቤት፣ ትንሽ የመኖሪያ አፓርትመንታቸው እንደደረስን የመመገቢያ ሳህኖቹንና የምግብ እቃዎችን አንድ በአንድ እያወጣሁ ሰጠኋቸው፣ ሁሉም መልካም ነበረ። በምሰጣቸው ጊዜ እንባቸው በፊታቸው ላይ ኩልል ብሎ መውረድ ጀመረ፣ በመቀጠልም የልጆቹ እናት “እያለቀስኩ ነው፣ እንባየን መቆጣጠር አልቻልኩም” አለች በተሰባበረ እንግሊዝኛ። እኔም “ሰኞ ማታ በቤቴ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እናደርጋለን፣ እናንተንም እንድትመጡ ጋብዣችኋለሁ” አልኳቸው። “እንመጣለን፣ መምጣት እንፈልጋለን” አሉ። “ስጦታ ስለሰጠኋችሁ፣ እንደ ውለታ ቆጥራችሁ እንድትመጡ ግን አልፈልግም” አልኳቸው፣ እነርሱም “አይደለም፣ መጥተን የአንተን ወዳጆችም መተዋወቅ እንፈልጋለን” አሉኝ።

ምንም መጓጓዣ ስላልነበራቸው እኔ እራሴ ሄጄ ወደ ቤታችን አመጣኋቸው፣ ብዙም ሳይቆይ እግዚአብሔር ይነካቸው ጀመር። እንግሊዝኛ መናገር እምብዛም ባይችሉም በምንጸልይላቸው ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር እየነካቸው የእግዚአብሔር ፍቅር እየተገለጠላቸው ነበር። ብዙም ሳንቆይ ሌሎች ሮሜኒያውያን ጥንዶችንም ማግኘት ችለን ነበርና ለመጀመሪያዎቹ - “ሌሎች ሮሜኒያውያን ጥንዶችን አግኝቻለሁ ወደ እነርሱ እብራችሁኝ ልትሄዱ ትችላላችሁ?” ብዬ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ስምምነታቸውን ገለጹልኝ። አዲሶቹ ጥንዶችም አንድ ቀን ደውለው እንዲህ አሉኝ “አቶ ዶን ስለአንተ ሁሉንም ሰምተናል፣ ብቸኝነት በጣም ጎድቶናልና ብናገኝህ እንወዳለን” አሉኝ።

ስለዚህ የመጀመሪያዎቹን ሮሜንያዊ ወዳጆቼን ይዤ አዲሶቹን ጥንዶች ለማግኘት ሄድኩ። ስጦታዎች፣ ምግብ እና ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች ያዝኩላቸው። እነርሱ ጋር እስከተገናኘንበት ሰዓት ሁሉም ነገር በመልካም ሁኔታ እየተጓዘ ነበር፣ በመካከሉ ግን የመጀመሪያዎቹ ጥንዶች ለአዲሶቹ "ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምጣት አለባችሁ፣ ስለ ኢየሱስ ይነግሯችኋል፣ በጣም የሚያስደንቅ ነገር ነው" አሉአቸው። አዲሶቹም "ረጋ በሉ እንጂ፣ እኛ እኮ የመጣነው ከኮሚዩኒስት አገር ነው እግዚአብሔር መኖሩንም እንኳን አናውቅም። ኢየሱስ ያላችሁትም ለእኛ አያስፈልገንም" አሉ።

እኔም "ግዴለም እኔም ወዳጃችሁ እንድሆን ነው የምፈልገው" አልኩና በሳምንቱ መጨረሻ ይዣቸው ወጣሁ። ልብሶች፣ መደረቢያ ኮት እና ሌሎች የሚያስፈልጋቸውን ነገሮችም ገዛሁላቸው። እነርሱም ሃፍረት ቢጤ ተሰማቸውና ሃሳባቸው መዋለል ጀመረ። እኔም አባወራውን "ኮት አያስፈልግህም እንዴ?" ስል ጠየኩት፤ "እሱማ ያስፈልገኛል፣ ብቻ…"፣ "እንግዲያው ይህን ኮት ለአንተ እንግዛው"። በእርግጥ በተግባር ፍቅሬን እየገለጽኩላቸው ነበር። ነገር ግን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምጣት ይችሉ ዘንድ አንድ ነገር ማድረግ ነበረብኝና እንዲህ አልኳቸው - "ከመጣችሁ ምናልባት ሥራ ሊያገኙላችሁ የሚችሉ አንዳንድ አሜሪካውያን እናገኝ ይሆናል" አልኳቸው። እነርሱም ቀጥ ብለው መጡ። በዛች ምሽት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን ላይ አንድ ምስኪን ሰው የሚጠይቀውን አይነት ሞኝ ጥያቄ ለጌታ አቀረብኩ "ጌታ ሆይ እርስ በእርስ እንኳን በቋንቋ መግባባት አንችልምና ዛሬ ምሽት ጥርት አድርገን የምንግባባበት ልሳን እንድትሰጠን እፈልጋለሁ" ስል ጠየኩ። በምሽቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ ምስክርነታቸውን የሚነግሩን አንዳንድ አሜሪካውያን በመካከላችን ነበሩ። እኔ መናገር እንደጀመርኩ ከሁለተኛዎቹ ሮሜኒያውያን ጥንዶች ውስጥ ሴትዮዋ የሆነ ነገር እንደበራላት አስተዋልኩና ከጥናታችን በኋላ "ልጸልይልሽ" ብዬ መጸለይ ስንጀምር ወዲያውኑ እግዚአብሔር ይነካቸው ጀመር፣ ያለንበት ክፍልና እየሩም፣ ሁሉም ነገር በፍቅሩ ሙላት ተሞላ። ሴትዮዋም በመቀጠል እዲህ አለች "ታውቃለህ! አሜሪካኖቹ ምስክርነታቸውን በሚናገሩበት ጊዜ የሚናገሩትን አንዱንም ቃል መረዳት አልችልም ነበር። ነገር ግን አንተ ተነስተህ ስለ ኢየሱስ በምትናገርበት ሰዓት፣ ለእኛ ያለውን ፍቅር እና እንደሚወደን በምትናገርበት ጊዜ፣ ከእርሱ ጋር ግንኙነት ይኖረን ዘንድ የሰራውን ስራ ሁሉ ስትናገር የምትናገረውን እያንዳንዱን ቃል በግልጽ እየተረዳሁና እየገባኝ ነበር! ሁሉንም ግልጽ እና ፍጹም ሆኖ እሰማ ነበር። እግዚአብሔር መሆን አለበት። እግዚአብሔር መሆን አለበት" አለች፣ በዚህም የሮሜኒያውያኑ ብቻ ሳይሆን የሁላችንም ህይወት ተለውጦ ነበር።

ቤቴ ሰኞ ምሽት ላይ ዓለም አቀፍ መሆንና በሁሉም አገር ሰዎች መሞላት ጀመረች፣ የሮሜኒያ፣ የቡልጋሪያ ሰዎች እና ራሻዎችም ነበሩበት። እግዚአብሔር የሰዎችን ሕይወት እየቀየረ ነበር፣ ሁሉም እንደወደድናቸው አውቀዋል። ከአፍሪካ የመጡ ሰዎች ጭምር ወደ እኛ መምጣት ጀምረዋል። ምንም እንኳን በቋንቋ ተግባብተን ማውራት ባንችል፣ አንድ ነገር ግን አውቀው ነበር ይኸውም - በምንጸልይበት ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር እራሱን ለእነርሱ ይገልጥ ነበር። ደግሞም በእኔ በኩል ምንም ነገር ቢሆን እንደማደርግላቸውና እንደማፈቅራቸው አውቀው ነበር። የእነርሱን እና የሌሎችን ብዙ ሰዎች ህይወት እግዚአብሔር ቀየረ። ይህ ሁሉ የሆነው አንድ ቀን በፓርክ ውስጥ ጸጉረ ልውጥ፣ የሌላ አገር ሰዎችን በማየቴ ምክንያት ነበር። ምንም ዓይነት የጋለ የመውደድ ስሜት አልነበረኝም፣ ነገር ግን ፍቅር ማለት ይህ እንደሆነ ተረድቻለሁ፡ ሰዎች ለእናንተ እንዲያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን፣ ለእነርሱ ማድረግ። የገዛ ስሜቴን ወደ ጎን ትቼ ለእነርሱ የሚያስፈልጋቸውን መልካም ነገር ስላደረግኩላቸው ይህን ተከትሎ ምን እንደተፈጠረ ታውቃላችሁ? እነርሱም ያደረግኩላቸውን በደስታ ተቀብለውታልና በእነርሱ ውስጥ ለእኔ ፊሊዓ የፍቅር ስሜት ተፈጥሮባቸው ነበር፣ ስሜት ያለው ፍቅር፣ እናም ወደ እኔ ቀርበው "እወድሃለሁ" ይሉኝ ነበር፣ ያቅፉኝና ይስሙኝም ነበር። ይህም በእኔ ውስጥ ለእነርሱ ተመሳሳይ ስሜት እንዲኖረኝ አደረገ። በህይወታችሁ ስሜት ያለው ፍቅር እንዲኖራችሁ ከፈለጋችሁ፣ አጋፔ ፍቅርን ተለማመዱ። የገዛ ስሜታችሁን ወደ ጎን ትታችሁ የሌሎችን ደህንነትና ብልጽግና ፈልጉ፣ ይህም ስሜት ያለው ፍቅር በውስጣችሁ እንዲመነጭ ያደርጋል።

## *የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች*

1. *1ኛ ዮሐንስ 5፡3 የእግዚአብሔር ፍቅር በ ____ ውስጥ ያታወቃል።*

   **1ኛ ዮሐንስ 5፡3** *"ትእዛዛቱን ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነውና፣ ትእዛዛቱም ከባዶች አይደሉም፣*

2. *ሮሜ 13፡9-10 በዚህ ቃል ላይ ያለው ትዕዛዝ ፍቅርን እንዴት እንደሚያሳይ አብራሩ፤*

   **ሮሜ 13፡9-10** *"አታመንዝር፥ አትግደል፥ አትሰረቅ፥ በውሸት አትመስክር፥ አትመኝ የሚለው ከሌላይቱትእዛዝ ሁሉ ጋር በዚህ። ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ በሚለው ቃል ተጠቅልሎአል። [10] ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም፤ ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው"።*

3. ሮሜ 12፡19-21 ውስጣችን ባይቀበለውም እንኳን ጠላቶቻችን እንዴት መውደድ እንችላለን?

   **ሮሜ 12፡19-21** *"ተወዳጆች ሆይ፥ ራሳችሁ አትበቀሉ፥ ለቍጣው ፈንታ ስጡ እንጂ፤ በቀል የእኔ ነው፥ እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ ይላል ጌታ ተብሎ ተጽፎአልና። [20] ጠላትህ ግን ቢራብ አብላው፤ ቢጠማ አጠጣው፤ ይህን በማድረግህ በራሱ ላይ የእሳት ፍም ትከምራለህና። [21] ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ"።*

4. ቲቶ 2፡4-5 ይህ ቃል ስለ ፍቅር ምን ያሳየናል?

   **ቲቶ 2፡4** *"ቆነጃጅትም የእግዚአብሔር ቃል እንዳይሰደብ፥ ባሎቻቸውን የሚወዱ፥ ልጆቻቸውን የሚወዱ፥ ራሳቸውን የሚገዙ፥ ንጹሖች፥ በቤት የሚሠሩ፥ በጎዎች፥ ለባሎቻቸው የሚታዘዙ እንዲሆኑ ይምከሩአቸው"።*

5. 1ኛ ቆሮንቶስ 13፡4-8 የፍቅርን አላማዎች ወይም መርሆች በዝርዝር ግለጹ፤

   **1ኛ ቆሮንቶስ 13፡4-8** *"ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም፤ [5] የማይገባውን አያደርግም፥ የራሱንም አይፈልግም፥ አይበሳጭም፥ በደልን አይቆጥርም፤ [6] ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤ [7] ሁሉን ይታገሣል፥ ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል። [8] ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም፤ ትንቢት ቢሆን ግን ይሻራል፤ ልሳኖች ቢሆኑ ይቀራሉ፤ እውቀትም ቢሆን ይሻራል"።*

6. 1ኛ ዮሐንስ 3፡18 ፍቅርን እንዴት መለማመድ አለብን?

   **1ኛ ዮሐንስ 3፡18** *"ልጆቼ ሆይ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ"።*

# ጠቋሚ መልሶች

1. 1ኛ ዮሐንስ 5፡3 የእግዚአብሔር ፍቅር በ ____ ውስጥ ያታወቃል።
**በትእዛዛቱ።**

2. ሮሜ 13፡9-10 በዚህ ቃል ላይ ያለው ትዕዛዝ ፍቅርን እንዴት እንደሚያሳይ አብራሩ፤
**ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም፤ እያንዳንዱ ትዕዛዝ ፍቅርን የሚያሳይ ሲሆን ለባልንጀራችን ምን ማድረግ እንዳለብንም ያሳዬናል፣**

3. ሮሜ 12፡19-21 ውስጣችን ባይቀበለውም እንኳን ጠላቶቻችን እንዴት መውደድ እንችላለን?
**ጠላታችን ቢራብ በማብላት፤ ቢጠማ የሚጠጣው ነገር በመስጠት። ከስሜት ነጻ ሆነን ለሌሎች መልካምን ማድረግ መፈለግ ይኖርብል።**

4. ቲቶ 2፡4-5 ይህ ቃል ስለ ፍቅር ምን ያሳየናል?
**ፍቅርን መማር እንደሚቻል እንማራለን።**

5. 1ኛ ቆሮንቶስ 13፡4-8 የፍቅርን አላማዎች ወይም መርሆች በዝርዝር ግለጹ፤
**ፍቅርይታገሣል፥ቸርነትንምያደርጋል፤ፍቅርአይቀናም፤ፍቅርአይመካም፥አይታበይም፤ የማይገባውን አያደርግም። የራሱንም አይፈልግም፥ አይበሳጭም፥ በደልን አይቆጥርም። ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም። ሁሉን ይታገሣል፥ ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል። ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም፤**

6. 1ኛ ዮሐንስ 3፡18 ፍቅርን እንዴት መለማመድ አለብን?
**በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ።**

## ትምህርት 13

# እንደ እግዚአብሔር ያለ ፍቅር - ክፍል 2

### በዶን ክሮው

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር ከመጡ ሰዎች ሁሉ ይልቅ፣ እጅግ የሚበልጥ፣ ታላቅ የፍቅር መገለጫ ነበር። ሆኖም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማንንም “እወድሃለሁ” ብሎ ሲናገር አናይም፣ በዚህ አልተገረማችሁም? ለምን ይሆን የሚል ጥያቄስ ፈጥሮባችኋል? ለዚህ ምክንያቱ ፍቅር ከንግግር ወይም ከቃላት በላይ ስለሆነ ነው፤ ፍቅር ተግባር ወይም ድርጊት ነው (Love is Action)። ለምሳሌ ሚስቴን በቃሌ “እፈቅርሻለሁ” እያልኩ ነገር ግን በተግባር ወጣ ብዬ በእርሷ ላይ ዝሙት ብፈጽም፣ ቃሌን ታምናለች ወይስ ድርጊቴን? እርሷ እኔን የምታምነኝ በቃሌ ሳይሆን እንደ ድርጊቴ መጠን በተግባሬ ነው። ምክንያቱም የፍቅር 95% የሚሆነው መገለጫ ቃላት ሳይሆን ድርጊት ወይም ተግባር በመሆኑ ነው። ፍቅር በንግግራችሁ የምትገልጹት ሳይሆን የምታደርጉት የምትፈጽሙት ተግባር ነው።

በ1ኛ ዮሐንስ 3፡18 ይህን እናነባለን - *“ልጆቼ ሆይ በሰራና በእውነት እንጅ በቃልና በአንደበት* [ለአፋችን ብቻ ፍቅርን በቃላት በመግለጽ] *አንዋደድ”* (በቅንፍ ያለው ከእኔ የተጨመረ ነው)። ፍቅር ተግባር ወይም ድርጊት ነው። በማቴዎስ 25፡35-36 ኢየሱስ ፍቅርን በተግባር እንዲህ ይገልጸዋል - *“ተርቤ አብልታችሁኛልና፣ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፣ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፣ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፣ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፣ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና”*። በመቀጠል በቁጥር 40 እንዲህ ይላል - *“እውነት እላችኋለሁ፣ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞች ለአንዱ እንኳ ካደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት”*። አያችሁ፣ ፍቅር ልትፈጽሙት የሚገባ ተግባር እንጂ ባዶ ቃላት ብቻ አይደሉም። ዕብራውያን 6፡10 ደግሞ እንዲህ ይላል፤ - *“እግዚአብሔር፤ ቅዱሳንን ስላገለገላችሁ እስከ አሁንም ስለምታገለግሉአቸው፣ ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙም ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይደለምና”*። በማቴዎስ 22 ከትዕዛዛት ሁሉ የትኛው ትዕዛዝ ይበልጣል ተብሎ ለቀረበለት ጥያቄ ኢየሱስ - እግዚአብሔርን መውደድ ደግሞም ባልንጀራህን መውደድ ነው በማለት ይመልሳል። እነዚህ ትዕዛዞች ሁለት ሳይሆኑ በእርግጥ፣ በትክክል ከተረዳነው አንድ ናቸው። ምክንያቱም ከታናናሾቹ ለአንዱ ፍቅር ብትሰጡ ለራሱ ለኢየሱስ እንደሰጣችሁት ተናግሯልና ነው። እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን ለኢየሱስ ያለንን ፍቅር ለመግለጽና እርሱን ለመውደድ ድንቅ አማራጭ የተሰጠን ሲሆን እርሱም ሌሎች ሰዎችን መውደድ ነው።

ከዚህ ትምህርት በፊት በነበረው ክፍል ላይ በመናፈሻ (ፓርክ) ውስጥ ስላገኘኋቸው የሮሜኒያ ሰዎች ተናግሬ ነበር። ህይወታቸው ሊቀየር የቻለው እኔ በግል የሚሰማኝን የራሴን ስሜት ወደ ጎን በመተው ለእነርሱ የሚያስፈልጋቸውን ጠቃሚ ነገር በማድረጌ ነበር። ዜግነታቸውና ቀለማቸው የተለየ ቢሆንም እንኳን እኛ ለሰዎች ደርሰን መልካም ነገር ስናደርግላቸው የእግዚአብሔር ፍቅር ራሱን እንደሚገልጥ ተረድቼ ነበር፣ ልክ ኢየሱስ እንዳደረገው። ኢየሱስ ወደ መስቀል ሞት መሄድን እንዲሁ አልወደደም፣ እንዲህም አለ “አባቴ ቢቻልስ፣ ሌላ አማራጭ መንገድ ካለ ይህ ከእኔ ይለፍ፣ ነገር ግን አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጅ እኔ እንደምወድ አይሁን” አለ። በዚህም ኢየሱስ የእኔን እና የእናንተን ህይወት ድህነትና ደህንነት ደግሞም ብልጽግና እንጂ የራሱን ስሜት አልተመለከተም።

አንድ ቀን ሮሜኒያውያኑ ደወሉልኝ፣ ሳግ እየተናነቃቸው ያለቅሱ ነበር። በአሜሪካ መኖር ከጀመሩ ሰባት ዓመት ተኩል ሆኗቸዋል። አሁን የሚኖሩት በካንሳስ ግዛት ውስጥ ሲሆን ስራም አግኝተው ነበር። እነርሱም እንዲህ አሉኝ “የፖለቲካ ጥገኝነት ጥያቄአችን በመጨረሻ ተቀባይነት አላገኘም። ይግባኝ የምንልበት የሰላሳ ቀን ጊዜ ገደብ ተሰጥቶናል ከዛ በኃላ ግን ወደ አገራችን ያባርሩናል”። በእርግጥ በዩናይትድ ስቴትስ የፖለቲካ ጥገኝነት የማግኘት እድል ከ2 እስከ 5 ፐርሰንት ቢሆን ነው። ሮሜኒያውያኑ ወደ ጠበቃ ሄዱ፣ ጠበቃቸውም ምንም እድል እንደሌላቸው ገለጸላቸው። እኔም እንደምንጸልይበትና ልረዳቸው እንደምሞክር ነገርኳቸው። እንዴት ለሚለው ግን መልስ የለኝም።

በተለይ ልጆቻቸው አሁን ላይ ምንም የሮሜኒያ ቋንቋ መናገር በማይችሉበት ሁኔታ እነርሱን ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ማድረግ ፍትሐዊ እንዳልሆነ ተሰምቶኛል።

አንድ ወዳጄ እኛ ከምንኖርበት ኮሎራዶ ግዛት ውስጥ ለሚያውቃቸው የምክር ቤት አባል ደውሎ በጉዳዩ ላይ ካናገራቸው በኋላ ሮሜኒያውያኑ በሚኖሩበት የካንሳስ ግዛት ውስጥ ሴናተር ሳም ብራውንባክ የተባሉ የግዛቱ የምክር ቤት አባልን እንድናናግርላቸው ነገረኝ። ይህ መልካም አጋጣሚ ነበር ምክንያቱም ለሴናተር ብራውንባክ የምትሰራ አንዲት ኪም የምትባል ወዳጅ አለችኝ። ኪምን አገኘኋትና በዚህ ጉዳይ የሚሰሩ አራት ሰዎችን ከዋሽንግተን ዲሲ አመቻቸች። በሰብሊት ካንሳስ የሚገኘው ማኅበረሰብም ከጉዳዩ ጀርባ ሆነው ሮሜኒያውያኑን በመደገፍ በግዛታቸው ውስጥ እንዲኖሩና እንዳይባረሩ ለማድረግ የድጋፍ ፊርማ ማሰባሰብ ጀመሩ። “መልካም ሰዎች ናቸው፣ ግብርም ይከፍላሉ፣ ደግሞም ጠንካራ ሰራተኞች ናቸው። ከእኛ ጋር እንዲኖሩ እንፈልጋለን” አሉ። ጉዳዩም በጋዜጦች ላይ ሙሉ ሽፋን አገኘ። ተዓምር ነበረ፣ ጉዳዩን የተረዱ የመንግሰት ከፍተኛ ባለስልጣናትም ነበሩና፣ ውሳኔው ተቀልብሶ በአሜሪካ መኖር እንደሚችሉ የሚገልጽ ደብዳቤ ለሮሜኒያኑ ደረሳቸው።

እኔም ወደ ሰብሊት፣ ካንሳስ ሄድኩ። ሮሜኒያውያኑ ወዳጆቼ እንደምመጣ አያውቁም ነበር። በደረስኩበት ሰዓትም ሴናተር ብራውንባክ የፖለቲካ ጥገኝነት እንዲያገኙ ስለረዷቸው በሰልክ እያመሰገኗቸው ነበር። የፕሬዚዳንት ክሊንተን ጉዳይ ይሰማ ስለነበር ሴናተሩ በጊዜው በቦታው አልተገኙም፣ ነገር ግን ኤ ቢ ሲ እና ኤን ቢ ሲ የዜና ጣቢያዎች ካሜራቸውን ይዘው በቦታው ተገኝተዋል። ሮሜኒያውያን ወዳጆቼ ሰልካቸውን እንደጨረሱ ሮጠው በመምጣት አንገቴ ላይ ተጠመጠሙብኝ፣ ካሜራዎቹም ወደ እኔ ዞረው መጡ። “አንተ ማነህ? እነዚህን ሰዎች የት ነው የምታውቃቸው?” የሚሉ ጥያቄዎችን ያዥጎደጉዱልኝ ጀመር። ሙሉውን ታሪክ ነገርኳቸው፣ እንዴት እንዳገኘኋቸውና በእግዚአብሔር ምክንያት እና ኢየሱስ በማቴዎስ 7፡12 እንደሚናገረው ለእነርሱ ጥቅም እና መልካምነት የሰራሁትን ነገርኳቸው።

በመቀጠል በቀይ፣ ነጭና ሰማያዊ ሪኛዎች ወደ አሸበረቀው አዳራሽ ሄድን። የአገር ፍቅርን የሚገልጹ የአርበኝነት መዝሙሮች ይሰሙ ነበር። ወዳጆቼ ወደ አዳራሹ ሲገቡ ሁሉም ሰው በጩኸት ተቀበላቸው እነርሱም ለቅሶአቸውን መቆጣጠር አቃታቸው። የከተማዋ ከንቲባም “ዛሬ፣ የካቲት 12 ቀን፣ ለሮሜኒያውያኑ ክብር፣ የጂካን ቤተሰብ ቀን ሆኖ ይታወሳል” ሲሉ ንግግር አደረጉ፣ ለክብራቸውም የአሜሪካንን ባንዲራ ሰጧቸው። በተጨማሪም እንደፈለጉ እስከ ህይወታቸው ፍጻሜ ድረስ ለመኖር ህጋዊ ፈቃድ የተሰጣቸው መሆኑን የሚገልጽ ደብዳቤ አበረከቱላቸው። ሁሉም ምስክርነታቸውን ካቀረቡ በኋላ ጸሎት እንዳደርግ ጠየቁኝ። እኔም “ዛሬ በሚገባ ሳናመሰግነው የቀረነው አንድ ሰው አለ፣ እርሱም ሁሉን ቻይ የሆነው እግዚአብሔር ነው። ከሰባት ዓመት ተኩል በፊት፣ በኮላሮዶ ስፕሪንግስ መናፈሻ ፓርክ ውስጥ፣ እግዚአብሔር ሆይ ፍቅርህን የማካፍለው ሰው እፈልጋለሁ ብዬ በዛች ቀን ጠይቄው ነበር። ወደ እነዚህ ሮሜኒያውያን መራኝ”። አልኩና በድጋሚ ታሪኩን አጫወትኳቸውና “እግዚአብሔር ሊረዳችሁ ይፈልጋል፣ እንኳን ወደ አሜሪካ በደህና መጣችሁ” አልኳቸው።

ሁሉም የሆነበት መንገድ ተዓምር ነበር። ትክክለኛ ሰዎችን፣ በትክክለኛ ቦታ፣ በትክክለኛው ሰዓት ተዋውቄ ነበር። ይህ ሁሉ ከመሆኑ ከአንድ ዓመት በፊት የካንሳሷ ወዳጄ ኪም፣ ሴናተር ብራውንባክ ወደ አንድሩ ዉማክ ሚኒስትሪስ እንዲመጡ እና እኔም እንድተዋወቃቸው አድርጋ ነበር። “ዶን ክሮውን ሊተዋወቁት ይገባል” ብላ ነበር ያስተዋወቀችኝ። እኔም ለምን እንደሆነ አላወቅኩምና በጊዜው ትንሽ ምቾት አልተሰማኝም ነበር። እግዚአብሔር ከዚህ ጀርባ እራሱን ለገለጠላቸውና፣ የእርሱ ፍቅር እንዲደርሳቸው ያደረገውን ያንን ቤተሰብ ለመርዳት በኢየሱስ ትዕዛዝ በኩል ይኸውም ሌሎች እንዲያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን እናንተም እንዲሁ አድርጉላቸው የሚለውን ትዕዛዝ እየፈጸመ መሆኑን አላወቅኩም ነበር። መቼም የማይረሱት ተዓምር ነበርና ዛሬ ላይ “በእግዚአብሔር የሆነ ነው” ይሏችኋል። ሮማኒያዊቷ ወይዘሮ አንካ - “እምነቴ እየዋዠቀ ነበር፣ እግዚአብሔር ግን ታማኝ ነው፣ እናም በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ እንድንቆይ አደረገ” አለች።

በአሁኑ ሰዓት በሐዘን ውስጥ ያሉ እና ፍቅር የሚያስፈልጋቸው በጣም ብዙ ሰዎች አሉ። ፍቅርን ሊያገኙ የሚችሉበት ብቸኛው መንገድም እኔና እናንተ የፍቅርን መሰረታዊ መርሆች ከእግዚአብሔር ቃል መረዳት እንችል ዘንድ ስንወስን ነው። ፍቅር ይታገሳል፣ የሌሎችን በጎነት ይፈልጋል - እንደ ኢየሱስ የእኛን ደህንነት ፈልጎ እስከ መስቀል ድረስ እንደተጓዘ። በእግዚአብሔር ፍቅር ሌሎችን ማፍቀር ምን እንደሆነ ታውቁ ዘንድ የፍቅርን መሰረታዊ ሃሳቦች በይበልጥ በምታጠኑበት ጊዜ፣ ዛሬ እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርካችሁ!

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ማቴዎስ 7፡12ን አንብቡና በራሳችሁ ቃል፣ ወርቃማው ትዕዛዝ ምን እንደሆነ ተናገሩ፣

   **ማቴዎስ 7፡12** *“እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ ሕግም ነቢያትም ይህ ነውና”።*

2. ማቴዎስ 7፡12 ፍቅርን ለማወቅ ባላቸው ፍላጎት ብዙ ሰዎች ትክክለኛ ሰውን ፍለጋ ይደክማሉ። እናንተስ ትክክለኛ ሰውን ትፈልጋላችሁ ወይስ ራሳችሁ ትክክለኛው ሰው ሆናችሁ ትገኛላችሁ?

3. 1ኛ ዮሐንስ 5፡3 ፍቅር ስሜት ነው ወይስ የምታደርጉት ድርጊት?

   **1ኛ ዮሐንስ 5፡3** *“ትዕዛዛቱን ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነውና፣ ትዕዛዛቱም ከባዶች አይደሉም”።*

4. 1ኛ ዮሐንስ 3፡18 የትዳር አጋራችሁን እወድሃለሁ/እውድሻለሁ እያላችሁ ከሌላ ሰው ጋር ዝሙት ብትፈጽሙ አጋራችሁ ቃላችሁን ወይስ ሥራችሁን ሊያምኑ ይችላሉ?

   **1ኛ ዮሐንስ 3፡18** *“ልጆቼ ሆይ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ”።*

5. ሮሜ 5፡6-8 ኢየሱስ ራሱን ለሞት አሳልፎ ለመስጠት ፍላጎት ያለው ይመስላችኋል?

   **ሮሜ 5፡6-8** *“ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና። [7] ስለ ጻድቅ የሚሞት በጭንቅ ይገኛልና፤ ስለ ቸር ሰው ግን ሊሞት እንኳ የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል። [8] ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል”።*

6. ገላትያ 5፡22 እግዚአብሔርን የሕይወታችን ማዕከል ሳናደርግ በእውነተኛ ፍቅር ሰዎችን ማፍቀር የምንችል ይመስላችኃል?

   **ገላትያ 5፡22** *“የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው”።*

7. 1ኛ ዮሐንስ 4፡8 ሌሎችን ለማፍቀር እግዚአብሔር የሚያስፈልገን እርሱ ____ ስለሆነ ነው።

   **1ኛ ዮሐንስ 4፡8** *“ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም፣ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና”።*

8. 1ኛ ቆሮንቶስ 13፡5 ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ ፍቅር ያልሆነውን ቃል ምረጡ - ክፉ፣ ራስ ወዳድ፣ ይቅር የማይል።

   **1ኛ ቆሮንቶስ 13፡5** *“የማይገባውን አያደርግም፣ የራሱንም አይፈልግም፣ አይበሳጭም፣ በደልን አይቆጥርም”።*

9. 1ኛ ቆሮንቶስ 13፡8 ከዚህ ህይወት በኋላ ወደ ዘላለም ህይወት ይዛችሁት የምትሔዱት ብቸኛው ነገር ምንድን ነው?

**1ኛ ቆሮንቶስ 13፡8** *“ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም፤ ትንቢት ቢሆን ግን ይሻራል፤ ልሳኖች ቢሆኑ ይቀራሉ፤ እውቀትም ቢሆን ይሻራል”።*

10. ምሳሌ 10፡12፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 13፡5 “ፍቅር በደልን አይቆጥርም”፣ ፍቅር ምን ያህል ኃጢአትን ይተዋል?

**ምሳሌ 10፡12** *“ጥል ክርክርን ታስነሣለች፤ ፍቅር ግን ኃጢአትን ሁሉ ትከድናለች”።*

**1ኛ ቆሮንቶስ 13፡5** *“የማይገባውን አያደርግም፣ የራሱንም አይፈልግም፣ አይበሳጭም፣ በደልን አይቆጥርም”፤*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ማቴዎስ 7፡12ን አንብቡና በራሳችሁ ቃል፣ ወርቃማው ትዕዛዝ ምን እንደሆነ ተናገሩ፣
**ለሌሎች ሰዎች እኛ እንዲያደርጉልን የምንፈልገውን ሁሉ ማድረግ፤**

2. ማቴዎስ 7፡12 ፍቅርን ለማወቅ ባላቸው ፍላጎት ብዙ ሰዎች ትክክለኛ ሰውን ፍለጋ ይደክማሉ። እናንተስ ትክክለኛ ሰውን ትፈልጋላችሁ ወይስ ራሳችሁ ትክክለኛው ሰው ሆናችሁ ትገኛላችሁ?
**ትክክለኛ ሰው ሆኖ መገኘት፣**

3. 1ኛ ዮሐንስ 5፡3 ፍቅር ስሜት ነው ወይስ የምታደርጉት ድርጊት?
**የእግዚአብሔርን መመሪያዎች (ትዕዛዞች) ተከትለን የምናደርገው ድረጊት ነው።**

4. 1ኛ ዮሐንስ 3፡18 የትዳር አጋራችሁን እወድሃለሁ/እውድሻለሁ እያላችሁ ከሌላ ሰው ጋር ዝሙት ብትፈጽሙ አጋራችሁ ቃላችሁን ወይስ ሥራችሁን ሊያምኑ ይችላሉ?
**ሥራችንን። ሥራ ከቃል የበለጠ ይናገራል፤**

5. ሮሜ 5፡6-8 ኢየሱስ ራሱን ለሞት አሳልፎ ለመስጠት ፍላጎት ያለው ይመስላችኋል?
**አይመስልም፣ ሆኖም ግን ከስሜቱ ይልቅ የእኛን ደህንነትና፣ መልካምነት ፈለገ።**

6. ገላትያ 5፡22 እግዚአብሔርን የሕይወታችን ማዕከል ሳናደርግ በእውነተኛ ፍቅር ሰዎችን ማፍቀር የምንችል ይመስላችኃል?
**አንችልም።**

7. 1ኛ ዮሐንስ 4፡8 ሌሎችን ለማፍቀር እግዚአብሔር የሚያስፈልገን እርሱ ____ ስለሆነ ነው::
**ፍቅር።**

8. 1ኛ ቆሮንቶስ 13፡5 ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ ፍቅር ያልሆነውን ቃል ምረጡ፤ ክፉ፣ ራስ ወዳድ፣ ይቅር የማይል።
**ሁሉንም አይደለም (ክፉ፣ ራስ ወዳድና ይቅር የማይል) የሚሉት ቃላት ፍቅርን አይገልጹ።ም**

9. 1ኛ ቆሮንቶስ 13፡8 ከዚህ ህይወት በኋላ ወደ ዘላለም ህይወት ይዛችሁት የምትሔዱት ብቸኛው ነገር ምንድን ነው?
**ፍቅር፣ ለዘወትር አይወድቅም።**

10. ምሳሌ 10፡12፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 13፡5 “ፍቅር በደልን አይቆጥርም”፣ ፍቅር ምን ያህል ኃጢአትን ይተዋል?
**ኃጢአትን በሙሉ።**

# ትምህርት 14

# ፋይናንስ - ክፍል 1

## በአንድሩ ዉማክ

ኢየሱስ በገንዘብ እንድትበለጽጉ ይፈልጋል። ይህ ለሁሉም ሰው ጠቃሚና አስፈላጊ ነገር ነው። ለመኖር ገንዘብ ያስፈልገናል፣ ለኑሮ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ለማሟላት፣ ለሌሎችም በረከት ትሆኑ ዘንድ ገንዘብ ያስፈልጋችኋል። እግዚአብሔር - "ከመንፈሳዊ ህይወታችሁ እንጅ፣ ገንዘብን በተመለከተ እናንተው ተጨነቁበት፣ አይመለከተኝም" ብሎ እንዲሁ አልተወንም፣ በፍጹም። ሁለንተናችሁን ይወዳል - መንፈስ፣ ነፍስና ስጋ፣ በሁሉም መስክ የሚያስፈልጋችሁን አቅርቦት አዘጋጅቶላችኋል። በእርግጥ ብዙ ሰዎች በተወሰነ ደረጃ በገንዘብ መበልጸግ አስፈላጊ ነው ብለው ቢያምኑም ሐይማኖት (Religion) ግን እጅግ መበልጸግ ተገቢ አይደለም የሚል ጥብቅ አቋም አለው።

የእግዚአብሔር ቃል፣ በብዙ ልዩ ልዩ መንገዶች፣ ስስታምነትን በመቃወም የሚያስተምር ሲሆን ገንዘብን በተመለተ ግን በረከት መሆኑን በግልጽ ይናገራል። በ3ኛ ዮሐንስ 1፡2 ሐዋርያው ዮሐንስ - *"ወዳጅ ሆይ ነፍስህ እንደሚከናወን በነገር ሁሉ እንዲከናወንልህ እፀልያለሁ"* ይላል። ይህ ጠንካራ መልዕክት ነው። ዮሐንስ "በነገር ሁሉ!" የሚለው - በፈውስ፣ በስሜት፣ በወዳጅነት እና በገንዘብ ሁሉ ማለት ነው። ጌታ ከሁሉም ነገር በላይ እንድትበለጽጉና ጤነኛ እንድትሆኑ ፍላጎቱ ነው። በመንፈስ፣ በነፍስ እና በስጋ የበለጸጋችሁ፣ ባለጠጎች እንድትሆኑም ይፈልጋል።

ብዙ የሐይማኖት ሰዎች ድሃ መሆንን ከብፅዕና ጋር በማያያዝ እግዚአብሔር ድሃ መሆናችሁን እንደሚፈልግ ሲናገሩ ሰምታችሁ ይሆናል። ደግሞም ሰው ድሃ በሆነ መጠን ይበልጥ መንፈሳዊ እንደሚሆን ይናገራሉ። ባለጠግነትን ወይም በገንዘብ መበልጸግን አይደግፉም። እኔም እራሴ ብሆን አገልጋዮች ብዙ ሊኖራቸው አይገባም፣ ክርስቲያን ማለት ምንም የሌለው ነው በሚል አስተሳሰብ ስር ነበር ያደግኩት። ነገር ግን ይህን የሚደግፍልን ምንም የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ ማቅረብ አንችልም። አብርሃም በዘመኑ እጅግ ባለጠጋ ሰው ከመሆኑ የተነሳ የእርሱ ሃብት ስጋት ላይ የጣላቸው ንጉሦች አገራቸውን ለቆ እንዲወጣ ይለምኑት ነበር። ይስሐቅ እና ያዕቆብም በተመሳሳይ እጅግ ባለጠጎች ነበሩ። ዮሴፍ የተትረፈረፈለት ባለጠጋ ሰው ነበር። ዳዊት በዘመኑ ለእግዚአብሔር ቤት መሰሪያ ከራሱ ካዝና የሰጠው ብርና ወርቅ በአሁኑ ምንዛሬ ሲሰላ ከ125 ቢሊዬን ብር በላይ የሚገመት ነበር። ልጁ ሰለሞንም በምድር ላይ ከተነሱ ነገስታት ሁሉ ይልቅ እጅግ ባለጠጋ ሰው ነበር። የእግዚአብሔርን ቃል በማስረጃነት ከተመለከታችሁ እግዚአብሔርን ያገለግሉ የነበሩ ሰዎች በገንዘብ ባለጠጋና እጅግ የበለጸጉ ነበሩ።

ምንም የሌላቸውና በችግር ውስጥ የኖሩ አገልጋዮችም እንደነበሩ ምሳሌ ማቅረብ እንችላለን። ጳውሎስ በፊሊጵስዩስ 4፡12-13 ሁሉን በክርስቶስ እንደሚችል እና በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ያለኝ ይበቃኛል ማለትን መማሩን ይናገራል። በተጨማሪም ማግኘትና ማጣትን አውቃለሁ ይላል። የእግዚአብሔር አገልጋዮች በማጣትና በችግር በድህነት ውስጥ ያለፉበት ጊዜ መኖሩ ግልጽ ነው። ነገር ግን በየትኛውም ቦታ የበለጠ ድሃ ስትሆን የበለጠ መንፈሳዊ ሰው ትሆናለህ የሚል ቃል በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ አናገኝም። ይህ ትክክል አይደለም፣ ወጣ ብላችሁ በማስተዋል ይህ ትክክል እንዳልሆነ ማረጋገጥ ትችላላችሁ። ደግሞም ስስታምነት በእርግጥ መልካም አይደለም የሚለውም እውነት ነው። 1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡10 *"ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና፣ አንዳንዶች ይህን ሲመኙ፣ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ስቃይ ራሳቸውን ወጉ"* ይላል። ከዚህ በመነሳት አንዳንዶች ገንዘብ የክፋት ሁሉ ሥር ነው ይላሉ፤ ነገር ግን "ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነው" እንደሚል ማስተዋል ትችላላችሁ። ገንዘብ የሚወዱ፣ ግን ምንም ሳንቲም የሌላቸው ሰዎች አሉ። ደግሞም በጣም ብዙ ሃብት ያላቸው እንዲሁ የሚጠቀሙበት እንጂ የማያፈቅሩት ሰዎችም አሉ።

ዘዳግም 8፡18 በገንዘብ የመበልጸግን ትክክለኛ አላማ ያሳያል። እግዚአብሔር ማርና ወተት ወደ

ሞታፈሰሰው፣ በበረከት ወደ ተሞላችው ምድር የሚገባውን የእስራኤል ሕዝብ እያናገረ ነበር፣ በህይወታቸው አይተው የማያውቁትን ሐብት እና ብልጽግና ነውና የሚያገኙት እግዚአብሔር እንዲህ አላቸው - *"ነገር ግን ዛሬ እንደሆነ ለአባቶችህ የማለውን ቃል ኪዳን ያጸና ዘንድ ሀብት ለማከማቸት እርሱ ጉልበት ሰጥቶሃልና አምላክህ እግዚአብሔርን አስብ"።* በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መሰረት የመበልጸጋችሁ ዋና ዓላማ ለራሳችሁ የግል ጥቅም እና ፍላጎት እጅግ የተትረፈረፈ ነገር እንዲኖራችሁ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ኪዳን በምድር ላይ መመስረት ትችሉ ዘንድ ነው። በሌላ አነጋገር እግዚአብሔር ይባርካችኋል፣ እናንተም በተራችሁ ለሌሎች በረከት ትሆናላችሁ። በዘፍጥረት 12፡2 እግዚአብሔር አብርሃምን እንዲህ አለው - *"ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፣ እባርክሃለሁ፣ ስምህንም አከብረዋለሁ፣ ለበረከትም ሁን"*። ለሌላ ሰው በረከት ከመሆናችሁ በፊት እናንተ እራሳችሁ መባረክ ይኖርባችኃል።

አንዳንድ እንዲኖሯችሁ እና እግዚአብሔር እንዲያሟላላችሁ የምትፈልጓቸው ነገሮች ይኖራሉ፣ ነገር ግን ከእራሳችሁ፣ ከግል ጥቅማችሁ ያለፈ ሊሆን ይገባል። እግዚአብሔር ባለጠጋ ሊያደርጋችሁ ይፈልጋል። ይህም ገንዘቡን በእናንተ በኩል ለሌሎች ሰዎች ለማድረስ ሲሆን እናንተም በረከት ሆናችሁለት ማለት ነው። 2ኛ ቆሮንቶስ 9፡8 *"እግዚአብሔር ሁልጊዜ በነገር ሁሉ ብቃትን ሁሉ አግኝታችሁ ለበጎ ስራ ሁሉ ትበዙ ዘንድ፣ ጸጋን ሁሉ ሊያበዛላችሁ ይችላል"* ይላል። ይህ ቃል እግዚአብሔር እናንተን መባረክ ለምን እንደሚፈልግ ይናራል - "ለመልካም ሥራ ሁሉ ለማዋል" ነው። ከላይ ያየነው ይህ ቃል በጥቅሉ የብልጽግና ትርጉም ወይም ፍቺ ነው ማለት እንችላለን። ስለዚህ ብልጽግና ምንድን ነው? ቆንጆ ቤት፣ ምርጥ መኪና፣ ጥሩ ልብስ መልበስ እና ማዕድ በገበታችሁ መሙላቱ ነው? በዚህ ቃል ፍች መሰረት ብልጽግና ማለት የሚያስፈልጋችሁ በቂ ነገር ኖሯችሁ ለበጎ ስራ ሁሉ ትበዙ ዘንድ ነው። በመሆኑም እግዚአብሔር በልቤ አስቀምጦታል ብላችሁ እርግጠኛ ለሆናችሁበት ጉዳይ የምትሰጡት ነገር ካጣችሁ፣ ለሌላ ሰው በረከት መሆን ፈልጋችሁ ነገር ግን ካልቻላችሁ፣ እንግዲያውስ መጽሐፍ ቅዱስ በሚናገረው መልኩ በገንዘብ በኩል አልበለጸጋችሁም ማለት ነው። እግዚአብሔር በሚያስፈልጋችሁ ሁሉ እንዲሟላላችሁ እና ለበጎ ስራም ትበዙ ዘንድ እንደሚባርካችሁ ይናገራል።

እውነተኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ብልጽግና የራስን ፍላጎት ማሟላት ሳይሆን ለሌሎች ሰዎች በረከት መሆን ነው። ለራሳቸው ብቻ የሚያስቡ ሰዎች ራስ ወዳዶች ናቸው። አንድ ሰው "እግዚአብሔር እንደሚጨምርልኝ አምናለሁ" ብሎ ቢናገር ሌሎች ሰዎች ስግብግብ ወይም ራስ ወዳድ ሊሉት ይችላሉ፤ ነገር ግን ሁኔታው የሚወሰነው ከአላማው በመነሳት ነው። እግዚአብሔር እንዲጨምርላችሁ የፈለጋችሁት ትልቅ ቤት ወይም የተሻለ መኪና ለማግኘት ከሆነ ይህ ትክክለኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከት አይደለም። ነገር ግን እግዚአብሔር እንደሚጨምርላችሁ ያመናችሁት ከራሳችሁ ባለፈ ለሌች ሰዎች በረከት ለመሆን ከሆነ እግዚአብሔር እንዲኖራችሁ የሚፈልገው ዓይነት በትክክለኛ አላማ ላይ የተመሰረተ አመለካከት ነው። እግዚአብሔር እንድትበለጽጉ ይፈልጋል። ተጨማሪ ነገር እንዲሰጣችሁ የምትፈልጉ ከሆነ ለትክክለኛው አላማ እርሱም ይጨምራላችኃል። የእርሱ ፈቃድ የእናንተ ብልጽግና ነው።

ማቴዎስ 6 ስለሚያስፈልጉን ነገሮች በዝርዝር ይናገርና ነገር ግን በቅድሚያ የእግዚአብሔርን መንግስት ጽድቁንም ከፈለግን ሌላው ሁሉ እንደሚጨመርልን ይመክራል። እግዚአብሔርን በነገር ሁሉ ማስቀደም ከጀመራችሁ እርሱ ሌሎች የሚያስፈልጓችሁን ነገሮች ሁሉ እንዲሰጣችሁ ያደርጋል፣ የሚያስፈልጋችሁን ታገኛላችሁ ለሌሎችም በረከት ትሆናላችሁ። እግዚአብሔር በእርግጥ እንድትበለጽጉ ይፈልጋል፤ ነገር ግን ይህ በእናንተ አላማ እና እንቅስቃሴ ላይ የተመሰረተ ነው።

ዛሬ በዚህ መልዕክት ውስጣችሁ እንዲነሳሳ ደግሞም እግዚአብሔርን በዚህ ጉዳይ እንድታምኑትና የእርሱን ምርጥ ነገር ሁሉ ተቀብላችሁ ትበለጽጉ ዘንድ እጸልያለሁ።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. 2ኛ ቆሮንቶስ 8፡7-8 ለሌሎች የሚያስፈልጋቸውን ስትሰጡ የምን መገለጫ ነው?

   **2ኛ ቆሮንቶስ 8፡7-8** *"ነገር ግን በነገር ሁሉ፥ በእምነትና በቃል በእውቀትም በትጋትም ሁሉ ለእኛም በፍቅራችሁ እንደ ተረፋችሁ፥ በዚህ ቸር ሥራ ደግሞ ትረፉ። [8] ትእዛዝ እንደምሰጥ አልልም፥ ነገር ግን በሌሎች ትጋት በኩል የፍቅራችሁን እውነተኛነት ደግሞ ልመረምር እላለሁ፤"*

2. 2ኛ ቆሮንቶስ 8፡13-14 ሁላችንም አንድ ላይ ሆነን ስንሰጥ እግዚአብሔር ምን እንዲኖር ይፈልጋል?

   **2ኛቆሮንቶስ8፡13-14** *"ለሌሎችዕረፍትለእናንተምመከራእንዲሆንአይደለም፥ትክክልእንዲሆንነውእንጂ፤ [14] የእነርሱ ትርፍ ደግሞ የእናንተን ጉድለት እንዲሞላ በአሁኑ ጊዜ የእናንተ ትርፍ የእነርሱን ጉድለት ይሙላ፤ በትክክል እንዲሆን፥ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ"።*

3. 2ኛ ቆሮንቶስ 8፡13-14 የሁሉም ፍላጎት እንዴት ሊሟላ ይችላል?

4. ኤፌሶን 4፡28 ሌባ የነበረ ሰው ከአሁን በኋላ አይሰረቅ፣ ነገር ግን ሰርተው ይብሉ ይላል። ሌላስ ምን ያድርጉ ይላል?

   **ኤፌሶን 4፡28** *"የሰረቀ ከእንግዲህ ወዲህ አይሰረቅ፥ ነገር ግን በዚያ ፈንታ ለጎደለው የሚያካፍለው እንዲኖርለት በገዛ እጆቹ መልካምን እየሠራ ይድከም"።*

5. ዘፍጥረት 13፡2 እና 12፡2 ሐብትን በተመለከተ እግዚአብሔር በአብርሃም ላይ እምነት ነበረው፤ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ አብርሃም ለራሱ ሳይሆን ለሌሎች _____ ስለሆነ ነው።

   **ዘፍጥረት 13፡2** *"አብራምም በከብት በብርና በወርቅ እጅግ በለጠገ"።*

   **ዘፍጥረት 12፡2** *"ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፥ እባርክሃለሁ፥ ስምህንም አከብረዋለሁ፤ ለበረከትም ሁን"፤*

6. 1ኛ ጢሞቲዎስ 6፡17-18 ባለጠጋዎች በገንዘባቸው ሊያደርጉ የሚገባቸው ሶስት አበይት ነገሮች ምንድን ናቸው?

   **1ኛ ጢሞቲዎስ 6፡17-18** *"በአሁኑ ዘመን ባለ ጠጎች የሆኑት የትዕቢትን ነገር እንዳያስቡ፥ ደስም እንዲለን ሁሉን አትረፎ በሚሰጠን በሕያው እግዚአብሔር እንጂ በሚያልፍ ባለ ጠግነት ተስፋ እንዳያደርጉ እዘዛቸው። [18-19] እውነተኛውን ሕይወት ይይዙ ዘንድ፥ ለሚመጣው ዘመን ለራሳቸው መልካም መሠረት የሚሆንላቸውን መዝገብ እየሰበሰቡ፥ መልካምን እንዲያደርጉ በበጎም ሥራ ባለ ጠጎች እንዲሆኑ፥ ሊረዱና ሊያካፍሉም የተዘጋጁ እንዲሆኑ ምከራቸው"።*

7. እግዚአብሔር በገንዘብ ጉዳይ ሊያምናችሁ ይችላል?

# ጠቋሚ መልሶች

1. 2ኛ ቆሮንቶስ 8፡7-8 ለሌሎች የሚያስፈልጋቸውን ስትሰጡ የምን መገለጫ ነው?
   **ለእነርሱ ያላችሁን ፍቅር መግለጫ ነው፣**

2. 2ኛ ቆሮንቶስ 8፡13-14 ሁላችንም አንድ ላይ ሆነን ስንሰጥ እግዚአብሔር ምን እንዲኖር ይፈልጋል?
   **ትክክል እንዲሆን፥ ሁሉም የሚችለውን እንዲሰጥ፣**

3. 2ኛ ቆሮንቶስ 8፡13-14 የሁሉም ፍላጎት እንዴት ሊሟላ ይችላል?
   **የምትችሉትን ያህል በምትችሉበት ጊዜ በመስጠት፣**

4. ኤፌሶን 4፡28 ሌባ የነበረ ሰው ከአሁን በኋላ አይሰረቅ፣ ነገር ግን ሰርተው ይብሉ ይላል። ሌላስ ምን ያድርጉ ይላል?
   **እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው፣ ለድሆች ይስጡ፣**

5. ዘፍጥረት 13፡2 እና 12፡2 ሐብትን በተመለከተ እግዚአብሔር በአብርሃም ላይ እምነት ነበረው፤ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ አብርሃም ለራሱ ሳይሆን ለሌሎች _____ ስለሆነ ነው።
   **በረከት።**

6. 1ኛ ጢሞቲዎስ 6፡17-18 ባለጠጋዎች በገንዘባቸው ሊያደርጉ የሚገባቸው ሶስት አበይት ነገሮች ምንድን ናቸው?
   **በጎ ስራ እንዲሰሩ፣ ለድሆች በልግስና እንዲሰጡ፣ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሁሉ ለሌሎች እንዲያካፍሉ፣**

7. እግዚአብሔር በገንዘብ ጉዳይ ሊያምናችሁ ይችላል?

# ትምህርት 15

# ፋይናንስ - ክፍል 2

## በአንድሩ ዉማክ

ባለፈው ትምህርታችን ትበለጽጉ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ተነጋግረን ነበር። ይህ እውን የሚሆንባቸው ቁልፍ ነገሮች መኖራቸው እውን ነው። ሉቃስ 6፡38 *“ስጡ ይሰጣችሁማል፤ በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋልና፥ የተጨቈነና የተነቀነቀ የተትረፈረፈም መልካም መስፈሪያ በእቅፋችሁ ይሰጣችኋል”* ይላል። በዚህ ዙሪያ ብዙ መርሆዎች ቢኖሩም ነገር ግን ስለ ብልጽግና ስናወራ ስለ መስጠት ሳናወራ ማለፍ አንችልም።

በገንዘብ መበልጸግን በተመለከተ ለሰዎች በምትናገሩበት ጊዜ ብዙ ሰዎች “እግዚአብሔር በገንዘብ እንድበለጽግ ፈቃዱ ከሆነ፣ እንግዲያውስ መስጠት የለብኝም” ይላሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዲት መበለት ሴት የነበሯትን ሁለት ሳንቲሞች ምንም ሳታስቀር እንደሰጠች ኢየሱስ የተናገረበትን ክፍል እናገኛለን። አንዳንድ ባለጠጋ ሰዎች መጠኑ እጅግ የበዛ ገንዘብ መስጠታቸውን የተመለከተ ቢሆንም ኢየሱስ ሁሉን ደቀ መዛሙርቱን ወደ እርሱ ጠርቶ ይህች ሴት ከሁሉም የበለጠ ገንዘብ ሰጠች አላቸው። ይህን ያለበት ምክንያት ባለጠጋዎቹ የሰጡት ከትርፋቸው ሲሆን እርሷ ግን ከጉድለቷ ወይም ከድህነቷ የሰጠች በመሆኑ ነው። እግዚአብሔር ካላችሁ ላይ ምን ያህል ክፋይ (percentage) እንደምትሰጡ እንጂ በምትሰጡት የገንዘብ ብዛት ወይም የገንዘብ ዓይነት ልክ አይመዝናችሁም። አንድ ሰው “እኔ የምሰጠው ምንም ነገር የለኝም” ብሎ ቢናገር እውነት እየተናገረ አይደለም። ሌላው ቢቀር ካላችሁ ልብስ እንኳን አንዱን አንስታችሁ መስጠት ትችላላችሁ። ሁሉም ሰው አንድ የሚሰጠው ነገር ይኖረዋልና ስለዚህ ምንም የምሰጠው ነገር የለኝም ብላችሁ የምታቀርቡት መከራከርያ ቢኖር ልታስወግዱት ይገባል። እንደ እውነቱ ከሆነ ጥቂት ባላችሁ ጊዜ የሰጣችሁት ነገር ምናልባት ከሌላው ጊዜ ሁሉ ይልቅ የበዛ ምጣኔ (percentage) ሊኖረው ይችላል። አንድ ሰው አስር ብር ቢኖረውና ካለው ላይ ግማሹን ወይም አምስት ብር ቢሰጥ፣ በቢሊዬኖች የሚቆጠር ገንዘብ ኖሯቸው አንድ ሚሊዬን ብር ከሚሰጡ ሰዎች ይልቅ ብዙ ገንዘብ ሰጥቷል ማለት ነው። እግዚአብሔር ይህ እንዲሆን ያደረገበት ምክንያት ሁሉም ሰው መስጠት እንዲችል ነው።

እግዚአብሔር ስጡ የሚለን ለምንድን ነው? ለዚህ ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩም በዋነኛነት ግን እግዚአብሔር በሁሉም የሕይወታችሁ መሰክ በእርሱ እንድትታመኑ ስለሚፈልግ ነው። እግዚአብሔር ባይኖር እና ቃሉም እውነት ባይሆን ኖሮ *“ስጡ ይሰጣችኋል”* ብሎ ሲናገር በእጃችሁ ካለው ላይ ከፊሉን ወስዳችሁ መስጠት ትልቅ ሞኝነት በሆነ ነበር። እግዚአብሔር እንደሚባርካችሁ ቃል ባይገባላችሁ ኖሮ፣ በመስጠታችሁ የሚያስፈልጋችሁን ለሟሟላት ወደ ምትደርሱበት ብቃት ከመጓዝ ይልቅ በተቃራኒ መንገድ ወደ ጉድለት እየተጓዛችሁ በሆን ነበር። እግዚአብሔር በተናገረው መልኩ መስጠት ትችሉ ዘንድ በእርግጥ እምነት ያስፈልጋችኋል፣ እርሱም ይህን ታደርጉ ዘንድ ያዘዘበት ምክንያት ለዚህ ነው።

የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 16 ስለ አንድ ጌታውን ያታለለ መጋቢ ታሪክ የሚነግረን ሲሆን በታሪኩ መጨረሻም እንዲህ ይላል፤ ከሁሉም ታናሽ፣ ዝቅተኛ በሆነው ነገር ካልታመናችሁ (ይህም ገንዘብ ነው) እውነተኛውን ገንዘብ ማን አደራ ይሰጣችኋል? እግዚአብሔርን ታናሽ በሆኑት ነገሮች ይኸውም ገንዘብን በተመለከተ ልታምኑት ካልቻላችሁ ውድ እና አስፈላጊ ወደ ሆኑት፣ መንፈሳዊ ዋጋ ያላቸው ነገሮች እንዴት መድረስ ትችላላችሁ? የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ባሉት ክፍሎች ለገንዘብ ዝቅተኛውን የአገልግሎት ደረጃ ይሰጠዋል። እግዚአብሔርን በገንዘባችሁ ማመን ካልቻላችሁ በዘላለም ዕጣ ፈንታችሁ እንዴት ልታምኑት ትችላላችሁ? ኢየሱስ ኃጢአታችሁን ይቅር እንዳላችሁና ለዘላላም በሰማይ እንደምትኖሩ እንዴት በእርግጠኛነት ማመን ትችላላችሁ? በንጽጽር ካየነው ጌታን አምነን ተስፋ ያደረግናቸው መንፈሳዊ ነገሮች ከገንዘብ ይልቅ እጅግ የከበሩ ናቸው። ገንዘብ ከሁሉም ያነሰ ነገር ነው፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ላይ እምነታችን ለመጣል መሰረታዊ ጉዳይ ነው። ምሳሌ 11፡24 አንዳንድ ሰዎች ከሚያስፈልገው በላይ ገንዘባቸውን የሚሰጡ ወይም የሚበትኑ እንዳሉ ሲናገር ነገር ግን ይበለጽጋሉ ይላል፤

ሌሎች ደግሞ ካላቸው ላይ ባለመስጠት ንፉግ እንደሆኑ ሆኖም ግን ድህነትን እንዳመጣባቸው ይናገራል።

በቅድሚያ የእግዚአብሔርን መንግስት ጽድቁንም ከፈለጋችሁ፣ እርሱ ሌሎችን ነገሮች ይጨምርላችኋል። እግዚአብሔር በፋይናንስ ጉዳይ እንዲረዳኝ እፈልጋለሁ ካላችሁና ለእርዳታውም የምትጸልዩ ከሆነ ነገር ግን በቅድሚያ የእግዚአብሔርን መንግስት የማትፈልጉ ከሆነ፣ በገንዘባችሁ እርሱን በማመን ለመኳዝ ካልወሰናችሁና መስጠት ካልጀመራችሁ - በእርግጥ እርሱን አልተማመናችሁም።

# የደቀመዝሙር ጥያቄዎች

1. ዮሐንስ 3፡16 እንብቡና እግዚአብሔር ስጦታ እንዲሰጥ ያነሳሳው ምንድን ነው?

   **ዮሐንስ 3፡16** *"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና"።*

2. 1ኛ ቆሮንቶስ 13፡3 ስጦታ ለመስጠት የምንነሳሳበት ምክንያት ምን መሆን አለበት?

   **1ኛ ቆሮንቶስ 13፡3** *"ድሆችንም ልመግብ ያለኝን ሁሉ ባካፍል፥ ሥጋዬንም ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም"።*

3. ያዕቆብ 2፡15-16 የዚህን ቃል ትርጉም አብራሩ፤

   **ያዕቆብ 2፡15-16** *"ወንድም ወይም እኅት ራቁታቸውን ቢሆኑ የዕለት ምግብንም ቢያጡ፥ [16] ከእናንተ አንዱም። በደኅና ሂዱ፥ እሳት ሙቁ፥ ጥገቡም ቢላቸው ለሰውነት ግን የሚያስፈልጉትን ባትሰጡአቸው ምን ይጠቅማቸዋል?"*

4. ሉቃስ 6፡38 ይህ ቃል ምን ይነግራችኋል?

   **ሉቃስ 6፡38** *"ስጡ ይሰጣችሁማል፤ በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋልና፥ የተጨቈነና የተነቀነቀ የተትረፈረፈም መልካም መስፈሪያ በእቅፋችሁ ይሰጣችኋል"።*

5. ኤፌሶን 1፡7 እግዚአብሔር ከባለጠግነቱ ነው ወይስ እንደ ባለጠግነቱ መጠን ስጦታ የሰጠን? ልዩነቱን አብራሩ፤

   **ኤፌሶን 1፡7** *"በውድ ልጁም፥ እንደ ጸጋው ባለ ጠግነት መጠን፥ በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ስርየት"።*

6. ምሳሌ 19፡17 ለድሃ ስትሰጡ ምን እያደረጋችሁ ነው? እግዚአብሔርስ መልሶ ይከፍላችኋል?

   **ምሳሌ 19፡17** *"ለድሀ ቸርነትን የሚያደርግ ለእግዚአብሔር ያበድራል፥ በጎነቱንም መልሶ ይከፍለዋል"።*

7. መዝሙር 41፡1-3 እግዚአብሔር ለድሆች ለሚሰጡ ሰዎች የሚያደርግላቸውን አምስት ነገሮች ዘርዝሩ፤

   **መዝሙር 41፡1-3** *"ለችግረኛና ለምስኪን የሚያስብ ምስጉን ነው፤ እግዚአብሔር በክፉ ቀን ያድነዋል። [2] እግዚአብሔር ይጠብቀዋል፥ ሕያውም ያደርገዋል፥ በምድር ላይም ያስመሰግነዋል፥ በጠላቶቹም እጅ አያሳልፈውም። [3] እግዚአብሔር በደዌው አልጋ ሳለ ይረዳዋል፤ መኝታውን ሁሉ በበሽታው ጊዜ ያነጥፍለታል።*

# የደቀመዝሙር ጥያቄዎች

1. የሐንስ 3፡16 እንብቡና እግዚአብሔር ስጦታ እንዲሰጥ ያነሳሳው ምንድን ነው?
   **ፍቅሩ።**

2. 1ኛ ቆሮንቶስ 13፡3 ስጦታ ለመስጠት የምንነሳሳበት ምክንያት ምን መሆን አለበት?
   **ፍቅር፣ ይህም ከስሜታዊነት ነጻ ሆነን የሌሎችን ደህንነትና ብልጽግና መፈለግ (ማቴ 7፡12)።**

3. ያዕቆብ 2፡15-16 የዚህን ቃል ትርጉም አብራሩ፤
   **የፍቅር 95% የሚሆነው በቃላት የሚገለጽ አይደለም። በምንናገረው ሳይሆን በምንፈጽመው ድርጊት ነው።**

4. ሉቃስ 6፡38 ይህ ቃል ምን ይነግራችኋል?
   **ለመስጠት በምትጠቀሙበት መስፈሪያ ልክ (ትልቅ ወይም ትንሽ)፣ ለእናንተም ተመልሶ በዚያው መስፈሪያ ይሰጣችኋል።**

5. ኤፌሶን 1፡7 እግዚአብሔር ከባለጠግነቱ ነው ወይስ እንደ ባለጠግነቱ መጠን ስጦታ የሰጠን? ልዩነቱን አብራሩ፤
   **እንደ ባለጠግነቱ መጠን ነው። እኛን ለመቤዠት ያለውን ሁሉ ሰጠ፣ አንድያ ልጁን።**

6. ምሳሌ 19፡17 ለድሃ ስትሰጡ ምን እያደረጋችሁ ነው?
   **ለጌታ እያበደርን።**
   እግዚአብሔርስ መልሶ ይከፍላችኋል?
   **አዎ።**

7. መዝሙር 41፡1-3 እግዚአብሔር ለድሆች ለሚሰጡ ሰዎች የሚያደርግላቸውን አምስት ነገሮች ዘርዝሩ፤
   **እግዚአብሔር በክፉ ቀን ያድናቸዋል፣ ይጠብቃቸዋል፥ ባለጠጋ ያደርጋቸዋል፥ በጠላቶቻቸው እጅ አያሳልፋቸው፣ ያድናቸዋል ይህም ወደ ጤንነት ያመጣቸዋል።**

# ትምህርት 16

# ጸሎታችሁ ያልተመለሰ ሲመስል ምን ማድረግ እንዳለባችሁ

## በአንድሩ ዉማክ

ጸሎታችሁ ያልተመለሰ ሲመስል ማድረግ የሚገባችሁን በተመለከተ ላካፍላችሁ እወዳለሁ፣ እዚህ ላይ አጽንዖት ልሰጠው የምፈልገው ጸሎታችሁ ያልተመለሰ "ሲመስል" የሚለውን እውነት ነው። እግዚአብሔር ሁልጊዜ፣ አዎ! ሁልጊዜ፣ እንደ እግዚአብሔር ቃል በእምነት የሚጸለይን ጸሎት ይመልሳል። 1ኛ ዮሐንስ 5፡14-15 *"በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፣ እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል። የምንለምነውንም ሁሉ እንዲሰማልን ብናውቅ ከእርሱ የለመነውን ልመና እንደ ተቀበልን እናውቃለን"* ይላል። ይህ ትልቅ መተማመኛ ነው። እግዚአብሔር ሁሌም ጸሎትን ይመልሳል፣ ነገር ግን ሁሌም ቢሆን መልስ ያገኘን አይመስለንም። ማቴዎስ 7፡7-8 እንዲህ ይላል *"ለምኑ ይሰጣችሁማል፣ ፈልጉ፣ ታገኙማላችሁ፣ መዝጊያን አንኳኩ፣ ይከፈትላችሁማል። የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና፣ የሚፈልገውም ያገኛል፣ መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል"*። እነዚህ ቃላት እግዚአብሔር ጸሎትን እንደሚመልስ ይናገራሉ። ነገር ግን እያንዳንዳችን በአንድ ወቅት በሕይወታችን ትክክለኛ ለሆነ ነገር፣ ለራሳችን የግል ጉዳይ ላልሆነ፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ ለሆነ መልካም ነገር በእምነት እንደ እግዚአብሔር ቃል ጸልዬን ነገር ግን ምንም ምላሽ ያላገኘንበት ጊዜ መኖሩን እናስታውስ ይሆናል።

የእግዚአብሔር ቃል መጠየቅ እንዳለብን፣ ከጠየቅን ደግሞ እንደሚሰጠን ይናገራል። የእኛ ተሞክሮ ደግሞ ጠይቀን እንዳልተሰጠን ይነግረናል። ከሁለቱ የትኛው ነው ትክክል? በማለት ልንጠይቅ እንችላለን። የዚህ ጥያቄ መልስ ሊያስገርማችሁ ይችላል፣ ነገር ግን በእርግጥ ምናልባት ሁለቱም ትክክል ናቸው። ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔር ቃል እርሱ እንደሚመልስ ይናገራል፣ እኔ ግን ተመልሶልኛ አላየሁም ብለው ያስባሉ። ዮሐንስ 4፡24 *"እግዚአብሔር መንፈስ ነው፣ የሚሰግዱለትም በመንፈስ እና በእውነት ሊሰግዱለት ያሰፈልጋቸዋል"* ይላል። እግዚአብሔር በመንፈሳዊው ክልል ውስጥ ጸሎታችን ለመመለስ ይሰራል፣ ነገር ግን ይህ እውን ይሆን ዘንድ በእኛ በኩል እምነት ያስፈልጋል። እምነት በመንፈሳዊው ዓለም ውስጥ ያሉ ነገሮችን እኛ ወዳለንበት ወደ ሚታዬው ዓለም በማንቀሳቀስ ማምጣት የሚችል መሳሪያ ነው። ዕብራውያን 11፡1 የሚናገረው ይህንን ነው - *"እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፣ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው"*። እምነት የሌሉ ነገሮችን የሚያስረዳ አይደለም፣ የሌሉ ነገሮች አይደሉም። በእርግጥ ያሉ ነገሮች ናቸው፣ ነገር ግን በዚህ በሚታዬው (physical) ዓለም ውስጥ ሳይሆን በማይታየው መንፈሳዊው ዓለም ውስጥ ያሉ ናቸው። እንግዲህ እምነት ወደ መንፈሳዊው ዓለም በመድረስ እነዚህን ነገሮች ወደ እኛ ወደ ሚታዬው ዓለም እንዲመጡ ያደርጋል ማለት ነው።

ይህ እንደ ሬዲዮ ሞገድ ነው። የሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያዎች ስርጭቶቻቸውን ቀኑን ሙሉ ያለማቋረጥ ይለቃሉ። እናንተ የተቀመጣችሁበት ክፍል ውስጥ ሞገዶቹን በአይናችሁ ባታዩም ድምጽ በጆሮአችሁ ባትሰሙም ነገር ግን ሞገዶቹ የሉም ማለት አይደለም። የምትፈልጉትን ድምጽ ለመስማት ሬዲዮአችሁን መክፈትና የምትፈልጉትን የአጭር ሞገድ ወይም የኤፍ ኤም ጣቢያ መፈለግ ይኖርባችኋል። ሬዲዮው ወይም ቴሌቪዥኑ ከማታዩት እና የት እንደሆነ ከማታውቁት ክልል ሰቦ ወደ እናንተ በማምጣት ሞገዶቹን በጆሮአችሁ እንድትሰሙ ያደርጋል። እግዚአብሔር ጸሎታችንን በተመሳሳይ መልኩ ይመልሳል፡ እግዚአብሔር የጸሎታችሁ መልስ የሆኑትን ነገሮች በመንፈሳዊው ዓለም ይሰጣል፣ እናንተም እምነታችሁን ተጠቅማችሁ ወደ ሚታየው ወደ ራሳችሁ ዓለም ማምጣት ይኖርባችኋል። ይህ የሚታየው (physical) ዓለም እና መንፈሳዊው ዓለም፣ ጎን ለጎን ይሰራሉ። እግዚአብሔር ለጸሎታችሁ መልስ ይሰጣል፣ ነገር ግን በማይታየው መንፈሳዊው ዓለም እና በሚታዬው በምንኖርበት ዓለም መካከል ድልድይ ሆኖ ማገናኘት ይችል ዘንድ እምነታችሁን እስካልተጠቀማችሁ ድረስ የጸሎታችሁን መልስ ተገልጦ የማዬት እድል ላይኖራችሁ ይችላል።

ለምሳሌ፣ የእግዚአብሔር ሰው ዳንኤል፣ መገለጥ ይሰጠው ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ይጸልይ ነበር። ጊዜ ለመቆጠብ ታሪኩን ባጭሩ ለማቅረብ እሞክራለሁ። እግዚአብሔር ለዳንኤል የጸሎት መልስ ተገልጦ እንዲሰጠው መልአኩን ገብርኤልን ላከ። ዳንኤል 9፡22-23 *"አስተማረኝም፥ ተናገረኝም እንዲህም አለ። ዳንኤል ሆይ፥ ጥበብንና ማስተዋልን እሰጥህ ዘንድ አሁን መጥቻለሁ። [23] አንተ እጅግ የተወደድህ ነህና በልመናህ መጀመሪያ ላይ ትእዛዝ ወጥቶአል፥ እኔም እነግርህ ዘንድ መጥቻለሁ፤ አሁንም ነገሩን መርምር፥ ራእዩንም አስተውል"*። ነገሩ እንዲህ ነው፡- መልአኩ ገብርኤል እንደተናገረው ገና በዳንኤል ጸሎት መጀመሪያ ላይ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለጸሎቱ መልስ እንዲሰጠው ትዕዛዝ ወጥቷል። መልሱን እርሱ ዘንድ ለማድረስ ምን ያህል ጊዜ እንደወሰደ ካነበባችሁ ሦሥት ደቂቃ ያህል እንደሚሆን መገንዘብ ትችላላችሁ፣ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ እና መልሱ እስከተገለጠበት ጊዜ የወሰደው ጊዜ ሦሥት ደቂቃ ብቻ ነበር።

ብዙ ዓይነት መላምቶችን እንገምታለንና እግዚአብሔር በእውነት ሁሉን ቻይ ከሆነ የእርሱ ፈቃድ የሆነ ነገር በአንድ አፍታ ሊሆን ይችል ነበር ብለን እናስባለን፤ ይህ ትክክል አይደለም። በዚህ ምሳሌ ላይ እግዚአብሔር ትዕዛዙን ሰጠ፣ ለገብርኤል ደግሞ ያንን ርቀት ለመሸፈን ሦሥት ደቂቃ ያህል ጊዜ ወሰደበታል። ይህ የሆነበትን ምክንያት እኔ አላውቅም፣ ምናልባት ምክንያቱን ማወቅ የሚጨምርልንም ነገር ላይኖር ይችላል። እኔ አሁን ለማስጨበጥ እየሞከርኩት ያለሁት ነጥብ እግዚአብሔር ትዕዛዙን በሰጠበትና መልሱ እስኪገለጥ ድረስ የተወሰነ የጊዜ ክፍተት መኖሩንና ይህም ሦሥት ደቂቃ ያህል መሆኑን ነው። እንግዲህ ጸሎትን ለመመለስ የሚፈጀው ረጅሙ ጊዜ ይህ እንደሆነ እንድናምን ቢደረግ ኖሮ፣ ብዙዎቻችን ምናልባት በዚሁ እንቆም ነበር፣ ነገር ግን ሁል ጊዜ እንደዚህ አይደለም።

በትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 10 ይኼው ዳንኤል እራሱ ሌላ ጸሎት ጸለዪ፣ በዚህ ጊዜ ግን የጸሎቱ መልስ ወደ እርሱ እስኪመጣ ሶስት ሳምንት ወሰደበት ነበር። ብዙ ሰዎች ይህንን ሲያነቡ "እግዚአብሔር የዳንኤልን ጸሎት ለመመለስ አንድ ጊዜ ሶስት ደቂቃ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሶስት ሳምንት የወሰደበት ምክንያት ምንድን ነው?" ማለታቸው አይቀርም። ዳንኤል 10፡11-12 እንዲህ ይላል *"እርሱም። እጅግ የተወደድህ ሰው ዳንኤል ሆይ፥ እኔ ዛሬ ወደ አንተ ተልኬአለሁናየምነግርህንቃልአስተውል፥ቀጥብለህምቁምአለኝ።ይህንምቃልባለኝጊዜእየተንቀጠቀጥሁቆምሁ። [12] ፤ እርሱም እንዲህ አለኝ። ዳንኤል ሆይ፥ አትፍራ፤ ልብህ ያስተውል ዘንድ፥ ሰውነትህም በአምላክህ ፊት ይዋረድ ዘንድ ካደረግህበት ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ቃልህ ተሰምቶአል፤ እኔም ስለ ቃልህ መጥቻለሁ"* ይላል። ይህም እግዚአብሔር በዳንኤል የመጀመሪያው ቀን ጸሎት መልዕክተኛውን ወዲያውኑ እንዳዘዘ ያሳየናል። መልሱ እስኪገለጥ ሦሥት ሳምንት ቢወስድም፣ እግዚአብሔር ግን ታማኝ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እርሱ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው ይላል (ዕብራውያን 13፡8)።

ምዕራፍ 9 እና 10ን አንድ ላይ ካየናቸው፣ እግዚአብሔር ሁለቱንም ጸሎቶች ወዲያውኑ እንደመለሰ እምናለሁ። አንደኛው ሦሥት ደቂቃ ሲወስድበት ሌላኛው ደግሞ ሦሥት ሳምንት ፈጅቶበታል፣ ልዩነቱ የመጣው ግን ከእግዚአብሔር አይደለም። እንግዲህ ዋናው ነጥብ ይህ ነው፡ እግዚአብሔር ጸሎታችንን ይመልሳል። ነገሮችንም እንዲሆኑ ያደርጋል፣ ነገር ግን እርሱ መልሱን ወደ እናንተ ከላከበት ጊዜ ጀምሮ መልሱ ተገልጦ እስከምታዩት ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ብዙ ልዩነት የሚያመጡ ነገሮች ሊፈጠሩ ይችላሉ። መንፈሳዊው ዓለም ውስጥ ያሉትን ነገሮች ወደ ሚታየው የእኛ ዓለም ማምጣት የሚችለው እምነት ነውና ፣ እምነት ሊኖራችሁ ይገባል። ስለዚህ እምነት ወሳኝ እና ዋና ከሆኑት መሳሪያዎች ውስጥ አንዱ ነው።

በተጨማሪም በዳንኤል 10፡13 እንደምንመለከተው፣ *"የፋርስ መንግሰት አለቃ ግን ሀያ አንድ ቀን ተቋቋመኝ፣ እነሆም፡ ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ፣ እኔም ከፋርስ ነገሥታት ጋር በዚያ ተውሁት"*። ይላል፣ ይህም የሚናገረው ስለ ምድራዊ አካል ሳይሆን ስለ አጋንንታዊ እንቅፋት ነው። መልሱ እስኪገለጥ ባለው ሂደት ውስጥ ሌላው ልዩነትን እምጭ አካል ሰይጣን ነው። አንዳንድ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ጸሎታችን ይመልሳል

ሰይጣን ደግሞ በሌሎች ሰዎች አማካኝነት መልሱ ወደ እኛ እንዳይደርስ ይከላከላል። ለምሳሌ በገንዘብ ጉዳይ እግዚአብሔር ጸሎታችሁን እንደሚመልስ ብታምኑ፣ እግዚአብሔር በእጁ ገንዘብ አይሰጣችሁም። እግዚአብሔር የየትኛውንም አገር ገንዘብ አስመስሎ በመሰራት ወደ እናንተ አይልክም። ገንዘብ ከሰማይ እንዲዘንብ በማድረግ ኪሳችሁን አይሞላም። ሉቃስ 6:38 እንዲህ ይላል *"ስጡ ይሰጣችሁማል፣ በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋልና፣ የተጨቆነና የተነቀነቀ የተትረፈረፈም መልካም መስፈሪያ በእቅፋችሁ ይሰጣችኋል"*። እግዚአብሔር ተንቀሳቅሶ የጸሎታችሁን መልስ ይሰጣል፣ ነገር ግን መልሱ ወደ እናንተ የሚደርሰው በሰዎች በኩል ነው። አንዳንድ ሰዎች በስግብግብነት የተያዙ ናቸው፣ በእናንተ ላይ ከተቆጡ ወይም ምናልባት የሚያስከፋቸውን ነገር ካደረጋችሁ፤ የጸሎታችሁ መልስ እንዳይገለጥ ለማድረግ ሰይጣን እነርሱን ይጠቀማል። ስለዚህ በተለይ ገንዘብን በተመለከተ የምትጸልዩ ከሆነ ምናልባት ሌሎች ሰዎች ተዓምራዊ የገንዘብ ምንጫችሁ ሊሆኑ እንደሚችሉ መገንዘብ ያስፈልጋችኋል፣ እናም ለእነርሱም ልትጸልዩላቸው አስፈላጊ ይሆናል።

እግዚአብሔር ታማኝ ነው። ቃሉን መሰረት አድርጎ፣ በእምነት የሚጸለይን ጸሎት ምንጊዜም ለመመለስ ወደ ኋላ አይልም። ሁሌም ይሰጣል፣ እናንተ ግን ከአንዳንድ ምክንያቶች የተነሳ መልሱን ተገልጦ ላታዩት ትችላላችሁ። ይህ ትምህርት ዛሬ እምነታችሁን ለማጠንከርና እግዚአብሔር ምንጊዜም ጸሎታችሁን እንደሚመልስ እንድታውቁ እንዲረዳችሁ እጸልያለሁ።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ማቴዎስ 7፡7-8 - ከጠየቅን፣ ከእግዚአብሔር ምን እንደሚደረግልን እንጠብቃለን?

   **ማቴዎስ 7፡7-8** *"ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል። [8] የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና፥ የሚፈልገውም ያገኛል፥ መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል"።*

2. ማቴዎስ 7፡7-8 እግዚአብሔርን ከፈለግን፡ ምን እንጠብቃለን?

3. ማቴዎስ 7፡7-8 ካንኳኳን ምን እንደሚደረግልን እንጠብቃለን?

4. ዮሐንስ 10፡35 እግዚአብሔር በቃሉ ተሰፋ ከተሰጠው ያነሰ ሊሰጥ ይችላልን?

   **ዮሐንስ 10፡35** *"መጽሐፉ ሊሻር አይቻልምና እነዚያን የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን አማልክት ካላቸው፥"*

5. ያዕቆብ 4፡1-3 እነዚህ ሰዎች ከእግዚአብሔር መቀበል የማይችሉት ለምንድን ነው?

   **ያዕቆብ 4፡1-3** *"በእናንተ ዘንድ ጦርና ጠብ ከወዴት ይመጣሉ? በብልቶቻችሁ ውስጥ ከሚዋጉ ከእነዚህ ከምኞቶቻችሁ አይደሉምን? [2] ትመኛላችሁ ለእናንተም አይሆንም፤ ትገድላላችሁ በብርቱም ትፈልጋላችሁ፥ ልታገኙም አትችሉም፤ ትጣላላችሁ ትዋጉማላችሁ ነገር ግን አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም፤ [3] ትለምናላችሁ፥ በምኞቶቻችሁም ትከፍሉ ዘንድ በክፉ ትለምናላችሁና አትቀበሉም"።*

6. 1ኛ ጴጥሮስ 3፡7 ለአጋራችሁ ያልተገባ ነገር የምታደርጉ ከሆነ፣ የጸሎት ህይወታችሁ ምን ይሆናል?

   **1ኛ ጴጥሮስ 3፡7** *"እንዲሁም፥ እናንተ ባሎች ሆይ፥ ደካማ ፍጥረት ስለ ሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ፤ ጸሎታችሁ እንዳይከለከል አብረው ደግሞ የሕይወትን ጸጋ እንደሚወርሱ አድርጋችሁ አክብሩአቸው"።*

7. 1ኛ ዮሐንስ 5፡14-15 ጸሎታችሁ መልስ ያገኝ ዘንድ ቁልፉ ምንድን ነው?

   **1ኛ ዮሐንስ 5፡14-15** *"በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፣ እንደ ፈቃዱ አንዳች ብልነለምን ይሰማናል። [15] የምንለምነውንም እንዲሰማልን ብናውቅ ከእርሱ የለመነውን ልመና እንደ ተቀበልን እናውቃለን"።*

8. ማርቆስ 11፡24 ስትጸልዩ ምን ማድረግ ይገባችኋል?

   **ማርቆስ 11፡24** *"ስለዚህ እላችኋለሁ፥ የጸለያችሁትን የለመናችሁትንም ሁሉ እንዳገኛችሁት እመኑ፥ ይሆንላችሁማል"።*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ማቴዎስ 7፡7-8 ከጠየቅን፣ ከእግዚአብሔር ምን እንደሚደረግልን እንጠብቃለን?
**እንደሚሰጠን እንጠብቃለን።**

2. ማቴዎስ 7፡7-8 እግዚአብሔርን ከፈለግን፡ ምን እንጠብቃለን?
**እናገኛለን።**

3. ማቴዎስ 7፡7-8 ካንኳኳን ምን እንደሚደረግልን እንጠብቃለን?
**ይከፈትልናል።**

4. ዮሐንስ 10፡35 እግዚአብሔር በቃሉ ተሰፋ ከተሰጠው ያነሰ ሊሰጥ ይችላልን?
**አይሰጥም።**

5. ያዕቆብ 4፡1-3 እነዚህ ሰዎች ከእግዚአብሔር መቀበል የማይችሉት ለምንድን ነው?
**ምኞቶቻቸውና የልባቸው ሃሳብ ትክክል ባለመሆኑ። ሁሉም ለግላቸውና ለራሳቸው ጥቅም ብቻ ነው፣ ሙሉ ምኞታቸው ራስ ወዳድነት ነው።**

6. 1ኛ ጴጥሮስ 3፡7 ለአጋራችሁ ያልተገባ ነገር የምታደርጉ ከሆነ፣ የጸሎት ህይወታችሁ ምን ይሆናል?
**ጸሎታችሁ ይከለከላል።**

7. 1ኛ ዮሐንስ 5፡14-15 ጸሎታችሁ መልስ ያገኝ ዘንድ ቁልፉ ምንድን ነው?
**እንደ ፈቃዱ (እንደ እግዚአብሔር ቃል) መጠየቅ።**

8. ማርቆስ 11፡24 ስትጸልዩ ምን ማድረግ ይገባችኋል?
**የጸለያችሁትን የለመናችሁትንም ሁሉ እንዳገኛችሁት ማመን፥ ይሆንላችሁማል።**

# የተሟላ ወንጌላዊ
# ደቀ መዝሙርነት

ክፍል 3

# ማውጫ


1. መለኮታዊው ፍሰት 3-166
2. ስጦታዎችን ለአገልግሎት ስለመጠቀም 3-170
3. ተዓምራት እግዚአብሔርን ያከብራሉ 3-175
4. የመልካም ግንኙነቶች ሃይል 3-180
5. ተቃውሞና ሰደት 3-184
6. ንጉሡና መንግሥቱ 3-189
7. የመዳን ዕምነት ዓላማ 3-196
8. የእግዚአብሔር ሕግ ትክክለኛ አጠቃቀም 3-200
9. ከሕግ በታች ሳይሆን ከጸጋ በታች 3-206
10. የኃጢአት እውቀት ቀርቷል 3-212
11. ተወዳጅ ነኝ፣ ውብ ነኝ 3-218
12. የመዳን ፍሬ - ክፍል 1 3-224
13. የመዳን ፍሬ - ክፍል 2 3-230
14. ጥሪ ለደቀመዝሙርነት 3-235
15. ምስክርነታችሁን ስለመጠቀም 3-241
16. የሁሉን ሰው ስጦታዎች ለደቀመዝሙርነት መጠቀም 3-248

# ትምህርት 1

# መለኮታዊው ፍሰት

## በአንድሩ ዉማክ

እግዚአብሔር በእናንተ ውስጥ አልፎ ለሌሎች መድረስ የሚችልበትን አገልግሎት መጀመር ትችላችሁ። በውስጣችሁ የእግዚአብሔር ሃይልና ቅባት አለ፤ ሆኖም ይህን አውጥታችሁ ለሌሎች ሰዎች እንዴት ማድረስ ይቻላችኋል? አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በማንሳት እንጀምር፡- ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ፊልሞና መልዕክቱ ቁጥር 6 *"የእምነትህም ህብረት፣ በእኛ ዘንድ ያለውን በጎ ነገር ሁሉ በማወቅ፣ ለክርስቶስ ኢየሱስ ፍሬ እንዲያፈራ እለምናለሁ"* ይላል። የእግዚአብሔር ሃይል በእናንተ በኩል አልፎ ወደ ሌሎች ሰዎች ይደርስ ዘንድ የመጀመሪያው እርምጃ በእናንተ ውስጥ ያሉትን በጎ ነገሮች በቅድሚያ ማወቅ ነው። የሌላችሁን ለሌሎች ልትሰጡ አትችሉም፤ ነገር ግን አንዴ ውስጣችሁ ያለውን ባወቃችሁ ጊዜ ነገሮች ወዲያውኑ መገለጥ ይጀምራሉ። ውስጣችሁ ያለውን ደስታና ሰላም ለሌሎች ማካፈል፤ ደግሞም እግዚአብሔር በህይወታችሁ ስላደረገው ድንቅ ነገር መመስከር ትጀምራላችሁ፤ በዚህም አንዳንድ ሰዎች ወዲያውኑ ተጠቃሚ ይሆናሉ።

በ1ኛ ዮሐንስ 4፡7-8 *"ወዳጆች ሆይ ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለሆነ የሚወደውም ከእግዚአብሔር ስለተወለደ እግዚአብሔርንም ስለሚያውቅ፣ እርስ በርሳችን እንዋደድ። ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም፤ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና"* ይላል። በማንኛውም ጊዜ ፍቅር ከእናንተ ወጥቶ ወደ ሌሎች ሰዎች ሲፈስ ከታወቃችሁ እግዚአብሔር በእናንተ በኩል ወደ ሰዎቹ እየደረሰ ነው ማለት ነው። በግሪክ ቋንቋ "ፍቅር" አራት ዋና ዋና ትርጓሜዎችን ይዟል። ከሁሉም የላቀው "አጋፔ" ፍቅር ከተፈጥሮ በላይ - ልዕለ ተፈጥሮ የሆነ የእግዚአብሔር አይነት ፍቅር ነው። ለአንድ ሰው ባላችሁ ዝንባሌ፣ ስሜት ወይም ፍላጎት መካከልና በዚህ ልዕለ ተፈጥሮ በሆነ የእግዚአብሔር ፍቅር መካከል ያለውን ልዩነት ልትገነዘቡት ይገባል። በማንኛውም ጊዜ የእግዚአብሔር ፍቅር ከእናንተ ወጥቶ በመፍሰስ ወደ ሌላ ሰው መድረሱ ከታወቃችሁ እራሳችሁን ለመጥቀም ወይም ለግል ጉዳያችሁ አይደለም። ይህ የእግዚአብሔር አይነት ፍቅር ምን አይነት መለያዎች እንዳሉት ለመረዳት 1ኛ ቆሮንቶስ 13፡4-8 ን በማየት ማረጋገጥ ትችላላችሁ። ይታገሳል፣ ቸርነትንም ያደርጋል፣ ፍቅር አይቀናም፣ ፍቅር አይመካም፣ አይታበይም ወዘተ…። እንግዲህ ፍቅር ብላችሁ የምታውቁት በእርግጥ የእግዚአብሔር ፍቅር መሆኑን መመርመር ይኖርባችኋል - ራስ ወዳድ አለመሆኑን፣ ለራስ ጥቅም አለመሆኑን - ሰዎችን የምትወዱትም ስለሚያደርጉላችሁ ነገር አለመሆኑን መለየት ይኖርባችኋል። እንደዚህ ማደግ ስትጀምሩ እና የእርሱን ፍቅር በውስጣችሁ መለየት ስትጀምሩ፣ አሁን በእናንተ ውስጥ አልፎ ወደ ሌላ ሰው ፍቅሩ መፍሰስ ሲችል፣ እግዚአብሔር መንቀሳቀሱን ትረዳላችሁ። አንዴ የእግዚአብሔር ፍቅር በእናንተ በኩል - ወደ ሌላ ሰው ሲፈስ ከታወቃችሁ ዝም አትበሉ፣ ነገር ግን ሰዎቹን በማጽናኛ ቃል፣ በማበረታቻ ቃል በማነጋገር ወይም በሌላ…. እንደ ሁኔታው አንድ ነገር በማድረግ ተከትላችሁ መፍሰስ ትችላላችሁ። አንድ ነገር አድርጉ እንጂ ዝም አትበሉ።

የእግዚአብሔር ፍቅር እና ርህራኄ ያገኘው ዘንድ አንድ ሰው ወደ ልቤ እንዲመጣልኝ የጸለይኩባቸው ጊዜዎች ነበሩ። ይህ ግን ሊሆን የሚችል ነገር አልነበረም፤ ምክንያቱም ደግሞ ከልዕለ ተፈጥሮ በላይ (Super natural) ስለሆነ ነው። ሰዎችን በስልክ፣ ደብዳቤ በመጻፍ ወይም በሌላ መንገድ የማግኘት ልምድ ነበረኝ። ይህን በማደርግበት በእያንዳንዱ ጊዜ ሁሉ የማገኘው ሰው "በአንተ የተናገረኝ እግዚአብሔር ነው፤ ውስጤን ነው የነካኝ" ይሉኛል። ይህ እንዴት እንደሆነ ታውቃላችሁ? ይህ የሆነው የእግዚአብሔር ፍቅር፣ መልካም ርህራኄው፣ በእኔ በኩል አልፎ ወደ ደወልኩለት ሰው ሲፈስ ስለሚታወቀኝ ነው። ይህ ስሜት አሁን ሲሰማኝ ከእኔ ሳይሆን እግዚአብሔር መሆኑን አውቃለሁ። እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ ሌሎችን ሰወድ እርሱ በእኔ በኩል ፍቅሩን እየገለጸላቸው መሆኑን እረዳለሁ። ኢየሱስም በዚህ መልኩ አገልግሎቱን ይፈጽም ነበር። ማቴዎስ 14፡14 *"ወጥቶም ብዙ ሕዝብ አየና አዘነላቸው ድውዮቻቸውንም ፈወሰ"*። የእግዚአብሔር ሃይል በኢየሱስ በኩል ያልፍ የነበረው ኢየሱስ ሕዝቡን በርህራኄና በፍቅር ያገለግላቸው ስለነበር ነው። በማቴዎስ 8፡2-3 የምናገኘው ለምጻም

(የሰጋ ደዌ በሽታ) የነበረበት ሰው በአይሁድ ህግ መሰረት ረክሷልና ማንም የሚነካው ቢኖር ሊረክስ ስለሚችል የሚጠጋው አልነበረም። ስለሆነም ይህ ሰው ከርቀት ድምጹን ከፍ አድርጎ ወደ ኢየሱስ ጮኸ *“ጌታ ሆይ ብትወድስ ልታነጻኝ ትችላለህ እያለ ሰገደለት። እጁንም ዘርግቶ ዳሰሰውና። እወዳለሁ፤ ንጻ አለው። ወዲያውም ለምጹ ነጻ”*። ለምጻሙን አዘነለትና በርህራኄ ዳሰሰው። የእግዚአብሔርን ቃል ስታጠኑ ይህን ርህራኄና መለኮታዊ ፍቅር በብዙ ቦታዎች ታገኛላችሁ። እንዲሁ ተራ ስሜት ሳይሆን በእኛ ውስጥ አልፎ የሚፈስ ርህራሄኄነው።

ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በነበረበት ጊዜ እንኳን ዙሪያውን ለነበሩት ሰዎች ፍቅሩ የበዛ ነበርና - *“አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው”* አለ፣ (ሉቃስ 23፡34።) እርሱን የሰቀሉት ሰዎች እራሳቸው ነበሩ፣ ነገር ግን ለእነርሱም በርህራኄና በፍቅር እግዚአብሔር ይቅርታ እንዲያደርግላቸው ለመነ። ይህንን ያደረገው በስሜት ተገፋፍቶ ወይም ሲቃ ይዞት ሳይሆን ምርጫው ስለሆነ ነው፤ የምርጫ ጉዳይ ነው። ምንም ቢሆን ውስጡ የነበረውን ለሰዎች አካፈለ። ሁላችሁም ዳግመኛ የተወለዳችሁ አማኞች እግዚአብሔር በእናንተ ውስጥ አለ፤ ከላይ ስንጀምር እንዳነሳነው ቃል 1ኛ ዮሐ 4፡8 እግዚአብሔር ፍቅር ነው፣ እናም በእናንተ በኩል ሰዎችን መድረስ ይፈልጋል። ይህን ለማድረግ ደግሞ ርህራኄውን ይልካል። እናንተም ከእናንተ ውስጥ ወጥቶ ወደ ሌሎች ሰዎች ሲደርስ ይታወቃችኋል፣ ይህን በተረዳችሁ ወይም ባወቃችሁ ጊዜ ታዲያ ምላሽ መስጠት ወይም የሚጠበቅባችሁን ማድረግ ይኖርባችኋል።

ሁሌም የተለየ ነገር ማድረግ አይጠበቅባችሁም። “ጌታ እንዲህ ይለኛል” ማለትም አይጠበቅባችሁም። አንዳንዴ ለአንድ ሰው የርህራኄ ስሜት ከተሰማችሁ ሰውየውን እጃችሁን ዘርግታችሁ እየጨበጣችሁ ወይም እጃችሁን ትከሻው ላይ አድርጋችሁ “እግዚአብሔር ይወድሃል፣ እኔም እወድሃለሁ” በሉት። ይህ የሚሰራ ለመሆኑ፣ ለእኔም የሰራልኝ ለመሆኑ እራሴ ምስክር ነኝ። በአንድ ወቅት በቤተ ክርስቲያን ትልቅ ተቃውሞ ደርሶብኝ ነበር፣ የተወሰኑ ሰዎች በእኔ ላይ የሃሰት ውንጀላ ማቅረባቸው ሳያንስ አንድ ሰው ደግሞ ሊገድለኝ ይዝት ነበር፣ ከቤተ ክርስቲያን እንኳን ሳይቀር ለመውጣት በሚያደርስ ሁኔታ ላይ ነበርኩ። በዚህም ተሰፋ ወደ መቁረጥና - “እንዲህ ከሆነ ጌታ ሆይ ምን ጥቅም አለው? ማንም የኔን አገልግሎት አልወደደልኝም” ብዬ ከዲያብሎስ ጋር ግብ ግብ በገጠምኩበት ሰዓት አንድ ጓደኛዬ ከሩቅ አገር ደወለ። ጥቂት ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላም “ዛሬ እንዴት ደወልክ?” ስል ጠየቅኩት። ወዳጄም “ዛሬ የደወልኩት እንደምወድህ እንድታውቅ ልነግርህ ነው። በጸሎት ላይ እያለሁ የእግዚአብሄር ፍቅር ወደ አንተ ሲመራኝ ታወቀኝ ስለዚህ እንደማደንቅህና እንደምወድህም እንድታውቀው ነው የደወልኩልህ” አለኝ። በቃ ይህንን ብቻ ነበር የተናገረኝ። በህይወቴ ስለገጠመኝ ችግርም ሆነ ሁኔታ ያ ወዳጄ የሚያውቀው ነገር አልነበረም እግዚአብሔር ግን ተጠቀመበት። በዚህ ጓደኛዬ በኩል ያጽናናኝና ፍቅሩን የገለጸልኝ እግዚአብሔር እንደሆነ ተረድቻለሁ። በአገልግሎቴ ቀጠልኩ፣ ህይወቴም በከፍተኛ ሁኔታ ተለወጠ።

እጅግ የተራቀቀ ወይም የተቀናበሩ ቃላት አያስፈልጓችሁም። እግዚአብሔር ፍቅር ነው፣ በማንኛውም ጊዜ ፍቅሩ በእናንተ ውስጥ ሲፈስ ከታወቃችሁ … ይህ መለኮታዊ ፍሰት ነው፣ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ህይወት ነው። ይህ በታወቃችሁ ጊዜ ልትከተሉት ይገባል። አንድ ነገር አድርጉ፣ ዝም አትበሉ ይልቅ አፋችሁን ከፍታችሁ ተናገሩና ለሰው በረከት ሁኑ። እግዚአብሔርም የምትናገሩትን ቃል ይሰጣችኋል። ይጠቀምባችኋል። በእናንተም ተጠቅሞ በፍቅርና በርህራኄ ያናገራችኋቸውንና ያገለገላችኋቸውን ሰዎች ከእስራታቸው እንዲፈቱ ያደርጋል።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

ማስታወሻ - በዚህ ትምህርት እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ያስቀመጠውን እንዴት ለሌሎች ማካፈል እንደምንችል እናጠናለን።

1. ፊልሞና 6 አንብቡና እግዚአብሔር ከእኛ ወደ ሌሎች እንዲደርስ ለማድረግ በመጀመሪያ ልናደርገው የሚገባን ምንድን ነው?

   **ፊልሞና 1፡6** *“የእምነትህም ኅብረት፥ በእኛ ዘንድ ያለውን በጎ ነገር ሁሉ በማወቅ፥ ለክርስቶስ ኢየሱስ ፍሬ እንዲያፈራ እለምናለሁ፤”*

2. 1ኛ ዮሐንስ 4፡7-8 ሌሎች ሰዎችን በፍቅር ለመድረስ የሚያስችለን ዓይነተኛ ምንጭ ምንድን ነው?

   **1ኛ ዮሐንስ 4፡7-8** *“ወዳጆች ሆይ፣ ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለሆነ፣ የሚወደውም ሁሉ ከእግዚአብሔር ስለ ተወለደ እግዚአብሔርንም ስለሚያውቅ፣ እርስ በእርሳችን እንዋደድ። [8] ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም፣ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና።”*

3. የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ (አንድሩ) - “ፍቅር ምንጊዜም ከእናንተ ወጥቶ ወደ ሌሎች ሲፈስ ከታወቃችሁ፣ እግዚአብሔር ከእናንተ ወደ ሰዎቹ እየደረሰ ነው” ብሎ እንደሚናገረው፣ ይህንን የሚያረጋግጥልን ቃል ከ1ኛ ዮሐንስ 4፡7 ውስጥ የትኛው ቃል ነው።

4. 1ኛ ቆሮንቶስ 13፡4-8ን አንብቡና የእግዚአብሔር ፍቅር ባህሪያት ከሆኑት ውስጥ ጥቂቶቹን ዘርዝሩ፤

   **1ኛ ቆሮንቶስ 13፡4-8** *“ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም፤ [5] የማይገባውን አያደርግም፥ የራሱንም አይፈልግም፥ አይበሳጭም፥ በደልን አይቆጥርም፤ [6] ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤ [7] ሁሉን ይታገሣል፥ ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል። [8] ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም፤ ትንቢት ቢሆን ግን ይሻራል፤ ልሳኖች ቢሆኑ ይቀራሉ፤ እውቀትም ቢሆን ይሻራል።”*

5. ማቴዎስ 14፡14ን አንብቡ፤ ኢየሱስ ሰዎቹን ሲያገለግላቸው ምን ይሰማው ነበር?

   **ማቴዎስ 14፡14** *“ወጥቶም ብዙ ሕዝብ አየና አዘነላቸው ድውዮቻቸውንም ፈወሰ።”*

6. ማቴዎስ 25፡37-40 ለሌሎች በፍቅር ስንደርስ፣ ስናዝንላቸውም፤ ማንን እየወደድንና እያገለገልን ነው?

   **ማቴዎስ 25፡37-40** *“ጻድቃንም መልሰው ይሉታል። ጌታ ሆይ፣ ተርበህ አይተን መቼ አበላንህስ? ወይስ ተጠምተህ አይተን መቼ አጠጣንህ? [38] እንግዳ ሆነህስ አይተን መቼ ተቀበልንህ? ወይስ ታርዘህ አይተን መቼ አለበስንህ? [39] ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ አይተን መቼ ወደ አንተ መጣን? [40] ንጉሡም መልሶ። እውነት እላችኋለሁ፣ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት ይላቸዋል።”*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ፊልሞና 6ን አንብቡና እግዚአብሔር ከእኛ ወደ ሌሎች እንዲደርስ ለማድረግ በመጀመሪያ ልናደርገው የሚገባን ምንድን ነው?
   **እርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ በእኛ ዘንድ ያስቀመጠውን በጎ ነገር ሁሉ ማወቅ።**

2. 1ኛ ዮሐንስ 4፡7-8 ሌሎች ሰዎችን በፍቅር ለመድረስ የሚያስችለን ዓይነተኛ ምንጭ ምንድን ነው?
   **እግዚአብሔር። እግዚአብሔር ፍቅር ነውና (1ኛ ዮሐንስ 4፡8)።**

3. የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ እንድሩው - "ፍቅር ምንጊዜም ከእናንተ ወጥቶ ወደ ሌሎች ሲፈስ ከታወቃችሁ፣ እግዚአብሔር ከእናንተ ወደ ሰዎቹ እየደረሰ ነው" ብሎ እንደሚናገረው፣ ይህንን የሚያረጋግጥልን ቃል ከ1ኛ ዮሐንስ 4፡7 ውስጥ የትኛው ቃል ነው።
   **"ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለሆነ" (ምንጩ እርሱ ነው)።**

4. 1ኛ ቆርንቶስ 13፡4-8ን የእግዚአብሔር ፍቅር ባህሪያት ከሆኑት ውስጥ ጥቂቶቹን ዘርዝሩ፤
   **ፍቅር ለቁጣ የዘገዬ ነው፣ ይታገሣል። ይህም አሁን ነው ሁሌም ፍቅር እንዲህ ያደርጋል። ቸርነትንም ያደርጋል፣ እራሱን ቸርነት በማድረግ ይገልጣል። ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፣ አይታበይም፤ የማይገባውን አያደርግም፣ የራሱንም አይፈልግም፣ አይበሳጭም፣ በደልን አይቆጥርም፤ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤ ሁሉን ይታገሣል፣ ሁሉን ያምናል፣ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፣ በሁሉ ይጸናል። ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም፤ ትንቢት ቢሆን ግን ይሻራል፤ ልሳኖች ቢሆኑ ይቀራሉ፤ እውቀትም ቢሆን ይሻራል።**

5. ማቴዎስ 14፡14ን አንብቡ፤ ኢየሱስ ሰዎቹን ሲያገለግላቸው ምን ይሰማው ነበር?
   **በርህራሄ ያያቸው ነበር። ርህራሄ የእዘኔታ እና የምህረት ስሜት ነው።**

6. ማቴዎስ 25፡37-40 ለሌሎች በፍቅር ስንደርስ፣ ስናዝንላቸውም፤ ማንን እየወደድንና እያገለገልን ነው?
   **ኢየሱስን እያገለገልን ነው፣ ዕብራውያን 6፡10 ን ተመልከቱ።**

## ትምህርት 2

# ስጦታዎችን ለአገልግሎት ስለመጠቀም

## በአንድሩ ዉማክ

የተቀበላችሁትን የእግዚአብሔር ፍቅር ከሌሎች ሰዎች ጋር እንዴት መካፈል ይቻላችኋል፣ ለሌሎችስ እንዴት ውጤታማ አገልጋይ መሆን ትችላላችሁ? 1ኛ ጴጥሮስ 4፡11 *“ማንም ሰው የሚናገር ቢሆን እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር”* ይላል። “የእግዚአብሔር ቃል” ወይም (The oracle of God) ተብሎ የሚታወቀው በብሉይ ኪዳን ዘመን በቅድስተ ቅዱሳን በሚገኘው ታቦት ውስጥ ያስቀምጡት የነበረው የእግዚአብሔር ቃል ነበርና የሚናገር “እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር” ሲባል እንደ እግዚአብሔር እንደበት ሆኖ ይናገር፤ ከእግዚአብሔር እንደተነገራችሁ ሆናችሁ ተናገሩ ማለት ነው። ቃሉ በመቀጠል እንዲህ ይላል *“የሚያገለግልም ቢሆን እግዚአብሔር በሚሰጠኝ ሃይል ነው ብሎ ያገልግል፤ ክብርና ሥልጣን እስከ ዘላለም ድረስ ለእርሱ በሚሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ይከብር ዘንድ፤ አሜን።”* ይህ ቃል የሚናገረው ሌሎች ሰዎችን በምታገለግሉበት ጊዜ በእናንተ በእራሳችሁ ችሎታ ሳይሆን እግዚአብሔር በሚሰጣችሁ ችሎታ ሊሆን ይገባል የሚል ነው፡

የክርስትና ሕይወት ካሉት አስደናቂ ነገሮች አንዱ እኔም ሆንኩ እናንተ ከግል ችሎታችን በመነሳት የምንናገርበትና የምናካፍልበት ሁኔታ ሳይሆን ያለው፣ እግዚአብሔር እራሱ ወደ እኛ መጥቶ በእኛ ውስጥ የሚኖር መሆኑ ነው። መጥቶም በእኛ በኩል መናገርና አልፎም ሌሎችን መድረስ ይጀምራል። እንዲሁ በእግዚአብሔር ሙላት ውስጥ እንሆንና የእግዚአብሔር መንፈስ በእኛ በኩል መፍሰስ ይጀምራል። ከሌሎች ሰዎች ጋር መካፈል በጀመርን ጊዜ ማስታወስ የሚገባን “የመንፈስ ስጦታዎች” ተብሎ የሚጠራው ይህ መሆኑን፤ አስፈላጊነቱም ለዚሁ አላማ መሆኑን ነው። እግዚአብሔር የክርስቶስ አካል ለሆነ ለእያንዳንዱ ሰው ልዩ ልዩ ስጦታዎችን ይሰጣል። በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 12 እያንዳንዳችን እንደ ፈቃዱ መጠን ስጦታ እንደተሰጠን ይናገራል። በቁጥር 4-6 እንዲህ ይላል *“የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው፤ አገልግሎትም ልዩ ልዩ (ብዙ ዓይነት) ነው ጌታም አንድ ነው፤ አሠራርም ልዩ ልዩ ነው፣ ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው”* (ቅንፍ በእኔ የተጨመረ ነው)። ይህም ማለት እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች ሁሉ በእኛ ይሰራል፣ ቁጥር 7 ላይ እንደሚናገረው *“ነገር ግን መንፈስ ቅዱሰን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል”* ወይም ሁሉም ተጠቃሚ ይሆኑ ዘንድ።

እንግዲህ እነዚህ ጥቅሶች እግዚአብሔር ከልዕለ ተፈጥሮ በላይ የሆነ ችሎታን በእያንዳንዳችን ውስጥ እንዳስቀመጠ ይናገራሉ። ምናልባት ላይሰማችሁ ወይም ላይታወቃችሁ ይችላል፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል የሰጠው ተስፋ ነው። በዚህ የደቀመዝሙር ትምህርት ይህን ያህል ርቀት ከመጣችሁ፣ ኢየሱስንም የግል አዳኛችሁ አድርጋችሁ የተቀበላችሁ ከሆነ፣ ከእግዚአብሔርም እንዴት መቀበልና በህይወታችሁ ጥቅም ላይ ማዋልን ካወቃችሁና ከጀመራችሁ፣ እንግዲያውስ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በእናንተ ውስጥ በስራ ላይ ስለመሆኑ አረጋግጥላችኋለሁ። ለሌሎች ሰዎች የሚያስፈልግ ተዓምር በውስጣችሁ አለ። እግዚአብሔር ሌላ ሰው የሚያስፈልገውን ተዓምር በዘር መልክ በእናንተ ውስጥ አኑሯል። ይሁን እንጂ በውስጣችሁ ያለውን እውጥታችሁ ለሌሎች ህይወት እንዲደርስ ማድረግ በእናንተ ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ነው። ይህም ለሁላችን በመንፈስ የተሰጠን መሆኑን የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል። ያልተሰጠው አንድም ሰው የለም። በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ አስራ ሁለት፣ ዘጠኝ የተለያዩ ዓይነት የመንፈስ ስጦታዎች የተዘረዘሩ ሲሆን ከእነዚህም መካከል ጥበብን መናገር፣ እውቀትን መናገር፣ መናፍስትን መለየት፣ ተአምራትን ማድረግ፣ የመፈወስ ስጦታ ወዘተ… ይገኙበታል። በሮሜ ምዕራፍ 12 የተጠቀሱ ሌሎች ስጦታዎችም አሉ። እነዚህን በራሳችሁ በማጥናት መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዳችሁ ላይ ልዩ ቅባት - ሌሎችንም የምታለግሉበትን ልዩ ችሎታ - ያስቀመጠ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋችኋል። ሆኖም ሁሉም ሰው አሁን እኔ እንደማገለግለው ላያገለግል ይችላል። የማስተማር ስጦታ ላይኖራችሁ ይችላል ነገር ግን በክርስቶስ አካል ውስጥ ያለ ሁሉም ሰው እምነቱን በማካፈል ሌሎችን ማስተማር ይችላል። ለማስተማር ብቻ የተጠሩ ሰዎች አሉ፣ ደግሞም ይሰብኩ ዘንድ እና የቤት ክርስቲያን አገልጋይ ይሆኑ ዘንድ የተጠሩም አሉ። በሮሜ 12 የተጠቀሰው

ሌላው ስጦታ ደግሞ እንግዶችን የመቀበል ስጦታ ያላቸው እንዳሉ ይናገራል። ብዙዎቻችሁ ያላወቃችሁት ችሎታ ወይም ስጦታ ይኖራችሁ ይሆናል። ለሌላ ሰው በረከት የመሆን ፍላጎትም ይኖራችኋል። ምናልባት ወደ አንድ ክፍል ስትገቡ በቀላሉ ሕመም ያለበትን ሰው ለይቶ የማውጣት ችሎታ ያለው ሰው ዓይነት ልትሆኑ ትችላላችሁ። ሰዎቹ ያለፉበትን መከራ ልታውቁና ደግሞም ልታጽናኗቸው፣ ሸክማቸውን ልታቀሉላቸውና ልታገለግሏቸው ትችላላችሁ። እናም ይህ ልዕለ ተፈጥሯዊ የእግዚአብሔር ስጦታ እንደሆነ ታውቃላችሁ?

ሮሜ ምዕራፍ 12 አንዳንድ ሰዎች የመስጠት ስጦታ እንዳላቸውና ለዚህ እንደተጠሩ ይናገራል፤ ገንዘብ የማግኘት ችሎታ ያላቸው ሲሆን በሚያገኙት ገንዘብ የወንጌል አገልግሎትን ይደግፋሉ። ይህም የተሰጣቸው ስጦታ ነው፣ የህይወት ጥሪአቸው ነው። አንዳንዶቻችሁም ምናልባት ለዚህ አገልግሎት ተጠርታችሁ ይሆናል። ሌሎቻችሁ ደግሞ የመምከር ስጦታ ይኖራችኋል። ሌሎች ደግሞ የአስተዳዳሪነት፣ በተለይ በቤተ ክርስቲያን እርዳታ ተብሎ የሚጠራው ስጦታ አላቸው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ሆነ ዘወትር ከሰዎች ጋር ባለን የዕለት ከዕለት ግንኙነት ልንሰራቸው የምንችላቸው ብዙ ነገሮች አሉ። አንዳንዶቻችሁ ተስፋ የቆረጡ ሰዎችን የማጽናናት ችሎታ አላችሁ ይህን እኔ አሁን ቃል በማስተማር ላደርገው የምችለው ነገር አይደለም። የሰዎች ትከሻ ላይ እጃችሁን በመጫን እንድትባርኳቸውና አቅማቸውን እንዲጠቀሙ ልትረዷቸው የምትችሉበት ልዕለ ተፈጥሮ የእግዚአብሔር ችሎታ አላችሁ። ይህን እንደ ማንኛውም የተፈጥሮ ባህሪ ቆጥራችሁ "ባህሪዬ ነው" እንዳትሉ ነው የመልዕክቴ ዋና ነጥብ። እራሳችሁን እንዲህ ወይም እንዲያ ዓይነት ሰው ነኝ ብላችሁ ልትቆጥሩ ትችላላችሁ ነገር ግን እግዚአብሔር በውስጣችሁ ያኖረው ልዕለ ተፈጥሮ ችሎታ ነው - ብቃት፣ አቅም፣ ችሎታ እና ይህን ታደርጉ ዘንድ ምሪት በመስጠት ወደ ነገሮቹ የሚስባችሁ።

ሌሎች ሰዎችን በምታገለግሉበት ጊዜ እግዚአብሔር በውስጣችሁ ባኖራቸው ነገሮች ታገለግሉ ዘንድ እንደሚገባ ቃሉ ይናገራል። በሙሉ ጊዜ አገልጋይነት፣ በሥራ ቦታ ወይም የትም ቦታ ሆነን ሊሆን ይችላል ሁላችንም አገልጋይ መሆን ይኖርብናል። ከጎረቤቶቻችሁ ጋር ይሁን ወይም በገበያ ቦታ ይህን በምታደርጉበት ጊዜ እግዚአብሔር በሰጣችሁ ችሎታ እንጂ ከራሳችሁ ችሎታ ተነስታችሁ ሊሆን አይገባም። ስለዚህ እግዚአብሔርን እንድትፈልጉ አበረታታችኋለሁ፤ በውስጣችሁ ያስቀመጠው ስጦታ ምን እንደሆነ እወቁ፣ በሃይማኖታዊ አገልግሎት ዘርፍ ያልተጠራችሁ ብትሆኑም እንኳን ስጦታዎችን ዋጋ ቢስ አታድርጉ። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ልዕለ ተፈጥሮ ስጦታዎችን በእያንዳንዳችሁ ውስጥ እንዳስቀመጠ በማወቅ እግዚአብሔር ውስጣችሁ ባስቀመጣቸው ስጦታዎች ሌሎችን አገልግሉ።

በእርግጥ ጊዜ እና ልምድ ይጠይቃል። ገና በመጀመሪያ ፍጹም አትሆኑምና ልምምዳችሁን ለመቀጠል መፍራት አይኖርባችሁም። ብትሳሳቱ እንኳን እግዚአብሔር ከዙፋኑ አይወርድም እንዲያውም ሌሎች ሰዎች የልባችሁን ቅንነት ያስተውላሉ። ነገሮችን በትክክል ባትፈጽሙላቸው እንኳን በፍቅራችሁ ይገለገላሉ። ከእግዚአብሔር የተሰጣችሁ መሆኑን አስታውሱና የተሰጣችሁን ልዕለ ተፈጥሮ የሆነ ችሎታ ለሌሎች ሰዎች ማካፈል ጀምሩ።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. 1ኛ ጴጥሮስ 4፡11 እንብቡና እንድናገለግል የሚያስፈለግን በማን ችሎታ ነው?

   **1ኛ ጴጥሮስ 4፡11** *“ማንም ሰው የሚናገር ቢሆን፥ እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር፤ የሚያገለግልም ቢሆን፥ እግዚአብሔር በሚሰጠኝ ኃይል ነው ብሎ ያገልግል፤ ክብርና ሥልጣን እስከ ዘላለም ድረስ ለእርሱ በሚሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ይከብር ዘንድ፤ አሜን።”*

2. 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡4 “የተለያዩ እና ልዩ ልዩ ዓይነት የመንፈስ ስጦታዎች አሉ፣ ነገር ግን የሁሉም ምንጭ ማን ነው?”

   **1ኛ ቆሮንቶስ 12፡4** *“የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው፤”*

3. 1 ቆሮንቶስ 12፡6 ተክክለኛውን አረፍተ ነገር ምረጡ፤

   ሀ. እግዚአብሔር በአንድ ነገር ብቻ ይሰራል፣
   ለ. እግዚአብሔር በሰዎች የሚሰራባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉ፣
   ሐ. እግዚአብሔር በሰባኪ ብቻ ይሰራል፣

   **1ኛ ቆሮንቶስ 12፡6** *“እሠራርም ልዩ ልዩ ነው፥ ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው።”*

4. 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡7 እውነት ወይም ሐሰት፤ የመንፈስ ቅዱስ መገኘትና መንፈሳዊ ስጦታዎቹ ለእያንዳንዳችን ለበጎ ይሰጡናል።

   **1ኛ ቆሮንቶስ 12፡7** *“ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል።”*

5. 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡8-10 እግዚአብሔር ለሰዎች የሰጣቸውን አንዳንድ የመንፈስ ስጦታዎች በመዘርዘር ምንነታቸውን ግለፁ።

   **1ኛ ቆሮንቶስ 12፡8-10** *“ለአንዱ ጥበብን መናገር በመንፈስ ይሰጠዋልና፥ ለአንዱም በዚያው መንፈስ እውቀትን መናገር ይሰጠዋል፥[9] ለአንዱም በዚያው መንፈስ እምነት፥ ለአንዱም በአንዱ መንፈስ የመፈወስ ስጦታ፥ ለአንዱም ተአምራትን ማድረግ፥[10] ለአንዱም ትንቢትን መናገር፥ ለአንዱም መናፍስትን መለየት፥ ለአንዱም በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር፥ ለአንዱም በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም ይሰጠዋል፤”*

6. ሮሜ 12፡6-8 በዚህ ቃል ውስጥ የተዘረዘሩትን እግዚአብሔር ለሰዎች የሰጣቸውን መንፈሳዊ ስጦታዎች ግለጹ።

   **ሮሜ 12፡6-8** *“እንደተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን፣ ትንቢት መናገር ቢሆን እንደ እምነታችን መጠን ትንቢት እንናገር፤ [7] አገልግሎትም ቢሆን በአገልግሎታችን እንትጋ፣ የሚያስተምርም ቢሆን በማስተማሩ ይትጋ፤ [8] የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ፣ የሚሰጥ በልግስና ይስጥ፣ የሚገዛ በትጋት ይግዛ፣ የሚምር በደስታ ይማር።”*

7. እነዚህ ስጦታዎች በእናንተ ውስጥ የሚሰሩ ለመ ሆናቸው አሰተውላችኋል? ከሆነ፣ የትኞቹ ስጦታዎች?

8. 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡7 በስጦታዎቹ ተጠቃሚ የሚሆነው ማን ነው?

# ጠቋሚ መልሶች

1. 1ኛ ጴጥሮስ 4፡11 እንብቡና እንድናገለግል የሚያስፈለግን በማን ችሎታ ነው?
**በእግዚአብሔር ችሎታ።**

2. 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡4 “የተለያዩ እና ልዩ ልዩ ዓይነት የመንፈስ ስጦታዎች አሉ፣ ነገር ግን የሁሉም ምንጭ ማን ነው?”
**እግዚአብሔር/መንፈስ ቅዱስ።**

3. 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡6 ተክክለኛውን አረፍተ ነገር ምረጡ፤
**ለ. እግዚአብሔር በሰዎች የሚሰራባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉ።**

4. 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡7 እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ፤ የመንፈስ ቅዱስ መገኘትና መንፈሳዊ ስጦታዎቹ ለእያንዳንዳችን ለበጎ ይሰጡናል።
**እውነት።**

5. 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡8-10 እግዚአብሔር ለሰዎች የሰጣቸውን አንዳንድ የመንፈስ ስጦታዎች በመዘርዘር ምንነታቸውንም ግለፁ።
   - **ጥበብን መናገር = ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ እና አላማ ልዕለ ተፈጥሯዊ የሆነ መገለጥ፤ የሐዋርያት ሥራ 27፡21-25 ተመልከቱ።**
   - **እውቀትን መናገር = ስለ አንድ ነገር ምንነት ወይም ክስተት ልዕለ ተፈጥሮ የሆነ የእግዚአብሔር መገለጥ፤የሐዋርያት ሥራ 9፡11-12 ተመልከቱ።**
   - **የእምነት ስጦታ = ያለመጠራጠር ወይም ያለማወላወል እግዚአብሔርን የማመን ልዕለ ተፈጥሮ ችሎታ፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 13፡2 ተመልከቱ።**
   - **የመፈወስ ስጦታ =ያለ ሰው ወይም ያለ ሕክምና እርዳታ ህመምን የመፈወስ ልዕለ ተፈጥሮ ችሎታ፤ ማርቆስ 16፡18 ተመልከቱ።**
   - **ተአምራትን ማድረግ = ከተፈጥሮ ሕጎች ውጭ በሆነ የልዕለ ተፈጥሮ ጣልቃ ገብነት ተዓምራት መከሰታቸው፤ ዕብራውያን 2፡3-4 ተመልከቱ።**
   - **ትንቢትን መናገር = ሰዎች በሚያውቁት ቋንቋ፣ ልዕለ ተፈጥሯዊ ንግግሮችን በእግዚአብሔር አነሳሽነት መናገር የሐዋርያት ሥራ 11፡27-28 እና 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡3 ተመልከቱ።**
   - **መናፍስትን መለየት = ከእግዚአብሔር በሚሰጥ ልዕለ ተፈጥሯዊ መገለጥ መናፍስትን ወይም አሰራራቸውን መለዬት፣ የሐዋርያ ሥራ 16፡16-18 ተመልከቱ።**
   - **በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር = በእግዚአብሔር አነሳሽነት ልዕለ ተፈጥሯዊ በሆነ የማይታወቅ ቋንቋ (ተናጋሪው በማያውቀው ቋንቋ) መናገር፣ የሐዋርያ ሥራ 2፡4-11 ተመልከቱ ።**
   - **በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም = ልዕለ ተፈጥሯዊ በሆነ የእግዚአብሔር አነሳሽነት የተነገሩ ልሳኖችን ትርጉም መናገር፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡13-14 ተመልከቱ።**

6. ሮሜ 12፡6-8 በዚህ ቃል ውስጥ የተዘረዘሩትን እግዚአብሔር ለሰዎች የሰጣቸውን መንፈሳዊ ስጦታዎች ግለጹ።
   - **ትንቢት = በእግዚአብሔር አነሳሽነት፣ ተናጋሪው በሚያውቀው ቋንቋ፣ ልዕለ ተፈጥሯዊ ንግግሮችን መናገር።**
   - **አገልግሎት = ሌሎችን ማገልገል፣ በሚያስፈልጋቸው ነገር፣ 2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡11ተመልከቱ።**

- **ማስተማር = ትምህርትን ማስረዳት፣ ማብራራት እና ማካፈል የሐዋርያ ሥራ 13፡1 ተመልከቱ።**
- **መምከር = ማሳሰብ፣ መምከር፣ ማደፋፈር፣ መለመን፣ ማበርታት፣ ማጽናናት ወይም ማስጠንቀቅ፣ የሐዋርያት ሥራ 13፡15 ተመልከቱ።**
- **መስጠት = ለእግዚአብሔርም ሆነ ለሌሎች የተሰጡ ስጦታዎችን በልግሰና ማካፈል፤ ምሳሌ 22፡9 ተመልከቱ።**
- **መምራት = መሪነት ወይም የመምራት ሥራ፤ የሐዋርያ ሥራ 20፡28 ተመልከቱ።**
- **ምህረት = ላሰቀየመ ወይም ለተጠቃ ርኅራኄ ማሳዬት፣ ማቴዎስ 5፡7።**

7. እነዚህ ስጦታዎች በእናንተ ውስጥ የሚሰሩ ለመሆናቸው አስተውላችኋል? ከሆነ፣ የትኞቹ ስጦታዎች?

8. 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡7 በስጦታዎቹ ተጠቃሚ የሚሆነው ማን ነው?
**ሁሉም። ስጦታዎችን ተጠቅማችሁ ሌሎችን ስትረዱ እግዚአብሔር በእናንተ እንዲሰራ እያደረጋችሁ ነው።**

# ትምህርት 3

# ተዓምራት እግዚአብሔርን ያከብራሉ

## በአንድሩ ዉማክ

ባለፉት ትምህርቶች በእግዚአብሔር ሃይል ስለመንቀሳቀስና እርሱ በሚሰጠን ስጦታዎች ሌሎች ሰዎችን ስለማገልገል ማውራታችን ይታወሳል። ይህም እግዚአብሔርን እንዴት እንደሚያከብር እና ልዕለ ተፈጥሮ ችሎታውን ስንጠቀም ከእኛ ምን እንደሚጠብቅ አንዳንድ ጉዳዮችን ማካፈል እወዳለሁ። በዚህ ዙሪያ ካሉት ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ውስጥ ጥቂቶቹን አብረን እንመልከት። በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 9 ኢየሱስ አንድን ሽባ ሰው የፈወሰበት አጋጣሚ ነበር፤ ይህን በተመለከተ በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 2 ያለውን ወረድ ብለን በሰፋት እናዬዋለን። ማቴዎስ 9፡8 እንዲህ ይላል *“ሕዝቡም አይተው ተደነቁ፣ ለሰውም እንዲህ ያለ ሰልጣን የሰጠ እግዚአብሔርን አከበሩ።”* የመንፈስ ስጦታዎች - ተዓምራት - እግዚአብሔርን እንደሚያከብሩ እና እነዚህን ተዓምራታዊ ችሎታዎች በዚህ ምክንያት እንደሰጠን ታውቃላችሁ?

ለሌሎች ማካፈል ስትጀምሩ የምትናገሩትን የመጠራጠር ተፈጥሯዊ ዝንባሌ ይኖራቸዋልና “ይህ የምትናገረው/የምትናገሪው እውነት መሆኑን እንዴት እውቃለሁ?” ብለው መጠየቅ ይጀምራሉ። በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን ወደ ጌታ ያመጣ ቲ ኤል ኦስቦርን የሚባል ታዋቂ ወንጌላዊ ለመጀመሪያ ጊዜ በውጭ አገር የነበረውን የሚሽነሪ አገልግሎት በተመለከተ እንዲህ ያስታውሳል። ለሰዎች መመስከር በሚሞክርበት ጊዜ ሁሉ፣ የሚሰሙት ሰዎች የሚናገረውን በፍጹም እያምኑም ነበር። በመጨረሻም፣ አንድ ቀን ለአንድ ሰው ሊመሰክር “መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው…” ብሎ ጀመረ። ሰውዬው ግን “ቆይ እስኪ አንዴ፣ ያንተ ጥቁር መጽሐፍ ከሌሎች ጥቋቁር መጽሐፍት በምን ይለያል?” ሲል አቋረጠው። ያን ጊዜ ቲ. ኤል ኦስቦርን - እነዚህ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ እውነት መሆኑን እንዴት ማወቅ ይችላሉ? መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ አምናለሁ፣ ነገር ግን ለእነርሱ ማስረዳት የምችለው እንዴት ነው? ሲል አሰበ።

በሚሽነሪው መሰክ ተሸንፎና ተሰፋ ቆርጦ በመመለስ ወደ ቤቱ መጣና እግዚአብሔርን መፈለግ ጀመረ። ጌታም ልዕለ ተፈጥሮ ችሎታውን መጠቀም እንደነበረበት ነገረው። ምልክቶች እና ድንቆች የእግዚአብሔርን ቃል ትክክለኛነት ለማሳየት የሚጠቅሙ ሲሆን ይህም የሰዎችን ሕይወት ይቀይራል። በ1ኛ ጴጥሮስ 1፡23 *“ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፣ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ”* ይላል። የሰዎችን ሕይወት የሚቀይረው የእግዚአብሔር ቃል ነው፣ ነገር ግን በእርግጠኝነት እግዚአብሔር የተናገረው ቃል ነው ብላችሁ እንዴት ልታሳምኗቸው ትችላላችሁ? እንግዲህ ተዓምራት የሚያስፈልጉት ለዚህ ነው። ሰው ፈውስ ያገኝ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ብለን ስንሰብክና ስንናገር፣ የተናገርነውን በእነርሱ ላይ የኢየሱስን ስም ተጠቅመን ማሳየት ይኖርብናል ማለት ነው። የጠፉ አይኖቻቸው ወይም የማይሰሙ ጆሮዎቻቸው ሲከፈቱ ይህን ያደረገው እግዚአብሔር መሆኑን ያረጋግጣሉ። ተዓምራት ሰዎችን አይቀይሩም፣ ነገር ግን የነገራችኋቸው ቃል የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን እንዲያምኑ ያደርጓቸዋል።

ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ማርቆስ 2፡1-9 ሲሆን ስለ ሽባው ሰው ተጨማሪ ማብራሪያ ይሰጠናል፡ *“ከጥቂት ቀን በኋላ ወደ ቅፍርናሆም ደግሞ ገብቶ በቤት እንደ ሆነ ተሰማ። በደጅ ያለው ሰፍራም እስኪጠባቸው ድረሰ ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡ፤ ቃሉንም ይነግራቸው ነበር። አራት ሰዎችም የተሸከሙትን ሽባ አመጡለት። ሰለ ሕዝቡም ብዛት ወደ እርሱ ማቅረብ ቢያቅታቸው እርሱ ያለበትን የቤቱን ጣራ አነሡ፣ ነድለውም ሽባው የተኛበትን አልጋ አወረዱ። ኢየሱሰም እምነታቸውን አይቶ ሽባውን። አንተ ልጅ፣ ኃጢአትህ ተሰረየችልህ አለው። ከጻፎችም አንዳንዶቹ በዚያ ተቀምጠው ነበር በልባቸውም። ይህ ሰው ሰለ ምን እንደዚህ ያለ ሰድብ ይናገራል? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ኃጢአት ሊያሰተሰርይ ማን ይችላል? ብለው አሰቡ። ወዲያውም ኢየሱሰ በልባቸው እንዲህ እንዳሰቡ በመንፈሰ አውቆ እንዲህ አላቸው። በልባችሁ ይህን ሰለ ምን ታሰባላችሁ? ሽባውን።*

*ኃጢአትህ ተሰረየችልህ ከማለት ወይስ። ተነሣ አልጋህንም ተሸከምና ሂድ ከማለት ማናቸው ይቀላል?"* እውነቱ እንግዲህ እኛ እስከምናውቀው ሁለቱንም ማድረግ የሚቻል አለመሆኑን ነው። ሰው የሰውን ኃጢአት ይቅር ማለት አይችልም፣ ደግሞም ሰው ሽባ የሆነን ሌላ ሰው መፈወስም አይችልም። ስለዚህ እግዚአብሔር አንደኛውን ማድረግ ከቻለ፣ በእርግጠኝነት ሁለተኛውንም ማድረግ ይችላል ማለት ነው።

ኢየሱስም በቁጥር 10-12 – *"ነገር ግን ለሰው ልጅ በምድር ላይ ኃጢአትን ሊያስተሰርይ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ፤ ሽባውን። አንተን እልሃለሁ፣ ተነሣ፣ አልጋህን ተሸከምና ወደ ቤትህ ሂድ አለው። ተነሥቶም ወዲያው አልጋውን ተሸክሞ በሁሉ ፊት ወጣ፣ ስለዚህም ሰዎች ሁሉ ተገረሙና። እንዲህ ያለ ከቶ አላየንም ብለው እግዚአብሔርን አከበሩ።"* ኢየሱስ *"ነገር ግን ለሰው ልጅ በምድር ላይ ኃጢአትን ሊያስተሰርይ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ፤ ሽባውን።"* ብሎ ሲናገር በጣም ግልጽ ያደረገው በቃሉ መሰረት ፈውስን  በምድር ላይ ማድረግ ከቻለ እንደ ተናገረው በመንፈሳዊው ዓለምም ደግሞ የኃጢአት ሰርዬት እና ሌሎችንም መንፈሳዊ ነገሮች ማድረግ እንደሚችል ሕዝቡ ያውቁለት ዘንድ ነው። ኢየሱስ ቃሉን ያረጋገጡለት ዘንድ ተዓምራትን ይጠቀማል።

በዕብራውያን 2፡2-3 የዚህን ተመሳሳይ እናገኛለን፡- *"በመላእክት የተነገረው ቃል ጽኑ ከሆነ፣ መተላለፍና አለመታዘዝም ሁሉ የጽድቅን ብድራት ከተቀበለ፣ እኛስ እንዲህ ያለውን ታላቅ መዳን ቸል ብንለው፣ እንዴት እናመልጣለን? ይህ በጌታ በመጀመሪያ የተነገረ ነበርና፣ የሰሙትም ለእኛ አጸኑት።"* እግዚአብሔር ይህንን ቃል በመንፈስ ቅዱስ ሃይል ያጸና ወይም ያረጋግጥ ነበር። ይህን ከማርቆስ 16፡20 ጋር አንድ ላይ ተመልከቱት፡- *"እነርሱም ወጥተው በየስፍራው ሁሉ ሰበኩ፣ ጌታም ከእነርሱ ጋር ይሠራ ነበር፣ በሚከተሉትም ምልክቶች ቃሉን ያጸና ነበር"* ይላል። እንግዲህ እየነገርኳችሁ ያለሁት ዋናው ነጥብ እግዚአብሔር የእርሱን ልዕለ ተፈጥሮ ችሎታ እና ሃይል ሌሎች ሰዎችን ለማገልገል እንድትጠቀሙበት ይፈልጋል የሚል ነው። በመንፈስ ቅዱስ በኩል የመንፈስ ስጦታ የሆኑትን ተዓምራትን በእርግጥ እግዚአብሔር እየተናገረቸው መሆኑን ያውቁ ዘንድ ለሰዎች ማረጋገጫ እንዲሆናቸው ይጠቀምባቸዋል። በዋነኛነት ሰዎች ልባቸው ፍጹም ነጻ እንዲወጣ ይፈልጋል፣ ነገር ግን የሰውን ልብ ለማግኘት በስሜታቸው እና በአካላቸው በኩል ማለፍ ግድ ይሆናል። በእነዚህ ዙሪያ ያለው ችግራቸው ተቀርፎላቸው ሰዎች ነጻ መሆን እንዲችሉ ካደረጋችሁ በእርግጥ ራሳቸውን ለጌታ ክፍት አድርገው ቀሪ ሕይወታቸውን እንዲነካላቸውና እንዲሁ ሙሉ ሰውነታቸውን ለእርሱ ለማስገዛት ፈቃደኛ ይሆናሉ።

በ1ኛ ቆሮንቶስ 2፡1 ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በመጀመሪያ ወደ እነርሱ ሲመጣ እንዴት እንደቀረባቸው የጻፈላቸውን እናገኛለን፡- *"እኔም፥ ወንድሞች ሆይ፣ ወደ እናንተ በመጣሁ ጊዜ በቃልና በጥበብ ብልጫ ለእግዚአብሔር ምስክርነቴን ለእናንተ እየነገርሁ አልመጣሁም። በመካከላችሁ ሳለሁ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር እርሱም እንደተሰቀለ ሌላ ነገር እንዳላውቅ ቆርጬ ነበርና።  እኔም በድካምና በፍርሃት በብዙ መንቀጥቀጥም በእናንተ ዘንድ ነበርሁ፤እምነታችሁም በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይሆን፣ ቃሌም ስብከቴም መንፈስንና ኃይልን በመግለጥ ነበረ እንጂ፣ በሚያባብል በጥበብ ቃል አልነበረም።"* ቃልን ብቻ እያጋነነ ወደ እነርሱ ያልመጣበትን ነገር ግን መንፈስን እና ሃይልን በመግለጥ ወደ እነርሱ የመጣበትን ምክንያት ግልጽ ሲያደርግላቸው እምነታቸው በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይሆን ነው ይላል።

ክርስትና አንድ ድንቅ አስተሳሰብ አለው። አንድ ጊዜ እውነትን ካወቃችሁ በኋላ፣ እስከ ዛሬ እንዴት እንዳለፋችሁትና ሌሎችም ይህን እውነት ማቀፍ እንዴት እንዳቃታቸው ትደነቃላችሁ። ክርስትና ግን አስተሳሰብ (Logic) ብቻ አይደለም… ይልቁንም ሕያው ከሆነ እግዚአብሔር ጋር ገሃድ የሆነ ወዳጅነትና ግንኙነት ነው። ዛሬም ሕያው ነው፣ እራሱን በቃሉ ውሰጥ በገለጠበት ሁኔታ ፍጹም በተመሳሳይ መልኩ  ዛሬም እራሱን በሃይል ሊገልጥ ይወዳል። ዕብራውያን 13፡8 *"ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለመምም ያው ነው"* ይላል። ኢየሱስ መጥቷል እርሱም በእኛ መካከል በምልክት፣ ድንቆች እና ተዓምራት በእግዚአብሔር የተመረጠ ሰው ነበር። የሐዋርያ ሥራ 10፡38 *"እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀባው፣ እርሱም መልካም*

*እያደረገ ለዲያብሎስም የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ፣ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረና፤”* ይላል። ኢየሱሱ እርግጠኛ ቃል ነበረው፣ ተዓምራቶችም ሰዎችን ወደ መልዕክቱ እንዲመጡ ለማድረግ የመጥሪያ ደወል ሆነው ያገለግላሉ። ተዓምራት እግዚአብሔርን ያከብራሉ። ብዙ ጥቅሶች እነዚህ ተዓምራት እግዚአብሔርን ስለማክበራቸው ይናገራሉ እናም ኢየሱስ ሰዎችን ለማገልገልና ህይወታቸውን ለመቀየር የመንፈስ ቅዱስን ሃይል ከተጠቀመ፣ እኛስ እርሱ ከሰራው የተሻለ መስራት እንችላለን ብለን እንዴት እናስባለን? ኢየሱስ ሰዎች መልዕክቱን ይሰሙ ዘንድ ወደ እርሱ እንዲመጡ ለማድረግ ተዓምራትን ከተጠቀመ፣ ልዕለ ተፈጥሮ በሆነው በእግዚአብሔር ሃይል ሳንጠቀም ዛሬ ላይ እኛስ ዓለምን ለማሳመን እንዴት እንሞክራለን? እውነቱ ያለው ተዓምራት እግዚአብሔርን የሚያከብሩ መሆናቸው ላይ ነው። ሰዎችን የመጥሪያ ደወል ናቸው። ልክ እንደ ምግብ ሰዓት ደወል መደወል ማለት ነው። ረሃባችሁን የሚያስታግሰው ምግቡ ቢሆንም ደወሉ ደግሞ እንድትመገቡ ያስታውሳችኋል። ያለ ማሳሰቢያ ደወል አንዳንድ ሰዎች የምግብ ሰዓታቸውን ይረሳሉ። ያለ እግዚአብሔር ተዓምራዊ ሃይል ብዙ ሰዎች እግዚአብሔር ስለመኖሩም ሆነ ልባቸውን መቀየር እንደሚችልና ኃጢአታቸውንም እንደሚምራቸው ሳያውቁ ያልፋሉ።

ግልጽ እንዲሆንላችሁና እንድታውቁት የማበረታታችሁ ጉዳይ እግዚአብሔር በእኛ በእያንዳንዳችን ውስጥ አልፎ እነዚህን ተዓምራት በእኛ በኩል የሌሎችን ሰዎች ሕይወት ለመቀየር መስራት ይፈልጋል። አንዳንዶቻችሁ ምናልባት “ለአንዳንድ ሰዎች ጸልዬላቸው ባይፈወሱ ምን ማድረግ እችላለሁ? ይሄ ያሰፈራኛል፣ የጸለይኩላቸው መፈጸም እንደሚችል እንዴት ማረጋጥ እችላለሁ?” ልትሉ ትችላላችሁ። ተዓምራቱን የምታደርጉት እናንተ እንዳልሆናችሁ መገንዘብ ያስፈልጋችኋል፤ እግዚአብሔር ነው። ተዓምሩ ተፈጽሞ አንድ ሰው ነጻ ቢወጣ ኃላፊነቱን የምትወስዱት እናንተ እንዳልሆናችሁ ሁሉ ተዓምሩ ሳይፈጸም ቢቀር ውግዘቱ እናንተ ላይ አይደርስም። ብቻ እናንተ ጸልዩ፣ ፈውሰን የሚያደርገው እግዚአብሔር ነው፤ ነገር ግን በእናንተ ውስጥ አልፎ መስራት አለበት። እግዚአብሔር በሚያስደንቅ ተዓምራዊ መንገድ ሊጠቀምባችሁ ይፈልጋል። ወደ እግዚአብሔር ቃል ሂዱና ቃሉን ተመልከቱ፣ እንዴት ለሌሎች እንደሰራ እጥኑ፣ እነዛን ነገሮች በሕይወታችሁ ላይ ማድረግን ተማሩና ተዓምራዊው ልዕለ ተፈጥሮ የእግዚአብሔር ሃይል ዛሬ በእናንተ በኩል መፍሰስ እንዲችል አድርጉ።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ተዓምር ምንድን ነው?

2. ማርቆስ 2፡10-12 ኢየሱስ የሚሰራቸው ተዓምራት ምን ለማድረግ ሃይል እንዳለው የሚያሳዩ ናቸው?

   **ማርቆስ 2፡10-12** *"ነገር ግን ለሰው ልጅ በምድር ላይ ኃጢአትን ሊያስተሰርይ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ፤ [11] ሽባውን። አንተን እልሃለሁ፥ ተነሣ፥ አልጋህን ተሸክምና ወደ ቤትህ ሂድ አለው። [12] ተነሥቶም ወዲያው አልጋውን ተሸክሞ በሁሉ ፊት ወጣ፥ ስለዚህም ሰዎች ሁሉ ተገረሙና። እንዲህ ያለ ከቶ አላየንም ብለው እግዚአብሔርን አከበሩ።"*

3. ማርቆስ 16፡15-18 አንብቡና እንደ አማኝ ምን ማድረግ አለብን?

   **ማርቆስ 16፡15-18** *"እንዲህም አላቸው። ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ። [16] ያመነ የተጠመቀም ይድናል፥ ያላመነ ግን ይፈረድበታል።[17] ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፤ እባቦችን ይይዛሉ፥[18] የሚገድልም ነገር ቢጠጡ አይጎዳቸውም፤ እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ።"*

4. የሐዋርያት ሥራ 8፡5-8 አንብቡና ሕዝቡ ያዩት ምንድን ነው፣ ምላሻቸውስ ምን ነበር?

   **የሐዋርያት ሥራ 8፡5-8** *"ፊልጶስም ወደ ሰማርያ ከተማ ወርዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው። [6] ሕዝቡም የፊልጶስን ቃል በሰሙ ጊዜ ያደርጋት የነበረውንምምልክት ባዩ ጊዜ፥ የተናገረውን በአንድ ልብ አደመጡ። [7] ርኵሳን መናፍስት በታላቅ ድምፅ እየጮኹ ከብዙ ሰዎች ይወጡ ነበርና፤ ብዙም ሽባዎችና አንካሶች ተፈወሱ፤ [8] በዚያችም ከተማ ታላቅ ደስታ ሆነ።"*

5. የሐዋርያት ሥራ 3፡12 ሐዋርያው ጴጥሮስ ተዓምር የተደረገው በእርሱ ጽድቅ አለመሆኑን ለማሳዬት ምን አለ?

   **የሐዋርያት ሥራ 3፡12** *"ጴጥሮስም አይቶ ለሕዝቡ እንዲህ ሲል መለሰ። የእስራኤል ሰዎች ሆይ፥ በዚህ ስለ ምን ትደነቃላችሁ? ወይስ በገዛ ኃይላችን ወይስ እግዚአብሔርን በመፍራታችን ይህ ይመላለስ ዘንድ እንዳደረግነው ስለ ምን ትኵር ብላችሁ ታዩናላችሁ?"*

6. የሐዋርያት ሥራ 3፡16 ተዓምራት እንዴት ይከሰታሉ?

   **የሐዋርያት ሥራ 3፡16** *"በሰሙም በማመን ይህን የምታዩትንና የምታውቁትን የእርሱ ስም አጸናው፥ በእርሱም በኩል የሆነው እምነት በሁላችሁ ፊት ይህን ፍጹም ጤና ሰጠው።"*

7. በአዲስ ኪዳን ከሐዋርያት ውጭ ተዓምራት የተከሱቱባቸው ጊዜያት ነበሩ?

8. 1ኛ ቆሮንቶስ 1፡7 ተዓምራት የማድረግ ስጦታዎች መቸ የሚቆሙ ይመስላችኋል?

   **1ኛ ቆሮንቶስ 1፡7** *"እንደዚህ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ ስትጠባበቁ አንድ የጸጋ ስጦታ እንኳ አይጎድልባችሁም፤"*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ተዓምር ምንድን ነው?
   **ተዓምር ማለት ልዩ የሆነ፣ ያልተለመደ መለኮታዊ እንደሆነ የሚታመን ክስተት ነው። በተጨማሪም ከተፈጥሮ ሕግ በላይ የሆነ ልዐለ ተፈጥሮ የእግዚአብሔር ሃይል ጣልቃ ገብነት ነው።**

2. ማርቆስ 2፡10-12 ኢየሱስ የሚሰራቸው ተዓምራት ምን ለማድረግ ሃይል እንዳለው የሚያሳዩ ናቸው?
   **ኃጢአትን ሊያስተሰርይ።**

3. ማርቆስ 16፡15-18 እንብቡና እንደ አማኝ ምን ማድረግ አለብን?
   **ወንጌልን መሰበክ፣ ያመኑትን ማጥመቅ፣ አጋንንትን ማውጣት፣ በአዲስ ቋንቋ (በልሳን) መናገር እና የታመሙትን መፈወስ።**

4. የሐዋርያት ሥራ 8፡5-8 አንብቡና ሕዝቡ ያዩት ምንድን ነው፣ ምላሻቸውስ ምን ነበር?
   **ተዓምራትን አይተዋል (ቁጥር 7)፣ በኢየሱስ አምነው በውሃ ተጠምቀዋል (ቁጥር 12)።**

5. የሐዋርያት ሥራ 3፡12 ሐዋርያው ጴጥሮስ ተዓምር የተደረገው በእርሱ ጽድቅ አለመሆኑን ለማሳዬት ምን አለ?
   **እግዚአብሔር እንጂ የእርሱ ጽድቅ ወይም ሃይል ሰውዬውን እንዳላደነው ተናገረ።**

6. የሐዋርያት ሥራ 3፡16 ተዓምራት እንዴት ይከሰታሉ?
   **በኢየሱስ ስም እና በእርሱ በማመን።**

7. በአዲስ ኪዳን ከሐዋርያት ውጭ ተዓምራት የተከሱቱባቸው ጊዜያት ነበሩ?
   **አዎ፤ ሰሙ ያልተጠቀሰ የክርስተስ ተከታይ )ማርቆሰ 9፡38-39)፣ ፊሊጶስ (የሐዋርያት ሥራ 8፡5-7)፣ እናንያሰ (የሐዋርያት ሥራ 9፡10-18)።**

8. 1ኛ ቆርንቶስ 1፡7 ተዓምራት የማድረግ ስጦታዎች መቸ የሚቆሙ ይመስላችኋል?
   **በጌታ ኢየሱሰ ምጽዓት ማለትም ዳግመኛ ሲመጣ።**

# ትምህርት 4

# የመልካም ግንኙነቶች ሃይል

## በዶን ክሮው

ዛሬ ደግሞ ስለ መልካም ግንኙነቶች እናወራለን። ልብ ብላችሁ ካስተዋላችሁ መጽሐፍ ቅዱስ ከጅማሬ እስከ ፍጻሜው በዚህ ርዕስ ዙሪያ ያወራል። “ቤተ ክርስቲያን” የሚለውን ቃል ለምሳሌ ብንወስድ በግሪክ ኤክሌዢያ ማለት ሲሆን ትርጉሙም “የተጠሩ ሰዎች ህብረት” ማለት ነው። ቤተ ክርስቲያን ወይም የእግዚአብሔር ህዝቦች እንዲገናኙ እና ህብረት እንዲያደርጉ የእግዚአብሔር ቃል በብዙ ሲያበረታታ ታያላችሁ። አንድ ላይ እንዲጸልዩ ይበረታታሉ ደግሞም በየቀኑ አንዳቸው ሌላውን እንዲደግፉና እንዲያጽናኑ ያበረታታቸዋል። አንድ ላይ በሚያደርጉት የሕይወት ጉዞ በመልካም ግንኙነቶች ሃይል ይበረታታሉ። “ሽማግሌ” የሚለውንም ቃል ካያችሁ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ሲሆን በእድሜ ጠና ያለውን፣ በእድሜ የበሰለውን፣ ዘመኑን ለክርስቶስ ያሰገዛ እና በቤተሰብና በትዳሩ ሁኔታ ስኬታማ የሆነ ሰውን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነው። በትዳሬ ችግር ቢያጋጥመኝ፣ በዘመኑ መልካም ጥበብን ወዳካበተ፣ መልካም ወደ ሆነው ሰው እሄዳለሁ።

በተጨማሪም የእግዚአብሔር ቃል የክርስቶስ አካል (The body of Christ) ብሎ የሚጠራው ህያው ሰውነት ያለው አካል መሆኑን ልናስተውል ይገባል። እጆች ያሉት፣ አይን እና ጆሮ፣ ሌሎች የአካል ክፍሎችም ያሉት ነው። እኛ ሁላችን አንዳችን የሌላው አካል ነን። አንዳችን የአንዳችን አካል ክፋይ እንደመሆናችንም አንዳችን ከሌላው ጥንካሬ እናገኛለን። እያንዳንዱ ጅማት፣ እያንዳንዱ የአካል ክፍል የራሱ ስጦታዎች፣ የራሱ ክህሎቶች፣ የራሱ የሆነ ጥንካሬን እና እውቀትን የሚሰጥበት መንገድ አለው።

መጽሐፍ ቅዱስ በያዕቆብ 5፡16 *“እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ። ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኀይል ታደርጋለች”* ይላል። ይህ ቃል በመልካም ግንኙነቶች ውስጥ ያለውን ኃይል በተመለከተ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ከምናገኛቸው ጥቅሶች እንደ ምሳሌ የሚጠቀስ ነው። በክርስቶስ አካል ውስጥ እየቀረ የመጣ አንድ ነገር አለ። አማኞች የእግዚአብሔር ካህናት በመሆናቸው አንዳቸው ወደ አንዳቸው ከሚሄዱ ይልቅ ወደ እግዚአብሔር በቀጥታ መቅረብ ይችላሉ የሚለውን እያጋነንን በመምጣታችን ምክንያት አንዳንድ ነገሮችን እያጣን ነው ብዬ አስባለሁ። መጽሐፍ ቅዱስ አንዳችን ለአንዳችን ስህተታችንን መናዘዝ እንደሚገባ ይናገራል። ዶ/ር ሎረን ልዊስ የሚባል ወዳጅ አለኝ። በእድሜ ጠና ያለ ደግ ሰው ሲሆን ብዙ ጊዜያት አብረን አሳልፈናል። የግሪክ ቋንቋ ምሑር ከመሆኑም በላይ የግሪክን ቋንቋ አጥርቶ ይናገራል። ከመጽሐፍ ቅዱስ አልገባህ ያለኝ ቃል ሲያጋጥመኝ የግሪኩ ምን ይላል ብዬ ወደ እርሱ እሄዳሁ። ስለ ቃላቱና በግሪክ ስላላቸው አገባብ እጠይቀዋለሁ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቴ እጅግ ብዙ ያግዘኛል። ከእርሱ ጋር ብዙ በጣም ብዙ ጊዜዎችን አሳልፌአለሁ። የጥበብ ሰው ነው። የእግዚአብሔር ሰው ነው። የመልካም ትዳር ባለቤትም ነው። ስኬታማ ቤተሰብ አለው። እናም ሁላችንም ስህተታችንን የምንናዘዝበት ጊዜ ይኖራል። እዚህ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ኃጢአታችንን ለእግዚአብሔር መናዘዝ እንደሚገባን የሚናገረውን አውቃለሁ እናም አንድ ሰው የኃጢአት ይቅርታን እንደሚያስገኝላችሁ አድርጋችሁ ኃጠአታችሁን ተናዘዙለት እያልኩ አይደለም፣ በእርግጥ በዚህ ጉዳይ መቅረብ የሚገባን ወደ እግዚአብሔር ነው። ነገር ግን በኑሮአችን ተጠያቂነት ሊኖረን ደግሞ ይገባል።

የመልካም ግንኙነት ኃይል ኖረን ማለት ለተጠያቂነት የሚያስፈልገን እና ጌታን እንድንፈልግ ያበረታታን ዘንድ ሰው እኛን ለመርዳት የሚያስችለውን ኃይል አገኘን ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በዕብራውያን መልዕክት፣ አንዳችን ሌላውን በየዕለቱ መምከር እንደሚገባን ይናገራል፣ መሰብሰባችንን እንዳንተው፣ አንዳችን ሌላውን ማጽናናት እንደሚያስፈልገን፣ በኃጢአት ማታለል ምክንያት ልባችን እንዳይደነድን አንዳችን ሌላውን ማስጠንቀቅ እንደሚገባን ይናገራል። ይህ ሁሉ የሚናገረው የመልካም ግንኙነቶችን ኃይል አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ነው። በሌላ በኩል በተቃራኒው መጽሐፍ ቅዱስ መልካም ያልሆኑ ግንኙነቶች የሚያስከትሉትን ጉዳት በተመለከተ እጅግ ብዙ ጊዜ

የሚያሰጠነቅቀን ሲሆን መልካም ያልሆኑ ግንኙነቶች በህሊናችን እና አዕምሮአችን ወይም አስተሳሰባችን ላይ ስለሚያሳድሩት ተጽዕኖም ይናገራል። ከማወቃችን በፊት ሳናስተውል፣ አስፈላጊ ወዳልሆኑ ነገሮች ተነድተን እራሳችን ባላስፈላጊ ሁኔታ ላይ የምናገኝበት ጊዜ አለ፣ ይህ የሚሆነው እራሳችንን በመልካም ወይም እንደ እግዚአብሔር ባለ ምክር ባለመጠበቃችንና ቅጥር ባለመሰራታችን ምክንያት ነው (ምሳሌ 11፡14፣ 13፡20 እና 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡33)። መጽሐፍ ቅዱስ በ2ኛ ቆሮንቶስ 6፡14 *"ጽድቅ ከኃጢት ጋር ምን መጋጠም አለው"* ሲል ይናገራል።

በክርስትና የሕይወት ጉዟችሁ መልካም ግንኙነቶች ዙሪያችሁን እንዲኖሯችሁ በርትታችሁ ፈልጉ፣ በተቃራኒ መንገድ ተፅዕኖ ከሚያሳድሩባችሁ ሽሹ። በሕይወታችን እራሳችንን መሳል ወይም መቅረጽ (ምሳሌ 27፡17) እንችል ዘንድ የሚጠቅሙና ተጠያቂነትም እንዲኖረን የሚያደርጉ መልካም የሆኑ አማኞች ወዳጆች ቢኖሩን መልካም ነው። በእነዚህ ነገሮች ዙሪያ ማሰብና ማሰላሰላችሁን ስትቀጥሉ እግዚአብሔር በብዙ አብዝቶ ይባርካችሁ።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. 1ኛ ቆሮንቶስ 15:33 ይህ ቃል ግንኙነቶችን በተመለከተ ምን ያስተምረናል?

   **1ኛ ቆሮንቶስ 15:33** *"አትሳቱ፤ ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል።"*

2. 1ኛ ቆሮንቶስ 12:12 ይህ ቃል ስለ ክርስትና ሕይወታችን ምን ያሳየናል?

   **1ኛ ቆሮንቶስ 12:12** *"አካልም አንድ እንደ ሆነ ብዙም ብልቶች እንዳሉበት ነገር ግን የአካል ብልቶች ሁሉ ብዙዎች ሳሉ አንድ አካል እንደ ሆኑ፥ ክርስቶስ ደግሞ እንዲሁ ነው፤*

3. ዕብራውያን 10:24 አንብቡና ስለ መልካም ግንኙነቶች ከዕብራውያን 10:24 ምን እንማራለን?

   **ዕብራውያን 10:24** *"ለፍቅርና ለመልካምም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ፤"*

4. ዕብራውያን 10:25 ስለ መልካም ግንኙነቶች ከዚህ ቃል ምን እንማራለን?

   **ዕብራውያን 10:25** *"በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደ ሆነው፥ መሰብሰባችንን አንተው እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ፤ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ።"*

5. ምሳሌ 5:22-23 ልባችን መልካም ካልሆኑ ግንኙነቶች መጠበቅ ያለብን ለምንድን ነው?

   **ምሳሌ 5:22-23** *"ኃጥኣንን ኃጢአቱ ታጠምደዋለች፥ በኃጢአቱም ገመድ ይታሰራል። [23] አልተቀጣምና እርሱ ይሞታል፤ በስንፍናውም ብዛት ይስታል።"*

6. 2ኛ ጢሞቴዎስ 2:22፣ ጽድቅን፣ እምነትን፣ ፍቅርን እና ሰላምን ከማን ጋር መከተል አለብን?

   **2ኛ ጢሞቴዎስ 2:22** *"ከክፉ የጎልማሳነት ምኞት ግን ሽሽ፥ በንጹሕም ልብ ጌታን ከሚጠሩ ጋር ጽድቅን እምነትን ፍቅርን ሰላምን አጥብቀህ ተከተል።"*

7. ዕብራውያን 13:7፣ ማንን ማስታወስና በህይወታችን ለመምሰል መጣር አለብን?

   **ዕብራውያን 13:7** *"የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋናቻችሁን አስቡ፥ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው።"*

# ጠቋሚ መልሶች

1. 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡33 ይህ ቃል ግንኙነቶችን በተመለከተ ምን ያስተምረናል?
   **ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል።**

2. 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡12 ይህ ቃል ስለ ክርስትና ሕይወታችን ምን ያሳየናል?
   **እንደ ሰውነታችን አካል ክፍሎች ሁሉ፣ ሌሎች የክርስቶስ አካል ክፍሎችም ያስፈልጉናል።**

3. ዕብራውያን 10፡24 እንብቡና ስለ መልካም ግንኙነቶች ከዕብራውያን 10፡24 ምን እንማራለን?
   **በመልካም ግንኙነት ውስጥ ያሉ በፍቅርና በመልካም ሥራ ሌሎችን ያነቃቃሉ።**

4. ዕብራውያን 10፡25 ስለ መልካም ግንኙነቶች ከዚህ ቃል ምን እንማራለን?
   **በአንድነት መሰብሰብ፣ ህብረት እና እንዳችን እንዳችንን ማበርታት ያሰፈልገናል።**

5. ምሳሌ 5፡22-23 ልባችን መልካም ካልሆኑ ግንኙነቶች መጠበቅ ያለብን ለምንድን ነው?
   **በሰንፍናችን ብዛት እንዳንስት (ቁጥር 23)።**

6. 2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡22፣ ጽድቅን፣ እምነትን፣ ፍቅርን እና ሰላምን ከማን ጋር መከተል አለብን?
   **በንጹሕ ልብ ጌታን ከሚጠሩ ጋር።**

7. ዕብራውያን 13፡7፣ ማንን ማስታወስና በህይወታችን ለመምሰል መጣር አለብን?
   **የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን መሪዎቻችሁን።**

# ትምህርት 5

# ተቃውሞና ስደት

## በዶን ክሮው

በማቴዎስ 10፡16-23፣ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ለሚገጥማቸው ተቃውሞ እንዲዘጋጁ እያደረጋቸው ነበር፤ ተቃውሞ እንደሚመጣ እንዲያውቁ ይፈልጋል። በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ የሚኖሩ ሁሉ ይሰደዳሉ (2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡12)። ይህ የምትገሰጹት ነገር አይደለም። ጠላትም ከጀርባ ሆኖ ይሰራ ይሆናል፣ ነገር ግን ተቃውሞና ስደት ለጽድቅ የመቆማችሁ አንዱ አካል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በክርስቶስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ የሚኖሩ ሁሉ ይሰደዳሉ ይላል። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን *"እነሆ፣ እኔ እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ፤"* (ማቴዎስ 10፡16) ሲል እንዲዘጋጁ ይነግራቸዋል። "እነሆ" የሚለው ቃል "ልብ ብላችሁ አድምጡኝ፣ በደምብ አስተውሉ እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ፣ ይህን ማስታወስ ይኖርባችኋል" ማለት ነው። በጎች ምንም መከላከያ የሌላቸው ምስኪን እንስሶች ናቸው። በግ - የሚናከስበት ስለታም ጥርስም ሆነ እንደ እባብ መርዝ የለውም - እራሱን የሚከላከልበት ምንም አይነት መከላከያ የለውም። ያለው ብቸኛ መከላከያ የበጉ እረኛ ነው።

የበጎች እረኛ ዋነኛ ተግባሩ በጎቹን ከነጣቂ ተኩላ መጠበቅ ሲሆን ኢየሱስ ግን በተቃራኒው፡ "እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ" እያላቸው ነው። አያስገርምም? ይህን የተናገረበት ዋናው ምክንያት ግን ለሚነሳባቸው ተቃውሞ እንዲዘጋጁ ለማድረግ ነው። ኤፌሶን 6፡12 *"መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፣ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።"* ተቃውሞ እና ስደት አይቀርም። የክርስትና ሕይወት አንዱ መለያ ነውና፣ ኢየሱስም ይህን እንድታውቁ ይፈልጋል። ለዚህ እንድትዘጋጁም *"እንደ እባብ ብልህ ሁኑ"* (ማቴዎስ 10፡16) ይላል። ይህ "ብልህ" የሚለው ቃል ልባም፣ በማንኛውም ሁኔታ ችግር ውስጥ የማይገባ አስተዋይና በጥበብ የሚራመድ ማለት ሲሆን እንደ እባብ ብልህ እንደ እርግብም የዋህ ሁኑ የሚለው ለዚህ ነው።

በመቀጠልም እንዲህ ይላል *"ከሰዎች ተጠበቁ፣"* (ማቴዎስ 10፡17)። ጠላት ሰዎችን ይጠቀማል። ኤፌሶን 2፡2 *"በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሰራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ"* በሚል ማን እንዳለ ይናገራል። እኛን ለመቃወም፣ የኢየሱስ ክርስቶስንም ስራ ለመቃወምና የእግዚአብሔርንም ቃል ለመቃወም ሰይጣን ሰዎችን ይጠቀማል። *"ነገር ግን ወደ ሸንጎ አሳልፈው ይሰጡአችኋል፥ በምኩራቦቻቸውም ይገርፉአችኋልና ከሰዎች ተጠበቁ፤"* (ማቴዎስ 10፡17)። ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮንቶስ 11፡23-24 መልዕክቱ *"ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መልዕክት፣ ደግሞም ስለ ወንጌል መልዕክት ስል አምስት ጊዜ ተደበደብኩ፣ ሰላሳ ዘጠኝ ግርፋት አምስት ጊዜ ተገረፍኩ፣"* ይላል። ኢየሱስም ወደ ገዥዎች ፊት ያቀርቧችኋል ይላል - የኢየሱስ ክርስቶስን ስራ ለመቃወም መንግስትም ቢሆን አልፎ አልፎ የሚነሳበት ጊዜ ይኖራል። በኢየሱስ ምክንያት በገዥዎች እና በነገስታት ፊት የምትቀርቡበት ጊዜ የሚኖር ሲሆን፣ ይህም ለእነርሱ ወይም በእነርሱ ላይ ለምስክር ይሆንባቸዋል።

በአንድ ወቅት፣ በወንጌላዊነት ዙሪያ በደብዳቤ የወንጌል መልዕክትም ሆነ የራሳቸውን ምስክርነት ለማያምኑ ሰዎች እንዴት ማስተላለፍ እንደሚችሉ ተማሪዎችን እያስተማርኩ ነበር። እኔ ራሴ አንድ መልዕክት በማዘጋጀት ከሃምሳ እስከ መቶ ለሚደርሱ ሰዎች ደብዳቤዎችን ላዕኩ። ይህ ከሆነ ከጥቂት ቀን በኋላ እዛው ከተማ ውስጥ ከምትኖር ሜሪ አን ከተባለች ሴት ስልክ ተደወለልኝ። እርሷም ደውላ "እንዲህ በቀላሉ የምንላቀቅ እንዳይመስልህ፣ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ልትነግረኝ አትችልም (አልፈልግም)፣ አልለቅህም። ለመሆኑ ስሜን ከየት ነው ያገኘኸው?" ስትል በቁጣ ጠየቀችኝ። እኔም "ስምሽን ከስልክ ማውጫ መጽሐፍ ላይ ነው ያገኘሁት" አልኳት። እርሷም "ውሸታም፣ ስሜም ሆነ አድራሻዬ በስልክ ማውጫ ላይ የለም" አለች። "እኔ ግን ያገኘሁት እዛ ነው" አልኳት ተረጋግቼ። እርሷ "ነገ ፖሊሶች እንዲያናግሩህ አደርጋለሁ" ብላኝ ዘጋች። እኔም መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው እውነት ነው ማለት ነው? ስል አሰብኩ። በበነጋታው ፖሊሶች ወደ እኔ መጥተው ለሁለት ሰዓት ያህል በጥያቄና መልስ ሲመረምሩኝ ቆይተው ሄዱ።

ምን የሞል ይመስላችኋል? እውጭ በየጎዳናው ብዙ ወንጀለኛ ሞልቶ ፖሊሶች ግን ከእኔ ጋር ሁለት ሰዓት ሙሉ ያባክናሉ። ለምን? ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ስለ ወንጌል። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል እውነት ነው ማለት ነው? በእግዚአብሔር ቃል ላይ ከቆማችሁ፣ ለመመስከር ከደፈራችሁ፣ ኢየሱስን ለማወጅ ካልፈራችሁ፣ በሰዎች ፊት በጽድቅ ለመኖር ከደፈራችሁ፣ ተቃውሞ ይኖራል። የክፉ ሃይሎች አሉ፣ የመልካም ሃይሎችም አሉ። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ እንዲዘጋጁ ይፈልጋል።

በማቴዎስ 10፡19 *"አሳልፈውም ሲሰጡአችሁ፥ የምትናገሩት በዚያች ሰዓት ይሰጣችኋልና እንዴት ወይስ ምን እንድትናገሩ አትጨነቁ፤"።* በእግዚአብሔር መንፈስ፣ ያ የጥንቱ ጥበብ እንደ እስጢፋኖስ ይሰጣችኋል። እርሱ የተናገረበትን ጥበብ ሕዝቡ ሊሸከሙት የሚችሉት አልነበረም። ኢየሱስ በመቀጠል በቁጥር 22-23 እንዲህ ይላል *"በሁሉም ስለ ስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ፤ እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል። በአንዲቱ ከተማም መከራ ቢያሳዩአችሁ ወደ ሌላይቱ ሽሹ፤"* ቃሉን የምትሰሙ ብቻ ሳትሆኑ የምታደርጉ ከሆናችሁ ተቃውሞ ስለ ጽድቅ፣ ተቃውሞ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ የማይቀርና ያለ ነው።

በአንድ ወቅት አንድ መናፈሻ ውስጥ ሳለሁ አንዲት በእድሜ የገፋች ሴት ብቻዋን ተቀምጣ አየሁ። መቸም ትልቅ ሰው ነችና የምነግራትን ረጋ ብላ ታዳምጣለች፣ አትጣላኝም ልትጎዳኝም አትችልም፣ ብዬ አሰብኩና አጠገቧ ለመቀመጥ ፈቃድ ጠይቄ ተቀመጥኩና ወሬ ጀመርኩ። ስሟ ጄን ነበረ "ለመሆኑ ስራሽ ምንድን ነው፣ ጄን?" ስል ከተዋወቅን በኋላ ጠየኳት። "አሮጊት ነኝ እኮ፣ በዚህ እድሜዬ ምን እሰራለሁ፣ ጡረተኛ ነኝ" አለችና "በነገራችን ላይ አንተስ ስራህ ምንድን ነው?" ስትል ረጋ ብላ ጠየቀችኝ። "በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የወንጌል ሚሽነሪ ድርጅት ውስጥ አገለግላለሁ" ስል ነገርኳት። ፊቷ በአንዴ ተቀያየረ። "ስለ እግዚአብሔር ምንም ነገር እንድትነግረኝ አልፈልግም፣ ስለ ኢየሱስ ምንም መስማት አልፈልግም" አለች። እኔም ተረጋግቼ "እንዴ ጄን፣ እንዲህ አይባልም" አልኳት፤ እርሷ ግን "ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ፊቴ ላይ ቢቆም እንኳን ምራቄን እተፋበት ነበር" አለች። "ጄን፣ እንዲህ ማለት እንኳን አልነበረብሽም፣ ምናልባት በነበርሽበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ሰዎች ያደረሱብሽ በደል ይሆናል እንዲህ እንድትናገሪ ያደረገሽ። እንዲህ መናገር ግን አልነበረብሽም። ቆይ እንዲያውም ስለ እኔ ቤተሰብ ላጫውትሽ" አልኳት፣ እርሷ ግን "አልፈልግም፣ አታናግረኝ ብዬሃለሁ። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እና እግዚአብሔር በቤተሰብህ ስላደረገው ነገር ልትነግረኝ ፈልገህ ነው፣ አልሰማህም፣ አትንገረኝ" ስትል አቋረጠችኝ። እኔም "እባክሽ ጄን፣ ስለ ኢየሱስ ልነግርሽ የሚገቡ ነገሮች አሉ" አልኳት። "አልፈልግም ብዬሃለሁ፣ ዝጋ! በቃህ" አለች።

ከንዴቷ ብዛት የተነሳ እንገቱ ላይ በተንጠለጠለ ገመድ ሲጫወት የነበረውን ውሻዋን፣ ስትጎትተው እርሱም እንደ እርሷ በቁጣ እያጉረመረመ፣ እየጎተተችው ሄደች። እኔም ርቃ እስክትሰወር ድረስ በዓይኔ ተከተልኳት። እንግዲህ መንፈስ ከቁጥጥር ውጭ እስክትሆን ድረስ የተነሳባት፣ የእምቢተኝነት መንፈስ ያለባት እንዲህ አይነት ሴት አለች። በጠላት ቁጥጥር ስር ሆናለች። ለራሴ ሰዎች ሲጮሁብኝ የምወድ ዓይነት ሰው አይደለሁም፣ ማንም በፊቴ እንዲህ ሲናገር ዝም የምልም አልነበርኩም አልኩ፤ ለጄን ግን ከብዙ ርህራሄ፣ ከብዙ ፍቅር ውጭ ሌላ የተሰማኝ ስሜት አልነበረም። እርሷ ከቁጥጥር ውጭ ሆና ነበር፣ እኔ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ራሴን ተቆጣጥሬ ነበር። ወደ ቤት ሄድኩና እንዲህ አልኩ "ጌታ ሆይ፣ ምን እንዳስተዋልኩ ታውቃለህ? ሰው እንዲህ ፊት ለፊት በተጋፈጠኝ ጊዜ እኔ ግን ሁሉንም መቆጣጠር መቻሌ ታላቅ ተዓምር ነው፣ ከፍቅርና ርህራሄ በቀር ምንም አልተሰማኝም ነበር" አልኩ።

የኢየሱስን ስም ይዛችሁ ስትወጡ ምንጊዜም ተቃውሞና ስደት ይመጣል። በእርሱ ምክንያት እየተገፋችሁና እየተጠላችሁ እንኳን ኢየሱስን እንድትመሰክሩ ድፍረትን የሰጣችሁ ያው የእግዚአብሔር መንፈስ በማንኛውም ሁኔታ ብንሆን እንክብካቤና ጥንካሬ ይሰጠናል።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡12 እግዚአብሔርን እየመሰሉ የሚኖሩ ሁሉ ምን ያጋጥማቸዋል?

   **2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡12** *“በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ።”*

2. “ስደት”ን እንዴት ትገልጹታላችሁ?

3. ማርቆስ 4፡16-17 መከራ እና ስደት የሚደርሰው በምን ምክንያት ነው?

   **ማርቆስ 4፡16-17** *“እንዲሁም በጭንጫ ላይ የተዘሩት እነዚህ ናቸው፥ ቃሉንም ሰምተው ወዲያው በደስታ ይቀበሉታል፥[17] ለጊዜውም ነው እንጂ በእነርሱ ሥር የላቸውም፥ ኋላም በቃሉ ምክንያት መከራ ወይም ስደት በሆነ ጊዜ ወዲያው ይሰናከላሉ።”*

4. የሐዋርያት ሥራ 8፡1 እና 4፣ በኢየሩሳሌም የደረሰው ስደት በምን ምክንያት ነው?

   **የሐዋርያት ሥራ 8፡1** *“በዚያን ቀንም በኢየሩሳሌም ባለች ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ሆነ፤ ሁሉም ከሐዋርያትም በቀር ወደ ይሁዳና ወደ ሰማርያ አገሮች ተበተኑ።”*

5. የሐዋርያት ሥራ 8፡4 “የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ።”

6. ማቴዎስ 5፡10-12 ስለ ________________ የሚሰደዱ ብጹአን ናቸው።

   **ማቴዎስ 5፡10-12** *“ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው፥ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና። [11] ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ። [12] ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ፥ ሐሴትም አድርጉ፤ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያትን እንዲሁ አሳድደዋቸዋልና።”*

7. ማቴዎስ 5፡12 ፣ ስለ ጽድቅ አማኞች በሚሰደዱበት ጊዜ ወደ ፊት ምን መጠበቅ ይኖርባቸዋል?

8. የሐዋርያት ሥራ 9፡4-5፣ ሳውል ማንን ነበር የሚያሳድደው?

   **የሐዋርያት ሥራ 9፡4-5** *“በምድርም ላይ ወድቆ ሳለ። ሳውል ሳውል፥ ስለ ምን ታሳድደኛለህ? የሚለውን ድምፅ ሰማ።[5] ጌታ ሆይ፥ ማን ነህ? አለው። እርሱም። አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ፤ የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብሰብሃል አለው።”*

9. የሐዋርያት ሥራ 9፡1፣ በጊዜው ሲታይ ግን ሳውል ማንን እያሳደደ ነበር?

   **የሐዋርያት ሥራ 9፡1** *“ሳውል ግን የጌታን ደቀ መዛሙርት እንዲገድላቸው ገና እየዛተ ወደ ሊቀ ካህናት ሄደ፥”*

10. ገላትያ 6፡12 በገላትያ መጽሐፍ ላይ የምናያቸውና ሰውን አይሁድ ለማድረግ በወንጌል ላይ የሐይማኖት

ሕግን ለመጨመር የሚሞክሩ ሁሉ፣ ይህን በማድረጋቸው ምን አስወግደዋል?

**ገላትያ 6፡12** *“በሥጋ መልካም ሆነው ሊታዩ የሚወዱ ሁሉ እንድትገረዙ ግድ አሉአችሁ፥ ነገር ግን ስለ ክርስቶስ መስቀል እንዳይሰደዱ ብቻ ነው።”*

# ጠቋሚ መልሶች

1. 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡12 እግዚአብሔርን እየመሰሉ የሚኖሩ ሁሉ ምን ያጋጥማቸዋል?
   **ስደት።**

2. “ስደት”ን እንዴት ትገልጹታላችሁ?
   **ማንቋሸሽ፣ በእምነት ምክንያት ማሰቃዬት።**

3. ማርቆስ 4፡16-17 መከራ እና ስደት የሚደርሰው በምን ምክንያት ነው?
   **በቃሉ ምክንያት፣ ማለትም ቃሉን ለመንጠቅ።**

4. የሐዋርያት ሥራ 8፡1 እና 4፣ በኢየሩሳሌም የደረሰው ስደት በምን ምክንያት ነው?
   **ሰዎች ቃሉን በየቦታው በመሰበካቸው ምክንያት።**

5. ማቴዎስ 5፡10-12 ስለ __________________ የሚሰደዱ ብጹአን ናቸው።
   **ስለ ጽድቅ።**

6. ማቴዎስ 5፡12፣ ስለ ጽድቅ በሚሰደዱበት ጊዜ፣ አማኞች ወደ ፊት ምን መጠበቅ ይኖርባቸዋል?
   **በሰማይ ታላቅ ሽልማት።**

7. የሐዋርያት ሥራ 9፡4-5፣ ሳውል ማንን ነበር የሚያሳድደው?
   **ኢየሱስን።**

8. የሐዋርያ ሥራ 9፡1፣ በጊዜው ሲታይ ግን ሳውል ማንን እያሳደደ ነበር?
   **የጌታ ደቀ መዛሙርትን (ክርስቲያኖችን)።**

9. ገላትያ 6፡12 በገላትያ መጽሐፍ ላይ የምናያቸውና ሰውን አይሁድ ለማድረግ በወንጌል ላይ የሐይማኖት ሕግን ለመጨመር የሚሞክሩ ሁሉ፣ ይህን በማድረጋቸው ምንን አሰወግደዋል?
   **ለክርሰቶስ መሰቀል መከራ መቀበልን፣ በሌላ አነጋገር መዳን በክርስቶስ በማመን በጸጋ የሚገኝ መሆኑን በመሰበክ የሚመጣባቸውን ሰደትና መከራ አሰወግደዋል።**

# ትምህርት 6

# ንጉሡና መንግሥቱ

## በዶን ክሮው

በብሉይ ኪዳን እስራኤልን ከሌሎች አገሮች ልዩ ያደርጋት የነበረው መንግስቷበእግዚአብሔር የሚመራ ወይም (Theocracy) መሆኑ ነበር። በሌላ አነጋገር እግዚአብሔር እስራኤልን በቀጥታ ይመራ ነበር (ኢሳይያስ 43:15)። ቆይተው ግን እስራኤል በታሪካቸው እንደ ሌሎች ሕዝቦች በምድራዊ ንጉስ መመራት ፈለጉ (1ኛ ሳሙኤል 8:5-19)። ስለዚህ እግዚአብሔርም የፈለጉትን ሊሰጣቸው ፈቃዱ ሆነና ሳኦል የተባለ ሰው መርጦ አነገሠላቸው (1ኛ ሳሙኤል 10:24-25)። በኋላ ግን በሳኦል አለመታዘዝ ምክንያት፣ እግዚአብሔር እንደ ልቡ የሆነውን፣ ዳዊትን ንጉሥ ይሆን ዘንድ አስነሳ (የሐዋርያት ሥራ 13:21-22 እና 1ኛ ነገሥት 15:3)።

ንጉሡ የማይታየው አምላክ የሚታይ  እንደራሴ ወይም ወኪል ነው (ዘዳግም 17:14-20)። ንጉሡ እግዚአብሔርን የሚከተል ንጉሥ ከሆነ እርሱም መንግስቱም ይበለጽጋሉ። ሆኖም በተቃራኒው ንጉሡ እግዚአብሔርን የማይከተል ከሆነ ደግሞ እርሱም መንግስቱም በጭቆና ስር ይወድቃሉ፣ ጥፋትም ያገኛቸዋል (1ኛ ሳሙኤል 15:22-23)።

እግዚአብሔር ንጉሥ ሲመርጥ፣ የመረጠውን ንጉሥ ዘይት እንዲቀባለት ነብይ ይልካል። ይህም (ቅባት) የሚመራበትን ሃይልና ቅባት ለመስጠት የመንፈስ ቅዱስን መምጣት የሚያመላክት ነበር። በዚህ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለሆነ፣ መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ላይ ይመጣና በጽድቅ ይመራ ዘንድ ልቡን ይቀይራል (1ኛ ሳሙኤል 10:1፣6-7 እና 9)። መሲህ የሚለው ሃሳብ የመጣው ከዚህ ለመሪነት መቀባት (ንጉሥ መሆን) ከሚለው ሃሳብ ነው። “ቅባት” የሚለው ቃል በዕብራይስጥ mashiac (Messiah) ወይም መሲህ ማለት ሲሆን በግሪክ ቋንቋ ደግሞ christos ወይም ክርስቶስ በሚል ተተርጉሟል። የብሉይ ኪዳን ነቢያት ወደፊት መሲሁ (የተቀባው) ይመጣል፣ እርሱ ሲመጣም የሰማይ አምላክ የማይናወጥ የጸና መንግሰትን ያቋቁማል ብለው ተንብዩዋል (ዳንኤል 2:44፣ 7:14 እና 27)። ቃሉን ካሰተዋላችሁ ኢየሱስ ለአይሁድ ሰለ መንግሰቱ ሲናገር ምን ማለቱ እንደሆነ በየትም ቦታ ማብራሪያ ሲሰጣቸው አናይም። እነርሱ እራሳቸው በብሉይ ኪዳን ይፈልጉት የነበረ ሃሳብ ነበርና (ኢሳይያስ 9:6-7፣ 11:1-6፣፤ ዳንኤል 2:44፣ 7:13-14፣ 18 እና 27)።

የመንግሥቱን መሰረታዊ ዋና ሃሳብ በትክክል መረዳት ሳይቻል የኢየሱስን መልዕክት በትክክል መረዳት አይቻልም። ኢየሱስ ይናገር የነበረውም መልዕክቱም ሰለ መንግሥቱ ሲሆን ደቀ መዛሙርቱንም የላካቸው ይህን (መንግሰቱን) ብቻ እንዲሰብኩ ነበር (ማርቆስ 1:14-15፣ ሉቃስ 9:1-2፣ የሐዋርያት ሥራ 28:23-31፣ ሉቃስ 16:16 እና ማቴዎስ 24:14)። በተጨማሪም ይህ መልዕክት “መዳን” ወይም “የዘላለም ሕይወት” ስጦታ ተብሎ ይታወቃል (ዕብራውያን 2:3፣ ማቴዎስ19:16 ንጽጽር ከ ማቴዎስ 19:23 ጋር፣ የሐዋርያት ሥራ 28:23-24፣ 28 እና 30-31)። “የእግዚአብሔር መንግስት” በሚለው አነጋገር ውስጥ በእግዚአብሔር የሚመሩ ሕዝቦች ሰብሰብ የሚለው ሃሳብ ይገኛል። ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባት ሊሟሉ የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች አሉ። የልብ መለወጥ ያሰፈልጋል። ይህን የልብ ለውጥ መጽሐፍ ቅዱስ ንስሐ በማለት ይጠራዋል። ልባችን ለውጠን ወደ እግዚአብሔር መመለስ ማለት ሲሆን ይህም ከሰይጣን፣ ከኃጢአትና ከመንገዱ ዞር በማለት ወደ እግዚአብሔር፣ ወደ ክርሰቶስ እና ወደ መንገዱ ማቅናት፣ መመለስ ማለት ነው። አንድ ሰው ሲመለስ፣ እግዚአብሔር ስጦታ አድርጎ (በክርሰቶስ ኢየሱስ በፈሰሰው ደም) የኃጢአት ይቅርታን እና የዘላለምን ሕይወት ይሰጠዋል (ሮሜ 6:23)። ይህ “የምስራች” በሌላ አጠራሩ “የጸጋ ወንጌል” ወይም ደግሞ “የእግዚአብሔር መንግሰት” ሰብከት በመባል ይታወቃል (የሐዋርያት ሥራ 20:24-25)። የእግዚአብሔር መንግሰት የሚታወቅበት ባህሪ ጸጋ ሲሆን (ማቴዎስ 20:1-16) የተገለጠውም በጸጥታ እና በምስጢር በኢየሱስ አገልግሎት ነው (ማቴዎስ 13:33)። ወደፊት ግን አንድ ቀን በብዙ ክብር ፍጹም በሙላት ተገልጦ ይታያል።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ዳንኤል 2፡44 አንብቡ። የብሉይ ኪዳን ነቢያት ወደፊት መሲሑ (የተቀባው) ይመጣል፣ የሰማይ አምላክም ያቋቁማል ብለው የተነበዩት መንግስት፤

    ሀ. ለአንድ ሽህ አመት የሚቆይ፣
    ለ. ምን ግዜም የማይጠፋ
    ሐ. ጊዜያዊ መንግስት

    **ዳንኤል 2፡44** *"በእነዚያም ነገሥታት ዘመን የሰማይ አምላክ ለዘላለም የማይፈርስ መንግሥት ያስነሣል፤ ለሌላ ሕዝብም የማይሰጥ መንግሥት ይሆናል፤ እነዚያንም መንግሥታት ሁሉ ትፈጫቸዋለች ታጠፋቸውማለች፥ ለዘላለምም ትቆማለች።"*

2. ማቴዋሰ 4፡17፣ 23 የኢየሱስ መልዕክት ምንድን ነው?

    **ማቴዋሰ 4፡17** *"የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሆነ። ከዚያ ዘመን ጀምሮ ኢየሱስ። መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያለ ይሰብክ ጀመር።*

    **ማቴዋሰ 4፡23** *"ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ በገሊላ ሁሉ ይዞር ነበር።"*

3. ማርቆሰ 1፡14-15 ኢየሱስ የሰበከው የ________________ ወንጌልን ነበር።

    **ማርቆሰ 1፡14-15** *"ዮሐንስም አልፎ ከተሰጠ በኋላ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል እየሰበከና። ዘመኑ ተፈጸመ የእግዚአብሔርም መንግሥት ቀርባለች ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ እያለ ወደ ገሊላ መጣ።"*

4. ሉቃስ 4፡43 ኢየሱስ ከእግዚአብሔር የተላከበት ምክንያት ________________ ነበር።

    **ሉቃስ 4፡43** *"እርሱ ግን። ስለዚህ ተልኬአለሁና ለሌሎቹ ከተማዎች ደግሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል እሰብክ ዘንድ ይገባኛል አላቸው።"*

5. ዮሐንስ 4፡25፣ አንብቡና በመጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር መንግስት በሚናገርበት ጊዜ ምን ማለት እንደሆነ ለአይሁድ ሲያብራራላቸው አናይም። ይህ በብሉይ ኪዳን የነበረ ሃሳብ ሲሆን እነርሱም፦

    ሀ. በጥቂቱ የሚያውቁት ነው፣
    ለ. ይፈጸማል ብለው አያሰቡም፣
    ሐ. የሚጠብቁት ጉዳይ ነበር፣

    **ዮሐንስ 4፡25** *"ሴቲቱ። ክርስቶስ የሚባል መሲሕ እንዲመጣ አውቃለሁ፤ እርሱ ሲመጣ ሁሉን ይነግረናል አለችው።"*

6. ሉቃስ 9፡1-2 አሰራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ያደረጓቸው ሦሥት ነገሮች ምንድን ናቸው?

**ሉቃስ 9:1-2** *"አሥራ ሁለቱንም ሐዋርያት በአንድነት ወደ እርሱ ጠርቶ በአጋንንት ሁሉ ላይ ደዌንም ይፈውሱ ዘንድ ኃይልና ሥልጣን ሰጣቸው፤ [2] የእግዚአብሔርንም መንግሥት እንዲሰብኩና ድውዮችን እንዲፈውሱ ላካቸው፥"*

7. ሉቃስ 10:1-2፣ 8-9 ሰባዎቹን ኢየሱስ ምን እንዲያደርጉ ላካቸው?

**ሉቃስ 10:1-2** *"ከዚህም በኋላ ጌታ ሌሎቹን ሰብዓ ሾመ፣ ሁለት ሁለትም አድርጎ እርሱ ሊሄድበት ወዳለው ከተማና ስፍራ ሁሉ በፊቱ ላካቸው። [2] አላቸውም። መከሩስ ብዙ ነው፣ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤ እንግዴህ የመከሩን ጌታ ለመከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት።"*

**ሉቃስ 10:8-9** *"ወደምትገቡባትም ከተማ ሁሉ ቢቀበሉአችሁ፣ ያቀረቡላችሁን ብሉ፤ [9] በእርሰዋም ያሉትን ድውዮችን ፈውሱና። የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ቀረበች በሉአቸው።"*

8. ሉቃስ 23፡2 እንደ አይሁድ የራሳቸው ትርጉም "ክርስቶስ" የሚለው ቃል __________ የሆነ ማለት ነው፤

**ሉቃስ 23፡2** *"ይህ ሕዝባችንን ሲያጣምም ለቄሣርም ግብር እንዳይሰጥ ሲከለክል ደግሞም። እኔ ክርስቶስ ንጉሥ ነኝ ሲል አገኘነው ብለው ይከሱት ጀመር።"*

9. የሐዋርያት ሥራ 17፡7 አንብቡና፣ አይሁድ ሐዋርያው ጳውሎስን ከሮማውያን ሕግ በተፃራሪ፣ __________ የሚሉት ሌላ __________ አለ ብሎ ያስተምራል ብለው ይከሱት ነበር፤

**የሐዋርያት ሥራ 17፡7** *"እነዚህም ሁሉ። ኢየሱስ የሚሉት ሌላ ንጉሥ አለ እያሉ የቄሣርን ትእዛዝ ይቃወማሉ ብለው ጮኹ።"*

10. የሐዋርያት ሥራ 19፡8-10 ጳውሎሰም በኤፌሶን __________ በተመለከተ በድፍረት ከሌሎች ጋር ይነጋገርና ያስረዳቸው ነበር፤

**የሐዋርያት ሥራ 19፡8-10** *"ወደ ምኵራብም ገብቶ ሰለ እግዚአብሔር መንግሥት እየተነጋገረና እያስረዳቸው ሦሰት ወር ያህል በግልጥ ይናገር ነበር።[9] አንዳንዶች ግን እልከኞች ሆነው በሕዝብ ፊት መንገዱን እየሰደቡ ባላመኑጊዜ፥ከእነርሱርቆደቀመዛሙርትንለየ፥ጢራኖስምበሚሉትበትምህርትቤትዕለትዕለትይነጋገርነበር። [10] በእሰያም የኖሩት ሁሉ አይሁድም የግሪክ ሰዎችም የጌታን ቃል እሰኪሰሙ ድረሰ ሁለት ዓመት ያህል እንዲህ ሆነ።"*

11. የሐዋርያት ሥራ 28፡23-31፣ በቁጥር 31 ሐዋርያው ጳውሎስ ይሰብክ የነበረው ምን ነበር?

**የሐዋርያት ሥራ 28፡23-31** *"ቀንም ቀጥረውለት ብዙ ሆነው ወደ መኖሪያው ወደ እርሱ መጡ፤ ሰለ እግዚአብሔር መንግሥትም እየመሰከረ ሰለ ኢየሱሰም ከሙሴ ሕግና ከነቢያት ጠቅሶ እያሰረዳቸው፥ ከጥዋት ጀምሮ እሰከ ማታ ድረሰ ይገልጥላቸው ነበር።[24] እኲሌቶቹም የተናገረውን አመኑ፥ እኲሌቶቹ ግን አላመኑም፤ [25] እርሰ በርሳቸውም ባልተሰማሙ ጊዜ፥ ጳውሎሰ አንዲት ቃል ከተናገረ በኋላ ሄዱ፤ እንዲህም አለ። መንፈሰ ቅዱሰ በነቢዩ በኢሳይያሰ ለአባቶቻችን።[26] ወደዚህ ሕዝብ ሂድና። መሰማትን ትሰማላችሁና አታሰተውሉም፥ ማየትንም ታያላችሁና አትመለከቱም፤[27] በዓይናቸው እንዳያዩ በጆሮአቸው እንዳይሰሙ በልባቸውም እንዳያሰተውሉ ተመልሰውም እንዳልፈውሳቸው፥ የዚህ ሕዝብ ልብ ደንድኖአል ጆሮአቸውም*

*ደንቁርአል ዓይናቸውንም ጨፍነዋል በላቸው[28] ሲል መልካም ተናገረ። እንግዲህ ይህ የእግዚአብሔር ደኅንነት ለአሕዛብ እንደ ተላከ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን፤ እነርሱ ደግሞ ይሰሙታል።[29] ይህንም በተናገረ ጊዜ አይሁድ እርስ በርሳቸው እጅግ እየተከራከሩ ሄዱ።[30] ጳውሎስም በተከራየው ቤት ሁለት ዓመት ሙሉ ተቀመጠ፥ ወደ እርሱም የሚመጡትን ሁሉ ይቀበል ነበር፤ [31] ማንም ሳይከለክለው የእግዚአብሔርን መንግሥት እየሰበከ ስለ ጌታ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እጅግ ገልጦ ያስተምር ነበር።"*

12. ማቴዎስ 24፡14 አንብቡና በዓለም ሁሉ ሊሰበክ ያለው መልዕክት ምን ነበር?

    **ማቴዎስ 24፡14** *"ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፥ በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል።"*

13. የሐዋርያት ስራ 20፡24-25 የመንግስቱ ወንጌል አንዳንድ ጊዜ የ__________ ወንጌል ተብሎ ይጠራል፤

    **የሐዋርያት ስራ 20፡24-25** *"ነገር ግን ሩጫዬንና ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልሁትን አገልግሎት እርሱም የእግዚአብሔርን ጸጋ ወንጌልን መመስከር እፈጽም ዘንድ ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደ ከንቱ ነገር እቆጥራለሁ።[25] አሁንም፥ እነሆ፥ እኔ የእግዚአብሔርን መንግሥት እየሰበክሁ በመካከላችሁ የዞርሁ ሁላችሁ ከእንግዲህ ወዲህ ፊቴን እንዳታዩ አውቃለሁ።*

14. ሉቃስ 16፡16ን አንብቡና፣ የኢየሱስን መልዕከት በትክክል ለመረዳት በዋነኛነት መንግስቱን መረዳት ያስፈልጋል። ኢየሱስ ስለ መንግስቱ የሚናገር ሲሆን ደቀ መዛሙርቱ እንዲያደርጉ የሚያዛቸውም፤

    ሀ. እንዲሰብኩ፣
    ለ. እንዲተዉ፣
    ሐ. እንዲያሰቡ፣

    **ሉቃስ 16፡16** *"ሕግና ነቢያት እስከ ዮሐንስ ነበሩ፤ ከዚያ ጀምሮ የእግዚአብሔር መንግሥት ይሰበካል፤ ሁሉም ወደ እርሰዋ በኃይል ይገቡባታል።"*

15. ማቴዎስ 6፡10ን አንብቡና፣ የእግዚአብሔር መንግሰት በእርግጥ በእግዚአብሔር ይመራል፤ ይህ ቃል ይህን እንዴት ይገልጸዋል?

    **ማቴዎስ 6፡10ን** *"ስምህ ይቀደስ፤ መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን፤"*

16. ቆላስያስ 1:13-14 እና ሮሜ 14፡9፣ "የእግዚአብሔር መንግስት" የሚለው ሐረግ የሰዎችን ሰብሰብ እሳቤ ያደረገ ሲሆን የሚያደርጉትም፡-

    ሀ. ኢየሱስን ወደ ልባቸው ይጋብዛሉ፣
    ለ. የእግዚአብሔርን መመሪያ ይቀበላሉ (የሰይጣንን ያስወግዳሉ)፣ ምህረቱን ይቀበላሉ፣
    ሐ. ቤተ ክርሰቲያንን ይቀላቀላሉ፣

    **ቆላሰያስ 1፡13-14** *"እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፥ ቤዛነቱንም እርሱንም የኃጢአትን ሰርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን።"*

**ሮሜ 14፡9** *“ስለዚህ ነገር ሙታንንም ሕያዋንንም ይገዛ ዘንድ ክርስቶስ ሞቶአልና ሕያውም ሆኖአልና።”*

17. ማቴዎስ 4፡17፣ ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባት የልብ መለወጥ ያስፈልጋል። ይህን የልብ መለወጥ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ብሎ ይጠራዋል፡-

ሀ. ቅጣት
ለ. የሕግ ሥራ፣
ሐ. ንስሐ፣

**ማቴዎስ 4፡17** *“የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሆነ። ከዚያ ዘመን ጀምሮ ኢየሱስ። መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንሰሐ ግቡ እያለ ይሰብክ ጀመር።”*

18. የሐዋርያት ሥራ 26፡18ን አንብቡና የኃጢአትን ስርየት ለመቀበል፣

ከ _____________ ወደ ብርሃን፣
ከ ሰይጣን _____________፣
ወደ _____________ ዘወር ብላችኋል።

**የሐዋርያት ሥራ 26፡18** *“ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።”*

19. ሕዝቅኤል 36፡26-27 እና የሐዋርያት ሥራ 11፡15-18፣ በእግዚአብሔር መንገድ መሄድ ትችሉ ዘንድ አዲስ ልብ እና አዲስ መንፈስ ተሰጥቷችኋል ማለት ነው?

**ሕዝቅኤል 36፡26-27** *“አዲሰም ልብ እሰጣችኋለሁ አዲሰም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ፤ የድንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ፤ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ።[27] ፤ መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ በትእዛዜም እሰሄዳችኋለሁ፥ ፍርዴንም ትጠብቃላችሁ ታደርጉትማላችሁ።*

20. ሉቃስ 18፡13-14 ለኃጢአት ይቅርታ ወደ እግዚአብሔር ተጣርታችኋል?

**ሉቃስ 18፡13-14** *“ቀራጩ ግን በሩቅ ቆሞ ዓይኖቹን ወደ ሰማይ ሊያነሣ እንኳ አልወደደም፥ ነገር ግን። አምላክ ሆይ፥ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ እያለ ደረቱን ይደቃ ነበር።[14] እላችኋለሁ፥ ከዚያ ይልቅ ይህ ጻድቅ ሆኖ ወደ ቤቱ ተመለሰ፤ ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳልና፥ ራሱን ግን የሚያዋርድ ከፍ ይላል።”*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ዳንኤል 2፡44 አንብቡ። የብሉይ ኪዳን ነቢያት ወደፊት መሲሑ (የተቀባው) ይመጣል፣ የሰማይ አምላክም ያቋቁማል ብለው የተነበዩት መንግስት፤
**ሀ. ለአንድ ሺህ አመት የሚቆይ።**
**ለ. ምን ግዜም የማይጠፋ።**
**ሐ. ጊዜያዊ መንግስት።**
**ለ. ምን ግዜም የማይጠፋ።**

2. ማቴዎስ 4፡17፣ 23 የኢየሱስ መልዕክት ምንድን ነው?
**ንሰሐ ግቡ፣ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና።**

3. ማርቆስ 1፡14-15 ኢየሱስ የሰበከው የ_______________ ወንጌልን ነበር።
**የእግዚአብሔርም መንግሥት።**

4. ሉቃስ 4፡43 ኢየሱስ ከእግዚአብሔር የተላከበት ምክንያት _______________ ነበር።
**የእግዚአብሔርን መንግሥት መሰበክ።**

5. ዮሐንስ 4፡25፣ አንብቡና በመጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር መንግሰት በሚናገርበት ጊዜ ምን ማለት እንደሆነ ለአይሁድ ሲያብራራላቸው አናይም። ይህ በብሉይ ኪዳን የነበረ ሃሳብ ሲሆን እነርሱም፡-
**ሀ. በጥቂቱ የሚያውቁት ነው።**
**ለ. ይፈጸማል ብለው አያስቡም።**
**ሐ. የሚጠብቁት ጉዳይ ነበር።**
**ሐ. የሚጠብቁት ጉዳይ ነበር።**

6. ሉቃስ 9፡1-2 አሰራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ያደረጓቸው ሦሥት ነገሮች ምንድን ናቸው?
**አጋንንት ማስወጣት፣ ደዌን መፈወስ እና የእግዚአብሔርንም መንግሥት መሰበክ።**

7. ሉቃስ 10፡1-2፣ 8-9 ሰባዎቹን ኢየሱስ ምን እንዲያደርጉ ላካቸው?
**የእግዚአብሔር መንግሥት።**

8. ሉቃስ 23፡2 እንደ አይሁድ የራሳቸው ትርጉም “ክርሰቶሰ” የሚለው ቃል __________ የሆነ ማለት ነው፤
**ንጉሥ።**

9. የሐዋርያት ሥራ 17፡7 አንብቡና፣ አይሁድ ሐዋርያው ጳውሎስን ከሮማውያን ሕግ በተፃራሪ፣ __________ የሚሉት ሌላ __________ አለ ብሎ ያስተምራል ብለው ይከሱት ነበር፤
**ኢየሱስ/ንጉሥ።**

10. የሐዋርያት ሥራ 19፡8-10 ጳውሎሰም በኤፌሶን __________ በተመለከተ በድፍረት ከሌሎች ጋር ይነጋገርና ያስረዳቸው ነበር፤
**የእግዚአብሔርን መንግሥት።**

11. የሐዋርያት ሥራ 28፡23-31 በቁጥር 31 ሐዋርያው ጳውሎስ ይሰብክ የነበረው ምን ነበር?
**የእግዚአብሔርን መንግሰት እና ኢየሱስን የሚመለከቱ ነገሮች።**

12. ማቴዋስ 24፡14 እንብቡና በዓለም ሁሉ ሊሰበክ ያለው መልዕክት ምን ነበር?
**የመንግሰቱ ወንጌል።**

13. የሐዋርያት ሥራ 20፡24-25 የመንግሰቱ ወንጌል አንዳንድ ጊዜ የ__________ ወንጌል ተብሎ ይጠራል፤
**የእግዚአብሔር ጸጋ።**

14. ሉቃስ 16፡16ን እንብቡና፣ የኢየሱስን መልዕክት በትክክል ለመረዳት በዋነኛነት መንግሰቱን መረዳት ያስፈልጋል። ኢየሱስ ስለ መንግሰቱ የሚናገር ሲሆን ደቀ መዛሙርቱ እንዲያደርጉ የሚያዛቸውም፤
**ሀ. እንዲሰብኩ።**
**ለ. እንዲተዉ።**
**ሐ. አንዲያሰቡ።**
**ሀ. እንዲሰብኩ።**

15. ማቴዋስ 6፡10ን እንብቡና፣ የእግዚአብሔር መንግሰት በእርግጥ በእግዚአብሔር ይመራል፤ ይህ ቃል ይህን እንዴት ይገልጸዋል?
**የእግዚአብሔር ፈቃድ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር እንድትሆን።**

16. ቆላሰያስ 1፡13-14 እና ሮሜ 14፡9፣ "የእግዚአብሔር መንግሰት" የሚለው ሐረግ የሰዎችን ስብሰብ እሳቤ ያደረገ ሲሆን የሚያደርጉትም፦
**ሀ. ኢየሱስን ወደ ልባቸው ይጋብዛሉ።**
**ለ. የእግዚአብሔርን መመሪያ ይቀበላሉ (ሰይጣንን ያርቃሉ)፣ የእግዚአብሔርን ምህረት ይቀበላሉ።**
**ሐ. ቤተ ክርሰቲያንን ይቀላቀላሉ።**
**ለ. የእግዚአብሔርን መመሪያ ይቀበላሉ (ሰይጣንን ያርቃሉ)፣ የእግዚአብሔርን ምህረት ይቀበላሉ።**

17. ማቴዋስ 4፡17፣ ወደ እግዚአብሔር መንግሰት ለመግባት የልብ መለወጥ ያሰፈልጋል። ይህን የልብ መለወጥ መጽሐፍ ቅዱሰ ምን ብሎ ይጠራዋል፦
**ሀ. ቅጣት።**
**ለ. የሕግ ሥራ።**
**ሐ. ንሰሐ።**
**ሐ. ንሰሐ።**

18. የሐዋርያት ሥራ 26፡18ን እንብቡና የኃጢአትን ሰርየት ለመቀበል፣
ከ ____________ ወደ ብርሃን፣
ከ ሰይጣን ____________፣
ወደ ____________ ዘወር ብላችኋል።
**ከጨለማ /ሥልጣን/ ወደ እግዚአብሔር።**

19. ሕዝቅኤል 36፡26-27 እና የሐዋርያት ሥራ 11፡15-18፣ በእግዚአብሔር መንገድ መሄድ ትችሉ ዘንድ አዲሰ ልብ እና አዲሰ መንፈሰ ተሰጥቷችኋል ማለት ነው?

20. ሉቃስ 18፡13-14 ለኃጢአት ይቅርታ ወደ እግዚአብሔር ተጣርታችኋል?

# ትምህርት 7

# የመዳን ዕምነት ዓላማ

## በዶን ክሮው

በምናባችሁ በአንድ ሰው ሰርግ ላይ እንደ ታደማችሁ አስቡ፤ ሰውዬው ቃለ መሐላ ሊገባ ቄሱ ፊት እንደ ቆመ ወዲያውኑ ቄሱ እንዲህ በማለት ቃለ መሐላውን ጀመሩ እንበል - "አንተ ሰው፣ ይህችን ሴት የግልህ ምግብ አብሳይ እንድትሆን፣ ቤትህን እንድታጸዳ፣ የተመገብክባቸውን ሰሃኖች እንድታጥብልህ ትወስዳታለህ? ከዛሬ ጀምሮ በጋራ በምትኖሩበት በህይወት ዘመናችሁ ሁሉ የቤትህን ምንጣፍ እና የቤት እቃዎችህን ሁሉ እንድታጸዳ ትወስዳታለህ?" ብለው ቢናገሩ ሴቲቱ በፍጥነት አቋርጣ - "በቃ! ያንተን ቁሳቁስ እንዳጸዳልህ ለሥራ ከሆነ የምትፈልገኝ አገልጋይ መቅጠር ትችላለህ። እኔ ግን እንድትወደኝና በእኔነቴ እንድትቀበለኝ እፈልጋለሁ። በእነነቴ ስትቀበለኝ ግን እነዛን ስራዎች ወድጄ እሰራቸዋለሁ፣ ሆኖም እኔን ተቀብለህ የምትወሰደኝ ከሆነ ነው። ሙሉ እኔነቴን። አገልግሎቴን ፈልገህ እኔን ሳትፈልግ እንድትወሰደኝ አልፈልግም" ማለቷ አይቀርም።

ኤ. ደብልዩ ቶዘር (A.W. Tozer) የተባለ ሰው ሲናገር "እሁን ላይ አንዳንድ የዕምነቱ አስተማሪዎች የመዳን ወንጌል ብቸኛው እውነተኛ ዓላማ "የክርስቶስ አዳኝነት" ወይም "የክርስቶስ ጌትነት" ሳይሆን ክርስቶስ እራሱ መሆኑን አለማስተዋላቸው የሚያሰገርም ነው። መዳን (ድኅነት) አንድ ሰው ከክርስቶስ ቢሮዎች በአንደኛው ሲያምን ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ስጦታ አይደለም ወይም የትኛውም ቢሮ ቢሆን በራሱ የመዳን ዓላማ ሆኖ አልቀረበም። ደግሞም በመታረቃችን ወይም በመስቀሉ ወይም በክርስቶስ ሊቀ ክህነት እንድናምንም አልተጠራንም፡ ፡ እነዚህ ሁሉ በክርስቶስ አካል ውስጥ የተጠቃለሉ ናቸው፣ ነገር ግን አንዳቸው ከአንዳቸው ፍጹም የተለያዩ ወይም አንዱ ከሌሎች የተነጠለ አይደለም። አንዱን የክርስቶስ ቢሮ ተቀብለን ሌላውን እንደማያስፈልግ መቁጠር ተቀባይነት የለውም። ይህን በማድረግ ላይ ከሆንን ዘመናዊ ኑፋቄ ነው፣ እደግመዋለሁ፣ እንደ ማንኛውም ኑፋቄ በክርስቲያኖች መካከል መልካም ያልሆኑ ክፉ ነገሮችን የሚያስከትል ጉዳይ ነው" (The Root of the Righteous, pp. 84-66)።

የመልዕክቱን ፍሬ ሃሳብ አገኛችሁ? ክርስቶስን ሳይሆን የክርስቶስን አንዱን ክፍል (ጥቅሞቹን)፣ የክርስቶስን አንዱን ቢሮ፣ ማጉላት ወይም ማግነን ለምን አስፈለገን? ይህም ሚስትን በእርሷነቷ ሳይሆን ለምግብ አብሳይነት እንደማግባት ነው።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. የሐንስ 1፡12 ን አንብቡና፣ ለተቀበሉት ሁሉ፣ _______ ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ስልጣንን ሰጣቸው፡፡

   ሀ. እርሱን (ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን)፡፡
   ለ. ኢየሱስን እንደ አዳኝ፡፡
   ሐ. ኢየሱስን እንደ ጌታ፡፡
   መ. ኢየሱስን እንደ ካህን፡፡

   **ዮሐንስ 1፡12** *"ለተቀበሉት ሁሉ ግን፣ በሰሙ ለሚያምኑ ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤"*

2. የሐዋርያት ሥራ 16፡31 ማንን ማመን (በማን እምነት መጣል) አለብን?

   **የሐዋርያት ሥራ 16፡31** *"እነርሱም፡- "በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን፣ አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ፣" አሉት።*

3. ሉቃስ 6፡46 "ጌታ" የሚለው ቃል ምን ያመላክታል?

   **ሉቃስ 6፡46** *"ሰለ ምን። ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ ትሉኛላችሁ፥ የምለውንም አታደርጉም?"*

4. ማቴዎስ 1፡21 "ኢየሱስ" የሚለው ቃል ምን ያመላክታል?

   **ማቴዎስ 1፡21** *"ልጅም ትውልዳለች፣ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ሰሙን ኢየሱስ ትለዋለህ።"*

5. ሉቃስ 23፡2 "ክርስቶስ" የሚለው ቃል ምን ያመላክታል?

   **ሉቃስ 23፡2** *"ይህ ሕዝባችንን ሲያጣምም ለቄሣርም ግብር እንዳይሰጥ ሲከለክል ደግሞም። እኔ ክርስቶስ ንጉሥ ነኝ ሲል አገኘነው ብለው ይከሱት ጀመር።*

6. ሮሜ 1፡16 በዚህ ቃል መሰረት ወንጌል ወይም የምስራቹ ቃል ____________ ነው፡፡

   **ሮሜ 1፡16** *"በወንጌል አላፍርምና፤ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው፥ ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና።"*

7. ሮሜ 1፡1-4 የእግዚአብሔር ወንጌል ማዕከል ያደረገው ወይም የሚመለከተው ____________ ነው፡፡

   **ሮሜ 1፡1-4** *"ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ጳውሎስ በነቢያቱ አፍ በቅዱሳን [2] መጻሕፍት አስቀድሞ ተሰፋ ለሰጠው ለእግዚአብሔር ወንጌል ተለየ።[3] -ይህም ወንጌል በሥጋ ከዳዊት ዘር ሰለ ተወለደ እንደ ቅድስና መንፈስ ግን ከሙታን መነሣት የተነሣ [4] በኃይል የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ሰለ ተገለጠ ሰለ ልጁ ነው፤ እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።"*

የልጁን የተወሰነ ክፍል ነው ወይስ ሙሉውን?

8. የሐንስ 6፡54 አንድን ነገር ስትመገቡ፣ ያ የሚያመለክተው ምንድን ነው?

**የሐንስ 6፡54** *"ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።"*

9. ገላትያ 3፡27 ሰው ከክርስቶስ ጋር አንድ ሊሆን ሲጠመቅ፣____________ ይለብሳል። የትኛውን የክርስቶስ አካል ነው የሚለብሱት?

**ገላትያ 3፡27** *"ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና።"*

10. የሐዋርያት ሥራ 9፡5-6 ሳውል በተለወጠ ጊዜ ለኢየሱስ ያቀረባቸው ሁለት ጥያቄዎች ምን ነበሩ?

**የሐዋርያት ሥራ 9፡5-6** *"ጌታ ሆይ፥ ማን ነህ? አለው። እርሱም። አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ፤ የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብሰብሃል አለው።[6] እየተንቀጠቀጠና እየተደነቀ። ጌታ ሆይ፥ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ? አለው። ጌታም። ተነሥተህ ወደ ከተማ ግባና ታደርገው ዘንድ የሚያስፈልግህን ይነግሩሃል አለው።"*

11. ሮሜ 7፡4 ከማን ጋር ጋብቻ ልንፈጽም ይገባል? ከየትኛው አካሉ ጋር ነው በጋብቻ የተሳሰርነው? ከክርስቶስ ጋር በመልካም ጋብቻ ደስተኛ ሆናችኋል?

**ሮሜ 7፡4** *"እንዲሁ፥ ወንድሞቼ ሆይ፥ እናንተ ደግሞ በክርስቶስ ሥጋ ለሕግ ተገድላችኋል፤ ለእግዚአብሔር ፍሬ እንድናፈራ፥ እናንተ ለሌላው፥ ከሙታን ለተነሣው፥ ለእርሱ ትሆኑ ዘንድ።"*

12. ከክርስቶስ ጋር በመልካም ጋብቻ ደስተኛ ሆናችኋል? ታወራላችሁ፣ ትወያያላችሁ፣ ትወዱታላችሁ፣ ታመልኩታላችሁ?

# ጠቋሚ መልሶች

1. ዮሐንስ 1፡12 ን እንብቡና፣ ለተቀበሉት ሁሉ፣ _______ ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ስልጣንን ሰጣቸው፡፡
**ሀ. እርሱን (ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን)፡፡**

2. የሐዋርያት ሥራ 16፡31 ማንን ማመን (በማን እምነት መጣል) አለብን?
**ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን፡፡**

3. ሉቃስ 6፡46 “ጌታ” የሚለው ቃል ምን ያመላክታል?
**ገዥ፣ መሪ፣ አለቃ፣ ሕይወታችን ሊቆጣጠር ስልጣን ያለው፡፡ ይህ ቃል አምላክነትንም ያመለክታል፡፡**

4. ማቴዎስ 1፡21 “ኢየሱስ” የሚለው ቃል ምን ያመለክታል?
**የኢየሱስን አዳኝነት፡፡**

5. ሉቃስ 23፡2 “ክርስቶስ” የሚለው ቃል ምን ያመላክታል?
**ኢየሱስ ንጉሣችንና መሲሕ መሆኑን፡፡**

6. ሮሜ 1፡16 በዚህ ቃል መሰረት ወንጌል ወይም የምስራቹ ቃል ____________ ነው፡፡
**ክርስቶስ እራሱ፣ ጥቅሞቹን ጭምር፡፡**

7. ሮሜ 1፡1-3 የእግዚአብሔር ወንጌል ማዕከል ያደረገው ወይም የሚመለከተው ____________ ነው፡፡
**የእግዚአብሔርን ልጅ፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን፡፡**
የልጁን የተወሰነ ክፍል ነው ወይስ ሙሉውን?
**ሙሉውን፡፡**

8. ዮሐንስ 6፡54 እንድን ነገር ስትመገቡ፣ ያ የሚያመለክተው ምንድን ነው?
**ሁለንተናውን መውሰዳችሁን፡፡ በሌላ አነጋገር፣ የተመገባችሁት ሕይወታችሁ ይሆናል፣ ጥንካሬአችሁ፡፡**

9. ገላትያ 3፡27 ሰው ከክርስቶስ ጋር አንድ ሊሆን ሲጠመቅ፣____________ ይለብሳል፡፡ የትኛውን የክርስቶስ አካል ነው የሚለብሱት?
**ሁለንተናውን፡፡**

10. የሐዋርያት ሥራ 9፡5-6 ሳውል በተለወጠ ጊዜ ለኢየሱስ ያቀረባቸው ሁለት ጥያቄዎች ምን ነበሩ?
**ጌታ ሆይ ማነህ? ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ?**

11. ሮሜ 7፡4 ከማን ጋር ጋብቻ ልንፈጽም ይገባል?
**ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር፡፡**
ከየትኛው አካሉ ጋር ነው በጋብቻ የተሳሰርነው?”
**ከሁለንተናው፡፡**

12. ከክርስቶስ ጋር በመልካም ጋብቻ ደስተኛ ሆናችኋል? ታወራላችሁ፣ ትወያያላችሁ፣ ትወዱታላችሁ፣ ታመልኩታላችሁ?

# ትምህርት 8

# የእግዚአብሔር ሕግ ትክክለኛ አጠቃቀም

## በዶን ክሮው

አንድ ቀን እኔ እና ጓደኛዬ ጆ ከቢል እና ስቲቭ ጋር ሐይቅ ላይ ሆነን እያወራን ነበር። በመካከል ድንገት አንድ ጥያቄ ተነሳ፤ ጥያቄውም "ስለ እግዚአብሔር ወይም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ምንም ሰምተው የማያውቁ ሰዎች እንዴት በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂ ሊሆኑ ይችላሉ?" የሚል ነው። እኔም ወደ ቢል ዞርኩና - "ቢል፣ ስቲቭን ለመጎብኘት ወደ ቤቱ ሄድክ እንበል። ቤቱ እንደ ደረስክ ባለቤቱን አገኘሃት፣ ስቲቭ ግን በቤት አልነበረም። ከባለቤቱ ጋር አላስፈላጊ መዳራት ውስጥ ብትገባ፣ የባልንጀራህን ሚስት በማማገጥህ የበደለኛነት ስሜት አይሰማህም? ከዚህ ቀደም ስለ አስርቱ ትዕዛዛት ሰምተህ የማታውቅ እና መጽሐፍ ቅዱስንም አንብበህ የማታውቅ ቢሆንም? ያ የበደለኛነት እና የጥፋተኛነት ስሜት ከወዴት የመጣ ይመስልሃል?" ስል ጠየኩት

እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው በጎ ሲያደርግ የመለየት እና ክፉ በማድረጉ የጥፋተኛነት ስሜት ይኖረው ዘንድ፣ በሕግ እና በህሊና በኩል፣ ችሎታ ሰጥቶታል። ሕግ እና ህሊና፣ ክፉም ሆነ ደግ ስናደርግ እንደ ጸባይና ባህሪአችን ወይ የምንከሰስበት ወይም ምህረት የምናገኝበት፣ እራሳችን የምንዳኝበት መሳሪያ ናቸው (ሮሜ 2፡14-15)።

ቢል ምን ዓይነት መልካም ሰው እንደሆነ እየተናገረ ነበር። አዳኝ እያስፈልገኝም የሚል ፍርጥም ያለ አመለካከት አለው። ዘጸአት 20 ን አወጣሁና አስርቱን ትዕዛዛት ለቢል ማንበብ ጀመርኩ። "ቢል በሕይወትህ ሁሉ እግዚአብሔርን አስቀድመሃል፣ በዓለም ካለው ከምንም ነገር በላይ እርሱን ትወደዋለህ? ይህን ካላደረግክ የመጀመሪያውን ትዕዛዝ ጥሰሃል" (ዘጸአት 20፡3)። "ከእግዚአብሔር ይልቅ ከፍ ያደረግከው ሌላ ነገር አለ፣ ካለ ሁለተኛውን ትዕዛዝ ሽረሃል" (ዘጸአት 20፡4)። "የኢየሱስን ስም እንደው እንደዋዛ እንደማንኛውም ባለ አራት ፊደል ቃል እንደመጣልህ ትጠቀማለህ? ሦሥተኛውን ትዕዛዝ ተላልፈሃል ማለት ነው" (ዘጸአት 20፡7)። "እግዚአብሔርን የምታከብርበት እና የምታመልክበት የተለየ ቀን አለህ? ከሌለህ አራተኛውን ትዕዛዝ ሽረሃል" (ዘጸአት 20፡8)። "በልጅነትህ አባት እና እናትህን ሁልጊዜ ታከብር ነበር? ይህን ባለማድረግህ አምስተኛውን ትዕዛዝ ተላልፈሃል" (ዘጸአት 20፡12)። "በሰው ላይ ያለ ልክ ተቆጥተህ ታውቃለህ? ስድስተኛውን ትዕዛዝ ጥሰሃል ማለት ነው" (ዘጸአት 20፡13 ከማቴዎስ 5፡21-22 ጋር በማነጻጸር ተመልከት)። "ወደ አንዲት ሴት ተመልክተህ ተመኝተሃት ታውቃለህ? ሰባተኛውን ትዕዛዝ ጥሰሃል" (ዘጸአት 20፡14 እና ማቴዎስ 5፡27-28 በማነጻጸር ተመልከት)። "ያንተ ያልሆነን ነገር ወስደህ ታውቃለህ? ስምንተኛውን ትዕዛዝ ተላልፈሃል" (ዘጸአት 20፡15)። "ሁል ጊዜ እውነት ትናገራለህ? ካልሆነ ዘጠነኛውን ትዕዛዝ ጥሰሃል" (ዘጸአት 20፡16)። "የሌላ ሰውን ንብረት ተመኝተህ ታውቃለህ? አስረኛውን ትዕዛዝ ተላልፈሃል" (ዘጸአት 20፡17)። "ኢየሱስ ለምን ኃጢአተኞችን ላድን መጣሁ እንዳለ ግልጽ ሆነልህ?" (ማርቆስ 2፡16-17)።

መልካም ነን ብለን እንዳናስብ ወይም በጎ ለመስራት በምናደርገው ጥረት መንግስተ ሰማያት እንዳንገባ ችግር የሚሆንብን አስርቱንም ትዕዛዛት መጣሳችን ነው። ያዕቆብ 2፡10 ትዕዛዛትን ሁሉ የሚጠብቅ ነገር ግን በአንዱ ብቻ የሚሰናከል ሕግን ሁሉ በመጣስ ጥፋተኛ ነው ሲል ይነግረናል። ሕጉ መቼም ቢሆን እናንተን ጻድቅ ሊያደርጋችሁ ሳይሆን ኃጢአታችሁን እንድታውቁ በማድረጉ ይታወቃል (ሮሜ 3፡19-20)።

ሁላችንም አዳኝ ያስፈልገናል! "አዳኝ" የሚለው ቃል ኃጢአት ከሚያስከትለው ቅጣት የሚያድናችሁን አንድ ሰው የሚጠቁም ነው። ኢየሱስ ሊጠፉ የነበሩትን ሁሉ በማዳን የዘላለም ሕይወት እንዲያገኙ አደረገ (ማቴዎስ 1፡21)።

መንግስተ ሰማያት ለመግባት ብቁ እንሆን ዘንድ ከእግዚአብሔር ጋር የተካከለ ጽድቅ ያስፈልገናል (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21)። የወንጌል የምስራች ኢየሱስ ኃጢአታችሁን ይቅር ማለቱ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን የራሱን ጽድቅ - በነጻ - ስጦታ አድርጎ የሰጣችሁ መሆኑ ነው (ሮሜ 5፡17፡- "በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ፣ ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ")።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ማርቆስ 2፡16-17 ኢየሱስ ማንን ሊያድን ነው የመጣው?

   **ማርቆስ 2፡16-17** *"ጻፎችና ፈሪሳውያንም ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋር ሲበላ አይተው ለደቀ መዛሙርቱ። ከቀራ ጮችና ከኃጢአተኞች ጋር የሚበላና የሚጠጣ ስለ ምንድር ነው? አሉ። [17] ኢየሱስም ሰምቶ። ሕመምተኞች እንጂ ብርቱዎች ባለ መድኃኒት አያስፈልጋቸውም ኃጢአተኞችን እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም አላቸው።"*

2. ሮሜ 2፡1 በሌሎች ላይ ስንፈርድ በእራሳችን ላይ ምን እያደረግን ነው?

   **ሮሜ 2፡1** *"ስለዚህ፥ አንተ የምትፈርድ ሰው ሁሉ ሆይ፥ የምታመካኘው የለህም፤ በሌላው በምትፈርድበት ነገር ራስህን ትኰንናለህና፤ አንተው ፈራጁ እነዚያን ታደርጋለህና። ለምን?"*

3. ያዕቆብ 2፡10 አብዛኛውን የእግዚአብሔርን ሕግ ብንፈጽም እና ነገር ግን በጥቂት ነገሮች ላይ ብንሳሳት ምን ያህል ጥፋተኛ እንሆናለን?

   **ያዕቆብ 2፡10** *"ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ፥ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል፤ አታመንዝር ያለው ደግሞ። አትግደል ብሎአልና፤"*

4. ገላትያ 3፡10 የእግዚአብሔርን ሕግ በመፈጸም ጻድቅ የምንሆን ከሆነ፣ ምን ያህሉን መጠበቅ ይኖርብናል? እነዚህን ትዕዛዞች ለምን ያህል ጊዜ መጠበቅ አለብን? ለምን በሥራ፣ በጥረታችን መዳን እንደማንችል አሁን ግልጽ ሆነላችሁ?

   **ገላትያ 3፡10** *"ከሕግ ሥራ የሆኑት ሁሉ በእርግማን በታች ናቸውና፤ በሕግ መጽሐፍ በተጻፉት ሁሉ ጸንቶ የማይኖር የማያደርግም ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና።"*

5. ገላትያ 2፡16 ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ይመስርትና በእግዚአብሔር ቀኝ ለመቆም የተገባው ይሆን ዘንድ ይህ ከእግዚአብሔር የተሰጠ የጽድቅ ሰጦታ ነው፣ ኃጢአተኞች ይጸድቁ ዘንድ ይህ በክርስቶስ ኢሱስ እምነት የተሰጠ ሰጦታ ሲሆን ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ በሞቱና በትንሳኤው የተፈጸመ ነው (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡3-4 እና ሮሜ 4፡25)። ሰው ሊጸድቅ የማይችለው በምንድን ነው? ሰው የሚድነው እንዴት ነው? በሕግ ምን ያህል ሰዎች ይጸድቃሉ?

   **ገላትያ 2፡16** *"ነገር ግን ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ በሕግ ሥራ እንዳይሆን አውቀን፥ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በሕግ ሥራ ስለማይጸድቅ፥ እኛ ራሳችን በሕግ ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ እምነት እንጸድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል።"*

6. ሮሜ 6፡14 እንደ ክርስቲያን እናንተ፦

   ሀ. ከሕግ በታች ናችሁ።
   ለ. ከጸጋ በታች ናችሁ።

**ሮሜ 1፡14** *"ኃጢአት አይገዛችሁምና፤ ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁምና።"*

7. ሕዝቅኤል 18፡20 ከሕግ በታች ብትሆኑ ኖሮ የኃጢአታችሁ ቅጣት ምን ይሆን ነበር?

**ሕዝቅኤል 18፡20** *"ኃጢአትን የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች፤ ልጅ የአባቱን ኃጢአት አይሸከምም፥ አባትም የልጁን ኃጢአት አይሸከምም፤ የጻድቁ ጽድቅ በራሱ ላይ ይሆናል፥ የኃጢአተኛውም ኃጢአት በራሱ ላይ ይሆናል።"*

8. ሮሜ 4፡6-8 እግዚአብሔር በጽድቅ ምክንያት፣ በኃጢአታችሁ ላይ ያደረጋቸው ሦሥት ነገሮች ምንድን ናቸው?

**ሮሜ 4፡6-8** *"እንደዚህ ዳዊት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ሥራ ጽድቅን ስለሚቆጥርለት ስለ ሰው ብፅዕና ይናገራል እንዲህ ሲል።[7] ዓመፃቸው የተሰረየላቸው ኃጢአታቸውም የተከደነላቸው ብፁዓን ናቸው፤[8] ጌታ ኃጢአቱን የማይቆጥርበት ሰው ብፁዕ ነው።*

9. ሮሜ 5፡1 አሁን ግን ስለ ጸደቅን ምን ዓይነት ጥቅም እናገኛለን?

**ሮሜ 5፡1** *"እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ፤"*

10. ሮሜ 5፡9 አሁን ግን በኢየሱስ ደም ስለዳንን ከምን እንድናለን?

**ሮሜ 5፡9** *"ይልቁንስ እንግዲህ አሁን በደሙ ከጸደቅን በእርሱ ከቍጣው እንድናለን።"*

11. ሮሜ 10፡4 ክርስቶስ ሕግን የፈጸመው በእግዚአብሔር ዘንድ _________ ለማስገኘት ነው።

**ሮሜ 10፡4** *"የሚያምኑ ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነውና።"*

12. 1ኛ ቆሮንቶስ 1፡30፣ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ _________, _________, _________, እና _________, አደረገልን።

**1ኛ ቆሮንቶስ 1፡30** *"ነገር ግን። የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ ተብሎ እንደ ተጻፈው ይሆን ዘንድ፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ጽድቅ ቅድስናም ቤዛነትም በተደረገልን በክርስቶስ ኢየሱስ የሆናችሁ ከእርሱ ነው።"*

13. ፊሊጵስዩስ 3፡9 ከሙሴ ሕግ በታች ስትሆኑ የእራሳችሁን _________ ለማግኘት ትጥራላችሁ።

**ፊሊጵስዩስ 3፡9** *"አዎን፥ በእውነት ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጥ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ጌታዬ እውቀት ነገር ሁሉ ጉዳት እንዲሆን እቈጥራለሁ፤ ስለ እርሱ ሁሉን ተጐዳሁ፥ ክርስቶስንም አገኝ ዘንድ፥ በክርስቶስም በማመን ያለው ጽድቅ ማለት በእምነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለው ጽድቅ እንጂ ከሕግ ለእኔ ያለው ጽድቅ ሳይሆንልኝ፥ በእርሱ እገኝ ዘንድ ሁሉን እንደ ጉድፍ እቈጥራለሁ፤"*

14. 1ኛ ቆሮንቶስ 11፡1 እንደ ክርስቲያን፣ እኛ የምንኖረው ከክርስቶስ ሕግ በታች ነው። የክርስቶስ ሕግ

የምንፈጽማቸው ዝርዝር ተግባራት አይደሉም፣ ነገር ግን እንደ ሰው የምንኖረው ሕይወት ነው። ያ ሰው _________ ነው።

**1ኛ ቆሮንቶስ 11፡1** *"እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ።"*

15. ሮሜ 8፡3-4 ሕጉ ፈጽሞ ሊያድነን አይችልም፣ ነገር ግን ሕጉ ትክክል ስላልሆነ ሳይሆን በእኛ _________ ምክንያት መጠበቅ ስለማንችል ነው።

**ሮሜ 8፡3-4** *"ከሥጋ የተነሣ ስለ ደከመ ለሕግ ያልተቻለውን፥ እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ በኃጢአትም ምክንያት ልኮ አድርጎአልና፤ እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ በባንመላለስ በእኛ የሕግ ትእዛዝ ይፈጸም ዘንድ ኃጢአትን በሥጋ ኰነነ።"*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ማርቆስ 2፡16-17 ኢየሱስ ማንን ሊያድን ነው የመጣው?
   **ኃጢአተኞችን።**

2. ሮሜ 2፡1 በሌሎች ላይ ስንፈርድ በእራሳችን ላይ ምን እያደረግን ነው?
   **ራሳችንን እንኮንናለን፣ ማለትም በእራሳችን ላይ እንፈርዳለን።**
   ለምን?"
   **ምክንያቱም በሌሎች ብንፈርድም እኛም ያንኑ እነርሱ ያደረጉትን እናደርጋለንና።**

3. ያዕቆብ 2፡10 አብዛኛውን የእግዚአብሔርን ሕግ ብንፈጽም እና ነገር ግን በጥቂት ነገሮች ላይ ብንሳሳት ምን ያህል ጥፋተኛ እንሆናለን?
   **በሁሉም ጥፋተኛ እንሆናለን።**

4. ገላትያ 3፡10 የእግዚአብሔርን ሕግ በመፈጸም ጻድቅ የምንሆን ከሆነ፣ ምን ያህሉን መጠበቅ ይኖርብናል?
   **ሁሉንም።**
   እነዚህን ትዕዛዞች ለምን ያህል ጊዜ መጠበቅ አለብን?
   **(ያለ ምንም ዕንከን) ሁሌም መጠበቅ አለብን።**
   ለምን በሥራ፣ በጥረታችን መዳን እንደማንችል አሁን ግልጽ ሆነላችሁ?
   **አዎን።**

5. ገላትያ 2፡16 ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት እንዲመሰርትና በእግዚአብሔር ቀኝ ለመቆም የተገባው ይሆን ዘንድ ይህ ከእግዚአብሔር የተሰጠ የጽድቅ ስጦታ ነው፣ ኃጢአተኞች ይጸድቁ ዘንድ ይህ በክርስቶስ ኢየሱስ እምነት የተሰጠ ስጦታ ሲሆን ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ በሞቱና በትንሳኤው የተፈጸመ ነው (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡3-4 እና ሮሜ 4፡25)። ሰው ሊጸድቅ የማይችለው በምንድን ነው?
   **በእራሱ ሥራ፣ ማለትም በሕግ ሥራ።።።**
   ሰው የሚድነው እንዴት ነው?
   **በእምነት፣ በኢየሱስ ክርስቶስ (በማመን)**
   በሕግ ምን ያህል ሰዎች ይጸድቃሉ?
   **ማንም፣ ሥጋ የለበሰ ሁሉ በሕግ አይጸድቅም።**

6. ሮሜ 6፡14 እንደ ክርስቲያን እናንተ፡
   **ለ. ከጸጋ በታች ናችሁ።**

7. ሕዝቅኤል 18፡20 ከሕግ በታች ብትሆኑ ኖሮ የኃጢአታችሁ ቅጣት ምን ይሆን ነበር?
   **ሞት።**

8. ሮሜ 4፡6-8 እግዚአብሔር በጽድቅ ምክንያት፣ በኃጢአታችሁ ላይ ያደረጋቸው ሦሥት ነገሮች ምንድን ናቸው?
   **ይቅር ይላቸዋል፣ ይከድናቸዋል እና አይቆጥራቸውም (በእኔ ላይ) አይመዘገቡም።**

9. ሮሜ 5፡1 አሁን ግን ስለ ጸደቅን ምን ዓይነት ጥቅም እናገኛለን?
   **ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም፣ በእኔ አይቆጣም።**

10. ሮሜ 5፡9 አሁን ግን በኢየሱስ ደም ስለዳንን ከምን እንድናለን?
**ከቍጣው እንድናለን (በኃጢአት ከሚመጣ ፍርድ)።**

11. ሮሜ 10:4 ክርስቶስ ሕግን የፈጸመው በእግዚአብሔር ዘንድ _________ ለማስገኘት ነው።
**ጽድቅ።**

12. 1ኛ ቆሮንቶስ 1፡30፣ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ _________, _________, _________, እና _________, አደረገልን።
**ጥበብ፣/ጽድቅ፣/ቅድስናም፣/ቤዛነትም።**

13. ፊሊጵስዩስ 3፡9 ከሙሴ ሕግ በታች ስትሆኑ የእራሳችሁን _________ ለማግኘት ትጥራላችሁ።
**ጽድቅ።**

14. 1ኛ ቆሮንቶስ 11፡1 እንደ ክርስቲያን፣ እኛ የምንኖረው ከክርስቶስ ሕግ በታች ነው። የክርስቶስ ሕግ የምንፈጽማቸው ዝርዝር ተግባራት አይደሉም፣ ነገር ግን እንደ ሰው የምንኖረው ሕይወት ነው። ያ ሰው _________ ነው።
**ክርስቶስ።**

15. ሮሜ 8፡3-4 ሕጉ ፈጽሞ ሊያድነን አይችልም፣ ነገር ግን ሕጉ ትክክል ስላልሆነ ሳይሆን በእኛ _________ ምክንያት መጠበቅ ስለማንችል ነው።
**ሥጋ።**

# ትምህርት 9

# ከሕግ በታች ሳይሆን ከጸጋ በታች

## በዶን ክሮው

በህልሜ አንዲት ሴት ስላጠፋችው ጥፋት (ስለ ኃጢአቷ) እየተቀጣች ተመለከትኩ። በተሳሳተች ቁጥር፣ የሚከታተላት አንድ ሰው፣ እራሱን በጥላቻ እየነቀነቀ ቀበቶውን ይመዝና ይገርፋታል። አንድ የተሳሳተ ቃል በተናገረች ወይም የተሳሳተ ስራ በሰራች ቁጥር ይቀጣት ነበር። የተሻለ ሰብዕና ለማሳየት፣ እያነከሰችም ቢሆን ህመሟን ታግሳ ፈገግ ለማለት ትሞክራለች ነገር ግን የምትሰራው ነገር ሁሉ ለበለጠ ቅጣት የሚዳርጋት ነበር። ትልቅ የሚባሉ ነገሮች አልነበሩም፣ ነገር ግን እርሷ ተሳስታ የምታደርጋቸውን እያንዳንዳቸውን ጥቃቅን ነገሮች ሁሉ ይህ ሰው እየተመለከተ ይደበድባታል። ሁኔታው ተስፋ አስቆራጭ ነበር። የምታደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ፍጹም ችግር ውስጥ የሚከቷት ነበሩ። ለእርሷ ማዘኔን አስታውሳለሁ። ሁሌ ከሚደበድባት ከዚህ ክፉ ሰው ልገላግላት ፈልጌ ነበር … ወዲያው ግን ከእንቅልፌ ነቃሁ።

ሰለ እግዚአብሔር ጸጋ ማሰብ ጀመርኩ፣ ያልለፋንበት፣ ይገባናል የማንለው ሞገስ እና የእግዚአብሔር ችሎታ። ልባችን በጸጋ ሲታነጽ በራሳችን ጥረትና ችሎታ ወይም የሕግን ሥራ በመፈጸም በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት መሞከር እናቆማለን። በዚህም የእግዚአብሔርን ሕግ በመተላለፋችን ምክንያት ሊደርስብን ካለው ዱላ እናመልጣለን። ኢየሱስ ታድጎናል።

እስኪ ሰለ ሞገስ አስቡ። ሞገስ ማለት የአንድን ሰው ተቀባይነት፣ ድጋፍ ወይም ምርቃት ማግኘት ማለት ነው። ከአንድ ሰው ሞገስ ማግኘት ስትፈልጉ ምን ታደርጋላችሁ? ሰዎቹ ደስ የሚያሰኛቸውን ሁሉ ታደርጋላችሁ ወይም ትናገራላችሁ እንጂ የሚያስቀይማቸውን አይደለም። ሁል ጊዜ መልካም ማድረግ ይኖርባችኋል። ሆኖም ይህን ማከናወን የሚቻል ይመስላችኋል? ልክ የመሬት ስበትን እንደ ማምለጥ ነው። ለአፍታ ልታደርጉት ትችሉ ይሆናል፣ በስተመጨረሻ ግን ትወድቃለችሁ። ከእናንተ ይልቅ የበለጠ ሃይል አለው።

በሕልሜ ካየኋት ሴት ጋር እራሴን ማነጻጸር ጀመርኩ። እኔም ብሆን ያን ሰሜት የተጋራሁበት ጊዜ ነበር፣ ሁሉንም ነገር በትክክል ለመስራት በሞከርኩበት ጊዜ ሁሉ አንድ ትንሽ ነገር ላይ እሳሳትና እወድቅ ነበር። ቀኑን ያለ ምንም ስህተት ባሳልፍ፣ አንድ ታላቅ ነገር ፈጸምኩ ማለት እችል ነበር ብየ እስባለሁ። ነገር ግን አልችልም፣ ሁሌም ፍጹም እንዳልሆን የሚያደርጉኝ ጉድለቶቼ ብዙ ናቸው። ስለዚህ የሰማይ አባቴን ማሳዘን ብቻ ሳይሆን እራሴንም እኮንነው እና መቀጣት አለብህ እለው ነበር። እኔው እራሴ በእራሴ መሸነፌን ተቀብያለሁ። በእራሴ ብቃትና ጉድለት ላይ ትኩረቴን አድርጌ ነበር። በውጤቱም ጥሩ የሚባል አፈጻጸም አልነበረኝም፣ የሚገባውን ውጤት አላመጣሁም፣ ከዚህ ጣጣ የሚያድነኝና የሚያወጣኝ ሰው ያስፈልገኝ ነበር።

እግዚአብሔር በምህረቱ የሚረዳንን ሰው ላከልን፤ ስሙም ኢየሱስ ይባላል። እርሱንም ልንፈጽመው ከማንችለው ሕግ እና ውጤት አልባ ሙከራችን፣ እኛን ነጻ ያወጣ ዘንድ ላከው። ኢየሱስ እኛ ልንፈጽመው ላልቻልነው ሕግ ቅጣትን ሁሉ ተቀበለ፣ ከዘላለም ሞት አምልጠን በነጻነት ከእርሱ ጋር የዘላለም ሕይወት ተካፋዮች እንድንሆን አደረገን። ኢየሱስ ጻድቅ እና ቅዱስ ሆነን በእግዚአብሔር አብ ፊት የምንቆምበትንና በሕግ የተቀመጡትን ግዴታዎች ሁሉ የተወጣንበትን የጽድቅ ሰጦታ ሰጠን። እርሱ በሞቱ፣ በመቀበሩና በትንሳኤው በፈጸመልን ሥራ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ሆነልን። ከእግዚአብሔርም፣ ያልለፋንበትንና ይገባናል የማንለውን ሞገስ አገኘን። ይህም ጸጋ ይባላል።

ይህን በማመን፣ ይህን ያደረገበት ምክንያት ስለሚያፈቅራችሁ እንደሆነ በማወቅ፣ ልባችሁ ያለ እንዳች ማወላወል ሊያርፍ ይገባል። ልባቸሁን በጸጋው ንቁ፣ ጥብቅ፣ የተደላደለ እና ጽኑ እንዲሆን አድርጉ፤ ይኸውም፣

ለሕይወት የሚያስፈልገንን የተትረፈረፈ ሕይወት በኢየሱስ እና በእርሱ በኩል እንደሰጠን ያለ ምንም ጥያቄ ወይም ጥርጣሬ ተቀበሉ።

ከእምነታችን ጀማሪ እና ፈጻሚ፣ ከኢየሱስ፣ ይልቅ ወደ እጥረቶቻችን፣ ጉድለቶቻችን፣ ስህተቶቻችን እና ኃጢአቶቻችን ትኩረት የምናደርግና የምንመለከት ከሆነ ግን ልባችን ከእግዚአብሔር፣ በእምነት ማንኛውንም ነገር መቀበል የማይችል ደካማ እና ብሶተኛ ይሆናል። ጸጋና ጽድቅን እምነን የምንቀበለው በልባችን ነው። ልባችን ሙሉ በሙሉ የእርሱ ሊሆን ይገባል። ያኔ ነው በእርሱ ማረፍና ፍጹም መከናወን የሚሆንልን።

“እጥብቀህ ልብህን ጠብቅ፣ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና።” (ምሳሌ 4፡23)

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. በዚህ ትምህርት “ጸጋ” እንዴት ነው የተገለጸው?

2. ልባችን በጸጋ ከጸና በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት የእራሳችን ________ ሙከራ እናደርግም።

3. ዕብራውያን 10፡14ን እንብቡና ጸሐፊው ጉድለቶቹ ሁሌም ፍጹም እንዳይሆን እያደረጉት እንደ ነበር ይናገራል። በዚህ ጥቅስ መሰረት ፍጹም መሆን የምንችለው እንዴት ነው?

   **ዕብራውያን 10፡14** *“አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጎአቸዋልና።”*

4. ሮሜ 5፡17 ኢየሱስ፣ በእግዚአብሔር አብ ፊት ጻድቅና ቅዱስ ሆነን ሕጉ የሚያዘውን ሁሉ የምንፈጽምበትን የጽድቅን ________ ሰጠን

   **ሮሜ 5፡17** *“በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ፥ ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ።”*

5. ኢሳይያስ 26፡3፣ በእምነታችን ጀማሪ እና ፈጻሚ በኢየሱስ ላይ ሳይሆን ትኩረታችን በስህተቶቻችን፣ ጉድለቶቻችን እና ኃጢአታችን ላይ ከሆነ ልባችን ከእግዚአብሔር አንዳች በእምነት ሊቀበል የማይችል ደካማና አቅመ ቢስ ሆናል። ልባችንን በምን ላይ ልናደርግ ይገባል?

   **ኢሳይያስ 26፡3** *“በአንተ ታምናለችና በአንተ ለምትደገፍ ነፍስ ፈጽመህ በሰላም ትጠብቃታለህ። ሰው የሚድነው እንዴት ነው?”*

6. ኤፌሶን 3፡17፣ ልባችን ሙሉ በሙሉ የእርሱ ሊሆን ይገባል፣ ያን ጊዜ ________ እንሆናለን።

   **ኤፌሶን 3:17** *“በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነክሩ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ ባለ ጠግነት መጠን ይሰጣችሁ፤ የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ፥”*

7. ሮሜ 4፡5 ድኅነት (መዳን) ለውጤታችሁ የሚሰጥ ሽልማት ነው ወይስ የእግዚአብሔር ነጻ የጸጋ ስጦታ?

   **ሮሜ 4፡5** *“ነገር ግን ለማይሠራ፥ ኃጢአተኛውንም በሚያጸድቅ ለሚያምን ሰው እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቆጠርለታል።”*

8. ሮሜ 5፡17 ጽድቅ (በእግዚአብሔር ቀኝ መቆም) ስጦታ ነው። ለስጦታ መስራት ይገባል? ስጦታን እንዴት ትቀበላላችሁ?

   **ሮሜ 5፡17** *“በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ፥ ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ።”*

9. ሮሜ 6፡23፣ በዚህ ጥቅስ የእግዚአብሔር ጸጋ ነጻ ስጦታ ምንድን ነው?

**ሮሜ 6፡23** *"የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው።"*

10. ቲቶ 3፡5 ምን ያህሉ የእናንተ መልካም ሥራዎችና ተግባሮች ለመዳናችሁ አስተዋጽኦ አድርገዋል?

    **ቲቶ 3፡5** *"እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ፥ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለ ነበረው ሥራ አይደለም፤"*

11. ሮሜ 6:14 ከእግዚአብሔር ጸጋ በታች መሆን ምን ማለት እንደሆነ በራሳችሁ አብራሩ።

    **ሮሜ 6፡14** *"ኃጢአት አይገዛችሁምና፤ ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁምና።"*

12. ሮሜ 11፡6 የእግዚአብሔር በረከት በጸጋ የተሰጠን ከሆነ በራሳችን __________ አይደለም።

    **ሮሜ 11፡6** *"በጸጋ ከሆነ ግን ከሥራ መሆኑ ቀርቶአል፤ ጸጋ ያለዚያ ጸጋ መሆኑ ቀርቶአል።"*

13. ሮሜ 3፡24 ይህን ጥቅስ በራሳችሁ ቃል አብራሩ።

    **ሮሜ 3፡24** *"በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ።"*

14. ኤፌሶን 1፡7 የኃጢአታችንን ይቅርታ ያገኘነው እንደ __________ ነበር።

    **ኤፌሶን 1፡7** *"በውድ ልጁም፥ እንደ ጸጋው ባለ ጠግነት መጠን፥ በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ስርየት።"*

# ጠቋሚ መልሶች

1. በዚህ ትምህርት “ጸጋ” እንዴት ነው የተገለጸው?
**ያልለፋንበት፣ ይገባናል የማንለው ሞገስ እና የእግዚአብሔር ችሎታ።**

2. ልባችን በጸጋ ከጸና በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት የእራሳችን _______ ሙከራ አናደርግም።
**ጥረት።**

3. ዕብራውያን 10:14ን አንብቡና ጸሐፊው ጉድለቶቹ ሁሌም ፍጹም እንዳይሆን እያደረጉት እንደ ነበር ይናገራል። በዚህ ጥቅስ መሰረት ፍጹም መሆን የምንችለው እንዴት ነው?
**በኢየሱስ አንድ ጊዜ በማቅረብ፣ የዘላለም ፍጹማን አድርጎናል።**

4. ሮሜ 5:17 ኢየሱስ፣ በእግዚአብሔር አብ ፊት ጻድቅና ቅዱስ ሆነን ሕጉ የሚያዘውን ሁሉ የምንፈጽምበትን የጽድቅን ________ ሰጠን።
**ስጦታ።**

5. ኢሳይያስ 26:3፣ በእምነታችን ጀማሪ እና ፈጻሚ በኢየሱስ ላይ ሳይሆን ትኩረታችን በስህተቶቻችን፣ ጉድለቶቻችን እና ኃጢአታችን ላይ ከሆነ ልባችን ከእግዚአብሔር እንዳች በእምነት ሊቀበል የማይችል ደካማና አቅመ ቢስ ይሆናል። ልባችንን በምን ላይ ልናደርግ ይገባል?
**አእምሮአችን በእርሱ ላይ ልናደርግ ይገባል።**

6. ኤፌሶን 3:17፣ ልባችን ሙሉ በሙሉ የእርሱ ሊሆን ይገባል፣ ያን ጊዜ ________ እንሆናለን።
**ይከናወንልናል፣ እናርፋለን።**

7. ሮሜ 4:5 ድኅነት (መዳን) ለውጤታችሁ የሚሰጥ ሽልማት ነው ወይስ እግዚአብሔር በጸጋ የሰጣችሁ ነጻ ሰጦታ?
**እግዚአብሔር በጸጋ የሰጠን ነጻ ስጦታ።**

8. ሮሜ 5:17 ጽድቅ (በእግዚአብሔር ቀኝ መቆም) ስጦታ ነው። ለስጦታ መስራት ይገባል?
**አይገባም።**
ስጦታን እንዴት ትቀበላላችሁ?
**እንዲሁ እጃችን ዘርግተን በመቀበል።**

9. ሮሜ 6:23፣ በዚህ ጥቅስ መሰረት የእግዚአብሔር ጸጋ ነጻ ስጦታ ምንድን ነው?
**የዘላለም ሕይወት (በዘላለም ሞት ፋንታ)።**

10. ቲቶ 3:5 ምን ያህሉ የእናንተ መልካም ሥራዎችና ተግባሮች ለመዳናችሁ አስተዋጽኦ አድርገዋል?
**ምንም።**

11. ሮሜ 6:14 ከእግዚአብሔር ጸጋ በታች መሆን ምን ማለት እንደሆነ በራሳችሁ አብራሩ።
**በኃጢአታችን የሚገባን ቅጣት አላገኘንም፣ ይልቁንም በክርስቶስ የእግዚአብሔር መልካም ነገሮች ሁሉ ሆነውልናል። ጽድቅ፣ ተቀባይነት፣ ምህረት ሁሉ የእኛ ናቸው (ሁሉም በእግዚአብሔር ምህረት ስጦታ ሆነውልናል)።**

12. ሮሜ 11፡6 የእግዚአብሔር በረከት በጸጋ የተሰጠን ከሆነ በራሳችን __________ አይደለም።
    ***ሥራ*** **።**

13. ሮሜ 3፡24 ይህን ጥቅስ በራሳችሁ ቃል አብራሩ።
    **ጽድቅ (ተቀባይነት) በክርስቶስ የመስቀል ሥራ እርሱ ቤዛ በመሆኑ ለሚያምኑ ሁሉ የተሰጠ ነጻ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ነው።**

14. ኤፌሶን 1፡7 የኃጢአታችንን ይቅርታ ያገኘነው እንደ __________ ነበር።
    **እንደ እግዚአብሔር የጸጋው ባለ ጠግነት መጠን።**

# ትምህርት 10

# የኃጢአት እውቀት ቀርቷል

## በዶን ክሮው

አንድ ቀን በመጠጥ የሰከረ አንድ ሰው፣ መኪናው ውስጥ ገብቶ በተሳሳተ አቅጣጫ በማሽከርከር ላይ እንዳለ ከተቃራኒ አቅጣጫ መስመሩን ጠብቆ ከሚመጣ ሌላ ተሽከርካሪ ጋር ፊት ለፊት ተጋጨ። በዚህ አደጋ አንዲት የአስራ ሰምንት ዓመት ወጣት ህይወት በማለፉ የወጣቷ ቤተሰቦች በሰውዬው ላይ ክስ መሰርተው የ1.5 ሚሊዬን ዶላር ካሳ እንዲከፈላቸው ተወስነላቸው።

ነገር ግን የልጅቱ ቤተሰቦች የተወሰነላቸውን ገንዘብ ከመውሰድ ይልቅ 936 ዶላር ብቻ እንዲከፈላቸው ይሰማማሉ። ምክንያታቸውም ሰውዬው ይህን ገንዘብ ለዬት ባለ መልኩ እንዲከፍላቸው በመፈለጋቸው ነበር። ይህ ሰው በሰካር ምክንያት ያጠፋውን ጥፋት እንዲያስታውስ ፈጽሞ እንዳይረሳ ፈልገዋል። በየሳምንቱ የአንድ ዶላር ቼክ በሟቿ ወጣት ሰም እየጻፈ ለቤተሰቡ እንዲልክላቸው ነበር ሰምምነታቸው። 1.5 ሚሊዮን ዶላር ከመክፈል ይልቅ 936 ዶላር መክፈል ያለጥርጥር ለሰውዬው የተሻለ እድል ነው ብላችሁ ታሰቡ ይሆናል። መጀመሪያ ላይ የአንድ ዶላር ቼክ ክፍያ በየሳምንቱ መክፈል በእርግጥ ቀላል ነበር፣ እየቆየ ግን በገደላት ልጅ ሰም ቼክ እየቆረጠ መላክ አዕምሮውን ያቆሰለው ጀመር። በየሳምንቱ የገደላትን ልጅ በማስታወስ ጸጸትና ተሰፋ መቁረጥ ውስጥ ይገባ ጀመር።

ይህን እያደረገ የተወሰኑ ዓመታትን ካሳለፈ በኃላ በመጨረሻ ክፍያውን መላክ አቋረጠ። የሟች ቤተሰብም እንደገና ፍርድ ቤት አቆሙትና ክፍያውን መላክ እንዲጀምር ተደረገ። ላለፉት ሰድት እና ሰባት ዓመታት አራት ወይም አምስት ጊዜ የሚሆን ክፍያውን መላክ አቋርጦ ነበር። ነገር ግን ባቋረጠበት ጊዜ ሁሉ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ያደርጉትና ክፍያውን መላክ እንዲጀምር ይደረጋል።

የሟቿ ቤተሰቦች ከአሁን በኃላ ምንም ቁጣ የሌለባቸው መሆኑን፣ ነገር ግን እርሱ ያደረገውን ሥራውን እንዲያስታውስ ብለው ያደረጉት መሆኑን ይናገራሉ።

ልብ ብላችሁ ካሰተዋላችሁ በየሳምንቱ የአንድ ዶላር ቸክ የሚልከው ጥፋተኛው ሰው እሰራት ውስጥ ነበር፣ ነገር ግን  እርሱ ብቻ ሳየሆን ቼክ የሚላክለት ያ ቤተሰብም ቢሆን እሰራት ውስጥ ነበር። በየሳምንቱ ያጧትን ልጃቸውን የሚያስታውሳቸው ቼክ በደረሳቸው ቁጥር የልጃቸውን ሞት እነርሱም ወደ ኋላ ትተው መርሳት አይችሉም ነበር ማለት ነው።

ሰውዬውም “ያልተለመደ የጭካኔ ቅጣት” ብሎ በጠራው ጭብጥ፣ አሰቃይተውኛል፣ በሚል በሟቿ ቤተሰብ ላይ ፋይል ከፍቶባቸዋል። እርሱ እንደሚለው “ቅጣታቸው እየገደለኝ ነው፣ ህይወቴን አበላሽቶታል፣ ያለፈውን ወደ ኋላ ትቼ ሕይወቴን እንዳልመራ አድርገውኛል” ሲል ይናገራል።

ልክ እንደዚህ ታሪክ በተመሳሳይ ፍርድ ሰር እንደሆኑ የሚሰማቸው ብዙ፣ እጅግ ብዙ ክርሰቲያኖች አጋጥመውኛል። “ሁሉንም ኢየሱስ ከፍሏል” ተብሎ ቢነገራቸውም እነርሱ ግን ሳምንታዊ ክፍያ ወይም ሐይማኖታዊ ግዴታ መፈጸም እንዳለባቸው ካልሆነ ግን እግዚአብሔር እንደማይቀበላቸው ያሰባሉ።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ጉደዩ በሂደት ላይ በነበረበት ጊዜ ይህ ሰው ከልጅቱ ቤተሰብ ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት ሊኖረው ይችላል?

2. ዕብራውያን 10፡1 እንብቡና ሕጉ ሊፈጽም ያልቻለው ምንድን ነው?

   **ዕብራውያን 10፡1** *"ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር እውነተኛ አምሳል ሳይሆን የነገር ጥላ አለውና፥ ስለዚህም በየዓመቱ ዘወትር በሚያቀርቡት በዚያ መሥዋዕት የሚቀርቡትን ሊፈጽም ከቶ አይችልም።"*

3. ዕብራውያን 10፡1 ን እንብቡና በአሮጌው ኪዳን የሚደረጉ መስዋዕቶች ፍጹም ሊያደርጉን እንደማይችሉ ይህ ጥቅስ ምን ያጠቁመናል?

4. ዕብራውያን 10፡2 ኃጢአት ማሰወገድ የሚችል መሰዋዕት ሲመጣ ለአማኞች ምን ያደርግላቸዋል?

   **ዕብራውያን 10፡2** *"እንደዚህማ ባይሆን፥ የሚያመልኩት አንድ ጊዜ ነጽተው ከዚያ በኋላ በሕሊናቸው ኃጢአትን ሰላላወቁ ማቅረብን በተዉ አልነበረምን?"*

5. ሰካራሙ አሽከርካሪ ምን እንዲያደርግ ተገደደ?

6. ዕብራውያን 10፡14 እግዚአብሔር ሕዝቡን ፍጹም የሚያደርገው፡

   ሀ. በበጎ ሥራቸው
   ለ. ቤተ ክርስቲያን በመሄዳቸው
   ሐ. አሰርቱ ትዕዛዛትን በመጠበቃቸው
   መ. በኢየሱሰ ባቀረበው (መሰዋዕት)

   **ዕብራውያን 10፡14** *"አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጎአቸዋልና።"*

7. ዕብራውያን 10፡14 ኢየሱሰ ያቀረበው (በእምነት በመቀበል) አማኙን ፍጹም የሚያደርገው፡

   ሀ. ሌላ ኃጢአት እሰኪሰሩ ድረሰ
   ለ. ካለፈው ኃጢአታቸው
   ሐ. ለዘላለም

8. ዘፍጥረት 20፡1-18 በዚህ ታሪክ የተጠቀሱት ሁለት ሰዎች እንማን ናቸው?

   **ዘፍጥረት 20፡1-18** *"አብርሃምም ከዚያ ተነሥቶ ወደ አዜብ ምድር ሄደ፥ በቃዴስና በሱር መካከልም ተቀመጠ፤ በጌራራም በእንግድነት ተቀመጠ። [2] ፤ አብርሃምም ሚሰቱን ሣራን። እኅቴ ናት አለ፤ የጌራራ ንጉሥ አቢሜሌክም ላከና ሣራን ወሰዳት። [3] ፤ እግዚአብሔርም ሌሊት በሕልም ወደ አቢሜሌክ መጣ፥ እንዲህምአለው። እነሆ፥ አንተ ሰለ ወሰድሃት ሴት ምውት ነህ፤ እርሰዋ ባለ ባል ናትና። [4] ፤ አቢሜሌክ ግን አልቀረባትም ነበር፤ እንዲህም አለ። አቤቱ፥ ጻድቁን ሕዝብ ደግሞ ታጠፋለህን? [5] ፤ እኅቴ ናት ያለኝ እርሱ አይደለምን? እርሰዋም ደግሞ ራሰዋ። ወንድሜ ነው አለች፤ በልቤ ቅንነትና በእጄ*

*ንጹሕነትይህንንአደረግሁ።[6]፤እግዚአብሔርምበሕልምአለው።ይህንበልብህቅንነትእንዲደረግህእኔአወቅሁ፥ እኔም ደግሞ በፊቴ ኃጢአትን እንዳትሠራ ከለከልሁህ፤ ስለዚህም ትነካት ዘንድ አልተውሁም።[7] ፤ አሁንም የሰውዬውን ሚስት መልስ፤ ነቢይ ነውና፥ ስለ አንተም ይጸልያል፥ ትድናለህም። ባትመልሳት ግን አንተ እንድትሞት ለአንተ የሆነውም ሁሉ እንዲሞት በእርግጥ እወቅ። [8] ፤ አቢሜሌክም በነገታው ማለደ፥ ባሪያዎቹንም ሁሉ ጠራ፥ይህንንምነገርሁሉበጆሮአቸውተናገረ፤ሰዎቹምእጅግፈሩ።[9]፤አቢሜሌክምአብርሃምንጠርቶአለው። ይህ ያደረግህብን ምንድር ነው? ምንስ ክፉ ሠራሁብህ? በእኔና በመንግሥቴ ላይ ትልቅ ኃጢአት አውርደሃልና፤ የማይገባ ሥራ በእኔ ሠራህብኝ። [10] ፤ አቢሜሌክም አብርሃምን አለው። ይህን ማድረግህ ምን አይተህ ነው? [11] ፤ አብርሃምም አለ። በዚህ ስፍራ እግዚአብሔርን መፍራት በእውነት እንደሌለ፥ ለሚስቴም ሲሉ እንደሚገድሉኝ ሰላሰብሁ ነው። [12] ፤ እርስዋም ደግሞ በእውነት እኅቴ ናት፤ የእናቴ ልጅ አይደለችም እንጂ የአባቴ ልጅ ናት፤ ለእኔም ሚስት ሆነች። [13] ፤ እግዚአብሔርም ከአባቴ ቤት ባወጣኝ ጊዜ አልኋት። በገባንበት አገር ሁሉ ለእኔ የምታደርጊው ወሮታ ይህ ነው። ወንድሜ ነው ብለሽ ስለ እኔ ተናገሪ። [14] ፤ አቢሜሌክም በጎችንና ላሞችን ወንዶችና ሴቶች ባሪያዎችን አመጣ፥ ለአብርሃምም ሰጠው፥ ሚስቱን ሣራንም መለሰለት። [15] ፤ አቢሜሌክም። እነሆ፥ ምድሬ በፊትህ ናት፤ በወደድኸው ተቀመጥ አለ። [16] ፤ ሣራንም አላት። እነሆ፥ ለወንድምሽ ሺህ ሚዛን ብር ሰጠሁት፤ ያም እነሆ ከአንቺ ጋር ባሉት ሁሉ ፊት የዓይኖች መሸፈኛ ይሁንሽ፤ ጽድቅሽ ለሰዎች ሁሉ ተገልጦአልና። [17] ፤ አብርሃምም ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ እግዚአብሔርም አቢሜሌክን ሚስቱንም ባሪያዎቹንም ፈወሳቸው፥ እነርሱም ወለዱ፤ [18] ፤ እግዚአብሔር በአብርሃም ሚስት በሣራ ምክንያት በአቢሜሌክ ቤት ማኅፀኖችን ሁሉ በፍጹም ዘግቶ ነበርና።”*

9. ዘፍጥረት 20:2 እና 5፣ በዚህ ታሪክ ከሁለቱ ሌላውን የዋሸውና ያታለለው ማን ነበር?

10. ዘፍጥረት 20:7 እግዚአብሔር የአብርሃምን ድርጊት እንደማይደግፍ እርግጠኛ ነኝ፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ከማን ጎን ነበር፣ ከአብርሃም ነው ከአቤሜሌክ?

11. ለምን? ዘፍጥረት 15:1፣ 18 እና ያዕቆብ 2:23 ን አንብቡ።

    **ዘፍጥረት 15:1** *“ከዚህ ነገር በኋላም የእግዚአብሔር ቃል በራእይ ወደ አብራም መጣ፥ እንዲህ ሲል። አብራም ሆይ፥ አትፍራ፤ እኔ ለአንተ ጋሻህ ነኝ፤ ዋጋህም እጅግ ታላቅ ነው።”*

    **ዘፍጥረት 15:18** *“በዚያ ቀን እግዚአብሔር ለአብራም እንዲህ ብሎ ቃል ኪዳን አደረገ። ከግብፅ ወንዝ ጀምሮ እስከ ትልቁ ወንዝ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ይህችን ምድር ለዘርህ ሰጥቼአለሁ፤”*

    **ያዕቆብ 2:23** *“መጽሐፍም። አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት ያለው ተፈጸመ፤ የእግዚአብሔርም ወዳጅ ተባለ።”*

12. ዘፍጥረት 20:7 እና 17-18 አንብቡና ምንም እንኳን ጥፋተኛው አብርሃም ቢሆንም እግዚአብሔር ግን ማን ለማን እንዲጸልይ አዘዘ?

    ሀ. አብርሃም ለአቢሜሌክ እንዲጸልይ
    ለ. አቢሜሌክ ለአብርሃም እንዲጸልይ
    ሐ. እንዳቸው ለአንዳቸው እንዲጸልዩ

13. ሮሜ 8:31 ምንም እንኳን አንዳንዴ ብንሰናከልም ማን ከጎናችን ነው?

**ሮሜ 8፡31** *“እንግዲህ ስለዚህ ነገር ምን እንላለን? እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?”*

14. ሮሜ 4፡8 ምንም ብንሳሳት እግዚአብሔር ግን ምን አላደርግም ብሏል?

    **ሮሜ 4፡8 “** *ጌታ ኃጢአቱን የማይቆጥርበት ሰው ብጹዕ ነው።”*

15. ዕብራውያን 8፡12-13 በአዲስ ኪዳን፣ እግዚአብሔር ምን ላለማድረግ ተሰፋ ሰጥቷል?

    **ዕብራውያን 8፡12-13** *“ዓመፃቸውን እምራቸዋለሁና፥ ኃጢአታቸውንም ደግሜ አላስብም። [13] አዲስ በማለቱ ፊተኛውን አሰረጅቶአል፤ አሮጌና ውራጅ የሆነውስ ሊጠፋ ቀርቦአል።”*

16. ኤፌሶን 2፡5 እና 8-9፣ መዳናችን ያገኘነው እንዴት ነው?

    **ኤፌሶን 2፡5** *“ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፥ በጸጋ ድናችኋልና፥”*

    **ኤፌሶን 2፡8-9** *“ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ [9] ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።”*

17. ቲቶ 3፡5 የማንድነውስ እንዴት ነው? እንዴት ነው የዳንነው?”

    **ቲቶ 3፡5** *“እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ፥ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ሰለ ነበረው ሥራ አይደለም፤*

18. ኤፌሶን 1፡5-6፣ እግዚአብሔር ሁላችንንም በ________ ሰላዳነን ለዘላለም እናመሰግነዋለን። በውዱ (በክርስቶስ ኢየሱስ) ________ አድርጎናል።

    **ኤፌሶን 1፡5-6** *“በበጎ ፈቃዱ እንደ ወደደ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አሰቀድሞ ወሰነን። [6] በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ይህን አደረገ።”*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ጉዳዩ በሂደት ላይ በነበረበት ጊዜ ይህ ሰው ከልጅቱ ቤተሰብ ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት ሊኖረው ይችላል?
**ያለ ምህረት፣ በምሬት እና በቁጣ የተሞላ ግንኙነት።**

2. ዕብራውያን 10፡1 አንብቡና ሕጉ ሊፈጽም ያልቻለው ምንድን ነው?
**የሚቀርቡትን ፍጹም ሊያደርጋቸው አይችልም (ያለ ችግር ወይም ያለ ጥፋት)።**

3. ዕብራውያን 10፡1 ን አንብቡና በአሮጌው ኪዳን የሚደረጉ መስዋዕቶች ፍጹም ሊያደርጉን እንደማይችሉ ይህ ጥቅስ ምን ያጠቁመናል?
**በተደጋጋሚ፣ በተከታታይ - በየቀኑ፣ በየሳምንቱ፣ በየወሩ ይደረጉ ነበር። በተደጋጋሚ መደረጋቸው ኃጢአትን በቋሚነት ሊያስወግዱ እንደማይችሉ ያረጋግጣል።**

4. ዕብራውያን 10፡2 ኃጢአት ማስወገድ የሚችል መስዋዕት ሲመጣ ለአማኞች ምን ያደርግላቸዋል?
**ትኩረታቸው ኃጢአት ላይ እንዳይሆን ያደርጋቸዋል (ሁሌ በኃጢአት እንደይወቀሱ)።**

5. ሰካራሙ አሽከርካሪ ምን እንዲያደርግ ተገደደ?
**ኃጢአቱን ሁልጊዜ እንዲያስታውስ።**

6. ዕብራውያን 10፡14 እግዚአብሔር ሕዝቡን ፍጹም የሚያደርገው፡
**መ. በኢየሱስ ባቀረበው (መስዋዕት)።**

7. ዕብራውያን 10፡14 ኢየሱስ ያቀረበው (በእምነት በመቀበል) አማኙን ፍጹም የሚያደርገው፡
**ሐ. ለዘላለም።**

8. ዘፍጥረት 20፡1-18 በዚህ ታሪክ የተጠቀሱት ሁለት ሰዎች እነማን ናቸው?
**አብርሃምና አቢሜሌክ።**

9. ዘፍጥረት 20፡2 እና 5፣ በዚህ ታሪክ ከሁለቱ ሌላውን የዋሸውና ያታለለው ማን ነበር?
**አብርሃም።**

10. ዘፍጥረት 20፡7 እግዚአብሔር የአብርሃምን ድርጊት እንደማይደግፍ እርግጠኛ ነኝ፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ከማን ጎን ነበር፣ ከአብርሃም ነው ከአቤሜሌክ?
**ከአብርሃም።**

11. ለምን? ዘፍጥረት 15፡1፣ 18 እና ያዕቆብ 2፡23 ን አንብቡ።
**አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር ኪዳን ስለነበረውና የእግዚአብሔር ወዳጅ ስለ ነበረ።**

12. ዘፍጥረት 20፡7 እና 17-18 አንብቡና ምንም እንኳን ጥፋተኛው አብርሃም ቢሆንም እግዚአብሔር ግን ማን ለማን እንዲጸልይ አዘዘ?
**ሀ. አብርሃም ለአቢሜሌክ እንዲጸልይ።**

13. ሮሜ 8፡31 ምንም እንኳን እንዳንዴ ብንሰናከልም ማን ከጎናችን ነው?
**እግዚአብሔር።**

14. ሮሜ 4፡8 ምንም ብንሳሳት እግዚአብሔር ግን ምን አላደርግም ብሏል?
**ኃጢአታችን አይቆጥርብንም፣ ማለትም በኃጢአታችን ተጠያቂ እንዳንሆን አድርጎናል።**

15. ዕብራውያን 8፡12-13 በአዲስ ኪዳን፣ እግዚአብሔር ምን ላለማድረግ ተስፋ ሰጥቷል?
**ኃጢአታችንን ደግሞ አያስብም፣ ኃጢአታችን ተጠያቂ አያደርገንም።**

16. ኤፌሶን 2፡5 እና 8-9፣ መዳናችን ያገኘነው እንዴት ነው?
**በጸጋ፣ እርሱ ለእኛ ባለው ያልተገደበ ደግነትና ርህራሄ።**

17. ቲቶ 3፡5 የማንድነውስ እንዴት ነው?
**እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለ ነበረው ሥራ አይደለም፤።**
እንዴት ነው የዳንነው?”
**እንደ ምህረቱ፣ በአዲስ ውልደት በመታጠብ፣ በመንፈስ ቅዱስም አዲስ ስላደረገን**

18. ኤፌሶን 1፡5-6፣ እግዚአብሔር ሁላችንንም በ________ ስላዳነን ለዘላለም እናመሰግነዋለን። በውዱ (በክርስቶስ ኢየሱስ) ________ አግኝተናል።
**ጸጋ / ተቀባይነት።**

# ትምህርት 11

# ተወዳጅ ነኝ፣ ውብ ነኝ

## በዶን ክሮው

አንድ ማይክል የሚባል ወዳጄ ስለ አንዲት ተማሪው ምስጢራዊ ታሪክ ሊያጫውተኝ አንድ ቀን ወደ ቢሮዬ መጥቶ ነበር። ካሪስ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ በሚያስተምርበት ወቅት በነበረው አንድ ክፈለ ጊዜ ፓትሪሻ የተባለች ተማሪ በደብተሯ ላይ አንዳንድ ማስታወሻዎችን ስለ ራሷ እየጻፈች ነበር። ማስታወሻዋም የሚከተሉትን ዓይነት ቃላት የያዘ ነበር - “ተወዳጅ ነኝ፣ ውብ ነኝ” ወዘተ...። ፓትሪሻ ሁሌም ለአለባበሷ የምትጠነቀቅ ለራሷ ትኩረት የምትሰጥ ዓይነት ወጣት ነች። እነዚህን ሃሳቦች የምታንጸባርቅበት እውነተኛው ምክንያት ግን የተወደደችም፣ ውብ እንደ ሆነችም ስለማይሰማት ነበር፤ እንደማትወደድና እንደማትፈለግ ይሰማት ነበር።

ሰው በመሆናችን ሁላችንም ተመሳሳይ ፍላጎቶች አሉን - የመወደድ ፍላጎት፣ ተቀባይነት የማግኘት እና ተፈላጊነት ብሎም ለራሳችን ዋጋ የመስጠት እና በእግዚአብሔር ፊት ትክክል ሆኖ የመገኘት ፍላጎቶች አሉን። ዛሬ ላይ ሐይማኖት በአብዛኛው እንደተወደድን ሳይሆን ተወዳጅ እንዳልሆንን እንዲሰማን ያደርጋል፣ ዋጋ እንደሌለን እና ተቀባይነት እንደሌለን ይሰማናል። ምንም እንኳን ፍጹም መንፈሳዊ እንደሆንን እየተሰማንም ቢሆን፣ ሰይጣን አማኞችን ከሚያጠቃባቸው ጠንካራ ምሽጎች ውስጥ ዋናው የጥፋተኝነት፣ የጸጸት እና ራስን የመኮነን ስሜቶች ናቸው።

አንድ ጥያቄ ላቅርብላችሁ፣ በመጀመሪያ ወደ ጌታ በመጣችሁ ጊዜ እርሱ እንደሚወዳችሁ ብቻ ሳይሆን፣ እርሱን በመቀበላችሁ፣ ለእናንተ ፍጹም ጽድቅ እንደሆነላችሁ የተነገራችሁ ስንቶቻችሁ ናችሁ? በእርግጥ በእርሱ የሆነላችሁ ጽድቅ ለእናንተ የሚያስፈልጋችሁ ጽድቅ፣ አንድም ሳይጎድል ሙሉ በሙሉ ነው (1ኛ ቆሮንቶስ 1፡30-31) እንዲህ ይላል “ነገር ግን። የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ ተብሎ እንደ ተጻፈው ይሆን ዘንድ፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ጽድቅ ቅድስናም ቤዛነትም በተደረገልን በክርስቶስ ኢየሱስ የሆናችሁ ከእርሱ ነው።” ይህ ነው የወንጌል የምስራች። “በወንጌል አላፍርምና፤ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው፥ ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና። ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎ እንደ ተጻፈ የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ ይገለጣልና።” (ሮሜ 1፡16-17)። “ነገር ግን ለማይሠራ፥ ኃጢአተኛውንም በሚያጸድቅ ለሚያምን ሰው እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቆጠርለታል።” (ሮሜ 4፡5)። እግዚአብሔር፣ በእምነት ላይ እምነት፣ ወይም ለነገሮቻችን እምነት እንዲኖረን አልጠራንም፣ ነገር ግን በእርሱ እንድንተማመን፣ እንድንደገፍና ሙሉ እምነት በእርሱ እንዲኖረን ይፈልጋል።

እግዚአብሔር ቀድሞ ከሚወዳችሁ የተለየ ወይም የበለጠ ሌላ ፍቅር የለውም። እግዚአብሔር ፍቅር ነው (1ኛ ዮሐንስ 4፡8)። ነገር ግን በእናንተ በኩል ይበልጥ መቀበል ትችላላችሁ፣ ፍቅሩ ይበልጥ ሊሰማችሁ ይችላል፣ ደግሞም ይበልጥ ልትገለገሉበት ትችላላችሁ። ይበልጥ ባመናችሁት ቁጥር ይበልጥ እግዚአብሔርን ልትወዱት ትችላላችሁ። የእግዚአብሔር ቃል “እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን” ይላል (1ኛ ዮሐንስ 4፡19)። ይህን ሁሌም አስቡ፣ ይህን እመኑ፣ እናም ተቀበሉት!!

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ሮሜ 8፡38-39 አንብቡና፣ ሐዋርያው ጳውሎስ የተረዳው ምን ነበር?

   **ሮሜ 8፡38-39** *“ሞት ቢሆን፥ ሕይወትም ቢሆን፥ መላእክትም ቢሆኑ፥ ግዛትም ቢሆን፥ ያለውም ቢሆን፥ የሚመጣውም ቢሆን፥ ኃይላትም ቢሆኑ፥ [39] ከፍታም ቢሆን፥ ዝቅታም ቢሆን፥ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ።”*

2. በመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ በነበርኩበት ጊዜ፣ አንዳንድ ማስታወሻዎች የሚሰጠን አንድ ፕሮፌሰር ነበረ። ማስታወሻው እንዲህ የሚል ነበር “ጽድቅ ማለት የሚያምን ማንም ቢኖር እግዚአብሔር ጻድቅ ነህ ብሎ የፍርድ ውሳኔ የሚሰጥበት እንጂ እርሱን ጻድቅ አድርጎ የሚሰራበት አይደለም” ይላል። እኔም በእራሴ ቃሉን በማጠናበት ጊዜ ጽድቅ ማለት በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሚያደርጋችሁ የጽድቅ ስጦታ መሆኑን እርግጠኛ ሆኜ ነበር። ሮሜ 5፡19 ን አንብቡ። በኢየሱስ ክርስቶስ መታዘዝ (ሕግን በመፈጸሙና ወደ መስቀል በመሄዱም) ብዙዎች፡-

   ሀ. ጻድቅ እንደሆኑ ይታወጃል።
   ለ. ጻድቅ እንደሆኑ ይታሰባል።
   ሐ. ጻድቅ ይሆናሉ።

   **ሮሜ 5፡19** *“በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደ ሆኑ፥ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ።”*

3. 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21 “እኛ በእርሱ (በኢየሱስ ክርስቶስ) ሆነን የእግዚአብሔር ________ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን (ኃጢአት ሰርቶ የማያውቀውን) እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው”። (በቅንፍ ያለው ከራሴ ነው)

   **2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21** *“እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን የማያውቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው።”*

4. ቆላስያስ 1፡21-22፣ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር መጣ እና ስለ ኃጢአታችን ሞተ። በዚህ ምክንያትእግዚአብሔር ባለበት ቅዱስ፣ ያለ ነውር እና ያለ ነቀፋ ሆነን የምንቆመው፤

   ሀ. በባለቤታችሁ ዓይን።
   ለ. በጓደኞቻችሁ ዓይን።
   ሐ. በእግዚአብሔር ዓይን።

   **ቆላስያስ 1፡21-22** *“እናንተንም ነውርና ነቀፋ የሌላችሁና ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ ፊት ያቀርባችሁ ዘንድ፥ በፊት የተለያችሁትን ክፉ ሥራችሁንም በማድረግ በአሳባችሁ ጠላቶች የነበራችሁትን አሁን በሥጋው ሰውነት በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ።*

5. ኤፌሶን 1፡5-6 አንብቡና እግዚአብሔርን ስለጸጋው ለዘላለም እናመሰግነዋለን ምክንያቱም ________ ስላደረገን።

**ኤፌሶን 1፡5-6** *"በበጎ ፈቃዱ እንደ ወደደ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን። በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ይህን አደረገ።"*

6. ዕብራውያን 10፡14 በኢየሱስ እና በመስቀል ላይ መሰዋዕቱ፣ ለምን ያህል ጊዜ ፍጹም ሆነናል?

ሀ. ዳግመኛ ኃጢአት እስካልሰራችሁ።
ለ. ቤተ ክርስቲያን እስክትሄዱ።
ሐ. ለዘላለም።

**ዕብራውያን 10፡14** *"አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጎአቸዋልና።"*

7. ዕብራውያን 10፡15-17 በአዲሱ ኪዳን እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ማሰብ የሚፈልገው፡

ሀ. ኃጢአት በሰራን ጊዜ ሁሉ
ለ. አስራታችንን ባልከፈልን ጊዜ
ሐ. መቸም ቢሆን አያሰበውም

**ዕብራውያን 10፡15-17** *"መንፈስ ቅዱስም ደግሞ ስለዚህ ይመሰክርልናል፤ ከዚያ ወራት በኋላ ከእነርሱ ጋር የምገባው ኪዳን ይህ ነው ይላል ጌታ፤ በልባቸው ሕጌን አኖራለሁ በልቡናቸውም እጽፈዋለሁ [17] ብሎ ከተናገረ በኋላ፥ ኃጢአታቸውንና ዓመጻቸውንም ደግሜ አላስብም ይላል።"*

8. ሮሜ 6፡1-2 የእግዚአብሔር ጸጋ ከኃጢአታችን ሁሉ ይልቅ እጅግ ትልቅ ነው። የእግዚአብሔር ጸጋ ትልቅ ሆኖ ይታይ ዘንድ በኃጢአት መኖራችን መቀጠል ተገቢ ነው?

**ሮሜ 6፡1-2** *"እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? አይደለም። [2] ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደ ፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን?*

9. ዕብራውያን 9፡12፣ ኢየሱስ ምን ዓይነት መዋጀት (ከኃጢአት ቅጣት ነጻነት) ለእኛ አስገኝቶልናል፣

ሀ. ጊዜያዊ መዋጀት።
ለ. ከፊል መዋጀት።
ሐ. የዘላለም መዋጀት።

**ዕብራውያን 9፡12** *"የዘላለምን ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ ቅድሰት በገዛ ደሙ ገባ እንጂ በፍየሎችና በጥጆች ደም አይደለም።"*

10. ሮሜ 8፡33 እግዚአብሔር የመረጣቸውን ሊከሳቸው የሚችል ካለ፣ ማን ሊሆን ይችላል?

**ሮሜ 8፡33** *"እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፥ የሚኰንንስ ማን ነው?"*

11. ሮሜ 8፡34 የእግዚአብሔርን ሕዝብ ሊኮንን (ወደ ፍርድ ሊያመጣ) የሚችልስ ማን ነው?

**ሮሜ 8፡34** *"የሞተው፥ ይልቁንም ከሙታን የተነሣው፥ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፥ ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።"*

12. ሮሜ 8፡35 አንድን ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለይ የሚችል ካለ ማን ነው?

    **ሮሜ 8፡35** *"ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ፥ ወይስ ጭንቀት፥ ወይስ ስደት፥ ወይስ ራብ፥ ወይስ ራቁትነት፥ ወይስ ፍርሃት፥ ወይስ ሰይፍ ነውን?"*

13. ሮሜ 8፡31 የዚህ የደቀ መዝሙር ትምህርት ጥቅል ሃሳብ ምንድን ነው ትላላችሁ?

    **ሮሜ 8፡31** *"እንግዲህ ስለዚህ ነገር ምን እንላለን? እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?"*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ሮሜ 8፡38-39 አንብቡና፣ ሐዋርያው ጳውሎስ የተረዳው ምን ነበር?
**ከእግዚአብሔር ፍቅር ማንም ሊለየን እንዳይችል ተረድቶ ነበር - ሞት ቢሆን፣ ሕይወትም ቢሆን፣ መላእክትም ቢሆኑ፣ ግዛትም ቢሆን፣ ያለውም ቢሆን፣ የሚመጣውም ቢሆን፣ ኃይላትም ቢሆኑ፣ ከፍታም ቢሆን፣ ዝቅታም ቢሆን፣ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ካለ ፍቅር ሊለየን አይችልም።**

2. በመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ በነበርኩበት ጊዜ፣ አንዳንድ ማስታወሻዎች የሚሰጠን አንድ ፕሮፌሰር ነበረ። ማስታወሻው እንዲህ የሚል ነበር “ጽድቅ ማለት  የሚያምን ማንም ቢኖር እግዚአብሔር ጻድቅ ነህ ብሎ የፍርድ ውሳኔ የሚሰጥበት እንጂ እርሱን ጻድቅ አድርጎ የሚሰራበት አይደለም” ይላል። እኔም በእራሴ ቃሉን በማጠናበት ጊዜ ጽድቅ ማለት በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሚያደርጋችሁ የጽድቅ ስጦታ መሆኑን እርግጠኛ ሆኜ ነበር። ሮሜ 5፡19 ን አንብቡ። በኢየሱስ ክርስቶስ መታዘዝ (ሕግን በመፈጸሙና ወደ መስቀል በመሄዱም) ብዙዎች፡-
**ሐ. ጻድቅ ይሆናሉ።**

3. 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21 “እኛ በእርሱ (በኢየሱስ ክርስቶስ) ሆነን የእግዚአብሔር ________ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን (ኃጢአት ሰርቶ የማያውቀውን) እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው”። (በቅንፍ ያለው ከራሴ ነው)።
**“በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ”።**

4. ቆላስያስ 1፡21-22፣ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር መጣ እና ስለ ኃጢአታችን ሞተ። በዚህ ምክንያትእግዚአብሔር ባለበት ቅዱስ፣ ያለ ነውር እና ያለ ነቀፋ ሆነን የምንቆመው፤
**ሐ. በእግዚአብሔር ዓይን።**

5. ኤፌሶን 1፡5-6 አንብቡና እግዚአብሔርን  ስለጸጋው ለዘላለም እናመሰግነዋለን ምክንያቱም ________ ስላደረገን።
**በውድ ልጁ (በክርስቶስ) ተቀብሎናል።**

6. ዕብራውያን 10፡14 በኢየሱስ እና በመስቀል ላይ መስዋዕቱ፣ ለምን ያህል ጊዜ ፍጹም ሆነናል?
**ሐ. ለዘላለም።**

7. ዕብራውያን 10፡15-17 በአዲሱ ኪዳን እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ማሰብ የሚፈልገው፡
**ሐ. መቼም ቢሆን አያስበውም**።

8. ሮሜ 6፡1-2 የእግዚአብሔር ጸጋ ከኃጢአታችን ሁሉ ይልቅ እጅግ ትልቅ ነው። የእግዚአብሔር ጸጋ ትልቅ ሆኖ ይታይ ዘንድ በኃጢአት መኖራችን መቀጠል ተገቢ ነው?
**አይደለም። በፍጹም!**

9. ዕብራውያን 9፡12፣ ኢየሱስ ምን ዓይነት መዋጀት (ከኃጢአት ቅጣት ነጻነት) ለእኛ አስገኝቶልናል፣
**ሐ. የዘላለም መዋጀት።**

10. ሮሜ 8፡33 እግዚአብሔር የመረጣቸውን ሊከሳቸው የሚችል ካለ፣ ማን ሊሆን ይችላል?
**ማንም የለም።**

11. ሮሜ 8፡34 የእግዚአብሔርን ሕዝብ ሊኮንን (ወደ ፍርድ ሊያመጣ) የሚችልስ ማን ነው?
**ማንም የለም።**

12. ሮሜ 8፡35 አንድን ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለይ የሚችል ካለ ማን ነው?
**ማንም የለም።**

13. ሮሜ 8፡31 የዚህ የደቀ መዝሙር ትምህርት ጥቅል ሃሳብ ምንድን ነው ትላላችሁ?
**እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ስለሆነ ሊቃወመን የሚችል ማንም የለም።**

# ትምህርት 12

# የመዳን ፍሬ - ክፍል 1

## በዶን ክሮው

አንዴ በማመናችን የያዝነው እምነት፣ ቀጣይ ካልሆነ “ያድናል” ማለት ይቻላል? ሊቋረጥስ ይችል ይሆን፤ ከሆነስ የተሰጠው ተስፋ እንደተጠበቀ ሊቆይ ይችላል? አብርሃምም በእግዚአብሔር አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት (ዘፍጥረት 15፡6)። የአብርሃም እምነት ቢቋረጥ (ቢቆም) የተቆጠረለት ጽድቅ ይቋረጣል?

ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንረዳው “እምነት” አንዴ የሚደረግ ወይም የአንድ ጊዜ ፍጹም ድርጊት ሲሆን ነገር ግን በክርስትና ሕይወት ውስጥ ቀጣይ ሆኖ የሚኖር መሆኑን እንገነዘባለን። በአሁን ድርጊት የሚነገሩ ቃላት (present tense) ቀጣይነት ወይም ተከታታይ አፈጻጸም ያላቸው ናቸው። ያሁን ጊዜ ቃላትን ሰንጠቀም፣ የሚከተሉትን ቃላት ለመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢው የምናቀርብለት ከሆነ የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍሎች በይበልጥ መረዳት የሚችልበትን አቅም ይጨምሩለታል። ቃላቶቹም፡ - በተደጋጋሚ፤ ይኸውም ደጋግሞ፣ (በላይ - በላይ) እንደገና፣ በቋሚነት፣ በተከታታይ፣ እንደተለመደው፣ እንደ ልማድና የሕይወት ዘይቤ ወይም ሳይቋረጥ የሚሉ ቃላት ናቸው።

በሚከተሉት ጥቅሶች የአሁን ጊዜ (present tense) እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋለ እንመልከት፡

ዮሐንስ 3፡16 “በእርሱ የሚያምን ሁሉ [የአሁን ጊዜ፡ የሚያምን እና ደግሞም ማመኑን የሚቀጥል] የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና” (በቅንፍ ያለው በእኔ የተጨመረ ነው)።

ዕብራውያን 10፡14 “አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጎአቸዋልና” [የአሁን ጊዜ፡- እነዛን የተቀደሱትን፣ የተለዩትን እና ደግሞም በቀጣይነት መለዬታቸውን የሚቀጥሉትን ያ አንድ ጊዜ የቀረበ መሰዋዕት ፍጹም አድርጓቸዋል] (በቅንፍ ያለው በእኔ የተጨመረ ነው)።

1ኛ ዮሐንስ 3፡9 “ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም፣ [የአሁን ጊዜ፡ እንደ የሕይወት ዘይቤ አድርጎ በኃጢአት መኖርን አይቀጥልም፣ ይህም ንሰሐ የማይገባ ልብን የሚመለከት ነው] ዘሩ በእርሱ ይኖራልና፣ [የአሁን ጊዜ፡ የእግዚአብሔር ዘር በእርሱ ላይ ይኖራል፣ መኖሩንም ይቀጥላል] ከእግዚአብሔርም ተወልዶአልና ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም፤” (በቅንፍ ያለው በእኔ የተጨመረ ነው)።

ማርቆስ 1፡15 “…ዘመኑ ተፈጸመ የእግዚአብሔርም መንግስት ቀርባለች ንሰሐ ግቡ [የአሁን ጊዜ፡ ንሰሐ ግቡ ደግሞም እንደ ሁኔታውና አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ንሰሐ መግባታችሁን ቀጥሉ]፣ በወንጌልም እመኑ፤” (በቅንፍ ያለው በእኔ የተጨመረ ነው)።

ዮሐንስ 5፡24 “እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን [የአሁን ጊዜ፡ ማመኑንም የሚቀጥል] የዘላለም ሕይወት አለው፥ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም። (በቅንፍ ያለው በእኔ የተጨመረ ነው)።

ሉቃስ 15፡7 “እላችኋለሁ፥ እንዲሁ ንሰሐ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንሰሐ በሚገባ [የአሁን ጊዜ፡ እናም ንሰሐውን በሚቀጥል]፣ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል።” (በቅንፍ ያለው በእኔ የተጨመረ ነው)።

የሐዋርያት ሥራ 17፡30 “እንግዲህ እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንስሐ ይገቡ ዘንድ [የአሁን ጊዜ፡ በንስሐቸውም ይቀጥሉ ዘንድ]፣ ሰውን ሁሉ ያዛል፤ [የአሁን ጊዜ፡ ማዘዙም፣ ይቀጥላል]። (በቅንፍ ያለው በእኔ የተጨመረ ነው)።

ዮሐንስ 6፡47 “እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን [የአሁን ጊዜ፡ ማመኑንም የሚቀጥል] የዘላለም ሕይወት አለው።” (በቅንፍ ያለው በእኔ የተጨመረ ነው)።

ሮሜ 4፡5 “ነገር ግን ለማይሠራ፥ ኃጢአተኛውንም በሚያጸድቅ ለሚያምን [የአሁን ጊዜ፡ ማመኑንም የሚቀጥል] ሰው እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቆጠርለታል። (በቅንፍ ያለው በእኔ የተጨመረ ነው)።

የሐዋርያት ሥራ 26፡20 “ነገር ግን አስቀድሜ በደማስቆ ላሉት በኢየሩሳሌምም በይሁዳም አገር ሁሉ ለአሕዛብም ንስሐ ይገቡ [የአሁን ጊዜ፡ እናም በንስሐ እንዲቀጥሉ] ዘንድና ለንስሐ የሚገባ ነገር እያደረጉ [የአሁን ጊዜ፡ ንስሐቸውን የሚያረጋግጥ ተግባር እንዲሰሩና መሰራት እንዲቀጥሉ] ወደ እግዚአብሔር ዘወር ይሉ ዘንድ [የአሁን ጊዜ፡ እና በዛው እንዲቀጥሉ] ተናገርሁ።

**ማጠቃለያ፡** የአሁን ጊዜ (present tense) በመጽሐፍ ቅዱስ በመቶዎች ለሚቆጠር ጊዜ ያህል ጥቅም ላይ ውሏል። ከዚህ ጋር የሚያያዙ ጥቅሶችን እዚህ ላይ ለማሳየት አሁን የእኔ ሃሳብ አይደለም። የመዳን እምነት እውነተኛ ባህሪ ግን ቀጣይነት ያለው ሲሆን ይህንን ከተለያየ የእምነት አስተሳሰብ ቢመጡም አርሜኒያኒዝምና ካልቪኒዝም በመንፈሳዊ ትምህርታቸው (theology) ያስተምሩት ነበር።

ካልቪኒዝም፣ የዘላለም ዋስትናን የሚያቀነቅን ሲሆን፣ የሚያስተምረውም እውነተኛ አማኞች ሊንገዳገዱና ሊወድቁ ይችላሉ፣ ነገር ግን በክርስትና ሕይወታቸው እስከ ፍጻሜ ድረስ ይጸናሉ (1ኛ ቆሮንቶስ 1፡8) የሚል ነው። እነዚህ በዘላለም ዋስትና የሚያምኑት፣ እውነተኛ ክርስቲያኖች ለኃጢአት ሞተዋልና በኃጢአት መቀጠል አይችሉም (ሮሜ 6፡1-3) ብለው በተጨማሪ ያምናሉ። ቆይተው በእራሳቸው ከክርስቶስ የራቁና ፍጹም ፊታቸውን አዙረው የሄዱት ግን ዳግመኛ ያልተወለዱ ናቸው (1ኛ ዮሐንስ 2፡19)።

የአርሜኒያን መንፈሳዊ ትምህርት ደግሞ እውነተኛ አማኞች ከክርስትና ሕይወት ሊወድቁ ይችላሉ ሲል ያስተምራል። እንደ እነርሱ እምነት እና ትምህርት ከሆነ የሚወድቁ አማኞች መዳናቸውን ያጣሉ፣ ወይም ይሰረዝባቸዋል። የእነርሱ አስተምህሮ የይሰሙላ ወይም (ለስሙ ክርስቲያን) ለሆኑት  የንስሐ ፍሬን ሳያሳዩ በአመጻቸው እንዲቀጥሉ ወይም ሆን ብለው በኃጢአት እየኖሩ የሚቀጥሉበትን ምንም ዓይነት ክፍተት አይሰጣቸውም።

ሐዋርያው ዮሐንስ “ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፣ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም” (1ኛ ዮሐንስ 1፡8) ካለ በኋላ፣ በተጨማሪም እንዲህ ይላል “ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም” (1ኛ ዮሐንስ 3፡9)። ይህ እንቆቅልሽ ነው፣ ነገር ግን እርስ በእርሱ የሚጣረስ ቃል አይደለም። ሁሉም ክርስቲያኖች ኃጢአትን ይሰራሉ (1ኛ ዮሐንስ 1፡8)፣ ነገር ግን ሁሉም ክርስቲያኖች ደግሞ ትእዛዛቱን ይጠብቃሉ (1ኛ ዮሐንስ 2፡3)። ኃጢአትና የሥጋ ሥራ በክርስቲያኖች ዘንድ አሁንም አሉ፣ ነገር ግን ኃጢአት አይገዛቸውም ወይም የሚሰጉበት መለያቸው አይደለም (1ኛ ዮሐንስ 3፡9)። እውነተኛ ንስሐና እምነት የአእምሮ መለወጥ ነው፣ የልብ ለውጥ፣ የአቅጣጫ ለውጥም ነው፣ ምንም እንኳን ፍጹምነት ባይሆንም (የሐዋርያ ሥራ 26፡18 እና 1ኛ ዮሐንስ 1፡8)። “ፍሬ” ምንጊዜም የእምነት ትክክለኛነትና እውነተኛነት ተፈትኖ የሚታወቅበት ማረጋገጫ ነው። እምነት ልዕለ ተፈጥሮ (Super natural) ጽኑ ውሳኔ ሲሆን የእውነተኛ አማኞችን ባህሪ የሚገዛና በውጤቱም የእምነት ሥራ እንዲሰሩ የሚያደርግ ነው። እምነት በድርጊት ወይም በተግባር የታጀበ ለመሆኑ ምሳሌዎችን በዕብራውያን መልዕክት፣

ምዕራፍ 11፣ ውስጥ እናገኛለን። በሌላ አነጋገር የምናደርገው ሁሉ ያመነውን ነገር ተከትሎ የሚመጣ ነው ማለት ነው። የያዕቆብ መልዕክት 2፡18 “እምነትህን ከሥራህ ለይተህ አሳየኝ፣ እኔም እምነቴን በሥራዬ አሳይሃለሁ” ይላል።

ሐዋርያቱ የሥራን አላስፈላጊነት የሚናገሩት “የሕግን ሥራ” በተመለከተ፣ ይኸውም ማንኛውም ለመዳን የሚደረግ ሥራን ወይም መዳንን በሥራ ለማግኘት ጥረት ማድረግን የሚመለከት ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ስለ መዳን ፍሬ ይናገራሉ፣ ይህም መልካም ሥራን፣ ወይም የእምነት ሥራን የሚመለከት ነው። ይህም ንስሐን ወይም እምነትን የሚመጣ ተከትሎ የሚመጣ ነው (የሐዋርያት ሥራ 26፡20፣ ማቴዎስ 3፡7-10፣ 1ኛ ተሰሎንቄ 1፡3 እና ያዕቆብ 2፡14-26)፣ እነዚህ የመዳንን ማረጋገጫ የሚያሳዩ ናቸው። በንስሐና በእምነት መካከል ያለው አንድነት ሁለቱም አንድ ዓይነት ፍሬ ወይም ማረጋገጫ፤ መልካም ሥራ ያላቸው መሆኑ ነው። በመልካም ሥራችን አልዳንም፣ ነገር ግን ለመልካም ሥራ ድነናል (ኤፌሶን 2፡8-10 በ እና ለ መካከል ያለ ልዩነት ነው)። ሥራዎች የእምነት ትክክለኛነት ማረጋገጫ ናቸው፣ ደግሞም ጸጋ የሰውን ሕይወት እና ተግባር የማይለውጥ ከሆነ እውነተኛ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው ተብሎ ሊወሰድ አይችልም (ቲቶ 2፡11-12)። ኢየሱስ በትምህርቱ እውነተኛ አማኞች በፍሬአቸው ይታወቃሉ ይላል (ማቴዎስ 3፡8፣ 7፡16-20፣ 25፡34-40፣ ዮሐንስ 13፡35፣ 14፡23፣ የሐዋርያት ሥራ 26፡20፣ ሮሜ 2፡6-11፣ ያዕቆብ 2፡14-18 እና 1ኛ ዮሐንስ 3፡10)።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. በአሁን ጊዜ የሚነገሩ ትዕዛዞች ________ ሊኖራቸው ይገባል።

2. ዮሐንስ 3፡16ን አንብቡና፣ እንደ ግሪኩ የአሁን ጊዜ (present tense) ዮሐንስ 3፡16ን እንዴት ይብራራል?

   **ዮሐንስ 3፡16** *"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።"*

3. 1ኛ ዮሐንስ 3፡9 ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም። ምን ማለት ነው?

   **1ኛ ዮሐንስ 3፡9** *"ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም፥ ዘሩ በእርሱ ይኖራልና፤ ከእግዚአብሔርም ተወልዶአልና ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም።*

4. ሉቃስ 15፡7 ________________ በሚገባ አንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል።

   **ሉቃስ 15፡7** *"እላችኋለሁ፥ እንዲሁ ንስሐ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል።"*

5. የሐዋርያት ሥራ 17፡30 እግዚአብሔር በየቦታቸው ________________ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል።

   **የሐዋርያት ሥራ 17፡30** *"እንግዲህ እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል፤"*

6. የሐዋርያት ሥራ 26፡20 አንብቡ። ይህ ጥቅስ ሰለ ምን ይናገራል?

   **የሐዋርያት ሥራ 26፡20** *"ነገር ግን አስቀድሜ በደማስቆ ላሉት በኢየሩሳሌምም በይሁዳም አገር ሁሉ ለአሕዛብም ንስሐ ይገቡ ዘንድና ለንስሐ የሚገባ ነገር እያደረጉ ወደ እግዚአብሔር ዘወር ይሉ ዘንድ ተናገርሁ።"*

7. 1ኛ ዮሐንስ 2፡3 ከእግዚአብሔር ጋር የግል ግንኙነትማድረጋችን፣ ማለትም እርሱን ማወቃችን፣ በምን ይታወቃል?

   **1ኛ ዮሐንስ 2፡3** *"ትዕዛዛቱንም ብንጠብቅ በዚህ እንዳወቅነው እናውቃለን"*

8. ያዕቆብ 2፡18 "እምነትህን ከሥራህ ለይተህ አሳዬኝ (ይህ የማይቻል ነው)፣ እኔም እምነቴን በ________________ አሳይሃለሁ ይላል።"

   **የዕቆብ 2፡18** *"ነገር ግን አንድ ሰው። አንተ እምነት አለህ እኔም ሥራ አለኝ፤ እምነትህን ከሥራህ ለይተህ አሳየኝ፥ እኔም እምነቴን በሥራዬ አሳይሃለሁ ይላል።*

9. 1ኛ ተሰሎንቄ 1፡3 ከእምነት የሚቀድሙ ሥራዎች ወይም ተግባራት______________ ይባላሉ።

**1ኛ ተሰሎንቄ 1:3** *"በጸሎታችን ጊዜ ስለ እናንተ ሰናሳስብ፥ የእምነታችሁን ስራ የፍቅራችሁንም ድካም በጌታችንም በኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን የተስፋችሁን መጽናት በአምላካችንና በአባታችን ፊት ሳናቋርጥ እያሰብን፥ እግዚአብሔርን ሁል ጊዜ በሁላችሁ ምክንያት እናመሰግናለን፤"*

10. ገላትያ 2:16፣ 21 አንብቡና፣ የሕግ ሥራ የሚባሉት ሰዎች የሕግን ሥራ በመፈጸም መዳንን ወይም _______________ (ቁጥር 21) ለማግኘት የሚሰሯቸው ናቸው። እነዚህ ግን አያድኑም ወይም የማዳን ኃይል የላቸውም::

**ገላትያ 2:16** *"ነገር ግን ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ በሕግ ሥራ እንዳይሆን አውቀን፥ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በሕግ ሥራ ስለማይጸድቅ፥ እኛ ራሳችን በሕግ ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ እምነት እንጸድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል።"*

**ገላትያ 2:21** *"የእግዚአብሔርን ጸጋ አልጥልም፤ ጽድቅስ በሕግ በኩል ከሆነ እንኪያስ ክርስቶስ በከንቱ ሞተ።"*

11. ሮሜ 2:7-10 ጥቅሶቹ በሚያፈሩት ፍሬ በሁለት የሚመደቡ ምን ዓይነት ሰዎችን ያሳያሉ?

**ሮሜ 2:7-10** *"በበጎ ሥራ በመጽናት ምስጋናንና ክብርንየማይጠፋንም ሕይወት ለሚፈልጉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸዋል፤ [8] ለዓመፃ በሚታዘዙ እንጂ ለእውነት በማይታዘዙትና በአድመኞች ላይ ግን ቍጣና መቅሠፍት ይሆንባቸዋል። [9] ክፉውን በሚያደርግ ሰው ነፍስ ሁሉ መከራና ጭንቀት ይሆንበታል፥ አስቀድሞ በአይሁዳዊ ደግሞም በግሪክ ሰው፤ [10] ነገር ግን በጎ ሥራ ለሚያደርጉ ሁሉ ምስጋናና ክብር ሰላምም ይሆንላቸዋል፥ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው።"*

# ጠቋሚ መልሶች

1. በአሁን ጊዜ የሚነገሩ ትዕዛዞች ________ ሊኖራቸው ይገባል።
**ቀጣይነት ወይም ተከታታይ አፈጻጸም።**

2. ዮሐንስ 3፡16ን አንብቡና፣ እንደ ግሪኩ የአሁን ጊዜ (present tense) ዮሐንስ 3፡16 እንዴት ይብራራል?
**በእርሱ የሚያምን ሁሉ (የአሁን ጊዜ፦ የሚያምን እና ማመኑን የሚቀጥል) የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።**

3. 1ኛ ዮሐንስ 3፡9 ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም። ምን ማለት ነው?
**ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም(የአሁን ጊዜ፦ ማለትም በኃጢአት መኖርን እንደ የሕይወት ዘይቤው አድርጎ አይቀጥልም፣ ንስሐ የማይገባ ልብን ያሳያል)፥ ዘሩ በእርሱ ይኖራልና፤ ከእግዚአብሔርም ተወልዶአልና ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም።**

4. ሉቃስ 15፡7 ________________ በሚገባ አንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል።
**ንስሐ በሚገባ፣ በንስሐም በሚቀጥል።**

5. የሐዋርያት ሥራ 17፡30 እግዚአብሔር በየቦታቸው ________________ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል።
**ንስሐ ይገቡ፣ በንስሐም ይቀጥሉ።**

6. የሐዋርያ ሥራ 26፡20 አንብቡ። ይህ ጥቅስ ስለ ምን ይናገራል?
**ነገር ግን አስቀድሜ በደማስቆ ላሉት በኢየሩሳሌምም በይሁዳም አገር ሁሉ ለአሕዛብም ንስሐ ይገቡ ዘንድና (የአሁን ጊዜ፦ በንስሐ እንዲቀጥሉ) እና እንዲመለሱ (የአሁን ጊዜ፦ መመለሳቸውንም እንዲቀጥሉ)፣ ለንስሐ የሚገባ ነገር እያደረጉ (የአሁን ጊዜ) ወደ እግዚአብሔር ዘወር ይሉ ዘንድ ተናገርሁ።**

7. 1ኛ ዮሐንስ 2፡3 ከእግዚአብሔር ጋር የግል ግንኙነት ማድረጋችን፣ ማለትም እርሱን ማወቃችን፣ በምን ይታወቃል?
**የሚናገረውን በማድረግ፣ ትዕዛዛቱን በመጠበቅ።**

8. ያዕቆብ 2፡18 "እምነትህን ከሥራህ ለይተህ አሳዬኝ (ይህ የማይቻል ነው)፣ እኔም እምነቴን በ______________ አሳይሃለሁ ይላል።"
**በሥራዬ ወይም በማደርገው።**

9. 1ኛ ተሰሎንቄ 1፡3 ከእምነት የሚቀድሙ ሥራዎች ወይም ተግባራት______________ ይባላሉ።
**የእምነት ሰራ።**

10. ገላትያ 2፡16፣ 21 አንብቡና፣ የሕግ ሥራ የሚባሉት ሰዎች የሕግን ሥራ በመፈጸም መዳንን ወይም ________________ (ቁጥር 21) ለማግኘት የሚሰሯቸው ናቸው። እነዚህ ግን አያድኑም ወይም የማዳን ኃይል የላቸውም።

11. ጽድቅ። ሮሜ 2፡7-10 ጥቅሶቹ በሚያፈሩት ፍሬ በሁለት የሚመደቡ ምን ዓይነት ሰዎችን ያሳያሉ?
**የሚያምኑ እና የማያምኑ።**

# ትምህርት 13

# የመዳን ፍሬ - ክፍል 2

## በዶን ክሮው

ቀጣዩን ጥቅስ ተመልከቱ፡ “የእግዚአብሔር ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች በዚህ የተገለጡ ናቸው፤ ጽድቅን የማያደርግና ወንድሙን የማይወድ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም” (1ኛ ዮሐንስ 3፡10)። ይህ ቃል “እራሳችንን ማዳን የምንችለው ይህን በማደረግ ነው” አይልም። ነገር ግን “የእግዚአብሔርን ልጆች ማወቅ የምንችለው በዚህ ነው” እያለ ነው (1ኛ ዮሐንስ 3፡10) (አጽንኦት ያደረኩት እኔ ነኝ)።

ኢየሱስም “ስለዚህ ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ” (ማቴዎስ 7፡20) ይላል።

እግዚአብሔር መዳንን በተመለከተ ሁለት መንገዶች እንዳሉ በቃሉ ያመለክታል፡ (1) በጸጋው በእምነት በኩል (ኤፌሶን 2፡8-9) እና (2) እያንዳንዱ የዳነ ሰው በሚፈጽመው በመልካም ሥራ በኩል (ኤፌሶን 2፡10)። ስለ አማኙ ፍሬ ለመናገር ለምን እንፈራለን? መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ዓይነት ርዕሶችን አለባብሶ አይተዋቸውም። በእግዚአብሔር መንግሰት እና በእግዚአብሔር አመራር ሥር መሆናችንን ማወቅ የምንችልባቸውን መንገዶች እንደሚከተለው ማየት እንችላለን፡-

1ኛ ዮሐንስ 2፡3-5 - ትእዛዛቱንም ብንጠብቅ በዚህ እንዳወቅነው እናውቃለን። አውቄዋለሁ የሚል ትእዛዛቱንም የማይጠብቅ ውሸተኛ ነው እውነትም በእርሱ ውስጥ የለም። ቃሉን ግን የሚጠብቅ ሁሉ በእርሱ የእግዚአብሔር ፍቅር በእውነት ተፈጽሞአል። በእርሱ እንዳለን በዚህ እናውቃለን። (አጽንኦት የእኔ)

እርሱ ጻድቅ እንደሆነ ካወቃችሁ፣ አውነትን የሚያደርግ ሁሉ ከእርሱ እንደ ተወለደ ታውቃላችሁ (1ኛ ዮሐንስ 2፡29)። (ይህ ስሜት አይሰጥም ትላላችሁ? የእግዚአብሔር እና የክርስቶስ ማንነት ጽድቅ ነው፤ እናም ማንም ጽድቅን የሚለማመድ ቢኖር የእርሱን ማንነት መካፈሉን ያሳያል፣ ከእርሱ ተወልዷልና፣ እንደሚል ሐዋርያው ዮሐንስ)።

1ኛ ዮሐንስ 3፡5-10 - እርሱም ኃጢአትን ሊያስወግድ እንደ ተገለጠ ታውቃላችሁ፥ በእርሱም ኃጢአት የለም። በእርሱ የሚኖር ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም፤ [በግሪክ ቋንቋ የዚህ ሐረግ ትርጉም የአሁን ጊዜን፡ ቀጣይነት ያለውን፣ ተከታታይ፣ ወይም ልማዳዊ ድርጊትን ያመላክታል። የመጽሐፍ ቅዱስ እንደባቢ ይበልጥ መረዳት ለማግኘት ይችል ዘንድ በተከታታይ፣ በተደጋጋሚ፣ በመደጋገም፣ ሳይቋረጥ፣ በቋሚነት፣ በቀጣይነት፣ እንደተለመደው፣ እንደ ሕያወት ዘይቤ የሚሉትን ቃላት በማስገባት ይበልጥ መረዳት ይችላል] ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ [የአሁን ጊዜ] አላየውም አላወቀውምም። ልጆች ሆይ፥ ማንም አያስታችሁ፤ እርሱ ጻድቅ እንደ ሆነ ጽድቅን የሚያደርግ [የአሁን ጊዜ እየደጋገመ፣ በተከታታይ] ጻድቅ ነው። ኃጢአትን የሚያደርግ [የአሁን ጊዜ እንደ ልማድ የሕይወት ዘይቤው ስለሆነ] ከዲያብሎስ ነው፥ ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኃጢአትን ያደርጋልና። ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ። ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም፥ [የአሁን ጊዜ እንደ ሕይወት ዘይቤ፣ ንሰሐ የማይገባ ልብን ያመለክታል] ዘሩ በእርሱ ይኖራልና፤ ከእግዚአብሔርም ተወልዶአልና ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም [የአሁን ጊዜ፡ ያለማቋረጥ]። የእግዚአብሔር ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች በዚህ የተገለጡ ናቸው፤ ጽድቅን የማያደርግና ወንድሙን የማይወድ [የአሁን ጊዜ] ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም። (ዮሐንስ “የእግዚአብሔር ልጆችን እና የዲያብሎስን ልጆች ማወቅ የምንችልበት መንገድ ይህ ነው” እያለ ነው። ጽድቅን የማያደርጉና ፍቅር የሌላቸው የእግዚአብሔር አብ ማንነት (ተፈጥሮ) የላቸውም። የአዲስ ፍጥረት መታወቂያ አስፈላጊ አይደለም ትላላችሁ?) (አጽንኦት የእኔ)።

1ኛ ዮሐንስ 3፡14 - እኛ ወንድሞችን የምንወድ ስለ ሆንን ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገርን እናውቃለን፤

ወንድሙን የማይወድ በሞት ይኖራል። (አጽንኦት የእኔ)

1ኛ ዮሐንስ 4፡6 - እኛ ከእግዚአብሔር ነን፤ እግዚአብሔርን የሚያውቅ ይሰማናል [ሐዋርያቱን]፤ ከእግዚአብሔር ያልሆነ አይሰማንም [ሐዋርያቱን]። የእውነትን መንፈስና የስሕተትን መንፈስ በዚህ እናውቃለን። (አጽንኦት እና ቅንፍ የእኔ)

1ኛ ዮሐንስ 4፡8 - ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም፥ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና። (ፍቅር የእማኙ ምልክት ነው፣ የእግዚአብሔር ማንነት ፍቅር ስለሆነ)

1ኛ ዮሐንስ 5፡2 - እግዚአብሔርን ስንወድ [የአሁን ጊዜ: እናም መውደዳችን ስንቀጥል] ትእዛዛቱንም ስናደርግ [የአሁን ጊዜ፡ እና ማድረጋችንንም ስንቀጥል] የእግዚአብሔርን ልጆች እንድንወድ በዚህ እናውቃለን። (አጽንኦት እና ቅንፍ የእኔ)

1ኛ ዮሐንስ 5፡18-19 - ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን እንዳያደርግ [የአሁን ጊዜ፡ ንስሐ የማይገባ ልብን የሚያመለክት የሕይወት ዘይቤ]፥ ነገር ግን ከእግዚአብሔር የተወለደው ራሱን እንዲጠብቅ [የአሁን ጊዜ፡ እና መጠበቁንም ሲቀጥል] ክፉውም እንዳይነካው እናውቃለን። ከእግዚአብሔር እንደ ሆንን ዓለምም በሞላው በክፉው እንደ ተያዘ እናውቃለን። (አጽንኦት እና ቅንፍ የእኔ)

ሐዋርያው ዮሐንስ እነዚህን ነገሮች ሁሉ የሚያካፍለን ለምን ይሆን? የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ (1ኛ ዮሐንስ 5፡13)።

ማጠቃለያ:- ጽድቅ፣ ቅድስና፣ ፍቅር፣ የመንፈስ ፍሬ የአዲስ ውልደት መለያዎች ናቸው። መልካም ያልሆኑ የሕይወት ልምምዶችን በምታድርጉበት ጊዜ እናንተ እራሳችሁ የእርሱ (የእግዚአብሔር) ስለመሆናችሁ መተማመኛ አይኖራችሁም። ሕሊናችሁ ይኮንናል፣ በእግዚአብሔርም አትተማመኑም። ሐዋርያው ጴጥሮስ መጠራታችሁንና መመረጣችሁን እንድታጸኑ ይመራችኋል (2ኛ ጴጥሮስ 1፡10)፤ ይህም ማለት ከክብር ወንጌል ጋር የሚጣጣም የሕይወት ዘይቤ በመከተል የእርሱ ለመሆናችሁ ለልባችሁ ማረጋገጫ ስጡት ማለት ነው። “የዳንነው በዚህ ነው” እያልኩ አይደለም፤ “የእርሱ መሆናችንን የምናውቀው በዚህ ነው” እያልኩ ነው።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. የሐዋርያት ሥራ 8:13 እና 18-22። አንደኛ ዮሐንስ ስለ "ፍሬ" ወይም የእውነተኛ አማኝ መለያ ይናገራል። እነዚህ ሁሉ ከውስጥ የሚመነጩ የልብ ጉዳዮች ናቸው። የአማኞች ልብ ትክክል (ለምሳሌ እንደ ስምኦን) በማይሆንበት ጊዜ ምን ያደርጋሉ?

   **የሐዋርያት ሥራ 8:13** *"ሲሞንም ደግሞ ራሱ አመነ፤ ተጠምቆም ከፊልጶስ ጋር ይተባበር ነበር፤ የሚደረገውንም ምልክትና ታላቅ ተአምራት ባየ ጊዜ ተገረመ።"*

   **የሐዋርያት ሥራ 8:18-22** *"ሲሞንም በሐዋርያት እጅ መጫን መንፈስ ቅዱስ እንዲሰጥ ባየ ጊዜ፥ ገንዘብ አመጣላቸውና። [19] እጄን የምጭንበት ሁሉ መንፈስ ቅዱስን ይቀበል ዘንድ ለእኔ ደግሞ ይህን ሥልጣን ስጡኝ አለ። [20] ጴጥሮስ ግን እንዲህ አለው። የእግዚአብሔርን ስጦታ በገንዘብ እንድታገኝ አስበሃልና ብርህ ከአንተ ጋር ይጥፋ። [21] ልብህ በእግዚአብሔር ፊት የቀና አይደለምና ከዚህ ነገር ዕድል ወይም ፈንታ የለህም። [22] እንግዲህ ስለዚህ ክፋትህ ንስሐ ግባ፥ ምናልባትም የልብህን አሳብ ይቅር ይልህ እንደ ሆነ ወደ እግዚአብሔር ለምን፤"*

2. 2ኛ ጴጥሮስ 1፡5-11ን አንብቡና፣ አንድ ሰው እግዚአብሔር ከጠራቸውና ከመረጣቸው ውስጥ ለመሆኑ ማረጋገጫው ምንድን ነው?

   **2ኛ ጴጥሮስ 1፡5-11** *"ስለዚህም ምክንያት ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ፥ [6] በበጎነትም እውቀትን፥ በእውቀትም ራስን መግዛት፥ ራስንም በመግዛት መጽናትን፥ በመጽናትም እግዚአብሔርን መምሰል፥ [7] እግዚአብሔርንም በመምሰል የወንድማማችን መዋደድ፥ በወንድማማችም መዋደድ ፍቅርን ጨምሩ። [8] እነዚህ ነገሮች ለእናንተ ሆነው ቢበዙ፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት ሥራ ፈቶችና ፍሬ ቢሶች እንዳትሆኑ ያደርጉአችኋልና፤ [9] እነዚህ ነገሮች የሌሉት ዕውር ነውና፥ በቅርብም ያለውን ብቻ ያያል፥ የቀደመውንም ኃጢአቱን መንጻት ረስቶአል። [10] ስለዚህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ መጠራታችሁንና መመረጣችሁን ታጸኑ ዘንድ ከፊት ይልቅ ትጉ፤ እነዚህን ብታደርጉ ከቶ አትሰናከሉምና። [11] እንዲሁ ወደ ዘላለሙ ወደ ጌታችንና መድኃኒታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት መግባት በሙላት ይሰጣችኋልና።"*

3. ማቴዎስ 25፡34-40፣ በዚህ ቃል መሰረት የአማኙ መታወቂያ የሆኑት ተግባራት ምንድን ናቸው?

   **ማቴዎስ 25፡34-40** *"ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል። እናንተ የአባቴ ቡሩካን፥ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ። [35] ተርቤ አብልታችሁኛልና፥ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፥ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፥ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፥ [36] ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፥ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና። [37] ጻድቃንም መልሰው ይሉታል። ጌታ ሆይ፥ ተርበህ አይተን መቼ አበላንህ? ወይስ ተጠምተህ አይተን መቼ አጠጣንህ? [38] እንግዳ ሆነህስ አይተን መቼ ተቀበልንህ? ወይስ ታርዘህ አይተን መቼ አለበስንህ? [40] ንጉሡም መልሶ። እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት ይላቸዋል።"*

4. ዮሐንስ 13፡35 የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት የሚታወቁት በምንድን ነው?

   **ዮሐንስ 13፡35** *"እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፥ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ።"*

5. ማቴዎስ 7፡21-23፣ እነዚህ ሰዎች ፊታቸውን ከእግዚአብሔር መንግስት ያዞሩት በምን ምክንያት ነው?

   **ማቴዎስ 7፡21-23** *"በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም። [22] በዚያ ቀን ብዙዎች። ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፥ በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፥ በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል። [23] የዚያን ጊዜም። ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።*

6. ዮሐንስ 14፡23 ሰው ኢየሱስን የሚወድ ከሆነ ምን ያደርጋል?

   **ዮሐንስ 14፡23** *"ኢየሱስም መለሰ አለውም። የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን።"*

7. የሐዋርያት ሥራ 26፡20 ይህ ቃል የሚናገረው ምንድን ነው?

   **የሐዋርያት ሥራ 26፡20** *"ነገር ግን አስቀድሜ በደማስቆ ላሉት በኢየሩሳሌምም በይሁዳም አገር ሁሉ ለአሕዛብም ንስሐ ይገቡ ዘንድና ለንስሐ የሚገባ ነገር እያደረጉ ወደ እግዚአብሔር ዘወር ይሉ ዘንድ ተናገርሁ።"*

8. ያዕቆብ 2፡17፣ እምነታችሁ ተከትሎ መልክማ ሥራ ወይም ተግባር ከሌለ ምን ዓይነት እምነት ነው?

   **ያዕቆብ 2፡17** *"እንደዚሁም ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው።"*

# ጠቋሚ መልሶች

1. የሐዋርያት ሥራ 8:13 እና 18-22። እንደኛ ዮሐንስ ስለ "ፍሬ" ወይም የእውነተኛ አማኝ መለያ ይናገራል። እነዚህ ሁሉ ከውስጥ የሚመነጩ የልብ ጉዳዮች ናቸው። የአማኞች ልብ ትክክል (ለምሳሌ እንደ ስምኦን) በማይሆንበት ጊዜ ምን ያደርጋሉ?
**ስለ ኃጢአታችሁ (ስለ ክፋታችሁ) ንስሐ ግቡ፣ የልባችሁን አሳብ ይቅር ይላችሁ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ለምኑ፣።**

2. 2ኛ ጴጥሮስ 1:5-11ን አንብቡና፣ አንድ ሰው እግዚአብሔር ከጠራቸውና ከመረጣቸው ውስጥ ለመሆኑ ማረጋገጫው ምንድን ነው?
**በእምነታቸው ላይ የመንፈስን መልካም ነገሮች ሁሉ ይጨምራሉ፣ የአዲሱን ተፈጥሮአቸውን መልካ ነገሮች ይጨምራሉ።**

3. ማቴዎስ 25:34-40፣ በዚህ ቃል መሰረት የአማኙ መታወቂያ የሆኑት ተግባራት ምንድን ናቸው?
**ከእምነት የመነጩ የሚታዩ ተግባራት፣ የተራቡትን ማብላት፣ ለሌሎች መልካም መሆን፣ የታረዙትን ማልበስ፣ ሕሙማንን መርዳት፣ የታሰሩትን መጠየቅ ወዘተ … ።**

4. ዮሐንስ 13:35 የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት የሚታወቁት በምንድን ነው?
**እርስ በእርሳቸው በመዋደድ።**

5. ማቴዎስ 7:21-23፣ እነዚህ ሰዎች ፊታቸውን ከእግዚአብሔር መንግስት ያዞሩት በምን ምክንያት ነው?
**ዓመፀኞች። የግሪኩ ትርጉም የአሁን ጊዜ ግስ ይጠቀማል ይህም ዓመፃ የሕይወት ዘይቤአቸው፣ ተፈጥሮአቸው መሆኑን ያመለክታል። ኢየሱስም ከቶ አላውቃችሁም አለ። እነዚህ የልብ ለውጥ የሌላቸው፣ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ የሚያደርግ የህሊና ለውጥ የሌላቸው የጠፉ የሐይማኖት ሰዎች ናቸው።**

6. ዮሐንስ 14:23 ሰው ኢየሱስን የሚወድ ከሆነ ምን ያደርጋል?
**ቃሉን መጠበቅ፣የሚናረውንም ማድረግ።**

7. የሐዋርያት ሥራ 26:20 ይህ ቃል የሚናገረው ምንድን ነው?
**ንስሐችሁን በተግባራችሁ ግለጹ።**

8. ያዕቆብ 2:17፣ እምነታችሁ ተከትሎ መልክማ ሥራ ወይም ተግባር ከሌለ ምን ዓይነት እምነት ነው?
**የሞተ እምነት፣ የማያድን እምነት (ያዕቆብ 2:14)።**

# ትምህርት 14

# ጥሪ ለደቀመዝሙርነት

## በአንድሩ ዉማክ

ዛሬ ደግሞ ደቀ መዝሙር ስለ መሆን እና ሌሎች ሰዎችን ደቀ መዝሙር እንዲሆኑ ስለ ማድረግ እናወራለን። ጌታ ትዕዛዝ እንደሰጠን፣ ነገር ግን ትዕዛዙ ሰዎች እንዲቀየሩ ስለ ማድረግ ወይም ኢየሱስ ጌታ መሆኑን በአፋቸው መስክረው የኃጢአት ይቅርታን እንዲቀበሉ ማድረግ ሳይሆን ደቀ መዝሙር እንዲሆኑ ስለ ማድረግ መሆኑን ላስታውሳችሁ እወዳለሁ። ምንም እንኳን ከፍ ብዬ ያነሳኋቸው ሁለቱ ወሳኝ ቢሆኑም፣ እኔም እነዚህን ፈጽሞ እያሳነስኳቸው ሳይሆን፣ ዋና ዓላማችን መሆን ያለበት ዳግመኛ ከመወለድ አልፎ ወደ ብስለት ደረጃ መድረስ ነው ለማለት ነው። ደቀ መዝሙር የሆነ ክርስቲያን ግቡ ሰዎችን ደቀ መዝሙር እንዲሆኑ ማድረግ ነው።

ኢየሱስ፣ ደቀ መዝሙር እንድናደርግ፣ ወደ መብሰል ደረጃ እንዲመጡና ፍሬ ማፍራት እንዲችሉ ጭምር ወደ ሰዎች እንድንሄድ ነግሮናል። የእኛ የአሁኗ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ይህን እያደረገች አይደለም። ሰዎች ዳግመኛ እዲወለዱ የማድረጉን ኃላፊነት ለቤተ ክርስቲያን ሰዎች ወይም ለአገልጋዮች ትተነዋል። በየአገሩ የሚጓዙ ወንጌላውያን አሉን፣ ታላላቅ ጉባኤዎችን ያካሂዳሉ፣ በሽዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ጌታን ለመቀበል ሲወስኑም እንመለከታለን። አንዳንዶች ጌታን የሚቀበሉት በእውነት ዳግመኛ ተወልደው ሳይሆን ከስሜታዊነት በመነሳት ይሁን እንጂ አንዳንድ ሰዎች ግን በእርግጥ ዳግመኛ የተወለዱ እና ከጌታ ጋር ግንኙነት የጀመሩ ለመሆናቸው እርግጠኛ ነኝ። ሆኖም ብዙ ጊዜ፣ ደቀ መዝሙር ሆኖ ለመቀጠል ትኩረት በመስጠት የሚደረግ እንቅስቃሴ የለም ለማለት ያስደፍራል፣ እንዲህ እንዲሆን ግን የእግዚአብሔር ሃሳብ አይደለም።

ይህ ለእኔ ሕጻናትን ከሚወድ ሰው ጋር ይመሳሰላል። ሕጻን እንዲኖረን የምንፈልገው በእርሱ ወይም በእርሷ ደስ እንዲለን እንጂ ሲወለዱ ማየት ብቻ የሚያስደስተን ከሆነ ይህ ሙሉ ኃላፊነት የጎደለው ተግባር ይሆን ነበር። ሕጻን ልጅ ያለው ሰው ሕጻኑን ለማስተማር እና ለማሳደግ ሙሉ ኃላፊነት ይወስዳል። እኛ ግን ሰዎችን እንዲህ እንላቸዋለን "ዋናው ነገር ዳግመኛ መወለድ ነው፣ ኢየሱስ ጌታ መሆኑን መቀበልህ ነው" እንላቸዋለን። ተሳክቶልን ያን ካደረጉልን ደግሞ ጀርባቸውን እየጠበጠብን - "አሁን ክርስቲያን ሆነሃል። በእግዚአብሔር ታመን፣ መጽሐፍ ቅዱስህን አንብብ፣ ሁሉም መልካም ይሆንልሃል" እንላቸዋን። የጌታ አጽንኦት ይህ አይደለም።

በዚህ ምክንያት ከልባቸው ጌታን ለመከተል የወሰኑ፣ ነገር ግን ምንም ብስለት የሌላቸውን ብዙ ሰዎች አፍርተናል። ምንም አጋዥ መሳሪያ ስለ ሌላቸው እምነታቸው ፍሬ እንዲያፈራ ማድረግ አልቻሉም። የኢየሱስ ትክክለኛ ምስክር ከመሆን ይልቅ፣ በእርግጥ ተቃራኒ ምስክር ሆነው እናገኛቸዋለን። እርሱ ግን ወደ ሰዎች ሁሉ እንድንሄድና እነርሱንም በኃይል የተሞሉ እምነታቸው በሌሎች ሰዎች ላይ ፍሬ ማፍራት የሚችል ሙሉ ደቀ መዛሙርት በሚሆኑበት መንገድ እንድንሰራ ይፈልጋል።

በየስድስት ወሩ አንድ ሰው ወደ ጌታ እንዲመጣ ብታደርጉና ጊዜያችሁን ሰውታችሁ ወደ ጌታ የመጡትን እምነታቸው ፍሬ የሚያፈራ የበሰሉ ወይም ብቁ ክርስቲያኖች ይሆኑ ዘንድ ደቀ መዝሙር ብታደርጓቸው፣ በስድስተኛ ወሩ መጨረሻ ላይ ሁለት ክርስቲያኖች ትሆናላችሁ። በመቀጠል ሁለታችሁ፣ እያንዳንዳችሁ አንድ ሰው ወደ ጌታ ብታመጡ ጊዜአችሁን ሰውታችሁ ደቀ መዝሙር እንዲሆኑ ብታደርጉ ከአንድ ዓመት በኋላ አራት ክርስቲያኖች ይኖሩናል። ይህ ግን አንድ ትልቅ ጉባኤ አካሂዶ በሽዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን በአንድ ጊዜ ወደ ጌታ እንዲመጡ ከሚያደርግ ሰው ጋር የማይነጻጸር ይመስላል። ብዙ ሰዎች እንግዲህ "ይህ የደቀ መዝሙር መንገድ በአንድ ዓመት ውስጥ አራት ሰዎችን ብቻ ነው የቀየረው፣ ነገር ግን በአንድ ጉባኤ በሽዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ወደ ጌታ መጥተዋል፣ ስለዚህ ይሄኛውን መንገድ ልንከተል ይገባል" ሊሉ ይችላሉ። በአንድ ጉባኤ አንድ ሽህ ሰዎችን ወደ ጌታ እንዲመጡ የሚያደርግ ሰው ምን አልባት 35000 ሰዎችን ወደ ጌታ እንዲመጡ ሊያደርግ ይችላል። ይህ ማንም ሊተቸው

የማይችለው መልካም ነገር ነው፣ ነገር ግን ከዓለም ሕዝብ አንጻር ሰናዬው በባልዲ ውሃ ውስጥ እንደ አንድ ጠብታ ነው። ቤተ ክርስቲያንም በእርግጥ በዚህ መንገድ ነው እየሰራች ያለችው።

በደቀ መዝሙርነት ላይ አጽንኦት ብናደርግ ግን፣ አንድ ሰው በየስድስት ወሩ አንድ ሌላ ሰው ወደ ጌታ እንዲመጣ ቢያደርግ እና ሁለቱ እንደገና ደቀ መዝሙር በማድረግ ሌሎች ሰዎችን ወደ ጌታ የማምጣት ሥራ ቢሰሩ በአስራ ሁለት ዓመት ተኩል ጊዜ ውስጥ በትንሹ አሁን ያለውን የዓለም ሕዝብ ያህል ሰው በወንጌል መድረስ ይችላሉ ማለት ነው። አንዳንድ ሰዎች ይህ ሊሆን አይችልም ሊሉ ይችላሉ፣ እኔ ግን ስሌቱን እንድትሰሩ እጠይቃችኋለሁ። በበኩሌ ቁጥሮቹን በማባዛት እንደ ደረስኩበት ከአስራ ሁለት ዓመትና ጥቂት ወራት በኋላ አንድ ሰው ሌላ ሰውን በስድስት ወር ውስጥ ደቀ መዝሙር ቢያደርግ፣ ሰዎቹም ፍሬ የሚያፈሩ የክርስቶስ አካል እንዲሆኑ በማድረግ አምስት ቢሊዮን ተኩል ሕዝቦችን በወንጌል መድረስ የሚችሉ ሲሆን እላይ ባነሳነው በጉባኤ ሰዎችን የመድረስ መንገድ ግን በተመሳሳይ ዓመት  አስራ ሁለት ሽህ አምስት መቶ ሰዎችን ብቻ እንደርሳለን።

ስኬት እና ብስለትን ወደ አገኛችሁበት ብቻ ሳይሆን በሌሎች ሰዎች ላይ ያንኑ ለማድረግ ዝንባሌ ወደ ሞታሳዩበት ጉዳይ ብወሰዳችሁ፣ ስልጣኝ ሳይሆን አስልጣኝ ከሆናችሁ፣ ኢየሱስን በመከተል ወደ ብስለት ደረጃ ደርሶ ሌሎችን ደቀ መዝሙር ማድረግ በጀመረ ሰው ላይ የሚከተሉት ነገሮች መታዬት ይጀምራሉ። ይህን ከአንድ ሰው ጋር በአንድ ዓመት ውስጥ ብታደርጉ፣ በዓመቱ መጨረሻ እናንተ እና ደቀ መዝሙር እንዲሆን የረዳችሁት ሰው ሁለታችሁ ብቻ ትሆናላችሁ - ሁለት ሰው። በሁለተኛው ዓመት መጨረሻ ደግሞ አራት ሰዎች ትሆናላችሁ። በዚህ መልኩ ከቀጠላችሁ በአስረኛው ዓመት መጨረሻ ላይ ደቀ መዝሙር ሆነው በክርስቶስ አካል ውስጥ ፍሬ የሚያፈሩ 1,024 ሰዎች ይኖሩናል። ይህን ሃሳብ በመጀመሪያ መቀበል በሚችል አንድ ሰው አማካኝነት በዚህ መንገድ መቀጠል ከቻላችሁ በሃያኛው ዓመት መጨረሻ ላይ ከሚሊዮን በላይ ሰዎች ይሆናሉ ማለት ነው። ይህ ድንቅ ነው። ጌታ የመሰረተው የመብዛት መንገድ ይህ ነው - ሄዶ ሰዎችን ደቀ መዝሙር ማድረግ፣ ሄዶ ሰዎችን እንዲለወጡ ማድረግ አይደለም። ይህ መንገድ በብዙ መልኩ የእግዚአብሔር መንግስት እንዲስፋፋና ሰዎችን እንዲደርስ ለማድረግ ተመራጭ መንገድ ነው፣ አእምሮአችን ግን ቶሎ አቋራጭ መንገድን ይፈልጋል።

ታላላቅ ጉባኤዎችን የተሳተፉ፣ ውሳኔዎችን ያደረጉ፣ ክርስቲያን መሆናቸውንም ያወጁ፣ ነገር ግን በቁጣ የሚነዱ፣ ምሬት እና ቅናትን የተሞሉና የጌታ ተቃራኒ ምስክር የሆኑ ስንት ሰዎች ናቸው? ቆጠራ ብናካሂድ፣ ምን ያህል ሰዎች ክርስቲያን ነኝ የሚል ሰውን በማዬት ብቻ - እኔ ከነዚህ ግብዝ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ይልቅ ሳልሻል አልቀርም፣ ይቅርብኝ! ብለው በማሰብ ከእውነተኛው ወንጌል ርቀዋል።

ጥቅል ሃሳቡን ስንቋጨው፣ ደቀ መዝሙርነት እግዚአብሔር ዓለምን በመወንጌል ለመድረስ ያዘጋጀው መንገድ ነው። በቃሉ እስካልጸናችሁ ድረስ እውነት አርነት አያወጣችሁም (ዮሐንስ 8፡31-32)። በዚህ መልኩ እግዚአብሔር ሰው ሁሉ የእርሱን ሙላት ይለማመድ ዘንድ ይፈልጋል፣ እርሱ ያዘጋጀው የወንጌላዊነት መንገድም ይህ ነው። ማንም በዚህ መንገድ መስራት ትክክል አይደለም ብሎ የሚወስን ቢኖር በምትኩ የማይሰራ መንገድን ይከተላል።

እግዚአብሔር የደቀ መዝሙርነትን ዋጋ ማየት እንድትችሉ በልባችሁ ይነግራችሁ ዘንድ እጸልያለሁ። ደቀ መዝሙር እንድትሆኑና ሄዳችሁ ሌሎች ሰዎችንም ደቀ መዝሙር እንድታደርጉ አበረታታችኋለሁ።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ኢየሱስ ማንንም “ክርስቲያን” ይሆን ዘንድ አለመጥራቱን ማወቅ ያስደንቃችኋል፤ ከዚህ ይልቅ የእርሱ ጥሪ ሰዎች “ደቀ መዝሙር” ይሆኑ ዘንድ ነው። አራቱንም ወንጌሎች (ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ እና ዮሐንስ) ተመልከቱ እና በሌላ ባዶ ወረቀት የኢየሱስ ጥሪ ደቀ መዝሙርነት መሆኑን የሚያሳዩ ጥቅሶችን ፈልጋችሁ በዝርዝር ጻፉ።

2. በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ለሰዎች ክርስቲያን እንዲሆኑ ጥሪ አይደረግላቸውም፣ ይልቁንም ደቀ መዝሙር ይሆኑ ዘንድ ጥሪ ይደረግላቸው ነበር። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን በመመልከትና ሌላ ባዶ ወረቀት በመጠቀም ለሰዎች ደቀ መዝሙር ይሆኑ ዘንድ ጥሪ የተደረገባቸውን የቻላችሁትን ያህል ጥቅሶች ፈልጋችሁ አስፍሩ።

3. “ደቀ መዝሙር” (ደቀ መዛሙርት) የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ከ273 ጊዜ በላይ ተጠቅሷል። “ክርስቲያን (ኖች)” የሚለው ቃል ሦሥት ጊዜ ብቻ ነው በሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰው። እነዚህ ሦሥት ጊዜ “ክርስቲያን (ኖች)” ተብለው የተጠቀሱትን ጥቅሶች ፈልጉና በሌላ ወረቀት ጻፉ።

4. ማቴዎስ 10፡25ን አንብቡና በዚህ ጥቅስ መሰረት ደቀ መዝሙር ማለት ምን ማለት ነው?

   **ማቴዎስ 10፡25** *“ደቀ መዝሙር እንደ መምህሩ፥ ባሪያም እንደ ጌታው መሆኑ ይበቃዋል። ባለቤቱን ብዔል ዜቡል ካሉት፥ ቤተሰዎቹንማ እንዴት አብዝተው አይሉአቸው!”*

5. ሉቃስ 14፡26 እውነት ወይም ሐሰት፣ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ማለት ለሌላ ሰው ሕይወት የራስን ሕይወት ሙሉ በሙሉ መሰዋዕት ማድረግ ማለት ነው።

   **ሉቃስ 14፡26** *“ማንም ወደ እኔ የሚመጣ ቢኖር አባቱንና እናቱን ሚስቱንም ልጆቹንም ወንድሞቹንም እኅቶቹንም የራሱን ሕይወት ሰንኳ ሳይቀር ባይጠላ፥ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።”*

6. ሉቃስ 14፡33 እውነት ወይም ሐሰት፣ በአንዳንድ ሁኔታዎች የኢየሱስ ደቀ መዝሙር መሆን ማለት፣ ኢየሱስን ለማስቀደም ሲባል ሁሉንም ነገር መተው ማለት ነው።

   **ሉቃስ 14፡33** *“ጌታውም ባሪያውን። ቤቴ እንዲሞላ ወደ መንገድና ወደ ቅጥር ውጣና ይገቡ ዘንድ ግድ በላቸው፤”*

7. ማቴዎስ 19፡29 እውነት ወይም ሐሰት፤ ማንም ቤቱን የሚተው፣ ወንድሞችን፣ እህቶችን፣ አባት፣ እናት፣ ሚስት፣ ልጆችን ወይም መሬቱን ለኢየሱስ ሲል የሚተው፣ ያንኑ መቶ እጥፍ ያገኛል የዘላለም ሕይወትም ይወርሳል።

   **ማቴዎስ 19፡29** *“ስለ ስሜም ቤቶችን ወይም ወንድሞችን ወይም እኅቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ ሁሉ መቶ እጥፍ ይቀበላል የዘላለምንም ሕይወት ይወርሳል።”*

8. የሐዋርያት ሥራ 14፡22 ደቀ መዛሙርት በእምነታቸው መቀጠል ያስፈልጋቸዋል።

**የሐዋርያት ሥራ 14፡22** *“በዚያችም ከተማ ወንጌልን ሰብከው እጅግ ደቀ መዛሙርትን ካደረጉ በኋላ፥ የደቀ መዛሙርትን ልብ እያጸኑ በሃይማኖትም ጸንተው እንዲኖሩ እየመከሩና። ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል እያሉ፥ ወደ ልስጥራን ወደ ኢቆንዮንም ወደ አንጾኪያም ተመለሱ።”*

9. ዕብራውያን 10፡14 ደቀ መዝሙርነት ላይ አጽንኦት በሚሰጡ ጥቅሶች ላይ ያለው የአንዳንዶች ተቃውሞ ክርስቲያን ለመሆን ምንም ጥረት እና ልፋት የማይጠይቅ (በጸጋ ስለሆነ) ነው፤ ነገር ግን “ደቀ መዝሙር” መሆን ተግባራዊ ውሳኔ እና መሰዋዕትነት የሚጠይቅ ነው። እውነቱ እንግዲህ ክርስቶስ የከፈለልን ዋጋ የእኛን ተግባር የሚጠይቅ አይደለም፣ ፍጹም ነውና የእኛን ጥረት አይጠይቅም ነገር ግን የክርስቶስ ጥሪ ሁሌም የእኛን ሙሉ እና ፍጹምሕይወት ነው።

**ዕብራውያን 10፡14** *“አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጎአቸዋልና።”*

10. የሐዋርያት ሥራ 11፡26 የክርስቶስ ጥሪ ለሁለት ዓይነት አማኞች ማለትም አንዳንዶች ክርስቲያን ሆነው በሥጋ ይሆኑ ዘንድ ሌሎች ደግሞ ደቀ መዝሙር ይሆኑ ዘንድ አይደለም። እንደ እውነቱ ከሆነ ክርስቲያኖች እና ደቀ መዛሙርት አንድ ሊሆኑ የተገባ ነው።

*የ**ሐዋርያ ሥራ 11፡26*** *“ባገኘውም ጊዜ ወደ አንጾኪያ አመጣው። በቤተ ክርስቲያንም አንድ ዓመት ሙሉ ተሰበሰቡ፥ ብዙ ሕዝብንም አስተማሩ፤ ደቀ መዛሙርትም መጀመሪያ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ።”*

11. ማቴዎስ 28፡19-20 የኢየሱስ ተልዕኮ ለአማኞች ሄደው _______________ እንዲያደርጉ ነው።

ሀ. ደቀ መዛሙርት
ለ. ሕዝቦቹን እንዲቀይሩ

**ማቴዎስ 28፡19-20** *“እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።”*

12. ማቴዎስ 28፡20 እውነት ወይም ሐሰት፤ አማኞች ኢየሱስ ያዘዘውን ሁሉ ይቀበሉ ዘንድ ሌሎችን ሊያስተምሩ ይገባል።

13. ዮሐንስ 1፡12 እውነት ወይም ሐሰት፤ ኢየሱስ የሚያስፈልጉንን ጥቅሞች ሁሉ ሰጥቷል (ምህረትን፣ ጽድቅን፣ ወዘተ…) ነገር ግን እራሱንም ጭምር ሳይቀር ነው።

**ዮሐንስ 1፡12** *“ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤”*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ኢየሱስ ማንንም “ክርስቲያን” ይሆን ዘንድ አለመጥራቱን ማወቅ ያስደንቃችኋል፤ ከዚህ ይልቅ የእርሱ ጥሪ ሰዎች “ደቀ መዝሙር” ይሆኑ ዘንድ ነው። አራቱንም ወንጌሎች (ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ እና ዮሐንስ) ተመልከቱ እና በሌላ ባዶ ወረቀት የኢየሱስ ጥሪ ደቀ መዝሙርነት መሆኑን የሚያሳዩ ጥቅሶችን ፈልጋችሁ በዝርዝር ጻፉ።

2. በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ለሰዎች ክርስቲያን እንዲሆኑ ጥሪ አይደረግላቸውም፣ ይልቁንም ደቀ መዝሙር ይሆኑ ዘንድ ጥሪ ይደረግላቸው ነበር። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን በመመልከትና ሌላ ባዶ ወረቀት በመጠቀም ለሰዎች ደቀ መዝሙር ይሆኑ ዘንድ ጥሪ የተደረገባቸውን የቻላችሁትን ያህል ጥቅሶች ፈልጋችሁ አስፍሩ።

3. “ደቀ መዝሙር” (ደቀ መዛሙርት) የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ከ273 ጊዜ በላይ ተጠቅሷል። “ክርስቲያን (ኖች)” የሚለው ቃል ሦሥት ጊዜ ብቻ ነው በሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰው። እነዚህ ሦሥት ጊዜ “ክርስቲያን (ኖች)” ተብለው የተጠቀሱትን ጥቅሶች ፈልጉና በሌላ ወረቀት ጻፉ።
   **የሐዋርያት ሥራ 11፡26፣ 26፡28 እና 1ኛ ጴጥሮስ 4፡16።**

4. ማቴዎስ 10፡25ን አንብቡና በዚህ ጥቅስ መሰረት ደቀ መዝሙር ማለት ምን ማለት ነው?
   **ደቀ መዝሙር እንደ ጌታው ወይም እንደ መምህሩ የሆነ ማለት ነው።**

5. ሉቃስ 14፡ 26 እውነት ወይም ሐሰት፣ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ማለት ለሌላ ሰው ሕይወት የራስን ሕይወት ሙሉ በሙሉ መሰዋዕት ማድረግ ማለት ነው።
   **እውነት።**

6. ሉቃስ 14፡33 እውነት ወይም ሐሰት፣ በአንዳንድ ሁኔታዎች የኢየሱስ ደቀ መዝሙር መሆን ማለት፣ ኢየሱስን ለማስቀደም ሲባል ሁሉንም ነገር መተው ማለት ነው።
   **እውነት።**

7. ማቴዎስ 19፡29 እውነት ወይም ሐሰት፤ ማንም ቤቱን የሚተው፣ ወንድሞችን፣ እህቶችን፣ አባት፣ እናት፣ ሚስት፣ ልጆችን ወይም መሬቱን ለኢየሱስ ሲል የሚተው፣ ያንኑ መቶ እጥፍ ያገኛል የዘላለም ሕይወትም ይወርሳል።
   **እውነት።**

8. የሐዋርያት ሥራ 14፡22 ደቀ መዛሙርት በእምነታቸው መቀጠል ያስፈልጋቸዋል።
   **እውነት።**

9. ዕብራውያን 10፡14 ደቀ መዝሙርነት ላይ አጽንኦት በሚሰጡ ጥቅሶች ላይ ያለው የአንዳንዶች ተቃውሞ ክርስቲያን ለመሆን ምንም ጥረት እና ልፋት የማይጠይቅ (በጸጋ ስለሆነ) ነው፤ ነገር ግን “ደቀ መዝሙር” መሆን ተግባራዊ ውሳኔ እና መሰዋዕትነት የሚጠይቅ ነው። እውነቱ እንግዲህ ክርስቶስ የከፈለልን ዋጋ የእኛን ተግባር የሚጠይቅ አይደለም፣ ፍጹም ነውና የእኛን ጥረት አይጠይቅም ነገር ግን የክርስቶስ ጥሪ ሁሌም የእኛን ሙሉ እና ፍጹምሕይወት ነው።
   **እውነት።**

10. የሐዋርያት ሥራ 11፡26 የክርስቶስ ጥሪ ለሁለት ዓይነት አማኞች ማለትም አንዳንዶች ክርስቲያን ሆነው

በሥጋ ይሆኑ ዘንድ ሌሎች ደግሞ ደቀ መዝሙር ይሆኑ ዘንድ አይደለም። እንደ እውነቱ ከሆነ ክርስቲያኖች እና ደቀ መዛሙርት አንድ ሊሆኑ የተገባ ነው።
**እውነት።**

11. ማቴዎስ 28፡19-20 የኢየሱስ ተልዕኮ ለአማኞች ሄደው ______________ እንዲያደርጉ ነው።
**ሀ. ደቀ መዛሙርት።**

12. ማቴዎስ 28፡20 እውነት ወይም ሐሰት፤ አማኞች ኢየሱስ ያዘዘውን ሁሉ ይቀበሉ ዘንድ ሌሎችን ሊያስተምሩ ይገባል።
**እውነት።**

13. ዮሐንስ 1፡12 እውነት ወይም ሐሰት፤ ኢየሱስ የሚያስፈልጉንን ጥቅሞች ሁሉ ሰጥቷል (ምህረትን፣ ጽድቅን ወዘተ...) ነገር ግን እራሱንም ጭምር ሳይቀር ነው።
**እውነት።**

# ትምህርት 15

# ምስክርነታችሁን ስለመጠቀም

## በዶን ክሮው

ዛሬ ደግሞ የእራሳችሁን ምስክርነት እንዴት መጠቀም እንዳለባችሁ ልነግራችሁ እፈልጋለሁ። የሐዋርያት ሥራ 5፡42 እንዲህ ይላል “ዕለት ዕለትም በመቅደስና በቤታቸው ስለ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ ማስተማርና መስበክን አይተዉም ነበር”። አስተውሉ፤ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ደቀ መዛሙርት በየቀኑ በቤተ መቅደስ እና ቤት ለቤት ይገናኙ ነበር፣ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ ያስተምሩና ይሰብኩም ነበር። ብዙ ሰዎች ቤት ለቤት ወይም በየበሩ የሚደረግ አገልግሎትን ያልተለመደ እና ምቾት እንደማይሰጥ ይሰማቸዋል። በበኩሌ በሮች ለደቀ መዝሙርነት እንዴት እንደተከፈቱልን፣ በመውጣታችን ምክንያት ያጋጠሙንን ጉዳዮች፣ ሰዎችም ተለውጠው እንዴት ወደ ክርስቶስ ኢየሱስ እንደዞሩ ጥቂት ነገሮችን ላካፍላችሁ እወዳለሁ።

የምትሰሙትን ያህል በእርግጥ አስቸጋሪ አይደለም፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ገና ካልተለወጠ ሰው ጋር በሚያወራበት ጊዜ ከአንዴም ሦሥቴ የእራሱን ምስክርነት እንደተጠቀመ ይህን አንድ ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማስተዋል ችያለሁ። በሐዋርያት ሥራ 9፣ 22 እና 26 ምስክርነቱን ሲሰጥ፣ ልምምዱን እና ያጋጠመውን ሁሉ ለማያምኑ ሰዎች ሲነግራቸው እናስተውላለን። የኢየሱስ ክርስቶስን መልዕክት ለሰዎች ለማድረስ ከተጠቀምንባቸው መልካም አማራጭ መንገዶች ውስጥ አንዱ “የእርምጃ ጸሎት” ወይም “prayer-walking” ነው። ከበር ወደ በር እየሄድን በማንኳኳት እንዲህ እንላቸዋለን “በዚህ አካባቢ ላሉ ሰዎች እየጸለይን ነው። እግዚአብሔር ጸሎትን እንደሚሰማና እንደሚመልስ እናምናለን እናም በቤተሰባችሁ ውስጥ አንዳች ችግር - የጤና ወይም ሌላ ዓይነት ችግር ካለ - ልንጸልይላችሁ እንፈልጋለን”። አንዳንድ ጊዜ “አዎ ችግር አለብኝ” ይሉና እንድንጸልይላቸው ይጠይቁናል፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ በመጠኑም ቢሆን ምቾት አይሰማቸውም ወይም እንደ ሃፍረት ይሰማቸውና “አንፈልግም፣ ምንም ዓይነት የጸሎት ጥያቄ በአሁኑ ጊዜ የለንም” ብለው ይመልሱናል። ያኔ የራሳችንን ምስክርነት ለእነርሱ መንገር እንጀምራለን።

እንዲህ በማለት እጀምራለሁ “ልጆች እንዳሏችሁ አይቻለሁ። እኔም እራሴ ሦሥት ልጆች አሉኝ። በታህሳስ 14/1981 እ.ኤ.አ መንታ ሴቶች ልጆች ተወለዱልኝ። ሁለተኛዋ መንታ ልጅ ስትወለድ ትንፋሽ ወይም እስትንፋስ አልነበራትም” እላቸዋለሁ። እነርሱም በሃዘን እያዩኝ “ያሳዝናል፣ አሳዛኝ ነገር ነው ያጋጠመህ” ይሉኛል። እኔም “እረ ማዘን አያስፈልጋችሁም፣ ቀጥሎ ምን እንደተፈጠረ ልንገራችሁ” እላቸውና ታሪኩን በዝርዝር እነግራቸዋለሁ። ከመንታዎቹ ሁለተኛዋ ልጅ ስትወለድ አመጣጧ በተቃራኒ አቅጣጫ ወይም በእግሯ በኩል ነበር የወጣችው። በምትወለድበት ጊዜ ለተወሰነ ጊዜ አየር (ኦክሰጂን) ተቋርጦባት ነበርና በዚህ ምክንያት ስትወለድ ምንም ትንፋሽ አልነበራትም። ሞታ ነበር የተወለደችው።

“አዋላጇ አንስታ ጀርባዋን ትጠበጥባት ጀመር (የቻለችውን ያህል ደጋግማ በሃይል ጠበጠበቻት)፣ ከሳምባዎቿ ፈሳሽ ለማስወጣትም በአፏ ትመጣት ነበር፣ የቻለችውን ሁሉ አድርጋ በመጨረሻ ተሸነፈች። እኔም እንደ ማንኛውም አባት ነኝ። ልጄን አጥቻለሁ ምን ባደርግ ይሻለኛል ማለቴ አይቀርም?” በራቸው ላይ ቆመው በደምብ እያዳመጡኛ መሆኑን ሳረጋግጥ እንዲህ በማለት ጥያቄ አቀርብላቸዋለሁ “አንድ ነገር ልጠይቃችሁ እስኪ፣ የመጽሐፍ ቅዱስን አብዛኛውን ክፍል አንብባችኋል?” እነርሱም “የተወሰነ ጥቂት ክፍሎችን አንብቤአለሁ” ይላሉ ወይም አንዳንዴ “እረ ምንም አንብቤ አላውቅም” በማለት ይመልሳሉ። እኔም እንዲህ በማለት ማብራሪያዬን እቀጥልላቸዋለሁ “ይህን ጥያቄ እንዳቀርብላችሁ ምክንያት የሆነኝ መጽሐፍ ቅዱስ በሐዋርያት ሥራ 10፡38 ኢየሱስ መልካም እያደረገ፣ ለዲያብሎስም የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ፣ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረና ስለሚል ነው። ምን እንደተፈጠረ ልንገራችሁ። እንደየፍላጎታችሁ መቀበል ወይም አለመቀበል ትችላላችሁ፤ ልጄ ሞታ ነበር፣ እኔም ከጥቂት ቀን በኋላ እንደምንቀብራት እያሰብኩ ነበር። ልጄን ማቀፍ እፈልጋለሁ ብዬ ለእራሴ

እሰብኩ። ልጄን ላነሳት ወደ እርሷ በተጠጋሁ ጊዜ በእርሷ ላይ ክፉ መንፈስ ሰፍሮ ነበር፣ ይህንንም መጽሐፍ ቅዱስ የአጋንንት መንፈስ በማለት ይጠራዋል። ይህ መንፈስ በእኔም አካል ላይ ጥቃት አደረሰብኝ፣ ለጊዜውም ቢሆን መንቀሳቀስ እንዳልችል አድርጎኝ ነበር። ይህ እንደሆነ ግን ወዲያውኑ "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፣ አንተ እርኩስ መንፈስ ከዚህች ሕጻን ላይ እንድትወጣ አዝሃለሁ፣ ደግሞም በኢየሱስ ስም በዚህች ህጻን ላይ ህይወትን እዝዛለሁ" ብዬ ተናገርኩ። ያች ምንም እስትንፋስ ያልነበራት ህጻን እንዴ በማቃሰት ተነፈሰችና እንደገና መልሳ ጸጥ አለች። እኔም እንደገና በድጋሚ ማዘዜን ቀጠልኩ "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፣ አንተ እርኩስ መንፈስ፣ ከዚህች ልጅ ላይ አሁኑኑ እንድትወጣ አዝሃለሁ ሕይወት ይሁንላት" አልኩ፣ በዚህ ጊዜ ግን ደጋግማ ብዙ ጊዜ አቃሰተችና ህይወቷ፣ እስትንፋሷ ተመለሰ፣ መተንፈስም ቀጠለች።"

በትኩረት ይሰማኝ የነበረውን ሰው በሰሙ ጠራሁና "እየህ፣ አንድ ሰው ለሦሥት ደቂቃ ያህል አየር (ኦክስጂን) ወደ አንጎሉ ካልደረሰለት አእምሮው ይጎዳል። የኔ ልጅ ግን በሁሉም ነገር ፍጹም ደህና ነበረች። ስሟንም ቪታ ብለን ጠራናት፣ ይህም በላቲን "ሕይወት" የሚል ትርጓሜ ያለው ሲሆን፣ እግዚአብሔር በእርሷ ላይ የሰራውን ታሪክ መናገር ስለፈለግን ነበር ይህን ያደረግነው። እግዚአብሔር እንደገና ህይወት ሰጥቷታል። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ መጽሐፍ ቅዱሴን አዘውትሬ እነብባለሁ፣ በዚህም አንድ ነገር መገንዘብ ችዬ ነበር፡ ልክ በልጄ ላይ እንደነበረው እርኩስ መንፈስ በሰይጣን አገዛዝ ስር የሚመራ የጨለማው መንግሰት አለ፣ ደግሞም የእግዚአብሔር ውድ ልጅ መንግሰት አለ።

"ኢየሱስ ወደ ምድር እንደ መጣ ሕዝቦችን ከጨለማው መንግሰት በመውጣት ወደ እርሱ መንግሰት በንስሐ እና በእርሱ በማመን - የኃጢአት ይቅርታን ተቀብለው ወደ እርሱ በመመለስ፣ እንዲመጡ ጥሪ ያደርግላቸው ነበር። እምነትህ ምን እንደሆነ ወይም በምን እንደምታምን አላውቅም፣ ነገር ግን እየነገርኩህ ያለሁት በእኔ እና በቤተሰቤ ሕይወት ውስጥ ያጋጠመንን ታሪክ ነው። አሁን ወደ አንተ በር የመጣንበትን ትክክለኛ ምክንያት እንድታውቅ እፈልጋለሁ። ኢየሱስ ወደ ሰዎች ሄደን ደቀ መዝሙር እንዲሆኑ እንድናደርግ ነግሮናል። እኔም ብዙ ሰዎች በሥራ ጫና ምክንያት ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ እንደሚቸገሩ ወይም እንደማይፈልጉ አስተውያለሁ። ጥያቄ ቢኖርህ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እጅህን አንስተህ መጋቢውን (ወይም ቄሱን) "እባክዎ አሁን የነገሩን ነገር ምን ማለት እንደሆነ ማወቅ እችላለሁ?" ብለህ መጠየቅ አትችልም። ስለዚህ ወደ አንተ በር የመምጣታችን ምክንያት ይህ ነው። ለአሰር ደቂቃ ያህል የእግዚአብሔርን ቃል በጥቅሉ እንመለከታለን። በመቀጠል ቃሉን በትክክል መረዳታችን ለማረጋገጥ ከቃሉ አንዳንድ ጥያቄዎችን እናነሳለን። ወደ ፊት እና ወደ ኋላ እያልን ውይይታችንን እንቀጥላለን። ለሰብከት ወይም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል እያልን ሰዎችን እየሰበክን ሳይሆን አንዳንድ ጥያቄዎችን በማንሳት ቃሉ የሚለውን መረዳት ይችሉ ዘንድ ለማገዝ እንሞክራለን።

"ይህ ይስማማሃል? አንተ የሚመችህን ሰዓት መምረጥ ትችላለህ በሚመችህ ሰዓት ወደ ቤትህ በመምጣት እናወራለን ትምህርቱንም እናካፍልሃለን። በመጀመሪያው ትምህርታችን ምንም መልካም ነገር ካላገኘኽበት፣ ምንም ካልጠቀመህ፣ ካላጽናናህና ካላነጸህ ዳግመኛ ፊታችንን አታይም እደጅህም ድርሽ አንልም። እዚህ መምጣታችን አንተን ለመነዝነዝ አይደለም። የቤተ ክርስቲያን ወይም የተቋማችን አባል እንድትሆንም አይደለም። እዚህ የመጣንበት ብቸኛ ምክንያት ኢየሱስ ክርስቶስ ለአንተ በግል ያደረገልህን ነገር እንድታውቅ ደግሞም የእግዚአብሔርን ቃል መረዳት እንድትችል ለመርዳት ብቻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ገና የማናውቃቸው እና ፍጹም ጨርሰን ያልተረዳናቸው ብዙ ነገሮች አሉ፣ ነገር ግን አሁን መጠነኛ ጥናት ልናቀርብልህ ተዘጋጅተናል። በዚህ ደስተኛ ነህ? ይስማማሃል?" ብዙ ሰዎች ለዚህ ጥያቄ የሚሰጡን መልስ "አዎ፣ ይስማማኛል" የሚል ነው፣ ስለዚህ ሰዓት መድበን ወደ ቤታቸው በመሄድ ይህን የደቀ መዝሙር ትምህርት እንጀምራለን። ቤታቸው የምንሄደው እኔ "የማይክሮዌቭ ወንጌላዊነት" ብዬ የምጠራውን፣ እጃቸውን በመጠምዘዝ፣ ምን እያደረጉ እንደሆነ እንኳን ገና ሳይረዱ አጭር ጸሎት እንዲያደርጉ ለማድረግ አይደለም። ነገር ግን የደቀ መዝሙርነት ትምህርትን በመከተል የተሰቀለውን፣ ክርስቶስን እንዲያውቁ እናግዛቸዋለን።

ለአንድ መጋቢ ስለ ደቀ መዝሙርነት ትምህርታችን ነግሬው ነበር፣ እርሱም "እሺ ዶን፣ ከመጀመሪያው ትምህርት በኋላ ምን ተፈጠረ?" ሲል ጠየቀኝ። ከመጀመሪያ ትምህርታችን በኋላ ሰዎች የሚያስፈልጋቸውንና ለኢየሱስ ክርስቶስ ራሳቸውን ለመስጠትና ምህረቱንና ይቅርታውን ለመቀበል ምን ማድረግ እንዳለባቸው ይረዳሉ። እኛ የተዋጣለት የሽያጭ ሰራተኛ አይደለንም። በዚህ መልኩ ወደ ሰዎች አንቀርብም፣ ነገር ግን ገና በመጀመሪያው ትምህርት ምን ማድረግ እንዳለባቸው ከልባቸው ወደ መገንዘብ ደረጃ ይደርሳሉ በማለት አብራራሁለት። እርሱም በመቀጠል "መልካም ነው፣ ከትምህርት 15 በኋላስ?" ሲል ጠየቀኝ። እኔም "ሰዎች እስከ ትምህርት 15 ከእኛ ጋር ከቆዩ፣ ኃጢአታቸውን በመናዘዝ የውሃ ጥምቀት ይጠመቃሉ፣ በመንፈስ ቅዱስም ይጠመቃሉ። ይህ ነገር ሲሆን አይተናል፣ ነገር ግን ከትምህርት 15 በኋላ ሳይሆን ገና ከትምህርት 6 በኋለም ይህ ሲሆን ተመልክተናል።"

በማቴዎስ 28 ኢየሱስ፣ ወደ አሕዛብ ሁሉ ሂዱና ሄዳችሁም በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስመ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው ይላል። ደቀ መዝሙር በማድረግ ሂደት ላይ የማያምኑ ሰዎች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስና ስለ ስቅለቱ ግንዛቤ እንዲኖራቸው እናደርጋለን። ከሳምንት ሳምንት ይህን መረዳት ባካፈልናቸው ቁጥር ከእነርሱ ጋር መልካም ወዳጅነት እየፈጠርን እንመጣለን። ለእኛ ያላቸው ፍቅር እና መተማመን ይጨምራል። የእግዚአብሔርን ቃል እያካፈልናቸው እንጂ እየሰበክናቸው አይደለም። ቃሉን እናነብላቸዋለን፣ እነርሱም እንዲያነብቡ እናደርጋለን፣ ደግሞም ለምናቀርብላቸው ጥያቄ መልሱን በራሳቸው ከእግዚአብሔር ቃል ላይ እንዲያገኙ እናደርጋለን። ከሳምንት ሳምንት፣ ሰዎች ክርስቶስን በነጻነት ለመመስከር ፈቃደኛ ሲሆኑ ተመልክተናል፣ እርሱን መቀበል ማለት ምን ማለት እንደሆነ በማወቅ፣ እርሱን ለመከተልና ለእርሱም ራሳቸውን ለመስጠት ሲወስኑ ተመልከተናል። ይህም አሁን ላይ ከተለመዱት የወንጌላዊነት አቀራረብ መንገዶች እጅጉን የተለየ ነው።

የጠፉ ሰዎችን መድረስ ከምንችልባቸው መንገዶች ውስጥ የመጀመሪያው የእራሳችንን ምስክርነት መጠቀም ነው፣ ሁላችንም የየግል ምስክርነት አለን። ብዙ ጊዜ የራሳችንን ማስታወሻዎች እንጽፋለን። እኔም "የልጄ ሞት" በሚል የጻፍኩትን ማስታወሻ ብዙ ጊዜ በየቤቶች በር ላይ አስቀምጥ ነበር። ሌሎች በእኛ የወንጌላዊ ደቀመዝሙርነት ቡድን ውስጥ የነበሩ ሰዎች ደግሞ፣ በአልኮል እና አደንዛዥ እፅ እስራት ውስጥ የነበረው የጀ ሮዝ "ከባርነት ነጻ መውጣት" ታሪክ እና ከአሥራ አምስት ዓመቱ ጀምሮ በአደንዛዥ እፅ እስራት የነበረውና ኢየሱስ ነጻ ያወጣው የሮኪ ፎሪ "የክፋ ሱሰኛው ሞት" በሚል ማስታወሻዎችን ይጽፉ ነበር። እነዚህን ምስክርነቶች በየቤቶች በር ላይ እንናገር ነበር።

አንዳንድ ሰዎች "እኔ እንኳን ይህ ነው የሚባል ምስክርነት የለኝም። ሞቶ ከሰምንት ደቂቃ በኋላ ከሞት የተነሳ ልጅም የለኝም" ሊሉ ይችላሉ። አዎ ብዙ ሰዎች እንዲህ ዓይነት ተመሳሳይ ምስክርነት እንደሌላቸው አውቃለሁ። ምናልባት እንደ አንድሩ ዉማክ ዓይነት ምስክርነት ደግሞ ሊኖራችሁ ይችላል፣ ለእርሱ የእግዚአብሔር ኃይል ከታናሽነቱ ዘመን ጀምሮ ብዙዎች ከሚቸገሩበት ከዚህ ዓለም ኃጢአት፣ ክፋት እና ርኩሰት ህይወቱን የጠበቀለት ሰው ነው። እያንዳንዳችን የራሳችን ምስክርነት ይኖረናል፣ የራሳችሁ ምስክርነት ምናልባት አይመጥንም ብላችሁ ካሰባችሁ የእኔን ምስክርነት መጠቀም ትችላላችሁ። የወንጌላዊ ደቀ መዝሙርነት ቡድናችን መሰርተን ወደ ሰዎች መድረስ በጀመርን ጊዜ ጆ ሮዝ የእኔን ምስክርነት ይጠቀም ነበር፣ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግን፣ ከእኔ በተሻለ አቀራረብ ያቀርብላቸው ነበር፣ እኔም "ቀጥል ጆ፣ የሆነልኝን ሁሉ ንገርልኝ" እለው ነበር።

በአዲስ ኪዳን፣ ሐዋርያው ጳውሎስ የእራሱን ምስክርነት ለሦሥት ጊዜ ያህል የጠፉ ሰዎችን ለመድረስ ከተጠቀመ እናንተም ይህን ማድረግ ትችላላችሁ። ዛሬ ላይ እኛ ብዙ ዓይነት ፕሮግራም የሞላቸው ከምፒውተሮች አሉን፣ "ወርድ ፐርፌክት፣ ማይክሮሶፍት ወርድ" እና የመሳሰሉት። የራሳችሁን ምስክርነት በአጭር ማስታወሻ (ትራክት) ማዘጋጀት ቀላል ነው። "ይህን ከመጽሐፍት ቤት አልገዛሁትም፣ ይህ የማካፍላችሁ በራሴ ህይወት የደረሰውን ታሪክ ነው" ብላችሁ መናገር ይበልጥ ውጤታማ አቀራረብ ነው።

አረፍ ብላችሁ - ያጋጠማችሁን - እንዴት ወደ ኢየሱስ እንደመጣችሁ የራሳችሁን የግል ማስታወሻ እንድታዘጋጁ እመክራችኋለሁ። ከዛም ምስክርነታችሁን ልክ በሰው ቤት በር ላይ እንደምታስቀምጡ ሁሉ ለአንድ ለሌላ ሰው ስጡት።

በዚህ ጉዳይ የበለጠ መረጃ ካስፈለጋችሁ ወደ በይነ መረባችን **www.krowtracts.com** በመግባት (Tips on Sharing Your Faith) በሚለው ርዕስ ስር አስፈላጊ መረጃዎችን ማግኘት ትችላላችሁ። የእራሳችሁን ምስክርነት በማስታወሻ አስፍሩ። ለሰዎች ማቅረብንም ተለማመዱ፣ "እምነታችሁን የማካፈያ ፍንጮች"ን አጥኑ። የጻፋችሁትን ማጥናት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን አትርሱ - ማንበብ አይደለም - አጥኑ፣ ሰዎችን ደቀ መዝሙር ለማድረግ ሂዱ፣ በተናጠል ለአንድ ሰው በመንገር ጀምሩ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ማርቆስ 16፡15ን አንብቡና ወንጌል ለማን ሊነገር ይገባል?

   **ማርቆስ 16፡15** *"እንዲህም አላቸው። ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ።"*

2. ማቴዎስ 28፡19-20 ደቀ መዝሙር መሆን የሚገባው ማን ነው?

   **ማቴዎስ 28፡19-20** *"እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።"*

3. የሐዋርያት ሥራ 8፡5፣26፤ የሐዋ ሥራ16፡13-15፣ 23 እና የሐዋ ሥራ 20፡20-21። ወንጌላዊነት የት ቢደረግ መልካም ነው?

   **የሐዋርያት ሥራ 8፡5** *"ፊልጶስም ወደ ሰማርያ ከተማ ወርዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው።"*

   **የሐዋርያት ሥራ 8፡26** *"የጌታም መልአክ ፊልጶስን። ተነሥተህ በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው ምድረ በዳ ወደ ሆነ መንገድ ሂድ አለው።"*

   **የሐዋርያት ሥራ 16፡13-15** *"በሰንበት ቀንም ከከተማው በር ውጭ የጸሎት ስፍራ በዚያ መሆኑን ስላሰብን ወደ ወንዝ አጠገብ ወጣን፤ ተቀምጠንም ለተሰበሰቡት ሴቶች ተናገርን። [14] ከትያጥሮን ከተማም የመጣች ቀይ ሐር ሻጭ እግዚአብሔርን የምታመልክ ልድያ የሚሉአት አንዲት ሴት ትሰማ ነበረች፤ ጳውሎስም የሚናገረውን ታዳምጥ ዘንድ ጌታ ልብዋን ከፈተላት። [15] እርስዋም ከቤተ ሰዎችዋ ጋር ከተጠመቀች በኋላ። በጌታ የማምን እንድሆን ከፈረዳችሁልኝ፥ ወደ ቤቴ ገብታችሁ ኑሩ ብላ ለመነችን፤ በግድም አለችን።"*

   **የሐዋርያት ሥራ 16፡23** *"በብዙም ከደበደቡአቸው በኋላ ወደ ወኅኒ ጣሉአቸው፥ የወኅኒውንም ጠባቂ ተጠንቅቆ እንዲጠብቃቸው አዘዙት።"*

   **የሐዋርያት ሥራ 20፡20-21** *"ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ንስሐንና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመንን ለአይሁድና ለግሪክ ሰዎች እየመሰከርሁ በጉባኤም በየቤታችሁም አወራሁላችሁና አስተማርኋችሁ እንጂ፥ ከሚጠቅማችሁ ነገር አንዳች ሰንኳ አላስቀረሁባችሁም።"*

4. ማርቆስ 4፡11-12 አንብቡና ውይይት ከመደረጉ በፊት ሰው ግዴታ ሊያደርገው የሚገባው፣

   ሀ. ማዬት።
   ለ. መገንዘብ።
   ሲ. መሰማት።
   ዲ. መረዳት።
   ኢ. ሁሉም።

   **ማርቆስ 4፡11-12** *"እንዲህም አላቸው። ለእናንተ የእግዚአብሔርን መንግሥት ምሥጢር ማወቅ*

*ተሰጥቶአችኋል፤ በውጭ ላሉት ግን፥ አይተው እንዲያዩ እንዳይመለከቱም፥ ሰምተውም እንዲሰሙ እንዳያስተውሉም፥ እንዳይመለሱ ኃጢአታቸውም እንዳይሰረይላቸው ነገር ሁሉ በምሳሌ ይሆንባቸዋል።”*

5. የሐዋርያት ሥራ 28፡23-24 ጳውሎስ ወንጌልን እያብራራ ሲመሰክር፣ ሰዎች በኢየሱስ ላይ የነበራቸውን ጥያቄ ለማስረዳት ለምን ያህል ጊዜ ይህን ያደርግ ነበር?

   **የሐዋርያት ሥራ 28፡23-24** *“ቀንም ቀጥረውለት ብዙ ሆነው ወደ መኖሪያው ወደ እርሱ መጡ፤ ስለ እግዚአብሔር መንግሥትም እየመሰከረ ስለ ኢየሱስም ከሙሴ ሕግና ከነቢያት ጠቅሶ እያስረዳቸው፥ ከጥዋት ጀምሮ እስከ ማታ ድረስ ይገልጥላቸው ነበር።”*

6. የሐዋርያት ሥራ 16፡14 ሰው በእውነት ወደ ክርስቶስ ሲመለስ፣ ምን ይከፈትለታል?

   **የሐዋርያት ሥራ 16፡14** *“ከትያጥሮን ከተማም የመጣች ቀይ ሐር ሻጭ እግዚአብሔርን የምታመልክ ልድያ የሚሉአት አንዲት ሴት ትሰማ ነበረች፤ ጳውሎስም የሚናገረውን ታዳምጥ ዘንድ ጌታ ልብዋን ከፈተላት።”*

7. የሐዋርያት ሥራ 2፡37 ሰው ሲነካ እና ልቡ ሲከፈት ምን ይሆናል?

   **የሐዋርያት ሥራ 2፡37** *“ይህንም በሰሙ ጊዜ ልባቸው ተነካ፥ ጴጥሮስንና ሌሎችንም ሐዋርያት። ወንድሞች ሆይ፥ ምን እናድርግ? አሉአቸው።”*

8. የሐዋርያት ሥራ 16፡31 እና 2፡38። ስለዚህ ሰው ምን ማድረግ አለበት

   **የሐዋርያት ሥራ 16፡31** *“እነርሱም። በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።”*

   **የሐዋርያት ሥራ 2፡38** *“ጴጥሮስም። ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።”*

9. የሐዋርያት ሥራ 2፡42 እና ዮሐንስ 8፡31-32 ከዚህ በኋላስ ሰው ምን ማድረግ አለበት

   **የሐዋርያት ሥራ 2፡42** *“በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር።”*

   **ዮሐንስ 8፡31-32** *“ኢየሱስም ያመኑትን አይሁድ። እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤ [32] እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው።”*

10. ሮሜ 10፡14-15 ከኋላ ወደ ፊት በቅደም ተከተል (በእነዚህ ቃላት ውስጥ) ሰው ወደ ክርስቶስ የሚመጣው እንዴት ነው?

    **ሮሜ 10፡14-15** *“እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ? [15] መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው ተብሎ እንደ ተጻፈ ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ?”*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ማርቆስ 16፡15ን እንብቡና ወንጌል ለማን ሊነገር ይገባል?
   **ለሁሉም፣ ለፍጥረት ሁሉ።**

2. ማቴዎስ 28፡19-20 ደቀ መዝሙር መሆን የሚገባው ማን ነው?
   **ሁሉም ሕዝቦች።**

3. የሐዋርያት ሥራ 8፡5፣26፤ የሐዋ ሥራ16፡13-15፣ 23 እና የሐዋ ሥራ 20፡20-21። ወንጌላዊነት የት ቢደረግ መልካም ነው?
   **በከተሞች፣ በበረሃ፣ በወንዞች ዳር፣ በእስር ቤቶች፣ በጉባኤ እና በየቤቶች።**

4. ማርቆስ 4፡11-12 እንብቡና ውይይት ከመደረጉ በፊት ሰው ግዴታ ሊያደርገው የሚገባው፣
   **ኢ. ሁሉም።**

5. የሐዋርያት ሥራ 28፡23-24 ጳውሎስ ወንጌልን እያብራራ ሲመሰክር፣ ሰዎች በኢየሱስ ላይ የነበራቸውን ጥያቄ ለማስረዳት ለምን ያህል ጊዜ ይህን ያደርግ ነበር?
   **ከጥዋት እስከ ማታ፣ ምናልባትም ከሰድስት እስከ ሰምንት ሰዓት ድረስ።**

6. የሐዋርያት ሥራ 16፡14 ሰው በእውነት ወደ ክርስቶስ ሲመለስ፣ ምን ይከፈትለታል?
   **ልቡ፣ የሰው ዋናው ማዕከላዊ ክፍሉ ይከፈታል።**

7. የሐዋርያት ሥራ 2፡37 ሰው ሲነካ እና ልቡ ሲከፈት ምን ይሆናል?
   **በትክክል የሚመልሱ ከሆነ “ምን ማድረግ ይገባኛል?” ብለው ይጠይቃሉ።**

8. የሐዋርያት ሥራ 16፡31 እና 2፡38። ስለዚህ ሰው ምን ማድረግ አለበት?
   **ንሰሐ መግባት፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን እና መጠመቅ።**

9. የሐዋርያት ሥራ 2፡42 እና ዮሐንስ 8፡31-32 ከዚህ በኋላስ ሰው ምን ማድረግ አለበት?
   **በሐዋርያት ሃይማኖት (ትምህርት) መቀጠል:: የኢየሱስን ትምህርቶችን መማርና መለማመድን መቀጠል።**

10. ሮሜ 10፡14-15 ከኋላ ወደ ፊት በቅደም ተከተል (በእነዚህ ቃላት ውስጥ) ሰው ወደ ክርስቶስ የሚመጣው እንዴት ነው?
    **ሰው ይላካል። ለአንድ ሰው ይሰብካል፣ ወይም ይናገራል። የኢየሱስን መልዕክት በመሰማታቸው ሊያምኑ ይችላሉ። በማመናቸው፣ ለመዳን የጌታን ስም ይጠራሉ።**

## ትምህርት 16

# የሁሉን ሰው ስጦታዎች ለደቀመዝሙርነት መጠቀም

## በዶን ክሮው

የሁሉንም ሰው ስጦታዎች ለደቀ መዝሙርነት መጠቀም ይቻላል። ይህን የደቀ መዝሙር ፕሮግራም ለረጅም ዓመት በታላቅ ስኬት ስንሰራበት ቆይተናል። ብዙ ሰዎች ዳግመኛ በመወለዳቸው ህይወታቸው ተቀይሯል፣ ብዙዎች በመንፈስ ቅዱስ እና በውሃም ተጠምቀዋል። አንድ ቀን ከአንድ ወዳጄ ጋር እያወራን በነበረበት ጊዜ ግን እንዲህ አልኩት - “አንዳንድ የረሳናቸው ነገሮች አሉ፣ የተወሰኑ ነገሮች ከእጃችን አምልጠዋል” አልኩት። እርሱም “ምን ማለትህ ነው፣ እኔ ግን ሁሉም ነገር መልካም እንደሆነ ነው የማውቀው” አለኝ።

እኔም ላካፍላችሁ የምፈልገው ጉዳይ፣ ሰዎች ቁጭ ብለው መጋቢውን ወይም ሰባኪውን ሰምተው ወደ የቤታቸው የሚሄዱበትን የውስጥ ቤተ ክርስቲያን (inward church) - ከተለመደው የአምልኮ አዳራሽ አራት ግድግዳዎች ውጭ ሌሎች ሰዎችን በመድረስ - የውጭ ቤተ ክርስቲያን (outward church) ማድረግ የሚቻልበትን መንገድ እንዴት ማምጣት እንችላለን የሚለውን ነው። የሚከተለውን እውነተኛ መረጃ ላቅርብላችሁ፦ 95% የሚሆኑ ሁሉም ቤተ ክርስቲያኖች አንድም ሰው ወደ ጌታ ያላመጡ ናቸው፣ 90% የሚሆነው የወንጌል ጥሪ የሚደረገው ለክርስቲያኖች ነው። በዓለም ዙሪያ አብዛኛው የወንጌል ሥርጭት የሚካሄድበት ሰፍራ ቢኖር ያው የቤተ ክርስቲያን ህንጻ ውስጥ ነው። የሰንበት ትምህርት ቤት ክፍሎችን በወንጌል እንሞላለን፣ የተጠበቁ ቦታዎችንም (sanctuary) ህንጻውን ሳይቀር ወንጌላዊ በምናደርግበት መንገድ፣ ቤተ ክርስቲያን መለወጥ እንዳለባት እናስባለን።

የቤተ ክርስቲያን ህንጻዎች ግንባታ በሦሥተኛው ክፍለ ዘመን በኮንስታንቲን በኩል እስኪጀመር ድረስ አይታወቅም ነበር። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የጠፉ ነፍሳትን በመድረስ በኩል ቤተ ክርስቲያን በራሷ ህንጻዎች ግድግዳ ታጥራ፣ ራሷን ደብቃ ኖራለች። ውስጣዊ የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን ውጫዊ እንድትሆን ለማድረግ ከታጠረችባቸው ግድግዳዎች ውጭ መድረስ ይኖርብናል። አንድ የተደረገ ጥናት እንደሚያሳየው ከቤተ ክርስቲያን ህንጻዎች ውጭ የሚደረጉ ፕሮግራሞች 0.5% (ከአንድ ፐርሰንት በታች) መሆናቸውን ያሳያል። ይህም ማለት ዛሬ ላይ ዩናይትድ ስቴትስ አሜሪካ ውስጥ የጠፉ ነፍሳትን የመድረስ ዓላማ ያለው የእምነት ተቋም የለም ማለት ነው። ከቤተ ክርስቲያን ቅጥር ውጭ ሰዎችን መድረስና ደቀ መዝሙር ማድረግ እንደገና ትኩረት ሊደረግበት የሚገባ የክርስትና ተግባር ነው።

ማርቲን ሉተር፣ በእምነት ስለ መጽደቅ ያገኘውን መገለጥ በተሃድሶ በኩል ወደ ቤተ ክርስቲያን ትኩረት አምጥቶ ነበር። በ1800ዎቹ እ.ኤ.አ በጆን ዌስሊይ አማካኝነት ሰፊ የወንጌል አገልግሎት የተካሄደበት ጊዜ እንደ ነበርም ይታወቃል። ነገር ግን ከሐዋርያት ዘመን በኋላ የአንድ - ለአንድ - የደቀ መዝሙርነት እና ወንጌላዊነት አገልግሎት ገና የታወቀ እንዳልሆነ ይሰተዋላል። “ለምን እንዲህ እንደሆነ አይታወቅም” ልትሉ ትችላላችሁ። ይህ ለምን እንደሆነ በእርግጠኝነት በዚህ ፕሮግራም እናሳያችኋለን - በጣም ቀላል ነው። ምስክርነታችሁን በመጠቀም ከሰዎች ጋር መስራት እና አዳዲስ ሰዎችንም ቤታቸው ድረስ ሄዳችሁ መተዋወቅ ቀላል መሆኑን እናሳያችኋለን። አሁን ትኩረት መስጠት የምፈልገው በዚህ ዙሪያ ሲሆን ይህ መልካም የምሰራች ነው።

እናንተ የምትፈልጉትን እንዴት መሰራት ትችላላችሁ፣ ሌላ ሰው እንድትሰሩ የሚፈልገውን (እናንተ ደግሞ ፈጽሞ የማትፈልጉትን) ሳይሆን ፍጹም ምርጫችሁ የሆነውን መሰራት እንዴት ትችላላችሁ? እያወራን ያለነው ፍሬ ሃሳብ ያለው እዚህ ላይ ነው። ወንጌላዊ ደቀ መዝሙርነት እንዴት እንደሚሰራ ለማሳዬት ለሰዎች በምናገርበት ጊዜ “የምንሰራውን ተመልከቱ፣ የሰዎች ህይወት እየተነካ ነው። ሰዎች እየዳኑ ነው፣ ዳግመኛ እየተወለዱ፣ በመንፈስ ቅዱስ እየተሞሉ፣ በውሃም እየተጠመቁ ነው” እላቸዋለሁ። እነርሱም “ይህ እጅግ መልካም ነገር ነው” ይሉኛል።

ነገር ግን “አሁን ስንቶቻችሁ ከእኔ ጋር መሄድ ትፈልጋላችሁ” ብዬ ብጠይቅ ምናልባት ሁለት መቶ ከሚሆኑ ሰዎች ውስጥ አንድ ሦሥት የምትሆኑት ፈቃደኛ ትሆናላችሁ፤ ምክንያቱም ቀሪዎቹ አንድም ይፈራሉ ወይም ማድረግ ያለባቸውን አያውቁምና ነው። ወይም በሌላ መንገድ “ሁሉንም እርሱት፣ በዚህ ጉዳይ አትጨነቁ፤ መፍራትም አያስፈልጋችሁም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችንን እንቀጥላለን፣ ኑ የደቀ መዝሙር ትምህርታችን እናዘጋጅ” ብዬ ብጠይቃቸው ምን ያህል ሰዎች ለመማር ይመጣሉ ካልን በእርግጠኝነት አስር፣ አስራ ሁለት የሚሆኑት “እሺ፣ እኔ መማር እፈልጋለሁ” እያሉ ይመጣሉ። ያም ቢሆን ከዚህ ያለፈ ነገር አይኖረውም።

አሁን እያደረግን ያለነው በክርስቶስ አካል ውስጥ ሁሉም ስጦታዎች እንዴት የጠፉ ነፍሳትን ለመድረስ ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ማሳዬት እና ሰዎችን ደቀ መዝሙር ስለማድረግ ደግሞም ፍቅር ስለ መስጠት ነው። ሁሉንም ስጦታዎች ይመለከታል፣ እነዚህ ስጦታዎች የሚገኙት ደግሞ በክርስቶስ አካል ውስጥ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ነው። ምናልባት አንዳንዶቻችሁ “የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት፣ ፈውስ እና የመሳሰሉትን ለመቀበል መጸለይ እፈልጋለሁ፣” ትላላችሁ። በእኛ የደቀ መዝሙር ክፍል ጊዜም ለዚህ አገልግሎት ሰዎችን የምንቀበልበት ጊዜ ነበረን። ሌሎች ሰዎች ደግሞ “እኔ እንዲህ ዓይነት ነገር አይመቸኝም” ይላሉ። ነገር ግን ከሰዎች ጋር ስጦታ መለዋወጥስ ትችላላችሁ? እንጀራ መጋገርስ? ሰልክ መደዋወልና ሰጦታ መላላክስ? የቤት ቀለም መቀባትስ? ሌላው ደግሞ ብቻዋን ልጅ የምታሳድግ፣ የምናገለግላት ሴት አለች እርሷ ወጣ ብላ እስክትመለስ ልጇን ለተወሰነ ሰዓት ልትይዙላት ትችላላችሁ? እንደዚህ ድርጊት የሚጠይቁ ነገሮችን መሰራት ትችላላችሁ? ምልጃስ? አንዳንዶቻችሁ ለምልጃ ለጸሎትም ተጠርታችኋል። እኛ የምናገለግናቸውን አንዳንድ ሰዎች ልናሳያችሁ እንችላለን፣ ስማቸውንም እንሰጣችሁና በግል ወይም በህብረት ሆናችሁ ለእነርሱ እና በየሳምንቱ ለሚሄዱት ለወንጌላዊ ደቀ መዝሙርነት ቡድኖች ልትጸልዩላቸው ልትማልዱላቸው ትችላላችሁ።

ሁሉም ሰው ሌሎችን ደቀ መዝሙር ለማድረግ መድረስ የሚችልበት መንገድ አለ። በእኛ በኩል ሁሉም ስጦታዎች ጥቅም ላይ የሚውሉበት ፕሮግራም አለን። በደቀ መዝሙርነት ችሎታቸው ወጥተው የሚያገለግሉ አስተማሪ እና ረዳት አስተማሪ የሚገኙባቸው ቡድኖችን እያዋቀርን ነው። እነርሱን ተከትለው በዕርዳታ አገልግሎት ውስጥ የሚሰሩ ሁለት ሰዎች ተግባራዊ ስራዎችን እንደ ምግብ መስጠት፣ ምግብ ማብሰል አይነት ስራዎችን ይከውናሉ ወይም ሁኔታዎች እንዴት እየሄዱ እንደሆኑ ይከታተላሉ። በተጨማሪም ስለ እኛ እና ስለምናገለግላቸው ሰዎች የሚማልዱልንም ሰዎች አሉ።

ምን ማየት እንደቻልን ታውቃላችሁ? ሰዎች በዚህ መልኩ በወንጌል ስለተገለገሉ እና እንክብካቤ ስለተደረገላቸው፣ ፍቅሩንም ማዬት በመቻላቸው እግዚአብሔር የሰዎችን ሕይወት ሲቀይር ተመልክተናል። አገልግሎቱን በማድረግ ላይ ያለው ማን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ይህን ሊያደርግ የተገባው ደግሞም በማድረግ ላይ ያለው - ሕዝቡ ነው። ኤፌሶን 4:11 ሐዋርያ፣ ነቢይ፣ ወንጌላዊ፣ መጋቢ እና አስተማሪ የተሰጡት ቅዱሳን አገልግሎታቸውን ይፈጽሙ ዘንድ ፍጹማን ለማድረግ መሆኑን ይናገራል። “መጋቢ” ተብሎ የሚጠራው፣ ከፊት ያለው ሰው ብቻ ሳይሆን ቤተ ክርስቲያንም የአገልጋይነትን ስራ እየሰራች ነው። እንግዲህ መጋቢው ቤተ ክርስቲያኑን ሲያስተምርና ለአገልግሎት ስራ ሲያስታጥቅ፣ ወጥተውም በተግባር ያንን ሲፈጽሙ ይህ እውነተኛ ስኬት ነው።

ይህን በሰዕላዊ መልኩ ላቅርብላችሁ። አገራችን በአንድ ሌላ አገር ላይ ጦርነት ብታውጅ እና መሪአችን በንግግራቸው “በጦርነቱ ላይ ብዙ ሰዎች ተሰውተውብናል ስለዚህ የጦር ሃይሉን እበትነዋለሁ፣ አልፈልገውም፣ ጄኔራሎቹ ራሳቸው እንዲዋጉ እልካቸዋለሁ” ብለው ቢናገሩ፣ ሌላው ዓለም ይሰቅብናል፣ እየሆነ ያለው ግን ይህ ነው። ጄኔራሎችን ስለምንልካቸው ዲያብሎስ በእኛ ይሰቃል። አምስቱን የአገልግሎት ቢሮዎች ሁሉንም እንዲፈጽሙልን እንልካለን። “እነርሱ ይሰሩት - ይህን እንዲሰሩ እየተከፈላቸው ነው” እንላለን። ሰራዊት መፍጠር አልቻልንም። እግዚአብሔር ደግሞ፣ ሁሉም ስጦታዎቻችን ለወንጌላዊ ደቀ መዝሙርነት ይውሉ ዘንድ ይህ ሰራዊት እንዲፈጠርለት ይፈልጋል።

ደቀ መዝሙር ለማድረግ የሚያስፈልገውን ሙሉ ሃይል የታጠቀ ሰራዊትን በመፍጠር ረገድ ማገዝ እንፈልጋለን - በዚህ በእኛ ከተማ ውስጥ ብቻ ሳይሆን - ነገር ግን በዓለም ዙሪያ ሁሉ። ይህን ተግባራዊ ለማድረግም ባዘጋጀናቸው መሳሪያዎች ይኸውም በደቀ መዝሙርነት ትምህርቶች እና እግዚአብሔር በሰጠን ልዩ ልዩ ዘዴዎች እንጠቀማለን። ስጦታዎቻችን ሁሉ በመጠቀም የጠፉትን እና አዳዲስ አማኞችን ለማገልገል እና የጌታን የኢየሱስን ሂዱና አሕዛብን ሁሉ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው የሚለውን ትዕዛዝ ለመፈጸም ሁላችሁም በአንድነት ሆናችሁ ስለምትተጉ እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

# የደቀ መዝሙር ጥያቄዎች

1. ለወንጌላዊ አገልግሎት፣ ለደቀ መዝሙርነት እና የጠፉትን ለመድረስ ቡድኖችን የምናዘጋጅበት አጭር መግለጫ ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርቧል። የቤተ ክርስቲያናችሁ ሕዋስ ከቡድኖቹ ውስጥ ለመረጠው ለአንዱ መፈረም ይችላል። ሁሉንም ስጦታዎቻችሁን ለአገልግሎት በመጠቀም ክትትሉን ከቀጠላችሁ፣ ሰዉን ወደ እግዚአብሔር መንግሰት እና ወደ ብስለት ደረጃ በፍጥነት ማምጣት ይቻላችኋል። ከዚህ በታች ለቤተ ክርስቲያናችሁ አባላት የምታቀርቡት መጠይቅ ቀርቦላችኋል። የክትትል ቡድኖችን ማዘጋጀት ያስፈልጋችኋል።

**ከሚከተሉት ውስጥ እኔ ማድረግ የምፈልገው**

(አንዱን ወይም ከዛም በላይ ምልክት አድርጉ)፦

☐ ሰዎችን በየቤታቸው በር ድረስ ሄዶ ማግኘት፣

☐ ምልጃ፦ ለጠፉት እና ለወንጌላዊ ደቀ መዝሙርነት ቡድኖች መጸለይ፣

☐ ምግብ እና ሌሎች ነገሮችን ለሚያስፈልጋቸው ቤተሰቦች መስጠት፣

☐ ሌሎች ሰዎችን በሰልክ ወይም በሌላ መንገድ ማግኘት፣

☐ የደግነት ወንጌላዊነት፣ ምግብ ማብሰል፣ ካርድ መላክ፣ በምትችሉት ሁሉ መርዳት፣

☐ ወደ ቤተ ክርስቲያን የትራንፖርት አገልግሎት መስጠት ወዘተ፣

☐ ሌላ፡ ማድረግ የምፈልገው ________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

2. ከዚህ በታች የቀረበው ሰነድ የደቀ መዝሙርነት ትምህርት ካለቀ በኋላ ለክትትል የተዘጋጀ የናሙና ሰነድ ነው። ሰነዱ መጋቢው ወይም የሚመለከታቸው የበላይ ሃላፊዎች ምን ያል ትምህርቶች እንዳስተማሩና በየትምህርቱ የተገኘውን ውጤት ያሳያል።

## የደቀ መዝሙር ክትትል ውጤት መገምገሚያ ሰነድ

የጉብኝት ቀን/ትምህርት:- ______________________________

ትምህርት የሚያስተምር ሰው ስም:- ______________________________

የተጎበኘው/የተማረው ሰው ስም (ሰሞች):- ______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

ትምህርቱ የተሰጠበት ቦታ:- ______________________________

የትምህርቱ ርዕስ:- ______________________________

ጥናቱ እንዴት ነበር? ______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

3. ያዕቆብ 1፡22ን አንብቡና የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተን ነገር ግን በተግባር የማናውለው ከሆነ፣ ምን አድርገናል?

   **ያዕቆብ 1፡22** *"ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ።"*

4. ማቴዎስ 7፡24-27 ልባም ሰው ለመሆን፣ ኢየሱስ የተናገረውን ብቻ መስማት ሳይሆን ሌላ ምን ማድረግ አለብን?

   **ማቴዎስ 7፡24-27** *"ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል። [25] ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋሰም ነፈሰ ያንም ቤት ገፋው፥ በዓለት ላይም ስለ ተመሠረተ አልወደቀም። [26] ይህንም ቃሌን ሰምቶ የማያደርገው ሰው ሁሉ ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሰነፍ ሰውን ይመስላል። [27] ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋሰም ነፈሰ ያንም ቤት መታው፥ ወደቀም፥ አወዳደቁም ታላቅ ሆነ።"*

5. ኤፌሶን 4፡11-12 አንብቡና አገልግሎቶችን መፈጸም የሚገባው ማን ነው?

   **ኤፌሶን 4፡11-12** *"እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤"*

6. የሐዋርያ ሥራ 8፡1 እና 4 ቃሉን እየሰበኩ በየቦታው ይዞሩ የነበሩት እነማን ናቸው?

   **የሐዋርያት ሥራ 8፡1** *"በዚያን ቀንም በኢየሩሳሌም ባለች ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ሆነ፤ ሁሉም ከሐዋርያትም በቀር ወደ ይሁዳና ወደ ሰማርያ አገሮች ተበተኑ።"*

   **የሐዋርያት ሥራ 8፡4** *"የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ።"*

7. የሐዋርያ ሥራ 8፡1 እና 4 ቃሉን እየሰበኩ በየቦታው ያልዞሩትስ እነማን ነበሩ?

8. የሐዋርያት ሥራ 11፡19 – 22። በአዲስ ኪዳን የቀደመችው ቤተ ክርስቲያን አማኞች የአገልግሎት ስራዎችን ይፈጽማሉ አገልግሎታቸውም የሐዋርያት ክትትልና አመራር ይደረግበት ነበር። በእኛዎቹ የዘመናችን አብያተ ክርስቲያናት ግን የአገልግሎት ስራዎችን የአብያተ ክርስቲያናቱ አመራር ይጀምራቸዋል፣ ምዕመኑም ይከተላሉ። ይህ ከሐዋርያት ሥራ 11፡19-22 አንጻር እንዴት ይብራራል?

   **የሐዋርያት ሥራ 11፡19-22** *"በእስጢፋኖስም ላይ በተደረገው መከራ የተበተኑት እስከ ፊንቄ እስከ ቆጵሮስም እስከ አንጾኪያም ድረስ ዞሩ፥ ቃሉንም ለአይሁድ ብቻ እንጂ ለአንድ ሰንኳ አይናገሩም ነበር። [20] ከእነርሱ ግን የቆጵሮስና የቀሬና ሰዎች የነበሩት አንዳንዶቹ ወደ አንጾኪያ መጥተው የጌታን የኢየሱስን ወንጌል እየሰበኩ ለግሪክ ሰዎች ተናገሩ። [21] የጌታም እጅ ከእነርሱ ጋር ነበረ፤ ቍጥራቸውም እጅግ የሚሆን ሰዎች አምነው ወደ ጌታ ዘወር አሉ። [22] ወሬውም በኢየሩሳሌም ባለችው ቤተ ክርስቲያን ስለ እነርሱ ተሰማ፥ በርናባስንም ወደ አንጾኪያ ላኩት፤"*

9. 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡14-18 ሁሉም የክርስቶስ አካል የሆኑት አስፈላጊ ናቸው። እርስ በእርስ ከእራሳችን ጋር ማወዳደር የለብንም። ይልቁንም እራስን ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ መስጠት ማለት ሁሉንም ነገር እራሳችን

መሰራት ማለት ሳይሆን እግዚአብሔር እንድትሰሩ ያስታጠቃችሁን መሰራት ማለት ነው። በዚህ ትምህርት ካገኛችሁት መረጃ በመነሳት ምን ለማድረግ አቅዳችኋል

**1ኛ ቆሮንቶስ 12፡14-18** *"አካል ብዙ ብልቶች እንጂ አንድ ብልት አይደለምና። [15] እግር። እኔ እጅ አይደለሁምና የአካል ክፍል አይደለሁም ብትል፥ ይህን በማለትዋ የአካል ክፍል መሆንዋ ይቀራልን? [16] ጆሮም። እኔ ዓይን አይደለሁምና የአካል ክፍል አይደለሁም ቢል፥ ይህን በማለቱ የአካል ክፍል መሆኑ ይቀራልን? [17] አካል ሁሉ ዓይን ቢሆን መስማት ወዴት በተገኘ? ሁሉም መስማት ቢሆን ማሽተት ወዴት በተገኘ? [18] አሁን ግን እግዚአብሔር እንደ ወደደ ብልቶችን እያንዳንዳቸው በአካል አድርጎአል።"*

# ጠቋሚ መልሶች

1. ለወንጌላዊ አገልግሎት፣ ለደቀ መዝሙርነት እና የጠፉትን ለመድረስ ቡድኖችን የምናዘጋጅበት አጭር መግለጫ ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርቧል። የቤተ ክርስቲያናችሁ ሕዋስ ከቡድኖቹ ውስጥ ለመረጠው ለአንዱ መፈረም ይችላል። ሁሉንም ስጦታዎቻችሁን ለአገልግሎት በመጠቀም ክትትሉን ከቀጠላችሁ፣ ሰዉን ወደ እግዚአብሔር መንግስት እና ወደ ብስለት ደረጃ በፍጥነት ማምጣት ይቻላችኋል። ከዚህ በታች ለቤተ ክርስቲያናችሁ አባላት የምታቀርቡት መጠይቅ ቀርቦላችኋል። የክትትል ቡድኖችን ማዘጋጀት ያስፈልጋችኋል።
**ለአቀማመጥ የቀደመውን ክፍል ተመልከት።**

2. ጠቋሚ መልሶች ጥያቄን ተመልከትከዚህ በታች የቀረበው ሰነድ የደቀ መዝሙርነት ትምህርት ካለቀ በኋላ ለክትትል የተዘጋጀ የናሙና ሰነድ ነው። ሰነዱ መጋቢው ወይም የሚመለከታቸው የበላይ ሃላፊዎች ምን ያል ትምህርቶች እንዳስተማሩና በየትምህርቱ የተገኘውን ውጤት ያሳያል።
**ለአቀማመጥ የቀደመውን ክፍል ተመልከት።**

3. ያዕቆብ 1፡22ን አንብቡና የእግዚአብሐርን ቃል ሰምተን ነገር ግን በተግባር የማናውለው ከሆነ፣ ምን እያደረግን ነው?
**እራሳችንን እያታለልን ነው።**

4. ማቴዎስ 7፡24-27 ልባም ሰው ለመሆን፣ ኢየሱስ የተናገረውን ብቻ መስማት ሳይሆን ሌላ ምን ማድረግ አለብን?
**መስማት ብቻ ሳይሆን በተግባር ማድረግ አለብን።**

5. ኤፌሶን 4፡11-12 አንብቡና አገልግሎቶችን መፈጸም የሚገባው ማን ነው?
**ቅዱሳን፣ የተወሰኑ ክፍሎች የቤተ ክርስቲያን አለቆች የሚባሉት ብቻ መሆን የለባቸውም።**

6. የሐዋርያ ሥራ 8፡1 እና 4 ቃሉን እየሰበኩ በየቦታው ይዞሩ የነበሩት እነማን ናቸው?
**በየቦታው የተበተኑት አማኞች።**

7. የሐዋርያ ሥራ 8፡1 እና 4 ቃሉን እየሰበኩ በየቦታው ያልዞሩትስ እነማን ነበሩ?
**ሐዋርያት። ከዚህ የምረዳው በቀደመችው የመጀመሪያዋ የአዲስ ቤተ ኪዳን ቤተክርስቲያን የደቀ መዝሙርነትና የወንጌላዊነት ሃላፊነት እንደነበረባት ነው።**

8. የሐዋርያት ሥራ 11፡19 – 22። በአዲስ ኪዳን የቀደመችው ቤተ ክርስቲያን አማኞች የአገልግሎት ስራዎችን ይፈጽማሉ አገልግሎታቸውም የሐዋርያት ክትትልና አመራር ይደረግበት ነበር። በእኛዎቹ የዘመናችን አብያተ ክርስቲያናት ግን የአገልግሎት ስራዎችን የአብያተ ክርስቲያናቱ አመራር ይጀምራቸዋል፣ ምዕመኑም ይከተላሉ። ይህ ከሐዋርያት ሥራ 11፡19-22 አንጻር እንዴት ይብራራል?
**ቤተ ክርስቲያን አዲስ አማኞች በጌታ የማመናቸውን ወሬ ሰማች በርናባሰንም እንዲረዳቸው ላከች (ቁጥር 22)።**

9. 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡14-18 ሁሉም የክርስቶስ አካል የሆኑት አስፈላጊ ናቸው። እርስ በእርስ ከእራሳችን ጋር ማወዳደር የለብንም። ይልቁንም እራስን ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ መስጠት ማለት ሁሉንም ነገር በእራሳችን

መሰራት ማለት ሳይሆን እግዚአብሔር እንድትሰሩ ያስታጠቃችሁን መሰራት ማለት ነው። በዚህ ትምህርት ካገኛችሁት መረጃ በመነሳት ምን ለማድረግ አቅዳችኋል

**ይህን ወደ ተግባር በመቀየር፣ ወጥቼ ያሉኝን ስጦታዎች በመጠቀም ሰዎችን ለመርዳት ተሰፋ አደርጋለሁ።**